## የኢትዮጵያ 5ሺ ዓመት ታሪክ

# ካልተዘመረለት እያሡ፣ እስከተዘመረለት ኢህአዴግ

### መጽሐፍ ፪

ፍስሐ ያዜ ካሣ
2004 ዓ.ም
አዲስ አበባ

ለክርስቲያኑ ቤተክርስቲያን ሲያሰራ ለሙስሊሞችም መስጊድ አሰራ፡፡ይህ ተግባሩ ብዙ ሹማምንትን አሳዘነ፡፡በዘመኑ ስለእሱ የሚወራው ለሙስሊሞች ያሰራው መስጊድ እንጂ ለክርስቲያኖች ያሰራው ቤተክርስቲያን አልነበረም፡፡

ሆኖም የአዲስ አበባውን ቀጨኔ መድሐኒዓለምና የሐረር መድሐኒዓለምን ቤተክርስቲያን አሰርቷል፡፡ (በአሁኑ ጊዜ የቀጨኔ መድሃኒዓለም የቤተክህነቱ የገንዘብ ቤት ሆኖ የሚያገለግለው መቃብር ቤት ከሌላ እናት የሚወለዱ እህቶቹና የሌሎች ቤተሰቦች መቃብር የነበረ ሲሆን፤የእህቱ የወ/ሮ ስሂን ሚካኤል፣የልዕልት እጅጋየሁ አስፋወሰን፣ የእመቤት ሆይ ዓለም ዐሐይ እያሡ፣የወ/ሮ አስከዳር ገ/ህይወት ሚካኤልና የሌሎች አፅም ይገኝበታል፡፡) አፄ ኃይለስላሴም በዘመናቸው ሄደውበት የሚያውቁት ብቸኛ ቤተክርስቲያን ይሄው ቀጨኔ መድሐኒዓለም ነበር፡፡

እናም በዚህ ተግባር "ሰልሟል" ብሎ ለመክሰስ የሚያስችለው መንገድ ተያዘ፡፡ይህ በእንዲህ እንዳለም ቀደም ሲል የተጠቀሰው ብዙ ሚስት የማግባቱና እቁባቶቹን የማበርከቱ ጉዳይ ሃይማኖታዊ ቅርፁን እያገኘው ሄደ፡፡ልጅ እያሡ ከሙስሊም ባላባቶች ጋር ጥብቅ ወዳጅነቱን አጠናክሮ ከመቀጠል ጎን ለጎን የአፋሩን ባላባት የደጃዝማች አቡበከርን ልጅ አፍቅሮ አገባት፡፡ወደ አፋር እየሄደም ጥሩ የፍቅር ጊዜ አሳልፏል፡፡

ቀደም ባለው ጊዜ የአፄ ዮሐንስን የልጅ ልጅ አግብቶ እንደነበርም አይተናል፡፡ እንደገና ከጎጃም ባላባት የተወለደችውን ሰብለወንጌልን አገባ፡፡ከዚያም የጅማውን የአባ ጅፋርን ልጅ አገባ፡፡እንደገና የሐረሩን አሚር የአብዱላሂን ልጅ አገባ፡፡ዙሪያውን ለማጠር የፈለገ ይመስል ሰሜን፣ደቡብ፣ምስራቅ፣ምዕራብና መሐል ላይ ጎጆ ቀለሰ፡፡ይህን መሰሉን ጋብቻ ጥቂት ፀሐፍት "ከሁሉም ጎሣ በመውሰድ አንድነትን ለማጠንከር ሲል የፈፀመው ነው" ይሉታል፡፡

ምንም ቢባል እያሡ ላይ ገኖ ተወራ እንጂ በይፋዊ ጋብቻ ባይሆንም ቀደምት ነገስታት የጭን ገረድ፣ቅምጥ፣እቁባት፣ውሽማ ... ወዘተ በሚሉ ተመሳሳይ ስሞች በገሃድ ፈፅመውታል፡፡እንደነዘርዓያዕቆብ ያሉ ገናና ነገስታት የግራ ባህልቲት፣የቀኝ ባህልቲት እያሉ በርከት ያሉ ሚስቶች ያገቡ የነበረ ሲሆን፤ነገር ግን ሙስሊሟን ሴት ክርስትና አስነስተው ነበር የሚፈፅሙት፡፡ይህም የሆነው ሳይወዱ በግድ በዚያ ዘመን የነበረውን ጦርነት ለማርገብ ሲሉ ነበር፡፡

ልጅ እያሡ ይህን ሲያደርግ ግን የነበረው ሰላም ዘላቂ ሆኖ እንዲቀጥል በማሰብ ይመስላል፡፡ይህ የልጅነት አስተሳሰቡ ከጥቅሙ ጉዳቱ እንደሚብስ ግን ማመዛዘን አልቻለም፡፡ በዚያ ዘመን ደግሞ ትኩረት በተነፈጉት መኳንንት ዘንድ መስጊድ ከማሰራትና ሙስሊም ከማግባት የከፋ መኮንኛ አልነበረም፡፡



ልጅ እያሡ የመኳንንቱን ክስ ቁብ ሳይሰጠው በምስራቃዊው የኢትዮጵያ ድንበር ላይ የሙጥኝ ብሎ ቀረ፡፡

ዘረፋ በመፈፀም ብቻ ኑሮአቸውን መስርተው የነበሩትን ሱማሌዎችን ልጅ እያሡ ልዩ ትኩረት እንክብካቤና አክብሮት በመስጠት ወዳጅ አደረጋቸው፡፡ በአካባቢው የጎሣ መሪ የነበረውን አብደላ ሰዴቅን የአጋዴን ገዥ አድርጎ ሾመው፡፡ ይህም በአካባቢው ለነበሩ ቅኝ ገዥዎች ትኩረት የሚስብ ሆነ፡፡ ይባስ ብሎ ቅኝ ገዥነታቸውን ካወጁበት ጊዜ ጀምሮ በእንግሊዞችና በጣሊያኖች ላይ ለ15 ዓመታት ያህል ብሔራዊ ጦርነት አውጆ የተካፈሏትን ሱማሌ ነፃ ለማውጣት ሲንቀሳቀስ ለነበረው የሱማሌ መሪ ለሰይድ ሙሐመድ አብደላ ሀሰን ልጅ እያሡ የገንዘብ፣የመሳሪያና የስንቅ ድጋፍ ሲያደርግለት የአውሮፓውያኑ ትልቅ የቤት ስራ እያሡን ከስልጣን ማስወገድ የሚለው ሆነ፡፡

አቤቶ እያሡ ምንም እንኳ እቅዱ ባይሰምርና ባይሳካለትም ሁሉን የኢትዮጵያን ጎሳ በማስተባበር ኤርትራን፣ጅቡቲን፣የበርበራንና የሞቃዲሾ ሶማሌን የማስመለስ ዕቅድ ነበረው፡፡ ከዚህም የተነሳ አቤቶ እያሡ 380 ሺ ጦር ለማሰናዳት ለየደጃዝማቾቹ በየግላቸው የሚያዘጋጁትን የጦር ሠራዊት ብዛት በመንገር የራሱንም ወስኖ "ፈረሴ ከቀይ ባህር ውሃ ሳይጠጣ ዘውድ አልጭንም" እያለ ይፎክር የነበረ ልዑል ነው፡፡

ከዚህ አንፃር ለአካባቢው ነዋሪዎች ድጋፍ ማድረጉ፣በጋብቻ መጣመሩም ሆነ መስጊድ ማሰራቱ፣እንደአፋሮች መፋቂያ መያዙ፣በየተጋበዘበት ቤት እንደእነሱ ለብሶ መታየቱ፣ወዘተ... በአገር ውስጥ ባለሥልጣናት ዘንድ "መናፍቅ" ቢያሰኘውም፤በእያሱ አገዛዝ ከፉኛ ቢበሳጩም፣እንዴት አድርገውና በምን አይነት ዘዴ ከስልጣን እንደሚያስወግዱት፣ጥፋቱን በማስረጃ ደግፈው ለህዝቡ እንዴት ማሳመን እንዳለባቸው የአገር ውስጥ ተቃዋሚዎቹ አልተረዱም ነበር፡፡ስለዚህ ኢትዮጵያውያኑ የልጅ እያሡን አካሄድ አለማማር መሠረት አድርገው ሲቃወሙት፣አውሮፓውያኑ ግን የልጅ እያሡ አካሄድ ሳይሆን አካሄዱ የሚያስከትለውን ውጤት አስበው ተቃወሙት፡፡እናም ኢትዮጵያውያኑ የጠፋባቸውን የማባረሪያ ዘዴ አውሮፓውያኑ በልግስና ሊሰጧቸው የስራ እቅድ ወጣ፡፡

ልጅ እያሡ ምንም የስልጣን ዘመኑ ቢያጥር ምኒልክ የጀመሩትን የአውሮፓ ስልጣኔ ወደአገር ውስጥ ለማስገባትና ኢትዮጵያም ሰልጡን አገር እንድትሆን መጣሩን ቢገፋበትም ብዙዎች ሊረዱት አለመቻላቸው ይታወቃል፡፡ ይህ ሲባል ግን የዘመኑ ጥቂት ምሁራን ከጎኑ ሆነው ድጋፋቸውን ይሰጡት እንደነበር አይዘነጋም፡፡

ልዑሉ በዳግማዊ ምኒልክ ት/ቤት ለ3 ዓመታት ያህል ስለተማረም ፈረንሣይኛ ቋንቋን በጥቂቱ ለምዶ ነበርና ከውጭ አገር ሰዎች ጋር

የራስ ተፈሪ ሚና እንደነበረው የሚያስጠረጥረው የአድማው ቃል ላይ ገና አልጋወራሽ በሆኑ በ1ኛ ዓመታቸው ከሳሾቹ የተፈሪን ስም እያሞገሱ፤አስተዳደራቸውን እያጋነኑ ከአቤቱታቸው ጋር ማቅረባቸው ነው፡፡

መጋቢት 4 ቀን 1910 ዓ.ም በመሀል ሰፋሪው አነሳሽነት ተጀምሮ ወዲያው ህዝባዊ ድጋፍ የተላበሰው የ"ሚኒስትሮች ይሻሩ" ጥያቄ ለራስ ተፈሪ እጅግ ጠቃሚ መሆኑ ግልፅ ሲሆን፤ነገር ግን ሁለት ስጋቶች ነበሩ፡፡አንደኛው ሚኒስትሮች የከፍተኛ ስልጣን ባለቤትና በሹም ሽር ጉዳይ የሚመክሩ፣ የየራሳቸው ብዙ ወታሮች የነበሯቸው ናቸውና አሜን ብለው መሻር ባይፈልጉ አመፁ ሲፈራ፤በሌላ በኩል ደግሞ ህዝቡ የመሀል ሰፋሪው አነሳስ ተገቢ ነው ብሎ በአደባባይ መሰብሰቡና በዚህ አይነት ጉዳይ ቀጥታ የህዝብ ተሳትፎ መኖሩ የራስ ተፈሪ ስጋት ነበር፡፡ በሚገርም ሁኔታ ግን አንዱ ስጋታቸው በሌላኛው ስጋት መቀረፍ መቻሉ ነው፡፡በሌላ አገላለፅ ራስ ተፈሪ ያልጠበቁት የህዝብ አመፅ ቢያስጋቸውና ባይወዱትም ሚኒስትሮችን ግን አንለቅም ብለው እንዳያውኩ አግዶላቸዋል፡፡
በየጊዜው እያደገ የሄደውን ይህን አድማ አስመልክቶ የህዝቡን የክስ ቃል፤የመሀል ሰፋሪውን የተቃውሞ ድምፅና ከአልጋ ወራሹ የተሰጠውን ምላሽ ለአንባብያን ማድረሱ ጠቃሚ ነውና በደጃዝማች ከበደ ተሰማ ተፅፎ በ1963 ዓ.ም "የታሪክ ማስታወሻ" በሚል ርዕስ የታተመውን መፅሐፍ ጠቅሼ በሚከተለው መልኩ አካትቸዋለሁ፡፡

በጉዳዩ ላይ ህዝቡ ተሰብስቦ በሚዶልትበት ጊዜ የተሰበሰበውን ህዝብ የሚያስፈርድ አጋፋሪ ተሹሞ ስለበር እያስነሳ ይጠይቃል፡፡ በዚህ ጊዜ አንዱ፤

"ጌታችን እግዚአነ ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን ዓለም ፈጥሮ 12 ሐዋርያትን አገር ከፍሎ እንዲያስተምሩ ያሰማራቸውን ለመምሰል ላገሩና ለመንግስቱ ልማት በውነት እንዲመክሩና እንዲሰሩ 12ቱን ሚኒስትሮች ደጉ ጌታችን አፄ ምኒልክ መርጠው ቢሾሟቸው፤ ለአገር ልማት ለህዝብ አንድነት በመምከር ፈንታ አንዱ ላንዱ ለየራሳቸው ጥቅም በመመልከት አገሩን አበላሹት፡፡ እንጂ ለመንግስት የጠቀሙትና የሰሩት ጉዳይ የለም፡፡ 12ቱን ሐዋርያት በማየት የተሾሙት ሚኒስትሮች 12 አጋንንት ስለሆኑ እንዲሻሩ ያስፈልጋል፡፡

ለምሳሌ የስራ ሚኒስቴር ተብሎ የተሾመው የራሱን ቤት ለመስራት በቤት ላይ ቤት እየቀጠለ ወደሰማይ ለመውጣት ይገሰግሳል፡፡ እንደዚሁም የግቢ ሚኒስቴር የተባለው የራሱን ሐብት ብቻ በማደራጀቱ ከምኒልክ ቤት ለግብር የሚሆን መሰናዶ ታጥቶ ባለፈው ሰሞን ከእርሱ ቤት ዱቄት ተግዞ ተሰናዳ፡፡ ይህ ምን ያሳያል? ሁሉም የየራሱን ጥቅም ለማደራጀት መዘጋጀቱን ነው፡፡"



በዚህ አይነት የአድማው ክስ እየተጧጧፈ ስለቀጠለ በቤተ-መንግስት ተመክረና ሊቀጳጳሱና እጨጌው ከሊጋባው (የመሃል ሰፋሪው አዛዥ) ጋር በመሆን በህዝቡና በመንግስቱ መካከል መላላክ ጀመሩ፡፡ ወዲያውም ጳጳሱ አቡነ ማቴዎስ፣ እጨጌ ወልደጊዮርጊስ፣ ሊጋባ መኮንን ተወንድ በላይ በአንድነት ሆነው አድማው ላይ ለተሰበሰበው ህዝብ ከቤተ-መንግስት የተላከውን ተከታዩን ፅሁፍ አነበቡላቸው፡፡

"ከቤተ-መንግስት የተላከው ቃል፡፡

የኢትዮጵያ መንግስት አልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪ፡፡

"በአንድነት ሆናችሁ በአባታችን እጅ የላካችሁት ቃል ደርሶናል፡፡ የንጉስ ወልደጊዮርጊስን መሞት የሰማነው ከትናንት ወዲያ ነው፤ (ዘውዲቱ በነገሱ በሳምንቱ የበጌምድርና የስሜን ንጉስ አድርገው የሾሟቸው በወቅቱ ሞተው ስለነበር) ይህም ለእናንተ የሚያሳዝናችሁ አይደለምን? ሁለተኛስ እቴጌ ጣይቱን ያህል እናታችሁን ተዝካራቸው በሚወጣበት ቀን በእንደዚህ ያለ ምክንያት ተጓድሎ ቢውልና ድግሱ ቢበላሽ ሐዘኑና ጉዳቱ መልሶ ለእናንተ አይደለምን? የላካችሁልኝን ቃል ለንግስት አሳውቃለሁ፡፡ ከጥንትም ቢሆን የሚኒስትሮችን ሹመት ደጉ ንጉሠ ነገስት አፄ ምኒልክ ለህዝባቸው ጥቅምና እድገት የሚሆነውን ለማስጠበቅና ለማሰራት ሲሉ አቅደውት ነበር እንጂ ህዝብን ለመጉዳት በማሰብ እንዳልነበር ታውቁታላችሁና፤ አሁን አሳቡን ከራሳችሁ አውርዳችሁ እኛ እንድናስብበት ካደረጋችሁ ለመላው ህዝብ ደስ የሚለውንና ለመንግስቱ ብልፅግናና ጥቅም የሚሆነውን ለሰኞ ጠዋት እስከናስታውቃችሁ ድረስ በንግግርም ሆነ ወይም በሌላ ረገድም ቢሆን ሽብር እንዳይነሳ አደራ ተጥሎባችኋል፡፡

ከሁላችሁም ወገን ሁከትና ሽብር እንዲነሳ ያደረገ ሰው ቢገኝ በመጀመሪያ ጠላትነቱ የኢትዮጵያ ስለሆነ፤ እኛም በበኩላችን ከእነሱ ወገን ሁከት እንዳይነሳ እናደርጋለን፡፡" የሚል ቃል ለተሰበሰበው ህዝብ ከተነበበለት በኋላ አድመኞቹም በበኩላቸው ተከታዩን ቃል በፅሁፍ ለመንግስቱ ላኩ፤

"የኢትዮጵያ መንግስት አልጋ ወራሽ ልዑል ራስ ተፈራ ሆይ፤

"እኛ ባሮችዎ የኢትዮጵያ ህዝብ በንግስታችን በንግስተ ነገስታት ዘውዲቱና በርስዎ በልዑል አልጋ ወራሻችን በኩል ተበድለናል፣ ተጎድተናል የምንለው ነገር የለም፡፡ ነገር ግን ታላቁ ንጉስ ዳግማዊ ምኒልክ ህዝቤን ይጠብቁልኛል፣ የጀመርሁትንም የስራ ውጥን ይፈፅሙልኛል ብለውና አስበው የሾሟቸው ሚኒስትሮች እንደገና ተሿሚዎቹ ብሰው ህዝብን መበተን፤አገራችንን ማጥፋት፣ አገሪቱን ከነገንዘቧ ለየራሳቸው መከፋፈልና፤እውቀትን ማጥፋት፣ ትምህርትንም

የአልጋወራሹ አካሄድም ሆነ ስራና ተግባር በሁሉም ዘርፍ ዘውዲቱን የበታች አልጋወራሹ የበላይ የሆኑበት አይነት ነበር። በዚህ ጊዜ ደጃዝማች በየነ (ሊጋባው) "ራስ ተፈሪ አልጋወራሽ ብቻ ናቸው እንጂ እንደራሴ አይደሉም። አልጋወራሹም ፊንታውን ይጠብቃል እንጂ በመንግስቱ ስልጣን ውስጥ ገብቶ የአስተዳደር ስራ መስራት አይችልምና፤በአስተዳደሩ ስራ የገቡት ያለሕግ ስለሆነ በአልጋወራሽነታቸው መብት ብቻ እንዲቆዩ ሆኖ ከሌላው ስራ እንዲታገዱ" የሚል ጥያቄ በማንሳት በአልጋወራሽ ላይ ማደምና ማሳደም ጀመሩ። ይህም ጥቂት እውነት አለውና ብዙዎች በዚህ አድማ ሊስማሙ አቆበቆቡ።

ይህ ወሬ ለአልጋወራሹ በየምድቡ ባስቀመጧቸው ሰላዮቻቸው አማካኝነት እንደደረሳቸው፣ ሊጋባው እንዲያዙ አደረጉና ፊታውራሪ ሐብተጊዮርጊስ በተገኙበት የአልጋወራሽ ችሎት ላይ እንዲቀርቡ ሆነ። ሊጋባ በየነ ልጅ እያሡ ተሽሮ ዘውዲቱ ሲተኩና ራስ ተፈሪ አልጋወራሽ ሲባሉ በቦታው የነበሩ ናቸው። ነገር ግን ችሎቱ ላይ "በዚያ ወቅት ራስ ተፈሪ አልጋወራሽና ባለሙሉ ስልጣን እንደራሴ መባላቸውን አልሰሙም ወይ? ይህንንስ በጊዜው የነበሩት መካሮች ሁሉ እርስዎን ጨምሮ የሰሙትና የሚያውቁት አይደለም ወይ?" በሚል ፀጥታ በማደፍረስ ተብለው ቅጣት ተወሰነባቸው። ቅጣቱም በአደባባይ እንዲገረፉና ወደሐረርጌ ሄደው እንዲታሰሩ የሚል ሲሆን፤ ያለምህረት በአደባባይ ተገርፈው ታሰሩ። አልጋወራሹ በዚህ ጉዳይ ላይ ምህረት ማድረጉ ምን እንደሚያስከትል ያውቃሉ። ይህ የ1917ቱ አድማ እጅግ ተገቢ ከመሆኑም በላይ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በአልጋወራሹ ላይ የተነሱት ተከታታይ አመጾች ሁሉ ምንጭ ተደርጎ የሚወሰድ ነው።

ራስ ተፈሪ ከነገሡ በኋላ በየፉት መፅሐፍ ላይም ሆነ በደጋፊዎቻቸው የተፃፉት መፃህፍት ላይ "አልጋወራሽ ተባልኩ፣ ቀጥዬ፣ እንደራሴ ሆንኩ፣ ከዚያ ንጉስ ተብዬ በመጨረሻ ንጉሠነገስት" እየተባለ ይፃፍ እንጂ እውነታው አይደለም።

በመጀመሪያ ደረጃ ንጉሠነገስት ወይም ንግስተ ነገስት ተብሎ ዘውድ ሲጫን እዚያው በዚያው አልጋወራሽ አይሰየምም።ቢሰየምም ቀደም ሲል እንዳየነው በተሿሚው ንጉሠነገስት ወይም ንግስተ ነገስት ተመርጦ መሰየም ይገባዋል።ያ ሳይሆን ቀርቶ ሁለቱ እኩል ተሾሙ።ይህ ያልተለመደ አካሄድ ይሁን ተብሎ ታልፎ ተግባራዊ ሆነና ዓመታት ካለፉ በኋላ "በወቅቱ አልጋወራሽና ባለሙሉ ስልጣን እንደራሴ ተባልኩ" ቢባል ሌላ ስህተት ይሆናል።ስህተቱም "ባለሙሉ ስልጣን እንደራሴ" የሚባለው ስልጣን ተተኪ ነገስታት እድሜያቸው ሳይደርስ ሲቀር እስኪያድጉ እንደራሴ ተሾሞላቸው በእንደራሴው አማካኝነት የመንግስት ስራ



ይከናወናል።በዘውዲቱ ዘመን የተፈጠረው አወዛጋቢ ነገር ግን አልጋወራሹ እንደራሴ መባሉ ነው።ዘውዲቱ ራስ ተፈሪን በ20 ዓመት እድሜ ይበልጧቸዋል። ሞግዚት አያስፈልጋቸውም።ዘውዲቱም ተፈሪም ለዙፋኑ ቅርብ ናቸው። በእድሜ ደረጃ ሁለቱም ያለእንደራሴ ለማስተዳደር የደረሱ ናቸው።ዘውዲቱ የማስተዳደር ብቃት ከሌላቸው ደግሞ አልጋወራሽ ለመሆን ብቁ ሆኖ የተገኘውና ለዘውዱ የሚቀርበው ወንድ ልጅ ብቻውን ንጉሠነገስት መሆን ይችል ነበር፣የግድ ቀጥተኛ ልጅ ይሁን አይባልም።ወንድ ሆኖ ለዙፋን ከቀረበ በቂ ነው።የምኒልክ ቀጥተኛ ልጅ ዘውዲቱ እያለች ነበር የልጅ ልጁ እያሡ ያውም በልጅነቱ ለሥልጣን የበቃው።ሌላው አማራጭ ሴት የነገስታት ዘሮች ልምድ ካላቸው የእቴጌነቱን ስልጣን ይዞ መቀጠል ነበር።ወይም የንግስቲቱ ባል በባለቤትነቱ አስተዳደራዊ ስራዎችን ሊከውን ይችላል።

ከተጠቀሱት ውስጥ አንዳቸውም ተግባራዊ ባለመሆናቸው ምክንያት ተጀምሮ እስኪጨረስ የዘውዲቱ ንግስና በዘመኑ መሣፍንት "ግንብ ጠባቂ" ይባሉ የነበሩትን ነገስታት ያስታውሰናል። ሁኔታው ሌላ የሚያስታውሰን ነገር በወቅቱ ልጅ እያሱን የሚደግፍ በርካታ ህዝብ እንደነበረና ይህንንም በመፍራት የተከናወነ መሆኑን ነው።

ይህ ውሉ ያልለየና ገደብ ያልተበጀለት ስልጣንን ጠቅልሎ የመያዝ ጉዳይ የዘውዲቱን ተቆርቋሪዎች ክፉኛ እያበሳጨና እያወዛገበ ሲቀጥል፤ አልጋወራሹም የዘውዲቱን ተቆርቋሪዎች የእኔ ጠላት እያሉ ጣት የመቀሰራቸውን ጉዳይ ገፉበት። በዚህም ክፍፍል ተፈጥሮ አንዱ ለአንዱ ጠላት የሆነበት እንዲሁም ተከታታይ አመጾች የተከታተሉበት ዘመን ሆነ። ይህን ጉዳይ በሚመለከት አርቀው ያሰቡ ጥቂት ሹማምንት "ሁለቱን በአንድ መሾሙ ወደፊት ችግር ሊፈጥር ይችላልና ይታሰብበት" ብለው የነበረ ቢሆንም ሰሚ አላገኙም። ሌላው ቀርቶ ፊታውራሪ ሐብተጊዮርጊስ የተፈሪ አካሄድ ወደመጨረሻው አላምር እያላቸው ሲሄድ "ምን አስቸኮለዎ? መንገዱን እየጠረግንና እያስተካከልን አይደለም ወይ? እኔስ አርጅቻለሁ ኢትዮጵያን አላያትም! እባክዎ እንዳያፈራርሷት አደራ!" ብለው በአክብሮት ነግረዋቸዋል።

ፊታውራሪ ሐብተጊዮርጊስ በምኒልክ ጊዜ የተከበሩ ባለሥልጣን የነበሩና በልጅ እያሡ ጊዜ አክብሮት ከተነፈጋቸው ባለሥልጣናት ውስጥ አንዱ ናቸው። እያሡን ለመሻርም ትልቁን ሚና ተጫውተዋል። በዘውዲቱ መሾምም የሚስማሙና የወግ አጥባቂው ወገን መሪ ናቸው። ድጋፋቸው ለዘውዲቱ ይሁን እንጂ የራስ ተፈሪ ስልጣኑን የመጠቅለል ጉዳይ ስኬታማ እየሆነ መሄዱን ሲያዩና የዘውዲቱ ወገን እየተጠለፈ መውደቁን ሲያጤኑ ወደ ተፈሪ ማዘንበል ጀምረው ነበር። ምንም ቢባል ግን በዋናነት የዘውዲቱ ደጋፊ መሆናቸው ግልፅ ነው። ከሽረት የተረፉ

ሚኒስትር መሆናቸውም ምንጩ በአንድ በኩል የአድማው ተካፋይ ስለነበሩና፤ በሌላ በኩልም ከፍተኛ የፖለቲካ ተደማጭነት ስለነበራቸው ሲሆን፤ ራስ ተፈሪ እኒህን ሰው በማለዳ መሻር ትልቅ ጉዳት እንደሚያስከትል በማሰብ ባይወዷቸውም እንኳ ተከታዩን በመስጋት እንዳስተረፏቸው ይገመታል፡፡ፊታውራሪ ሐብተጊዮርጊስ በ1919 ዓ.ም በሞት ሲለዩ ለአልጋወራሹ እፎይታ ነበር፡፡ ከዚህ በኋላ ለዘውዲቱ የሚቆረቆር ጠንካራ ክንድ አይኖርምና፡፡

በዚህ ጊዜ አልጋወራሹ የፊታውራሪ ሐብተጊዮርጊስን 15 ሺ ጦር ወረሱና የራሳቸው አደረጉት፡፡አልጋወራሹ በየጊዜው የሚነሳባቸውን አድማ በዘዴ እያከሸፉ፤ አድመኞቹን እያንበረከኩ ቀጥለዋል፡፡አሁን ሦስት ታላላቅ የዘውዲቱ ተቆርቋሪዎች የሆኑ ባለሥልጣናት ቀሯቸው፡፡ደጃዝማች ባልቻ፣አባ ውቃውና የዘውዲቱ ባለቤት ራስ ጉግሳ፡፡

ደጃዝማች ባልቻ አባነፍሶ የአፄ ምኒልክ ታማኝ፣የጦር ሜዳ ጀግና፤ በአድዋው ጦርነት በፈፀሙት ጀብድ የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆች ከተሰኙት የዘመኑ ጀግኖች ውስጥ አንዱ ናቸው፡፡የእያሡ መሻር ካልተዋጠላቸው ውስጥም አንዱ ነበሩ፡፡ከራስ ተፈሪ ተቃዋሚዎች ውስጥም ከማለዳ ሆነ፤ በአልጋወራሹ ከተበደሉት ውስጥም አንዱ ናቸው፡፡ገና በማለዳ በአልጋወራሹ ላይ የክስ አድማ ካደረጉት ውስጥም እንደዚሁ አንዱ ነበሩ፡፡

አልጋወራሹ የዘውዲቱን ስልጣን እየገዘገዙ መሄድ ያስቆጣቸው ባልቻ የተገዘገዘው ስልጣን ተገንድሶ ከመውደቁ በፊትም ሆነ በኋላ ለዘውዲቱ እንጂ እንደሌላው ባለሥልጣን አንድም ቀን ለተፈሪ ታዛዥ ሆነው አያውቁም፡፡ የኃይል ሚዛኑ ወደ አልጋወራሹ ማዘንበሉን እያዩ እንኳ የተለሳለሱበት ጊዜ የለም፡፡

በወቅቱ የሲዳሞ ገዥ ነበሩና፤ አልጋወራሹ ወደአዲስ አበባ እንዲመጡ (መጥተውም ታማኝነታቸውን እንዲገልፁ) መልዕክት ላኩባቸው፡፡ደጃች ባልቻ ግን የራስ ተፈሪን ጥሪ በእንቢታ መለሱት፡፡አልጋወራሹ ንዴታቸውን በውስጣቸው ይዘው ንግስት ዘውዲቱን "እንዲመጡ የሚያሳስብ መልዕክት ላኩላቸው" አሏቸው፡፡ ንግስት ዘውዲቱ የተባሉትን ፈፀሙ፡፡

የዘውዲቱን መልዕክት ሲሰሙ ባልቻ በ1920 ዓ.ም በየካቲት ወር ጦራቸውን አስከትለው ከሲዳሞ ወደ አዲስ አበባ መጡና ሠራዊታቸውን በከተማው በስተደቡብ በሚገኘው በፉሪ ተራራ ላይ አስፍረው፤ ጥቂት አጃቢዎቻቸውን ብቻ አስከትለው ወደቤተ-መንግስት በማምራት በጥቂት ሠራዊታቸው ሰልፍ አሳይተው ንግስትና አልጋወራሹ ወደተቀመጡበት ሠገነት ሄደው እጅ ከነሱ በኋላ የዘውዲቱን ጫማ ሲስሙ፤አልጋወራሹ በተራቸው ለሰላምታ ሲነሱ ባልቻ ግን "ጉንፋን ይዞኛል" አሉና ሰላም



ሳይሏቸው ተቀመጡ፡፡በዚህም በተፈሪ ላይ ያላቸውን ጥላቻ ባደባባይ ገለፁ፡፡

በግብር ሰዓትም ቦታቸው ከአልጋወራሹ ጋር ስለነበር "እሞኛል" ብለው እልፍኝ ሳይገቡ ወደማረፊያቸው ባቀኑ ጊዜ ብልጡ ተፈሪ ወዲያው ታማኞቻቸውን ደጃዝማች ብሩ ወልደገብርኤልን የሲዳሞ ገዥ አድርገው ሾመው፤ሹመቱንም ፉሪ በሰፈረው የባልቻ ጦር ላይ አዋጅ አስነግረው ጉድ አደረጓቸው፡፡የባልቻ ጦር "ቁጥር ጦር" የሚባለው የንጉሠነገስቱ ጦር በመሆኑ አዋጁን እንደሰማ አዲሱን ገዥ ተከትሎ ወደ ሲዳሞ ሄደ፡፡በዚህ ጦር ላይ ማዘዝ የሚችሉት ንግስተነገስቷ የነበሩ ቢሆንም የሆነው ግን ያ አልነበረም፡፡ ስለዚህ ባልቻ አባነፍሶ ነፍሳቸውን ብቻ ይዘው ቀሩ፡፡

የደጃዝማች ብሩ ሹመትም ብዙ አልቆየም፡፡እሳቸው ተሽረው የአልጋወራሹ ልጅ የልዕልት ተናኘወርቅ ባል ለሆኑት ለራስ ደስታ ዳምጠው ተሰጠች በቡና ሐብቷ የምትታወቀው ሲዳሞ፡፡

ደጃዝማች ባልቻ ጥቂት አጃቢዎቻቸውን ይዘው መጋፈጣቸውን ቢቀጥሉም ያመጡት ለውጥ የለም፡፡ በመጨረሻም በግዞት እንዲቀመጡ ተፈረደባቸው፡፡ በግዞት እንዳሉ ኢጣሊያ ኢትዮጲያን ዳግም ስትወርር እንኳ በተፈሪ ላይ እንጂ በኢትዮጵያ ላይ ቂም ስለሌለባቸው በሽምግልና ዘመን በአርበኝነት ጠላትን ሲያጠቁ ቆይተው ከብዙ ፍልሚያ በኋላ በወራሪው ኃይል ተገድለዋል፡፡

ሌላው በአልጋወራሹ ላይ ጠንከር ያለ ተቃውሞ ያነሱና የንግስት ዘውዲቱ ስልጣን አልባነት በእጅጉ ያስቆጣቸው ደጃዝማች አባውቃው ብሩ ያነሱት አመፅ ነው፡፡ አባ ውቃው በአፄ ምኒልክ ቤተ-መንግስት በእልፍኝ አሽከርነት ያደጉ ናቸው፡፡ አስፈሪውን ስም ያገኙት በልጅነታቸው በእድሜ የሚበልጧቸውን በትግል እያሸነፉ ስላደጉና በጉልበት የሚወዳደራቸው ስላልነበረ ነው፡፡ ብዙዎችን ስለወቁም ውቃው የሚለው ስማቸው ፀንቶ "የሻለቃ አባውቃው" ተብለው የደረጃ እድገት አገኙ፡፡ ቀጥሎ የቤተ-መንግስቱ የወታደር አለቃ ሆነው፣በዘውዲቱ ጊዜ በሊቀመኳስነት የቡኖ ደጃዝማች ተብለው የወላሞ አውራጃ ገዥ ሆኑ፡፡ከዚያም የእልፍኝ ዘበኞች አለቃ ሆነው ተሾሙ፡፡

ደጃዝማች አባውቃው ለአመፅ የተነሱበት ምክንያት ዘርፈ ብዙ ይሁን እንጂ ዞሮ ዞሮ ግን የዘውዲቱ በተፈሪ የመገፍተር ጉዳይ ነው፡፡ተጀምሮ እስኪጨረስም አባውቃው ሙሉ በሙሉ የዘውዲቱ ደጋፊ የነበሩ ናቸው፡፡አልጋወራሹ ከኢትዮጵያ ጠላት ከኢጣሊያ ጋር የተፈራረሙት የወዳጅነት ውል አባውቃውን አስቆጥቷል፡፡ በተለይ ፊታውራሪ ሐብተጊዮርጊስ ከሞቱ በኋላ የአልጋወራሹ የዙፋን መንገድ ጠረጋ በጣም እየፈጠነ በመሄዱ ዘውዲቱ ማንም እንደሌላቸው በመረዳታቸውና፣ ከንግስቲቱ በኩልም "ተፈሪ ሐብተጊዮርጊስ ከሞተ ብሎ

ዘውዱን ሲነጥቀኝ ነው" የሚል ወሬ ተሰማ በመባሉ የአባውቃው ቁጣ እየተባባሰ ሄዷል፡፡ከሁሉም በላይ ግን በ1920 መግባደጃ ላይ ከመሀል ሰፋሪ ቡድኑ የተውጣጡ የአልጋወራሹ ደጋፊ የሆኑ ግለሰቦች በሌሎች ግፊት ተነሳሱና "ተፈሪን ያንግሱልን" የሚል ጥያቄ ማስተጋባት ጀመሩ፡፡ይህን የሰሙት አባውቃው ልባቸው ተነክቶ ያለማንም አነሳሽነት በራሳቸው ጊዜ በአልጋወራሹ ላይ ይነሳሉ፡፡ከዚህ ወሬ ጎን ለጎን ደግሞ የአባውቃው "እኛ በህይወት እያለን ይህን የመሰለ ተግባር አይፈፀምም!" የሚለው ዛቻ አብሮ መስተጋባቱ ቀጠለ፡፡

ይህ ሁሉ ሲሆን ንግስተ ነገስታት ዘውዲቱ አንድም ጊዜ የሌሎችን እርዳታም ሆነ የደጋፊዎቻቸውን ድጋፍ ፈልገውም ጠይቀውም አያውቁም፡፡ ጥያቄውን ዘውዲቱ ለጊዜው የሰሙት ልክ እንደ አባውቃው በወሬ ደረጃ ነበር፡፡ የዚህን ወሬ በሚመለከት ዘውዲቱ ለተፈሪ ሲጠይቋቸውም ተፈሪ የሚያውቁት ነገር እንደሌለ በመግለጽ በጉዳዩ ላይ ለመነጋገር ቀጠሮ ይይዛሉ፡፡በቀጠሮው እለት አልጋወራሹ ከንግስት ዘውዲቱ ጋር ለመነጋገር በማለዳ ሲመጡ፤ደጃዝማች አባውቃው ከቀጠሮው በፊት ወደ ንግስት ይሄዱና "ዛሬ እኔ ልታሰርና የታሰበው ሊፈፀም በእኔም ስራ ላይ አጋፋሪ ወልደማርያም ሊሾም ተመክሮ መወሰኑን ሰምቻለሁ፡፡ እኔ ከመያዜ በፊት አልጋወራሽ ከቤታቸው ሲመጡ ከዋናው በር ላይ እከላከላለሁና ይፈቀድልኝ" ብለው ጠየቁ፡፡ ዘውዲቱ በበኩላቸው "አልጋወራሽ የሚመጣው ይህንኑ ያድማውን አነሳስ አጣርቶ ለመነጋገር በቀጠሮ ነውና መከልከል አይሆንም፡፡አንተም አሁን የነገርከኝን ሲመጣ ብጠይቀው ይነግረኛልና ነገሩን አጣርቸ እስካስታውቅህ ድረስ አርፈህ ተቀመጥ" ብለው ገሰፁ፡፡ ጳጉሜ 1 ቀን 1920 ዓ.ም በቀጠሮው መሰረት ማለዳ 3 ሰዓት ላይ አልጋወራሽ ከመኖሪያቸው ከገነተ ልዑል ወደ ቤተ-መንግስት ገብተው ከንግስት ዘውዲቱ ጋር ያስማጽረጥ ለ8 ሰዓታት የቆየ ረጅም ውይይት አደረጉ፡፡

የምክክሩ ውጤት ምን ይሆን በሚል በአደባባይ የተሰበሰበው ህዝብ ይጠባበቃል፡፡ በመጨረሻ ጉባኤው 11 ሰዓት ላይ ተጠናቆ አባውቃውና አድማውን አስወርተዋል የተባሉት ደጃዝማች ወዳጀ እንዲታሰሩ ተወሰነ፡፡ ደጃዝማች ወዳጀ በአፈንጉስ አረጋይ እጅ እንዲታሰሩ ሆኖ ተይዘው ሲሄዱ፤ ደጃዝማች አባውቃውን ሊይዙ የሄዱት አጋፋሪ ወልደማርያም ግን ሳይሳካላቸው ቀረ፡፡

አባውቃው የምኒልክ እፅም ካረፈበት ግቢ ውስጥ በሚገኘው መታሰቢያ ቤት ከወታደሮቻቸው ጋር መሽገው መድፋቸውን ጠምደው አላስቀርብ አሉ፡፡ የተለያዩ መልዕክተኞች እየተላኩ በግድም በውድም፣ በሽምግልና መልክም አባውቃውን እጃቸውን እንዲሰጡ ቢጠይቁም፤



አልጋወራሹን ሲወቁ የተዘጋጁት አባውቃው ምላሻቸው "ደርበህ በለው!" የሚል ሆነ፡፡

አልጋወራሹ በየበሩ ታማኞቻቸውን እያቆሙ ራሳቸው ደግሞ በኢትዮጵያ ታሪክ የመጀመሪያ የሆነውን ታንክ ወደመታሰቢያ ቤቱ ጠምደው፤ከንግስት ዘውዲቱ ጋር በመልዕክተኛ የመፍትሄ ኀሳብ መለዋወጥ ጀመሩ፡፡ነገር ግን አባውቃውን ለመማረክ የተደረጉ ሙከራዎች ሁሉ ያሰቡትን አይነት ውጤት ሊያስገኙላቸው አልቻለም፡፡አባውቃው ባሉበት የፉከራና የሽለላ ድምፅ እየተሰማ ሌሊቱ ተገባደደ፡፡ በሽብር ስጋት ተወጥራ የዋለችው አዲስ አበባ በዚያው ሁኔታ ወደማደር ስትቃረብ ከምሽቱ ዘጠኝ ሰዓት አልጋወራሹ ባሳሰቡት መሠረት ንግስት ዘውዲቱ ቃላቸውን ስለሚሰማ እንዲልኩበት አዘዙ፡፡

ግርማዊት ንግስትም "አሁን በአጠገቤ የሚገኙት ሊቀመኳስ መኮንን ዋልቴና ቀኛዝማች ኃይለሰላሴ ብቻ ናቸውና ማንኛቸው ቢላኩ ይሻላል!" የሚል ጥያቄ ወደ አልጋወራሹ ላኩ፡፡

"ሊቀመኳስ መኮንን ይሂድ" ብለው መለሱ አልጋወራሹ፡፡ ሊቀመኳስ መኮንን ግን "ብቻዬን አልሄድምና ከአልጋወራሹ ዘንድ ከሚገኙ መኳንንቶች አንድ ሰው ይጨመርልኝ" ስላሉ ይሄም ቃል ተላከ፡፡ የአልጋወራሹ መልስ "ፊታውራሪ ታፈሰ ሐብተሚካኤል አብሮ ይሂድ" የሚል ሆነ፡፡ "የታፈሰ መሄድ ጠቃሚ አይሆንምና ሌላ ሰው ይመረጥ" መለሱ ንግስት፡፡ ለነገሩ የታጨት ሁሉ የወቅቱን ሁኔታ እያገናዘቡ ሰበብ እየፈጠሩ ፈቃደኛ አልሆን አሉ፡፡ በመሃል ደጃዝማች አምደሚካኤል "ልጅ ተሰማ ከበደ ቢላክ ይሻላል" ስላሉና ልጅ ተሰማም ፈቃደኛ ስለሆኑ ለንግስት ሲነገራቸው፣ "ተሰማን ልጅ ነው በማለት እንዳይመለከተው መምህር ደስታና አለቃ ደስታ አብረው ቢሄዱ የተሻለ ነው" የሚል ቃል ለአልጋወራሹ ላኩና በዚህ ተስማሙ፡፡ እነዚህን የመሰሉ አለመተማመንን የሚያንፀባርቁ የቃላት ምልልሶችን ስናይ፤ በተለይ የዚያ ዘመን ፀሐፍት በዚያ ወቅትና ከዚያም በኋላ በነበሩ ክንውኖች ላይ "አልጋወራሹና ንግስት ፍፁም ቤተሰባዊ በሆነ የእህትና የወንድም አይነት ምክክር እያደረጉ ሁሉንም ነገር በሰላምና በስምምነት ይፈፅሙት ነበር ..." የሚል ገለፃቸውን ጥያቄ ውስጥ የሚከትና እውነቱ ተቃራኒው እንደነበር ይጠቁመናል፡፡

የተባሉት ሰዎች አባውቃው ወደመሸጉበት ቦታ ሲያመሩ "በጌታችን በምኒልክ ልጅ የደረሰ ክፉ ነገር አለወይ?" የሚል ጥያቄ ነበር የቀረበላቸው፡፡ መልዕክተኞቹ ምንም ክፉ ነገር እንዳልደረሰና የመጡትም የንግስትን የሰላም ይውረድ ቃል ይዘው መሆኑን ገለፁ፡፡ አባውቃው የተነገራቸውን ቃል ከሰሙ በኋላ "ከንግስት ከራሳቸው ቃል ካልሰማሁ በቀር ይሄን መልዕክት መስማትም ማመንም አልችልም" አሉ፡፡

ከመልዕክተኞቹ አንዱ "የኛን ቃል ካልሰሙ በማሕተማቸው የተረጋገጠ ጽሁፍ እናምጣልዎ" የሚል ምርጫ አቀረቡ፡፡በዚህ ጊዜ አባውቃው ጽሁፍ "ማሕተሙን የሚይዘው ፀሐፌ ትዕዛዝ ወልደመስቀል ስለሆነ ጽሁፉ ቢመጣም አልስማማም፡፡ንግስት ግን ሁልጊዜ የሚመጡበት ቤተ-ክርስቲያን ስለሆነ፣ወደዚህ መጥተው ከንደበታቸው ካልሰማሁ በመልዕክት የምፈፅመው ነገር አይኖርም፡፡እስካሁንም የቆየሁት በመጨለሙ ሀፃን፣ ሴት መለየት ስላልተቻለ ነው፡፡እላይ ባመለከትኩት አይነት የንግስትን ደህንነት ከቃላቸው ካልሰማሁ ወገግ ብሎ ብርሃን ሲታይ መታኮሴ የማይቀር ነው" የሚል መልስ ሰጥተው መለሷቸው፡፡መልዕክተኞቹ ይህን ቃል ለንግስት ተናገሩ፡፡

ምስኪኗ ዘውዲቱ በእኔ ምክንያት ደም መፋሰስ ከሚደርስ ሁሉም ነገር ቢቀርብኝ ይሻላል በማለት ይመስላል ክብራቸው ባይፈቅድም ለባብሰው በሌሊት ለመሄድ ተነሱ፡፡"መሄዴ ነው ብላችሁ ለአልጋወራሹ ንገሩ" ብለው ሲነሱ፣ በቅርባቸው የነበሩ መኳንንቶችም "ከንግስት ቃል ካልሰማሁ ካለ በዚህ ምክንያት ተኩስ ተነስቶ ደም ከሚፈስ መሄድዎና ነገሩን ማብረድዎ መልካም ነው" ሲሉ ተስማሙ፡፡

በዚህ ጊዜ እርቆ አሳቢው፣ ጠርጣራውና የዋህነት በአጠገባቸው የማያልፈው አልጋወራሽ ራስ ተፈሪ የዘውዲቱን ለመሄድ መነሳት ሲሰሙ "እንድ ሽፍታ በተነሳ ጊዜ ንጉሠ ነገስቱ ራስ ሄዶ መማለድ አይገባምና ንግስት እንዲሄዱ አልስማማም፡፡" የሚል ምላሽ ስለላኩ ግርማዊት ንግስት እንዳይሄዱ ሆነ፡፡ ሁሉም ግራ ተጋብቶ ፀጥ ባለበት ሰዓት ቀኛዝማች ኃይለስላሴ የተባሉት "ከንግስት ቃል ካልሰማሁ ካለና ንግስትም መሄድ ካልቻሉ አሁን ስልክ ቢጠለፍ ይደርሳልና ንግስት በስልክ ማነጋገር ቢችሉ የተሻለ ነው" የሚል ኀሳብ አቀረቡ፡፡ በዚህ ሁሉም ተስማምቶበት ባለሙያዎች ተጠርተው ገመድ የመቀጣጠሉ ስራ ሁለት ሰዓት ከፈጀ በኋላ ተሳካ፡፡

ንግስት ዘውዲቱ አባውቃውን በስልክ አነጋገሩ፡፡አባውቃው "እረ ለመሆኑ ንግስት ደህና ነዎት ወይ" ሲሉ "ደህና ነኝ" አሏቸው፡፡ "በንግስት ላይ የደረሰ ነገር ከሌለማ እኔ ምን ገዶኝ? አልነግስ" ብለው እጃቸውን ሰጡ፡፡ተፈሪ እፎይ አሉ፡፡ ቀጣዩ ስራ ስለፍርድ ሂደት መወያየት ነበርና ንግስትና አልጋወራሽ በፍርዱ ጉዳይ ሲወያዩ ራስ ተፈሪ "አባውቃው የሰው ህይወት ለማሳለፍ የተነሳ አመፀኛ ስለሆነ በችሎት ቀርቦ ነገሩ ታይቶ ውሣኔ በሚሰጥበት ጊዜ የፍርዱ ውሳኔ በሞት እንዲቀጣ የሚል የሆነ እንደሆነ ያለምህረት እንደፍርዱ ቅጣቱ በሞት እንዲፈፀም ያስፈልጋል፡፡" አሉ፡፡

ዘውዲቱ በበኩላቸው "እስቦ ይነሳ እንጂ በተነሳበት ነገር ነፍስ የጠፋ ስላልሆነ ሞት ቢፈረድበትም በእስራት ቢቀጣ እንጂ በሞት



መቅጣቱ ቅር ያሰኛል" የሚል መልስ ስለሰጡ፣በአልጋወራሹና በንግስት መካከል ከፍተኛ የኀሳብ ልዩነት ተፈጠረና ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የውስጥ ለውስጥ ፍልሚያው ገሃድ ወጥቶ በሽማግሌ ብቻ የሚነጋገሩ ሆኑ፡፡

ዘውዲቱ አድርገውት የማያውቁትን ጠንከር ያለ ምላሽ በመስጠታቸው ተፈሪ ቢበሳጩም ዋናው የአባውቃው እጅ መስጠት እንጂ ቀሪው ጉዳይ ቀላል ስለሆነ በደጃዝማች ሙሉጌታና በደጃዝማች ወልደፃድቅ ሽምጋይነት ስለፍርዱ ሁኔታ ንግስትና አልጋወራሹ ሲነጋገሩበት ቆይተው በመጨረሻ አባውቃው በአልጋወራሽ ችሎት የሞት ፍርድ ተፈረደባቸው፡፡ከዚያም የሞቱ ፍርድ በእስራት ተለውጦ ደጃዝማች አባውቃው ታስረው ወደ እንኮበር እንዲሄዱ ተወሰነ፡፡ይህ ፍርድ በተፈረደበት እለት በወቅቱ የወንጀለኛ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት የነበሩት ደጃዝማች መሰፍን ገመቹ ባልተለመደ ሁኔታ በችሎቱ ላይ አልተገኙም፡፡ፍርዱ ከተከናወነ በኋላ ለምን ችሎቱ ላይ እንዳልተገኙ ሲጠየቁ የሰጡት መልስ ሁሉንም ያስገረመ ነበር፡፡ እንዲህ ይነበባል፤

"ብፍትሐ ነገስቱ ባንዱ አንቀፅ ጌታውን የከዳና የወጋ ይሙት ሲል፤ በአንደኛው አንቀፅ ደግሞ በጌታው ላይ የደረሰውን አደጋ ለመከላከል ሲል ቢገድል ሞት የለበትም ይላል፡፡ስለዚህ የዚህ ሰው ጥፋት ማንኛው ነው?" የሚል ነበር መልሳቸው፡፡

የአባውቃው ፍርድ ከተከናወነ በኋላ በከተማይቱ ለቀናት ሰፍኖ የነበረው ውጥረት ቢረግብም፤ ወዲያው ደግሞ በአባውቃው መያዝ የተደፋፈሩት የአልጋወራሹ ደጋፊዎች ያችኑ ጥያቄ እንደገና በገሃድ አነሷት፡፡

እነዚህ የተፈሪ ደጋፊ የሆኑ ግለሰቦች በወቅቱ ዝቅ ያለ ስልጣን የነበራቸውና ለመልዕክትም የማይመጥኑ ቢሆኑም፤በነሲቡ ዘ-አማኑኤል እየተመሩ በሌሎች ግፊት ተደርጎ የማያውቀውን ተግባር (በንግስተነገስት ፍላጎትና በምክክር ብቻ መፈፀም የነበረበትን) በኃይል ለመፈፀም ወደ ቤተ-መንግስቱ ሄዱና በድፍረት "ተፈሪን ያንግሱልን" የሚል ጥያቄ አቀረቡ፡፡በዚህ ጊዜ በፈቃድ የሚደረገውን ባድማ ማድረጉ ሳያንስ የተላኩት ሰዎች በንግስት ዘንድ የማይታወቁና ለመግባትም ማዕረጋቸው የማይፈቅድ መሆኑን አይተው ዘውዲቱ በእጅጉ አዘኑ፡፡ሆኖም ምንም ምርጫ አልነበራቸውም፡፡ከግራ ከቀኝ ሲያዋክቧቸው "እሺ ብየዋለሁ፤ ንጉስ ብየዋለሁ" አሉ፡፡ የተለመደው የአንድ ግዛት ንጉስ ማድረግ ነበር፡፡ አዲስ አበባ ደግሞ ንጉስ ተሾሞባት አያውቅም፤ንጉሰ ነገስት እንጂ፡፡ስለዚህ ግርማዊት ንግስተ ነገስታት ዘውዲቱ ሁሉም ወደ ተፈሪ አዘንብለው፣የነበሩት ደጋፊዎቻቸው ተማርከው፣ ተግዘውና ታስረው ብቻቸውን ቀርተው ስለበር ምንም ምርጫ አልነበራቸውምና "ንጉስ" አሏቸው እንጂ "የምን ንጉስ?" ተብለው ቢጠየቁ ራሳቸውም

አይመልሱትም።የአንድ ክፍለ ሀገር ንጉስ እንዳይባሉ መቀመጫቸው አዲስ አበባ ነው።አልጋወራሽም ናቸው።የአዲስ አበባ ንጉስ የሚባልም የለም ሊኖርም አይችልም።በጥቅሉ በንጉሰነገስት መቀመጫ (መናገሻ) ከተማ ላይ ንጉስ አይሾምም።ግራ የተጋባ ብቻ ያን ሊያደርግ ይችላል።ዘውዲቱ ይሄን ይመስሉ ነበር።

እናም ልዑል አልጋወራሽ ራስ ተፈሪ መኮንን መስከረም 27 ቀን 1921 ዓ.ም ንጉስ ሆኑ። እሁንም ይሄ ሳያንስ ንጉስ ተፈሪ "የንግስ በዓሉ የሚደረገው በቤተ-ክርስቲያን ይሁንልኝ" አሉ።ንግስት ዘውዲቱም "በቤተ-ክርስቲያን የሚደረገው የዘውድ በዓል ለንጉሰ ነገስት እንጂ ንጉሰነገስቱ የሚሾመው ንጉስ ዘውድ የሚጫንለት በቤተ-መንግስት ነው" ብለው ሞገቱ።በዚህ ጉዳይ ብዙ ክርክር ከተካሄደ በኋላ ሁለቱን ሊያስማማ የሚችል አማካይ ቦታ ተመረጠና ከቤተ-መንግስቱ በላይ ከመታሰቢያ ቤቱ በታች ባለው ጎተራ ሜዳ በሚባለው ቦታ ትልልቅ ድንኳኖች ተጥለው የንግስ በዓሉ በድምቀትና የውጭ አገር መንግስታት ልዑካን ጭምር የተገኙበት ሆኖ በተጠቀሰው ዕለት ተከናወነ።ንጉስ ተፈሪ ዘውዳቸውን ከደፉ በኋላ እዚህ ደረጃ ላደረሳቸው አምላክ የምስጋና ፀሎት ለማድረግ በቀረበላቸው ያማረ ሰረገላ ላይ ተሳፍረውና በክብር ታጅበው ወደ ቅድስት ስላሴ ቤተ-ክርስቲያን በማምራት የምስጋና ፀሎታቸውን ካደረሱ በኋላ ወደቤታቸው ወደገነተ ልዑል (ወደላይኛው ጊቢ) ሄደው መሳፍንት፣መኳንንት እና ህዝቡን ሰበሰበው ግብር አበሉ።

ከዚህ ጊዜ በኋላ ንጉስ ተፈሪና ንግስት ዘውዲቱ ግንኙነታቸው ተቋርጦ በጣም አስፈላጊ ጉዳይ ከሆነ ብቻ በቀጠሮና በመልዕክተኛ አልፎ አልፎ ከመገናኘት በቀር በአካል ተያይተው አያውቁም። ይህም ብቻ አይደለም ላይኛውና ታችኛው ቤተ-መንግስት እየተባለ ቀድሞ ባንድ ቤተ-መንግስት ይደረግ የነበረው የግብር ማብላት ስርዓት ቀርቶ በሁለት ቤተ-መንግስት ሁለት ግብር ሆኖ አረፈው።

ሹማምንቱም የለየው ለይቶለት አንዱን ወግኖ ሲቀር፤ ጥቂት ሹማምንት ደግሞ ጉዳዩ "ለሁለት ጌቶች መገዛት..." ሆኖባቸው በግራ መጋባት ቀሪዋን ዓመት ተኩል እንደምንም ለማሳለፍ ተገደዋል።

ቀደም ሲል የተጠቀሰውን "የታሪክ ማስታወሻ" የሚለውን መፅሐፍ የፃፉትና ተጀምሮ እስኪጨረስ የተፈሪ ደጋፊ የነበሩት ልጅ ከበደ ተሰማ (በኋላ ደጃዝማች) "ይህን ታሪክ ማስታወሻ የምፅፈው በቅርብ ሆኜ ሁኔታውን እንዳጠናሁት የንግስትን አስተያየትና ኀሳብ ከዚህ በታች በተመለከተው አረፍተነገር በአጭሩ እገልፃለሁ።" በማለት የንግስት ዘውዲቱን ሁኔታ እንዲህ ይነግሩናል።"እኔን ሳያውቀኝና ሳልጠቅመው የአባቴን ውለታና ወሮታ ለመመለስ ሲል የኢትዮጵያ መሣፍንት መኳንንትና ህዝቡም በፈቃደ እግዚአብሔር ታዝዞ ለአባቴ ዙፋን



ቢያበቃኝ፣ ከእኔ አስተዳደር አለማወቅ የተነሳ ህዝቡ እርስ በርሱ ተፋጅቶ ከሚያልቅና ራሳቸውን አልቻሉም ተብሎ በዘመነ መንግስቴ የባዕድ መንግስትና ገዥ በኢትዮጵያ ላይ ከሚገባ እኔ የተጠየቅሁትን ስልጣን እየለቀቅሁና እየሰጠሁ ነገሩን ማብረድ ይሻላል" በማለት የሚገጥማቸውን ችግር ሁሉ ከፍ ባለ ትዕግስት ያሳልፉት እንደነበረ በግልፅ ይታወቅ ነበር" ይሉናል። ሲቀጥሉም "ይህ የእኔ ኀሳብ ብቻ ሳይሆን በዚያን ዘመን አንዳንድ ሰዎች ከመኳንንቱም ሆነ ከመሐል ሰፋሪው ወደ ንግስት ዘንድ እየመጡ ጥቃትዎንና በደልዎን አንወድምና ቅር የተሰኙበት ነገር እንዳለ ይንገሩን እያሉ ሲጠይቋቸው ለነዚህ ሰዎች ንግስት የሚመልሱትን መልስ በመስማቴ ገለፅኩ እንጂ አስመስዬ በመናገር የተፃፈ አይደለም" ይላሉ ያይን እማኙ።

ከዚህ አንፃር በየትኛውም ፀሐፊ እይታ አገላለፁ ይለያይ እንጂ የንግስት ዘውዲቱ ስልጣን አለአግባብ እየተገዘገዘ መኖሩን ማንም የማያስተባብለው ሐቅ ነው። ንጉስ ተፈሪ አሁን አንድ አስጊ ባለሥልጣን ቀርቷቸዋል።የዘውዲቱ ባለቤት ራስ ጉግሣ ወሌ።ህዝቡ እንዳሰበው አልሆነም እንጂ እያሡ ወርዶ ዘውዲቱ ሲተኩ የአስተዳደሩን ስራ በባልነታቸው ራስ ጉግሳ ይይዙታል ተብሎ ተገምቶ ነበር። በእርግጥም ግምቱ ያስኬድ ነበር።ሆኖም ወቅቱ ለተገቢ አካሄዶች የማይመች ነበርና ራስ ጉግሳ ከባለቤታቸው እንዲርቁ አስበው የሸዋ መኳንንት በዘየዱት መሰረት ወደቀድሞው ግዛታቸው በጌምድር ሾመው ልከዋቸዋል።

ራስ ጉግሳ በግዛታቸው ላይ ሆነው የባለቤታቸውን በደል ቢያውቁም፤ለጊዜው እንደማንኛውም ባለሥልጣን ተመልካች ከመሆን በቀር ሌላ ዘዴ አልታያቸውም። ስለዚህም በስተመጨረሻ ቂማቸው ገንፍሎ በገሃድ ለማመፅ ይዘጋጁ እንጂ፤ ከዚያ ጊዜ በፊትም ፀረ-ተፈሪ መሆናቸው ለማንም ግልፅ ነበር።

ራስ ጉግሳ በተፈሪና በተከታዮቻቸው ላይ ሃይማኖትን ማዕከል ያደረገ "ተፈሪና የሸዋ መኳንንት የውሻ ሥጋ ይበላሉ" ከሚለው ክስ ጀምሮ የተለያዩ መጥፎ መጥፎ ወሬዎችን ያስወሩ ነበር።በዚህም ላይ እንደባልቻ የተፈሪን ትዕዛዝ "አልቀበልም" ባይ ሆነው የቆዩ ናቸው።እነዚህን ወሬዎች የሰሙት አልጋወራሽም በራስ ጉግሳ ስር የነበሩትን ትልልቅ ሹማምንት በችሮታ እያባበሉ ጉግሳን ከድተው ለራሳቸው እንዲገቡ ማድረግ ከጀመሩ ቆይተዋል።ከእነዚህም ውስጥ የስሜኑ ገዥ ደጃዝማች አያሌው ብሩ አንዱ ናቸው።

ከሐሜቱም ባለፈ አልጋወራሹ በራስ ጉግሳ ስር የነበረውን የመተማን ጉምሩክ በስራቸው ለማድረግ ብዙ ጥረት ሲያደርጉ በራስ ጉግሳ እንቢተኝነት ሳይሳካ ቀርቷል። በእነዚህና በሌሎች ምክንያቶች የሁለቱ ጠላትነት ስር ሰዶ የቆየ ሲሆን፤ የጎጃሙ ራስ ኃይሉና የትግራዩ ራስ ስዩምም ውስጥ ውስጡን ለራስ ጉግሳ ከጎንህ ነን ባዮች መሆናቸው በአልጋወራሹ ዘንድ የተሰማ ስለሆን

ህይወታቸው አለፈ፡፡ ልጅ ተፈሪ የእናትን ጣዕም ሳያውቀው ቀረ፡፡ ከህፃንነቱ ጀምሮ የአጎቱ የደጃዝማች ብሩ ሐይለማርያም ባለቤት ወ/ሮ ትሰሜ አባይርጋ ከእምሩና ከልጃቸው ጋር አሳደጉት፡፡



ተፈሪ በልጅነቱ ከአብሮ አደጎቹ እምሩና ማሚትጋር።

በዚያም ሳሉ አባታቸው ራስ መኮንን የፈረንሣይኛ ትምህርት እንዲማሩ መምህር ቀጠሩላቸውና ልጅ ተፈሪ ትምህርታቸውን እየተከታተሉ አደጉ፡፡ በ10 ዓመታቸው በ1894 ዓ.ም ከሐረር ወደ አዲስ አበባ መጥተው ለመጀመሪያ ጊዜ ከአፄ ምኒልክ ጋር ተገናኝተው /ተዋውቀው/ ተመልሰው ወደ ሐረር ሄዱ፡፡

አባታቸው ራስ መኮንን በ1898 ዓ.ም ህዳር 10 ቀን የደጃዝማችነት ማዕረግ ሰጥተው "ጋራ ሙለታ" የተባለውን አውራጃ ሾሟቸው፡፡ "ተከታይ ልጇ ደጃዝማች ተፈሪ ነው" ብለውም ለመኳንንቶቻቸው ይፋ አደረጉ፡፡ ልጅ ተፈሪ በ14 ዓመታቸው የደጃዝማችነት ማዕረግ እንዳገኙ ወዲያው በ1898 ዓ.ም መጋቢት 13 ቀን አባታቸው ራስ መኮንን ሞቱ፡፡ በዚህ ጊዜ አፄ ምኒልክ ተፈሪን ከሐረር ወደ አዲስ አበባ አስመጥተው ደጃዝማችነታቸው እንደፀና ቀረብ የሚለውን የሰላሌን ግዛት ሾሟቸው፡፡ ተፈሪ ግን ለተሰጣቸው ግዛት ሌላ እንደራሴ ወክለው በኢትዮጵያ ብቸኛ ትምህርት ቤት በነበረው በዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ገብተው ሐረር እያሉ የጀመሩትን ትምህርታቸውን ቀጠሉበት፡፡





ህጻኑ ተፈሪ እና አባታቸው ራስ መኮንን

ከዚያም በ1899 ዓ.ም የባሶ /በጌምድር/ ግዛትን፣ ቀጥሎ በ1900 ዓ.ም ሲዳሞን ተሾሙ፡፡ ከሁለት ዓመት በኋላም ሲዳሞን ትተው የአባታቸውን ግዛት ሰፊውን ሐረርጌንና አውራጃዋን እንዲያስተዳድሩ ተደረገ፡፡ የሐረርጌ ህዝብም በደስታ ተቀበላቸው፡፡ በ1903 ዓ.ም በሐምሌ ወር የንጉስ ሚካኤልን የልጅ ልጅ ወ/ሮ መነንን አግብተው መኖር ጀመሩ፡፡



ደጃዝማች ተፈሪ በ19 ዓመታቸው ወ/ሮ መነንን አግብተው በ1905 ዓ.ም የመጀመሪያ ልጃቸውን ልዕልት ተናኘወርቅን ወለዱ፡፡ ከምኒልክ ሞት በኋላ ስልጣን የያዘው እያሡ በ1907 ዓ.ም ደጃዝማች ተፈሪን ከሐረርጌ ግዛት ሽረው ወደአዲስ አበባ መጥተው እንዲቀመጡ ተደረገና ወዲያው የከፋን ግዛት ሾማቸው፡፡ ሆኖም ደጃዝማች ተፈሪ አልሄዱበትም፡፡ ተፈሪ የአውሮፓ ቋንቋ የሚያውቁ፣ ከአውሮፓውያኑ ጋር ያለአስተርጓሚ በቀጥታ የሚነጋገሩ ጨዋ፣ ዝምተኛ ... እየተባሉ ቆዩ፡፡

በ1909 እያሡ ከስልጣን ተወግዶ ዘውዲቱ ሲነግሱም በወቅቱ አዲስ አበባ የነበሩት ደጃዝማች ተፈሪ ራስ በሚል ማዕረግ አልጋወራሽ ሆነው የራስ ወርቅ አሰሩ፡፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ንጉሠ ነገስት እስከሆኑበት እስከ 1923 ዓ.ም ድረስ በተከታታይ ልዑል አስፋወሰንን፣ ልዕልት ዘነብወርቅን፣ ልዕልት ፀሐይን፣ ልዑል መኮንንን እና አቤቶ ሳህለስላሴን ወልደዋል፡፡

የሚያዳፍን ሆኖ አይገኝም፡፡የአድናቂዎቻቸውና የተቺዎቻቸው የገለፃ ልዩነት የሰሩትን ስራ በማግዘፍና በማጣጣል የሚገለፅ መሆኑ እንጂ፤ጃንሆይ ይህችን አገር የማዘመኑን ስራ በፅኑ መሠረት ገንብተው ለትውልድ ማስረከባቸው መስተባበል የማይችል ሐቅ ነው፡፡

በጃንሆይና በኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ጉዳዮች በርከት ያሉ መፃህፍት የፃፉት አሜሪካዊ ሐሮልድ ማርከስ ጃንሆይን "የዘመናዊት ኢትዮጵያ አርክቴክት" ይሏቸውና፤ ኢትዮጵያን በስልጣኔ ለማራመድ ስለሚጠቀሙበት ዘዴም ጥንቁቅ ነበሩ ብለው ይገልጿቸዋል፡፡ ስልጣኔ በእጠገቡ አልፎ ለማያውቀው ህዝባቸው ፈጣንና ድንገተኛ ማኅበራዊ ለውጥ ቢፈጠር ለህዝቡ ክፉ ፅጣ እንዳይሆንበት በመስጋታቸውም አረማመዳቸውን ለዘብ እንዳደረጉ ይጠቁማሉ፡፡

በተቃራኒው ፕሮፌሰር አለማየሁ ገብረማርያም "Atse Haileselassie and Modern Ethiopia" በተሰኘ ጽሁፋቸው "ጃንሆይ አገር የማዘመን ሂደትን እንደ ውስብስብ መስተጋብር እንዳልተረዱት ..." በመግለጽ፤ ለመንግስታቸው በነበራቸው እመለካከትና ዘመናዊነትን ለማስፋፋት በሚያደርጉት ጥረት መካከልም የማይታረቅ ተቃርኖ ነበረ ይሉናል፡፡ ከተቺዎቻቸው በኩል የሚሰነዘረው ተደጋጋሚ ትንተና "የአፄ ኃይለስላሴ አገር የማዘመን ፕሮጀክት ቁልፍ ፍላጎት ስልጣናቸውን በተደላደለ መሰረት ላይ ለማስቀመጥ ሲሉ የተጓዙበት መንገድ የወለደው ነው" የሚል ነው፡፡

የ"SurviVal and Modernization" ፀሐፊ ፕሮፌሰር መሳይ ከበደ "ዘመናዊነት የአፄ ኃይለስላሴ መንግስት እውነተኛና ትክክለኛ ግብ ነው የሚለውን አስተሳሰብ ወደ ጎን ካላልነው በስተቀር፤ ኢትዮጵያን የማዘመን ፕሮጀክትን ፅንሰ ኀሳባዊ ድቀት ከመሰረቱ ልንረዳው አንችልም" በማለት የዘመን ሂደቱ ድቀት የመጣው በመዋቅራዊ ችግሮች ወይም ተገቢ ያልሆኑ ፖሊሲዎችን በመተግበር እንዳልሆነና፤ ይልቁንም ምንጩ ዘመናዊ ዘዴዎችን በመጠቀም ልማዳዊ ግቦችን ለማሳካት በሚደረጉ ሂደቶች በመጣ ተቃርኖ መሆኑን ያሰምሩበታል፡፡ "በውስጣዊ ለውጥ ያላለፉ ባህላዊ ኃይሎች ማኅበራዊ ለውጥን ከማነሳሳት ይልቅ ዘመናዊ ዘዴዎችን በመጠቀም ስልጣናቸውን ወደማጠናከር ያዘነብላሉ" ሲሉም ያክሉበታል፡፡

ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ "Haylasellasie: From progressive to reactionary" በተሰኘ ጥናታዊ ጽሁፋቸው "ኢትዮጵያ በአውሮፓዊ ቅኝ ገዥዎች ታጥራ ነፃነቷ እንደእዋኪ ቅንጦት በሚታይበት ጊዜ የነበራት አማራጭ ማዕከላዊ መንግስት ማጠናከር ብቻ ነበር፡፡ የኃይለስላሴም ታሪካዊ ሚና የውስጥ ሐብትንና የውጭ እርዳታን አቀናጅቶ ይህን አላማ ማሳካት ሆነ" ይላሉ፡፡



እነዚህንና እነዚህን መሰል ትንታኔዎች ስናይ አፄ ኃይለስላሴ በዘመናቸው ያከናወኗቸው ትልልቅ ስራዎቻቸውን አፍቃሬ ስልጣንነታቸው እንደጋረደባቸው፤ ወይም ስራቸው በበጎ ገፅታው ብቻ እንዳይታይላቸው ማድረጉን በቀላሉ እንረዳለን፡፡

ከዚሁ ጋር ተያይዘውም ጎን ለጎን የሚነሱ የጃንሆይን ሰብዕና የሚገልፁ ትንታኔዎች አሉ፡፡ ገሚሱ ደግ፣ ሩህሩህ፣ እያለ ሲገልፃቸው፣ የቀረው ጨካኝ፣ ምህረት የለሽ... እያለ ይፅፉቸዋል፡፡

ይህንኑ ጉዳይ በተመለከተ ሁሉንም የሚያስማማ ሆኖ ያየሁትን ገለፃ ሳስከትልና ወደ ዋናው ታሪካቸው እንለፍ፡፡ አምባሳደር ብርሃኑ ድንቄ "ቄሳርና አብዮት" በሚል መጽሐፋቸው ያሰፈሩት ገለፃ ነው፡፡ "በግል ጥላቻ ሳንታወር፣ ያለአንዳች አድልዎ ያለፈውን ድርጊት ለማስታወስና ትርጓሜውን ለመመርመር ጥቂት ጊዜ ካገኘን፣ አፄ ኃይለስላሴ ብዙ ገጾች ያሏቸው አስደናቂ ሰው መሆናቸውን ለመገንዘብ እያስቸግረንም፡፡ "ኮንሰርቫቲቭ" ናቸው ስንላቸው "ሊበራል" የሆነ ስራ ሲሰሩ ይገኛሉ፡፡ ንቅዝ ናቸው ስንል ፍትህ ለመስጠት ሲሞክሩ ይታያሉ፡፡ ጨካኝ ሲሆኑ፤ ደግሞ የርህራሄ ስራ ከመፈፀም አያቋርጡም፡፡ በቀለኛ ናቸው ሲሏቸው ምህረት ያደርጋሉ፡፡ ይህ ቅያጤ (combination) በምሳሌና በማስረጃ የሚደገፍ "ፓራዶክስ" ወይም ሊታመን የማይችል እውነተኛ ነገር ነው፡፡" ይሉናል የዓይን እማኙ፡፡ አፄ ኃይለስላሴ ንጉሰነገስት እንደሆኑ የፈፀሙት የመጀመሪያ ተግባር በኢትዮጵያ ታሪክ የመጀመሪያ የሆነውን ሕገ-መንግስት ማፅደቅ ነበር፡፡ ከዚሁ ተግባራቸው ተነስተን እንቀጥላለን፡፡

## የጃንሆይ ሕገ-መንግስት፤ ፓርላማና ምርጫ

አይነትና አደረጃጀቱ፣ ዘመኑና ሁኔታዎች ይለያዩ እንጂ አፄ ኃይለስላሴ የመሰረቱት መንግስት አፄ ቴዎድሮስ ሞክረው ያቃታቸውን አይነት ነው፡፡ ዘመናዊነትን የተላበሰው አስተዳደጋቸውም የስልጡን አስተሳሰብ ባለቤት ያደረጋቸው ይመስላል፡፡

ኢትዮጵያን በአንድ የዘውድ ስርዓት ስር አድርጎ ለመግዛት የቴዎድሮስ መሻት ነበር፡፡ የኃይለስላሴም ተመሣሣይ ነው፡፡ ነገር ግን የተጠቀሙት ዘዴ ለየቅል ነው፡፡ ኃይልና ብልሃት፡፡

አፄ ኃይለስላሴ የንጉሠ ነገስትነት ስልጣኑን ስለያዙ ብቻ "እፎይ" ተብሎ እንደማይኖር ገብቷቸዋል፡፡ በግልፅ ስናየው እንደመጣነው ያለፉት ነገስታት ከነገሱበት ጊዜ ጀምሮ ዙፋን ላይ ተቀምጠው ሳይሆን "ኮርቻ"ላይ ተቀምጠው ነበር የሚገዙት ለማለት ይቻላል፡፡ ሁሌ ዘመቻ ነው! አገሌ የተባለው መሳፍንት በጎንደር ተነሳ ይባላል፤ ነገስታት ወደ ጎንደር ጋልበው በኃይል አሣምነው መንገድ እንደጀመሩ፤ የወሎው ባላባት ሸፈተ ይባላል፡፡ በዚያው ወደ ወሎ፣ ቀጥሎ ሲዳሞ ... ወዘተ፡፡ ኃይል ሲጠፋ ጋብቻ እንዳማራጭ ይወሰዳል፡፡

እንዲሆን ጥረዋል፡፡ የተጠቀሱት አንቀጾችም ቢሆኑ ለዘመናት የኖሩ ናቸው፡፡ንጉሡ የነበረውን ባህል ፃፉት፡፡ ፅፈውም ሕግ አደረጉት፡፡

በርካታ ምሁራን የተጠቀሱትን አንቀጾች እየጠቀሱ ሕገ-መንግስቱን ይተቹታል፡፡በእውነቱ ያን ሕገ-መንግስት ለመተቸት የሚያስችል አንዳችም ታሪካዊ መነሻ በኢትዮጵያ ምድር ኖሮ አያውቅም፡፡እርግጥ ነው በሕገ-መንግስቱ ንጉሠነገስቱ ለመሾምና ለመሻር፣ፍርድ ለመስጠት፣ጦርነት ለማወጅና ለማቆም፣ መሬትና የክብር ማዕረግ ለመስጠት ስልጣን አላቸው፡፡ማንኛውም መሳፍንት ግን በግሉ እንዳለፈው ዘመን ከውጭ አገር መንግስታት ጋር መዋዋል፣መሳሪያ፣ ሽልማትና ማናቸውንም አይነት ጥቅማ ጥቅም መቀበል አይችልም፡፡በአጠቃላይ እያንዳንዱ ነገር ከንጉሠነገስቱ የምትመነጭ ሆና መሳፍንቱን በቁጥጥር ስር ማድረግ ተችሏል፡፡

"የመሳፍንቱ ስልጣን እንዳለ ነው፤ ነገር ግን ለሕግ መገዛት መልመድ፣ መቻል አለባቸው" በሚለውን እቅድ ብቻ እንኳ በበጎ ጎኑ ማየት ይቻላል፡፡ "ስልጣናቸውን ለማጥበቅ" ሲሉ እንጂ አንዳችም ብሔራዊ ፋይዳ አልነበረውም ይባላል፡፡ አፄ ኃይለስላሴ ስልጣናቸው ላይ አልተኙም፡፡ ሠርተውበታል፡፡ ስልጣን በማፍቀር ኃይለስላሴ እንደማንኛውም አፍሪካዊ መሪ ተወዳዳሪ እንዳልነበራቸው ግልፅ ነው፡፡ ለዚህ ርህራሄም የላቸውም፡፡ ታሪካቸውን ከልብ ስንመረምር ግን "ለኢትዮጵያ የማስፈልጋት እኔ ነኝ" ያሉ ይመስለናል፡፡

ከሁሉም በላይ ደግሞ የ1923ቱ ሕገ-መንግስት ምን አይነት ይዘት ቢኖረው ይሻል ነበር? ብለን መጠየቅ አለብን፡፡ መቼም ... መሳፍንቱን፣ መኳንንቱን በአንድ ጊዜ ስልጣናቸውን ነጣጥቀው እጅግ ዘመናዊ የሆነውን ዴሞክራሲያዊ ስርዓት እንዲዘረጉና ራሳቸውን አደጋ ላይ እንዲጥሉ አሁን ላይ ሆነን እንመክራቸውም፡፡ ያን ሁሉ ወግና ባህል በአንዴ መናድ እብደት ይሆናል፡፡

የሆነ ሆኖ የ1923ቱ ሕገ-መንግስት መሳፍንቱ፣ መኳንንቱና ሚኒስትሮች ጥቅማችን ተነካ ብለው እንዳያጉረመርሙ አድርጎ ፀጥ ለማሰኘት ሲባል ፊውዳላዊ አካሄዱ እንዲቀጥል ግድ ሲሆን፤ ተራው ማኅበረሰብም እውቀትና ችሎታ እስካለው ድረስ የሚሾምበትን ሁኔታ አመቻችቷል፡፡

አፄ ኃይለስላሴ "በዓለም ላይ ፊውዳሊዝም መቅረቱን እያወቅን..." ስላሉ አገዛዛቸው ፊውዳል አልነበረም ለማለት አያስችልም፡፡ ሹማምንቱ የርስትና ጉልት ተተካዮች ስለሆኑም አገዛዛቸው ፊውዳል ነበር ለማለት አያስችልም፡፡

አሁንም በርካታ ምሁራን አፄ ኃይለስላሴንም ሆነ አገዛዛቸውን ሙሉ በሙሉ "ፊውዳል" የሚል መጠሪያ ሰጥተውታል፡፡ (አብዮቱን



ለማግነን ሲባልም ብዙ ተብሏል፡፡) የፊውዳል ትርጓሜ የቀጥቃጭ ልጅ ቀጥቃጭ፣ የሸማኔ ልጅ ሸማኔ፣ የገበሬ ልጅ ገበሬ፣ የገባር ልጅ ገባር፣ የባላባት ልጅ ባላባት ... ነው፡፡ ይሄኛው የፊውዳል ትርጓሜ በአፄ ኃይለስላሴ እጠገብ አልፎ አያውቅም፡፡ ሹማምንቱ በርስትነት የሚይዙት ሰፊ መሬት ቀጥሎ መቆየቱ "ፊውዳላዊ" ካልተባለ በቀር፡፡ እሱም ቢሆን ተራ ሰው ከተሾመ ከሹመቱ ጋር አብሮ ይሰጠዋል፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት ደግሞ ለጊዜው የነበረው ሐብት መሬት ነው፡፡ ጥቅማ ጥቅሙም በመሬት ነው፡፡ በአጭሩ የኃይለስላሴ ዘመን ፊውዳል አልነበረም፡፡ ከፊል ፊውዳል፣ ከፊል ካፒታሊዝም ነው፡፡ እንደዛሬው፡፡ መሬቱም ህዝቡም የንጉሡ ነገስቱ ነው...፡፡

አፄ ኃይለስላሴን በንግስት ዘውዲቱ ዘመን በወግ አጥባቂዎቹ ጥርስ ውስጥ ያስገባቸው አንዱ ምክንያት ፊውዳል አለመሆናቸው ነው፡፡ አሁን ግን ሕገ-መንግስቱም ይፈቅዳልና እንደልባቸው ሁሉንም አይነት የኅብረተሰብ ክፍል "ምን ሞያ አለው?" እያሉ ማሳተፍ የሚችሉበትን ሁኔታ አረጋግጠዋል፡፡

ከእርሳቸው በፊት በነበረው ዘመን ግን ጥያቄው "የሰው ልጅ ነው ወይ?" የሚል የዘር ሐረግን ማዕከል ያደረገ ነበር፡፡ የ1923ቱ ሕገ-መንግስት ኢትዮጵያ በውስጧ ሁከት የሌለባትና በሕገ-መንግስት የምትተዳደር አገር ተብላ እንድትታይ፣ ህዝቡ አዲስ የአስተዳደር ስርዓት እንዲለምድ መሠረት በመጣል፣ የመሳፍንቱን ልቅ ስልጣን ለመገደብ፣ ፊውዳሊዝምን በከፊል ቆርሶ ለመጣል፣ ምሁራንን እንደልብ ለማሳተፍ በማስቻል ... ከፍተኛ ሚና ነበረው፡፡ አንዳንድ ምሁራን ዛሬ ላይ ሆነው እንደሚያጣጥሉት አይደለም፡፡

ኢትዮጵያ በሕገ-መንግስቱ መሠረት የሁለት ፓርላማ ባለቤት ሆነች፡፡ አንደኛው /የላእላይ ፓርላማው/ የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት የሚል ስያሜ ሲሰጠው ሁለተኛው ፓርላማ ደግሞ የሕግ መምሪያ ምክር ቤት ተሰኘ፡፡

ሁለት ምክር ቤቶች ያሉት ፓርላማ የአባላቱ አመራረጥ የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባላት መሳፍንቱና መኳንንቱ ሲሆኑ፤ እነሱም በቀጥታ በንጉሠነገስቱ የሚመረጡ ናቸው፡፡ ይህም ሲባል መንግስታቸውን ብዙ ካገለገሉና መሳፍንት ካልሆኑ ተራ ሰዎችም ጭምር የተውጣጡ ተመራጮች ይሳተፉበታል፡፡

የሕግ መምሪያ ምክር ቤት ደግሞ "ህዝቡ ለቀጥተኛ ፖለቲካዊ ተሳትፎ /ምርጫ/ ገና አልበቃም" በሚል መነሻ መሳፍንቱና መኳንንቱ፣ እንዲሁም ሌሎች ሹማምንት ያመኑባቸውን የበታች ሹማምንት የህዝብ እንደራሴዎች እንዲሆኑ የመምረጥ ስልጣን ተሰጣቸው፡፡

እንደራሴዎች ከሚመረጡበት መስፈርት አንዱም "ሀብትና ንብረት ያላቸው" የሚል ተጠያቂነትን ማዕከል ያደረገ ነበር፡፡ ምክር ቤቶቹ "ወደፊት አስፈላጊ ሲሆን የሚጨመሩ" ተብሎ 56 አባላት እንዲኖሯቸው ተደረገ፡፡ሂደቱ በግልፅ እንደሚያሳየው ሕግ አውጭው አካልና ሕግ አስፈፃሚው አካል የተያያዙ እንጂ ለየቅል ሆነው የሚጓዙበት ሁኔታ የለም፡፡ለዚህም ነው "ንጉሡ ፓርላማ እንዲኖር ፈቅደው መልሰው በራሳቸው ቁጥጥር ስር አደረጉት" ተብለው የሚወቀሱት፡፡እሁንም በተመሳሳይ ለመንቀፍ የሚያስችል "ትክክለኛ" ሞራል እጃችን እስኪገባ ድረስ፣ወይም ማነፃፀሪያውን በአገራችን እስክናገኝ ድረስ በዚህ ጽሁፍ ከመንቀፍ ተቆጥበን እንቀጥላለን፡፡እንደዚያ መሆን እንዳልነበረበት ከታወቀ አልፎ ሄዶ ሙታንን መውቀሱ አሀያውን ፈርቶ ዳውላውን ስለሚሆን እንጂ ወቀሳው ግን ተገቢ ነው፡፡

የመጀመሪያውን ፓርላማና ሕገ-መንግስቱን በሚመለከት የሕገ-መንግስቱ "ዋና" አርቃቂ በጅሮንድ ተክለሐዋርያት ነበሩና ከብዙ ዓመታት በኋላ ትዝታቸውን በቃለመጠይቅ ሲያካፍሉ፣

"በዚያን ወቅት የእኛ ፍላጎት የፓርላማ አባላት በደንብ እንዲሰሩ ወይ ዘመናዊ ሕግ እንዲያወጡ አልነበረም፡፡ እኛ የፈለግነው ህዝቡ መንግስት የሚያወጣውን ሕግ እንዲቀበልልን ነው፡፡ ይህንንም ተቀባይነት ለማግኘት የሚያመቸው መሣፍንቱ መጀመሪያ ተነጋግረውበት ከተቀበሉት ነው፡፡ /በሌላ አነጋገር/ እኛ የፈለግነው የኢትዮጵያን ሕዝብ በመሳፍንቱ አማካይነት ለማነጋገር ነው፡፡ ስለዚህ መሳፍንቱን ለአቅዳችንና ለዓላማችን መሳሪያ አደረግናቸው ማለት ይቻላል" ብለዋል፡፡

መሳፍንቱና መኳንንቱ የሕግ መወሰኛ ምክር ቤትና የሕግ መምሪያ ምክር ቤት አባል ሆነው እንዲሰሩ መደረጋቸው እንዳለ ሆኖ፣ ነገር ግን የሚሾሙት መሳፍንትና መኳንንት ብቻ እንዳልነበሩ በቀላሉ መረዳት እንችላለን፡፡ ንጉሡ ሕገ-መንግስቱ ባጎናፀፉቸው የመምረጥ መብት ተጠቅመው የምክርቤቶቹ ፕሬዝዳንትና ምክትል ፕሬዝዳንት እንዲሆኑ የመረጧቸው ከመሳፍንት ወገን ያልሆኑና ቀደም ካለው ጊዜ ጀምሮ ታማኝ ሆነው የመጡትን ነው፡፡ ለምሳሌ የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት ፕሬዝዳንትና ምክትል ፕሬዝደንት ሆነው የተሾሙት ቢትወደድ ወልደፃድቅ ጎሹና ብላቴን ጌታ ሣህሌ ፀዳሉ ነበሩ፡፡ ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ ይህን ጉዳይ፣ "እነዚህ ሹማምንት እንደነራስ ካሣ ኃይሉ፣ ራስ ኃይሉ ተክለሐይማኖትና፣ ራስ ስዩም መንገሻን የመሳሰሉ መሳፍንት እንዲዳኙ መደረጋቸው መሳፍንቱ ምን ያህል በንጉሠነገስቱ መዳፍ ስር እንደወደቁ ጉልህ ማስረጃ ነው" ይሉታል፡፡

በዚህ መልኩ ጥቅምት 23 ቀን 1924 ዓ.ም ምክር ቤቶች በይፋ ስራ ጀመሩ፡፡ፓርላማው ሰባት ቋሚ ኮሚቴዎችን አደራጅቶ መንቀሳቀስ



ጀመረ፡፡ ቋሚ ኮሚቴዎቹ በቅደም ተከተል የሕግ ስራ ኮሚቴ፣ የውጭ ጉደይ ቋሚ ኮሚቴ፣ የመከላከያ ኮሚቴ፣የገንዘብ ኮሚቴ፣የበጀት ኮሚቴ፣ የህዝብ እድገት ኮሚቴ፣እንዲሁም የኮሚቴዎችን አባላት የሚመርጥ አንድ መራጭ ኮሚቴ ተብለው ተዋቀሩ፡፡

ሰባት አባላት ያሉት የሕግ ስራ ኮሚቴ የሕግ ረቂቆች ለምክር ቤቱ ከመቅረባቸው አስቀድሞ የሕግ ቅርፅ ይዘው መቅረባቸውን የሚያረጋግጥ ተግባር ያከናውናል፡፡ የውጭ ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ የሚላኩለት ስራዎች ኢትዮጵያ የምታደርጋቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና የተባበሩት መንግስታት የስምምነት ግዴታዎች ናቸው፡፡
መከላከያን የሚመለከቱ ጉዳዮች የሚላኩለት የመከላከያ ኮሚቴ ነው፡፡የአገርን ኢኮኖሚ በማስፋፋት ረገድ ትልቁን ድርሻ የሚወጣው የገንዘብ ኮሚቴ ነው፡፡ የህዝብ እድገት ኮሚቴም ትምህርትን፣ ጤና ጥበቃን፣ እርሻን የሚመለከቱ ጉዳዮች ይቀርቡለታል፡፡መራጭ ኮሚቴው ደግሞ የቋሚ ኮሚቴ ዕጩዎችን በመምረጥ ለፓርላማው ያቀርባል፡፡ይህ የፓርላማ አሰራር እስከተሻሻለው ሕገ-መንግስት ድረስ ሲሰራበት ቆይቷል፡፡ሕገ-መንግስቱ የተሻሻለው በ1948 ዓ.ም ቢሆንም፣ በዚህ ጽሁፍ ዘመኑን ተከትለን ሄደን ከምናገኘው ከወዲሁ አጠቃለነው ማለፉ ይመረጣል፡፡

የተሻሻለው ሕገ-መንግስት የተሻለ የመምረጥ መብትን ለኅብረተሰቡ ሰጥቷል፡፡ በተሻሻለው ሕገ-መንግስት መሠረት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ 18 ዓመት ከሞላው የመምረጥ መብት ሲኖረው ለመመረጥ ደግሞ ከ21 ዓመት በላይ ሊሆን ይገባል፡፡ ማንበብና መፃፍ መቻል ግድ ነበር፡፡ የሚመረጡት አባላት የሕግ መምሪያ ምክር ቤት ይገባሉ፡፡ የሕግ መወሰኛ ምክር ቤቱ ግን አባላቱ እንደቀድሞው በንጉሠነገስቱ የሚመረጡ ናቸው፡፡

የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት ከንጉሱ በታች እና ከሕግ መምሪያ በላይ ሲሆን፣ ከንጉሡ በታች ሕግ የማፅደቅ ወይም ያለማፅደቅ ስልጣን ነበረው፡፡ በ1948ቱ ሕገ-መንግስትም ሆነ በ1923ቱ ንጉሡ ምክርቤቶችን መበተንና ምክር ቤቱ የሚያወጣቸውን ሕጎች መሻር የሚያስችላቸው አንቀጾች የተካተቱበት ነበር፡፡ የምክር ቤቱ ስልጣን የሚመነጨው ከንጉሠነገስቱ መሆኑም ግልፅ ነው፡፡ ቀደም ሲል እንዳየነውም ሕጎች የሚፀድቁት የሕግ መምሪያው ምክር ቤት መክሮበትና ሕግ መወሰኛው ምክር ቤት ወዶ ሲቀበለው ነው፡፡ ያም ሆኖ የመጨረሻው የመወሰን ስልጣን የንጉሠ ነገስቱ እንደሆነ ግልፅ ድንጋጌ አለ፡፡ የምክር ቤቶቹ አባላት ሚኒስትሮች የሚያቀርቡላቸውን ጉዳዮች እየተቀበሉ ይመክራሉ፡፡ ምክርቤቶቹ በሚኒስትሮች ምርጫ ውስጥ ግን ጣልቃ አይገቡም፡፡ በ1948ቱ ህዝቡ እንደራሴውን በቀጥታ መምረጥ መቻሉ ደግሞ አንድ





ወደ ኢትዮጵያ ይጓዝ የነበረው የጠላት ጦር።

በ1928 ዓ.ም ግን ከኤርትራ በመነሳት ይፋዊ ወረራውን ጀመረ፡፡ ወረራው ከሁለት አቅጣጫ ሆነና የምስራቁ የፋሽስት ጦር በጄኔራል ግራዚያኒ እየተመራ፣ የሰሜኑ ግንባር በጄኔራል ባዶሊዮ እየተመራ፤ "የአድዋው ሽንፈት እንዳይደገም" በሚል 100 ሺ ጥቁሮች የተካተቱበት 500 ሺ ወታደሮች፣ በመቶዎች የሚቆጠሩ አዋጊ ጄኔራሎች፣ በሰሜኑ ግንባር 300 የጦር አውሮፕላኖች፣ በምስራቁ ግንባር 100 የጦር አውሮፕላኖች በድምሩ 400 አውሮፕላኖች በርካታ ታንክና መትረየስ፤ መድፎች ... ወዘተ ታጥቀው ወረራውን ቀጠሉ፡፡ ኢትዮጵያም 8 አውሮፕላኖች ያውም ለጭነት እንጂ ለውጊያ የማያገለግሉ ነበሯትና እነሱን ይዛ፤ ቁጥሩ በብዙ ፀሐፍት ዘንድ ስምምነት ላይ ያልተደረሰበት ሠራዊትና /3 መቶ ሺ የሚደርስ/ 60 ሺ የድሮ ጠመንጃ ካለ በቂ ጥይት ...ፍፁም እንደማይመጣጠኑ መገንዘብ እንችላለን፣ ገጠመች፡፡ በመስከረም ወር አጋማሽ 1928 ዓ.ም የኢጣሊያ ጦር ከ40 ዓመት በፊት አፍሮ የተመለሰባትን አድዋን ያዘ፡፡ በዚሁ ጊዜም በምስራቅ በኩል ቀራሂ ተያዘች፡፡ ... እያለ ቀጠለ፡፡ በእንግሊዝና በፈረንሣይ ክህደት ያዘኑት ንጉሡ የትኛውም አቤቱታቸው ተቀባይነት አላገኘምና ወደ ማይጨው ለመዝመት ወሰኑ፡፡

መስከረም 22 ቀን 1928 ዓ.ም ክተት አወጁ፡፡ ወደ ሰሜን ገስግሰውም ከፍተኛ ውጊያ በተካሄደበት በማይጨው ጦርነት ተካፈሉ፡፡ "አርሊኮን" የሚባለውን የአየር መጣያ ተኳሽ ሆነው አውሮፕላን ለመጣል በመሞከር አገራዊ ግዴታቸውን ሊወጡ ጥረት አደረጉ፡፡





ጃንሆይ አርሊኮን የተባለውን የአየር መጣያ ደግነው

ከታህሳስ እስከ ጥር ወር ድረስ እልህ አስጨራሽ ትግል ተደረገ፡፡ በተለይ በሰሜኑ ግንባር ኢትዮጵያውያኑ ከመከላከል ወደማጥቃት ተሸገሩ፡፡ በዚህ ጊዜ ያለፈው ሽንፈት የመደገም አዝማሚያ እንደመታየት ሲል ነው ፋሽስት የመርዝ ጋዝ መጠቀም የጀመረው፡፡"ሙስታርድ" እና "ኤፕሪት" የተባሉ በመንግስታት ማህበር የተከለከሉ የመርዝ ጋዞች በአውሮፕላን ሲያዘንቡ የኢትዮጵያ ጦር በአሰቃቂ ሁኔታ ማለቅ ጀመረ፡፡በዚህ መሰሉ አደገኛ ጥቃትም ተዋጊ ወታደሮችን ብቻ ሳይሆን ንፁሐን ሴቶችን፣የቤትና የዱር እንስሶችን፣የምግብ ሰብሎችንና መኖሪያ ቤቶችን አነደዷቸው፡፡

የኢጣሊያ መንግስት ራሱ ብቻ ሳይሆን መላው አውሮፓዊ ቅኝ ገዥዎች በኢትዮጵያውያን ቢሸነፍ ያውም በድጋሚ እጅግ ሐፍረትና ስጋት ነበርና አሰቃቂውን የመርዝ ጋዝ ሲያዘንብ በቃል እንኳ ያወገዘው አባል አገር አልነበረም፡፡

በዚያ ጊዜ የሰራዊታቸውን ማለቅ የተረዱት ንጉሱ ጦሩ እንዲሸሸ አዘዙ፡፡ ሸሽተውም ወደ አደስ አበባ በመገስገስ ሚያዚያ 22 ቀን 1928 ዓ.ም ማለዳ ላይ አዲስ አበባ ደረሱ፡፡ አፄ ኃይለሥላሴ በማይጨው ጦርነት ድል ሆነው ወደ አዲስ አበባ እንደተመለሱ የመሳፍንትና የመኳንንት አስቸኳይ ስብሰባ በቤተ-መንግስት ተደረገ፡፡ በዚህ ስብሰባ ሁለት ዓይነት ኀሳቦች ቀርበው ተነጋገሩባቸው፡፡

የመጀመሪያው ኀሳብ ከብላታ ታከለ ወልደሐዋርያት የቀረበ ነው፡፡ እንደ ብላታ ታከለ አስተያየት የኢትዮጵያ መንግስት ዋና የጦር ሠፈርና የአስተዳደር ከተማ በፍጥነት ወደ ጎሬ መዛወር ያስፈልገዋል፡፡ ንጉሠነገስቱ የመሪነት ተግባራቸውን ለመቀጠል ወደ ጎሬ ያምሩና በየአውራጃው የአርበኝነት ውጊያ እንዲቀጥል ይደረግ፡፡ ጎሬ ከእንግሊዝ

ሲከላከሉና ሲያጠቁ ነበር ያሳለፉት፡፡ በ5 ዓመቱ የአርበኝነት ዘመን ተዘርዝረው የማያልቁ ውድ የኢትዮጵያ ጀግኖች በየግዛቱ መሽገው አገራቸውን ከወራሪው ፋሽስት ለመታደግ በቁርጠኝነት ተፋለሙ፡፡ በዚያን ጊዜ ሴት ወንድ፣ ሽማግሌ አሮጊት፣ ህፃናት ሳይቀሩ በየዘርፉ ለአርበኞች ያበረከቱት አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነበር፡፡

መረጃ በማቀበል፣ ስንቅ በመቋጠር፣ ዶሮና እንቁላል ለኢጣሊያ ወታደሮች እየሸጡ በሚያገኙት ገንዘብ መልሰው ከራሳቸው ጥይት ገዝተው ለወገኖቻቸው በመላክ በራሳቸው ጥይት ራሳቸው እንዲሞቱ አድርገዋል፡፡ በባንዳነት ለኢጣሊያ ወግነው ወገናቸውን የወጉ የመኖራቸውን ያህልም ባንዳ መስለው ለአገራቸው ነፃነት የታገሉ የውስጥ አርበኞች የተጫወቱት ሚና ቀላል አልነበረም፡፡ 5 ጥይት የተኮሰ ባንዳ "25 ተኮስኩ" ብሎ ተናግሮ ሃያውን ለወገኖቹ ይልክላቸዋል፡፡ እንዲህና እንዲያ እያደረጉ ድፍን 5 ዓመቱን እረፍት ነስተዋቸዋል፡፡

የኢጣሊያ ጀኔራሎች የኢትዮጵያውያኑን ጀግንነት መቋቋም ሲሳናቸው የትግል ስልታቸውን በመለወጥ እርስ በርስ ለማፋጀት በዘር፣ በጎሣ፣ በሃይማኖት ህዝቡን ከፋፍለው ኦሮሞውን "የአማራ ተገዥነት ይብቃህ... ነፃ ልናወጣህ ነው የመጣነው..." እያሉ ለሌላው ብሔርም ተመሣሣይ መልዕክታቸውን እያሰራጩ የአገሩን ሰርዶ በአገሩ በሬ ለማሳጨድ ያልፈነቀሉት ድንጋይ አልነበረም፡፡ ሆኖም እምብዛም ስሚ አላገኙም፡፡

ቀጥለው ደግሞ ሃይማኖተኛ የሆነውን ህዝብ በጳጳስ ለማስገዘት ፈለጉ፡፡ አቡነ ጴጥሮስን ህዝቡ ለኢጣሊያ እውቅና እንዲሰጥ መልዕክታቸውን እንዲያስተላልፉለት /እንዲገዝቱለት/ ፈለጉ፡፡ አቡነ ጴጥሮስ ግን በተቃራኒው "የግፈኛውን ወራሪ የኢጣሊያን ገዥነት የተቀበለ ኢትዮጵያዊ የተረገመ ይሁን፤ እንኳዋን ሰው ምድሪቱ የተረገመች ትሁን" ብለው ገዘቱ፡፡

በዚህ ጊዜ የኢትዮጵያ የበላይ ገዥ ተብሎ የተሾመው ጀኔራል ግራዚያኒ እልህ ይዞት በጳጳሱ ላይ ሞት ፈረደባቸውና በአደባባይ በ11 ጥይት ተበሳስተው እንዲገደሉ አደረገ፡፡ሐምሌ 22 ቀን 1928 ዓ.ም ይህን ግፍ ፈፀመ፡፡ህዝቡ በእልህ ትግሉን አቀጣጠለው፡፡እኒህን ጀግና ኢትዮጵያዊ ታሪክ በልዩ ሁኔታ ሲዘክራቸው ይኖራል፡፡ከነፃነት በኋላም ለእኒህ ጀግና ጳጳስ በተረሸኑበት ቦታ በመዘጋጃ ቤቱ ጀርባ የአቡነ ጴጥሮስ ሐውልት ቆሞላቸው ዛሬም ድረስ ታሪካቸውን እየዘከረ ይገኛል፡፡

የካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም ደግሞ በገነተ ልዑል ቤተ-መንግስት ግራዚያኒ የኢጣሊያው ንጉስ ቪክቶር ኢማኑኤል ወንድ ልጅ የመውለዱን ደስታ ለአዲስ አበባ ህዝብ ሊያበስር ስብሰባ ባደረገ ጊዜ ሞገስ አስገዶምና አብርሃ ደቦጭ የተባሉ ወጣቶች በአዳራሹ ውስጥ ቆሞ ንግግር



የሚያደርገውን ግራዚያኒን ቦንብ ወርውረው እሱን አቁስለው ሌሎች ጀኔራሎችን ገድለው አመለጡ፡፡ግራዚያኒ ባይሞትም በቁሙ ገድለውት ነበር የሸሹት፡፡የእነዚህን ሁለት ጀግኖች ፍፃሜ ከወዲሁ አይተን ለማለፍ ያህል፤ከዓለም ጀግኖች ታሪክ መፅሐፍ ውስጥ የተካተተውን አሟሟታቸውን ላስፍር፡፡

አብርሃ ደቦጭና ሞገስ አስገዶም ጥቃቱን ካደረሱ በኋላ ስምኦን በሚባለው በጓደኛቸው ታክሲ ከአዲስ አበባ ወደ ፍቼ ከተማ ነበር የሄዱት፡፡ ስምኦን እነሱን አድርሶ ተመለሰ፡፡ ሁለቱ ጀግኖች እስከ 1932 ዓ.ም ድረስ ከራስ አበበ አረጋይ ጎን ተሰልፈው በአርበኝነት ሲታገሉ ቆይተዋል፡፡ ፎቶግራፋቸው ተበትኖ ስለነበር አርበኞችን አስፈቅደው ወደ ሱዳን ለመሻገር ተነሱ፡፡ ተጉዘውም ቋራ ደረሱ፡፡ ምግብና ውሃ ለመፈለግ ወደ አንድ መንደር ሲጠጉ በጠላት እጅ ወደቁ፡፡ ወዲያው የስቅላት ፍርድ ተበየነባቸውና በመጀመሪያ ሞገስ ሲሰቀል ሲል አብርሃ "የወንድሜን ሞት አላይም፤ በመጀመሪያ እኔን ግደሉኝ" ብሎ ለስቅላት ቀረበ፡፡ ከዚያም "በግራዚያኒ ላይ አደጋ የጣልኩ እኔ ነኝ፡፡ ለሀገሬ በሰራሁት ሁሉ እኮራለሁ፡፡ አሁንም ለሀገሬ ስሞት ደስ ይለኛል" ብሎ ሲናገር አዛዡ ንዴቱን መቆጣጠር አቅቶት በስቅላት እንዲገደል የተወሰነውን ሽጉጡን አውጥቶ በፍጥነት ገደለው፡፡ ሞገስም በቁጣ "አንተ ፋሽስት አሁን የገደልከው የዚህ አገር ውድ ልጅና ደም መላሽ ነበር፡፡ ብዙ አብርሐሞች በዚህ ጀምበር በቅለው ያድራሉ፤ አንተም እተላ ከሆነው ታሪክህ ጋር ወደ መሬት ትወርዳለህ" ብሎ ሲናገር እሱንም በሽጉጥ ገደለው፡፡ ሬሳቸው ቋራ ላይ እንደነገሩ ተቀብሮ ነበር፡፡ በኋላ ግን ነፃነት ሲመለስ በአፄ ኃይለስላሴ ትዕዛዝ አፅማቸው መጥቶ በክብር ከአርበኞች የመቃብር ቦታ በአዲስ አበባ በስላሴ ቤተ-ክርስቲያን አረፉ፡፡ (መቼም ኤርትራዊነታቸው ኢትዮጵያዊነታቸውን አይቀብረውም!)

ግራዚያኒ በዚህ ብስጭት 30 ሺ የሚሆኑ የአዲስ አበባ ነዋሪዎችን በመሣሪያ፣ በመጥረቢያ፣ በገጀራ አስጨፈጨፋቸው፡፡ እነ ሞገስ ወደሸሹበት ተብሎ ወደደብረሊባኖስ ገዳም የኢጣሊያ ወታደሮች ሄደው በገዳሙ ብቻ 358 ካህናትን ገደሉ፡፡ ይህንንም ግራዚያኒ ለኢጣሊያው ገዥ ለቢኖቶ ሞሶሎኒ እና ለንጉሡ ቪክቶር ኢማኑኤል በላከው የቴሌ ግራም መልዕክት ሲያረጋግጥ፤ በዚህ ቂም በቀል ሳቢያ ገና ብዙ ሺዎችን ሊያስፈጅ መዘጋጀቱንም አብሮ ገልጾ ነበር፡፡ በየካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም በመጥረቢያ ለተጨፈጨፉት ንፁሐን ዜጎች መታሰቢያ ይሆን ዘንድም ከነፃነት በኋላ ከየካቲት 12 ሆስፒታል ፊት ለፊት የሚገኘው የስድስት ኪሎው ሐውልት ተሰርቶላቸዋል፡፡

ግራዚያኒ መረር ያለ እርምጃውን በመቀጠል ተማርከው የተያዙትን ኢትዮጵያዊ ጀግኖች፤ የጥቁር አንበሳ አባላትን ጨምሮ

የእንግሊዝ ጦር ባለስልጣኖች በሁለት ዓመት የጥገኝነት አገዛዛቸው ወቅት "በኢትዮጵያ የእንግሊዝ ወታደራዊ ተልዕኮ" የሚባል ቡድን በማቋቋም የአገሪቱን የመከላከያ አቋም በዘመናዊ መልክ ለማደራጀት ተስማምተው እንቅስቃሴያቸውን ጀመሩ፡፡ በአገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ የበላይ ተቆጣጣሪ ሆኑ፡፡ የኢጣሊያ ጦር ይጠቀምባቸው የነበሩትን ልዩ ልዩ ማቴሪያሎች ከአገር አወጡ፡፡ በአንድ በኩል የንጉሡ የፖለቲካና የጦር አማካሪ ሆነው እየሰሩ፣ በሌላ በኩል በድብቅ ህዝቡን ማጋጨት፣ አርበኛውን ከስደተኛ፣ ስደተኛውን ከአርበኛ በዘዴ እያፋጩ ከውል ውጭ በሆነ መንገድ ኦጋዴንን በቁጥጥራቸው ስር አደረጉ፡፡

ኤርትራ ከ1881 ዓ.ም ጀምሮ በኢጣሊያ ስር ስለነበረችና አሁን እንግሊዞች ስላስለቀቋት ከሌሎች የአፍሪካ ቅኝ ግዛት አገሮች ጋር እጣዋ እስኪወሰን በሞግዚትነት መያዛቸው አግባብነት ቢኖረው እንኳ፣ ኦጋዴን ግን እስከ 1928 ዓ.ም ድረስ ተነጥሎ ስለማያውቅ እንግሊዞች በአዲሱ የኢጣሊያ ክለላ መሰረት አድርገው ወደ ቅኝ ግዛታቸው መቀላቀላቸው ሕገ-ወጥ ነበር፡፡

የእንግሊዝ ጦር ባለስልጣኖች በዚህ ሳይወሰኑ የኤርትራን ህዝብም በዘር፣ በሃይማኖት፣ በጎሳ እየከፋፈሉ ወደፊት ከእናት አገሩ ከኢትዮጵያ ጋር እንዳይቀላቀልና ለነፃነት እንዳይነሳ ያመቻቹት ነበር፡፡

ንጉሱ ኤርትራ ለኢትዮጵያ መሰጠት አለባት ብለው እየተከራከሩ፣ ጭራሽ ኦጋዴንን ሊነጥቋቸው በመሞከራቸው ሊታገሱት አልቻሉም፡፡ የእንግሊዝ አካሄድ መጥፎ አቅጣጫ እየያዘ ሲሄድ ሌላ ረዳት ፍለጋ ማማተር ነበረባቸው፡፡ የሁለት ዓመቱ ውል አልቆ በታህሳስ ወር 1936 ዓ.ም ሌላ ውል ሲፈራረሙ የኦጋዴንን ጉዳይ ቢያነሱትም እንግሊዞች መልቀቅ አልፈለጉም፡፡ ለ2 ዓመት የዘለቁት ውሎች በሁለተኛው ውል አማካኝነት ቢሻሩም የኦጋዴን ጉዳይ አልተመለሰም ነበር፡፡ በተረፈ የ1936ቱ ውል የባቡር መስመር ሐዲዱን ለኢትዮጵያ ያስመለሰ፣ የአምባሳደሩን የበላይነት ያስቀረ፣ ኢትዮጵያ ከየትኛውም አገር ጋር በነፃነት በአማካሪነትም ሆነ በቅጥረኝነት እንዲሁም በማናቸውም አይነት ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ቀጥታ ማድረግ የምትችል በአጠቃላይ ሙሉ ለሙሉ ለማለት በሚያስችል ሁኔታ ነፃነቷን የመለሰ ውል ነበር፡፡

ከዚህኛው ውል በኋላም ነው ንጉሡ ከሌሎች ኃያላን አገራት ጋር ጥብቅ ትስስር ለመፍጠር እንቅስቃሴ የጀመሩት፡፡ የኦጋዴን ጉዳይ ግን እስከ 1941 ዓ.ም ድረስ በጅጅጋ ማዕከልነት በእንግሊዞች እጅ ቆይቶ በ1941 ከፊሉን የኦጋዴን ድንበር ማለትም ከእንግሊዝ ሶማሌላንድ ጋር የሚዋሰነውን ሀውድን ቆርሳ ወደራሷ ከቀላቀለች በኋላ "የተከለለ ድንበር" ብላ ወስና ከፊሉን ለኢትዮጵያ መለሰች፡፡ በመጨረሻ በ1947 ዓ.ም ደግሞ እሱንም መልሳ ለቃ ወጣች፡፡



ይህም የኢትዮጵያ መንግስት ሙግትና ክርክር ብቻውን ያስገኘው ውጤት ሳይሆን ዓለም አቀፍ ይዘት ያለውን የኢምፔሪያሊዝም መፍረክረክን ተከትሎ የመጣ ነው፡፡ የኦጋዴን ወደ ኢትዮጵያ መመለስ ደግሞ ከሶማሊያዎች ነፃ መውጣት በኋላ የይገባናል ክርክር አስነስቶ ነበር፡፡ በመጨረሻ ግን የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ከተቋቋመ በኋላ በቅኝ ገዥዎች የተከለሉ ድንበሮች ሁሉ በዚያው መፅናት አለባቸው የሚል የውሳኔ ስምምነት ላይ ተደርሶ ኦጋዴን በትክክለኛ ታሪኩ የኢትዮጵያ ሆኖ እንዲቀጥል ሆኗል፡፡

የእንግሊዝ የበላይነት ቆይታ ምንም እንኳ የንጉሠ ነገስቱን መንግስት አስተዳደር ባይጋፋም ሴራ የተቀላቀለበት ችሮታ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ የኢትዮጵያ መንግስት በእነዚያ ጊዜያቶች የድንበር ይገባኛል ጥያቄውንም፣ የአዲስ የአስተዳደር ስራውንም፣ ሕጎችን በማውጣት፣ አዋጆችንና ድንጋጌዎችን በማፅደቅ ... ወዘተ ተጠምዶ ነው የቆየው፡፡

ምንም እንኳ የኦጋዴን ጉዳይ የኃያላን አገራቱን ትኩረት መሳብ ቢሳነውና እንግሊዝ በራሷ የውስጥ ፖለቲካ ችግር ለመልቀቅ ብትገደድም የኤርትራ ጉዳይ ግን በደንብ መገላበጥ ነበረበት፡፡ ንጉሡም ለኤርትራና ለኦጋዴን መመለስ የጣሩት ጥረት እጅግ ከፍተኛና የሚያስደንቃቸው ነው፡፡ ነገር ግን ይህች ዓለም "የኔ" ተብላ የምትወሰንና እንደልብ የሚያደርጓት የየግል ግዛት ያላቸው መንግስታት የተካፈሏት ፈለክ ትሁን እንጂ የአንድ ወይም የጥቂት ልእለ ኃያላን ብቻ ንብረት ናት፡፡ ጥንትም ዛሬም ያው ነው፡፡ የዘመንና የአገዛዙ አይነት ብቻ ይለያያል፡፡

እንግሊዝ በኦጋዴን ተክላው የሄደችው እሾሃማ ችግኝ በ1950ዎቹና በ1960ዎቹ የሱማሊያንና የኢትዮጵያን ልጆች እያዋጋ አፋጅቷቸዋል፡፡ አውሮፓውያን ኢምፔሪያሊስቶች ምንም እንኳ ሳይወዱ በግድ አፍሪካን ለቀው ቢሄዱም፤ ለዘመናት ስንናጭ እንድንኖር የሚያደርገውን የቤት ስራቸውን አጠናቀው ነው የሄዱት፡፡ ፈፅሞ የአፍሪካን ሰላም አይፈልጉም ነበር፡፡ አሁንም ወደፊትም አይፈልጉም፡፡

የተባበሩት መንግስታት ድርጅትም ቢሆን የጥቂት ኃያላን ፍላጎት ማሳኪያ እንጂ ሐቀኛ ድርጅት አለመሆኑ ጥንትም ዛሬም ግልፅ ነው፡፡ ኃያላኑ እርስ በርስ የተጣሉ ቢመስለንም፣ አፍሪካን በማተራመስ ረገድ አቋማቸው አንድ ነው፡፡ ልዩነቱ አንድ ኃያል አገር ስትከሰት ሰፊውን የአፍሪካ ክፍል የመቆጣጠር እድሏ መስፋቱ ብቻ ነው፡፡ አንድ ግልፅ ነገር አለ፡፡ ይረዱናል፡፡ መልሰውም ያርዱናል፡፡ እንግሊዝ ለቃ የወጣችው በተባበሩት መንግስታት ውሣኔ ይሁን እንጂ ለአሜሪካ መልቀቅ ስለነበረባት ነው፡፡ አሜሪካ በአልበርት አንስታይን ምክር የአቶሚክ ቦምብ ባለቤት ሆና በጃፓን ሁለት አውራጃዎች የፈፀመችው ከፍተኛ ግፍ የበላይነቷን አረጋግጧል፡፡ እግረመንገዷንም በአለም ላይ የምትከተለውን

ፖሊሲ ማመላከቷ ነው፡፡ ጉዳዩ "እኔ ነኝ የማዋጣችሁ" አይነት ነው፡፡ እንዳለችውም ከ2ኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ብቸኛዋ የሶቪየት ኅብረት ተፎካካሪ ሆናለች፡፡

የኤርትራ ጉዳይ

2ኛው የዓለም ጦርነት በኃያላኑ ትብብር በአሜሪካ፣ በሶቭየት፣ በፈረንሣይና በእንግሊዝ የበላይነት ከተጠናቀቀ በኋላ የኤርትራ ጉዳይ ውይይት እየተካሄደበት ነበርና የእንግሊዝ ሞግዚትነት ቀጥሏል፡፡

ኤርትራን ከ1881 ዓ.ም ጀምሮ ኢጣሊያ በጉልበት ወስዳ እስከ 1933 ዓ.ም ድረስ ስትገዛት ኖራለች፡፡ የኢጣሊያ ጦር ከምስራቅ አፍሪካ እንዲለቅ ከተገደደ በኋላም የእንግሊዝ ጦር ባለስልጣኖች ይዘው ቀደም ሲል እንዳየነው የኤርትራን ህዝብ የመከፋፈል አላማቸውን ገፍተውበታል፡፡

ከኢጣሊያ መልቀቅ ጀምሮ በኤርትራ የተለያዩ ቡድኖች ተፈጠሩ፡፡ በመጀመሪያ "ማኅበረ አገር ፍቅሮ" በሚል የአንድነት ቡድን ተመሠረተ፡፡ ከዚህ ቡድን ተቃራኒ የሆኑ ሌሎች ቡድኖችም ተመሰረቱና የ‹‹ነፃነት››እና የ‹‹አንድነት›› ቡድኖች ሆኑ፡፡ የአንድነት ቡድኑ ሰፊ ህዝባዊ መሠረት የነበረውና ከኢትዮጵያ መንግስትም ድጋፍ ይደረግለት የነበረ ሲሆን፣ ዓላማው ኤርትራን ከእናት አገሯ ከኢትዮጵያ ጋር ማዋሐድ የሚል ነው፡፡

የነፃነት ቡድኑ ድግሞ በእንግሊዞች አማካኝነት ተወልዶ ከሁለት ተከፈለና አንዱ የሙስሊም ሊግ /ራቢጣ አል ዓረቢያ/ በሚል ስያሜው መሠረቱን በቆላማው የኤርትራ ክፍል አድርጎ ሲንቀሳቀስ፣ ሌላው ሊበራል ፕሮግሬሲቭ ፓርቲ በሚል ስያሜው መሠረቱን በደጋማው የኤርትራ ክፍል አድርጎ መንቀሳቀስ ጀመረ፡፡

የሙስሊም ሊጉ /ራቢጣ አል ዓረቢያ/ ዓላማው በምዕራባዊ ቆላ የሚኖረው ህዝብ በቋንቋ በሐይማኖትና በባህል ከሱዳን ጋር ስለሚመሳሰል ከኤርትራ ተገንጥሎ ከሱዳን ጋር ይዋሐድ የሚል ነው፡፡

ሊበራል ፕሮግሬሲቭ ፓርቲ ደግሞ ዓላማው ከሙስሊም ሊጉ ሳይቃረን ደጋማውና ትግርኛ ተናጋሪውን ክፍል ከመረብ ማዶ ከሚገኘው ወገኑ ጋር አዋህዶ ነፃ መንግስት ለማቋቋም ነበር፡፡ የኤርትራ ትግርኛ ተናጋሪዎችን ከትግራይ ጋር ቀላቅሎ ነፃ አገር ለመመስረት መሆኑ ነው፡፡ ሌላው ደግሞ የኢጣሊያ ክልሶችና የቀድሞው ወታደሮች እንዲሁም የኢጣሊያ ወዳጆች ተደራጅተው የመሠረቱት "አፍቃሬ ኢጣሊያ ፓርቲ" ሲሆን፣ ዓላማው በነፃነት ሽፋን የኢጣሊያ የበላይነት (በሞግዚትነት) እንዲቀጥል የሚፈልግ ነው፡፡ ከፍተኛ የገንዘብ ድጋፍም ከኢጣሊያ በኩል ይደረግለት ነበር፡፡ ሙስሊም ሊጉም በዓረቦች ይደገፍ ነበር፡፡ እንግሊዝ የወለደችው ፕሮግሬሲቭ ፓርቲ ደግሞ በእንግሊዝ ይደገፍ ነበር፡፡



እንደሚታወቀው እንግሊዝ በወቅቱ ሱዳን ግዛትዋ ስለነበረች የኤርትራን ግዛት ከሱዳን አጣምራ መያዝ ትፈልግ ነበርና ፕሮግሬሲቩን ፈጥራ ማሳደግ ነበረባት፡፡ ሙስሊም ሊጉንም ቢሆን ዓላማው ከተሳካ በተዘዋሪ የእንግሊዝ አላማ መሳካቱ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ሙስሊም ሊጉና ፕሮግሬሲቩ የተለያዩ ይምሰሉ እንጂ በዓላማም በውልደትም አንድ ነበሩ፡፡ ነገር ግን ሁሉም ቅድመ ዝግጅቷ ሳይሳካ ቀረና የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ከተለያዩ ገለልተኛ አገሮች የተውጣጡ አባላት ያሉበት ኮሚሽን አቋቁሞ ወደ ኤርትራ ሄደው የህዝቡን ትክክለኛ ፍላጎት እንዲያጠኑ አዘዘ፡፡ ኮሚሽኑ የታዘበው ከፍተኛ የአንድነት ስሜት ነበረና ይሄንኑ ሪፖርት አደረገ፡፡ ሪፖርቱን መሰረት በማድረግም ትዋሐድ፣ ነፃ ትውጣ፣ በፌዴሬሽን ትተሳሰር የሚሉ ተወካይ አገሮች ነበሩ፡፡

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በፌዴሬሽን ትተሳሰር የሚለውን ውሣኔ ተቀበለው፡፡ ይህም ሙሉ በሙሉ የአሜሪካ ይሁንታ የነበረ ሲሆን፣ ኃያሏ አሜሪካ በኤርትራ የሚገኘው "ሬዲዮ ማሪና" የተባለው የመገናኛ ጣቢያዋ ደህንነትን መሠረት ያደረገ ነውና ለጊዜው ኢትዮጵያ እንደምትሻላት መርጣ የፌዴሬሽን ፎርሙላውን ደገፈች፡፡

በዚህ መሠረት የእንግሊዝ የሞግዚትነት አስተዳደር እክትሞ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን እንድትተዳደር በመስከረም ወር 1945 ውሣኔው ፀደቀ፡፡ የአንድነት ቡድኑ ፓርቲ መሪ የነበሩት ተድላ ባይሩ በፌዴራሉ መንግስት ስር የኤርትራ ፕሬዝዳንት፣ የሙስሊም ሊጉ ፓርቲ መሪ ሼህ ዓሊ መሐመድ ሙሴ ራዳይን ደግሞ የኤርትራ ምክትል ፕሬዝዳንት ሆነው ተሾሙ፡፡

ሁለቱ አገሮች ለተወሰኑ አመታት በፌዴሬሽን ሲተዳደሩ ቆይተው ከ5 ዓመት በኋላ በ1950 ዓ.ም በፌዴሬሽኑ ምክር ቤት ውሣኔ ውህደት ተፈጥሮ ኤርትራ የኢትዮጵያ አንደኛዋ ክፍለሀገር /13ኛዋ/ ሆነች፡፡ የኤርትራ ፕሬዝዳንት እና ምክትል ፕሬዝዳንት የነበሩትና ግብራበሮቻቸው ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር ስትዋሃድና ፌዴሬሽኑ ሲፈርስ የኤርትራ ክፍለሃገር አስተዳዳሪነት ይሰጠናል ብለው ተስፋ አድርገው ነበር፡፡ የኢትዮጵያ መንግስት ራስ አንዳርጋቸውን ስለሾመባቸው አኩርፈው አገር ጥለው ወደ ግብፅ ተሰደዱ፡፡

በዚህ ጊዜ በመካከለኛው ምስራቅ በስደት የሚኖሩ ሙስሊም ኤርትራውያን ኤርትራ በትጥቅ ትግል ነፃ መውጣት አለባት ብለው በመነሳት የመጀመሪያውን ድርጅት የኤርትራ ነፃነት ግንባር በሚል ስያሜ አቋቋሙ፡፡ ግንባሩ የሙስሊም ኤርትራውያን እንደሆነና ትግሉም የዓረብ ህዝቦች እንደሆነ አድርገው በመነሳታቸው የዓረብ አገራት ለግንባሩ ልዩ ድጋፍ እንዲያደርጉ አነሳሱዋቸው፡፡ የዓረብ አገራት መሪዎችም ድጋፋቸውን ሰጡ፡፡ ሶሪያና ኢራቅ የግንባሩ የረጅም ጊዜ ዋና ደጋፊዎች

ዘመናዊ መሣሪያ ለሻዕቢያ አሜሪካ እንደምትለግስ ቃል ስለገባች እሱው ተግባራዊ ተደረገ፡፡ ይህ የኢትዮጵያ መንግስት ሳያውቅ በሚስጥር ሲከናወንም፤ ከኢትዮጵያ ጋር ወዳጅ የሆኑት አሜሪካውያን በይፋ ጀንሆይን "ከሻዕቢያ ጋር ጉዳዩን በድርድር መፍታት መሞከሩ የተሻለ እንደሚሆን በመምከርና፤ ከዚያ በፊት ግን ዓረባዊ ስሜት ያለውን ጀብሐን እራሱ ሻዕቢያ እንዲያጠፋው እርዳታዎን ለሻዕቢያ ቢያደርጉ የተሻለ ነው" እያሉ በወዳጅነት ያግባቡ ነበር፡፡

እናም ሻዕቢያ በጀብሐ ላይ ጦርነት ከፍቶ ሁለቱ ሲፋለሙ ከ1964 - 1966 ዓ.ም ድረስ የኢትዮጵያ መንግስት ትንፋሽ ማግኘት ችሎ ቆይቶ ነበር፡፡ የሻዕቢያና የጀብሐ ጦርነት ለዓመታት እንደቀጠለ ቆይቶ ስለነበር በደርግ ጊዜም አልተጠናቀቀም፡፡ በመጨረሻ በሻዕቢያ የበላይነት ተጠናቆ በ1970ዎቹ የመጀመሪያ ዓመታት ጀብሐ ከትጥቅ ትግሉ ጎራ እስከመጨረሻው ተሰናበተ፡፡ አሜሪካም እፎይ አለች፡፡ ከደርግ ዘመን በፊትና በኋላ ሻዕቢያ ቀላልና ከባድ መሣሪያዎች ከምርኮና ከደጋፊዎቹ ከአሜሪካውያን በብዛት አሰባሰበ፡፡
ኤርትራዊ የሆነ ወጣት በውዴታ ግዴታ ለትጥቅ ትግሉ ከጎኑ እንዲሰለፍ በማድረግ የሰው ኃይሉን አሳደገ፡፡ሠራዊቱም ለአመራርና ለቁጥጥር እንዲመች በክፍለ ጦር አደራጅቶ ስለቱንም ለውጦ ወደ መደበኛ /Conventional/ ስልት ተሸጋገረ፡፡

በዚህ መሰሉ አካሄድ የተጀመረው ትግል ከሌሎች የኢትዮጵያ የሽምቅ ተዋጊዎች ጋር የተቀናጀ እንቅስቃሴ ጋር ተዳምረው የደርግን ስርዓት እስከመጣል የደረሱ ሲሆን፤ ትግሉ ከንጉሡ የግዛት ዘመን መገባደጃ ጊዜ አንስቶ የተጀመረ ነበር፡፡ ከዚያም ከደርግ ውድቀት በኋላ ኤርትራ በ1984 ዓ.ም ተገነጠለች፡፡ ይህ ሁሉ ፍልስልሱ የወጣ ነገር የተከፈተው በእነዚያው በኃያላኑ ሸር ጉድ ነው፡፡ ኢሳያስ አፈወርቂ ዛሬ ላይ ሆኖ "እኔን የወለደኝ ሲ.አይ.ኤ ነው" እያለ ከተጣሉ በኋላ አሜሪካ ላይ ይፎትታል፡፡

ያ ሴራቸውም ዛሬም ድረስ ወንድማማች ህዝቦችን እያፋጀ ይገኛል፡፡ ምንትሴ ፓርቲ ቅብጥርሴ ፓርቲ ... ቢባል ያው ዞሮ ዞሮ ወላጆቹ ባዕዳን ናቸው፡፡ መውለድ ብቻ ሳይሆን የረቀቀ ጡጦ እያጠቡ ያሳድጋሉ፡፡ አሳድገው "ጧሪ" ያደርጓቸዋል፡፡መሣሪያ እየገዙ የራሳቸውን ወገን በመፍጀትና በማስፈጀት ያሳደጓቸውን ወላጆች ውለታ ይመልሳሉ፡፡

ጃንሆይ "ጀብሃን አጥፉልኝ" ብለው ለኢሳያስ እርዳታ ሰጥተዋል የሚለውን በይፋ ሲገልፁ የኖሩት ባዕዳኑ፤ ለረጅም ዓመት ራሳቸው ሻዕቢያን እንደረዱና እንደወለዱት ግን ትንፍሽ ብለው አያውቁም፡፡ አዎ ጃንሆይ ሰጥተዋል፡፡ ነገር ግን ጀብሐ ሙሉ ለሙሉ ሙስሊም ባይሆንም የዓረብነት ስሜቱን ፈርተው አሜሪካኖች አካሄዱን ስላልወደዱት እንዲጠፋ



ይፈልጋሉና ሻዕቢያን ለመርዳት በስውር መሳተፋቸውን የሸሸጉት እንሶ፤ ጃንሆይን መገፋፋታቸውንም ረስተው በስተመጨረሻ "ጃንሆይ ሻዕቢያን አምነው ባይረዱ ኖሮ የተሻለ ይሆን ነበር" እያሉ የዛሬውን መገንጠል እያነሱ የቱሰማቸውን ሲገልፁ "ሁለቱንም ደርበው መምታት ነበረባቸው" ብለው ይሳለቃሉ፡፡ እነሱ እንዲህ ናቸው፡፡

ያኔ መሳፍንቱን መሣሪያ እየሰጡ በእነአፄ ቴዎድሮስ ዘመን ያፋጁ እንደነበር ሁሉ አሁንም፤ ምናልባትም ወደፊት ያፋጁናል፡፡

የኤርትራ ጉዳይ ተጀምሮ እስኪጨረስ የነበረው ሂደት በአጭሩ ያየነውን ሲመስል፤ በቁጥር አንዱ መፅሐፍ እንዳየነው በአፄ ዮሐንስ 4ኛ ጊዜ እንግሊዝና ጣሊያን አፄ ዮሐንስን አታለው በ1881 ዓ.ም የነጠቋት ባህረ ነጋሽ /ኤርትራ/ ከ64 ዓመታት በኋላ ከኢጣሊያ አገዛዝ ነፃ ወጥታ፤ በጃንሆይ ልዩ የዲፕሎማሲ ጥረት ወደ እናት አገሯ ተቀላቅላ 40 ዓመታት እንዳሳለፈች በደርግ ውድቀት ማግስት ራሷን የቻለች አገር ሆነች፡፡

መስከረም 1 ቀን 1952 ዓ.ም ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር የተዋሃደችበት 7ኛ ዓመት ክብረ በዓል በታላቁ ቤተ-መንግስት በተከበረ ጊዜ ልዩ ልዩ ሰዎች በጃንሆይ ፊት ንግግር አድርገው ነበር፡፡ ከእነዚህም ውስጥ አንዱ ተናጋሪ ክቡር አባ ጉግሣ ግደይ ነበሩ፡፡ አባ ጉግሣ ግደይ የኤርትራን ጉዳይ በሚመለከት ያደረጉት ንግግር እንዲህ ይነበባል፡፡

"... ኤርትራ በግርማዊነትዎ ብርቱ ድካምና ትግል ከባዕድ አገዛዝ ነፃ ከወጣች 7 ዓመት ጨርሰን 8ኛውን ዓመት መጀመራችን ነው፡፡ ግርማዊነትዎ ዘወትር የማይደክም ሀሊና በፈጣሪው ተማምኖ የጀመረውን እፍፃሜው ሳያደርስ በማይተው ሰፊ በሆነ ልቦናዎ ታግሰው ኤርትራን ከእናት አገሯ ከኢትዮጵያ ጋር አቀላቀሏት፡፡ ኤርትራ በር ናት፡፡ የኢትዮጵያ ጉሮሮ ናት፡፡ ህይወት የሚሰጥ ምግብ የሚያልፍባት ሊባል ይችላል፡፡ ሰው ጉሮሮው ከታነቀ ህይወት የለውም፡፡

ጃንሆይ፤እንደ ሰው በር የሌለው ትልቅ አዳራሽ ቢሰራ እብድ በተባለ ነበር፡፡ ባለፉት ዘመናት ኢትዮጵያም በር የሌላት ውብ ህንፃ መስላ ትታይ ነበር፡፡ ዳሩ ግን ግርማዊነትዎ ሌት ከቀን ያለ እረፍት ጥረው ተጣጥረው በሯን ከፍተው ባህሯን ተረክበው ይኸውና ሰው ሁሉ በነፃነት ወደ ውጭ አገር እንደፈቀደው ይመላለሳል፡፡ ቶሎ ብለውም የመርከብና የአየር ትምህርት ቤት አቋቁመው በሚገባ ሠርተዋል፡፡

ከብዙ ስራ በኋላ እረፍት ለህይወት አስፈላጊ ነው፡፡ ነገር ግን ግርማዊ ጃንሆይ ከዚህ ሁሉ ስራቸው በኋላ እረፍት ያደርጋሉ የሚል ሰው አይገኝም፡፡ ቢገኝም ሀሊና የሌለው ሰው ነው ተብሎ በተፈረደበት ነበር፡፡ ...." እያለ ይቀጥላል *(ፍሬ ከናፍር 1952)*

የኤርትራ ተወላጅ የሆኑት ሌላው የእለቱ ተናጋሪ የነበሩት ብላታ መሐመድ ኡስማን የነበሩ ሲሆን፣ ካደረጉት ረጅም ንግግር ውስጥ ጥቂት አንቀጾችን ጨምረን እንለፍ፡፡

"…. ግርማዊ ሆይ ኤርትራ ግዛትዎ በፋሽስቶች ተወርራ ከእናትዋ ኢትዮጵያ ተነጥላ፣ጥንታዊ ክብሯን እጥታ በጠላት አገዛዝ ስር ወድቃ የግርማዊነትዎ አርቆ ተመልካችነት የወጠኑት ተስፋ ባለማቋረጥ እነሆ ጽኑ በሆነ መሠረት ላይ የጣሉት ተስፋ ተፈፅሞ ኤርትራን ከጠላት መንጋጋ ፈልቅቀው ነፃነቷን አልብሰው መታየቷ ግርማዊነትዎ ከፈፀሟቸው እጅግ ሰፊና ታላላቅ ከሆኑት ታሪካዊ የድካም ፍሬዎች አንዱን ምዕራፍ ይዞ የሚገኘው የኤርትራ ከእናትዋ ከኢትዮጵያ ጋር መዋሃድ ነው፡፡

ግርማዊ ሆይ፡- እኛ ኤርትራውያን ህዝቦችዎን ከጠላት አገዛዝ ነፃ ለማውጣት ልዑል እግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ በዘመናችን ግርማዊነትዎን ስለሰጠን ከሙሉ ጤንነት ጋር እድሜን እንዲሰጥልን ፈጣሪን ከመለመን በቀር ግርማዊነትዎ ለእኛ ለህዝቦችዎ የፈፀሟቸውን ታሪካዊ ስራዎች ይህን ያህላል ወይም ይህን ይመስላል ብሎ ለመተንተን ችሎታዬ ስለማይፈቅድልኝ ንግግሬን ባጭሩ እቆማለሁ፡፡" *(ዝኒ ከማሁ)*

## ጃንሆይና አዲሱ የመንግስት አወቃቀር

አፄ ኃይለስላሴ ከስደት ከተመለሱበት ከሚያዚያ 27 ቀን 1933 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1966 ዓ.ም ያለ እረፍት ይችን አገር ለመገንባት በተቻላቸው ሁሉ ጥረዋል፡፡ ከስደት እንደተመለሱና ኢትዮጵያም በእንግሊዞች የበላይነት ከነበረችበት ጊዜ ጀምሮ በውስጥ አስተዳደራቸው ጣልቃ ስላልገባች ሕጎችን ሲያወጡ፣ አዋጆችን ሲያውጁ፣ ድንጋጌዎችን ሲደነግጉ … ነው ያሳለፉት፡፡



ነፃነት በተመለሰ ማግስት የአገሪቱ ታላላቅ ሰዎች በሦስት ተከፈሉ፡፡ ስደተኛ፣ አርበኛ፣ ባንዳ በሚል፡፡ ባንዶችን በተመለከተ ወንጀላቸውን የሚያጣራ ልዩ ፍርድ ቤት እንዲቋቋም ተደረገ፡፡ በስደተኞችና በአርበኞች መካከል ግን ከረር ያለ ውዝግብ ተፈጠረ፡፡ በዚህ ላይ አንዱ የአንዱን ስም በከንቱ እያነሳ መወንጀል፣ የግል ቂም በቀልን



ለመወጣት በሐሰት ስም ማጥፋት፣ ሹመት ለማግኘት ያልነበሩትን "ነበርን" ማለትና የመሳሰሉት ጉዳዮች ለፍርድ የማይመች ሁኔታን ፈጠሩ፡፡ ንጉሡ ስደተኞችን ማስከፋት አልፈለጉም፣ ራሳቸውም ስደተኛ ናቸውና፡፡ አርበኞችን ማግለል አይችሉም፣ ከሃዲ መባልን ይፈራሉና፡፡ ባንዶችንም በሙሉ ማጥፋት አይችሉም፣ አገር ምድሩ ባንዳ ነበርና፡፡

በዚህ ውዝግብ አረበኞች ተሸነፉ፡፡ ስደተኞች ትልልቁን ስልጣን ያዙ፡፡ እዚህ ላይ ፍትሐዊ የስልጣን ክፍፍል አለመደረጉ ብዙዎችን አሳዝኗል፡፡ ለተሿሚዎችም ሰፋፊ መሬት ተሰጣቸው፡፡ ንጉሡ ከስደት መልስ የመጀመሪያ ስራቸው ያደረጉት የሚኒስትሮች ምክር ቤት አዲስ ሹመትን ማፅደቅ ነበር፡፡ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ማለትም ከ1933 ዓ.ም በኋላ ባሉት ተከታታይ ዓመታት አዳዲስ ሕግና ደንቦች እየቆሙ፣ የነበሩት እየተሻሻሉ አዲስ አስተዳደራዊ መዋቅር ለመዘርጋት ተቻለ፡፡

ለምሳሌ በ1934ቱ የአገር ግዛት ደንብ መሠረት ኢትዮጵያን በ12 የሸዋ፣ የአርሲ፣ የሐረርጌ፣ የሲዳሞ፣ የጋሞጎፋ፣ የከፋ፣ የኢሊባቡር፣ የወለጋ፣ የጎጃም፣ የበጌምድር፣ የወሎ፣ የትግራይ ተብለው ተከፈሉ፡፡ "የእውራጃ ግዛት" ተብለው ተከፍለው የነበረ ቢሆንም በኋላ በ1938 ጠቅላይ ግዛት ተሰኙና ለግብር አሰባሰብ ምቹ እንዲሆኑ ተደረገ፡፡ ከዚያ በኋላ ነው ኤርትራ ስትጨመር 13፣ በሐረርጌ ግዛት ስር የነበረው ባሌ ራሱን ሲችል 14 የሆነው፡፡ አዲስ አበባም "እምብርት" ተብላ በ1940 የጠቅላይ ግዛት ማዕረግ ተሰጣት፡፡

በመጀመሪያው ሹመት የአገር ግዛት፣ የፅህፈት፣ የውጭ ጉዳይ፣ የትምህርት፣ የፍርድ፣ የንግድና ኢንዱስትሪ፣ የፖስታ የቴሌግራፍና የቴሌፎን ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች እንደ አዲስ ተዋቀሩ፡፡ በየጊዜውም እየበዙ፣ እየሰፉ ሄደዋል፡፡ በዚህ መሰሉ የማዕከልና የክፍለ አገር ክፍፍል መሠረት አዲሱ የአገር ግዛት ደንብ ተግባራዊ ሆነና ዋናውን ስልጣንና ሰፊውን ስራ የአገር ግዛት ሚኒስቴር የሚሰራው ሆነ፡፡



አዲስ የተቋቋመው የሚንስትሮች ካቢኔ

ከንጉሡ የሚመነጨውና በማዕከል ከሚኒስትሩ ቢሮ ወደታች የሚተላለፈውን የስራ አመራር በክፍለ አገር ደረጃ በተግባር ላይ የሚያውሉ የአገር ግዛት ሚኒስትር ባለሥልጣናትና ሠራተኞች፣ 1. ጠቅላይ አገር ገዢዎች፣ 2. ዳይሬክተሮች፣ 3. ፀሐፊዎች፣ 4. የአውራጃ፣ የወረዳና የምክትል ወረዳ ገዢዎች፣ 5. ዳኞች፣ 6. የኃይል አዛዦች፣ 7. ወታደሮች፣ የፖሊስና የፀጥታ ተወካዮች፣ 8. ሌላ አግባብ ያላቸው፣ ለምሳሌ የገንዘብና የጤና ሚኒስቴር መስሪያቤቶች ተወካዮች ናቸው።

የአገር ግዛት ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ሁለት ዋና ተግባራት አሉት። በአንድ በኩል በፀጥታ፣ በፖሊስ፣ በወህኒ ቤት፣ በጠረፍ ጥበቃና በኢሚግሬሽን ክፍሎች አማካኝነት የመንግስትን ደህንነትና ፀጥታ መጠበቅ፣ በሌላ በኩል በልዩ ልዩ የግብር፣ የቀረጥና የብድር ምንጮች የመንግስትን የገንዘብ ገቢ መጠን ማሳደግ ናቸው።

በአዲሱ መንግስታዊ አወቃቀር ላይ ታማኝ ባለሥልጣናትን እየሾሙ፣ የሁሉም የበላይ ንጉሠ ነገስቱ ሆነው ሚኒስትሮች እስከ ቀበሌ ድረስ ስራው በተዋረድ እንዲቀጥል እያደረጉ በደሞዝ መስራት ጀመሩ።እንደተባለውም የመንግስት ገቢ በግብር፣በቀረጥ፣በአገልግሎት ክፍያዎች ላይ ተመሰረተ።የገቢ አሰባሰብን በተመለከተም በተለያዩ ጊዜያት ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች እየወጡ ተግባራዊ ተደረጉ።

ከ1928 - 33 የነበረው የፋሽስቶች ቆይታ የንጉሡን ስልጣን ለማጠናከር ረድቷል። ለአብነት ያህል አንዳንድ ተቃዋሚዎቻቸው ተደምስሰዋል፣ የየመኳንንቱና መሳፍንቱ የግል ጦር ፈርሷል። ምንም እንኳን ጣሊያን ዝሙትን አስፋፍቶ፣ ባህልን በርዞ፣ አንድ ህዝቦችን ለራሱ



በሚያመች መንገድ በብሔር፣ በጎሳ፣ በሃይማኖት ለመከፋፈል የሸረበው ሴራ ባይዘነጋም፣ አንዳንድ የመሠረተ ልማት ዝርጋታዎቹን ለራሱ መጠቀሚያ ሲል ለማከናወን እንቅስቃሴ ጀምሯል፣ በሕግ ሸረው ያልሻሩትን የባሪያ ስርዓት ሙሉ ለሙሉ እንዲደመሰስ አስችሏል።በዚህም በገንዘብ ተቀጥረው የሚሰሩ ሰዎች በመበርከታቸው ጅምሩን ካፒታሊዝም አጠናክረው እንዲቀጥሉበት ረድቷል።

ከጦርነቱ በኋላ በእንግሊዝ ተፅዕኖ ስር ቢሆንም፣ በትምህርት፣ በአስተዳደር፣ በጦር፣ በፖሊስ፣ በፀጥታ፣ በቢሮክራሲ፣ በመንገድ፣ በመገናኛ በንግድና በገንዘብ ስራዎች፣ ድርጅቶችን መልሶ ለመገንባት በተወሰዱ እርምጃዎችና ኤርትራ ወደ እናት አገሯ የመቀላቀሏ ጉዳይ ተደማምረው የጃንሆይን ስልጣን የበለጠ ሲያጠነክሩ፣ በሌላ በኩልም የካፒታሊዝሙ ስርዓት የበለጠ እያደገ እንዲሄድ በር ከፍቷል።

ንጉሡ ከእንግሊዝ በኋላ በአሜሪካ፣ በስዊድን፣ በስዊዝ፣ በፈረንሣይ፣ በህንድ፣ በዩጎዝላቪያና በጃፓን አሰልጣኞችና አማካሪዎች፣ እንዲሁም እርዳታና እገዛ እየተደገፉ ሁሉንም ነገር በቁጥጥራቸው ስር ለማድረግ ችለዋል።

የጃንሆይ መንግስት ቢሮክራሲ ላዕላይ መዋቅሩ በተለያዩ በአዋጅ በሚቋቋሙ መስሪያ ቤቶች እየደረጀና ሕግ እየወጣለት ሲቀጥል፣ ታህታይ መዋቅሩ በልዩ ልዩ የገቢ አሰባሰብ መሰረቱን ጥሎ በየእለቱ እየዘመነና እየጠነከረ እንዲቀጥል ሆነ።

በወቅቱ የእንግሊዝ የበላይነት ጠንከር ያለ ነበርና የገንዘብና የወጪ ንግድ ቁጥጥሩ በእንግሊዞች የበላይነት ስር ነበር። ኢትዮጵያም የራሷ የሆነ የመገበያያ የወረቀት ገንዘብ አላሳተመችም። የእንግሊዝ የሁለት ዓመት ውል ካበቃ በኋላ ግን ነገሮች መልካቸውን ቀየሩ።

ከዚህ ቀደም የኢትዮጵያ የመገበያያ ገንዘቦች የማሪያ ትሬዛ፣ የኢጣሊያ ሊሬ፣ የእንግሊዝ ፓውንድ ስተርሊንግና የምስራቅ አፍሪካ ሽልንጎች ነበሩ። የገንዘብ ቦርዱም በእንግሊዝ ለንደን የነበረ ሲሆን፣ ከሦስቱ የቦርድ አባላት ሁለቱ እንግሊዛውያን አንዱ ኢትዮጵያዊ ናቸው።

በ1937 ዓ.ም ኢትዮጵያ የራሷን "የኢትዮጵያ ብር" አሳተመች። ስርዓት ያልነበረው የኢኮኖሚ መዋቅር ዘመናዊ እየሆነ ሄደ። እጅግ ዘመናዊ የተባለው የግብር አሰባሰብና አጠቃላይ የበጀት ስርዓቱ ተግባራዊ መሆን የጀመረው በ1953 ይሁን እንጂ ከነፃነት በኋላ ዘመናዊ የበጀት ስርዓትን ተግባራዊ ማድረግ ተችሏል።

ከነፃነት በኋላ ንጉሡ ኢትዮጵያዊ ምሁራንን ያስማሩት በአምባሳደርነት እየሾሙ ነበር። አገር ውስጥም በትልልቅ የመንግስት ተቋማት ታማኞቻቸው የሆኑ ምሁራንን መድበዋል። የእንግሊዞች የበላይነት በነበረ ጊዜ የውጭ ግንኙነቱን በአምባሳደሮቻቸው አማካይነት እንዲከናወን

አድርገዋል፡፡ በዚህም ጥረት ለምሳሌ በሰኔ ወር 1936 ዓ.ም ቁጥራቸው ከ250 በላይ የሆኑ አሜሪካውያን የልዩ ልዩ ሙያ ባለቤቶች በፍራንክሊን ሩዝቬልት መልካም ፈቃድ ወደ ኢትዮጵያ መጥተዋል፡፡ እነዚህም በሲቪሉ ዘርፍ እንጂ በፖለቲካው ጣልቃ ገብነት አልነበራቸውም፡፡ ኢንጅነሮች፣ የቴክኒክ አማካሪዎች፣ ነርሶች፣ ዶክተሮች፣ መምህራን፣ አናፂዎችና የልዩ ልዩ ዕደጥበብ ባለሙያዎች ነበሩ፡፡

ከ1937 በኋላ ግን ንጉሡ በነፃነት ከተለያዩ ስልጡን አገራት መንግስታት ጋር ግንኙነት በመመስረት አገር ግንባታውን በኢኮኖሚ፣ በጦር፣ በፖለቲካ፣ ወዘተ በስፋት ተያያዙት፡፡ ወደፊት እንደምናገኘው ሰፋ ያለው እገዛ ከአሜሪካ ነበር የተገኘው፡፡ የሚገርመው ግን ጃንሆይ አገር አይመርጡም፡፡ በአሜሪካ ድጋፍ ስራቸውን እየሰሩ በጎን ደግሞ የሶሻሊስቷን የዩጎዝላቪያን ድጋፍ ፈለጉ፡፡ አገኙም፡፡ ማርሻል ብሮዝ ቲቶ ምርጥ ወዳጅ ሆነው ተገኙ፡፡

የዩጎዝላቪያ እገዛ በኢኮኖሚው ዘርፍ ነበር፡፡ በተለይ በ1949 ዓ.ም የመጀመሪያውን ዘመናዊ የ5 ዓመት የበጀት እቅድ ነድፈው አበረከቱ፡፡ በዚህም ጥሩ የሚባል ኢኮኖሚያዊ እመርታ ታዬ፡፡ ከዚህ በኋላ በተከታታይ በወጡ የበጀት እቅዶች ዘርፈ ብዙ ስራዎች ተሰሩ፡፡ ይህም ከከፍተኛው የነዳጅ ማጣሪያ ፋብሪካ ጀምሮ እስከ አነስተኛ ተመሣሣይ የኢንዱስትሪ ዘርፍ፣ ከትልልቅ የትራክተር እርሻዎች እስከ አነስተኛው ተመሣሣይ የግብርና ዘርፍ፣ ከተራ አውራ ጎዳናዎች እስከ ዘመናዊ አየር መንገድ፣ በጦሩም ረገድ ከእግረኛ እስከ ታንከኛ፣ ከአየር ኃይል እስከ ባህር ኃይል በስልጡን አገሮች ድጋፍ ያቀላጥፉት ጀመር፡፡ እነዚህንም በአጭሩ በተከታታይ ለማየት እንሞክራለን፡፡

### የጃንሆይ መሬትና እርሻ

‹‹በ1930ዎቹ አጠቃላዩ የኢትዮጵያ የህዝብ ቁጥር የኤርትራን ህዝብ ሳይጨምር 20 ሚሊዮን ያህል ነበር፡፡ አጠቃላይ የኢትዮጵያ የመሬት ቆዳ ስፋት ደግሞ 120 ሚሊዮን ሔክታር ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥ 80 ሚሊዮን ሔክታሩ ለግብርና ስራ ተስማሚ እንደነበር ተገምቷል››(ፐ/ር ላጵሶ 1983)

በ ፕ/ሩ ጥናት እንደተመለከተው በዚያ ወቅት 57 ሚሊዮን ሔክታር በመንግስት ይዞታ ስር የነበረ ሲሆን፤ ከዚህም ውስጥ 40 ሚሊዮን ሔክታሩ የሚገኘው በደቡብ፣ 15 ሚሊዮን ሔክታሩ በመሐልና በምዕራብ፣ 2 ሚሊዮን ሔክታሩ በሰሜን ነበር፡፡ ከ1933 - 1966 ዓ.ም የኢትዮጵያ ዋና ዋና የመሬት ይዞታ አይነቶች ደግሞ 1ኛ. የመንግስት ይዞታ፣ 2ኛ. የታላላቅ ጉልተኛ መሳፍንቶች፣ መኳንንቶች፣ ባላባቶች፣ ነጋዴዎች፣ የቤተ-ክርስቲያን፣ የጦርና የፖሊስ ሹማምንቶች ይዞታ፣ 3ኛ. የእርሶ አደሮች



የማሳ ይዞታ ተብለው ይታወቃሉ፡፡ ንጉሡ በተለይ ከስደት መልስ ለታላላቅ ሹማምንት በልዩ ሁኔታ የመሬት ችሮታ አድርገዋል፡፡

ከ1933 ጀምሮ 5 ሚሊዮን ሔክታር መሬት ለሹማምንቶቻቸው በስጦታ በርስትነት ለግሰዋል፡፡ እነዚህም የመንግስት ባለሥልጣን እንደመሆናቸው መጠን በከተማ እየኖሩ በተቀጣሪ ያሳርሳሉ፡፡ በዚህም ላይ ግብር አይከፍሉም ነበር፡፡ በተጨማሪም የመሬት ስጦታው ወደ ደቡብ ነበር፡፡ 20 ከመቶ ያህሉ የቤተ-ክርስቲያን ርስት ነው፡፡ ቤተ-ክርስቲያንም ለመንግስት ግብር መክፈል አታውቅም፡፡ አልለመደችም፡፡

ቀደም ባለው ጊዜ በኢትዮጵያ ለቤተ-መንግስት፣ ለቤተ-ክርስቲያን፣ ለጦርና ለጉልተኛ ባለሥልጣኖች የገባሩ አገልግሎት የምግብ ግብር፣ የምርት ስፍር፣ የአስራት መዋጮ እየተባለ በአይነት ነበር የሚገበረው፡፡ በኃይለስላሴ ጊዜ ግን በገንዘብ እንዲለወጥ ሆኗል፡፡ ሙሉ ለሙሉ የነበረ ባይሆንም፡፡

ጃንሆይ "የ1923ቱን ሕገ-መንግስት መሠረት በማድረግ የመንግስት ገቢ በገንዘብ ግብር እንዲሆን አውጀዋል፡፡ በአዋጁም መሠረት ከ1926 - 1927 ዓ.ም ድረስ ከአገራቱ መኳንንት፣ ሻለቃና ባለማደሪያ ሹማምንቶች፣ ከከተማ ነዋሪዎችና ከገጠር ገባሮች በአንድነት ለመንግስት የገንዘብ ግብር 2.5 ሚሊዮን ብር ገቢ ተሰብስቦ እንደነበር" የፕሮፌሰሩ ጥናት ያመለክታል፡፡

ንጉሡ በ1934 በታወጀው የመሬት ግብር አዋጅ መሠረት ከወረራው በፊት በመሬት ላይ ተጥሎ የነበረው ግብር ህዝቡ በጦርነቱ ስለተጎዳ በሚል በግማሽ ቀነሱት፡፡ በ1927 በአንድ ጋሻ መሬት 30 ብር ይከፈል የነበረውን 15 ብር እንዲሆን ተደርጎ ነበር፡፡ በአዲሱ አዋጅ መሠረትም አንድ ወጥ ብሔራዊ የመሬት ግብር ሕግ ሲደነገግ ከአፈሩ ልማት አኳያ "ለም"፣ "ለምጠፍ" እና "ጠፍ" ተብሎ በሦስት ተመደበ፡፡ በአገር አቀፍ ደረጃ ለአንድ ጋሻ ለም መሬት በአመት 15ብር፣ በለምጠፍ 10 ብር በጠፍ 5 ብር እንዲሆን ተወስኖ የነበረ ቢሆንም፤ በተሻሻለው በ1937ቱ የመሬት ግብር አዋጅ ግን ለለም በዓመት 50 ብር ለለምጠፍ 40 ብር፣ ለጠፍ 15 ብር እንዲሆን ተደርጓል፡፡ ይህ የሆነውም በአይነት ይከፈል የነበረውን ተጨማሪ የአስራት ግብር በጥሬ ገንዘብ ለመተካት ሲባል ነው፡፡ የዋጋ ተመኑ በስራ ላይ የዋለው በሸዋ፣ በሐረር፣ በወሎ፣ በወለጋ፣ በአርሲ፣ በሲዳሞ፣ በኢሊባቡር፣ በጋሞ ጎፋና በከፋ በሚገኙ የተለኩ መሬቶች ላይ ነበር፡፡

በሸዋ የርስት መሬት ላይ ዝቅ ያለ ተመን ሲጣልበት፣ የጎጃምና የበጌምድር መሬት ግን ግብሩ በቀድሞው ተመን ሆኖለት በአስራት በተገመተው እንዲከፍል ተደረገ፡፡ ከዚሁ አዲስ እርምጃ ጋር በተያያዘም

ቀደም ሲል በገበሬው ላይ ተጭነው የነበሩት ልዩ ልዩ ክፍያዎችና የጉልበት ስራዎች ተሸረዋል፡፡

ነገር ግን አዋጁ በበታች ሹማምንት እየተጣሰ ገበሬው ሕገ-ወጥ ጭቆናው አልቀረለትም፡፡ የንጉሡ ስርዓት ያለው የግብር አሰባሰብ ዓላማም ግቡን ሊመታ አልቻለም፡፡ በስተመጨረሻ ከፍተኛው ዓመታዊ ግብር 80 ብር የደረሰበት ሁኔታ ሲኖር፤ በ1958 ዓ.ም በታወጀው 3ኛው የመሬት ግብር አዋጅ መሠረት ባለመሬቶች ግብሩን እንደቀድሞው ለጉልተኛ ሳይሆን በቀጥታ ለመንግስት እንዲያስገቡ ተደነገገ፡፡

ፕ/ር ባህሩ ዘውዴ "ይህ እርምጃ ተፈፃሚነት ቢያገኝ ኖሮ ርስተጉልትንና ሲሶ ጉልትን የመሻር ያህል ነበር፡፡ ነገር ግን እንዲህ አይነቶቹ ባለመብቶች በተለይም ርስተ ጉልተኞች ከፖለቲካ ስልጣን ጋር ባላቸው የተሳሰረ ግንኙነት ተጠቅመው የአዋጁን ተግባራዊነት ለማሰናከል ችለዋል፡፡ የቤተ-ክህነትን የጉልት መብት የመንካቱ ጉዳይ እንደሆነ ከቶም አልታሰበም" በማለት ያብራሩታል፡፡

የአፄ ኃይለስላሴ መንግስት ሲነሳ የመሬት ግብርና የገበሬ አመፅ የሚሉ ቃላቶች አብረው ይጠቀሳሉ፡፡ ነገር ግን የኢትዮጵያ ዋናው ሀብት ምናልባትም ብቸኛው ያኔ መሬት ነው፡፡ ሹመትና ሽልማት መሬት፣ የገቢ ምንጭ መሬት፣ ሁሉም ነገር መሬት ነውና የንጉሡ ዘመናዊ አስተዳደር ዝርጋታም ሆነ የመንግስት ገቢ በመሬት ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ የመንግስትን ገቢ ለማሳደግ የመሬት ግብር ግድ ነው፡፡ ንጉሡን ወደ መሬት ያወረዳቸውም መሬት ነው፡፡ ጥፋታቸው የመሬት ግብር መጣላቸው ሳይሆን ሰፋፊውን መሬት ለሹማምንቱ መስጠታቸው፣ ሰጥተውም ግብሩን አለመጣላቸው፣ በክልሎች ደረጃ ከዘመኑ ፖለቲካ ጋር በተያያዘ ችግር ፍትሐዊ የግብር አጣጣል ማድረግ አለመቻላቸው ነው፡፡ ሆኖም በተደጋጋሚ የተለያዩ እርምጃዎችን ወስደዋል፡፡በ1960 የመጨረሻውን የእርሻ ገቢ ታክስ አወጁ፡፡ እስከዚህ ጊዜ ድረስ ከግብርናው የሚገኘው ገቢ እጅግ ዝቅተኛ ነበር፡፡

የመጨረሻው አዋጅ እጅግ ፍትሐዊ የተባለና ሁሉንም ያማከለ፤ በመሬቱ አይነት ሳይሆን በምርት መጠን የሚለካ፣ ከፍተኛ ገቢ ያላቸውን በርከት ያለ ግብር የሚጠይቅ ሆኖ ቢታወጅም ማን ይፈፅመው? ገማች ኮሚቴዎች ማዳላት ጀመሩና አበላሹት፡፡ ምንም እንኳ ሰፊው መሬት ለግብርና ምቹ ሆኖ ቢገኝም፤ በተለያዩ ችግሮች ምክንያት በግብርናው ዘርፍ ተጨባጭ ለውጥ ሊመጣ አልቻለም፡፡ ለዚህ ደግሞ ዋናው ችግር ዘመናዊ የማምረቻ ግብአት አለመኖር ነው፡፡ ስለዚህ በውጭ ንግድ ላይ ያተኮረ ከፍተኛ የትራክተር እርሻ ተመራጭ ነበርና እሱኑ ተግባራዊ አስደረጉ፡፡



የዚህ ተሳታፊዎች መንግስት፣ የውጭ ባለሃብቶችና የአገር ውስጥ ባለሃብቶች ናቸው፡፡ ባለመሬቶች የራሳቸውን መሬት ሲያርሱና ሲያሳርሱ፣ ሌሎች መሬት ተከራይተው ማረስ ጀመሩ፡፡ እነዚህ በሰፊ የእርሻ ልማት የተሰማሩ ባለሃብቶች በዋናነት በደቡብ ሸዋና በሁመራ አካባቢ ነበር፡፡ ለአብነትም በእንግሊዛዊው ሜቼል ኮትስ ኩባንያ የተቋቋመው የተንዳሆ የጥጥ እርሻ ልማት በአዋሽ ሸለቆ፣ በኤርትራ የጣሊያን ከበርቴዎች ያቋቋሙት የኤላበረድ እርሻ፣ በመንግስት በኩል በ1954 በአዋሽ ሸለቆ ባለስልጣን አማካኝነት የእርሻ፣ የአግሮ ኢንደስትሪና የሐይድሮ ኤሌክትሪክ እንቅስቃሴዎች ይካሄዱ ነበር፡፡

ለተራው ገበሬም "ሁለገብ የእርሻ ልማት" በተሰኙ ፕሮግራም ምርጥ ዘርና ማዳበሪያ በማደል ግብርናውን ለማሳደግ ተሞክሯል፡፡ ይህም የእርሻ ዘዴና ጥቅም ማስፋፊያ በሚባለው የመንግስት ተቋም አማካይነት ይከናወን ነበር፡፡ ከዓለም ባንክ በተገኘ እርዳታ የተቋቋመው የወላይታ እርሻ ድርጅት "ዋዱ" በሰፈራ ፕሮግራሙ አማካይነት የመሬት መጣበብን ለማቃለል በመቻሉ ደሃውን ገበሬ በማገዝ ውጤታማ ነበር፡፡

የስዊድን ዓለም አቀፍ የልማት ድርጅት /ሲዳ/ ገበሬውን በልማት ሊያግዝ ቢቋቋምም ሐብታም ባለመሬቶች እነሱን የሚያግደውን ሕግ ጥሰው ዋና ተጠቃሚዎች ሆኑበት፡፡ ይህም የጭላሎ እርሻ ልማት "ካዱ" በመባል የሚታወቀው ነው፡፡ ድሆችን ሊረዳ ተቋቁሞ ማናለብኞች ተሻሙት ማለት ነው፡፡ ይሄው ነው፡፡ ፍትህ ከሌለ እርሻ ብቻ ሳይሆን "መና"ም ቢወርድ አይሳካልንም፡፡

የትራክተር እርሻ በተስፋፋበት ጊዜ ለበርካታ ጭሰኞች መፈናቀል ምክንያት ሆነ፡፡ ምክንያቱም ባለመሬቶች በጭሰኛ ከማሳረስ ይልቅ መሬት ማከራየቱን አዋጭ ሆኖ አገኙት፡፡ እለት እለት የጭሰኛው ችግር እየተባባሰ ስለሄደም መንግስት የተለያዩ የመፍትሄ እርምጃዎችን ለመውሰድ ቢሞክርም አጥጋቢ አልሆነም፡፡

በዚህ ረገድ መንግስት የጭሰኛውን ሁኔታ በሚመለከት በ1954 አንድ ኮሚቴ እንዲቋቋም አድርጎ ነበር፡፡ ይህ ኮሚቴ በ1957 ወደ "የመሬት ይዞታ ማሻሻልና ልማት ባለስልጣን" አድጎ ከዓመት በኋላ የመሬት ይዞታና አስተዳደር ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ለመሆን በቃ፡፡ በሂደቱም የጭሰኛውን ችግር ለመፍታት ተንቀሳቀሰ፡፡ "ነገር ግን የሚወጡት ረቂቅ ሕጎች /የጭሰኛውን ጥቅም በሚመለከት/ የባለመሬቱን መደብ ጥቅም ስለሚፃረሩ ምክር ቤቱና አባላቱ እያደናቀፉና እያንተቱ አዘገዩት፡፡ የጭሰኛውን ችግር ይፈታል ተብሎ የታመነበት የ1957ቱ ረቂቅ ሳይፀድቅ በመቅረቱም ነው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች "መሬት ላራሹ" ብለው ሰልፍ የወጡት" እንደ ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ

አገላለፅ፡፡ ከዚያ በኋላ ባሉት ዓመታትም ተመሣሣዩ የመጨረሻ እቅድ /ረቂቅ/ ሳይሰምር ቀርቷል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለም ድርቅ፣የአንበጣ መንጋና ሌሎች የተፈጥሮ አደጋዎች ባደረሱት ቀውስ በ1950 በትግራይ፣ በ1958 በወሎ፣ ጥቂት ቆይቶ በ1965ም በዚያው በወሎ ተደጋጋሚ ድርቅና ረሃብ ተከስቶ የብዙ ዜጎችን ህይወት ቀጠፈ፡፡

ተሸፋፍኖ የቆየው ረሃብ በዩኒቨርስቲው ማኅበረሰብና በውጭ ጋዜጠኞች ተጋለጠ፡፡ የተፈጥሮ አደጋው እንዳለ ሆኖ፤ ዋናው ተጠያቂ ሙስና ነው፡፡ ሙስና ጉቦ መቀበል ብቻ አይደለም፡፡ ይህን ጉዳይ በስተመጨረሻ በሰፊው እንቃኘዋለን፡፡ የጃንሆይ አስተዳደርና መሬት በጣም በአጭሩ ያየነውን ሲመስል፤ በአጠቃላይ የግብርናው ዘርፍ በየጊዜው እየተስፋፋ ሄዶ በ1966 ዓ.ም ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት የመጀመሪያውን ደረጃ ይዞ 49.3 በመቶ ቢደርስም በውጤቱ ህዝብን መመገብ የሚችል አልሆነም፡፡

ጃንሆይና ንግድ

ንግድ በጃንሆይ ዘመን ነው የዘመነው፡፡ አብዛኛው ወደ ውጭ የሚላኩ ሸቀጦች የእርሻ ውጤቶች ነበሩ፡፡ከጠቅላላው የውጭ ንግድ 60 በመቶውን የሚይዘው በዘመናቸው ግጥም ተገጥሞ በጅማ ወጣቶች ዜማ የተሰራለትና ዛሬም ድረስ የሚዘመርለት ቡና ነው፡፡ ቀጥሎ ቆዳና ሌጦ ነው፤ ከዚያም ጥራጥሬና የቅባት እህሎች ይከተላሉ፡፡

የወጪና ገቢ ንግዱ ከወደመጀመሪያ ተመጣጣኝ ስላልነበረ የውጪ ንግዱ ውጤት እዚህ ግባ የሚሉት አልነበረም፡፡ ከውጭ የሚገቡ ሸቀጦችን አገር ውስጥ ማምረት ሲጀመርና ኢንዱስትሪዎች ሲስፋፉ ግን መጠነኛ ለውጥ ታይቷል፡፡ የንግድ ሂደቱ የአገሪቱን የዓለም አቀፍ ግንኙነት አቅጣጫ የተከተለ በመሆኑ 40 በመቶው ከአሜሪካ ጋር ሲሆን በተለይ የቡና ንግድ 70 በመቶው በአሜሪካ ገበያ የሚጣራ ነበር፡፡

በገቢ ንግድ ረገድ ደግሞ በቅደም ተከተላቸው ጣሊያን፣ ጃፓንና አሜሪካ በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡ ንግዱ ኪሣራ መሆኑ ሲታይም ነው የኢንደስትሪ ፖሊሲው ላይ ማተኮር ያስፈለገው፡፡ የውጪ ሸቀጦች ዋጋ እየወረደ፣ የገቢ ሸቀጦች ዋጋ እየናረ ብዙ ኪሳራዎች ታይተው ነበር፡፡ የአገር ውስጥ ንግድን በሚመለከትም ቀደም ሲል በወደቦች አቅራቢያ በሚገኙ የኢትዮጵያ ከተሞች ተዉጡፎ በመሐል ከተማው የቀዘቀዘ የነበረው የአገር ውስጥ ንግድ ወደ አዲስ አበባ አተኩሯል፡፡

የቀድሞው የምኒልክ የአራዳ ገበያ ከወረራው ጊዜ ጀምሮ "ፒያሣ" በሚል አዲስ ስም ተሰይሞ የነጮች መገበያያ ሆኖ ነበር፡፡መርካቶን ለሐበሻ መከለላቸውም ይታወቃል፡፡ ስለዚህ የችርቻሮው ንግድ ከፒያሣ ወጥቶ ወደ መርካቶ ተዛወረ፡፡ ፒያሣ ላይ ሰፍረው ይነግዱ የነበሩ የውጭ



ዜጎች የበላይነታቸው በታታሪው የጉራጌ ብሔረሰብ እየተሸረሸረ ከስሟል፡፡ የመርካቶ ጉራጌዎች በየመን ዓረቦች ቁጥጥር ስር ሆኖ የነበረውን የችርቻሮ ንግድ ለመቆጣጠር የቻሉትም ከነፃነት በኋላ ነው፡፡

አንዳንድ የሳይኛው መደብ አባላትም አስመጪና ላኪ በመሆን አንዳንዴ በግላቸው፣አንዳንዴ በመንግስት ሽፋን ተሰማርተውበታል፡፡በመንግስት ደረጃም ብሔራዊ ኮርፖሬሽን የተባለው ድርጅት ተቋቁሞ የእህል ምርትን ለአገር ውስጥ ዜጎችም፣ ለውጭ አገር መንግስታትም ይሸጥ ነበር፡፡ ይህ ድርጅት በ2ኛው የዓለም ጦርነት የኢኮኖሚ ቀውስ ለደረሰባቸው ለአውሮፓውያን ጦርነቱ እየተካሄደ በነበረባቸው ተከታታይ 4 ዓመታት የእህል ምርቶችን በመላክ በሚሊዮን የሚቆጠር ትርፍ አግኝቷል፡፡ ከዚያም የኮርፖሬሽኑን ተሞክሮ መሠረት በማድረግ የውጭ ንግዱን ለመቆጣጠር ወይም ለማመጣጠን ሌሎች ተመሣሣይ የንግድ ተቋማት በመንግስት ደረጃ ተመስርተዋል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ "የንግድና የትራንስፖርት ማኅበር" ተብሎ የተሰየመው ድርጅት በቀድሞው አጠራር "ማኅበር ቤት" የሚባለው የተለያዩ የውጭ ሸቀጦችን ወደአገር ውስጥ የማስገባት ሞኖፖል የነበረው ይጠቀሳል፡፡ ሌሎችም ቡና ቦርድ፣ እህል ቦርድ ... ወዘተ ቦርድ የሚባሉ ነበሩ፡፡ የጃንሆይ ዋና የገቢ ምንጭ ጉምሩክ ነው፡፡ የወጪና የገቢ ንግድ ቀረጥ ድንጋጌዎች በተለያዩ ጊዜያቶች ተደንግገዋል፡፡

የአዋጆቹ ትኩረት ከሚወጡት ይልቅ በሚገቡት ላይ ነበር፡፡ በውጪ ንግድ በኩል ታሪፋቸው የተደነገገው ቆዳና ሌጦ፣ ቡና፣ ሰም እና ዝባድ ነበር፡፡ ይህም ዘመናዊ የሆነ አሰራር እስኪዘረጋ ድረስ የቆየ ነበር፡፡ ከገቢ ንግድ የሚገኘውን ቀረጥ ከፍ በማድረግም የመንግስትን ገቢ ማሳደግ ተችሏል፡፡ሆኖም ከወጪ ንግዱ የሚገኘው ገቢ አናሳ ስለሆነ በንግዱ ዘርፍ ተጨባጭ ለውጥ ሳይታይ ቀርቷል፡፡

በጥቅሉ አዲሱ የብሔራዊ ባንክ በገንዘብ ሚ/ር አጠቃላይ መመሪያ ስር የአገሪቱን የውጭ ምንዛሬ፣ የገንዘብ ሕትመት፣ የባንክ ብድርና የወለድ ፖሊሲ በሚመለከት ሃላፊነት ነበረበት፡፡ በ1935 የትራንስፖርት ሕግ ደግሞ በአገሪቱ ታሪክ ለዘመናት በንግድና በመገናኛ ስራዎች እድገት ላይ ተፅዕኖ ሲያደርግ የኖረውን የኬላ ስርዓትና ቀረጥ አስቀርቶ፣ በማዕከላዊ የመገናኛ መስሪያ ቤት ስር ዘመናዊ የሞተር ተሽከርካሪ ስርዓትና አሰራር በመፍጠር በአገራችን የንግድና የመገናኛ ታሪክ አዲስ የእድገት ምእራፍ ከፈተ፡፡ የ1935ቱ የጉምሩክ ሕግ የኢትዮጵያ መንግስት የገንዘብ ገቢ ዋናው ምንጭ የውጭ ንግድ እቃ ቀረጥ እንደሆነ አሳየ፡፡

ነገር ግን ምንም እንኳ እነዚህ መሠረታዊ የባንክ፣ የመገናኛ፣ የጉምሩክና፤ የገንዘብ ድርጅቶችና ስራዎች በአገሪቱ ለዘመናዊ የንግድና የመገናኛ እድገት አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎች ቢሆኑም፤ የኢትዮጵያ

ቁልፍ የእርሻና የእደ ጥበብ ክፍለ ኢኮኖሚዎች ኋላቀር በመሆናቸው ለንግዱ ክፍለ ኢኮኖሚ እድገትና መስፋፋት ሊያደርጉ የሚችሉት አስተዋፅኦ በአይነትም በመጠንም የተወሰነ ሆነ፡፡
ቢሆንም የንግድና የመገናኛ ክፍለ ኢኮኖሚው ዘርፍ ከኪሣራ ተነስቶ በየእለቱ እያደገ ሄዶ በአብዮቱ ዋዜማ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ጠቅላላ የአገር ውስጥ አመታዊ ምርት /ገቢ/ 15.6 በመቶ ሆኖ ነበር፡፡ ይህም ከእርሻ፣ ከአገልግሎት፣ ከኢንደስትሪ ዘርፎች ቀጥሎ የመጨረሻ ደረጃ ላይ የሚቀመጥ ዘርፍ ሆኗል ማለት ነው፡፡

## ጃንሆይ እና ኢንደስትሪ

የኢንደስትሪው ዘርፍ ከወረራው በፊት ከነበረው ጋር ሲነፃፀር ከነፃነት በኋላ የታየው ለውጥ ከፍተኛ የሚባል እንደነበር ብዙዎች ያምናሉ፡፡ የዚያ ዘመን ንግድና ኢንደስትሪ እንደ አቅሙ መስፋፋት የቻለው ንጉሡ አገሪቱን ለኢንቨስተሮች ምቹ በማድረጋቸው ነው፡፡ ለምሳሌ በ1941 ዓ.ም የተደነገገው የገቢ ቀረጥ አዋጅ ከ2 መቶሺህ ብር በላይ ካፒታል ያለውና በማዕድን፣ በኢንደስትሪና በትራንስፖርት ዘርፍ የተሰማራ ማንኛውም ኢንቨስተር በመጀመሪያው 5 ዓመት የሚያገኘው ትርፍ ከቀረጥ ነፃ ነበር፡፡ በንግድ ኩባንያዎች ትርፍ ላይ የሚሰበሰበው ቀረጥም ከ15 በመቶ እንዳይበልጥ ተደርጎ ነበር፡፡ በሦስተኛው የበጀት ዓመትም ትራክተሮችና ልዩ ልዩ ኬሚካሎች ከቀረጥ ነፃ ሆነው ነበር የሚገቡት፡፡

የንጉሡ አስተዳደር የኢንደስትሪ ፖሊሲ ወጪና ገቢው ይመጣጠን ዘንድ "ከውጭ የሚገቡ ሸቀጦችን በአገር ውስጥ ምርት መተካት" የሚል ነው፡፡ በዚህም መሠረት መጀመሪያ ጨርቃጨርቅ ትኩረትን አገኘ፡፡ አቃቂ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካና ባህርዳር ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡

በኢንደስትሪ መስፋፋት ትልቅ ድርሻ የሚሰጠው በሆላንዱ ኩባንያ ቧኤች.ቪ.ኤ ይካሄድ የነበረው የስኳር ኢንደስትሪ ሲሆን፤ ከነፃነት በኋላ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮለት በ1946 ዓ.ም ሁለት የስኳር ማምረቻ ፋብሪካዎች ማለትም ወንጂ እና መተሐራን አቋቋመ፡፡ የወንጂ ስኳር ፋብሪካ መሠረቱ የጣሊያን ነበር፡፡ ጣሊያን በአዋሽ ሸለቆ የሸንኮራ ተክል ማሳ መስርቶ ነበር፡፡ በ1953 ዓ.ም ኤች ቪ ኤ ተብሎ የሆላንድና የኢትዮጵያ ተብሎ ተሰየመ፡፡ በርካታ ኢትዮጵያውያንም በሥራ ተሳታፊ ነበሩ፡፡ በኩባንያው አክሲዮንም ኢትዮጵያ አንድ ሦስተኛ ድርሻ ነበራት፡፡ በ1959 ከፍተኛ የተባለውን 10 ሚሊዮን ብር ትርፍ ያስገኘ ኩባንያ ነበር፡፡ ለሸማቹም ትልቅ ለውጥ ነበረው፤ ቀድሞ ስኳር ከውጭ ይገባ ስለነበር፡፡

ሌላው መጠጥ ሲሆን፣ የመንግስት የገቢ ምንጭ በመሆን ሰፊ ድርሻ ነበረው፡፡ ከወረራው በፊት የተመሠረተው የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ



ፋብሪካ የረጅም ዘመን ሞኖፖሉን ከሜታ አቦ ቢራ ፋብሪካ ጋር መጋራት ጀመረ፡፡ ኮካ ኮላና ፔፕሲም አገር ውስጥ መዘጋጀት የጀመሩት በንጉሡ ዘመን ነው፡፡

የማዕድን ኢንደስትሪን በተመለከተም ከነፃነት በኋላ በአዶላ የተጀመረው የወርቅ ማዕድን ቁፋሮ እጅግ የላቀውን ገቢ ያስገኘ ሆኗል፡፡ ለምሳሌ በ1937 ዓ.ም ከመንግስት ገቢ አንድ አምስተኛ የተገኘው ከአዶላ ወርቅ ነው፡፡ ይህ ዘርፍ መንግስትን ስላከበረ አዶላ የሚለው የአገር ስም በክብረ መንግስት ተቀየረ ይባላል፡፡

በጥቅሉ የኢጣሊያ መሠረት ያላቸውን ጨምሮ የጨርቃ ጨርቅና ሲሚንቶ ፋብሪካዎች፣የዘይት መጭመቂያዎች፣የእንጨት መሰንጠቂያዎችና የእህል ወፍጮዎች በእጅጉ ተስፋፍተዋል፡፡ የቆቃ ግድብም በ40 ሚሊዮን ብር ተሰርቷል፡፡ ይህ 40 ሚሊዮን ብር የኢትዮጵያ መንግስት ከኢጣሊያ ማግኘት የነበረበትን ካሳ ሳያገኝ ቀርቶ፤ነገር ግን 40 ሚሊዮን ብር ብቻ በሰጠው ካሣ የተሰራ ነው፡፡ የኢጣሊያ መንግስት ለሊቢያ ተገቢውን የጦር ካሣ በቢሊዮን የሚቆጠር ዶላር ቢከፍልም፤ኢትዮጵያ የጠየቀችውን ገንዘብ ግን አልከፈለም፡፡ከ40 ሚሊዮን ብር ውጪ፡፡

ሌላው የኢጣሊያ ጅምር ኢንደስትሪ የአዲስ አበባው የቃጫ ፋብሪካ የሚጠቀስ ሲሆን፤ አባ ሳሙኤል ተብሎ ከሚጠራው ግድብ የተጠለፈው የመብራት ኃይል ምንጭም የእነሱው አሻራ ነው፡፡ በንጉሡ ጊዜ ባየነው መልኩ ከውጭ በሚገቡ ምርቶች ላይ ከፍተኛ ቀረጥ በመጣል ያገር ውስጡን ኢንደስትሪ ለማስፋፋት ተሞክሯል፡፡
የኢንደስትሪዎች ማዕከል በአብዛኛው በአስመራ፣ በአዲስ አበባና በድሬዳዋ ከተሞች ሲሆን፤ በተለይ በአገሪቱ ካሉ ፋብሪካዎች ውስጥ ግማሽ ያህሉ በአዲስ አበባ ይገኙ ነበር፡፡ ለአብነት ያህል የተነሱት ዘርፎችና መሰል የኢንደስትሪ ተቋማት እየተስፋፉ በመሄዳቸውም የሰራተኛው ገቢ የጨመረበት ሁኔታ ከመፈጠሩም በላይ፤ በአብዮቱ መዳረሻ የሰራተኛው ቁጥር 54 ሺ ያህል ደርሶ ነበር፡፡

የዜጎች አማካይ የዓመት የነብስ ወከፍ ገቢም 72 ዶላር ከሃምሳ ሣንቲም ደርሶ ነበር፡፡የሰራተኛው መደብ ከየክልሉ መጥቶ ኢንደስትሪ በተቋቋሙባቸው ቦታዎች በጋራ ሲሰራም የመሰብሰብ እድሉን አግኝቶ በእድርም፣በእቁብም መልክ የተለያዩ ማኅበራትን መመስረት ጀመረ፡፡የክፍያ መሻሻልና የመሣሠሉት ጥያቄዎች በአቤቱታ መልክም በአድማ መልክም መካሄድ ሲጀምሩ፤ መንግስት በ1954 ዓ.ም የመጀመሪያውን የሠራተኛ ማኅበር አዋጅ ደነገገ፡፡ በዓመቱ የኢትዮጵያ ሰራተኞች ማኅበር ኮንፌዴሬሽን ተቋቋመ፡፡ የወንጂ አድማ በ1953 ነበር የተቀጣጠለው፡፡ የመጀመሪያው የስራ ማቆም አድማ በወንጅ ሠራተኞች

ተዳምሮ በአራት ክፍለጦሮች ተደራጀና አንደኛው ክፍለ ጦር /ክቡር ዘበኛ/ በአዲስ አበባ፣ ሁለተኛው ክፍለ ጦር መጀመሪያ ደሴ፣ ቀጥሎ ኤርትራ፣ ሦስተኛው ሐረር፣ አራተኛው ከፊሉ አዲስ አበባ ከፊሉ ነገሌ ቦረና ተመደበ፡፡

በየክፍሉም አሜሪካውያን አማካሪዎች ተመደቡ፡፡ የምድር ጦሩን በዘመናዊ መንገድ ካደራጁ በኋላም በስዊዲኖች ተጀምሮ የነበረውን የአየር ኃይልና በኖርዌጆያኖች እየተደራጀ የነበረውን የባህር ኃይል ተሳትፈውበታል፡፡ በእንግሊዝ ስር በነበሩት ህንዶች ይተዳደር ለነበረው የሐረር ጦር አካዳሚም የማቴሪያል ድጋፍ ያደረጉ ሲሆን፤ የአሜሪካውያን አሻራ ያሳረፈባቸው የጦር ክፍሎች ተብለው የሚጠቀሱት ክቡር ዘበኛና ፖሊስ ናቸው፡፡

በጃፓን አማካሪነትም ባፋጣኝ የማዕረግ እድገትና ሹመት ብዙ ከፍተኛ መኮንኖች ሊፈጠሩ ችለዋል፡፡ "ከ1939 እስከ 1948 ድረስ በዘጠኝ ዓመታት ውስጥ አራት ብርጋዴር ጄኔራሎች ብቻ የነበሩ ሲሆን፤ ከ1949 እስከ 1959 ድረስ በአስር ዓመታት ውስጥ 42 ብርጋዴር፣ ሜጀርና ሌተናል ጄኔራል መኮንኖች ተፈጥረዋል፡፡" (ፕ/ር ላጲሶ1983)

አጠቃላይ ጦር ኃይሉም በአንድ የጦር ሚኒስቴር ስር እንዲተዳደር ተደርጓል፡፡ ኢትዮጵያ ከ1940ዎቹ ጀምሮ በተከታታይ በአሜሪካውያን ሰፊ ድጋፍ በባህር ኃይል፣ በአየር ኃይል፣ በምድር ጦር በኩል በደንብ የተደራጀ የምርጥ ዘመናዊ ጦር ባለቤት ሆነች፡፡ ከባድ የጦር ካሚዮኖች፣ ታንኮች፣ ወዘተ አሜሪካውያን ለገሱ፡፡ ምንም እንኳ የ2ኛው የዓለም ጦርነት ቅሪት ቢሆንም፡፡

በጥቅሉ አሜሪካ ኢትዮጵያ ለኮሚኒዝም ጥቃት እንዳትጋለጥ በደንብ አዘጋጅታታለች ለማለት ይቻላል፡፡ (የሚገርመው ኮሪያ የዘመቱትና ከአሜሪካውያን ወታደሮች ጎን ተሰልፈው የተዋጉት ቃኘው ሻለቃ በአሜሪካውያን ካልሰለጠኑት ከክቡር ዘበኛ የተመለመሉ መሆናቸው ነው፡፡)

የአሜሪካ ድጋፍ በጦር ኃይሉ ብቻም ሳይሆን በአየር ትራንስፖርት በኩልም አለ፡፡ በ1938 ዓ.ም ከኢትዮጵያ ወደ አሜሪካ ያቀናው ልዑክ በኢትዮጵያ የአየር መንገድ ለማቋቋም የአሜሪካን እርዳታ ጠየቀ፡፡ በሚቀጥለው አመትም በኢትዮጵያ መንግስትና በትራንስኮንትኔታል ኤንድ ዌስተርን ኤር ላይን /T.W.A/ መካከል ስምምነት ተደርጎ የኢትዮጵያ አየር መንገድ በ1939 /1946 እ.ኤ.አ/ ተቋቋመ፡፡

ዋና ስራ አስኪያጆችና የቴክኒክ ተቆጣጣሪዎች አሜሪካውያን ሆነው ከቀጠሉ በኋላ፤ በ1964 ዓ.ም የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ስራ አስኪያጅ ተሾመ፡፡ ለየብስ መንገድም ቢሆን አሜሪካ ዋናውን ድርሻ



ትይዛለች፡፡ ቀደም ሲል በወረራው ጊዜ ተሰርተው የነበሩ መንገዶች በጦርነቱ ፈራርሰው ነበር፡፡አዳዲስ መንገዶችም በብዛት አልነበሩም፡፡ በ1943 ዓ.ም የአውራ ጎዳና ባለስልጣን ተቋቁሞ የኢትዮጵያን መንገዶች ለመጠገንና አዳዲስ መንገዶችን ለመገንባት እንቅስቃሴ ተጀመረ፡፡ የባለስልጣን መስሪያቤቱም የተቋቋመው በአሜሪካ ድጋፍና ትብብር ነው፡፡

የባለስልጣኑ መስሪያ ቤት በአሜሪካውያኑ የበላይነት ተቋቁሞ ስራውን ሲጀምርም ግንባታው እንደ አገራቸው አምሳያ /ኦፊስ ኦፍ ፐብሊክ ሮድስ/ ሆኖ ተነድፎ ነበር የቀጠለው፡፡በ1953 ዓ.ም የስራ አስኪያጅነቱን ስልጣን ኢትዮጵያውያኑ ቢረከቡም፤የመንገድ ስራ እንቅስቃሴዎች ይከናወኑ የነበሩት ግን በአሜሪካ ስር ከሚገኘው ከዓለም አቀፍ የመልሶ ግንባታና ልማት ባንክ /ኢንተርናሽናል ባንክ ኦፍ ሪኮንስትራክሽን ኤንድ ዴቨሎፕመንት/ በተገኘ ብድር ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት ባንኩ በባለስልጣኑ ተግባራት ላይ ከፍተኛ የቁጥጥር ኃይል ነበረው፡፡

ቴሌን ለረጅም ጊዜ ይዘው የቆዩት ሲውዲኖች የነበሩ ቢሆንም፤ እንደገና በዘመናዊ መልክ ለማደራጀት የአሜሪካ እጅ ነበረበት፡፡ ከአፄ ምኒልክ ጀምሮም በየጊዜው እየተስፋፋ መሄዱ ይታወቃል፡፡

ከባንክ ጋር በተያያዘ እንግሊዞች ሰፊ ተሳትፎ ነበራቸው፡፡ በወረራው ጊዜ ቀደም ሲል ከነበረው ባንክ ውጪ ባንኮ ዲሮማና ባንኮ ዲናፖሊ የሚባሉ የኢጣሊያ ባንክ ቅርንጫፎች ተቋቁመው ነበር፡፡ ጣሊያኖች ከወጡ በኋላ በ1934 የተቋቋመው የኢትዮጵያ መንግስት ባንክ እንደ ንግድ ባንክም፣ እንደ ብሔራዊ ባንክም ሲያገለግል ከቆዩ በኋላ፤ በ1955 ዓ.ም ተግባራቸው በአዋጅ የተለየ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክና ብሐራዊ ባንክ ተቋቋሙ፡፡ ከዚያ በኋላም እየተስፋፋ ሄደ፡፡

በትምህርቱም እንግሊዝና ፈረንሣይ የማይናቅ ተሳትፎ.የነበራቸው መሆኑ እንዳለ ሆኖ፤ አሜሪካ የአንበሳውን ድርሻ ትይዛለች፡፡ በርካታ ኢትዮጵያውያን ለትምህርት የሚላኩት አሜሪካ ነበር፡፡ በጥቅሉ በአገር ግንባታው ዘርፍ ሰፊ አስተዋፅኦ ያበረከተችው አገር አሜሪካ ነበረች፡፡ ሂደቱ በዚህ ቀጥሎ በስተመጨረሻ ግን የንጉሡን አፍቃሬ ካፒታሊዝምነት እየተቃወሙ የመጡትና የኢትዮጵያን መንግስት ፊውዳል እያሉ የሚጠሩት ምሁራን /ተማሪዎች/ ይሄ የኢምፔሪያሊዝም ነፀብራቅ ነው እያሉ መንቀፍ ጀመሩ፡፡ የሚገርመው ልክ በዚያው ዘመን የሶሻሊስት ርዕዮት ይከተል የነበረውና ለአስዋን ግድብ ከሶቭየት እርዳታ ይጠይቅ የነበረው፣ ሲውዝ ካናልን ከእንግሊዝና ከፈረንሣይ ሊወርስ የተነሳው ጋማል አብደል ናስር ሞቶ አንዋር ሳዳት የግብፅ መሪ ሲሆን፤ ሶቭየትን ትቶ አሜሪካን ወዳጅ አደረገ፡፡ የቃኘው ጦር ሠፈር አስፈላጊነትም አከተመ፡፡ አሜሪካም የመካከለኛው ምስራቅ ስጋቷ ተወገደ፡፡ በዚያ ላይ ዘመን ተራቆ

በሳተላይት መረጃን መሰብሰብ ተችሎ ነበርና የስለላ እምብርቱ ዋጋ ቢስ ሆነ፡፡ ተማሪዎችም አሜሪካን፣ አሜሪካም ተማሪዎችን ተገላገሉ፡፡

አፄ ኃይለስላሴ ተደጋግሞ እንደተገለፀው ኢትዮጵያን ዘመናዊ አገር ለማድረግ የውጭ እርዳታ የግድ አስፈላጊ መሆኑን በማመን በዲፕሎማሲው መስክ ልዩ ጥረት አድርገዋል፡፡

ከአፍሪካ መሪዎችም ተወዳዳሪ ያልተገኘላቸው አገር ጎብኝ በመሆን /የዓለም አገራትን በመጎብኘት/ የአንደኘነቱን ስፍራ ይይዛሉ፡፡ ይህም ለመዝናናት ሳይሆን እርዳታ ፍለጋ ነው፡፡ ከግንቦት 1946 እስከ ታህሳስ 1947 ዓ.ም ድረስ ባሉት 8 ወራት ውስጥ ከፍተኛ ባለስልጣኖቻቸውን አስከትለው አሜሪካን፣ ካናዳን፣ ሜክሲኮን፣ ዩጎዝላቪያን፣ ግሪክን፣ ፈረንሣይን፣ ሆላንድን፣ ምዕራብ ጀርመንን፣ ሲውዲንን፣ ኖርዌይን፣ ዴንማርክን፣ እስትሪያን የጎበኙ ሲሆን፣ በህዳር 1949 ደግሞ ህንድንና ጃፓንን እንዲሁም ሌሎችን ጎብኝተዋል፡፡

ዋና አላማቸውም የኢኮኖሚና የቴክኒክ እርዳታ ለማግኘት ነበር፡፡ ለምሳሌ በህዳር 1949 ጃፓንን በጎበኙ ጊዜ በቶኪዮ ከተማ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ባደረጉት ንግግር "የአገራችንን የተፈጥሮ ሐብት በስራ ለማዋልና የህዝባችንን የኑሮ ደረጃ ከፍ ለማድረግ በያዝነው ተግባር አፈፃፀም የጃፓን ገንዘብና የቴክኒክ እውቀት ተካፋይ እንዲሆን በደስታ የምንቀበለው መሆኑን ለክቡርነትዎ ለማረጋገጥ እንፈልጋለን" ብለዋል፡፡በሌሎች አገራትም ተመሣሣይ ተማፅኖቸውን እንደቀጠሉ ግልፅ ነው፡፡ አገራቱም ኢትዮጵያን በማዘመን ረገድ የየድርሻቸውን ተወጥተዋል፡፡

እነዚህን የመሳሰሉ የስልጡን ባዕድ አገራት አስተዋፅኦ ስናይም እንዲሁ በችሮታና በርህራሄ ለኢትዮጵያ አዝነው እንዳደረጉት መወሰድ የለበትም፡፡ አገራቱ የየራሳቸውን ጥቅም፣ ክብርና ተወዳዳሪነትን በማሳየት ፖለቲካዊ ትርፍ ለመሸመትና በርዕዮትም በኩል ቀዳሚነትን ለማወጅ ሲሉ የሚራመዱበት መንገድ ነው፡፡

ሐሮልድ ማርከስ "The Politics of empire Ethiopia Great Britain and the United Sates 1941 - 1974" በሚል መፃህፋቸው፤ "ይህ አይነቱ ቀዳማዊ ኃይለስላሴ የወሰዱት ዲፕሎማሲያዊ እርምጃ በቀዝቃዛው ጦርነት ኢትዮጵያ ወደ ምስራቁ ርዕዮት ልታዘነብል ትችላለች የሚል ፍርሃት አሜሪካን ከፉኛ እንቀጥቅጧት ነበር" በማለት ገልፀውታል፡፡ ስለዚህም "አሜሪካ የኢትዮጵያን ጉዳይ ከልቧ እንድታስብበትና ሙሉ ትኩረት ለኢትዮጵያ ፀጥታ እንድትሰራ የሚጋብዝ ነበር" ሲሉ ያክሉበታል፡፡



ጃንሆይና ትምህርት

ጃንሆይና ትምህርት አብረው የተወለዱ እስኪመስል ድረስ አስገራሚ ፍቅር ነበራቸው፡፡ጃንሆይን ለመተቸት ብዕራቸውን የሚቀስሩ ምሁራን ጃንሆይ ያስተማሯቸው ናቸው፡፡በራሳቸው ገንዘብ ከፍለው ባያስተምሯቸውም፤ዜጎች በአገራቸው ላይ የመማር መብት ቢኖራቸውም፣ መንግስት ትምህርትን የማስፋፋት ግዴታ ቢኖርበትም፣ብዙ ብዙ ነገር ቢባልም፤የዛሬ አገር መሪዎችን በጊዜ እንዲሰለጥኑ አድርገዋልና ቢያንስ በትምህርቱ ዘርፍ በእጅጉ ሊመሰገኑበት የሚገባ ስራ ሰርተዋል፡፡

የትምህርት ፖሊሲው ልክ አልነበረም፣ የምዕራባውያን ምንትስ ነው፣ የመኳንንቱ ልጆች ናቸው የሚማሩበት፣ ትምህርቱ የመንግስት ሃብት ነው፣ የቅበላ አቅሙ አነስተኛ ነው... ወዘተ... እየተባለ ይወራል፡፡ ይኼን ሁሉ ወሬ ለማውራት የሚያስችል እውቀት፣ ስድብን ወደ ወረቀት ገልብጦ መፃፍ የሚያስችል ግንዛቤ፣ መፈክር ካርቶን ላይ በቀለም መፃፍን ሳይቀር ያለማመደ ዘመን ግን የጃንሆይ ዘመን ነው፡፡

ስለዚህ አንዱን መንግስት አግንኖ ሌላውን መንግስት ለማጣጣል ሲባል የሚካሄድ የትችት ዘመቻ፤ ምንም እንኳ "ጨቋኝ" የሚባል ስርዓት ነበረው ቢባልም፣ በመልካም መታወስ የሚችልበትን ታሪክ አብሮ ማንቋሸሽ ተገቢ አይሆንም፡፡ የውጭ አገር ጠላት ይመስል ይህንን ስራቸውን ሳይቀር ሊያዳፍኑ የሚሞክሩ ጥቂት አይደሉም፡፡ ይሄ አካሄድ የቀጣዩን መንግስት መንሳሳት ሊያዳክመው ይችላል፡፡ የምናወራው ስለ ኢትዮጵያ ነው፡፡ እናም ስለ ጃንሆይ የትምህርት አጀማመርና የሚደነቅ የማስፋፋት ስራቸው፡፡

አንድ የነበረችውን የምኒልክ ትምህርት ቤት እሱዋም በፈረንሳይኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተወሰነ ትምህርት የሚሰጥባትን ተቋም ከአልጋ ወራሽነት ዘመናቸው ጀምሮ በጥረታቸው በእርዳታም ይሁን በብድር በአገሪቱ ሃብትም ይሁን በምን መልካም ፈቃዳቸው ሆኖ አስፋፍተው ብዙ ምሁራንን ለኢትዮጵያ አስረክበዋል፡፡የጃንሆይ በትምህርት ማመን ቀደም ብሎ የታወቀ ነው፡፡ የንግስና መንገዳቸውን ይጠርጉ በነበረበት ጊዜ የወደፊቷ ኢትዮጵያ በምሁራን አሰራር ትገነባ ዘንድ ዘር ሳይመርጡ ብዙዎችን ወደሰለጠነው ዓለም ለትምህርት ልከዋል፡፡ አፄ ምኒልክ በጣሉት መሠረት ላይ ተንጠላጥለው ጃንሆይ ከአልጋወራሽነት ዘመናቸው ጀምሮ ልዩ ትኩረት የሰጡት ጉዳይ ነው፤ ምሁራንን ማብዛት፡፡

ከኢጣሊያ ወረራ በፊት 250 ምሁራን ውጭ አገር ተምረው መጥተው የመንግስት ባለሥልጣን ሆነው ይሰሩ ነበር፡፡ በወረራው ዘመን የኢጣሊያ ባለስልጣኖች ምሁራኑን እያደኑ ገደሏቸው፡፡ በዚህም ከፊሉ አለቁ፡፡ የተረፉት ከነፃነት በኋላ አገራቸውን እንዲያገለግሉ ተደረገ፡፡

ከጦርነቱ በኋላ ባሉት ተከታታይ 10 ዓመታት ምሁራንን የማበርከቱ ስራ ቀጥሎ ጃንሆይ ብዙዎችን ወደ ውጭ አገር ልከዋል፡፡በ1934 ዓ.ም የትምህርት ሚኒስቴር ተቋቁሞ የትምህርት ሚኒስትርነት ስልጣኑን ንጉሱ ራሳቸው ደርበው ይዘው እስከ 1958 ዓ.ም ድረስ ቆይተዋል፡፡ ይጠነቀቁለትም ነበር፡፡



ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ተማሪዎችን ሲጎበኙ

ከዚያ ጊዜ ጀምሮ 2ሺ ከ1ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ትምህርት የሚሰጥባቸው ትምህርት ቤቶች፣ 14 ዩኒቨርሲቲና ኮሌጆች፣ እንዲሁም 4 ለዩኒቨርሲቲ ዝግጅት የሚያበቁ የተሻለ ውጤት ያመጡ ተማሪዎች የሚማሩባቸው ከፍተኛ ትምህርት ቤቶችን አቋቁመዋል፡፡ በ1960ዎቹ የመጀመሪያ አመታት አጠቃላይ የተማሪው ብዛት 700,000 ደርሶ ነበር፡፡

ለትምህርት ቤቶች መስሪያነት የንጉሱ የግል ርስቶች ነበሩ የሚውሉት፡፡ በየትምህርት ቤቱ እየዞሩ፣ ድንገት እየደረሱ የትምህርት አሰጣጡን ይፈትሻሉ፡፡ ጥሩ ውጤት ላመጡ ተማሪዎች (ከ1 እስከ 3 ለወጡ) በየአመቱ ሽልማት ይሰጣሉ፡፡ የገና በዓልን ዘወትር የሚያከብሩት ከሁሉም የአዲስ አበባ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች ጋር ሆነው በልደት አዳራሽ ነው፡፡ ልዩ ልዩ ስጦታዎችን እየሰጡም ያበረታታሉ፡፡ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ውጭ አገር የሚሄዱትንም ሆነ ተምረው የሚመለሱትን አሸኛኘትና አቀባበላቸው የተለየና ዛሬ ለአንድ ዲፕሎማት እንደሚደረገው መሽቆጥቆጥ ያህል ነበር፡፡ መቋቋሚያ ከመስጠት ጀምሮ ወጪያቸው ይሸፈናል፡፡

ጃንሆይ ቤተ-መንግስታቸውን ለትምህርት ቤትነት የሰጡ፣ትምህርትን የሚያከብሩ ንጉሰ ነገስት ናቸው፡፡ጥቂቶችን ለመጠቃቀስ ያህል የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ በ1943 ዓ.ም ከመከፈቱ በፊትና በኋላ በድህረ ነፃነት የኮተቤ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ የጄኔራል ዊንጌት 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአዳሪ ትምህርት ቤቶች



ሆነው ተቋቁመዋል፡፡ የኮተቤው በ1935 ተቋቁሞ የምግብ ማብሰያ ቤት እስኪሰራለት ድረስ የተማሪዎች ምግብ ከቤተመንግስት ነበር የሚሄደው፡፡ የ1938ቱ ዊንጌት ደግሞ በትምህርት ሚኒስትርና በብሪቲሽ ካውንስል ትራድኦ ትብብር የተገነባ እንጂ እንግሊዞች ሰርተው ያበረከቱት አይደለም፡፡ የትምህርት ስርዓቱ የእንግሊዝን ስርዓት የተከተለ ሲሆን፣ ኢትዮጵያዊ ምሁራን እንዳሉ ሆነው የበላይ ዳይሬክተሮቹ ካናዳውያን ነበሩ፡፡

የአርትና የሳይንስ ፋክልቲዎችን ያቀፈው ዋናው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ከተቋቋመ በኋላ በነበሩት ተከታታይ 5 አመታትም በአዲስ አበባ "የመሐንዲስ ኮሌጅና የህንፃ ኮሌጅ" በአለማያ "የእርሻ ኮሌጅ"፣ በጎንደር "የጤና ጥበቃ ኮሌጅ"... ተከፈቱ፡፡ በ1953 ዓ.ም እነዚህን የተለያዩ ኮሌጆችና ፋክልቲዎች ጠቅልሎ እንዲያስተዳድር የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (በድሮ አጠራሩ የቀዳማዊ ሃይለስላሴ ዩኒቨርሲቲ) ተመሰረተ፡፡ ከዩኒቨርሲቲው ምስረታ በኋላ የህግ፣ የህክምና፣ የንግድ፣ የአስተዳደር... ወዘተ ዲፓርትመንቶች ተከፈቱ፡፡በ1942 ሰባ አንድ የነበረው የተማሪ ቁጥር (በኮሌጅ ደረጃ) እየቀጠለ ሄዶ በ1965 ዓ.ም የማታ ተማሪዎችን ጨምሮ 10ሺ ደረሰ፡፡

ለድህረ ምረቃ ትምህርት ግን ወደ ውጭ አገር በተለይ ወደ አሜሪካ መሄድ የግድ ነበር፡፡ በ1962 ዓ.ም በአሜሪካ የድህረ ምረቃ ትምህርት የሚከታተሉ ኢትዮጵያውያን ቁጥር 700 የሚደርስ ነበር፡፡

በቅኝ አገዛዝ ይማቅቁ ለነበሩት አፍሪካውያንም ኢትዮጵያ ነፃ የትምህርት እድል መስጠት የጀመረችው በጃንሆይ ጊዜ ነው፡፡ ኢትዮጵያን ዘመናዊ አገር ለማድረግ ለጀመሩት ፕሮግራም ጃንሆይ ትምህርት ወሳኝ ግብአት መሆኑን ስላመኑበት ለዘርፉ ልዩ ትኩረት መስጠታቸው ግልፅ ነው፡፡ ሆኖም በከፊል ምሁራን የሚደነቅ ተብሎ ሲገለፅ፣ በተቃራኒውም የትምህርቱን ስርዓት ከፉኛ የሚተቹት ምሁራን ቀላል ቁጥር የላቸውም፡፡ምንም እንኳ ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች የአስተሳሰብ አድማሳቸው እየሰፋ በሄደ ቁጥር የጃንሆይን አገዛዝ ፊውዳላዊነት የተላበሰ መሆኑን ወደመረዳት እያመሩ ለአመፅ ቢነሳሱም ጃንሆይ ይህ ይሆናል ብለው አስበው አያውቁም ነበር፡፡ ይህን ጉዳይ በተመለከተ፡-

ዶ/ር ፍቅሬ ቶሎሣ "Alienation፡ A Result of The Impact of western education of Ethiopian intellectuals" በሚል ርዕስ ባቀረቡት ፅሁፍ "አፄ ምኒልክና ቀዳማዊ ኃይለሰላሴ የምዕራባውያንን ትምህርት ሲያስተዋውቁ የኢትዮጵያ ልጆችን ከመሰረታቸው እንደሚነጥላቸው አላጡትም ነበር" በማለት ይገልፃሉ፡፡ የጃንሆይን የትምህርት ስርዓት የሚተቹ ምሁራን የትችታቸው መንስኤ ምን እንደሆን ስናይም የብዙዎቹ የምዕራባውያን የእጅ አዙር ቅኝ ነበር ወደማለት ያዘነብላሉ፡፡

ሆስፒታሎች ተገንብተው አገልግሎት ይሰጡ ነበር፡፡ ጣሊያን ኢትዮጵያን ሲወር በደብረማርቆስ አንድ ሆስፒታል እየተገነባ ነበር፡፡ በተረፈ ይሄ የንጉሡን ስራ ለማኮሰስ እየተባለ የሚደሰኮረው ሁሉ ከእውነት የራቀ ነው፡፡ ቀለም መቀባትና መስራት ይለያያል፡፡

ባጠቃላይ ሌሎች የኢጣሊያ ጅምሮች መኖራቸውን ሳንዘነጋ፣ በጤናው ዘርፍ ጣሊያን አንድም ስራ አልሰራም፡፡ ጣሊያን የኢትዮጵያ ህዝብ እንዲያልቅ የበሽታ ፋብሪካ ቢያቋቁም ይመርጥ ነበር፡፡ ለማንኛውም ከወረራው በፊት የነበረው ጅምር ከነፃነት በኋላ በ1934 በጤና ዘርፍ ብቻ የሚያተኩር ተቋም ሆኖ፤ ነገር ግን በአገር ግዛት ሚኒስቴር ስር የሚተዳደር "የህዝብ ጤና ጥበቃ ደሬክሲዮን" ተቋቋመና ቀደም ሲል የተጀመሩ ስራዎችን እንዲቀጥል ሆነ፡፡

እየቆየ የታካሚው ቁጥር ማለትም ከባህላዊው ወደ ዘመናዊው የህክምና ተቋም የሚጎርፈው ሰው ስለበዛ፣በ1939 የጤና ጥበቃ ሚኒስቴርን ለማቋቋም የሚያስችል ረቂቅ ህግ ተዘጋጅቶ በ1940 ሚኒስትር መስሪያ ቤቱ በአዋጅ ተመሰረተ፡፡

ከዚያ ጊዜ ጀምሮ በሁሉም ግዛቶች የጤና አገልግሎት ሽፋኑን ሙሉ ለሙሉም ባይሆን በተቻለ መጠን ለማዳረስ ተሞክሯል፡፡ኢትዮጵያ የአለም የጤና ጥበቃ ድርጅት አባል የሆነችውም ከዚያ በኋላ ነበር፡፡እስከ 1966 ዓ.ም ድረስ ከወረራው በፊት 10 የነበሩ ሆስፒታሎች በአጭር ጊዜ ውስጥ 66 ሆስፒታል፣ 679 ክሊኒኮች፣93 ጤና ጣቢያዎች ሊቋቋሙ ችለዋል፡፡የጤና ጥበቃ ሚኒስትር ከ1950 እስከ 1966 ድረስ በነበሩት አመታት ብቻ 9,167 የሆስፒታል አልጋዎች እንዲኖር አድርጓል፡፡

የሐኪሞች ቁጥር 375፣ የነርሶች ቁጥር 934፣ ጤና መኮንኖች 376፣ ነርሶች 286፣ እንዲሁም 270 የጤና ተቆጣጣሪዎች እንደነበሩ የአሁኑም የድሮውም ሚኒስቴር መስሪያቤቶች መረጃ በግልፅ ያሳያል፡፡

እንግዲህ እስካሁን በተናጠል ባጭር ባጭሩ ያየናቸው ፍንጮች ከነፃነት በፊትና በኋላ ተጀምረው እስከ አብዮቱ ዋዜማ በሂደት እያደጉ የደረሱበትን ሁኔታ ነው፡፡ የቀረውን ከራሳቸው ከጃንሆይ እንስማ፡፡

የጃንሆይ ልማታዊ ንግግር

ይህ ሐተታ ጃንሆይ ስልጣን በያዙ በ30ኛ ዓመታቸው ያደረጉት ንግግር ነው፡፡ የጃንሆይ ልማታዊ ንግግር ብየ የሰየምኩትም በመግቢያው ዘርዘር ያሉ ልማታዊ ትንታኔዎች ስላሉበት ነው እንጂ ርዕሱ "ግርማዊ ንጉሠ ነገስት ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ሚያዚያ 6 ቀን 1953 ዓ.ም በገነተ ልዑል ቤተመንግስት ለክቡራን ሚኒስትሮችና ለመንግስት ባለስልጣኖች ያደረጉት ንግግር" የሚል ነው፡፡ በተለይ ለወደፊት እንግዳ አንባብያን የጃንሆይን ንግግር እንደወረደ ማንበብ ጥቅም ይኖረዋል፡፡ የዚያን ወቅት አጠቃላይ ሁኔታንም ያስቃኛል፡፡ በደንብ እንድንስላቸው የሚያግዝም



ነው፡፡ እናም ከጉዳያችን ጋር ተያያዥነት ያለውን እየመረጥኩ አጭሯን "ፓምፍሌት" አሳጥሬ አቀርባለሁ፡፡ በዚህም የጃንሆይን የመናገር መብት ከመጣስ እንቆጠባለን፡፡ በተጨማሪም ሳናውቀው የመጣነው ነገር ካለ በማሳወቅ ያግዙናል፡፡ በመረጃ ሰነድነትም ያገለግሉናል፡፡ ይቀጥሉ ጃንሆይ....

"ከዛሬ ሠላሳ አመት በፊት በእግዚአብሔር ፈቃድ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገስትነትን በመቀባት ዘውድ ጭነን የተወደደችው አገራችን ባህሏንና ልማዷን እያዋሃደች በዘመናዊው የስልጣኔ ጎዳና እንድትራመድ ለመምራት የተመረጥንበትን ተግባር ስንጀምር ኢትዮጵያ እምን ደረጃ እንደነበረች ታውቁታላችሁ፡፡"

ከዚህ ከፊታችን የተሰባሰባችሁ የመንግስታችን ሚንስትሮችና ባለስልጣኖች እስኪ በዚያን ዘመን የነበረውን ወደ ኋላ መለስ ብሎ በህሊና ሲመለከቱት የነበረውን ልታስታውሱት ትችላላችሁ፡፡

ኢትዮጵያ ስልጣኔዋ ተረስቶ ለቅኝ ግዛት የሚወዳደሩባትና ለዚሁ እንድትሆን በምትመራበት ጐዳና ገብታ ወራዳነት ሊያደርስባት በሚችል በልማድ ሽባነት የምትተዳደር፣ ከሌላው ዓለም በብዙ አኳኋን ተለይታ የምትኖር፣ በጅምር ያለ እንጂ ያልተሟላ፣ በቃል ታሪክ እንጂ በፅሁፍ የተመሰረተ የመንግስት አስተዳደር የሌላት በፊውዳል የምትገዛ፣ ንጉሡና ሹማምንቱ እንዳፈተታቸው የሚያዙበት፣ የታወቀ ቋሚ የውጭ አገር ንግድ የሌላት አገር አልነበረችምን? በዚያን ጊዜ የነበረውን ሁኔታ ከዛሬው ጋር በማመዛዘን ይህ ሁሉ መለዋወጥ እንዴት እንደተደረገ ያለፈውን ጊዜ ስራ በፅሁፍ የሚገኘውን ሁሉ እያያችሁ ስትመረምሩት ስራው ምስክርነቱን ይሰጣል፡፡

ይህ መለዋወጥ ያስከተላቸው ችግሮች ወይም ቁልፍልፍ ስራዎች ምንድን ናቸው? በዛሬው በ1953 ዓ.ም የሚኖሩብንን ችግሮች በምን አኳኋን ምን እርምጃ በመውሰድ ልንወጣቸውና ልናስወግዳቸው እንችላለን?

ለአንድ አገር የሚደረገው የመሻሻል እርምጃ ያገሩን መላ ህይወት የሚመለከተው ክፍል ሁሉ ተባብሮ በአንድነት እንዲከናወን ማድረግ የሚያስፈልግ ነው፡፡ አንድ አገር የኢኮኖሚክ መሻሻል በሚያደርግበት ጊዜ እንደዚሁም የተሻሻለ የማኅበራዊ ኑሮና የፖለቲካም ድርጅት እንዲፈጠር ተመሳሳይ የሆነ መሻሻል ማድረግ አለበት፡፡ በአንደኛው ክፍል ያለውን እርምጃ ወደ ኋላ ለማስቀረት የሚደረገው ሙከራ ሁሉ መላውን የመሻሻል እርምጃ ወደኋላ መጎተቱ የማይቀርና በጠቅላላውም የአገሪቱን መሠረታዊ ድርጀት ከትክክለኝነት መስመሩ የሚያቃውስ ነገር የሚፈጥር ይሆናል፡፡

እኛም በእግዚአብሔር አሠሪነት ተስፋ ሳንቆርጥ ስልጣኔ የሚስፋፋበትን፣ እውቀት የሚገኝበትን፣ ተማሪ ቤት ከነተማሪው በማብዛት

ጉዳት ፀፀትና ቁጭት በመላው ህዝባችን አድሮበት እንዲሰራበት አደረግን፡፡ በ1935 ዓ.ም የመንግስታችን ሚኒስትሮችና በልዩ ልዩ ክፍል ያሉት ሹማምንት የሚኖራችሁን ተግባርና ኃላፊነት ልትፈፅሙ የምትችሉበትን ስልጣን የሚወስን ትእዛዝ በአዋጅ አወጣን፡፡ ህዝባችንም ፍትህን ለማግኘት የሚችልበትን እና በሕገ-መንግስቱም የተሰጠውን መብት የሚያስከብርበት ፍርድ ቤት አቋቋምን፡፡ ይህንንም ስናደርግ ራሳችን የወጠንነውን የመሻሻል እርምጃ ሊያስከትል የሚችለውን ሁሉ በመገመትና ህይወት የሚመራበትንም መሠረታዊ ሃሳቦች በመገንዘብ የበለጠ መሻሻል እንዲኖር ለማበረታታትና ስራንም ለማቃለል ባለን በፅኑ ፍላጎትና ምኞት ተመርተን፣ ንጉሠነገስት ለመባል ህዝቡም ወዶ በእግዚአብሔር ስንመረጥ ለገባነው ቃል ኪዳን ለህዝባችን ታማኝነት ራሳችን እየሰራንና. እየተቆጣጠርን ለመርዳት በራሳችን ሙሉ ፈቃድ ያደረግነው እንጂ ተጠይቀን አልነበረም፡፡

"የኢትዮጵያን የልማት እድገት ለማስገኘት የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ መብራት ኃይል ባለስልጣንን፣ የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ቦርድን፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድን የአውራጎዳና ባለስልጣንና ልዩ ልዩ ኢንዱስትሪ እነዚህን የመሳሰሉትን ራሳቸውን ችለው የሚተዳደሩ ድርጅቶች ስራቸውን በሚመለከታቸው ክፍል ሙሉ ኃላፊነትና ስልጣን ኖሯቸው ራሳቸውን ችለው እንዲሰሩ በልዩ ሕግ አቋቁመን ይሰራባቸዋል፡፡

"... የንጉሠነገስት መንግስት ግዛታችን ስራና የመሻሻል እርምጃ እያደገና እየተስፋፋ በመሄዱ መጠን በ1923 ዓ.ም በራሳችን ሙሉ ፈቃድ የሰጠነው ሕገ-መንግስት ህዝባችን ከደረሰበት ደረጃ ጋር ሲመዛዘን በቂ አለመሆኑን ራሳችን ተገንዝበን የህዝባችንም እውቀት በማደጉ በ1948 ዓ.ም አዲሱን የተሻሻለውን ሕገ-መንግስት አሁንም ሳንጠየቅ ተቃዋሚም ቢኖርም በራሳችን ሙሉ ፈቃድ አውጀን ለህዝባችን ሰጠን፡፡

በዚህም በተሻሻለው አዲሱ ሕገ-መንግስት መሠረት በእኛ ሹሞች ጭምር ሲመረጥለት የነበረውን ህዝባችን በቀጥታ ለእማካሪነት የሚመረጡትን በመምረጥ በመንግስታችን ያስተዳደር ስራ ተካፋይ የሚሆንበት መብት እንዲኖረው አደረግን፡፡

በእኛ፣ በሚኒስትሮቻችንና በፓርላማችንም መካከል ያለው የስልጣን መከፋፈል ተወስኖና ፀንቶ ለሁልጊዜም የሚኖርበትን የድርጅት መልክ አገኘ፡፡ እንደዚሁም ህዝባችን በእለት ኑሮው በሚያጋጥመው ጉዳይ ሁሉ እርስ በርስና ከመንግስቱም ጋር በሚያገናኘው ነገር የሚመራበት በትክክልና በዝርዝር ተወስኖ የተመለከተ የፍትሐብሔር፣ የባህር፣ የንግድና የወንጀል ሕጎች ተዘጋጅተው እንዲወጡና የኢትዮጵያም የኢኮኖሚ እድገትና ጠቅላላው የመሻሻል እርምጃ መልክ ባለውና በተባበረ እኳኃን እንዲመራ አሁንም የህዝብ ሐብትና መብት ከፍ የሚልበት፣ ለሰው ልጅ



በተወሰነው ደረጃ የሚደርስበትን የብድር ገንዘብም በብዙ ጥረት አገራችን የመታመን ዋስትና እንዲኖራትና የሚበቃ ዋስትና እንዳላት በማረጋገጥ እያሳየን ስንበደር መክፈልም እንዳለብን ቢታወቅም ያምስት ዓመት ፕላን ተዘጋጅቶ እንዲሰራበት አደረግን፡፡ ፍሬውንም ወደፊት የሚሰጥ ነው ብለን እምነናል፡፡

"ይህንን ሁሉ ስናደርግ ለኢትዮጵያ የመሻሻል እድገቷ እርምጃ አስፈላጊ የሆኑትን እርምጃዎች እንደወሰድን ፈጣሪያችን እንዲያውቅልን በማመን የልማት ፕሮግራማችን በቴክኒክ ረገድም ሆነ በቁጥራቸው እጅግ እየበዙና እየተስፋፉ በመሄዳቸው በ1934 ዓ.ም 11 ሚሊዮን የነበረው ዛሬ በ1953 ዓ.ም 272 ሚሊዮን የደረሰው የመንግስታችን በጀት ከዚሁ ጋር እያደገ በመሄዱ መጠን ዘር የበዛውን ያህል ምርቱንም ሰብስቦ ማሳደግ አስፈላጊ እንደሚሆን ሁሉ በመንግስታችን አመራር ውስጥ በየክፍሉ ያሉት አላፊ ባለስልጣኖቻችን በየደረጃቸው ሊወስኗቸው የሚገባቸው ጉዳዮችን እንዲከፋፈሉ በማድረግ የበለጠ አስፈላጊ እየሆነ መሄዱ የታወቀ ነው፡፡ በተለይ በዛሬው ጊዜ ሁሉንም ጉዳይ ጠንቅቆ ለማወቅ እኔ እበቃለሁ የሚል ማን አለ? የአንድን መንግስት የተስፋፋ ፕሮግራም ለማከናወን አስፈላጊ የሆነውን ውሣኔ ሁሉ በዛሬው ሰዓት ብቻውን ለመወሰን የሚቻለው ማን አለ? እነዚህ ጥያቄዎች መልስ የሚያስፈልጋቸው አይደሉም፡፡

እንግዲህ አንድ እውነተኛ ኃላፊነት ያለው የአስተዳደር ሁናቴ ለመፍጠር ከዚህ የበለጠ የሚያስፈልግ ነገር አለን? ምንስ ይጎድላል? የሚያስፈልግና የሚጎድልም ከዓለም ሰው ፍላጎት እንደማይጠፋ ይሰማናል፡፡

በአዲሱ ሕገ-መንግስት በዚህ አስተዳደር ድርጅት ውስጥ ያለውን እያንዳንዱን ክፍል ትክክለኛ ተግባሩና ኃላፊነቱ ምን እንደሆነና ይህንንም ተግባራችንን ለመፈፀም የሚችልበት መብቱ ተረጋግጧል፡፡

ሚንስትሮቻችንና በቅርብም በሩቅም ያሉት የየክፍሉ ሹማምንቶቻችን ሁሉ በማናቸውም ዓይነት የፖለቲካ አመራር ከሚተዳደሩ ከዓለም አገሮች ያንዳቸውም መንግስት ሚኒስትሮችና ባለስልጣኖች ካላቸው ያላነሰ ለስራችሁ የተመደበ ኃላፊነት ተሰጥቷችኋል፡፡ፓርላማችንም ማናቸውም በፓርላማ ሁናቴ የሚተዳደር አገር ካለው መብት ጋር ተመዛዛኝ የሆነ የሕግ ጎሳብ አቅራቢነት ስልጣን አለው፡፡ነገር ግን ኃላፊነቱን በሙሉ ተቀብለው በታማኝነት የሚሰሩ በቂ ሰዎች እንደሚያስፈልጉን ታውቁታላችሁ፡፡ የራሳችሁን ስራ ወደእኛ ማምጣታችሁ አላቋረጠም፡፡....

የበታችንም ሠራተኛ በማትጋትና በመጎትጎት የሚሰራ ስላልተገኘ ለስራ አፈፃፀም መሰናክል የሆኑ ብዙ ችግሮች ተፈጥረዋል፡፡ በስልጣን

አስታኮ ራስን መጥቀም ሲቆረቁረን መኖሩ ግልፅ ነው። ይህንንም በመመራመራችን እቅመቢስም ቢሆን ስም አጥፊ እንዳልቆመ እናውቃለን። መንግስት ዝርዝር በሆኑ ነገሮች ተውጦ ከፍ ያለ ዋናነት ያላቸው ጉዳዮች ውሣኔ ሳያገኙ ዘግይተዋል። ይህ የምንናገረው ቃል ራሳችሁ የምታስታውሱትና የምትመሰክሩት ነው።

በአሁኑ ጊዜ ልናስጠንቅቃችሁ የምንወደው ለወደፊቱ ይህ አሰራር ሊቀጥል የማይችል መሆኑን ነው። የመንግስታችን አስተዳደር ደምና ስጋ እንደሌለው አካል ድርጅቱ ብቻ ኖሮ አፈፃፀሙ የተጓደለ መሆን ሳይኖርበት ስልጣን ተሰጥቷችሁ ሳለ ኃላፊነቱን ወደእኛ ማሳለፍ ቀርቶ ተግባራችሁንና ኃላፊነታችሁን በሙሉ ተገንዝባችሁ መስራት አለባችሁ።

በስልጣን ምክንያት ለግል ወገን ከማድላትና የራስን ጥቅም ፈላጊ በመሆን እምነትን ከማጉደል በብርቱ ልትጠነቀቁበት የሚገባችሁና ከእኛና ከህዝብም የተጣለባችሁን ከፍተኛ አደራና እምነት ጠብቃችሁ መገኘት የመጀመሪያ ዋና ተግባራችሁ እንዲሆን በአደራ ጭምር አጥብቀን የምናዘው ነው።

በተሰጣችሁ መምሪያና ኃላፊነት መውሰጃ ዝርዝር ውስጥ ሊታረምና ሊሻሻል የሚያስፈልግ ቢኖር ብታመለክቱን በደስታ እንቀበላለን። ተቀብለንም እናቃናለን።

"ከዛሬ ጀምሮ እያንዳንዳችሁ በተመደባችሁበት ሚኒስቴር ተቀምጣችሁ የየክፍላችሁን የስራ ፕሮግራም በቀጥታ ማስተዳደርና መፈፀም አለባችሁ። በየዓመቱ በሕገ-መንግስቱና ለአገራችን እድገት መሻሻልና ብልፅግና ተጠንቶ በተዘጋጀው የአምስት ዓመት ፕላን መሠረት ለሚቀጥለው ዓመት በየክፍላችሁ የምትፈፅሙትን የስራ ፕሮግራም እያዘጋጃችሁ፤ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ተመክሮበት እየቀረበልን ከተፈቀደ በኋላ በዚሁ ፕሮግራም መሠረት ስራችሁን በቀጥታ መምራትና ማከናወን አለባችሁ። የስራ ፕሮግራማችሁን በሚገባ አዘጋጅታችሁ በመልካም ያከናወናችሁ እንደሆነ ችሎታችሁ የሚታወቅበትና የምትመሰገኑበት ነው። ነገር ግን ስራችሁን በሚገባ አቅዳችሁ ማከናወን ቢያቅታችሁ ችሎታችሁ የሚነቀፍበትና ከስራችሁም ተሽራችሁ በምትካችሁ ሌላ ችሎታ ያለው የሚደረግበት ነው። ከፍተኛ ትልቅ ስራና የፖሊሲ፣ የፖለቲካ ጉዳይ በሚያጋጥማችሁ ጊዜ በማናቸውም ሰዓት የምንቀበላችሁ ነን። ባዘጋጃችኋቸውም የስራ ፕሮግራሞች አፈፃፀም የሚገጥሟችሁን የዘወትር ችግሮች ለማቃናት የሚረዳችሁ ጠቅላይ ሚኒስትራችንን ሾመናል። የእርሱም ዋና ተግባር የሚንስትሮቻችንን ስራ ማስተባበርና በመንግስቱም የስራ ፕሮግራሞች አፈፃፀም የሚገጥሙትን ችግሮች እንዲቃኑ ማድረግ ነው። ከፍተኛ የፖሊሲ ጉዳዮች በሚያጋጥሙት ጊዜ ግን እርሱም እንደዚሁ ለእኛ ያቀርብልናል።



አዘጋጅታችሁ የምታቀርቧቸው የስራ ፕሮግራሞችና እነርሱንም የምትፈፅሙበት ሁኔታ ህዝብ እንዲያውቀው ይሆናል። ዞሮ ዞሮ ጠቅላላው ሹማምንት የሆናችሁ ሁሉ ከትልቅ እስከ ትንሽ ኃላፊነታችሁ ለኢትዮጵያ ህዝብ ስለሆነ በአስተዳዳሪነታችሁና በስራ አስፈፃሚነታችሁ ለምትጠየቁበት መልስ የሚኖርባችሁ መሆኑን እወቁ። በሕገ-መንግስቱም ለፓርላማውና ለእኛ ኃላፊ ናችሁ ያልነው ስለዚህ ነው። በህይወታችን ዘመን ሙሉ በራሳችን ላይ የሚደርሰው ጉዳት ሳይሰማን ለተወደደው ህዝባችን፣ለአገራችን ልናደርገው የሚገባን ተግባር ሆኖ የተሰማንን ሁሉ ያለማጓደል የፈፀምን ለመሆናችን ሁሉን አዋቂ የሆነው አምላክ ታዛቢያችን ነው።

እናንተ በመንፈስና በእውቀት በማሰራት በስራ የቀረፅናችሁ ሚንስትሮችና ባለስልጣኖች የተሰጣችሁ ስራ አንድ ጊዜ ከተወሰነ በኋላ ራሳችሁን ችላችሁ ለመፈፀም ከምትበቁበትና እኛም ለኢትዮጵያ ዘለቄታ እድል አስፈላጊዎች በሆኑት ዋናዎች ጉዳዮችና የፖለቲካ አመራር አሳባችንን በሙሉ ለማዋል ከምንችልበት ደረጃ ላይ እንደምንደርስ እምነን ያለማቋረጥ የደከምንበት ስለሆነ ለተሰጣችሁ ግምት የተገባችሁ ሆናችሁ እንድትገኙ ራሳችሁን ለአገራችሁ ለመሰዋት ቆርጣችሁ የጣልንባችሁን አደራ ታላቅ መሆኑን ልታውቁት ይገባል።

ለዚህ አደራ የደረሳችሁ መሆናችሁን የሚመሰክረው እኛ የጣልንባችሁ እምነት ብቻ ሳይሆን፤ እናንተም ራሳችሁ ለህዝቡ አገልግሎትና ለተወደደችው አገራችን እድገት የመሠረትነውን ሁሉ በመፈፀም በዚህ በተቀበላችሁት ስልጣን ወደፊት የምታሳዩት የስራ ፍሬ መሆኑን ልትዘነጉት አይገባም።

ቢሮዋችሁን ቤታችሁ አድርጋችሁ እለት በእለት የሚያጋጥማችሁን ጥቃቅን ጉዳይ ሁሉ ፈፅሙ፤ ከሾምናችሁ ውስጥ ባለፈውም ጊዜ እንደዚህ የሰሩ ነበሩ፤ አሉም። ያለረዳትና የስራ አስተናባሪ አለተውናችሁምና የሰጠናችሁ የቴክኒክ አማካሪዎችና በቢሮ ውስጥ ያሉ ሠራተኞች በወገንነት፣ በዝምድና ብቻ ያልተመረጡ ከሆኑ ትጋት ያገኛሉ። እየተቆጣጠራችሁም ልታሰሯቸው ትችላላችሁ። በስህተታችሁ እየተነቀፋችሁና ለወደፊቱም ትምህርት እየሆናችሁ በመልካም ስራችሁ እየተመሰገናችሁ ኃላፊነታችሁን ይዛችሁ መስራት አለባችሁ።

በዘመድና በዝምድና ብቻ ያልተመረጡ ስንል ዘመድ የሌለው ሰው አይገኝም። በዝምድና እውቀቱ ከመረጠው ዘመዴ ከሆነ ስራ አይግባ ለማለት ምክንያት ሊሆን አይችልም። (እገሌን ስራ ባስገባው "ዘመዱ ነው ወይም ዘመዱ ስለሆነ ስራ አስገባው እባላለሁ" በሚል ስጋት እውቀት ያለው ሰው እንዳይገለል ሊያስጠነቅቁ ነው።)

በስራ ፕሮግራማችሁ አፈፃፀም ያከናወናችሁትንና የገጠማችሁንም ችግር ልትገልፁልን እንድትችሉ በየሳምንቱ እያንዳንዳችሁን ለተወሰነ ሰዓት ተቀብለን እናነጋግራችኋለን፡፡ ነገር ግን ይህ ሰዓት የስራ ፕሮግራማችሁ ከምን እንደደረሰና የፖለቲካም ችግር ቢኖር ለማወቅ የምንረዳበት ጊዜና የምንረዳችሁ ነው እንጂ ራሳችሁ ልትወስኑት የሚገባችሁን ጉዳይ ከእኛ ውሣኔ የምትጠብቁበት ወይም የምታገኙበት ጊዜ አይደለም፡፡...

"በዘመነ መንግስታችንም በተከናወነውና በተፈፀመው ስራና ለወደፊት በመሰረትናቸው ሁሉ ፈጣሪያችንን እያመሰገንን ከፍ ያለ ደስታ ይሰማናል፡፡ ለአገራችንና ለህዝባችን በፈፀምነውና ወደፊት በምንፈፅመው ተግባር ባለን አቅማችን ከመስራት አናቋርጥም፡፡ ብዙ ስራ አለ፡፡

በየእለቱ መፈፀም የሚገባው ስራና እያንዳንዱም ቀን የሚያስከትለው አስቸጋሪ ተግባር የቱን ያህል አስቸኳይና አጣዳፊ መሆኑን ሳንዘነጋ የአገራችን ታሪክ የረጅም ዘመን ጉዞ አልፎ እንደመጣ ሁሉ ወደፊታችንም ያለው ይልቁንም የኑክሌርና ሰውም ወዳልታወቀበት ዓለም የሚላክበት ዘመን የሚያስከትለው ወሰን የሌለው ተግባር መኖሩን አጥብቀን መገንዘብ ይኖርብናል፡፡ (ወደ ሌላ ፕላኔት ማለታቸው ነው) በምንፈፅማቸው ስራ ሁሉ ዛሬ ውሣኔ የምንሰጥበት እያንዳንዱ ጉዳይ በወደፊቱ ላይ ሊያስከትል የሚችለውን በመገመትና በመገንዘብ መስራት አለብን፡፡ ይህ ዛሬ የምንነግራችሁ ቃል በወደፊቱ የኢትዮጵያ ትውልድ ላይ ሊያስከትለውና ሊያኖረው የሚችለው ሁኔታ ሊገመትበት ይቻላል፡፡

ዛሬ የተናገርነው ቃላችን የሚያስገኘው ውጤት ከእኛም በኋላ የሚከተሉን ለሁልጊዜም የሚጠቀሙበት እንደሚሆን እናምናለን፡፡ ሰው ሟች ነው፡፡ እዚህ ያለነው እያንዳንዳችን ለሰራነው ሁሉ በፈጣሪያችን ዘንድና በዚህ ዓለም ዋጋችንን እንቀበልበታለን፡፡

ለህዝብ መሪነትና አስተዳዳሪነት ከባዱን ሸክም የተቀበልነውም ሰዎች ይህንን የጣሉብንን ከፍተኛ አደራ በትክክልና በሚገባ ለመፈፀማችን በህዝባችንና በእግዚአብሔር ፊት ያለብን ኃላፊነት እጅግ ከባድ ነው፡፡ ኢትዮጵያ አገራችንና የተወደደውም የኢትዮጵያ ህዝባችን በደስታና በብልፅግና እንዲኖር ይህንን ኃላፊነት በመገንዘብ በሙሉ ልባችንና ኃይላችን በቅንነት እንድንሰራ ኃያሉ እግዚአብሔር ይርዳን" ብለዋል፡፡ አሜን ብለን እንቀጥል፡፡

ይህንን የአፄ ኃይለስላሴን ንግግር አንብበን እንድናዝንላቸው ወይም ደግነታቸውን እንድንረዳላቸው ወይም ለሌላ ተመሳሳይ ውዳሴ በር ልከፍትላቸው አይደለም ያካተትኩት፡፡ ጥቂት መንግስታት ባዶ ፕሮፓጋንዳ መንዛት ቋሚ ስራቸው እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ነገር ግን የጃንሆይ ንግግር አንድም የሚጣል የሌለው ጠጣር እውነት ነው፡፡



ከዚህ በፊት ያየናቸውን አጫጭር ታሪኮች በሙሉ ጃንሆይን በእጅጉ ከሚተቹ ምሁራንና በከፊል ከሚተቹ ምሁራን ነው የቃረምኳቸው ናቸው፡፡ የአቀራረባቸው መለያየት ብቻ እንጂ ስለተሰሩት ስራዎች የጃንሆይ ንግግርም፣ የምሁራኑም የሚጣረስ አይደለም፡፡

ንጉሡ እንዳሉት "የተሰሩት ስራዎች ለትውልድ ቋሚ እንደሚሆኑ እናምናለን" በትክክል እንደዚያ ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ለመተቸት ያመቸ ዘንድ የተሰሩትን ስራዎች የጃንሆይ ውጤት እንዳይመስሉ "አሜሪካ፣ ጣሊያን፣ እንግሊዝ፣ ፈረንሣይ፣ ... ወዘተ ናቸው የሰሯቸው" በሚል መነሻ ጃንሆይን ዋጋ ቢስ ለማድረግ ይሞከራል፡፡

አዎ! እንዳየነው እያንዳንዱ ዘመናዊ ስራ የሰልጡን አገሮች አሻራ አለበት፡፡ ታዲያ ከየት ይመጣል? ምሁር የለ ምን የለ! ትምህርት ቤት ተሰርቶ በነጮች የበላይነት ይተዳደር ነበር፡፡ ኢትዮጵያ የራሷ ምሁራን እስኪኖሯት ድረስ፡፡ አየር መንገድ ተመስርቶ በአሜካኖች የበላይነት ተመርቷል፡፡ ኢትዮጵያ የራሷ ባለሙያዎች እስኪኖሯት ድረስ፡፡ አውራጎዳናም እንደዚያው፣ ሌላውም በተመሳሳይ፡፡ አንድ አፍሪካዊ መሪ የነበረው ብቸኛ አማራጭ ይሄው ነበር፡፡ እርዳታውም ያስፈልግ ነበር ለምነዋል፡፡ ብድሩንም እንደዚያው፡፡ እኛን ቢገድሉንም፣ ቢያድኑንም ዛሬ ድረስ ነጮች ናቸው፡፡ ይህችን አገር ሙሉ ለሙሉ በጦር ይዘው አይግዟት እንጂ በምሁርነትና በርእዮተዓለም ሽፋን ሲያሽከረክሯት ኖረዋል፡፡ ይሄ ሁሉ የምን ችግር ነው? ኢትዮጵያ የራሷ ምሁራን ስለሌላት ብቻ፡፡ ጃንሆይ ይሄን ለመቅረፍ ጥረዋል፡፡ ወደፊትም ትምህርት ላይ ካልተተኮረ ይህች አገር ታሪኳን ስትደግም ትኖራለች፡፡ ትምህርት ሲባል ግን ‹‹አለምን በመርከብ የዞረው ማነው፣ አውሮፕላንን የሰሩት ወንድማማቾች ስማቸው ማን ይባላል፣....››እየተባለ የሚደሰኮረውን አይነት ትምህርር አይደለም፡፡ ስለነሱ ለማወቅ ከመማር ያለፈ ት/ት ያስፈልጋል፡፡የሰሪውን ስም ሳይሆን ያሰራሩን ጥበብ እንደማለት፡፡ እናም.... የጃንሆይን ጅምር ልናበረታታው እንጂ ልናጣጥለው ይከብዳል፡፡

ዙፋኑን የገዘገዘው ሙስና

የቀደምቶቹም ሆነ የአሁኑ ዘመን ኢትዮጵያውያን አቶ ብርሃኑ ድንቄን ጠንቅቀው ያውቋቸዋል፡፡ ለማያውቋቸው አንባብያን ለመግለፅ ካስፈለገ "አቶ ብርሃኑ ድንቄ ድንቅ ኢትዮጵያዊ ናቸው" ብዬ በድፍረት እገልፃቸዋለሁ፡፡

አቶ ብርሃኑ ድንቄ በዚያ ዘመን አገላለፅ ከአፈር ተነስተው በልዩ ልዩ የስራ ዘርፍ አልፈው አምባሳደር መሆን የቻሉት በጃንሆይ መልካም ፈቃድ ነበር፡፡ ነገር ግን በስተመጨረሻ ጃንሆይ ሊያስገድሏቸው ለአመታት ሞክረው ሳይሳካላቸው ቀርቷል፡፡

ከተራ ትኬት ቆራጭነት ጀምረው በአሜሪካ የኢትዮጵያ አምባሳደርና ባለሙሉ ስልጣን እንደራሴ መሆን እስከቻሉበት ጊዜ ድረስ በበርካታ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ተመድበው ሲያገለግሉ፤ በተመደቡባቸው መስሪያ ቤቶች ሁሉ ከፍተኛ ምዝበራ ይካሄድ እንደነበር ይነግሩናል፡፡ እዚህ ላይ ቀድሜ ለአንባብያን በአፅንኦት መግለፅ የምፈልገው ጉዳይ አለ፡፡ ይኸውም አንባብያን በአንድ የብርሃኑ ድንቄ ገጠመኝ ብቻ ሳትወሰኑ በየመንግስት መስሪያ ቤቱና በየአገልግሎት ሰጭ ተቋማቱ አቶ ብርሃኑ ያሳዩዋቸው ሌሎች ከፍተኛ ምዝበራዎች ምን እንደሚመስሉ በጥምረት ማሰብ ሞክሩ፡፡

ተከታዩን ታሪክ በዚህ መፅሐፍ ለማካተት ያስፈለገኝ ታሪኩ በአንድ መፅሐፍ ብቻ ተካቶና ተወስኖ መቅረቱ ስለከነከነኝ ነው፡፡ ማለትም ከረጅሙ የኢትዮጵያ ታሪክ ጋር ቢካተት ብዙ ነገር ያስገነዝባል ብዬ ስላመንኩ ነው፡፡

ሙሉውን ታሪክ የፈለገ አንባቢ "ቄሣርና አብዮት" በሚል ርዕስ በአንድ በኩል፣ በጀርባዋ ደግሞ "አልቦ ዘመድ" በሚል ርዕስ የተጠናቀረች ሆና በሁለቱም በኩል 145 ገጾች ያሏት ትንሽዬ፣ ነገር ግን ግዙፍ የሆነች መፅሐፍ በቀላሉ አግኝቶ ማንበብ ይችላል፡፡ የታተመው በ1987 ዓ.ም ነው፡፡ ያነበባችኋት ካላችሁ ግድየለም፡፡ ሁለት አማራጭ መሆኑ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን ቢጠቅም እንጂ አይጎዳም፡፡ በጃንሆይ ጊዜ ተደርጎ ያለፈ ብቻ ስላይደለና አሁንም ድረስ በከፍተኛ ሁኔታ ተስፋፍቶ ስለሚገኝም ልዩ ትኩረት መስጠቱ ተገቢ ነው፡፡

"ቄሣርና አብዮት" ውስጥ በመግባት ከዚህ ንዑስ ርዕስ /ሙስና/ ጋር ግንኙነት ያለውን ብቻ እየመረጥኩ አቀርባለሁ፡፡ አቶ ብርሃኑ ድንቄ በአንደኛ መደብ የትረካ አንፃር "እኔ" እያሉ ነው የተረኩት፡፡

እንግዲህ ጃንሆይን በተመለከተ ቀደም ሲል መንግስታዊ አወቃቀራቸውና የሚኒስትሮች የስራ ስምሪት፣የመስሪያ ቤቶች አላማና ተግባር፣ጅምር ስለመሆናቸው እንዲሁም ለባለስልጣናቱ ስለተሰጡት አደራዎች ብዙ ነገር አይተናል፡፡ከዚያስ? የሚለውን ነው የምናየው፡፡ አቶ ብርሃኑ ድንቄ የሚገጥሟቸውን ሙሰኞች ስማቸውን እስከነአባት፣እስከነማዕረጋቸው እንደወረደ ጠቅሰው ፅፈዋቸዋል፡፡በዚህ መፅሐፍ ያባትን ስም ባለመግለፅ ለመራራት ተሞክሯል፡፡መጥፎ ስራ የሰሩትን ለማለት ነው፡፡

ለማንኛውም ክቡር አቶ ብርሃኑ ድንቄ በመፅሐፋቸው መግቢያ ካሰፈሩዋቸው ሐተታዎች ጥቂት አረፍተ ነገሮችን ላስቀድምና ልቀጥል፡፡

"... ቄሣርና አብዮት በሚል ስያሜ ይህችን መፅሐፍ ለማሰናዳት ስሞክር የአፄ ኃይለስላሴን ውድቀትና የአብዮቱን አሸናፊነት እያጋነንሁ



የምተርክ መስሏቸው አንባብያን በውሸት ተስፋ እንዳይጠባበቁ አስቀድሞ ማስጠንቀቅ ይኖርብኛል፡፡

"... አንዳንድ ሰዎች በአሁኑ ጊዜ ስለ አፄ ኃይለስላሴ መናገር ወይም መፃፍ የሚያሳፍር ነገር መስሎ ሊታያቸው ይችላል፡፡ በእኔ አስተያየት ይህ ታላቅ ስህተት ነው፡፡ መጪው ትውልድ ስለኒህ ሰው ውነተኛውን ታሪክ ለማወቅ ያለውን መብት መንፈግ ከቶ አይገባንም፡፡

"ይችን መፅሐፍ ለማሰናዳት ያለኝን ኀሳብ ያካፈልኩት አንድ ኢትዮጵያዊ ወዳጄ በጉዳዩ ተገርሞ የሰጠውን ሐተታና የተለዋወጥነውን ንግግር ሳልጠቅስ አላልፍም፡፡

"አቶ ብርሃኑ ያ ሁሉ ችግር፣ መከራ፣ ስደት፣ የሐብት መወረስ፣ የቤትና የንብረት መፍረስ ከደረሰብዎ በኋላ፣ አሁን ስለ አፄ ኃይለስላሴ መፅሐፍ እጽፋለሁ ብለው ጊዜዎን ለምን በከንቱ እንደሚያጠፉ አይገባኝም፡፡ ... ምናልባት ጠላታችሁን ውደዱ የሚለውን ወርቃማ ሕግ ለመፈፀም ይሆን" ሲሉ አቶ ብርሃኑ እንዲህ ይመልሳሉ፡፡

"ወዳጄ ሆይ ጠላትን መውደድ ምንም እንኳ አስቸጋሪ ነገር ቢሆንም፤ ስለእርሱ የምናውቀውን እውነት መናገር ይህን ያህል የሚያስደንቅ ሞያ ሆኖ አላገኘውም፡፡ በእርግጥ ዛሬ በኢትዮጵያ ያለው ፕሮብሌም ይህ ነው፡፡ አንድ ሰውን የጠላን እንደሆነ የጥላቻችንን ምክንያት በመናገር ፋንታ የሌለውን ነገር ፈጥረን በእርሱ ላይ ስናወራ እንደሰታለን፡፡ ይህ ታላቅ የሞራል ውድቀት ይባላል፡፡ የእኔ ሙከራ ስለአፄ ኃይለስላሴ በምናውቀው መጠን እውነተኛውን የታሪክ ቅርስ ለሚመጣው ትውልድ ለማቆየት ብቻ ነው፡፡" ...

"... አገራችን ኢትዮጵያ የሚጠብቃትን የፖለቲካ ትርምስ አስቀድሞ በመገንዘብ የወደፊቱን ችግር ለማቃለል የሚቻለው አፄ ኃይለስላሴ ስልጣናቸውን በሕገ-መንግስት ወስነው እንደ ምዕራባውያን ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ ህዝብ በመንግስቱ ጉዳይ በቀጥታ ተካፋይ እንዲሆን ሲፈቅዱ ብቻ መሆኑ ስለታየኝ ይህንኑ ደጋግሜ አመልክቻቸው ነበር፡፡ ግን እርሳቸውን በመደለል መጠቀም የለመዱ ሹማምንቶቻቸው ኀሳቡን ሳይደግፉት ስለቀሩ በመጨረሻ ግልፅ ደብዳቤ እንድፅፍላቸው ተገደድሁ፡፡

ይህ የእኔ ግልፅ አቋም አፄ ኃይለስላሴን በብርቱ ስላስቀየማቸውና ስላስቆጣቸው በሚስጥራዊ የፀጥታ ጠባቂዎቻቸው አማካይነት ህይወቴን ለማስጠፋት ዘጠኝ አመታት ያህል ተከታትለውኛል፡፡ ግን በእኔ ላይ ስላመጡብኝ መከራና ጭንቀት ለመበቀል ወይም በልዩ ልዩ ምክንያት ይጠሏቸው የነበሩትን ሰዎች ለማስደሰት ስል በዘመነ መንግስታቸው የተመለከትሁትን ሁሉ አጣምሜ ባቀርብ የታሪክ ቅርስነቱ ስለሚቀር ኃላፊነቱ ይሰማኛል፡፡ ከዚህም በቀር ከመቃብር በታች ድንጋይና አፈር

ተጭነውት አፉን ዘግቶ፣ ትንፋሹ ጠፍቶ ስለሚገኝ ሰው በምንናገርበት ጊዜ የሚከተለውን ማሰብ አለብን፡፡

1ኛ. ሟቹ የራሱን ወገን የመከላከያ ታሪክ ለማቅረብና ምስክርነታችንን ለማስተባበል እድል የለውም፡፡

2ኛ. በምንም ሊዛነፍ የማይችለው መለኮታዊ ሕግ ነገ በእኛም ላይ ተጠቅሶ በፈረድንበት እንዲፈረድብን ሊያደርግ ይችላል፡፡ ስለዚህ ሌላው ቢቀር በወቀሳችን ተቀይሞ ይበቀለናል ወይም በምስጋናችን ተደልሎ ውለታ ይከፍለናል ብለን ስለማንጠብቀውና ወደ ትቢያነት ስለተመለሰው ሰው ያለፈ ህይወት እውነትን ለመናገሪያ ከአሁን የተሻለ ምን ጊዜ አለ?" ብለው ይጠይቃሉ፡፡

"ይህ መፅሐፍ" ይላሉ አቶ ብርሃኑ "ይህ መፅሐፍ የአፄ ኃይለስላሴ የፍትሐት ማሳረጊያ ቡራኬ አለመሆኑን ለመግለጥ የአንባቢን ትኩረት መጥራት እፈቅዳለሁ፡፡ ለምሳሌ ስለመንግስታቸው አቋም፣ ስለ ትምህርት ቤቶች፣ ስለአገር አገዛዝ፣ ስለፍርድ ቤቶች፣ ስለውጪ አገር ፖሊሲ፣ ስለኢኮኖሚ ፕላን... የተናገርሁት ነገር የለም፡፡ በተለይ አንባቢን ለመርዳት ያሰብሁት፣ የመንግስታቸው ክፍል በነበርሁበት ጊዜ የተመለከትኳቸውን የተወሰኑ ድርጊቶች እንደ ዓይን ምስክር ለማቅረብ ነው፡፡ ይህ በማድነቅም፣ በመንቀፍም ሊሆን ይችላል..." እያሉ ይቀጥላሉ፡፡

አቶ ብርሃኑ ድንቄ ለአፄ ኃይለስላሴ በስተመጨረሻ እዚያው አሜሪካ ሆነው የፃፉት ድፍረት የተሞላበት ግልፅ ደብዳቤ አለ፡፡ አቶ ብርሃኑ በዚች መፅሐፋቸው ባያካትቷትም እኔ በቀላሉ ማግኘት ስለቻልኩ ወደበኋላ አስገባታለሁ፡፡ እኒህ "ምሁር" ይችን መፅሐፍ የፃፏት ስለሙስናው ብቻ ማውራት ፈልገው አይደለም፡፡ ከልጅነታቸው ጀምሮ ... ከጃንሆይ ጋር እንዴት እንደተዋወቁ ... ወዘተ ... እየተረኩ በሰራው ዓለም የገጠማቸውን ሲያሳዩን የምናገኘው ነው፡፡ ስለዚህ የእኔ ስራ ሙስናውን መልቀምና ይዘቱን ባልለቀቀ አተራረክ ደግሞ ማሳየት ነው፡፡ ይህችን አገር አወዛውዞ አወዛውዞ ከስሯ መንግሎ ሊጥላት የሚችለውና እያወዛወዛትም ያለው ይሄው ጉዳይ ስለሆነ ነው፡፡ ኢትዮጵያ በህይወት እስካለች ድረስ መንግስታት ሊያተኩሩበት የሚገባ ዋነኛ ነጥብ ንቅዘት! ለዚህ የግድ ሰፊ ሽፋን መሰጠት አለበት፡፡ ሌላው ነገር ሁሉ ቢቀር ይሻላል ባይ ሆኛለሁ፡፡

ከነፃነት በኋላ እንደነአቶ ብርሃኑ ድንቄ ላሉ ወይ አርበኛ ወይ ስደተኛ ላልነበሩ ሰዎች ስራ ማግኘት ከባድ ነበር፡፡

ወ/ሮ ሸዋረገድ ገድሌ በወረራው ዘመን በፈፀሙት ስራ ሳቢያ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ተሰሚነት ያላቸው ሆነው ነበር፡፡ ከአቶ ብርሃኑ ድንቄ ጋር ትውውቅ ነበራቸውና ሊጠይቋቸው በሄዱ ጊዜ ወ/ሮዋ "ብርሃኑ



ባለፈው አዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ የፃፍከውን አነበብሁት፤ በጣም ጥሩ ኀሳብ ነው" እየተባባሉ ጥቂት ተጫወቱ፡፡

አቶ ብርሃኑ ድንቄ በልጅነታቸው የቤተ-ክህነቱን ትምህርት ፋት አድርገውታል፡፡ "እያሌ ዓመታት ዘግይቼ የፈረንሣይ ቋንቋ ካወቅሁ በኋላ ከሰመጥሩው ደራሲ ከቮልቴር የተፃፈ መፅሐፍ ሳነብ የእስተሳሰባቸውን እድማስ ጠባብ አድርገው ለሚኖሩ ሰዎች ማዘን ጀመርኩ" በማለትም በልጅነታቸው ከእንጦጦ በቀር ሌላ አድማስ ያለ አይመስላቸው እንደነበር ይነግሩናል፡፡ ያች የልጅነት ጠባብ አእምሮ በየጊዜው እየሰፋች ሄዳ ነው እንግዲህ ኀሳባቸውን በብዙሃን መገናኛ ወደማስራጨትና ሌሎችን ወደማስደመም የደረሰችው፡፡

ስራ ያልነበራቸው አቶ ብርሃኑ ድንቄ አንዳንድ ጠቃሚ የሆኑ በኢጣሊያ ቋንቋ የተፃፉ ፅሁፎችን መተርጎም የሚችሉበት ስራ ቢገኝላቸው ይመርጡ ነበር፡፡ ጣሊያንኛ ለምደው ነበርና፡፡ ሆኖም በመጀመሪያ የተገኘው ስራ በተሽከርካሪ መኪና ክፍል ገንዘብ ተቀባይነት የነበረ ሲሆን፤ እሱም በሸዋረገድ ገድሌ ጥረት የተገኘ ነው፡፡

ከባባድ መኪናዎች እቃ ጭነው ከአንድ አውራጃ ወደ ሌላ አውራጃ ለመሄድ ከአገር ግዛት ሚኒስቴር ፈቃድ መጠየቅ ነበረባቸው፡፡ የሚከፍሉት ቀረጥም እንደየርቀቱ ይወሰናል፡፡ ባለቤቶቹም ከመዘጋጃ ቤት የተሰጣቸውን የባለቤትነት ማስረጃ ከማቅረብ ጀምሮ ልዩ ልዩ መመዘኛዎችን ማሟላት ይጠበቅባቸዋል፡፡

- የአገር ግዛት ሚኒስቴር ዋና ዳይሬክተር የነበሩት የፊት አውራሪ ደምሴ ወንድም አቶ ኃይሌ ግን መቶ መቶ ብር ጉቦ እየተቀበለ ይሸኛቸዋል እንጂ ብዙዎች መመዘኛውን አሟልተው ማቅረብ የማይችሉ ነበሩ፡፡ እንዳንዱ ካሚዮን ከጣሊያን በዘረፋ የተገኘና በአፈሳ የተወሰደ ነበር፡፡ አቶ ኃይሌ ቀደም ሲል ፀሐፊም፣ ገንዘብ ተቀባይም ሆነው ነበርና የሚሰሩት፤ አቶ ብርሃኑ የገንዘብ ተቀባይነቱን ስራ ሲይዙ ባለመኪኖችን ማስረጃ በሚጠይቁ ጊዜ 50 ብር ለአቶ ብርሃኑ፣ 50ብር ለአቶ ኃይሌ ሊያካፍሉ ሞከሩ፡፡ አቶ ብርሃኑ "አይደረግም!" አሉ፡፡ ኃይሌ ሊያግባባቸው ሲሞክር ተቆጡት፡፡ "በጭራሽ!" ሲሉም አረጋገጡለት፡፡

የአገር ግዛት ሚኒስቴር ዋና ፀሐፊ የነበሩት አቶ ኃይሌ መርሻ የአቶ ብርሃኑን ሁኔታ ሰምተው አድናቆታቸውን ቸሩ፡፡ ኃይሌ ግን ለወንድሙ ለፊት አውራሪ ደምሴ ተናገረ፡፡ አቶ ብርሃኑ እንዲህ ይሉናል፤ "በ5ኛው ቀን ዋናው ዳይሬክተር ይጠሩሃል ተብዬ ተነገረኝ፡፡ እኔ ደግሞ ስለእምነቴ ማን ነግሯቸው ይሆን? ምስጋና ሊሰጡኝ ይሆናል እያልኩ አስብ ነበር፡፡ ... ከቢሮዋቸው እንደገባሁ እጅ ነስቼ ከፊታቸው ቆምሁ፡፡ ... ግንባራቸውን ቁጥር አድርገውታል፡፡ በቁጣ መልክ ትክ ብለው እኔን እያዩ፤

"ማን ትባላለህ?" አሉኝ፡፡

"ስሜ ብርሃኑ ድንቄ ነው" ብዬ መለስኩላቸው፡፡

"ማነው ይሄን ስራ የሰጠህ?"

"ዋናው ፀሐፊ አቶ ኃይሌ መርሻ ናቸው፡፡"

ወደ ፐርሰኔሉ ሹም ፊታቸውን ዘወር አደረጉና ... "በል አሁን በእጁ ያለውን ማናቸውንም ገንዘብና ማስረጃ ሁሉ ተረክበው" ብለው ከቢሮዋቸው አስወጡኝ፡፡ ምስኪን ብርሃኑ! ምን ማድረግ ይቻላል? ጠመንጃ ይዞ እያስፈራራ የሚቀማ ወንበዴ በድንገት ሳልጠነቀቅ እንዳነቀኝ እንጂ ከአንድ የመንግስት ባለስልጣን ፊት እንደቆምሁ ለማሰብ በፍፁም አልቻልኩም፡፡ ልሳኔ ተሳሰሮ፣ አፌ በፍርሐት አመድ ቅሞ፣ ፊቴ በቁጣ ደም ለብሶ፣ ሰውነቴ እየተንዘፈዘፈ በእጄ ያለውን ማናቸውንም ገንዘብና ማስረጃዎች ወዲያው አስረክቤ ከአገር ሚኒስቴር አዲሱ ስራዬ በአንድ ሳምንት ውስጥ ተሰናበትሁ፡፡ እንግዲህ ይሄን ለማን ያዋዩታል? ያ ነፃነት የሚባለው ትርጓሜው ምንድነው? እያልኩ ብቻዬን ማልጎምጎም ብቻ ሆነ!..." አንድ በሉ እንግዲህ፡፡...

"የቤተ-ክህነት ሰው እንደመሆኔ መጠን ህይወቴ ሰላምና ፀጥታ ማግኘት የሚችለው በማስተማር ላይ መሆን አለበት ብዬ አስብ ነበር፡፡ ግን አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የደራሲነት ፍላጎት ይመጣብኛል፡፡ በህይወት ላይ የሚያሳዝን ወይም የሚያስደስት ነገር ስመለከት በፅሁፍ ለመግለጥ እሞክራለሁ፡፡ ግን የመንግስት ሹም እሆናለሁ ብዬ ከቶ አስቤ አላውቅም ነበር፡፡

"የኑሮ ፍላጎት አስገድዶኝ በአገር ግዛት ሚኒስቴር ከያዝኩት ስራ ፊትአውራሪ ደምሴ በግፍ ባባረሩኝ ጊዜ የደረሰብኝ የመንፈስ ቁስል በቶሎ ሊድን አልቻለም፡፡ አገር፣ ነፃነት፣ ትክክልነት፣ ወንድማማችነት፣ ፍትህ ... የሚባሉት እንደኔ ያሉትን ተራ ሰዎች ለመደለያና ለማጭበርበሪያ የተፈጠሩ ቃላት እንጂ ከእውነተኛ ህይወት ጋር ምንም የተያያዘ ነገር እንደሌላቸው ለመመልከት ስላጋጠመኝ ሁሉንም በኑፋቄ ዓይን ማየት ጀመርሁ፡፡ ይሄን ግብዝነት እንዴት ነው የማጋልጠው? እያለኩ በብርቱ አስብ ነበር፡፡ ስለዚህ አልፎ አልፎ በውስጠ ወይራ አማርኛ ምሬቴን የሚገልጥ የጋዜጣ አንቀፅ እየፃፍኩ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ማሳተም ጀመርሁ፡፡..." ይሉናል፡፡

አቶብርሃኑ ድንቄ የሚፅፉትን ጽሁፍ ውስጠ ወይራው የገባቸው "ብርሃኑ የምትለው ገብቶናል" እያሉ የጥቅሻ ምልክት ያሳዩዋቸው እንደነበርም ፅፈዋል፡፡

"በህዳር 21 ቀን በየዓመቱ የፅዮን በዓል በአባቴ ቤተ-ክርስቲያን በወጨጫ ማርያም ስለሚከበር አባቴ እጣን ሞገር ቅኔ እንድቀኝ



ጠየቁኝ፡፡..." የተቀኙትን ከግዕዝ ወደ አማርኛ ተርጉመው እንዲህ አስፍረውታል፡፡

"በኢትዮጵያ የብዙ ሰዎችን ደም የጠጣው ጦርነት አለቀ፡፡
ግን ረቂቅና ብርቱ የሆነ የሠላም ጊዜ ጦርነት ተከቷል፡፡
በመሪያችን በኃይለስላሴ እናምናለን፡፡
አድሎአዊነትንና ጉቦኝነትን በሕግ ተቆጣጥሮ
ድል አድራጊነቱን አሁንም እንዲያረጋግጥ፡፡"

ይህ ቅኔ በአዲስ ዘመን ታትሞ ወጣ፡፡ ብርሃኑ ድንቄ ተደነቁበት፡፡ ጃንሆይ ጋዜጣ ሲያነቡ አዩትና ከ15 ቀን በኋላ አቶ ብርሃኑን ቤተ-መንግስት አስጠሯቸው፡፡ ኮሎኔል አብይ /በኋላ ጄኔራል/ ይዘው ወደ ጃንሆይ ቢሮ ማስገባት፡፡ አቶ ብርሃኑ በድንጋጤ በግንባራቸው ተደፍተው እጅ መንሳት፡፡

"ብርሃኑ ድንቄ አንተ ነህ?"

"አዎን ጃንሆይ"

ጠረጴዛው ላይ ያለውን ጋዜጣ አንስተው የግዕዙን ቅኔ ደግመው አነበቡት፡፡ "በአነባበባቸው እንደተመለከትኩት ግዕዝ ስለማይችሉ ብዙ ስህተት አድርገዋል" ይሉናል አቶ ብርሃኑ፡፡

"ቅኔ ማነው ያስተማረህ?"

"አባቴ ሊቀ ጠበብት ድንቄ የቅኔ መምህር ናቸው፡፡"

"ድንቄ የራጉኤሉ? ስላባትህ ሀሩይ ይነግረን ነበር፤ ሀሩይን ታውቀዋለህ?"

"እዎ ጃንሆይ፤ ያባቴ ጓደኛ ነበሩ፡፡"

"በጣሊያን ጊዜ ምን ትሰራ ነበር?"

"አስተርጓሚ ነበርሁ ጃንሆይ፡፡"

"የኢጣሊያ ቋንቋ የት ተማርህ?"

"ከትምህርት ቤት አልሄድሁም፤ በራሴ ነው የተማርኩት፡፡"

"ከኢጣሊያ ወደ አማርኛ መፅሐፍ መተርጎም ትችላለህ?"

"እዎ ጃንሆይ፡፡"

"ይገርማል! አሁን ምን ትሰራለህ?"

"ስራ የለኝም ጃንሆይ፡፡"

በዚህ ጊዜ ጃንሆይ "አብይ ማስታወሻ ያዝ" ሲሉ አቶ ብርሃኑ እጅ ነስተው ይሰናበታሉ፡፡ "ሰዓቱ ትልቅ ትዝታ ነው ትቶልኝ ያለፈው ..." ይሉታል ይህንኑ ክስተት፡፡

ከቀናት በኋላ ከኮሎኔል አቢይ አበበ ቢሮ ተጠርተው ወደ ጽህፈት ሚኒስቴር የተፃፈ ደብዳቤ ተሰጣቸው፤ እንዲህ ይላል፤

"አቶ ብርሃኑ ድንቁ በግርማዊነታቸው መልካም ፈቃድ የወላሞ አውራጃ ግዛት ዋና ፀሐፊ ሆነው መሾማቸውን እንዳስታውቅዎ ስለታዘዝሁ ይህንኑ ለአገር ግዛት እንዲያስተላልፉላቸው በማክበር አሳስባለሁ፡፡"

በወቅቱ የሲዳሞና የወላሞ /በአሁኑ አጠራር የወላይታ/ ጠቅላይ ገዥ ሆነው የተሾሙት ራስ አበበ የነበሩ ሲሆን "አሳሽ" የሚባሉ ሹማምንት በስራቸው ሆነው የአካባቢውን ግዛቶች ያስሱ ነበር፡፡ "አሳሽ" በቀድሞው ልምድ የዋናው ሹም ወኪል ነው፡፡ ዋናው አዛዥ እስኪመጣ ያዛል፣ ያስገብራል፣ ያሥራል፣ ይፈታል፣ ይቀጣል...፡፡

በአዲሱ የአገር ግዛት ደንብ ግን ቀርቷል፡፡ ስለዚህ ራስ አበበ ከሕግ ውጪ "አሳሽ" ሾመዋል፡፡ የራስ አበበ የወላይታ አሣሽ ፊትአውራሪ ተሰማ ይባላሉ፡፡
አቶ ብርሃኑ ድንቁ ጉድ አዩ! ዘረፋ፣ ግድያ ... ግፍ ይፈፀማል ከሕግ ውጪ፡፡ እንደ አቶ ብርሃኑ አገላለፅ "በየቀኑ ሦስት ሰው ሳይሞት አይውልም" "የሚዘረፈውን ሐብት ለመገመት ያስቸግራል" ሲሉም ይነግሩናል፡፡

የእረመኔው የፊት አውራሪ ተሰማ ስም ሲጠራ የማይበረግግ የለም፡፡ አቶ ብርሃኑ የአውራጃ ግዛት ዋና ፀሐፊ ሲሆኑ፣ የወላይታ ገዥ ደግሞ /ጠቅላይ ገዥ አይደለም/ ፊትአውራሪ ግርማ ነበሩና "ይህን ሁሉ እየተመለከትኩ ዝም ብዬ መኖር አልችልም" ይሏቸዋል ለፊትአውራሪ ግርማ፡፡ "ታዲያ ምን ማድረግ ትችላለህ?"

"አንድ ረዥም ሪፖርት ለግርማዊነታቸው ልፃፍና ፈርመውበት ወደ አዲስ አበባ ይላክ፡፡"

"ብርሃኑ፣ እኔ አዋቂ ሰው መስለኸኝ ነበር፡፡ ለካ ልጅ ኖረሃል" ብለው ሳቁባቸው፡፡

አቶ ብርሃኑ ለወላይታ ባላባቶች ለፊታውራሪ ደስታ ጦና እና ለፊትአውራሪ ገብረስላሴ ጦና ወደ አዲስ አበባ የሚላክ ሰው እንዲያዘጋጁ በሚስጥር ነግረው ተከታዩን ደብዳቤ ላኩ፡፡

"ግርማዊነትዎ ከማይታወቅ ስፍራ ፈልገው ይህን ሹመት ስለሰጡኝ የማመሰግንበት ቃል ያጥረኛል፡፡ ግን ሹመት የተሰጠኝ ደመወዜን እየተቀበልሁ በምቾት ለመኖር ብቻ እንዳይደለ አውቃለሁ፡፡ ከፍ ያለ ኃላፊነት አለብኝ፡፡ እዚህ እወላሞ ከደረስሁ 30 የሚያህሉ ሰላማውያን ሰዎች በአርበኞች ተገደሉ፡፡ ዘረፋው በየቀኑ ይቀጥላል፡፡ አንድ መቶ ባላገሮችና ባላባቶች ፊት አውራሪ ተሥማ በተባለው በራስ አበበ አሳሽ እጅ ታስረው ይማቅቃሉ፡፡ የወላሞ ህዝብ የወተት ላሙን ሳይቀር ይገብራል፡፡ ያ አዲስ ዘመንና ነፃነት የምንለው ትርጓሜ የሌለው ባዶ ቃል ሆኗል፡፡ የግርማዊነትዎ ሹም መሆኔ ቀርቶ ተራ ሰው ብሆንም ይህን አሰቃቂ ግፍ ዝም ብል የኢትዮጵያ አምላክ ይፈርድብኛል፡፡ በዚህ ጉዳይ ከአገረ ገዥው ከፊት አውራሪ ግርማ ጋር አልተስማማንም፡፡ ግን እኔ ህሊናዬ የሚያዘኝን አድርጌያለሁ፡፡ ይኸውም ለግርማዊነትዎ ማመልከት ነው፡፡ ግርማዊነትዎ ከማናችንም ይልቅ ታላቅ ኃላፊነት ስለተሰጠዎ ይህን ግፍ ከወላሞ ህዝብ እንዲያስወግዱለት ዝቅ ብዬ እለምናለሁ፡፡"

አቶ ብርሃኑ ይህን ጽፈው ከግንብ ጋር እንደመላተም ቢቆጥሩትም፣ አንድ ነገር በውስጣቸው ያውጠነጥኑ ነበር፡፡ "ጃንሆይ እንደ ሌሎች ሹሞቻቸው ስለ ፍትህ ስሜት የሌላቸው ሆነው ከተገኙ የመንግስት ስራ ለእኔ አይደለም!"....

መልሱ መጣ፡፡

"አቶ ብርሃኑ ድንቁ፣

ለግርማዊነታቸው የፃፉት ራፖር ደርሶ ተመልክተውታል፡፡ ጉዳዩን በጥንቃቄ ተከታትለው በማመልከትዎ ግርማዊነታቸው እንደተደሰቱ እገልፅልዎት ዘንድ አዘውኛል፡፡ ፊት አውራሪ ተሠማ በቶሎ ወደዚህ እንዲላክ ለራስ አበበ ትዕዛዝ ተላልፏል፡፡

ከሠላምታ ጋር፡፡"

የወላይታ ባላባቶች እነፊታውራሪ ደስታ ጦና የደብዳቤውን መልስ ሰምተው ኖሮ ወደ አቶ ብርሃኑ ሄደው "እንኳን ደስ ያለን!" ሲሉ "ምን ተገኘ ደግሞ" አቶ ብርሃኑ፡፡

"መቼም እናንተ አማራዎች ሁሉን ሚስጥር ማድረግ ትወዳላችሁ" በደስታ ተቃቀፉ፣ ተሳሳቁ፡፡ የወላይታ ህዝብ የወተት ላሙን መገበር ቀርቶ ቅንጣት ችግር እንድትደርስበት አይፈለግም፡፡ ነገር ግን ማን አለብኝ ባዮች ከሕግ ውጪ ይዘርፋሉ ይገድላሉ፡፡ ፊትአውራሪ ተሠማ ደንግጠ አሉ፡፡ ራስ አበበ ንዴታቸውን በውስጣቸው ይዘው ከይርጋለም ወደ ወላይታ ሰደ መጡ፡፡ ችሎት ሰይመው አቶ ብርሃኑን ጠሩ፡፡

"አሁን የጠራንህ በቅርብ ጊዜ እዚህ አገር ስለሞቱት ሰዎችና ስለተዘረፈው ንብረት አላፊው ፊትአውራሪ ተሠማ ነው ብለህ ለጃንሆይ ስለፃፍህ ሁለት ጥያቄዎች ልንጠይቅህ ነው፡፡

1ኛ. ምን ማስረጃ አለህ?

2ኛ. መጀመሪያ ለእኛ ሳታመለክት ለጃንሆይ የፃፍክበት ምክንያት ምንድነው?"

አቶ ብርሃኑ ይቀጥላሉ፣ "ክቡር ሆይ በዚህ ጉዳይ እኔ ከሳሽ ወይም ተከሳሽ አይደለሁም፡፡ ደረጃዬ ዝቅ ቢልም የመንግስት ሹም ነኝ፡፡ ስለዚህ ለግርማዊነታቸው በፃፍኩት ራፖር ምክንያት በችሎት ቆሜ መልስ እንድሰጥ የተጠየቅሁት ያለአግባብ ነው፡፡ በፅህፈት ቤት በኩል ነገሩን ከቡርነትዎ ለመረዳት ቢፈቅድ ለማብራራት ፈቃደኛ ነኝ፡፡"

"ሰው እየከሰሱ መልስ አልሰጥም ማለት የት አለ!"

"ክቡር ሆይ እኔ ማንንም አልከሰስሁም፡፡ እኔ የግል ዘመድ አልተገደለብኝም፡፡ እኔ የግል ሐብት አልተዘረፈብኝም፡፡ ሀብታቸውን የተቀሙት፣ ዘመዶቻቸው የተገደሉባቸው ሰዎች ዳኝነት በተሰጣቸው ጊዜ ክሳቸውን እንደሚያቀርቡ አልጠራጠርም፡፡ እኔ በሹመተ ኃላፊነቴ የፃፍኩት ሪፖርት እውነት ቢመስልዎ ተቀበሉት፡፡ እውነት ባይመስልዎ ሊተውት ይችላሉ፡፡"

"ቆይ የሚሆነውን እናስታውቅሃለን፡፡" ብለው ከችሎት ተነሱ፡፡ ፊት አውራሪ ተሠማ ወደ አዲስ አበባ መጥቶ ፍርድ ቤት ቀርቦ ታሠረ፡፡ ፍፃሜውም እዚያው ሆነ፡፡ የወላይታ ህዝብ "እፎይ" አለ፡፡ ራስ አበበ ፊትአውራሪ ተሠማን ለማዳን ያደረጉት ጥረት ሁሉ አልተሳካም፡፡ አቶ ብርሃኑ እንዲህ ይሉናል፤ "... እነራስ አበበን የመሳሰሉ ሹማምንቶቻቸውን ይቀየማሉ ሳይሉ አፄ ኃይለስላሴ ያሳዩት የፍትህ ሚዛንነት የወላሞን ህዝብ ፍርሃትና ስጋት ከሞላበት አኗኗር ነፃ አድርጎ ሰላምን ስለሰጠው በንጉሠነገስቱ ላይ ያለኝ እምነት ጠንካራ ሆነ፡፡ ..."

አቶ ብርሃኑ የወላይታ ተጠባባቂ ገዥ ከሆኑ በኋላ ወደ አዲስ አበባ የመመላለስ እድል ነበራቸውና ጃንሆይን ለማመስገን በሄዱ ጊዜ እንዲህ እንዳሏቸው ይነግሩናል፤ "እኛን እምነህ በቅንነት ከሰራህ ምንም ችግር አያገኝህም፡፡"

ከዚህም በላይ በተለያዩ የአስተዳደር ጉዳዮች ላይ አቶ ብርሃኑ ያቀረቧቸውን ምክሮች ጃንሆይ ተቀብለው ተግባራዊ ማድረጋቸውን ይገልፁልናል፡፡ ከአዲስ አበባ ወደ ወላይታ ሲመለሱ ሲሰናበቱ በቅርብ ጊዜ ለሌላ ስራ ወደ አዲስ አበባ እንደሚመለሱ ተነግሯቸው ነበርና የሄዱት፤ ወዲያው የወሊሶው ጀግና አርበኛ ደጃዝማች ገረሡ ዱኪ ተሾመው መጡ፡፡ አቶ ብርሃኑ ጥቂት አለማምደው ወደ አዲስ አበባ መጡ፡፡ ብላታ መርስኤ ሐዘን ወልደቂርቆስና አቶ ብርሃኑ ድንቄ "የታሪክና የቤተ-መንግስት ዜና ማሰናጃ" የሚባል መስሪያቤት እንዲያቋቁሙ ታዘዙ፡፡ ብላታ መርስኤ ሐዘን ዋና ዳይሬክተር፣ አቶ ብርሃኑ ዋና ፀሐፊ ሆነው ተሾሙ፡፡

ስራቸው የተቃና ይሆን ዘንድም የብርሐንና ሠላም ማተሚያ ቤት በእነሱ ስር እንዲተዳደር ሆነ፡፡ መስሪያ ቤቱ /የዱክ ቤት/ ቤተ-መንግስቱ ጊቢ ውስጥ ነበር፡፡

"... መስሪያ ቤቱ ጊቢ ውስጥ ስለሆነ ለጃንሆይ በማናቸውም የቅርብ አገልጋዮች አደረገን፡፡ እለት እለት ጃንሆይ የሚፈፅሟቸውን ዋና ዋና ታሪካዊ ጉዳዮች ከመከታተል በቀር አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በአስተዳደር ወይም በፍርድ ያለአግባብ ተወሰኑ ስለሚባሉት ነገሮች አጥንተን ጎሳብ እንድናቀርብ እንታዘዝ ነበር" ይሉናል፡፡ "ብላታ መርስኤ ሐዘን በአገራችን



ባህል ረገድ የተሟላ ድርጅት ያላቸው ሰው ናቸው..." ሲሉም ያደንቋቸዋል፡፡

በታሪክና ዜና ማሰናጃ ጽ/ቤት ሁለት ዓመት ከሰሩ በኋላ ጃንሆይ አቶ ብርሃኑን የጤና ጥበቃ ሚኒስትር ዋና ዳይሬክተር አድርገው ሾሟቸው፡፡ ብዙዎች ተገረሙ፡፡ ወይ ጤና! ጤና!

ጃንሆይ የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታልን አሰርተው ለስራ ማስኬጃ ገንዘብ ያጥራል፡፡ በዚህ ጊዜ ከመንግስት ንብረት ውስጥ ጥሩ ገቢ ያለውን ለሆስፒታሉ መርጃ መስጠት አስፈላጊ ሆኖ ተገኘ፡፡ ከጠላት የተወረሰው መካኒሳ የአልኮልና የአረቄ ፋብሪካ ለሆስፒታሉ እንዲተላለፍ አዘዙ፡፡ ነገር ግን የግል ተጠቃሚ /ባለአክሲዮን/ ከሌለ ስራው ሊቀዘቅዝ ስለሚችል በሚል 30 በመቶ ክፍያ ለቀድሞ አስተዳዳሪዎቹ ለፊትአውራሪ አስፋው፣ ለቀኝአዝማች ገ/ህን፣ ለአቶ በቀለ እንዲሰጥና የቀረው 70 በመቶ ለቅዱስ ጳውሎስ መተዳደሪያ እንዲሆን ተወስኖ ነበር፡፡ እነ አጅሬ ግን 4 ዓመት ሙሉ ቤሳቤስቲኒ ሳያቀምሱ እንደቆዩ የሚያረጋግጥ ሪፖርት ለአቶ ብርሃኑ ደረሳቸው፡፡ በዚህ ሚስጥራዊ ሪፖርት መነሻነት አቶ ብርሃኑ ያደረጉትን ከራሳቸው እንስማ፡፡ "... ከፋብሪካው መስሪያ ቤት ራሴ ሄጄ መዝገቦቹ የሚገኙበትን ክፍል አሳሸግሁት፡፡ እንዲሁም የየቀኑን የአልኮል "ፕሮዳክት" የሚቆጣጠሩ ኢንስፔክተሮች ሾምኩ፡፡ የሰጡት ሪፖርት እንደሚያመለክተው ሦስቱ ሰዎች የተጣራ 350,000.00 ብር ለግላቸው ተከፋፍለው ተገኙ፡፡... በዚህ ጊዜ እኔ በሦስቱ ሰዎች ላይ፤

1ኛ. የተካፈሉትን ገንዘብ ከነወለዱ እንዲከፍሉ፣

2ኛ. ከአስተዳዳሪነት ስራቸው እንዲወገዱ፣

3ኛ. እምነታቸውን አጉድለው ስለተገኙ በወንጀል እንዲቀጡ ስል ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ክስ አቀረብሁ፡፡..."

ወሬው ተነዛ፡፡ የጃንሆይ ታላላቅ ሹማምንትኮ ናቸው፡፡ ታማኝ፡፡ እናማ... ብዙ ዛቱ፣ ለህይወታቸው ፈርተው ጉዳዩን እንዲተውት አስፈራሩ ... ወዘተ፡፡ አልሆነም፡፡ በመጨረሻ ፊትአውራሪ አስፋው ለጃንሆይ ጉዳዩ በፍርድ ቤት ከሚታይ በኮሚሲዮን /በኮሚሽን ወይም በኮሚቴ/ እንዲታይ ጠየቀ፡፡

አቶ ብርሃኑ ተጠርተው ወደ ጃንሆይ ሄዱ፡፡ ፊትአውራሪ አስፋው ከጃንሆይ ጋር ነው፡፡ ጃንሆይ "ብርሃኑ ይሄውልህ በል ተናገር!" አሉት፡፡

"ጃንሆይ የመካኒሣ ፋብሪካ በትክክል እንዲሰራ ለማድረግ የቱን ያህል ችግር እንዳጋጠመን ብርሃኑ አያውቀውም፡፡ ... አሁን በድንገት ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ጃንሆይ ስራ ቢሉት የራሱን ስራ ሳያስተካክል የሚያደርገው ሁሉ የእኛን ስራ መበጥበጥ ብቻ ሆነ፡፡ ነገሩ ረዥም ስለሆነ ሁኔታውን በአጭር ጊዜ ለማስረዳት አልችልም፡፡ ስለዚህ ጃንሆይ በኮሚሲዮን እዛው እንዲመረመርና እርሱ ከፍርድ ቤት የጀመረው ክስ

"በዚያው ሰሞን ብላታ ዘውዴ ከስራ ሚኒስትር ወደ ጤና ጥበቃ ሚኒስትር ተዛወሩ። የስራ ሚኒስትር በነበሩ ጊዜ ልዩ ልዩ ክስ ቀርቦባቸው ነበር። የተዛወሩበትም ምክንያት በዚሁ ነው። የስራ ሚኒስትር ስጉቦ በጣም ያመች ነበር። አንዳንድ የስራ ተቋራጮች ከትርፋቸው 30 በመቶ ወይም 40 በመቶ ጉቦ ለመስጠት አያመነቱም። ከዚህም የተነሳ ወደ ጤና ጥበቃ በመዛወራቸው አዝነዋል። ይልቁንም የስራ ተቋራጮችን እርዳታ በመተማመን አንድ ትልቅ ቤት ለመስራት ጀምረው ለመፈፀሚያ ገንዘብ ስለጎደላቸው የሚያደርጉትን አጥተው ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የገንዘብ ቤት ሹም ጋራ በመመሳጠርና በብድር 60ሺ ብር መውሰድ ግድ ሆኖባቸው ኖሯል። ይህን ገንዘብ የተበደሩበትን ፊርማ በምስጢር አግኝቼ ግምጃ ቤቱን ካሸግሁ በኋላ ገንዘቡ እንዲቆጠር አዘዝሁ።"

ብላታ አበዱ። ጨሱ። ቤታቸው ሳያልቅ? ከስንቱ ተቋራጭ ስንት ነገር እንዳልቀረጡ ዛሬ የእሳቸው ቤት ተቋርጦ እንዴት ይቀራል? "አይደረግም!" አሉና ሄደው እሽጉን ቀደዱት። እሽ አቶ ብርሃኑ ምን አደረጉ በዚያ ሰዓት? "... ስለዚህ የሚከተለውን ፃፍሁላቸው።"

"ክቡር ሆይ፤

በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ግምጃ ቤት የገንዘብ መጉደል መድረሱን ሰምቶ ሳጥኑን ራሴ አሽጌ፣ ዋናው ኢንስፔክተር፣ የፐርሶኔል ሹሙና የሆስፒታሎች አስተዳደር መሪ ሹም ባሉበት ገንዘብ እንዲቆጠር አዝዤ ነበር። ነገር ግን የገንዘቡ ቤት ሹም እሽጉን ክቡርነትዎ እንደቀደዱትና ወደፊትም ያለእርስዎ ፈቃድ እንዳይታሽግ መከልከልዎን ነገረኝ። ማመን ያስቸግረኛል። ስለዚህ ነገሩን በግልጥ ለመከታተል እንድችል በጉዳዩ አንድ መግለጫ ይሰጡኝ ዘንድ በማክበር እለምናለሁ"

ብላታ ተከታዩን ምላሽ ፃፉ።

"ደብዳቤህ ደርሶኛል። ይህን የመሰለ ደብዳቤ ወደፊት ብትፅፍልኝ ከፍ ያለ የዲሲፕሊን ጉድለት ስለሆነ ቅጣት እንደሚያስከትል እግልፅልሃለሁ።" አያችሁ! ዲሲፕሊን! ይሄን አይነት ዲሲፕሊን ነው ዛሬ ድረስ በጉያችን ሸጉጠን የምናቀነቅነው። አይ ሚኒስትር! አይ ኢትዮጵያ! የዋህ ቀኝአዝማች አትል፣ ፊትአውራሪ አትል፣ ሚኒስቴር አትል፣ ብላታ አትል፣ ዘበኛ አትል ... በቃ!

አቶ ብርሃኑ ይቀጥሉ። "ይህ እጅግ ጥሬ የሆነ የማናለብኝ አፃፃፋቸው እንደሚያስደነግጠኝና ራሴን ዝቅ አድርጌ በመለማመጥ እንደምተዳደር ብላታ ዘውዴ ጠብቀው ነበር። ደብዳቤያቸውን ሲፈርሙ "እምቢ ካለ እናሳየዋለን!" ብለው እንደተናገሩ ከዚያ የነበረ ሰው ነገረኝ። ግን ይህ ሊያስደነግጠኝ ቀርቶ የታጋይነት መንፈሴን ስለቀሰቀሰው የሚከተለውን ፃፍሁ።

"ክቡር ሆይ



ደብዳቤ አትፃፍ የሚል ትዕዛዝ ሲደርሰኝ ይህ ለመጀመሪያ ጊዜ ነው። ጉዳዩ በጠቅላላ የሰውነትን ነፃነት የሚነካ ስለሆነ የመናገርና የመፃፍ መብቴን በቀላሉ ለማስረከብ ያስቸግረኛል። ስለዚህ ባለፈው ላቀረብሁት ጥያቄ መልስ እንዲሰጠኝ እንደገና ስጠይቅ በትዕግስትዎ ተስፋ አደርጋለሁ።"

ብላታ "አትፃፍልኝ ብዬ ካስጠነቀቅሁህ በኋላ ስለፃፍክልኝ 50 ብር ቀጥቼሃለሁ"

አቶ ብርሃኑ፤ "ቅጣቱን አልተቀበልሁትም፤ አሁንም ለመጀመሪያው ጥያቄዬ መልስ በመጠበቅ ላይ ነኝ"

"አትፃፍልኝ ብዬ ስለፃፍክ ቅጣቱን 100 ብር አድርጌዋለሁ"

"አትፃፍ" "እፅፋለሁ" ሲባባሉ ቅጣቱ 1 ሺ ብር ደረሰ። የወሩ መጨረሻ ሲደርስ አቶ ብርሃኑ የሚከፍላቸው ሹም ሲቀር ራሳቸው ሄደው ቆጥረው ወስደው ፈረሙ። "ሚኒስትሩ ለዋናው ዳይሬክተር ደሞዝ አትክፈሉ ብለውናል" ሙግት ሆነ። አቶ ብርሃኑ አልሰሚቸውም ይዘው ሄዱ። ብላታ አበዱ እንደገና። ስለዚህ "ከስራ አግጄሃለሁ!" ብለው ፃፉ። አቶ ብርሃኑም "የርስዎ ቅጥር ሠራተኛ አይደለሁም" የሚል መልስ ሰጥተው ስራቸውን ቀጠሉ። ይህ በእንዲህ እንዳለ ሚኒስትሩ ብላታ 25 የጤና ጥበቃ የጥገና ክፍል ሠራተኞች በጥገና ክፍል ኃላፊው እየተመሩ የተጀመረውን ቤታቸውን እየሰሩላቸው መሆኑ ተደረሰበት። ደመወዝ የሚከፍላቸው ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ነው። እነሱ ግን የብላታን ቤት እየሰሩ ነው። ስራውን ትተውታል። እዚያኛው መስሪያ ቤት ...!

"…. እንደገና አቤቱታ ፃፍኩላቸው። በዚህ አኳኋን ነገሩ እየተካረረ ስለሄደ ሁኔታውን በሰፊ ጽሁፍ ለግርማዊነታቸው ማመልከት ግድ ሆነብኝ። ብላታም እንዲሁ አመልክተው ኖሮ ቢትወደድ መኮንን እንዳልካቸው፤ ራስ አበበ አረጋይ፣ ፀሐፊ ትዕዛዝ ወለደጊዮርጊስ ባሉበት ሁለታችንም ተጠርተን ከጃንሆይ ፊት ቀረብን።" ይላሉ አቶ ብርሃኑ ድንቄ።

ጃንሆይ፤ "ሁለታችሁም የፃፋችሁትን አቤቱታ ተመልክተናል። ዘውዴ ብርሃኑን ከስራው አግጄዋለሁ ያልከው አግባብ አይደለም። በእኛ የተሾመ ስለሆነ ጥፋቱ ሲረጋገጥ በእኛ ይሻራል። ለሁሉም በመኮንን ሰብሳቢነት ነገራችሁን እነሱ መርምረው እንዲያቀርቡልን አዘናል" ሁሉም ተሰናብተው ወጡ።

ራስ ቢትወደድ መኮንን ጠቅላይ ሚኒስትር ናቸው። ፀሐፊ ትዕዛዝ ወልደጊዮርጊስ የጽህፈት ሚኒስትር ናቸው። ራስ አበበም የጦር ሚኒስትር መሆን የቻሉ ናቸው። በነገራችን ላይ በታሪክም በስፋት እንደሚታወቀው እነዚህ ሦስቱ ባለስልጣናት የወሰኑትን ውሣኔ ጃንሆይ ፈፅሞ "ውድቅ" አድርገውት አያውቁም። ኮሚሲዮኑ መቸም በአቶ ብርሃኑ ላይ ምን

አገር መሬት ተስማሚ ነው፡፡ ስለዚህ የእርሱን ጨረታ ተቀብለናል" የሚል ነው፡፡

ጨረታው ተዘጋጅቶ አቶ ብርሃኑ እንዲፈርሙበት ወደቢታቸው ተላከ፡፡ ግራ የሚያጋባ ልዩነት ስላዩ ከመፈረማቸው በፊት የቧንቧዎቹን ልዩነት ለማጣራት ፈለጉ፡፡ እነደጃዝማች ቸኩለዋል፡፡ የኢጣሊያ ኩባንያ ኮንትራቱን ሲያገኝ ደጃዝማች ከቤ 60 ሺ ብር፤ ለመዘጋጃ ቤት ሹማመንቶችና መሐንዲሶች 20 ሺ ብር፤ ሌላውን ለግብሻ አቅደው ጨርሰዋል፡፡

ደጃዝማች ከቤ ደወሉ ወደ አቶ ብርሃኑ "ቶሎ ፈርመህ ላክ እንጂ!"

"ቆይ የማጣራው ነገር አለ፡፡"

"አንተ መቼም ቄንጥ ማውጣት ትወዳለህ፡፡ ለመፈረም ያልፈለግህ እንደሆነ ላክልኝና እኔ እፈርመዋለሁ" አሉ፡፡

"ደጃዝማች ይህ የቄንጥ ነገር አይደለም የዋጋ ልዩነት ነገር ነው፡፡ ይህ ከመጣራቱ በፊት እርስዎም ቢሆን እንዲፈርሙበት አልመክርዎም፡፡"

ደጃዝማች በቁጣ "አንተ ታዘኛለህ? ይልቁንስ ቶሎ ወረቀቶችን ላክልኝ" አሉና ስልኩን ጠረቀሙት፡፡ ወዲያው ወረቀቶችን ለመውሰድ አቶ ተፈራ የተባለውን ልዩ ፀሐፊያቸውን ላኩ፡፡ የዚህን ታሪክ ሙሉውን እንደወረደ እንየው፡፡

"እርሱ ወረቀቶቹን ይዞ ከቤቴ ወጣ ሲለ ወደ ቤተ-መንግስት ስልክ ደውዬ አድማሱ ረታን "ለሚያስቸኩል ጉዳይ ከጃንሆይ በስልክ መነጋገር እፈልጋለሁ" አልሁት፡፡ በአንድ ደቂቃ ውስጥ ጃንሆይ ከስልክ ስለቀረቡ የሚከተለውን አመለከትሁ፡፡

"ጃንሆይ በድፍረቴ ይቅርታ ይደረግልኝ፡፡ እኔ በጤና ጉድለት ከቤቴ ተኝቻለሁ፡፡ ስለገፈርሳ ውሃ ግድብ ደጃዝማች ከበደ አሁን ኮንትራት ሊፈርሙ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት የመዘጋጃ ቤት ብዙ ገንዘብ ይከስራል፡፡ እኔ ምክር ብሰጣቸው ደ ዝማች መስማት አልፈለጉም፡፡ ነገ እኔ ራሴ ቀርቤ በሰፊው እስካስረዳ ድ ስ ኮንትራቱ እንዳይፈረም ጃንሆይ ያዙልኝ ዘንድ እለምናለሁ፡፡"

ጃንሆይ፤ "መልካም ነገ መጥተህ እሱ ባለበት አስረዳ፡፡" ካሉኝ በኋላ ለደጃዝማች ወዲያው ስልክ ተደውሎ ኮንትራቱን እንዳይፈርሙ ተከለከሉ፡፡ ሁኔታው አምስት ደቂቃ በማይሞላ ጊዜ ውስጥ ስለተፈፀመ በዚያን ጊዜ ደጃዝማችን ያዩ ሰው እንደነገረኝ፤ ከነጭ ሰማይ ላይ በድንገት ሳይጠብቁት ነጎድጓድ እንደወረደባቸው ሁሉ ክው ብለው ነበር፡፡ እየደጋገሙ የተናገሩት ቃል "ምን ያለ ሰይጣን ነው! ምን ያለ ሠይጣን ነው! የሚል ብቻ ነበር፡፡ ኮንትራቱን ለመፈራረም መጥተው የነበሩት የኢጣሊያ ኩባንያ ወኪሎችና የማዘጋጃ ቤት መሐንዲሶች ከቢሮዋቸው



እንዳሉ ምክንያቱን ሳይገልፁላቸው ትተዋቸው በችኮላ ወደ ቤተ-መንግስት ሄዱ፡፡

ይህን አሳፋሪ ሁኔታ ለማስወገድ ኮንትራቱ እንዲፈረም ይፈቅዱ ዘንድ ጃንሆይን ለማግባባት በብርቱ ተጣጥረው ነበር፡፡ ጃንሆይ ግን "ብርሃኑ ቀርቦ የተቃወመበት ሳይሰማ ኮንትራቱ አይፈረምም፡፡" ብለው በውሣኔያቸው ፀኑ፡፡ ደጃዝማች ቤተ-መንግስት እንዳሉ ለፀሐፊያቸው ደውለው ባለጉዳዮቹ የኢጣሊያ ኩባንያ ወኪሎችና ለሴሪሞኒ የተሰበሰቡት ሰዎች፤ ፎቶግራፍ አንሺዎች ሳይቀሩ እንዲሰናበቱ አደረጉ፡፡ ምክንያቱን ግን አልገለፁም፡፡ በጣም የሚያሳፍር ሆኖ አገኙት፡፡

በማግስቱ ደጃዝማች ከበደ እና እኔ ከጃንሆይ ፊት ቀርበን የተደራጀው ኮንትራት፤

ሀ. የጨረታውን ስርዓት ስላልተከተለ፣

ለ. ማዘጋጃ ቤትን ብዙ ሺ ብር ስለሚያከስር፣

ሐ. የኢጣሊያ መሐንዲሶች የአገራቸውን ኩባንያ ለመደገፍ ስለቧንቧ አሰራር የሰጡት ኀሳብ ትክክል ስላይደለ መጣራት አለበት ስል መቃወሚያዬን በዝርዝር አቀርባለሁ፡፡

ደጃዝማች በበኩላቸው "ኮንትራቱን ከመፈረም የሚያዘገይ በቂ ምክንያት የለም" ሲሉ የኔን ኀሳብ አስተባበሉ፡፡ ጃንሆይ የሁለታችንም አቋም ከሰሙ በኋላ፤

1. ደጃዝማች ከበደ /ሰብሳቢ/
2. ባላምባራስ ማሕተመ ስላሴ
3. ደጃዝማች ክፍሌ
4. አቶ ምናሴ
5. አቶ ብርሃኑ ድንቁ
6. Mr. Clark /አሜሪካዊ የኢትዮጵያ ባንክ አዛዥ/
7. Mr Pery /ካናዳዊ የገንዘብ ሚኒስትር አማካሪ/
8. ባላምባራስ እማኙ
9. Dr Naudeha /የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት አማካሪ/

በኮሚሲዮን አይተውና ነገሩን አብራርተው እንዲያቀርቡላቸው አዘዙ፡፡ ይህ ትዕዛዝ በተሰጠበት እለት የተባሉት ሰዎች ተሰብስበው አንድ ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ተነጋግረው ቃላቸውን ሰጡ፡፡ ሚስተር ፔሪ እና እኔ ብቻ በኀሳብ ስንለይ የቀሩት በሙሉ ደጃዝማችን ደገፉ፡፡ በዚያን ጊዜ በእያንዳንዱ የኮሚሲዮን አባል አእምሮ የሚመላለሰው አሳብ፤ "ብርሃኑ ማነው? ምንስ ማድረግ ይችላል?" የሚል እንጂ የገፈርሣ ውሃ ጉዳይ አልነበረም፡፡ Mr Pery የሰጠው አስተያየት በጣም ያስደንቃል፡፡ ይህ ሰው ካናዳዊ ነው፡፡ ኢኮኖሚስት በመሆኑ የገንዘብ ሚኒስትር በአማካሪነት ቀጥሮት ለረጅም ጊዜ ሰርቷል፡፡ ሰውየው, በጣም ትሁት ነው፡፡ ግን

በአማካሪነት ስለሚሰጠው አስተያየት "ጎሳቤን እገሌ ይወደዋል፤ ወይም እገሌ ይጠላዋል" ብሎ የሰውን ዓይን የማይመለከት፤ በኢትዮጵያ ካሉ የውጭ አገር አማካሪዎች እርሱ ብቻ ነበር ይባላል፡፡ በዚህ ጉዳይ የሰጠው አስተያየት በአጭሩ እንደሚከተለው ነው፡፡

"እኔ የአቶ ብርሃኑ ድንቄን ኀሳብ በሙሉ እደግፋለሁ፡፡ እዚህ አሁን የተሰበሰብነው ሁሉ አድሚኒስትሬተሮች እንደመሆናችን መጠን ገንዘብ እንዲቆጠብና በማይበቃ ምክንያት እንዳይጠፋ መጠንቀቅ ተግባራችን ነው፡፡ በሁለቱ የቧንቧ አይነቶች ዋጋ መካከለ በሺ የሚቆጠር የገንዘብ ልዩነት አለ፡፡ አንዱ የቧንቧ አይነት ከሌላው በማናቸውም እንደሚበልጥ እርግጠኛ ማስረጃ ሳይጨበጥ ከፍተኛ ዋጋ እንዲከፈል አይገባም፡፡" መቼም በድምፅ ብልጫ ደጃዝማች ከበደ አሸንፈዋል፡፡ ግን ክርክሩን እንዲሁ በቀላሉ ለመተው አልተዘጋጀሁም ነበር፡፡

ስለዚህ ቃለ-ጉባኤ ተዘጋጅቶ ለፊርማ ሲቀርብ "አቶ ብርሃኑ ድንቄና ሚስተር ፔሪ አልተስማሙም" ከሚል በቀር፤ ያልተስማማንበትን ምክንያት አለመገለጡን ተመልክቼ እንደገና ተብራርቶ እንዲፃፍ ጠየቅሁ፡፡ ደጃዝማች ግን "ባይፈርም ይተወው!" ብለው አስቀድመው ያዘጋጁትን ቃለ-ጉባኤ እኔ ሳልፈርምበት ለጃንሆይ አቀረቡ፡፡

መቼም በማሸነፋቸው የተሰማቸው ደስታ ሊዘረዘር አይቻልም፡፡ አያሌ ወዳጆቻቸውን እየጨበጡ እያቀፉ የደስታቸው ተካፋይ መሆናቸውን ገለጡላቸው፡፡ ማታውን የኢጣሊያ ኩባንያ እንደራሴ በራስ ሆቴል ምርጥ ለሆኑ ሰዎች ራት ጋበዘ፡፡

በዚህ ጊዜ እኔ ደጃዝማች ከበደን በግል ከስሼ ለጃንሆይ አቤቱታ ፃፍሁ፡፡

አቤቱታዬ፤ "ደጃዝማች ከበደ የአዲስ አበባ መዘጋጃ ቤት ከንቲባ መሆናቸውን ረስተው የኢጣሊያ ኩባንያ እንደራሴ የሆኑ ይመስላል፡፡" የሚል ብርቱ ክስ የያዘ ስለሆነ እንደገና ጃንሆይ ሁለታችንንም አቀረቡን፡፡ በዚህ ጊዜ ደግሞ በተጋነነ ቃል የከንቲባው ስራ የሚያጠራጥር ነው ብዬ ተናገርሁ፡፡ በቃለ-ጉባኤውም ውስጥ የእኔና የሚስተር ፔሪ አስተያየት ተብራርቶ ያልተፃፈበትን ምክንያት ጠየቅሁ፡፡ ደጃዝማች ለማልቀስ የተዘጋጀ ፊት ነበራቸው፡፡ እንደሚገባም ራሳቸውን ለመከላከል አልቻሉም፡፡

በዚያ ሰዓት ጃንሆይ ወደእኔ ፊታቸውን ቀና አድርገው፤ "እሆን ምን ይሁን ነው የምትለው?" አሉኝ፡፡ እኔም፤

"ጃንሆይ በለንደን "ስኩል ኦፍ ቴክኖሎጂ" የተባለ አንድ ትምህርት ቤት አለ፡፡ ይህም ትምህርት ቤት የንግድ ጥቅም የለውም፡፡ ግን ስለአንዳንድ እቃዎች አሰራር በቴክኖሎጂ ረገድ ኢንፎርሜሽን ሲጠየቅ የተጣራ መልስ ይሰጣል፡፡ አሁን እኔ የማሳሰበው ለዚህ ትምህርት ቤት



ቴሌግራም አድርገን SEAMLESS እና WELDED በሆነ የቧንቧ አሰራር ልዩነት እንዳለው ጠይቀን ከዚህ ትምህርት ቤት በምናገኘው መልስ መሠረት ነገሩን እንድንወስን ብቻ ነው፡፡"

ጃንሆይ፤ "መልካም ነው!" ብለው የውጪ ጉዳይ ሚኒስትሩ አቶ አክሊሉ ሐብተወልድ ቴሌግራሙን እንዲያስተላልፉ አዘዙ፡፡ ከሁለት ቀን በኋላ የቴሌግራሙ መልስ መጣ፡፡"

እነ አቶ ብርሃኑ እንዳሉት WELDED "በማናቸውም የመሬት አይነት ያለአንዳች ስጋት ሊዘረጋ ይችላል" የሚል መልስ ሲሆን፤ ከSEAMLESS እንደሚበልጥም ተረጋገጠ፡፡

"ግርማዊነታቸው ቁጣና ሐዘን በተቀላቀለበት መልክ ደጃዝማች ከበደን ገላምጠው "ይገርማል እኮ!" አሉ፡፡ ከዚህ ሌላ አንድ ቃል ሳይጨምሩ የልፍኝ አስከልካዩ ከግርማዊነታቸው ጽ/ቤት እንድንወጣ የእጅ ምልክት አሳየን፡፡ በዚያን ጊዜ ደጃዝማች ከበደ የተከናነቡት ሐፍረት እንደ ሐምሌ ጥቁር ደመና በፊታቸው አካባቢ ተንጠልጥሎ ይታይ ነበር፡፡ ስለዚህ የገፈርሳ ውሃ ግድብና የቧንቧ ስራ እርሳቸው እንደተመኙት ሳይሆን፤ በጨረታ ላሸነፈው ለፈረንሣይ ኩባንያ ለዴግሬሞን ተሰጠ፡፡ ማዘጋጃ ቤትም ብዙ ሺ ብር አዳነ፡፡ ቀጥሎም ከጥቂት ጊዜ በኋላ ራሳቸው ደጃዝማች ከመዘጋጃ ቤት ስራቸው ኃላፊነት ተራገፉ..."

አቶ ብርሃኑ ድንቄ በምዕራፍ 9 እንዲህ ይሉናል፡፡

"አንዳንድ ሹማምንቶች በንቅዘት ምክንያት ከስራ ሲወገዱ፤ ወይም ከሹመት ደረጃቸው ዝቅ ሲሉ የሚያስደስተኝ የነርሱ ሐዘን ወይም እኔ ከእነርሱ ጋር ታግዬ ማሸነፌ አይደለም፡፡ ነገር ግን፤

ሀ. የእነርሱን እድል በመመልከት ሌሎች ይታረማሉ፤

ለ. በእነርሱ ምክንያት የተበደሉ ወይም የተገፉ ሰዎች ነፃነት ይሰማቸዋል፤

ሐ. የፍትህ መተካከል ቀስ በቀስ እያለ በንጉሠነገስቱ መንግስት አስተዳደር ይዛመታል የሚል ጠንካራ ተስፋ ነበረኝ፡፡

የሆነ ሆኖ የግል ጠላቶች ከማብዛቴ በቀር ይህን ተስፋዬን የሚደግፍ አንዳች ምልክት አይታየኝም ነበር፡፡ ..." በማለት በተሻሩት ደጃዝማች ምትክ ቀደም ሲል ያየናቸው የጤና ጥበቃው ሚኒስትር ብላታ በመተካታቸው ማዘናቸውን ይገልፁልናል፡፡ (የጃንሆይ ትልቁ ጥፋትም ይሄ ነበር) ስለዚህም ወደ ጃንሆይ ሄደው አለመደሰታቸውን ተናገሩ፡፡ በዚህ ጊዜ ጃንሆይ አቶ ብርሃኑ ስላደረጉት ብርቱ ትግል አመስግነው እንዲህ አሉ፡፡

"ብርሃኑ አንድ ህዝብን ማስተዳደር የበጎች መንጋ እንደመጠበቅ ቀላል ነገር አይደለም፡፡ እግዚአብሔር ሲያስችለን ብቻ የሚቻለውን እናደርጋለን፡፡" አሏቸው፡፡ የመልሶ መሾሙ ሁኔታ አንድ ራሱን የቻለ

ፖለቲካዊ ዱለታ በውስጡ ስለነበረው ይህን ከመፅሐፉ ማግኘት ትችላላችሁ፡፡ ብቻ ጃንሆይ አጣብቂኝ ውስጥ ነበሩ፡፡

አቶ ብርሃኑና ብላታ ደግሞ በአንድ ክፍል አብረው መስራት የማይታሰብ ነበር፡፡ በስምንተኛው ቀን ጃንሆይ አቶ ብርሃኑን ጠርተው፤ "እውጭ አገር ብንልክህ ትወዳለህ?" ብለው ጠየቁ፡፡ አቶ ብርሃኑ ፈቃደኝነታቸውን ገልፀው የመጀመሪያውን የዲፕሎማትነት ስራ ለሦስት ዓመት ያህል በዋሽንግተንና በሳዑዲ /ጅዳ/ አገልግለው ከ3 ዓመት በኋላ ወደ አዲስ አበባ እንዲመለሱ ተደረገ፡፡ በየጊዜውም ወደ አዲስ አበባ እየመጡ ከጃንሆይ ጋር ይገናኙ ነበር፡፡

መጥተውም የፖስታ፣ የቴሌግራፍና ቴሌፎን /ቴ.ቴ/ ምክትል ሚኒስትር ሆነው ተሾሙ፡፡ በወቅቱ ዋናው ሚኒስትር ቢትወደድ መንገሻ ነበሩ፡፡ እኚህ ሰው "ቤተ-መንግስቱ የእኛ ነው" የሚሉ አባታቸው የዘውዲቱ ባል የነበሩ የተኮፈሱ ሰው እንደነበሩ ይነግሩናል፡፡ ቢትወደድ መንገሻ አንዳንዴ ያማቸው ስለነበር ቤት ነው የሚውሉት፡፡ እንደ ሚኒስትር ሆኖ የሚሰራውና የማያዘው ልዩ ፀሐፊያቸው አቶ ታደሰ ነው፡፡ እየሰማችሁ ነው? ሚኒስትሩ ሌላ ሚኒስትር ቀጥረዋል፡፡ እሳቸው እርፍ ብለው በወኪል እያሰሩ ነው፡፡ አቶ ብርሃኑ እንዲህ ይሉናል፤ "... ስለዚህ ከደንበኛ ደመወዙ በቀር ልዩ አበል ተመድቦለታል፡፡ ነፃ የቴሌፎን አገልግሎት ከቤቱ ገብቶለታል፡፡ ለተመደበለት መኪና ትርፍ ቤንዚል ይሰጠዋል፡፡ ይህ ትክክል መስሎ ስላልታየኝ ቢትወደድ ከመስሪያ ቤት ባልነበሩበት ጊዜ እንዲሰረዝ ትዕዛዝ ፈርሜ አስተላለፍሁ፡፡ ቢትወደድ ግን ለእረፍት ከሄዱበት በፍጥነት ተመልሰው እኔ የሰጠሁትን ትእዛዝ የሚያፈርስ ደብዳቤ ብቻ ፈርመው ወደ እረፍታቸው ተመለሱ፡፡"

እሺ ከዚያስ? "... ስለዚህ የሚከተለውን ልፅፍላቸው ግድ ሆነብኝ" ይሉናል አቶ ብርሃኑ፡፡ እኛም ምን ብለው ፃፉላቸው? ብለን እንጠይቃለን በጋራ፡፡ ይሄው፡፡

"ክቡር ሆይ

ይህን መስሪያ ቤት ክቡርነትዎ እንዲያስተዳድሩ ኃላፊነት ሲሰጥዎ በነጋሪት ጋዜጣ ስለሚንስትሮች ስልጣን የወጣውን ሕግ እንደሚያከብሩ በመተማመን መሆኑን አልጠራጠርም፡፡ የፖስታ ቴ.ቴ ሚኒስትር የመንግስት መስሪያ ቤት እንጂ የክቡርነትዎ ማዕድ ቤት እንዳልሆነ ማስገንዘብ ያስፈልገኝ አይመስለኝም፡፡ ልዩ ፀሐፊዎ ከተወሰነለት ደመወዝ በቀር ልዩ አበልና ነፃ የቴሌፎን አገልግሎት እንዲሰጠው የበጀት ስርዓቱ አይፈቅድም፡፡ ልዩ ፀሐፊዎ እርስዎ በሌሉበት ሚኒስትር እንዲሆን ሕግ አይፈቅድለትም፡፡ እርስዎ በሌሉ ጊዜ ምክትል ሚኒስትሩ አለ፡፡ ምክትል ሚኒስትሩ በሌሉ ጊዜ ዋና ዳይሬክተር አለ፡፡ ይህን ሁሉ አልፈው ልዩ ፀሐፊውን የሚወክሉበት ምክንያት አይገባኝም፡፡



የንጉሠነገስቱ መንግስት አስተዳደር አልተስማማዎት እንደሆነ የተሻለ መንገድ ስለሌለ ቢሰናበቱ መልካም ይመስለኛል"

"ከዚህ በላይ የተፃፈው ደብዳቤ ጠንካራ እንደሆነ ይሰማኛል፡፡ ግን የቢትወደድ አደራረግ ለእኔ ጠንካራ ሆኖ ነው ያገኘሁት፡፡ ከሁሉ አስቀድሞ አሰራራቸው ከሕግ ውጪ እንደነበረ ሳያውቁት አይቀርም፡፡ ቀጥሎም የእኔን ትዕዛዝ ከመሻራቸው በፊት ጠርተው እንኳ ሊጠይቁኝ አልፈቀዱም፡፡ ስለዚህ ለዘብ ያለ አቤቱታ እንደማይበግራቸው ተረድቼ ሆነ ብዬ ነው ያጠነከርኩት፡፡" ይላሉ አቶ ብርሃኑ፡፡ እኛም "ኸረ እንኳን አጠነከሩት!" እንላቸዋለን በጋራ፡፡

ቢትወደድ ደብዳቤው ሲደርሳቸው በንዴት ጨሱ! አይገልፀውም፡፡ በቀጥታ ወደቤተ-መንግስት ሄደው ለጃንሆይ "ጃንሆይ፤ ምን በደልኩዎና ነው ይህን ሰው ልከው የሚያዋርዱኝ?!" በማለት ደብዳቤውን አሳዩዋቸው፡፡ ጃንሆይ አነበቡትና ወዲያው፤ "ታዲያ አንተ ሕጉን እየጣስህ ስትሰራ ምን ያድርግህ? ውሸት ነው ትላለህ ብርሃኑ በደብዳቤው የፃፈው?" ሲሉ ቢትወደድ መልስ አልነበራቸውም፡፡ ስለዚህ በስምንተኛው ቀን ከስራቸው ተነሱ፡፡

አቶ ብርሃኑ እንዲህ ይላሉ፤ "በዚህ አደራረግ ከቢትወደድና ከተከታዮቻቸው ይልቅ የደነገጥሁ እኔ ነኝ፡፡ ጃንሆይ እንደዚህ ፍጡን የሆነ እርምጃ ይወስዳሉ ብዬ በፍፁም አልጠበቅሁም ነበር"

"በፖስታ ቴ.ቴ ሚኒስቴር በተጠባባቂነት /በምክትልነት/ ስሰራ የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ቦርድ ሊቀመንበር ሆኜ ቦርዱን መሰብሰብ ጀመርኩ፡፡ በዚያን ጊዜ የቴሌኮሙኒኬሽን መስሪያቤት ስራውን ለማሻሻል ከዓለም ባንክ ከፍ ያለ ብድር ጠይቆ ነበር፡፡ ነገር ግን ብድሩ ከመፈቀዱ በፊት የዓመቱን ገቢና ወጪ ሂሳብ፣ አገልግሎት ተሰጥቷቸው ያልከፈሉ ሰዎች እንዳሉ የእዳቸውን መጠን የሚያሳይ ጠቅላላ ሪፖርት የቴሌኮሙኒኬሽን መስሪያቤት ለባንኩ እንዲልክ ማስታወሻ ደርሶት ስለነበር የሲውዲን ተወላጅ የሆነው ዋና አስተዳዳሪው ሚስተር ሊንድ ኮስት ባዘጋጀው መልስ እንደተመለከትሁት ብዙ ሺ ብር ያልተከፈለ እዳ ተገኘ፡፡ ምክንያቱን ብጠይቀው አብዛኛው ገንዘብ የቴሌኮሙኒኬሽን ስለሰጠው የቴሌፎን አገልግሎት ንጉሣዊ ቤተሰቦችና መኳንንቶች ያልከፈሉት እዳ መሆኑን ገለጠልኝ፡፡ ካቀረበው ዝርዝር ውስጥ የሚከተሉትን ሰዎች ስም ተመለከትሁ፤

- ልዑል አልጋወራሽ አስፋወሰን ኃይለስላሴ፣
- ልዑል ሣህለስላሴ፣
- ራስ ቢትወደድ መኮንን እንዳልካቸው፣
- ራስ አበበ አረጋይ፣
- ራስ ቢትወደድ አንዳርጌ መሣይ፣

የሚፈፀምባት አገር ላይ ረሃብና ድርቅ ካልተከሰተ የት ይከሰት? እያልን ስንቀጥል ነው የአገሪቱ ባለችበት የመርገጥ ጉዳይ ምንጩ የሚገባን፡፡ ይህ የታሪክ መጽሐፍ ነው፡፡ ከላይ ያየነው እውነትም ታሪክ ነው፡፡ ዛሬም ድረስ ያለ ህያው ታሪክ! መንግስትና ህዝብ ሊማርበት የሚችል፣ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ግለሰብ ራሱን ሊፈትሽበት የሚችልና የሚገባ ድንቅ ታሪክ!

ታሪኩ እውነት ለመሆኑ የሚጠራጠር አንባቢ ካለ ኢትዮጵያን የማያውቅ ብቻ ነው፡፡ ይሄ ስም ለማጥፋት ተብሎ የተፃፈ ታሪክ ነው ብሎ የሚከራከር ካለ ከእውነት አብልጦ ራሱን የሚወድ ብቻ ነው፡፡ ግልፅ ነዋ! አገር ያወቀው ሐቅ፡፡ ከታሪክ መማር ካለብን በአንደኛነት ይህንኑ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡ አሁን አሁን በዚህ ሰዓት የእነ ብላታ፣ የነደጅአዝማች፣ የእነ እገሌ ተግባር እየተፈፀመ እንዳለ ወይስ እንደሌለ ነው የሚሰማን? ኢትዮጵያን በድህነት እርቃኗን ያስቀራት የዝናብ እጥረት አይደለም፡፡ የመሬት ጥበት፣ የረጂዎቻችን ማነስ አይደለም፣ የርዕዮተ ዓለም ትክክል መሆን ያለመሆን አይደለም፡፡ ብዙ ነገር አይደለም፡፡ ሙስና ነው፡፡

"ባላባት፣ መሣፍንት፣ ሹማምንት ..." ይባላል፡፡ ያ ስም እና ዘርን ብቻ ነው የሚያመለክተው፡፡ "የመንግስት ባለስልጣን" አበቃ፡፡ በጃንሆይ ዘመን የነበረውን ሙስና በአንድ ብርሃኑ ድንቄ ነጠላ ገጠመኝ ስንረዳ ለውድቀታቸው አንዱ መንስኤ ሊሆን እንደሚችል እናስባለን፡፡

በዘመናቸው የነበረው ብልሹ አሰራር ህዝቡን ምን ያህል ሊጎዳና ሊያማርር እንደሚችልም ግልፅ ነው፡፡ ፍትህ የለም፣ ሕግ ይጣሳል፣ የህዝቡ ጉርምርምታ በታላላቅ ሹማምንቱ ተውጦ የሚቀር እንጂ ወደጃንሆይ ጆሮ የሚደርስ አይደለም፡፡ ትልልቅ ባለሥልጣናቱ አገር ሲበዘብዙ አብሮ መተባበር እንጂ አፈንግጦ ለጃንሆይ ማመልከት አይችልም፡፡ ቢችል ምን እንደሚገጥመው በግልፅ ያየነው ነው፡፡

የተለመደው የተማሪ አመፅ፣ የገበሬ አመፅ፣ ረሃብ፣ የወታደር አመፅ የሚሉትንና ብዙዎች ለለውጥ ሲሉ ያደረጉትን ትግልም ሆነ የከፈሉትን መስዋዕትነት ቆየት ብለን እንደ ሌሎች ታሪኮች ሁሉ በአጭሩ እናያቸዋለን፡፡ ከዚያ በፊት ግን እያየናቸው የመጣነውን ብልሹ አካሄዶች መሠረት አድርገን ጥቂት ነጥቦችን ብናነሳ አመፅ እንዴት እንደሚረገዝ ግልፅ ይሆንልናልና እሱኑ እናስቀድም፡፡

ለምሳሌ ቀኝአዝማች እገሌ በእርዳታ የመጣውን መድሐኒት ብቻ ሳይሆን ሰሃን ሳይቀር በሞኖፖል ይዘው መጋዘኑ ላይ ቆመው "ማነው ወንድ ይህችን መጋዘን የሚያሸግ!" እያሉ እየፎከሩ እንደ ነጋዴ በችርቻሮም በጅምላም ሲቸበችቡት አይተናል፡፡ በሽተኛ አቅም ስለሌለው ሊያምፅ አይችልም እንጂ በዚህ ድርጊት "የበሽተኞች እመፅ" ሊኖር ይችል ነበር ብንል ማጋነን አይሆንም፡፡



ወታደሩ "ደመወዝ ይጨመርን፣ ስንቃችን የተበላሸ ነው፣ የምንጠጣው ውሃ ቆሻሻ ነው ..." በሚል ለአመፅ ተነሳሳ፡፡ ብላታ እገሌ ቤት ያሰሩበት ገንዘብ በዚያ ዘመን ለአራቱም ክፍለ ጦር ሠራዊቶች ለረጅም ጊዜ እጥፍ የደመወዝ ጭማሪ ይሆናቸው ነበር፡፡ የወታደር ደመወዝ 15 ብር ነበራ! ቆሻሻ ውሃን በተመለከተ ጉዳዩ የሚመለከተው ደጃዝማችን ነው፡፡ እንኳን ነገሌ ቦረና ለአዲስ አበባው የገፈርሣ ውሃ ግድ አልነበራቸውም፡፡ እሳቸው እዚህ ጨረታውን ጣሊያን ይውሰድ፣ የፈረንሣዩ ለጉቦ አይተርፍም፣ ራስ ሆቴል ድግስ አለብኝ እያሉ እንዴት ነው ንፁህ ውሃ ነገሌ ቦረና የሚደርሰው? የወታደር አመፅ፡፡

ወደ ገበሬ አመፅ ስንመጣ፣ ገበሬው ያመፀው ምርር ብሎት እንደሆነ ጥርጥር የለውም፡፡ የመሬት ግብር ግን አልነበረም ያማረረው፡፡ ሕገ-ወጥ ግብር ነው ያማረረው፡፡ አንድ መንግስት ያለ ግብር ምንም ሊፈጥር አይችልም፡፡ ስለዚህ ግብር ተጥሎበታል፡፡ ቀደም ሲል እንዳየነው ፍትሐዊ ያልሆነ የግብር አጣጣል ነበረ፡፡ ያ ግን ተጋኖ የሚወራ አልነበረም፡፡ ችግሩን የፈጠረው ሕጉ-ወጥ አሳሽ ነው፡፡

ፊታውራሪ እገሌ የወላይታን ሕዝብ የውትት ላሙን ሲያስገብሩት ለምን አያምፅ? ጃንሆይ ይሄን አላዘዙም፡፡ ሰው ግደሉ፣ ዝረፉ አላሉም፡፡ እሉ የተባሉ ሹማምንት ግን እላፊ ያስገብራሉ፣ ይገድላሉ፣ ይዘርፋሉ፣ ከሕግ ውጪ ያስራሉ ... ወዘተ፡፡ ስለዚህ ገበሬው አመፀ፡፡ የሚስተር ሉንድክቪስት አለአግባብ የሆነ ጥቅማ ጥቅምና የባእዳን መንፈላሰሻ የነበረው ገንዘብ በቀጥታ የወሎን የአንድ ዙር ድርቅ ለመቆጣጠር ይችል ነበር፡፡

ጃንሆይ ለህዝባቸው የማያስቡ ባይሆን ኖሮ በስማቸው ተመዝግቦ የነበረውን ከጠላት የተወረሰውን የመካኒሳ ፋብሪካ በፈቃዳቸው ላሰሩት ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል መተዳደሪያ ሙሉ ለሙሉ ባልሰጡት ነበር፡፡

በዚህ መሠረት በዘመናቸው ይከሰቱ የነበሩትን ረሃቦችም ሆኑ ድርቆች ለመቋቋም ጥረት ሊያደርጉ ይችሉ እንደነበር ስንረዳ፣ ነገር ግን የመንግስታቸው ገቢ በየሚኒስትር መስሪያ ቤቱ ተውጦ ስለሚቀር ይህን ለማድረግ የሚያስችል አቅም አይኖራቸውም፡፡ ለ4 ዓመታት ያህል 70 በመቶ ለሆስፒታሉ መስጠት እየነበረባቸው ምንም ሳይከፍሉ ቆዩ ማለት ምን ማለት ነው? 350 ሺ ብር! ሦስት ሰዎች የወሰዱት፡፡ ለሆስፒታል ስራ ማስኬጃ የሚሆን፡፡ ስንት ሰው ያድናል? ግማሹ እንኳ ቢዘረፍ ሌላው ለሰፊ የመስኖ ልማት ሊውል ይችል ነበር፡፡ በዚህ ብቻ የአንድን ዘመን ረሃብ እንደምንም ማሳለፍ ይቻል ነበር፡፡ አልሆነም፡፡ (የዚያን ዘመን የገንዘብ ሁኔታ ለመረዳት ኢጣሊያ በወልወሉ ግጭት ለ80 ዜጎቿ ሞት የጠየቀችው 200 ሺ ብር መሆኑን ማሰብ ይበቃል፡፡)

የተማሪ አመፅ ግልፅ ነው፡፡አዲስ አበባ ሆነው ባያምፁ ነው የሚገርመው፡፡ማገናዘብ የሚችል ጭንቅላት አላቸው፣ጭቆናው ይገባቸዋል፤ቢሮክራሲውን ያውቁታል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጉቦ የማይቀበል ባለስልጣንን እውቅና አይሰጡም ነበር፡፡ ያስወግዱታል! (መሬት ላራሹ፣ ጭሰኛ፣ ገባር፣ ፊውዳላዊ አገዛዝ ... ወዘተ ሁሉም በዚህ ስር ነው) ነገር ግን ተማሪው ብዙ መነሻ ሊያገኝ የሚችልበት አጋጣሚ ሰፊ እንደነበር ከወዲሁ ተረድተን እንለፍ፡፡ ተማሪው የባላባቱን ንቅዘት በግልፅ ስለሚያውቀው ለማለት ነው፡፡ ነጋዴም ያው ፊታውራሪ ከወንድማቸው ጋር ያሸጉበት ስለነበር ሊያምፅ ይችላል፡፡

ሠራተኛውማ ምን ጥርጥር አለው? የመንግስት ሠራተኛ በዚያ ዘመን ካላመፀ መቼ ሊያምፅ ኖሯል? የመንግስት መስሪያ ቤት ተቀጥሮ የግል ቤት እንዲሰራ እየታዘዘ! እንዲያ ነበር...ዛሬም እንዲህ ነው.....

የጃንሆይን ጥፋትና የአቶ ብርሃኑን ደብዳቤ ወደማየት እንለፍ፡፡

ጃንሆይና ጥፋታቸው

የጃንሆይ ትልቁ ጥፋት ስልጣን አፍቃሪነታቸው ነው፡፡ይሄን ሁሉ ሙስና እያዩ አንዳንዶችን መልሰው ትልቅ ቦታ ላይ ይሾሟቸዋል፡፡ጠንካራና ዘላቂ እርምጃ ቢወስዱ ስልጣናቸው አደጋ ይደርስበታል፡፡ስለዚህ ለሥልጣናቸው ሲሉ ብቻ ሕገ-መንግስቱም ሆነ ማናቸውም አይነት ሕግ ሲጣስ እያወቁ በቸልታ ያልፉ እንደነበር ግልፅ ነው፡፡

ዋና ትኩረታቸው ዙፋናቸው ላይ ሆነና ኢትዮጵያን ረሷት፡፡ ወይም "በስልጣኔ አትምጡብኝ እንጂ እንዳሻችሁ" ያሉ ይመስላል፡፡ ስለዚህ የየዘርፉ ሹማምንት በነፃነት መበዝበዛቸውን ቀጠሉ፡፡ የአቶ ብርሃኑን ገጠመኞች በጥቂት መስሪያቤቶች ብቻ ያየናቸው ናቸው እንጂ በሁሉም መሰል የመንግስት መስሪያቤት፣ ተቋማትና ድርጅት ይፈፀሙ እንደነበር አይሰወርብንም፡፡

ጃንሆይ በተለይ ከ1950 ጀምሮ ባሉት ጊዜያቶች ፍፁም አምባገነን እየሆኑ እንደሄዱ የብዙዎች ስምምነት ነው፡፡ በተለይ በ1951 - 52 ዓ.ም በጃፓኖች የረቀቀ ምክርና የቴክኖሎጂ ድጋፍ በመመርኮዝ ስልጣናቸውን ለማጥበቅ የወሰዷቸው እርምጃዎች ወይም በተግባር የተረጎሟቸው አሰራሮች ለዚህ እውነታ ማስረጃ ናቸው፡፡

ሙስናን ለማስወገድ ቆርጠው ተነሱ ማለት በሹማምንቱ ሁሉ ተቃውሞ ይመጣል ማለት ነው፡፡ ሁሉም ሹማምንት ተቃወመ ማለት ዙፋኑን ለቀቁ ማለት ይሆናል፡፡ ለዚህም ይመስላል አቶ ብርሃኑን የመሰሉ ጽኑ አጋላጭ ከሁሉም ጋር እንዳያጋጪቸው ሰግተው ራቅ ያደረጓቸው፡፡



"በአሜሪካ የኢትዮጵያ አምባሳደርና ባለሙሉ ስልጣን እንደራሴ" ብለው ሾመው ላኳቸው አቶ ብርሃኑን፡፡

ይህ ምን ያሳያል? "እጉል ትግል አያዋጣኝምና ተዋቸው ይዝረፉ፡፡ እምላክ ልቦና ይስጣቸው እንጂ ሌላ ምን ይባላል፤ እነሱን ማን ተቆጣጥሮ ይችላል?" የማለት ያህል ነው፡፡ አቶ ብርሃኑ ድንቄ ግን ሁሉንም ነገር አውቀው ለህሊናቸው ያደሩ ሰው ነበሩና ከአሜሪካ ወደ ጃንሆይ በመጨረሻ በ1952 ዓ.ም የሚከተለውን ደብዳቤ ፃፉላቸው፡፡

"ለግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ንጉሠ ነገስት ዘኢትዮጵያ"

<u>አዲስ አበባ</u>

ግርማዊ ሆይ፤ በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ማኅበራዊ ህይወት የሚታየውን ምሬትና ግፍ በፍትህም መጓደል ምክንያት የሚደርሰውን የአስተዳደር በደል ስመለከት ወደአገሬ ለመግባት ያለኝን ኀሳብ ማቆየት ግድ እንደሆነብኝ ለግርማዊነትዎ መግለጥ አስፈላጊ መስሎ ታይቶኛል፡፡ ይህ ሁኔታ የሚታረምበትን በኅብረት ለመስራት ባንሞክር ታላቅ ብጥብጥ እንደሚያስከትልብን ከታሪክ መማር ካልቻልን ከተከታዩ መቅሰፍት የምናመልጥበትና የምንከለልበት ሰው ሰራሽ ዘዴ ይገኝለታል ብሎ ራስን መደለል በህልም ዓለም ውስጥ ለመኖር እንደመሞከር ይቆጠራል፡፡

ከዚህም በቀር ለተተኪው ትውልድ አቋም ይሆናሉ ብለን ተንከባክበን ልናሳድጋቸው ኃላፊነት ያለብንን ህፃናትና ውለታ ትተው ለማለፍ የተዘጋጁትን ሽማግሎቻችንንም ደህና እረፍት እንዲያገኙ ከአገሪቱ በተፈጥሮ ያገኙትን ዕድል መንፈግ ያሰኛል፡፡በዚህም ምክንያት በፈፀምነው ስህተት ታሪክ ምህረት ሊያደርግልን በፍፁም አይችልም፡፡ይህን የመሳሰለው ሁኔታ በብርቱ የሚያሳስበን መሆኑን ስንገልጥ ምንም እንኳ አንዳንድ ሰዎች "አንተ ምን አገባህ" በማለት በጉዳዩ ባለቤትነት ክፍያ ድርሻችንን ለማሳነስ ቢሞክሩም፤በኢትዮጵያዊነት ትክክለኛ መብት ላይ አጥብበው ያስመሩትን የወሰን ክልል አሜን ብሎ ለመቀበል ከቶ ስለሚያስቸግር እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ኃላፊነቱን የማስወረድ ተግባር እንዳለበት አይካድም፡፡

እኔም ይህን ምክንያት አድርጌ በአሁኑ የመንግስት አስተዳደር የደረሰውን ሕጉወጥ አፈፃፀም ሁሉ ለማረምና ፍትህን ለማደላደል የሚቻልበትን ኀሳብ በነፃ ለመግለጥ ስል ከውጭ አገር መቆየትን መረጥሁ፡፡

በአሁኑ አያያዝ እንዲቀጥል የተተወ እንደሆነ በኢትዮጵያ የወገን መለያየትና የደም መፋሰስ እንደሚያሰጋ የመላው ኢትዮጵያውያን ግምት የወደቀበት ነው፡፡ ዋናው ዓላማ ይህ እልቂት የሚወገድበት መድሐኒቱ ምንድነው? ለተባለው ጥያቄ ለመመለስ እንደሆነ ጥርጥር የለውም፡፡ መቼም እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በሚመስለውና በሚያምንበት ረገድ

በመሐላ የተሰጠው ቃል ፈርሷል እያሉ አያሌ ኢትዮጵያውያን እንደሚያማርሩ ግርማዊነትም ሳይሰማው አይቀርም፡፡ መቼም ሕገ-መንግስቱን ለመጣስ አንድ የጽህፈት ሚኒስቴር ደብዳቤ ይበቃል፡፡ እንግዲህ ህዝቡ ወይም ሹማምንቱ ለንጉሠ ነገስቱ ታማኝ ነኝ እያሉ ቢምሉም፤ ንጉሠ ነገስቱ በበኩሉ መሐላውን የሚጠብቅ ካልሆነ በመሐላቸው ታስረው እንደማይኖሩ በልጅ እያሡ ጊዜ የደረሠው ሁኔታ ምሳሌ ሊሆን ይችል ይመስለኛል፡፡

ቀሽንግተን፤ ግንቦት 25፤52

ከታላቅ አክብሮታዊ ፍርሐት ጋራ

ብርሃኑ ድንቄ፡፡" ይላል ደብዳቤው፡፡

ጃንሆይ ግን ዛሬም ድረስ በአፍሪካ መሪዎች ዘንድ የማይሞከረውን ዙፋን መልቀቅን በሚመለከት መልሳቸው አንድ ነው፡፡ "ሞት ይንቀለኝ" አበቃ፡፡

አፍሪካ ውስጥ መፈንቅለ መንግስት ያላስተናገደ አገር የለም፡፡ በፈቃደኝነት ስልጣን መልቀቅ? አይታሰብም፡፡ እንኳን በዚያን ጊዜ ሕገ-መንግስቱ እንደማይለቁ አረጋግጠላቸው፣ንጉሰነገስት ሆነው፣ ዛሬ እንኳን ፓርቲ፣ ምርጫ ባለበት ዘመን ማንም አይለቅም፡፡ ሶስት ያህል አፍሪካዊ አገሮች ብቻ ታይተዋል፡፡ ስልጣንን በምርጫ /በሰላማዊ/ ያስተላለፉ፡፡ በነገራችን ላይ ከነፃነት በኋላ በአፍሪካ መፈንቅለ መንግስት አንደኛ ደረጃ ላይ የምትገኘው ሱዳን ስትሆን 25 ጊዜ የተሳካና ያልተሳካ መፈንቅለ መንግስት ተካሂዶባታል፡፡ ኢትዮጵያ ዝቅተኛውን ደረጃ ይዛለች 6 ጊዜ በቻ ስለሆነ፡፡ ሌላውም በአሰራዎቹ ይተመናል፡፡ ችግሩ ግን ይሄ ብቻ አይደለም፡፡ ስልጣንን ለማጥበቅ የሚሰሩ ስራዎች ብዙ በመሆናቸው፤በዚህም ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊና በተለይም ኢኮኖሚያዊ ብክነት ይከሰታል፡፡ ታማኝ ሹማምንት ሲዘርፉ እንዲኖሩ መፍቀድንም ያካትታል፡፡ የ"አባልን" "አበል" ጨምሮ ብዙ ገንዘብ በስልጣን ላይ ኢንቨስት ይደረጋል፡፡ የጃንሆይ ጥፋት በዚህ ክብ ውስጥ የሚሽከረከር ነው፡፡ እናም ከክቡ ውጪ ያለውን ህዝብ ዘነጉት፡፡

ጃንሆይ የከተማውን ንቅዝ ሹማምንት እያወቁ ትተውታል፡፡ይህም ህዝቡን በንቅዝ ሹማምንት የጭቆና ቀንበር ስር እንዲኖር መፍቀድ ማለት ሲሆን፤ከህዝቤ ስልጣኔ ይበልጣል የሚል እንድምታ ያለው ግዙፍ ጥፋት ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል ነው፡፡

ከዚህም ባለፈ ጃንሆይ በወቅቱ የነበረውን ዓለም አቀፍ የአስተዳደር ስርዓትና የኢትዮጵያ ህዝብም የግንዛቤ አድማሱ መስፋቱንም ሆነ ለውጥ መፈለጉን ማሰብ አልፈለጉም፡፡ ሌላው ቀርቶ ብዙ የአፍሪካ አገሮች ከቅኝ ገዥዎቻቸው ነፃ ለመውጣት የተንቀሳቀሱበትና ነፃ ከሆኑ በኋላም የይስሙላም ቢሆን ዲሞክራሲያዊ ምርጫ እያካሄዱ በነበረበት



ሁኔታ የኢትዮጵያ ሕገ-መንግስት ግን ንጉሠነገስቱን "ኃይሉ የማይደፈር፣ የማይገሰስ" በሚል የእድሜ ልክ ሕግ ሆኖ ይቀጥላል ብለው መታተራቸው አንዱና ዋናው ጥፋታቸው ሲሆን፤ ዘውዱ እንደተከበረ ሆኖ ከዘውዱ ቤታች እንኳ ዴሞክራሲያዊ መንግስት ለመመስረት የሚቻልበትን አማራጭ አልተጠቀሙበትም፡፡ የጳጳሡን ግዝትም ሆነ "በእግዚአብሔር የተሾሙ" የሚለውን ቃል እንደጥንቱ ህዝብ ምሁሩም ጠብቆትና አክብሮት ይቀጥላል ብለው ማሰባቸውም በዘመናቸው ያሳዩት የመጀመሪያው "የዋህነታቸው" ሆኖ የሚመዘገብ ነው፡፡ እነዚህን የመሰሉ የለውጥ አስተሳሰቦች በተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ዘንድ ሊብላላ እንደሚችል ቢያስቡም፤ ጥቂቶች ሊጠቁሟቸው ቢሞክሩም "የኢትዮጵያ ህዝብ ለዚያ አይነቱ አስተዳደር ልምድ የለውም፤ ኃላፊነቱን ለመሸከም ገና አልደረሰም" የሚል ምላሽ እየሰጡ፤ ነገር ግን በጎን የሁኔታውን አስጊነት ተመልክተው ወደመፍትሔው ከማምራት ይልቅ የመረጡት መንገድ ሥልጣናቸው ከዚህ መሰሉ አደጋ ተጠብቆ የሚቀጥልበትን ሁኔታ ማመቻቸት ሆነ፡፡ ከዚሁም ጋር ተያይዞ የአስተዳደር ክሽፈት ተፈጠረና አልደረሰም ያሉት ህዝብ ደርሶ ጠበቃቸው፡፡ ከዚህ አንፃር የጃንሆይ ጥፋት በአፍቃሬ ስልጣንነታቸው ስር ተጠቃሎ የሚገለፅ ሆነ፡፡

በጃንሆይ ላይ የተነሱ አመጾች

ጃንሆይ ለአመፅ ብርቅ አይደሉም፡፡ ከስደት ከተመለሱ በኋላ በሰጡት ሹመትና ሽልማት "ፍትሐዊ አይደለም" በሚል ተዝቢ መነሻ በርካቶች ባይሆኑም አምፀዋል፡፡ ለምሳሌ ጀግናው የጎጃም አርበኛ በላይ ዘለቀ የንጉሡን ሹመት አሰጣጥ ተቃውሟል፡፡ በጎጃም የጠላትን ጦር ሲያንቀጠቅጥ የነበረ የተዋጣለት ጀግና ነው በላይ ዘለቀ፡፡ ከእርሱም ጋር ልጅ ኃይሉ በለው፣ ደጃዝማች መንገሻ ጀንበሬና ደጃዝማች ነጋሽ በዛብህ በድፍን ጎጃም በአርበኝነት ይታገሉ ነበር፡፡ ከበላይ ዘለቀ በስተቀር ሦስቱ የነገስታት ዘር ናቸው፡፡ ከነፃነት በኋላ በ1934 ዓ.ም ጃንሆይ ከጎጃሙ ንጉስ ተክለሐይማኖት ለሚወለዱት ለልጅ ኃይሉ በለው ከራስ ማዕረግ ጋር የጎጃም ጠቅላይ ገዥነት፣ ለደጃዝማች መንገሻ ከቢትወደድ ማዕረግ ጋር የጎጃም ምክትል ጠቅላይ ገዥነት፣ ለደጃዝማች ነጋሽ ከቢትወደድ ማዕረግ ጋር የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት ፕሬዝዳንትነትን ሲሰጡ ለልጅ በላይ ዘለቀ ደግሞ ከደጃዝማች ማዕረግ ጋር በጎጃም የቢቸና አውራጃ ገዥነትን ሾሙት፡፡

በአርበኝነቱ ዘመን መሪ የነበረውና በጀግንነት ማንም ያልደረሰበትን ሰው ከእነርሱ ያነሰ ሹመት ሲሰጡት ቅር ተሰኘ፡፡ የንጉሡን ትዕዛዝና ሹመት ውድቅ በማድረግ ከተከታዮቹ ጋር የጎጃሙን የሶማ ኮረብታን ይዞ አልገዛም አለ፡፡

ሚያዚያ 16 ቀን 1935 ዓ.ም የመንግስት ጦር ዘምቶበት የተኩስ ልውውጥ ተደርጎ 38 ሰዎች ሞተው 92 ቆሰሉ፡፡ከሦስት ወር በኋላ ከ19 ተከታዮቹ ጋር ተማርኮ ወደ አዲስ አበባ መጣ፡፡የእስራት ቅጣት ተፈረደበትና ወሊሶ ሄዶ ታሰረ፡፡ ከወሊሶ ሲያመልጥ በድጋሚ ተያዘና ወንድሙን እጅጉ ዘለቀን ጨምሮ ከሌሎች እስረኛ ከሆኑ ባንዳዎች ጋር በአዲስ አበባ ታሰረ፡፡ታህሳስ 19 ቀን 1937 ዓ.ም ከ5 እስረኞች ጋር ከእስር ቤት አምልጠው ወደ ጎጃም ለመገስገስ ጉዞ ሲጀምሩ በ3ኛው ቀን ሱሉልታ ላይ ተይዘው እንደገና ወደ አዲስ አበባ አመጧቸው፡፡ የጦር ፍርድ ቤት የወሰነው የሞት ቅጣት በጥር 5 ቀን 1937 ዓ.ም ተግባራዊ ሆነና በአደባባይ በስቅላት ተቀጣ፡፡

ሌላው አደገኛ አመፀኛ ደጃዝማች ታከለ ወልደሐዋርያት ናቸው፡፡ንጉሡ ስደትን ከመረጡ ጊዜ ጀምሮ ለ30 ዓመታት ያህል መንግስታቸውን ለመፈንቀል ሲጣጣሩ ነው የኖሩት፡፡እኒህ ሰው ሲታሰሩ፣ሲፈቱ፣ሲሾሙ፣ሲሻሩ፣ሲያሴሩ ነው ያሳለፉት፡፡

በመጀመሪያ አርበኞችን አስተባብረው አሳድመዋል ተብለው ታሰሩ፡፡ እንደገና ተፈትተው በ1938 ዓ.ም ምክትል አፈ-ንጉስ ሆነው ተሾሙ፡፡ አመት ሳይቆዩ ሌላ ተመሳሳይ ሴራ ሲጠነስሱ ተደረሰባቸውና ታስረው 7 ዓመታትን አሳለፉ፡፡ ተፈቱና የአገር ግዛት ምክትል ሚኒስትርና የአፈ-ንጉሥነቱ ስልጣን ተመለሰላቸው፡፡ ይሄ ሁሉ ሲሆን ጃንሆይ ከአሁን አሁን ይበርድላቸዋል ብለው በመገመትና ጀግንነታቸውንም በደንብ ስለሚያውቁት ነበር የሚታገሷቸው፡፡ በመጨረሻ በ1962 ዓ.ም ጃንሆይ የሜታ አቦ ቢራ ፋብሪካን ለመጎብኘት ሲሄዱ ሰበታ አካባቢ ፈንጅ አጥምደው ንጉሡን ከነመኪናቸው ድምጥማጣቸውን ሊያጠፉ ተዘጋጁ፡፡ ሁኔታው ቀድሞ በጥቆማ ተደረሰበትና ከሸፈ፡፡ ደጃዝማች ታከለ ቤታቸው መሸገው ነበርና በወታደር ተከቦ ተኩስ ተከፈተ፡፡ እጅ አልሰጥም ብለው ሲዋጉ ቆይተው ሊያዙ ሲሉ ራሳቸውን ገደሉ፡፡

የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት ፕሬዝዳንት ሆነው የተሾሙት ቢትወደድ ነጋሽ በዛብህም እንዲሁ በንጉሡ ላይ አምፀው ነበር፡፡ ወታደራዊ መኮንኖችን አስተባብረው ንጉሡን በመግደል የሪፐብሊክ መንግስት ለመመስረት እንደነበር ይነገራል፡፡ ይህም ልክ እንደ ደጃዝማች ታከለ አይነት መሆኑ ነው፡፡ በመጨረሻ ግን በ1943 ዓ.ም ይሄው ሴራ ተደርሶበት በእስራት ተቀጡ፡፡ የእነዚህን አድመኞች እንቅስቃሴ ሁሉ በቁጥጥር ስር ያውል የነበረውና ለፍርድ ያቀርብ የነበረው ኮሎኔል መንግስቱ ንዋይ ነበር፡፡ የ1943ቱን አመፅ በቁጥጥር ስር ካዋለ በኋላ ደግሞ በ10 ዓመቱ ብርጋዴር ጄኔራል መንግስቱ ንዋይ ራሱ ከወንድሙ



ከገርማሜ ንዋይ ጋር ሆኖ የታህሳስ 5 ቀን 1953 ዓ.ምቱን መፈንቅለ መንግስት ሞከረ፡፡

ይህ ሙከራ ከላይ እንዳየናቸው በግል ኩርፊያና በመሳሰሉት ሳይሆን፤ምሁራዊ አስተሳሰብ የታከለበትና ፖለቲካዊ፣ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ መሠረት የነበረው ስርነቀል ለውጥን የሚሻ እንደነበር ከአነሳሱ ያስታውቅ ነበር፡፡ አነሳሱም ነው ለዘላቂ ለውጥ ፍለጋ ብዙዎችን እንዲነቃቁ በር የከፈተው እንጂ ከዚህ ጊዜ በፊት ምሁሩም፣ጠሩም፣ሠራተኛውም ሆነ ሌላው ምን አይነት ለውጥ እንደሚፈልግ ለይቶ አያውቀውም ነበር ለማለት ይቻላል፡፡ቢያውቅም እንዴት መነሳት እንዳለበት አያውቅም ወይም አይደፍርም፡፡በአጠቃላይ የንጉሡ ዙፋን እንደሚነቃነቅ የተደረሰበት ዘመንና ሁኔታ የተከሰተው በመንግስቱ ንዋይ ሙከራ ነው፡፡

ገርማሜ ንዋይ በአገር ውስጥም በአሜሪካም በዘመናዊ ትምህርት ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰ የዚያ ዘመን ምሁር ነበር፡፡ ብርጋዴር ጄኔራል መንግስቱ ነዋይም ከወረራው በፊት ተጀምሮ በነበረው ዘመናዊ የጦር ትምህርት ቤት መሰልጠን ጀምሮ የነበረና ከጥቁር አንበሳ አባላት ውስጥ አንዱ የነበረ አርበኛ ነው፡፡ ከነፃነት በኋላም በወታደራዊ ማዕረጎች በየጊዜው እያደገ የንጉሡ ታማኝ ሆኖ ጄኔራልነት ደርሷል፡፡ በዚህም የክቡር ዘበኛ ክፍለ ጦር አዛዥ ሆኗል፡፡

የጎሳቡ አፍላቂ ገርማሜ እንደሆነ የሚነገርለት ይህ መፈንቅለ መንግስት የኮሎኔል ወርቅነህ ገበየሁ /የፀጥታ ኃላፊው/ና የመንግስቱ ንዋይ የጦር ትብብርን አግኝቶ ጥቂት ተራምዶ ነበር፡፡ በሬዲዮም በአልጋወራሽ አስፋወሰን ኃይለስላሴ ንባብ አዋጅ አሰምተው ነበር፡፡

"የኢትዮጵያን ማኅበራዊና ብሔራዊ የእድገት እርምጃ ጥቂት ራስ ወዳድ ግለሰቦች ወደኋላ አስቀርተውታል፤ በቅርቡ የተነሱ የአፍሪካ አገሮች በስልጣኔና በእድገት ጥለውን ሄደዋል፤ አጠቃላይ አገዛዙ ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍል እየጎዳ ነው፤ የህዝቡ ቁጭት ለዚህ ተግባር አነሳስቶናል፤ ፋብሪካዎችን እናበዛለን፤ ትምህርት ቤቶች ይስፋፋሉ፤ የወታደር ደመወዝ ይጨመራል፤ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ሁሉ እናከብራለን..." የሚል ማኑፌስቷቸውን ታህሳስ 5 በሬዲዮ አሰራጩ፡፡ ብዙ ባለሥልጣናትንም አሰሩ፡፡ ሆኖም የክቡር ዘበኛና የፖሊስ ሠራዊት ብቻውን በቂ አልነበረም፡፡

ላጺሶ አገላለፅ፣ "በ1956 ዓ.ም ንጉሡ በሰራ ጉብኝት እስከ ባሌ ክፍለአገር በመሄድ 1ኛ. በሌላ ደቡብ ክፍላተ አገር ድሮ እንደተደረገው ሁሉ አሁን ለባሌም ባላባቶች ከመሬት የባላባት ሲሶ እንደሚሰጣቸው ቃል ገቡ። 2ኛ. ከ1945 - 1954 ዓ.ም የግብር ውዝፍ ምክንያት "ግብረ ጠል" ተብሎ በመንግስት የተወረሰው መሬት (ለዓመታት ግብር ያልተከፈለበት ሆኖ ሲገኝ ይወረስ ስለነበር) ለህዝብ እንደሚመለስለት ተናገሩ። 3ኛ. ለብዙ የክፍለአገሩ ተወላጆች ሹመትና ማዕረግ ሰጡ። 4ኛ. የሼክ ሁሴንን መስጊድ ጎብኝተው ወደአዲስ አበባ ተመለሱ።

ይሁን እንጂ በአመፅ መንፈስና ተግባር አንዴ ከተቀሰቀሰ በኋላ ለረጅም ዘመን በጉልተኞችና ባለሥልጣኖች ጭቆና በኃይል የተመረረው የባሌ ህዝብ በንጉሡ ጉብኝትና መልካም ቃላት ከአመፅ እርምጃው አልተገታም። በአጭሩ ከ1956 - 1959 ዓ.ም የክፍለ አገሩ እንደራሴ በፊትአውራሪ ወርቁ እንቁስላሴ መሪነት የባሌ ክፍለአገር ጉልተኞችና ባለሥልጣኖች ከፖሊስና ከብሔራዊ ጦር ጋር የህዝቡን አመፅ መቆጣጠርና ማቆም ፈፅሞ አቃታቸው። በመሆኑም እንደራሴው እንዲነሳ ተደርጎ በታህሳስ 1959 ዓ.ም የባሌ አራቱ የኤልከሬ፣ የዶሎ፣የገናሌና የዋቤ የአመፅ አውራጃዎች ከአጎራባቹ የቦረና አውራጃ ጋር በወታደር ስር እንዲሆኑ ተወሰነ።" በ4ኛ ክፍለ ጦር ስር መሆኑ ነው።

እናም በክፍለ ጦሩ አዛዥ በጄኔራል ጃገማ ኬሎ አመራር ስር ከሆኑ ጊዜ ጀምሮ ልዩ ዲፕሎማሲያዊ ጥረት ተደርጎ በ1962 ዓ.ም ጄኔራል ዋቆ ጉቶ ለመንግሰት እጁን ሲሰጥ የባሌና የአጎራባቾች አመፅ ተገታ።

በአብዮቱ መዳረሻ ከአገሪቱ ገበሬዎች ውስጥ ከአጠቃላዩ ሲሶ ያህሉ ጭሰኛ ነበሩ። "ጭሰኛ" ማለት የራሱ መሬት የሌለውና በሌሎች መሬት ላይ በጉልበቱ እያገለገለ የሚኖር፣ በማንኛውም ሰዓት ባለቤቱ ሊያፈናቅለው የሚችል አገልጋይ ማለት ነው። "ተቀጣሪ" ማለት ነው።

"ገባር" ሲባል ደግሞ በጃንሆይ ጊዜ "ግብር ከፋይ" ማለት ነው።

"ፊውዳል" ማለት ደግሞ መሬትን በሞኖፖል ይዞ እንዳሻው የሚያደርግ አገዛዝ ማለት ነው። ጥቂት ምሁራን የጃንሆይን አገዛዝ "ፊውዶ ቡርዧ" ብለው ወፈር አድርገው ይጠሩታል። ከፊል ካፒታሊዝም ማለት ነው።

ወዝአደር፣ ላብአደር፣ ሠርቶአደር የሚባሉ የዚያ ዘመን ስያሜዎችም ግልፅ ናቸው። በጃንሆይ ጊዜ ባላባቱና ባለሐብቱ የያዙት ሰፋፊ መሬት እንዳለ ሆኖ፣ ተራ ገበሬዎች ደግሞ 1 ሔክታር ማሳ ነበራቸው። ከአሁኑ ጋር ሲነፃፀር ባለፀጋ የሚያሰኝ ይዞታ ነበር። ለማንኛውም በዚያ ጊዜ ገበሬው ሁሉ ከየአቅጣጫው ጭቆናው በዝቶበት ስለነበር አመፀ።



በየካቲት ወር 2002 ዓ.ም ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ /የቀድሞው የኢህፌዲሪ ፕሬዝዳንት/ በአንድ ስብሰባ ላይ ለስራ ተገኝቼ ነበርና እንዲህ ሲሉ አደመጥኩ "ከ1950ዎቹ ጀምሮ መሬት ላራሹን ሳቀነቅን ኖሬያለሁ፣ አሁንም ማሰብ እስካቆም ድረስ ይሄንኑ አቋሜን አልለቅም"

በጃንሆይ ላይ ከተነሳው ዘርፈ ብዙና ከየአቅጣጫው የተቀጣጠለው አመፅ ይሄን ያህል ፈታኝ አልነበረም። በከፍተኛ ሁኔታ ስርዓቱን የተፈታተነው ተማሪው ነው። የተማሪው ተቃውሞ ከ1953 ዓ.ም ጀምሮ ውስጥ ውስጡን ሲብላላ ቆይቶ፣ ከ1957 ዓ.ም በኋላ ወደ አደባባይ በመውጣት የተቃውሞ ሰልፍ ማድረግ ተለመደ። በድርድር የማይከሽፍና ስር ነቀል ለውጥ የሚፈልግ ሆኖ የተነሳው ምሁር እስከመጨረሻው የሚያቆመው ኃይል ጠፍቶ አብዮቱን አሳብጧል።

በዩኒቨርሲቲው ውስጥ የተለያዩ ማኅበራት በተማሪው እየተመሰረቱ፣ የክርክር መድረኮች እየተዘጋጁ፣ ለከፍተኛ ትምህርት ወደሌላው ዓለም የተላኩ ምሁራንም ተመሳሳይ ማኅበር እየመሠረቱ ስርዓቱን በእጅጉ በመተቸት ተግባር ላይ ተጠመዱ።በተማሪው ልሳን በሆኑ መጽሔቶች የተለያዩ ፖለቲካዊ ትንታኔዎች ይቀርቡ ጀመር።ርዕዮተ ዓለማዊ መፈክሮችና መግለጫዎች በየጊዜው ይሰራጫሉ።

እንዲህ እንዲያ እያሉ በ1957 "መሬት ለአራሹ" ብለው ሰልፍ ወጡ። ከመንግስት የፀጥታ ኃይሎች ጋር ፊት ለፊት መጋተር የተጀመረውም በዚሁ ዘመን ነበር። በየጊዜው የሚያነሱት አጀንዳ የተለያዩ እየሆነ ቀጠለና በ1961 ዓ.ም "የትምህርት ፖሊሲው ይሻሻል" የሚል ጥያቄ ሲያነሱ ይህ ጉዳይ ከዩኒቨርሲቲው ማኅበረሰብ አልፎ በ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችም ድጋፍ ያለው ጥያቄ ሆነ። በ1962 ዓ.ም በደንብ ያላብላሉትን ጥያቄ ይዘው የወጡት ወገኖች ነበር መንግስትን ቁጡ ያደረገው። ይህም በግርግር መሃል ድንገት የተሰነዘረና "ብሔር ብሔረሰቦች የራሳቸውን እድል በራሳቸው መወሰን አለባቸው" የሚል ነው። የጃንሆይ መንግስት ከተራ ድብደባና ግርፋት አልፎ ጠንከር ያለውን እርምጃ ወሰደ። በታህሳስ 19 ቀን 1962 ዓ.ም ስመጥር የሆነው የተማሪዎች መሪ ጥላሁን ግዛው በአደባባይ ተመታ።(የጥላሁንን መመታት በሚመለከት ሁለት ነጥቦች ይነሳሉ።አንዱ ከመንግስት ታጣቂዎች በተተኮሰ ጥይት የሚል ሲሆን፣ሌላውና ሰፊ ተቀባይነት አግኝቶ ያለው ገለጻ ደግሞ ወደፊት ስውር አሰራራቸውን በስፋት በምናይላቸው የአመጽ አነሳሽ በነበሩ የኤርትራ ድርጅት አባላት አማካኝነት በግርግሩ መሀል በረቀቀ ዘዴ እንደተመታ ነው)በዚህ ጊዜ ተማሪው "የጀግናችን ሬሣ እንቀብራለን" በሚል ወደ የካቲት 12 ሆስፒታል ሆ ብሎ ሲነጉድ ጥላሁን አርፏል።አመፁ ተቀጣጥሎ ቀጠለ። የፀጥታ ጥበቃ አባላቱ ተኩስ ከፍተው

ጥቂቶች ሲገደሉ ብዙዎች ቆሰሉ፡፡ ዓለም አቀፉ ተቃውሞም እጅግ እየበረታ ሄደ፡፡



የጸጥታ ጠባቂዎች እና የተማሪዎች ግብግብ

ገሚሱ አገር ውስጥ ሆኖ ሲፋለም የቀረው በየውጭ አገሩ እየፈለሰ ማኅበራቱን ተቀላቀለ፡፡ አመፁ የአውሮፕላን ጠለፋንም ያካተተ ነበር፡፡ ህዳር 29 ቀን 1965 ዓ.ም እንዋለልኝ መኮንን እና ማርታ መብራቱን የመሣሠሉ አደራጅና አስተባባሪዎች ወደ ኤርፖርት አምርተው ፕሌን ውስጥ ከገቡ በኋላ ጠለፋውን ከመተግበራቸው በፊት መንግስት ባዘጋጃቸው የጠለፋ አክሻፊ ኃይሎች እዚያው በጥይት ተደብድበው ሞቱ፡፡

የኢትዮጵያውያን የፖለቲካ ልዩነት፣ የፓርቲ ምስረታ፣ የርዕዮት መለያየት፣ በቡድን መደራጀትና ፖለቲካዊ አጀንዳ አንስቶ መንግስትን የመሞገት ተግባር ምንጭም ሆነ አፈሳሰሱ የሚነሳው ከዚሁ ከዩኒቨርሲቲው ማኅበረሰብ ሆነ፡፡ በኢትዮጵያ ታሪክም ለመጀመሪያ ጊዜ ያልታጠቀ ኅብረተሰብ መንግስትን ተቃውሞ ድምፁን ያሰማበት ዘመን ተከሰተ፡፡ የመጀመሪያዎቹ ኢትዮጵያዊ ምሁራን ምንም እንኳ የተቀረፁት በምዕራባውያን ትምህርት የነበረ ቢሆንም፤ የምዕራባውያንን የቡርዣ አገዛዝ አንሸከምም አሉ፡፡

ሐሮልድ ማርክስ "THE ULTIMATE IRONY" ብለው እንደገለፁት ጃንሆይ በስኬታቸው የመውደቃቸው ጉዳይ ግልፅ እየሆነ ሄደ፡፡ በወቅቱ የጃንሆይ መንግስት በተማሪዎች ላይ ጨከን ያለ እርምጃ ወሰዷል፡፡

ተማሪውም በተጨከነበት ቁጥር የታጋይነት መንፈሱ እያደገ የማይገሠሠውን ማዕረግ ገሶ፣የማይደፈረውን ክብር ደፍሮ፣ የጃንሆይን ዙፋን ገዝግዞ አብዮቱን አሳበጠ፡፡ ነገር ግን ሳይፈነዳ ጥቂት ጊዜ ይቆይ ዘንድ የእገዛዙ (የዘውዱ) ጠበቃ መስለው የራሳቸውን የዘረፋ ጊዜ



ለማራዘም የሚሹ ባለስልጣናት መፍትሔው ኃይል እንደሆነ ገልፀው እሱኑ ተገበሩት፡፡

ጃንሆይ እና ኪነ-ጥበብ

በጃንሆይ ጊዜ ዘመናዊ ማተሚያ ቤቶች ተከፍተዋል፡፡ የቴአትርና የስነ-ጥበብ ትምህርቶች እንዲሁም የስነ-ጽሁፍ ዲፓርትመንቶች ተከፍተው ትምህርቱ በአገር ውስጥ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት መሰጠት ጀምሯል፡፡ ይህ ከመሆኑ በፊትም በጋዜጠኝነትና በሌሎች ዘርፎች ወደ ውጪ አገር ሄደው እንዲማሩ የጃንሆይ መልካም ፈቃድ ሆኖ ተምረው የተመለሱ ኢትዮጵያውያን ነበሩ፡፡ ከዚሁም ጋር ተያይዞ ጋዜጦች፣ መፅሔቶች፣ የልብወለድና የኢ-ልብወለድ መጽሐፍቶች፣ የታሪክ መጽሐፍትና የግጥም መድብሎች እየታተሙ ለአንባብያን ይደርሱ ነበር፡፡ ቴአትር ቤቶችም ተከፍተው በየመድረኩ ተውኔቶች ይቀርቡ ነበር፡፡

ምንም እንኳ እንደዛሬዎቹ አፍሪካውያን መሪዎች አገዛዛቸውን በብዕር የሚያወግዙ ደራሲያንና ፀሐፌ ተውኔቶች በገኸረው አካል የተለመደው ኃይለኛ በትር በጃንሆይ ጊዜም መኖሩ ባይዘነጋ፣ በተጠቀሰው ዘርፍ በርካታ ስራዎች የተሰሩት በጃንሆይ ዘመን ነው፡፡በዘርፉ የጃንሆይን አገዛዝ በጥልቀት የሚተቹ የኪነ-ጥበብ ውጤቶች ይታገዱ እንደነበር የመታወቁን ያህልም፤ለዘብተኛ ትችት የያዙት ሳይታገዱ መቀጠላቸው አይካድም፡፡ጃንሆይንና አገዛዛቸውን የሚያሞካሹት በርክተው የመገኘታቸውን ያህልም፤የሚያጣጥሉዋቸውም በጥቂቱ እንደነበሩ ግልፅ ነው፡፡

ገጣሚያን፣ደራሲያንና ፀሐፌ ተውኔቶች በስራቸው የመታሰር የመንገላታታቸውን ያህልም በይቅርታ የታለፉ በርካታ የእገዛዙ ተቺ የሆኑ ባለሙያዎች ነበሩ፡፡ በዚህ መሰሉ እንግልት ሞራላቸው የተነካ የኪነ-ጥበብ ሰዎች እንደነበሩ ሁሉም፤ በዘርፉ ባበረከቱት አስተዋፅኦ የማበረታቻ ሽልማት ከጃንሆይ እጅ የተቀበሉ ሞልተዋል፡፡ ለአብነትም የ1952ቱ የብላቴን ጌታ ፀጋዬ ገብረመድህን ሽልማትን መጥቀስ ይቻላል፡፡ምንም ቢባል ግን በኢትዮጵያ ታሪክ ለዚህ ዘርፍ የጃንሆይን ያህል ትኩረት ሰጥቶ የተንቀሳቀሰ መንግስት ኖሮ አያውቅም፡፡ ቴአትር ቤቶችን ብቻ ነጥለን ብናይ በጃንሆይ ጊዜ የተመሠረቱት ናቸው ዛሬም ድረስ አገልግሎት እየሰጡ ያሉት፡፡

ከጃንሆይ በኋላ በተነሱ የኢትዮጵያ መንግስታት አንድም ቴአትር ቤት ተገንብቶ አልተጨመረም፡፡(በቅርቡ በእቅድ ደረጃ ሊገነባ የታሰበው የብሔራዊ ቴአትር አዲስ ተጨማሪ ህንፃ ምናልባት ተግባራዊ ከሆነ ብቻ የጃንሆይ ውጤት ያልሆነ ቴአትር ቤት ሆኖ ይመዘገባል) በተረፈ ያሉት ሁሉ የጃንሆይ ዘመን ውጤቶች ናቸው፡፡

በዘመነ ዛግዌ ብልጭ እንዳለ የሚነገርለትና በጎንደሩ ንጉስ በአፄ ዳዊት ዘመን በቤተ-መንግስት ደረጃ በኢትዮጵያ እየተለመደ የሄደው ቴአትር፤በዳግማዊ ምኒልክ ጊዜ ዘመናዊ ቅርፅ ይዞ በትምህርት ቤቶች አካባቢ ቀጥሎ ነበር፡፡

ከትምህርት ቤቶች አልፎ ቴአትር (ድራማ) ወደ መድረክ የወጣው ግን በጃንሆይ ዘመን በ1927 ዓም በተቋቋመው በአገር ፍቅር ማኅበር አማካኝነት ነው፡፡ በወቅቱ ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ከመውረሯ አንድ ዓመት ቀደም ብሎ የስነልቡና ጦርነት ተጀምሮ ነበር፡፡ ይህም በተለያዩ የሐሰት ፕሮፖጋንዳዎች የኢትዮጵያን ህዝብ የትግል መንፈስ አዳክሞና አንድነቱን ሸርሽሮ፣ ወረራው በሚጀመርበት ወቅት ህዝቡ ከመንግስት ጎን ቢቆም ከሞት በቀር የሚያተርፈው አንዳች ነገር እንደማይኖር የሚገልፅ ሆኖ በኢጣሊያ መንግሰት እየተዘጋጀ የሚቀርብ ነበር፡፡ ከዚያ ይልቅ የኢትዮጵያ ህዝብ ሊያሰለጥነው ከሚመጣ ቅኝ ገዥ አገር ጋር ቢወዳጅ ትርፋማ እንደሚሆን ለማስገንዘብ የሚጠቀሙበት የፕሮፖጋንዳ ስልት ነበር፡፡

የኢጣሊያ የፕሮፖጋንዳ ስራ በህዝቡ ዘንድ የሚያሳድረው ተፅዕኖ ከባድ መሆኑን በመገንዘብም ፕሮፖጋንዳን በፕሮፖጋንዳ የማክሸፉን ስራ ኢትዮጵያውያኑ ጀመሩት፡፡ በ1927 ዓ.ም "የኢትዮጵያ ሀገር ፍቅር ማኅበር" ተቋቋመና በየሳምንቱ እሁድ ስብሰባ እየተደረገ፣ ለህዝቡ ኪነ-ጥበባዊ ለዛ ባለው አቀራረብ የአገርን ፍቅር የሚያስታውሱ፣ የጀግንነት መንፈስን የሚቀሰቅሱ ንግግሮች፣ ግጥሞች፣ መጣጥፎችና መዝሙሮች ይቀርቡ ጀመር፡፡በተጠቀሰው ጊዜ የኢጣሊያን ወራሪ ጦር በኦጋዴን ድንበር መክተው የመለሱት የእነደጃዝማች ኡመር ሰመተር ጀግንነት ሲሰማም፤ የአገር ፍቅር ማኅበር ከነበረበት የበለጠ ተሻሽሎ ብዙ ታዳሚዎችንም እያፈራ ተግባሩን በመቀጠል ወኔ ቀስቃሽ ንግግሮች መቅረብ ጀመሩ፡፡በወቅቱ ታዋቂ ከነበሩ ተናጋሪዎች ውስጥ አቶ ዮፍታሔ ንጉሴ (በኋላ ብላታ)፣ አቶ ደምሴ ወልደአማኑኤል (ደጃዝማች)፣ አቶ ክፍለ እግዚአ ይህደጎ (ብላታ)፣ አቶ ተመስገን ገብሬ፣ አቶ ኃይለገብርኤል ነገሮ፣ አቶ መንገሻ ከፈለ ይገኙበታል፡፡ እነዚህን የመሣሠሉ የአገር ፍቅር አባላት በንጉሡ ፊት ቀርበው የጠላትን ፕሮፖጋንዳ በመቃወምና የህዝቡን ወኔ በማነሳሳት የተጫወቱት ሚና በቀላሉ የሚታይ አልነበረም፡፡ በዚህ መልኩ የተጀመረው የመጀመሪያው ቴአትር ቤት አገር ፍቅር ሆነና፤ ቀጥሎ በ1948 ዓ.ም የዛሬው ብሔራዊ ቴአትር ቤት ተከፍቶ ስራውን ቀጠለ፡፡ ከዚያም የመዘጋጃ ቤት ቴአትር፣ቀጥሎም የቀድሞው የራስ ኃይሉ ሲኒማ ቤት የቴአትር መድረክ ተዘጋጅቶለት በመከፈቱ የቴአትር ቤቶችን ቁጥር ወደ 4 ከፍ ማድረግ ተቻለ፡፡ በተጨማሪም የድሮው "ሰይጣን ቤት" ይባል የነበረው ተሐድሶ ተደርጎለት "አምፊ ቴአትር" በሚል ስያሜው



ስራውን ቀጠለ፡፡ ከእነዚህ የጃንሆይ ዘመን ውጤቶች ውጪ ባለፉት 50 ዓመታት ውስጥ ምንም አይነት አዲስ ቴአትር ቤቶች አልተሰሩም፤ አልተጨመሩም፡፡



አርቲስት ዘነበች ታደሰ(ጭራ ቀረሽ)በወጣትነቷ ለጃንሆይ በበዓል ጊዜ እቅፍ አበባ ስታበረክት፡፡

ጥቅምት 25 ቀን 1952 ዓ.ም በቀድሞው ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ቴአትር ቤት የሩሲያ አርቲስቶች መጥተው ጃንሆይና እቴጌ መነን በተገኙበት የኪነጥበብ ውጤታቸውን አሳይተው ነበር፡፡ ከትእይንቱ በኋላ ጃንሆይ ለኢትዮጵያውያን የኪነ-ጥበብ ባለሙያዎች ተከታዩን መልዕክት አስተላልፈዋል፤

"ትምህርት ለሁሉ የሚሰጥ ነገር ነው፡፡እንደባህሪው ለመምረጥ ግን የእያንዳንዱ መንፈስና አካል የሚይዘው ነገር ነው፡፡

አሁን እዚህ ያየነው ሁሉ እድላችሁ ለዚሁ የመራችሁ መሆኑን ይገልፃል፡፡ መጀመር ብቻ ጠቃሚ ነገር አይደለም፡፡እስከፍፃሜው ግብ ማድረስ የበለጠ ነገር ነው፡፡ በዓለም ላይ ያሉ የታወቁ ሰዓሊዎች ስመ ጥሩ ሆነው፤ እነሱ ቢሞቱ አሁን እንዳልሞቱ ሆነው የሚቆጠሩት በእጃቸው ስራና በአእምሮአቸው ፈተናውን አልፈው ስለደረሱ ነው፡፡አሁን ከመካከላችሁ አዲስ የጀመራችሁም የቆያችሁም ትገኛላችሁ፡፡ ስለዚህ የጀመራችሁትን ወደ ጫፍ ብታደርሱ የራሳችሁን ስም ታስከብራላችሁ፡፡ ለእናንተም የዘላለም መታሰቢያ ይሆንላችኋል፡፡ለዚህ ነገር ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ያሰብንበት ለመሆኑ እነ አፈወርቅ ተክሌ ሄደው እንዲማሩ ያደረግነው ይህን የመሰለ ፍሬ እንዲገኝ በማመን ነው፡፡በየአይነቱም ዘመናዊውንም የጥንቱንም ስዕል ታዩታላችሁ፡፡ አሁን በሰራችሁት ስራ

ሁሉ ደስ እንዳሰኛችሁን እንደዚሁም ወደፊት ለአገራችሁ ስም ለምናስብለትም የትምህርት እድገት ምስክር እንድትሆኑ ጠንክራችሁ መስራት ነው።"/ፍሬ ከናፍር 1952ዓ.ም/

**ጃንሆይ እና ስፖርት**

ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ከመውረሩዋ በፊትና በኋላ በአዲስ አበባና በአስመራ ጥቂት የእግር ኳስ ቡድኖች ነበሩ።

በ1928 ዓ.ም የቅዱስ ጊዮርጊስ ቡድን አዲስ አበባ፣ በ1929 ዓ.ም የሐማሴን ቡድን አስመራ፣ በ1938 ዓ.ም የጦር ሠራዊት ጠቅል ቡድን አዲስ አበባ፣ እንዲሁም የተፈሪ ቡድን ከድሬዳዋ ተመስርተው የእግር ኳስ ውድድር ያደርጉ ነበር። በብዙ የውጭ ጨዋታዎችም ኢትዮጵያ ተካፋይ ነበረች። የኢትዮጵያ ሻምፒዮና በ1937 ዓ.ም ሲጀመርም፤ በጥሩ ድርጅት ባይሆንም በመካከለኛ ዝግጅት የተቋቋሙት 5 ያህል ቡድኖች በኢትዮጵያ ሻምፒዮና ተካፋይ ነበሩ።

ጃንሆይ ለስፖርቱ ምን ያህል ትኩረትና ዋጋ ይሰጡ እንደነበር ከአንደኛው እስከ ስድስተኛው የአፍሪካ ዋንጫ የብሔራዊ ቡድኑ ቋሚ ተሰላፊ የነበሩት አቶ አዋድ መሐመድ ለአዲስ ነገር ጋዜጣ በሰጡት ቃል አስታውሰዋል።

"ኢትዮጵያ አገራዊ ውድድር ስታደርግ ቀዳማዊ ኃይለሰላሴ አሉ ማለት ነበር። በወቅቱ መንግስት ለእግር ኳሱ ምን ያህል ትኩረት እንደሚያደርግ ብዙ መጠየቅ ሳያስፈልግ ዛሬም የምንጫወተው ያኔ በተገነባው ስቴዲየም መሆኑን ማሰብ ብቻ ይበቃል" ባይ ናቸው።

በእንጨት ታጥሮ የነበረውና በሚስማር ተራ በኩል ባለው የጎል ጀርባ ወንዝ የሚያልፍበት የዛሬው የአዲስ አበባ ስታዲየም የቀድሞው የቀዳማዊ ኃይለስላሴ ስታዲየም ከመሰራቱ በፊት ጨዋታዎች በጃንሆይ (ጃን) ሜዳ ላይ ነበር የሚካሄዱት። ጃን ሜዳ 30 ሺ ተመልካች የመያዝ አቅም ነበረው። ከ50 ዓመታት በላይም አገልግሏል።





ይድነቃቸው ከቀ.ኀ.ሥ ዋንጫ ሲቀበል

ከአዲስ አበባ ቀጥሎ በአስመራ የንግስተ ማባ ስታዲዩም፤ በድሬዳዋ-አስፋወሰን ስታዲየም እንዲሁም በሐረር፣ በባህርዳርና በሌሎች አስር የአገሪቱ ጠቅላይ ግዛቶች የተገነቡት ስታዲየሞች የጃንሆይ ዘመን ውጤቶች ናቸው።

ኢትዮጵያ የአፍሪካ ዋንጫን የማዘጋጀት እድል ያገኘችውም የአስመራውና የአዲስ አበባው ስታዲየሞች በተገነቡ ጊዜ ነው። ኢትዮጵያ፣ ግብፅና ሱዳን የጀመሩት የአፍሪካ ዋንጫ መካሄድ ከመጀመሩ በፊትም ታህሳስ 28 ቀን 1940 ዓ.ም ጃን ሜዳ ላይ ኢትዮጵያ ጅቡቲን 6 ለ 0 በማሸነፍ ነበር አገራዊ ውድድር የጀመረችው።

ኢትዮጵያ በ1954 ዓ.ም ሦስተኛውን፣ በ1960 ዓ.ም ስድስተኛውን የአፍሪካ ዋንጫ አስተናግዳለች። በዚያ ዘመን ለብሔራዊ ቡድኑ ከክለቦች ብቻ ሳይሆን ከየትምህርት ቤቱም ተጫዋቾች ይመለመሉ ነበር። ተጫዋቾችም ለጥቅማ ጥቅም የታደሉ አልነበሩም። ለእግር ኳስ ያላቸውን ፍቅር ብቻ መሠረት አድርገው ይጫወቱ የነበሩ ናቸው።

በባዶ እግር መጫወት በዓለም አቀፍ ደረጃ ሲከለከልና ታኬታ ብቻ ለኳስ ጨዋታ ሲፈቀድም ትጥቆቹ የሚመረቱት በውጭ አገር ስለሆነ መንግስት ወጪውን በማገናዘብ የስፖርት ትጥቆች ከቀረጥ ነፃ እንዲሆኑ

አድርጓል፡፡ ከትኬት ሽያጭ ላይም መንግስት ቀረጥ እንደማይወስድ በሕግ ተደነገገ፡፡

ሁኔታዎች እስኪመቻቹ ተጫዋቾች በትጥቅ አለመሟላት ምክንያት የደረሰባቸውን ችግር ለአብነት ስናነሳ፤ በ1951 ዓ.ም በግብፅ ካይሮ የተካሄደውን 2ኛውን የአፍሪካ ዋንጫ ያስታውሰናል፡፡ ግንቦት 14 ቀን በኢትዮጵያና በግብፅ መካከል የተደረገው ጨዋታ ግብፅ 4 ለ 0 ያሸነፈችበት ነበር፡፡ ለዚህ ሽንፈት የኢትዮጵያ ቡድን የሰጠው ምክንያት በሜዳ ውስጥ እንዳሉ የተጫዋቾቹ ታኬታዎች የመርገጫ ጡቶች እየወላለቁ በመበተናቸው ሳይጫወቱ ቀርተው ለመሸነፍ እንደተገደዱ ነው የገለፁት፡፡

ኢትዮጵያ በጃንሆይ ዘመን በተከታታይ በአፍሪካ ዋንጫ መካፈሏ በወቅቱ የዘርፉ ትልቅ ስኬት ሲሆን፤ ለተለያዩ የወዳጅነትና የአቋም ማጠንከሪያ ጨዋታዎች ከአውሮፓ ቡድኖች ጋርም ታደርግ ነበር፡፡ ከጎረቤት አገሮች ጀምሮ እስከ ሜክሲኮ ድረስ በመጓዝ ብሔራዊ ቡድኑ ተጫውቷል፡፡

ከእነዚህም ውስጥ መስከረም 19 ቀን 1961 ዓ.ም ሜክሲኮ እና ኢትዮጵያ በሜክሲኮ ሊእን ስታዲየም ተጫውተው ሜክሲኮ ኢትዮጵያን 3 ለ 0 አሸንፋለች፡፡ ጥር 14 ቀን 1959 ዓ.ም በአዲስ አበባ ኢትዮጵያና ሮማንያ ተጋጥመው ኢትዮጵያ ሮማንያን 2 ለ 1 አሸንፋለች፡፡ በአዲስ አበባ ታህሳስ 10 ቀን 1955 ዓ.ም ኢትዮጵያና ቱርክ ተጫውተው 0 ለ 0 በሆነ ውጤት ተለያይተዋል፡፡

በተጨማሪም ቺሊ ላይ ይካሄድ ለነበረው የዓለም ዋንጫ ኢትዮጵያ የማጣሪያ ጨዋታ የምታደርገው ከእስራኤል ጋር ነበር፡፡ (ያኔ የማጣሪያ ጨዋታ በእህጉር አይወሰንም ነበር) እናም የደርሶ መልስ ጨዋታ ግድ ነበርና የአዲስ አበባው ስታዲየም የተሟላ ስላልነበር ኢትዮጵያ ሁለቱንም ጨዋታዎች በቴላቪቭ ከተማ ማድረግ ነበረባት፡፡ የእስራኤል ቡድን በለመደው አየርና በደጋፊዎቹ ድጋፍ 3 ለ 2 እና 1 ለ 0 ኢትዮጵያን ማሸነፍ በመቻሉ የዚያ ወቅት የብሔራዊ ቡድን አባላትን በእጅጉ የሚከነክን ትውስታ ሆኖ አልፏል፡፡

በጃንሆይ ዘመን የነበረውን የእግር ኳስ ፌዴሬሽን ለመምራት የሚመረጡት በጊዜው ከነበሩ ባለሥልጣናትና ሚኒስትሮች እንደሆነ የሚገልፁት አቶ አዋድ መሀመድ "እግር ኳሱ ህይወት የነበረው የተከበሩ ሰዎች ይመሩት ስለነበር ብቻ ሳይሆን፤ ስፖርቱን ከልባቸው ይወዱት ስለነበረም ነው" በማለት "እንደ አቶ ይድነቃቸው ተሠማ ያሉ ስፖርቱ ደማቸው ውስጥ የተዋሃደባቸው ሰዎች እግር ኳሱ ስላገኘ" የላቀ ደረጃ ላይ ሊደርስ መቻሉን ይነግሩናል፡፡ ሚኒስትሮችና ከንቲባዎችም ለፌዴሬሽኑ ልዩ ትኩረት ሰጥተው እየተከታተሉና ያለአንዳች ጥቅማ ጥቅም



ኃላፊነታቸውን በአግባቡ እየተወጡ በጃንሆይ ጊዜ የነበረውን ስፖርት ውጤታማ እንዲሆን አድርገውታል፡፡

ጃንሆይ ፌዴሬሽኑ 25ኛ ዓመቱን ሲያከብር ያደረጉት ንግግር እንዲህ የሚል ነበር፤ "የኢትዮጵያ ፉትቦል ፌዴሬሽን ሃያ አምስተኛውን ዓመት ሲያከብር በማየታችን በጣም ተደስተናል፡፡ የዛሬ ሃያ አምስት ዓመት ድርጅቱ ገና ለመቋቋም በሚራመድበት ጊዜ ከዚያም በጥርጊያ ሜዳ ላይ ጃንሜዳ ከጅቡቲ ቡድን ጋር ሲጋጠም በድንኳን ውስጥ ተቀምጠን የተመለከትንበትን ጊዜ እናስታውሳለን፡፡

ይህ ስፖርት በኢትዮጵያ እንዲስፋፋ ያደረግነው ጥረትና እርዳታ ባሬ በአዲስ አበባ በድሬዳዋ፣ እንደዚሁም በልዩ ልዩ ጠቅላይ ግዛቶች በተሰሩት ስታዲየሞችና በውድድሩ ኃይል ድምቀት በማያቋርጠው ኢንተርናሽናል ግንኙነትና በየሳምንቱ ጊዜውን ስፖርት በመመልከት በሚያሳልፈውና ወደስታዲየም በሚጎርፈው ህዝብ ብዛት ፍሬ ያገኘ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

የእኛን ምክርና እርዳታ በመልካም ዘዴ ላይ በማዋል ሃያአምስት ዓመት ሙሉ በመከታተል ፌዴሬሽኑን የጠቅላይ ግዛት መምሪያዎችና ክለቦችን በጉልበት፣ በእውቀት፣ በገንዘብ አገልግሎታቸውን የሰጡትን አባሎች ስናመሰግን፣ ከጥንት ጀምሮ ለዚህ ስፖርት መመስረትና መስፋፋት ምክንያት የሆኑትን፣ ሰውነታቸውንና ጊዜያቸውን ለዚህ ስፖርት አገልግሎት ያዋሉትን ሁሉ በተለይም ይድነቃቸው ተሰማን ልናመሰግን እንወዳለን፡፡"

ጃንሆይ በወቅቱ ቁንጮ ተጫዋች የነበሩትን አዋድ መሐመድ ሔማቸውን የመስቀላቸውን ወሬ ጋዜጠኛ ሰለሞን ተሰማ በዜና ማሰራጫቱን በሰሙ ጊዜ አዋድ መሐመድን፣ መንግስቱ ወርቁንና ሉቺያኖ ባሳሎን ወደ ቤተ-መንግስት ጠርተው ለማነጋገር ተገደዱ፡፡ በወቅቱ ኢትዮጵያ በአዲስ አበባ ስታዲየም ሊቢያን አሸንፋ ስለነበርም በቤተ መንግስቱ ግብዣ ተደርጎ ነበር የተጠሩት፡፡ ጃንሆይ የሁለቱን ተጫዋቾች እድሜ ሲጠይቁ ሠላሳ ዓመት እንደሞላቸው ተናገሩ፡፡ "አንተስ?" አሉት አዋድን "30 ዓመት ሞላኝ" መለሰ አዋድ፡፡ "ታዲያ በ30 ዓመት ማርጀት አለ ወይ? በል ተጫወት! ገብታችሁ ተጫወቱ፣ በርቱ" ብለው አበረታተው ሸኟቸው፡፡/አዲስ ነገር 2001ዓ.ም/ ጃንሆይና ስፖርት ከዚህም በላይ ነበሩ፡፡

ለአትሌቲክሱም ቢሆን ጃንሆይ ትኩረታቸው ተመሳሳይ የነበረ ሲሆን፤ በዘመናቸውም እንደነ አበበ ቢቂላ ባሉ ጀግኖች ኢትዮጵያ የተወደሰችበት ዘመን እንደነበር በደንብ የሚታወቅ ነው፡፡ በተለይ የእግር ኳሱን ጉዳይ ዛሬስ? ብሎ ጠይቆ ለማለፍ በቂ ነው፡፡

*ጃንሆይ እና አፍሪካ*

ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በፊት አፍሪካውያን ለብሔራዊ ነፃነት ያደረጓቸው ትግሎች ሁሉ አልተሳኩም ነበር፡፡ ከጦርነቱ ፍፃሜ በኋላ ግን የፓን አፍሪካን እንቅስቃሴ በመከተል በአውሮፓና በአሜሪካ የተማሩ አፍሪካውያን ወደየአገራቸው በመመለስ የነፃነት ትግሉን በማቀጣጠል መላው አፍሪካን ከቅኝ ገዥዎች ነፃ ማድረግ ችለዋል፡፡

የቅኝ ገዥዎች እስራት፣እፈና፣ግድያና ስቃይ ሳይበግራቸው በዲፕሎማሲ እና በጦር ግንባሮች እየተፋለሙ ህዝባቸውን ብሔራዊ ነፃነት አጎናፅፈዋል፡፡ክዋሜ ኑክሩማ ጋናን፣ ሴኩ ቱሬ ጊኒን፣ጆሞ ኬንያታ ኬንያን፣ኒሬሬ ታንዛንያን፣ኬኔት ካውንዳ ዛምቢያን፣መሐመድ 5ኛ ሞሮኮን፣ሐቢብ ቡርጊባ ቱኒዚያን፣ቤንቤላ አልጀሪያን፣ኔልሰን ማንዴላ (ከአፓርታይድ አገዛዝ) ደቡብ አፍሪካን ነፃ አውጥተዋል፡፡

እነዚህ የነፃነት አባቶች ኅብረታቸውን በማጠንከር የፓን አፍሪካ ፅንሰ ኀሳብን በተግባር በመተርጎም ለአፍሪካውያን ትልቅ ኩራት የሆነውን የአፍሪካ አንድነት ድርጅትን እ.ኤ.አ በ1963 ዓ.ም ለጥቁር ህዝብ የነፃነት ምሳሌ በሆነችው በኢትዮጵያ መዲና በአዲስ አበባ ለማቋቋም ችለዋል፡፡ ለውጤት ከመብቃታቸው በፊት የነበረው ሂደትም ፈታኝና እልህ አስጨራሽ የነበረ ሲሆን፤ የኢትዮጵያና የጃንሆይ እገዛ ለአፍሪካውያን ህልም እውን መሆን ወሳኝ አስተዋፅኦ ነበረው፡፡

ያኔ ፋሽስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በወረረበት ዘመን ጃንሆይ ለመንግስታቱ ማኅበር አቤቱታቸውን ለማቅረብ በ1929 ዓ.ም በሲውዘርላንድ ጄኔቭ በአዳራሹ መድረክ ላይ ቆመው ንግግር ለማድረግ ሲዘጋጁ የነበረው ሁከት አሳዛኝ ነበር፡፡ የተቃውሞ ጩኸት፣ የዘለፋ ቃል፣ የእስክብሪቶ ክዳኖችና የመሳሰሉ ጥቃቅን ነገሮች ወደንግግር ማድረጊያው መድረክ የተወረወረበት ሁኔታ ተስተውሏል፡፡ ኢትዮጵያ አባል የሆነችበት ያ ማኅበር የየአገራቱ ተወካይ የሆኑ ታላላቅ ምሁራንና ባለሥልጣናት የተሰበሰቡበት አዳራሽ አልመሰለም፡፡ ከወሮበሎች ቡድን የማይጠበቅ ክንውን ነበር በአዳራሹ የነበረው፡፡

ጃንሆይ ዙሪያ ገባውን እየተዟዟሩ በዓይኖቻቸው ፀጥታ እንዲከበር ቢማፀኑም ፀጥታ ሊያስከብር የደፈረ ባለስልጣን አልነበረም፡፡በወቅቱ በኢትዮጵያ ምድር የመርዝ ጋዝ በአውሮፕላን እየተረጨ ዜጎች ያለቁበት ሁኔታ ነበር፡፡ጃንሆይና ቤተሰቦቻቸው ሰደት ላይ ናቸው፡፡ፍፁመ ብቸኝነት ተሰምቷቸዋል፡፡ተስፋ የጣሉበት ማኅበርና ዓለም አቀፍ ሕግ በዚያ ሁኔታ ይጠብቀኛል ብለው አላሰቡም፡፡ በጃንሆይ ዘመን የተቀረፁ ምስሎች እና ፎቶግራፎችን ሁሉ ያየ ሰው የዚያችን እለት የጃንሆይን የፊት ገፅታ በማየት ብቻ በዘመናቸው ክፉኛ የተናደዱበት እለት መሆኗን በቀላሉ ይረዳል፡፡እንባ እየተናነቃቸው፣ የንዴት ላባቸው ፊታቸው ላይ ቸፍ ብሎ



ይታያል፡፡ነገር ግን የመጡበት ነውና ካባቸውን ገለጥ አድርገው ከኪሳቸው አቤቱታ የያዘውን ወረቀታቸውን አውጥተው በሲቃ ድምፅ በጩኸቱ መካከል አነበቡት፡፡ያ ታሪካዊና "ነብይ" ያሰባላቸው ንግግራቸው ለሁከት በተሰበሰቡት ባለሥልጣናት ልብ ውስጥ እየጠለቀ ሲሄድ፤ ብዙዎች መበጥበጣቸውን ትተው በጥሞና ማዳመጥ ጀመሩ፡፡ቢሆንም ኃያላኑ ለኢጣሊያ እውቅና ከመስጠት አልታገዱም፡፡

ያ አስጨናቂ ወቅት ካለፈ በኋላ ጃንሆይ ዓለም አቀፍ ሕግ ለጥቁሮች እንደማይሰራ በውል ተረድተዋል፡፡ ይህ ከሆነ ከአሩብ ምዕት ዓመት በኋላ ጃንሆይና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ክቡር አቶ ከተማ ይፍሩ "የጄኔቡ አይነት የመንፈስ ስብራት ዳግም ቢደርስብን ከጎናችን የሚቆመው ማነው?" በሚል መነሻ አጭር ውይይት አድርገው የደረሱበት ድምዳሜ "ኢትዮጵያ መወዳጀትም ሆነ መደጋገፍ ያለባት ከመሰሎቿ ከአፍሪካውያን ጋር እንጂ ከሌላ ከማንም ጋር ሊሆን አይችልም" የሚል ነው፡፡ በመሆኑም ከ1950 ዓ.ም ጀምሮ ኢትዮጵያ አፍሪካውያንን በመደገፍ፣ በማስተባበርና በልዩ ልዩ መንገዶች መርዳት ዋና ስራዋ አድርጋ ያዘችው፡፡

በዓለም አቀፍ የጥናት ውጤት ይፋ እንደተደረገው ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በፊትና በኋላ በነበሩት ጊዜያቶች ከዓለም ህዝብ ውስጥ 66 በመቶ የሚሆነው ቅኝ ተገዥ ህዝብ የነበረ ሲሆን፤ ከአጠቃላዩ የዚህች ምድር ስፋት ውስጥ 63 በመቶው የብስና ባህር በተለይ በእስያና በአፍሪካ አህጉር የሚገኘው በቅኝ ገዥዎች የበላይነት የተያዘ ነበር፡፡አፍሪካ ውስጥ ደግሞ ከኢትዮጵያ በስተቀር ሁሉም አገር በአውሮፓውያኑ ቅኝ ገዥዎች ስር የተያዘ ነው፡፡ብዙ ጊዜ "ኢትዮጵያና ላይቤሪያ" ተብሎ ይገለፃል፡፡ነገር ግን ላይቤሪያ በካርታ አቀማመጧ ማዕከላዊነት ሳቢያ ቅኝ ገዥዎች በአፍሪካ ላይ በሚሰሩት ስራና ሴራ የሚገለገሉባቸውን እቃዎች የሚያወርዱ የሚያወጡባት፣የሚያሰራጩ የሚያራግፉባት፣አንዳንዴም ጥቁሮችን የሚያጉሩባት መጋዘን አድርገው ስለተጠቀሙባት ነው፡፡ከዚህ አንፃር ብቸኛ ነፃ አፍሪካዊት አገር ኢትዮጵያ በመሆኗ አፍሪካን ባላት አቅም ለመርዳት የምትችል ሲሆን፤የአፍሪካ ህዝቦችና የነፃነት ታጋዮችም የኢትዮጵያ እርዳታ በእጅጉ ያስፈልጋቸው ነበር፡፡

የጀርመን ፋሽዝም በአውሮፓ፣የጃፓን ሚሊታሪዝም በእስያ ድል ከሆኑበት ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ፍፃሜ በኋላ የተፈጠረው ሁኔታ የቅኝ ተገዥ አገራት ህዝቦችን የነፃነት ጥያቄና ትግል ተጠናክሮ እንዲቀጥል አድርጓል፡፡

ድል ባደረጉት በተባበሩት አገራት ጦር ሠራዊት ውስጥም የአፍሪካውያን ወታደሮች ተሳታፊ ሆነው ለድሉ ሰፊ አስተዋፅኦ አበርክተዋል፡፡በዚያ

ጦርነት አንድ ሚሊዮን አፍሪካውያን ወታደሮች በተባበሩት ጦር ኃይሎች ውስጥ ተሰልፈው ተዋግተዋል፡፡

ለምሳሌ ፓሪስ ነፃ ከመውጣቷ በፊት የጀርመንን ፋሽዝም ለመደምሰስ በተካሄደው ውጊያ ከፈረንሣይ ጎን የተሰለፉት አፍሪካውያን ወታደሮች በቁጥር ከፈረንሣውያን ወታደሮች ይበልጡ ነበር፡፡ አልጀሪያውያን ወታደሮች ብቻ ሦስት መቶ ሺ ይደርሱ ነበር፡፡ በተመሳሳይም የእስያ ህዝቦች የጃፓንን ሚሊታሪዝም በመደምሰስ በኩል ከፍተኛ ተሳትፎ አድርገዋል፡፡

የፋሽስት ኢጣሊያን ጦር ከአፍሪካ ለመደምሰስም አፍሪካውያን ወታደሮች ትልቁን ሚና ተወጥተዋል፡፡ 50 ሚሊዮን ህዝብ ያለቀበት ሁለተኛው የዓለም ጦርነት የተጀመረው ኢትዮጵያ ላይ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ምንም እንኳ "የዓለም ጦርነት" የሚለው ስያሜና አገላለፅ በይፋ የታወቀው ጀርመን ፖላንድን በወረረች ጊዜ ይሁን እንጂ፤ ጀማሪዋ ጣሊያን፣ ተጀማሪዋ ኢትዮጵያ ነበረች፡፡

ጦርነቱ ተጀምሮ እስኪጨረስም ኢትዮጵያ አርበኞቿን ጨምሮ አንድ ሚሊዮን ዜጎቿን አጥታለች፡፡ የኢጣሊያን ጦር ከአፍሪካ ለማስወጣት በተካሄደው ውጊያ የኢትዮጵያ ወታደሮች አገራቸውን ነፃ ከማውጣት አልፈው ከእንግሊዝ ጦር ጋር ወደ ሊቢያ ዘምተዋል፡፡

በሂደቱ አፍሪካውያን በጥይትና በቦምብ ካለቁት ውጪ በርካታ ምሁራን በየእስር ቤቱ ታጉረው እድሜያቸውን አባክነዋል፡፡ የአፍሪካ ህዝቦች በቅኝ ገዥ አገራቱ እየተመለመሉ በጦርነቱ ገዥ አገራቸውን ለመርዳት ሲሰለፉም የተገባላቸውን ቃል መሠረት አድርገው ነው፡፡

በተለይ እንግሊዝና ፈረንሣይ ለረጅም ዓመታት የገዟቸውን የአፍሪካ ዜጎች በዚያ አጣብቂኝ ላይ በነበሩበት ጊዜ የአፍሪካውያኑ ትብብር ያስፈለጋቸው ነበርና "ለነፃነታችሁ መዋጋት አለባችሁ" ከማለት አልፈው "ከድል በኋላ ነፃነታችሁን መልሰን እንሰጣችኋለን" በሚል ቃል ገቡላቸው፡፡

ለጥቁር ህዝቦች ማንም ያሸንፍ ማን እዚህ ግባ የሚሉት ለውጥ አይኖርም፡፡ "ከማያውቁት መላዕክ የሚያውቁት ሠይጣን"ን ካልተረቱት በቀር ከሁለት አውሮፓዊ ገዥ አንዱን የመምረጥ ያህል ነበር፡፡ኢምፔሪያሊዝምም ፋሺዝምም ተገዥ ለሆነ አገር ልዩነቱ ያዘለና ያቀፈ መሆኑን ስለተረዱም ነው "ነፃነታችሁን እንመልሳለን" ወደማለት ያመሩት፡፡በዚህ መሠረት አፍሪካውያን በጦርነቱ ሊሳተፉ ችለዋል፡፡ ቅኝ ገዥ አገራቱ ከድል በኋላ ቃላቸውን ሙሉ በሙሉ ለመጠበቅ ባይችሉም፤ ለአፍሪካውያኑ ግን ከጦርነቱ ፍፃሜ በኋላ የገዥዎቻቸውን ቀንበር ከላያቸው ላይ ለማውረድ የራሳቸውን ትግል ብቻ እንጂ በገዥዎች ችሮታ እንደማይገኝ አስገንዝቧቸዋል፡፡



ከዚህም በላይ የጦርነቱ ፍፃሜ በራሱ ለብሔራዊ ነፃ አውጪና ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄዎች መስፋፋት ከፍተኛ ግፊት ፈጥሯል፡፡ የነበሩት የነፃነት ትግሎች ተጠናክረው፤ ያልነበሩት በአዲስ መልክ ብቅ ብቅ እያሉ የቀጠሉት ከድል በኋላ ምንም ያተረፉት ነገር ባለመኖሩ ነው፡፡

ለፋሽዝም መሸነፍ ትልቅ አስተዋፅኦ ያበረከቱት፣ በጦርነቱም ቀዳሚ ተዋጊ እየተደረጉ ከፍተኛ መስዋዕትነት የከፈሉትና መራራ ስቃይ የተቀበሉት አፍሪካውያን የተገባላቸው ቃል በመታጠፉም ብቻ ሳይሆን፤ በጦርነቱ ወቅት የተለያዩ አገራት ዜግነት ካላቸው ወታደሮች ጋር ተሰባጥረው ስለተዋጉ አመለካከትና ግንዛቤያቸው ዳብሮ ነበርና ግዳጃቸውን ተወጥተው ወደሰላማዊ ኑሮዋቸው እንዲመለሱ በተደረገ ጊዜ በቅኝ አገዛዝና በፖለቲካዊ፣ በኢኮኖሚያዊ፣ በአይዲዮሎጂያዊ መሠረቶች ላይ በመነሳት ቀደም ብለው በተጀመሩት በነፃነት ትግሎች ላይ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ ጀመሩ፡፡

አፍሪካውያን ሚሊቴሪዎች በአገራቸው ውስጥ ሆነው ለነፃነታቸው መታገላቸውን በቀጠሉበት ሁኔታም፤ በውጭ አገር ትምህርታቸውን የተከታተሉ የየአገራቱ ምሁራንና ፖለቲከኛ የሆኑ ሲቪል ዜጎችም በዲፕሎማሲና በተለያዩ የትግል ስልቶች የነፃነቱን ንቅናቄ የሚያጎለብት ስራ ይሰሩ ነበር፡፡

በመሆኑም ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ፍፃሜ በኋላ አፍሪካውያን የፓንአፍሪካኒዝም ንቅናቄያቸውን አጧጧፉት፡፡ በአህጉሪቱ ውስጥም ብዙ የፖለቲካ ፓርቲዎችና ድርጅቶች ፈለቁ፡፡ የፓን አፍሪካ ጉባኤዎችም በየጊዜው መካሄድ ጀመሩ፡፡ ኢትዮጵያም ምንም ነፃ አገር ብትሆን የፓን አፍሪካኒዝም ንቅናቄ ደጋፊ መሆኗን ገለፀች፡፡ ጃንሆይ "በማናቸውም ረገድ ቢሆን አፍሪካውያን ወንድሞቻችንን ለነፃነት የሚያደርጉትን ትግል ደግፈን የሚቻለንን ሁሉ እንረዳለን" አሉ፡፡

አፍሪካውያኑ በውስጣቸው ያለውን ምሬት ይፋ ያወጡትና ጠንካራ ውሣኔ የወሰኑት ጦርነቱ በአውሮፓ ሙሉ በሙሉ ሊጠናቀቅ የጥቂት ወራት እድሜ በቀረበት በጥቅምት ወር እ.ኤ.አ 1945 ላይ በእንግሊዝ ማንችስተር ከተማ ውስጥ በተደረገው በ5ኛው የፓን አፍሪካ ጉባዔ ላይ ነው፡፡ በዚያ ጉባዔ በአህጉሪቱ የፈለቁ የፖለቲካ ፓርቲዎችና ድርጅቶች አባላት የተካፈሉ ሲሆን፤ ከእነርሱ ውስጥ የጋናው ክዋሜ ኑክሩማ እና የኬንያው ጆሞ ኬንያታ ይገኙበታል፡፡ እነርሱና መሰል እውቅ የብሔራዊ ነፃ አውጪ ንቅናቄ መሪዎች በጉባኤያቸው ለአፍሪካ ህዝቦች ያቀረቡት ማሳሰቢያና የወሰዱት አቋም እንዲህ የሚል ነበር፡፡

"ሁሉም ህዝቦች ራሳቸውን ለመምራት መብት እንዳላቸው እናምናለን፡፡ ሁሉም ቅኝ ግዛቶች ከባእዳን የፖለቲካና የኢኮኖሚ ቁጥጥር ነፃ መሆን አለባቸው፡፡ የቅኝ ግዛት ህዝቦችም ባእዳን ኃይላት ከሚጥሉት

ማንኛውም ገደብ ነፃ ሆነው የየራሳቸውን መንግስታት የመምረጥ መብት ሊኖራቸው ይገባል" ሲሉ አስገነዘቡ።

ይህን የውሣኔ አቋም ኢምፔሪያሊስቶች ለማፈን ጥረት አደረጉ። አፍሪካውያኑ ግን የነፃ አውጪ ንቅናቄ መሪዎችን መልዕክት ተቀብለው በተግባር ወደመተርጎም አመሩ።

ጦርነቱ በአውሮፓ ባበቃበት ግንቦት 8 ቀን 1945 እ.ኤ.አ የፈረንሣይ ቅኝ ገዥዎች በግዛታቸው በአልጀሪያ ውስጥ የተነሳውን የነፃነት አመፅ ለማዳፈን ከፍተኛ ወረራ አካሂደው 45 ሺ አልጀሪያውያንን ገደሉ። በ1947 ማዳጋስካር ውስጥ ለነፃነቱ ለመዋጋት በተነሳውና ምንም ባልታጠቀው የማላጋሲ ህዝብ ላይ የፈረንሣይ ወታደሮች በዘመናዊ መሣሪያ ታግዘው በከፈቱት ተኩስ 100 ሺ የደሴቲቱን ተወላጆች ፈጁቸው።

የነፃ አውጪ ንቅናቄ መሪዎች የትግል ስልት አይነቱ ይለያይ እንጂ በአህጉሪቱ በሚካሄዱ ትግሎች ምክንያት ተመሳሳይ የኢምፔሪያሊስቱ የጭካኔ እርምጃ ለዓመታት በየአገሩ ሲፈፀም ቆይቷል። በሰሜን አፍሪካ የሚገኙ አገራት ውስጥ ኮሚኒስት ፓርቲዎች እንደመበርከታቸው መጠንም በኃያሏ ሶቭየት እርዳታ ምክንያት የትግላቸው ጊዜ አጭር እንዲሆን አግዟቸዋል።

ነፃነቷን በመቀዳጀት ረገድ የመጀመሪያዋ የአፍሪካ አገር ሊቢያ ናት። ከቀድሞ ገዥዋ ከኢጣሊያ ነፃ ከሆነች በኋላ በእንግሊዝና በፈረንሣይ ወታደሮች ተይዛ የቆየችው ሊቢያ፤ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ውሣኔ መሠረት መንግስታዊ ሉዓላዊነት ያገኘችው ታህሳስ 24 ቀን 1951 እ.ኤ.አ ነው። ሆኖም ባዕዳኑ አገሪቱን ሙሉ ለሙሉ ለቀው የወጡት እ.ኤ.አ በ1970 ነበር።ጋዳፊ ስልጣን እንደያዙ ጠራርገው አባረሯቸው።

በሐምሌ ወር 1952 እ.ኤ.አ ግብፅ በጋማል አብድል ናስር መሪነት ፀረ-ኢምፔሪያሊስት አብዮት ተከናውና የአብዮታዊ መምሪያ ምክር ቤት ከተቋቋመ በኋላ የአርበኞች ድርጅት አባሎችን የያዘ ቡድን ስልጣኑን ይዞ በጋማል አብድል ናስር ሲመራ ቆይቶ፤በግብፅ አብዮታዊ መንግስት ጥያቄ መሠረት ከረጅም ጊዜ ግብግብ በኋላ እንግሊዝ ወታደሮቿን ሙሉ በሙሉ በሰኔ ወር 1956 እ.ኤ.አ ከአገሪቱ አስወጣች።በአገሪቱ የኢምፔሪያሊስት መንግስትን መልሶ ለማቋቋም የሚፈልጉ ኃይሎች ቢኖሩም ሶሻሊስቱ ቦታውን ሳይለቅ ቆዩ።እንግሊዝና ፈረንሣይ የስዊዝ ካናል ኩባንያን ለግብፅ ማስረከብ እንዳለባቸው የተጠየቁትን ጥያቄ መሠረት አድርገው እስራኤልንም ከጎናቸው አሰልፈው በግብፅ ላይ ጦርነት ቢከፍቱም የግብፅ ህዝብ በጀግንነት ተዋግቶ መከተ።ለዚህም የሶሻሊስት አገሮች በተለይ ሶቭየትና ቼኮዝላቫኪያ ለግብፅ የሰጡት የመሣሪያ እርዳታ ለድሉ ከፍተኛ



አስተዋፅኦ ነበረው።ሦስቱ አገሮች ግብፅን መልሰው ለማጥቃት ሲዘጋጁም ሶቭየት በሦስቱ አገሮች ላይ ጦርነት እንደምትከፍት ስላስጠነቀቀች ወራሪዎቹ ተኩስ አቁመው ከግብፅ ወጡ።የግብፅ ድል ለሰሜን አፍሪካና ለዓረቡ ዓለም የነፃነት እንቅስቃሴ ወኔን የሚቀሰቅስ ሆኖ ሲገኝ፤ናስርም የዓለም ነፃ አውጪ ንቅናቄ እውቅ መሪ ተሰኘበት።በመሆኑም ጥር 1 ቀን 1956 እ.ኤ.አ በእንግሊዝ ስር የነበረችው ሱዳን ነፃ ሪፐብሊክ ሆነች።ፈረንሣይ በበኩሏ መጋቢት 2 ቀን 1956 የሞሮኮን፣መጋቢት 20 ቀን የቱኒዚያን ነፃነት እውቅና ለመስጠት ተገደደች። የግብፅ ተፅዕኖ ለተጠቀሱት የአፍሪካ ዓረብ አገራት ነፃነት የራሱ የሆነ አስተዋፅኦ ነበረው።እ.ኤ.አ መጋቢት 6 ቀን 1957 ጋና ነፃነቷን መጎናፀፏ ታወጀ።እ.ኤ.አ በ1958 ጊኒ ነፃ ወጣች።በዚያ ጊዜ (በእኛ አቆጣጠር 1950 ዓ.ም) "ነፃ የአፍሪካ መንግስት ጉባዔ" ተመሠረተና በጋና አክራ ከተማ የመጀመሪያው ውይይት ተካሄደ። እለቱንም "የአፍሪካ ቀን" በማለት በአህጉር ደረጃ ሰየሙት።የነፃ መንግስታቱ ድርጅት ጉባዔ በፖለቲካና በኢኮኖሚ ጉዳዮች እየተወያዩ ሌሎች አገራት በአጭር ጊዜ ውስጥ ለነፃነት የሚበቁበትን መንገድ ማመቻቸትና መርዳት እንዲሁም ግፊት ማድረግ ነበረበት።ለዚህም ምቹ ሁኔታ መፍጠር የምትችለው ኢትዮጵያ ነበረችና ተከታታይ ጉባኤዎች በኢትዮጵያ መካሄድ ጀመሩ። የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽንም በኢትዮጵያ ተመሠረተ።ነፃ የአፍሪካ አገሮች ኅብረት ፈጥረው ያደረጉት ግፊትም ፍሬ መስጠቱን ቀጠለ።



ጃንሆይ ከአፍሪካውያን መሪዎች ጋር

በኛ አቆጣጠር ሚያዚያ 7 ቀን 1952 ዓ.ም ጃንሆይ የአፍሪካን ጉዳይ በሚመለከት በሬዲዮ የተናገሩት ንግግር በአጭሩ እንዲህ ይነበባል፡

“የአፍሪካ ቀን ክብረ በዓል የተመሠረተበት ሁለተኛው ዓመት በሚውልበት በዛሬው እለት ከልብ የሆነውን የራሳችንን ሠላምታና የምንወደው ህዝባችን ለአፍሪካውያን ወንድሞቹ የሚልከውን የወንድማማችነት በጎ ምኞት ለመላው አፍሪካ ህዝቦች እንገልፃለን፡፡

ስለዚህ ታላቅ ስለሆነው ክፍለ ዓለም ህዝቦች ነፃነትና የወደፊት እርምጃ በሚያደርገው ትግል ባለፈው ዓመት ውስጥ የአፍሪካ አገሮች ያሳዩት መተባበር ደስ የሚያሰኝና የሚያበረታታ ነው፡፡

ካሜሮን ነፃ እንደወጣች እንዲሁም ኮንጎ፣ ናይጀሪያ፣ ሶማሊያና ቶጎ ላንድ በዚህ ዓመት ውስጥ ነፃነታቸውን የሚያገኙ በመሆናቸው አፍሪካውያን ወንድሞቻቸው በሙሉ ይደሰቱበታል፡፡ የእነዚህ አገሮች ነፃ መውጣት የአገሬውን ህዝብ በተለይ የሚያስደስተው ብቻ ሳይሆን ይህንኑ መልካም ውጤት ለማስገኘት ሳይሰለቹ ለደከሙት እህትማማች አገሮች ህዝብ ጭምር ብርታትን የሚሰጣቸው ነው፡፡ በዚህም አኳኋን ከአስር ዓመት በማያንስ ጊዜ ውስጥ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት አባል የሆኑት የአፍሪካ አገሮች ቁጥር በዝቶ ከሦስት እስከ አራት መድረሱ ስለአፍሪካ ነፃነት የሚደረገውን እንቅስቃሴ በበለጠ የሚያጠነክረው ስለሆነ ሌሎችም በአፍሪካ ውስጥ የሚገኙ ግዛቶች በአጭር ጊዜ ውስጥ ነፃነታቸውን እየተጎናፀፉ ከአፍሪካውያን ወንድሞቻቸው ጎን ተገቢ የክብር ስፍራቸውን እንደሚይዙ አያጠራጥርም፡፡

አሁንም እንኳ ቢሆን በማናቸውም አገር የሚገኙ ህዝቦች ሁሉ በዘር ምክንያት ልዩነት እንዳይደረግባቸውና የእድል እኩልነት እንዳይነፈጋቸው ለማድረግ በተባበሩት መንግስታት ሸንጎ በሚደረገው ትልቅ የአፍሪካ መንግስታት ኅሳብና ዓላማ አንድ መሆንና በሰፊው መተባበራቸው ከብዛታቸው ጋር ሆኖ በተባበሩት መንግስታት ሸንጎ የሚናገሩዋቸውን ቃላት በተለይ ተደማጭ አድርጎታል፡፡
ይህ ኅብረትና መረዳዳት በመጠኑ ከታሪካቸው ቅርስ የተገኘ እንዲሁም የጋራ ተጋድሏቸውን ባለመዘንጋት ላይ የተመሠረተ ሆኖ ሲገኝ፤ስለኢኮኖሚና ስለፖለቲካ ጉዳዮች መመካከሪያ እንዲሆን የተቋቋመው ድርጅት መሠረታዊ ስለሆኑት የኅሳብ አንድነት ተባብሮ በጥንካሬ ስለመስራት መርዳት ደስ የሚያሰኘን ነው፡፡

በዚህ ዓመት ከአራት ወራት በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ የአፍሪካ አገሮች በቱኒዝ፣ በአክራና በኮናክሪ ሦስት ጊዜ ስብሰባ ያደረጉ ሲሆን፤ በሚመጡት ወራት ውስጥ ደግሞ በመናገሻ ከተማችን ሁለት ጊዜ እንዲሰበሰቡ መታቀዱን እኛን አፍሪካውያንን የሚያኮራን ነው፡፡

.... በዚህ በዛሬው የአፍሪካ ቀን ለወንድሞቻችን ነፃነት፣ ደህንነትና መሻሻል እንቅፋት የሆኑትን ነገሮች ሁሉ ለማስወገድ ያለንን ከፍተኛ



ዓላማ በበለጠ እንድናከናውን ኅሳባችንንና ቆራጥነታችንን እንደገና እናድስ፡፡” *(ፍሬ ከናፍር 1952 ዓ.ም)*

በዚሁ የአፍሪካ ቀን በተከበረበት እለት እ.ኤ.አ 1960 ዓ.ም 17 የአፍሪካ አገሮች ነፃነታቸውን ተቀዳጁ፡፡ በተጠቀሰው ዓመት የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባዔ ለቅኝ ግዛት አገሮችና ህዝቦች ነፃነት ስለመስጠት ጉዳይ የቀረበውን ውሣኔ አፀደቀ፡፡

የካፒታሊስት አገራት ተወካዮች ረቂቁን ውድቅ ለማድረግ አልሞከሩም፡፡ ነገር ግን ቅኝ አገዛዙ በተሻሻለ ሁኔታ የሚቀጥልበትን መንገድ ለማመቻቸት ጥረው ነበር፡፡ ሆኖም የገለልተኛ አገራትና የሶሻሊስት አገራት በተለይ የሶቭየት ኅብረት ተወካዮች ካፒታሊስቶችን ተቃውመው ጥረታቸውን አከሸፉት፡፡

43 የእስያና የአፍሪካ አገሮች ያረቀቁትን መግለጫ ጠቅላላ ጉባኤው በከፍተኛ የድምፅ ብልጫ ሲያፀድቀውም “ቅኝ አገዛዝ ከተባበሩት መንግስታት ድርጅት መርሆዎች ጋር የማይጣጣም” መሆኑን በመግለፅና፤ ህዝቦች የራሳቸውን እድል በራሳቸው የመወሰንና በነፃነት የመኖር መብት እንዳላቸው በማረጋገጥ ነው፡፡ ከውሣኔው መፅደቅ በኋላ ለብሔራዊ ነፃነት የሚካሄደው ትግልና የሚከተለው እልቂት ሙሉ ለሙሉም ባይሆን በመጠኑ ጋብ አለ፡፡

ለ7 ዓመታት ያህል ደም ያፋሰሰው የአልጀሪያና የፈረንሣይ ጦርነትም ተገታ፡፡ ሐምሌ 1 ቀን 1962 እ.ኤ.አ አልጀሪያ ነፃ አገር ሆነች፡፡ ከዚህ በኋላ ባሉት ተከታታይ ዓመታት የቅኝ ግዛት ስርዓት በመላው ዓለም እየፈራረሰ ሄደ፡፡

አፍሪካውያን ቀስ በቀስ ነፃነታቸውን እየተጎናፀፉ ለመሄድ ካስቻሏቸው መንገዶች ውስጥ አንዱ ኅብረታቸው እንዳለ ሆኖ፤ በኢኮኖሚ በኩል ሊረዳዱ የሚችሉበት “የአፍሪካ ኢኮኖሚ ኮሚሽን” በተባበሩት መንግስታት አማካኝነት ማቋቋም በመቻሉ ነው፡፡

በእኛ አቆጣጠር 1951 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ የአፍሪካ ኢኮኖሚ ኮሚሽን የመጀመሪያ ጉባዔ ተመርቆ ከተከፈተ ከአንድ ዓመት በኋላ ጃንሆይ በሁለተኛው የአፍሪካ ነፃ መንግስታት ኮንፈረንስን ሲከፍቱ ባደረጉት ንግግር ውስጥ ያካተቱት ገለፃም ይህንኑ የሚያረጋግጥ ነው፡፡

“... የአፍሪካ ኢኮኖሚ ኮሚሲዮን የመጀመሪያው ጉባዔ በተደረገበት ጊዜ የአፍሪካ ህዝብ ያደረገውን የተፋጠነ የፖለቲካ እድገት በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ከተፈፀሙት እጅግ አስገራሚና አስደናቂ ሆነው ከሚታዩት የስልጣኔ እርምጃዎች አንዱ መሆኑን ገልጠናል፡፡ ከዚያም ወዲህ በተከተሉት ወራት ውስጥ የቀጠለው ትግል በአጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ አዳዲስ መንግስታት በማስገኘቱና የቅኝ ግዛት ሰዎች ወደነፃነት

ግባቸው የሚያደርጉትን እርምጃ በማፋጠኑ መጠን ከታሰበው በላይ የሆነ መልካም ውጤት አስገኝቷል፡፡

በዚህ ከእግዚአብሔር በተመረጠው እድል ጊዜና ቀን መመስረትና መስራት የሚገባን መሆኑን አውቀን እድል ህልም ሆኖ እንዳይቀር የአንድነትን መሠረት መጣል ስራችን እናድርግ፡፡

ኮንጎ፣ ካሜሩን፣ ቶጎላንድ፣ ናይጄሪያና ሶማሊያ ዛሬ ከመካከላችን ተገኝተው በዚህ ጉባዔ ስራ ሙሉ ተካፋይ ለመሆን በመቻላቸው ሁላችንም ደስ ይለናል፡፡ ከአሁን በፊት እንደተናገርነው የአፍሪካ ህዝቦች የፖለቲካ እድገት ወደመጨረሻው ግቡ ሳይደርስ የማያቋርጥ መሆኑን በጥብቅ እናምንበታለን፡፡ከዚሁም ግብ የሚደርሰው መላው የአፍሪካ ህዝብ ነፃነቱንና ሠብዓዊ መብቱን በሙሉ ሲያገኝ ነው...፡፡"

በዚያ ወቅት ኢትዮጵያ ለአፍሪካውያን ነፃነትና የወደፊት ዕጣ ሲባል ያደረገችው ድጋፍ ዘርፈ ብዙና ሁሉን አቀፍ መሆኑን ለመገንዘብ የሚያስችለን ጃንሆይ በእኛ አቆጣጠር ሰኔ 7 ቀን 1952 ዓ.ም ሁለተኛውን የአፍሪካ ነፃ መንግስታት ኮንፈረንስ በከፈቱ ጊዜ ከተናገሩት ውስጥ ተካቶ እናገኛለን፡፡

"... በደቡብ አፍሪካ የሚደረገውን የዘር ልዩነትና ግፍ ተባብረን ለህዝቡ ጠበቃ ለመሆን በስራ መግለጥ አለብን፡፡ አባቶቻቸው በግፍ ለሞቱባቸው የደቡብ አፍሪካ ወጣቶች እስኮላርሽፕና የገንዘብ እርዳታ የሰጠነው በዚሁ በመቆርቆር ነው፡፡" ብለዋል፡፡

በእለቱ ከወቅቱ ኢትዮጵያዊ ምሁራን ውስጥ አንዱ የነበሩት ክቡር አቶ ይልማ ደሬሳ (የታዋቂው የኢኮኖሚ ሊቅ የብላታ ደሬሳ አመንቴ ልጅ) በስብሰባው ከተናገሩት ንግግር ውስጥ ጥቂት ሐተታዎችን ስናይም የኢትዮጵያ ሚና እምን ድረስ እንደሆነ በአጭሩ እንገነዘባለን፡፡

"ክቡራን መልዕክተኞች፤

ወይዛዝርትና መኳንንት፡፡

ይህ የአፍሪካ ነፃ መንግስታት ሁለተኛ ጉባዔ ሊቀመንበር እንድሆን በመመረጤ ከፍ ያለ ክብር ይሰማኛል፡፡

ይህ ምርጫ የእኔ መሆኑ ስለአገሬ ክብርና በተለይም ታላቁ መሪ ገናናው ገኘርዩና ንጉሠነገሰቴ ስለአፍሪካ ህዝብ ነፃነት ህዝባዊ መብትና በመሻሻል ወደፊት መራመድ በዚህ ክፍለ ዘመን ያደረጉትን ተጋድሎ ከማወቅ የተነሳ እንደተደረገ እቆጥረዋለሁ፡፡ ...

.... የአፍሪካ ህዝብ እንደራሴዎች አከታትለው ባደረጓቸው ስብሰባዎች የአክራ ጉባዔ የመጀመሪያ እንደነበረ በደስታ የምናስታውሰው ነው፡፡ ይኸውም ጉባዔ ከተደረገ በኋላ ከአንድ ዓመት በሚያንስ ጊዜ ውስጥ የአፍሪካ ኤኮኖሚ ኮሚሲዮን የመጀመሪያው ጉባዔ የድርጅቱ ዋና መስሪያ ቤት በተቋቋመበት ከተማ እዚሁ አዲስ አበባ ላይ ተደረገ፡፡ ከጥቂት



ወራት በኋላ ደግሞ አሁን ስራው ለማለቅ በተቃረበው በአዲሱ የአፍሪካ አዳራሽ የዚሁ ድርጅት ሦስተኛ ጉባኤ እንዲሰበሰብ ተወስኗል፡፡

ስለዚህ ለኢኮኖሚ ጉዳዮች መመካከሪያ የሚሆን ድርጅት እንዲቋቋም የአክራ ጉባኤ ያሳሰበውም አሟልቶ ከስራ በማዋል ረገድ በጣም የተጋፋበት መሆኑን በአጭር ጊዜ ውስጥ ልናውቀው ችለናል፡፡

እንደዚሁም ሁለት መቶ አፍሪካውያን ተማሪዎች በኢትዮጵያ ከፍተኛ ት/ቤቶች ትምህርታቸውን እንደሚከታተሉ ገናናው ገኸርዩ ያቋቋሙት እስኮላር ሽፕ፣ ስለካልቸር ጉዳዮች የተደረገው ውሣኔ በሥራ ላይ ማዋሉን በጉልህ የሚያስረዳ ነው ..." ጉባኤው የሚመክርባቸውን ጉዳዮች በአጭሩ አጠቃለው ሲገልፁም፤

"…. ዛሬም ቢሆን ዋናው ችግራችን በአጀንዳችን ተራ ቁጥር 11 የተመለከተውና የቅኝ ግዛትን ከአፍሪካ ጨርሶ ስለማስወገድ፤

ሀ. ነፃ ያልሆኑት አፍሪካውያን አገሮች ነፃነታቸውን እንዲያገኙ ስለሚወሰደው እርምጃ፤

ለ. አዳዲሱ አይነት ኮሎኒያሊዝም ወደ አፍሪካ እንዳይገባ ስለመከላከል" በሚለው እርእስት ተጠቃሎ የሚገኘው ጉዳይ ነው፡፡ ..."

የላይቤሪያ የልዑካን መሪ ሆነው የመጡት ክቡር ሚስተር ሩዶልፍ በእለቱ ከመግቢያ ንግግራቸው አስከትለው የተናገሩት ንግግርም ጃንሆይ ለአፍሪካ ነፃነትና ሠላም ሲሉ በሰሯቸው ስራዎች በአፍሪካውያን መሪዎች ዘንድ ልዩ አክብሮት እንዳሰጣቸው ከማስረዳት ባለፈ፣ የኢትዮጵያን የአፍሪካ ተምሳሌትነት የሚያረጋግጥ ነው፡፡

"... ግርማዊ ሆይ፤

የውቢቷ አገርዎ ታሪክ የመላው አፍሪካ ህዝብ መመኪያ ሆኖ ይታያል፡፡ ግርማዊነትዎም በአፍሪካ ብቻ ሳይሆን በመላው ዓለምም ጭምር ጥንካሬ ክብሩህነት ጋር የተመላበት መሪ ምልክት ሆነው ይታያሉ፡፡ ግርማዊነትዎ በታላቅ መከራና ችግር ዘመን ለነፃነቱ እየታገለ ለመዋጋት ለቆረጠው ህዝብ ምልክት ነው፡፡

ግርማዊነትዎ ፋሽዝም ለዘለዓለም አይኖርም፤ ይደመሰሳል ብሎ ያምን ለነበረው በሚሊዮን ለተቆጠረው ህዝብ ምሳሌ ነው፡፡ ኢትዮጵያ የብዙ ሺ ዘመናት የነፃነት ጣዕም የቀመሰች አገር በመሆኗ ነፃነትን ለሚፈልጉ በሚሊዮን ለሚቆጠሩ ህዝቦች መፅናኛና መነቃቃቂያ፣ መበረታቻም ሆና ትታያለች፡፡

ግርማዊነትዎ የእኩልነት መብት በሰው ልጅ እንዲኖር በሚጥሩ መካከል ታላቅ ምሳሌ ሆነዋል፡፡..." ካሉ በኋላ "ብሁለኛው የነፃ አፍሪካ አገሮች ጉባዔ ስም ሆኜ ዳግም ምስጋናዬን በማቅረብ ለግርማዊነትዎና ለቤተሰቦችዎ ጤናና ረጅም እድሜ፣ ለኢትዮጵያና ለህዝቧም ብልፅግና እመኛለሁ" በማለት ነበር ንግግራቸውን የደመደሙት፡፡

አፍሪካን በሚመለከት ጃንሆይ የነበራቸውን አቋምና ታሪካዊ ንግግራቸውን እውቁ የሬጌ ሙዚቃ አቀንቃኝ ቦብ ማርሌ ሳይቀር "War" በሚለው ዜማ አካቶት እናገኛለን፡፡

"... በደቡብ አፍሪካ፣ በአንጎላ፣ በሞዛምቢክ የሚገኙት ወንድሞቻችን ካሉበት የባርነት ቀንበር ነፃ እስኪወጡ ድረስ መላው አፍሪካውያንና እስያውያን በዓለም ሸንጎ በእኩልነት ደረጃ ድምፃቸው እስኪደመጥ ድረስ የአፍሪካና የእስያ ክፍለ ዓለም ሙሉ ሠላም አላቸው ለማለት አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ .... የዘር ልዩነትና ጭቆና የቅኝ አገዛዝ መሠረቱ ኢኮኖሚ ነው፡፡

እነዚህም አሰቃቂ ተግባሮች የሚወገዱት በኢኮኖሚክ መሣሪያ ነው፡፡ በአዲስ አበባው የመሪዎች ጉባዔ የአፍሪካ አገሮች በቅኝ አገዛዝ ስር የሚገኙት አፍሪካውያን ካሉበት የባርነት ቀንበር ነፃ ለመውጣት በሚያደርጉት ትግል እንዲረዷቸው በማለት በገዥዎቻቸው ላይና ሙሉ የኢኮኖሚ አክሲዮን እንዲደረግ ወስነው በስራ ላይ አውለውታል፡፡..." እያሉ በማተት "በመጨረሻም መልካም መጥፎን ድል እንደሚነሳና እኛም እንደምናሸንፍ ጥርጥር የለውም" ባሉት መሠረት የአፍሪካውያን ጥረት ለመጨረሻው ድል በቅቶ በ1970ዎቹ አጋማሽ አመታት የአንጎላ፣ የሞዛምቢክና የጊኒ ቢሳው ህዝቦች ነፃነታቸውን ተቀዳጁ፡፡ እነዚህ የፖርቹጋል ይዞታዎች ነፃነታቸውን ካወጁ በኋላም እ.ኤ.አ በ1989 የመጨረሻዋ አፍሪካዊት አገር ናሚቢያ ለህዝቦቿ በተሰጠው የመምረጥ እድል አማካኝነት ነፃ አገር በቀል መንግስት መመስረት ቻለች፡፡

የደቡብ አፍሪካ የአፓርታይድ አገዛዝም በሕግ ተሽሮ ከዘር ነፃ የሆነ ምርጫ ተካሂዶ በምርጫው /A.N.C./ ኤ. ኤን. ሲን ወክለው የተወዳደሩት ኔልሠን ማንዴላ እ.ኤ.አ በ1994 ዓ.ም በከፍተኛ ድምፅ አሸንፈው በደቡብ አፍሪካ ሪፐብሊክ የመጀመሪያው ጥቁር ፕሬዝደንት ለመሆን ቻሉ፡፡

ባየነው መልኩ የቅኝ አገዛዝ ስርዓት ቢያከትምም የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዙ ዛሬም ድረስ እንደቀጠለ መገኘቱ አይዘነጋም፡፡ ጃንሆይ "የቅኝ አገዛዝ መሠረቱ ኢኮኖሚ ነው፣ ማስወገጃውም ኢኮኖሚ ነው" እንዳሉት የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዙም በኢኮኖሚ ድክመት በኩል የሚተገበር መሆኑን እያየን ነው፡፡

በእነዚያ ዘመናት ከኢትዮጵያ በስተቀር መላው አፍሪካና ህዝቦቿ ለነፃነታቸው ሲፍጨረጨሩ ኢትዮጵያ ነፃ የትምህርት እድል ለአፍሪካውያን ከመስጠት ባለፈ፤ ራሱን የቻለ በባለሙያ የተሞላ የውጭ ግንኙነት የነበራትና ቢሮክራሲዋም ዓለም አቀፍ ይዘት የነበረው አገር ነበረች፡፡



ልክ በዚሁ መጠንም ጃንሆይ አፍሪካ ውስጥ ራሱን የቻለ መንግስት ባልተመሰረተበት አህጉር ከታዋቂ መሪዎች ተርታ የተሰለፉ፣ ዓለም አቀፍ እውቅናቸው የዳበረና የተከበሩ ተሰሚነት የነበራቸው መሪ ነበሩ፡፡

ለውጭ ግንኙነት ምቹ የሆነ የአየር መንገድ ስለነበረም አፍሪካውያን የነፃነት ታጋዮች ባሻቸው ጊዜ በነፃነት ወደ ኢትዮጵያ እየመጡ በአህጉሪቱ ቀጣይ ዕጣ ፋንታ የመወያየት እድል ነበራቸው፡፡ በእኛ አቆጣጠር በ1953 ዓ.ም ግንባታው የተጠናቀቀውን የኢ. ሲ. ኤን /E.C.A/ አዳራሽ የመሰሉ ምቹ መሰብሰቢያዎችን ጃንሆይ በራሳቸው ገንዘብ አስገንብተው የፓን አፍሪካኒዝም ውልድ ለሆነው ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት አበርክተዋል፡፡ የድርጅቱ ቋሚ መቀመጫ ኢትዮጵያ እንድትሆን የተደረገውም የጃንሆይ መንግስት ለአህጉሪቷ ነፃነት ያበረከተው አስተዋፅኦ ከፍተኛ በመሆኑ ምክንያት ነው፡፡

ጃንሆይ "የአፍሪካ አባት" ነበሩና ዛሬም ድረስ በዚሁ ስም ይጠራሉ፡፡ ኢትዮጵያ "የአፍሪካ እናት" የተሰኘችውም በቅኝ ግዛት ያልተያዘች ብቸኛ አፍሪካዊት አገር በመሆኗ ብቻ ሳይሆን ለአፍሪካ ነፃነት ተምሳሌት በመሆኗ ነው፡፡ ከአፍሪካም ባለፈ በቆየው የአድዋ ድል ለመላው ተገዥ ህዝቦች የፅናት ተምሳሌት ሆና የተጠቀሰች ብቸኛ አገር ናት፡፡

ይህን መነሻ በማድረግም በርካታ የአፍሪካ አገሮች ከነፃነታቸው በኋላ የየራሳቸውን ሠንደቅ ዓላማ ሲያዘጋጁ የቀለም ምርጫቸው የኢትዮጵያን ሠንደቅ ዓላማ መሠረት ያደረገ ሆኖ ቀርቷል፡፡

ይህን ንዑስ ርዕስ ከማጠቃለላችን በፊት አንድ ከአፍሪካ ጉዳይ ውጪ የሆነ የጃንሆይን ተግባር እንይ፡፡ በእኛ አቆጣጠር በ1952 ዓ.ም በፈረንሣይ አገር የተፈጥሮ አደጋ ደርሶ ነበር፡፡ በዚያን ጊዜ ጃንሆይ የሐዘን መግለጫቸውን ከላኩ ከጥቂት ቀናት በኋላ የገንዘብ እርዳታ ለፈረንሣይ ሰጥተዋል:: በዚያ አፍሪካውያን ልዩ እርዳታ በሚያስፈልጋቸው ወቅት ጃንሆይ ከአፍሪካ አልፈው ለፈረንሣይ ያደረጉት እርዳታ ቀደም ሲል ያየናቸው ሐተታዎች ከወጡበት ከ1952ቱ "ፍሬ ከናፍር" ከተሰኘው መጽሐፍ ተካቶ የሚገኝ ሲሆን፤ የፈረንሣዩ መሪ ቻርለስ ደጎል እና ጃንሆይ የተለዋወጧቸው ቴሌግራሞች የሚከተሉትን ይመስላሉ፤

"ለክቡር ፕሬዝዳንት ደጎል
ኤሊዜ ቤተ-መንግስት
ፓሪስ፡፡

የፍሬጁስ ከተማ በደረሰባት አሰቃቂ አደጋ ምክንያት ጉዳቷን ለማቃለል ይረዳ ዘንድ በፓሪስ ኢንዶሺን ባንክ በኩል አምስት ሚሊዮን ፍራንክ ልከንልዎታል፡፡ ይህ የተላከው እርዳታ በዚህ መቅሰፍት ለተጎዳው ህዝብ በመሰለዎ አይነት ለእርዳታ ይውል ዘንድ ክቡርነትዎን እንጠይቃለን፡፡"

ከፕሬዝዳንት ቻርልስ ደጎል የተሰጠ መልስ፤

"የኢትዮጵያ ንጉሠነገስት ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለስላሴ

አዲስ አበባ፡፡

በፍሬዥስ ከተማ ላይ በወደቀበት አሰቃቂ መቅሰፍት ምክንያት ጉዳት ለደረሰበት ህዝብ ማቃለያ ይሆን ዘንድ ግርማዊነትዎ ርህራሄ በተመላ ቸርነቱ ስላደረገው ከፍ ያለ ስጦታ በሙሉ ልቤ ሳመሰግን፤ እንዲሁም በእኔና ይህ ጉዳት በወደቀበት ህዝብ ስም ሆኜ ጥልቅ የሆነ ባለውለታ መሆኔን እገልፃለሁ፡፡

ቻርልስ ደጎል፡፡"

ጃንሆይና ራስ ተፈሪያውያን

የጃንሆይ ንጉሠነገስትነት ለእኛ ነው፡፡ ለሌሎች ደግሞ አምላክ የሆኑበት ሁኔታ አለ፡፡ ይህን ታሪካቸውን ላለመዝለል ያህል ጥቂት ማለት ተገቢ ይመስላል፡፡ ኢትዮጵያን የዓለም ህዝቦች ዓይን ማረፊያ ካደረጓት ነገሮች ውስጥ አንዱ ነፃነቷን ሳታስደፍር መቆየቷና ብቸኛዋ ነፃ አፍሪካዊት አገር መሆኗ ነው፡፡ አውሮፓውያን በአፍሪካ ምድር ቅኝ ግዛታቸውን አንሰራፍተው ከዚችው አህጉር ጥቁር ህዝቦችን በባርነት እያጋዙ በየአገሮቻቸው የጥጥ፣ የትምባሆ እና የሌሎች ሰፋፊ የግብርና መስኮች ስራ ላይ እያሰማሩ በአሰቃቂ ሁኔታ ጉልበታቸውን በሚበዘብዙበት ጊዜ የጥቁር ህዝቦች ብቸኛ ተስፋና አርአያ የነበረችው ኢትዮጵያ ብቻ ነበረች፡፡

በተለይም የየካቲት 23/ 1888ቱ የዓድዋ ድል የበርካታ ጥቁሮችን ስሜት ያነሳሳና የነፃነት እንቅስቃሴያቸውን ያቀጣጠለ ክስተት ሆኖላቸዋል፡፡ ከተለያዩ ቅኝ ተገዥ አገራት የሚጋዙ ጥቁር ህዝቦችም በጉዞ ላይ ሳሉ በሚደርስባቸው ስቃይ ሳቢያ ሲታመሙ፣ ሲቆስሉና ጉዳት ሲደርስባቸው እስኪያገግሙ ይቆዩ የነበረበት ቦታ ጃማይካ ነበረች፡፡

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የነበረው ፍልሰት ቀጥሎ ብዙሃኑ ለረጅም ዓመታት በአውሮፓ ምድር ሲሰቃዩ ኖረው ከነፃነት በኋላም ዛሬም ድረስ ያልተመለሱ ኑሮዋቸው እዚያው የሆነ ጥቁር ህዝቦች ሞልተዋል፡፡

"ነብይ በአገሩ አይከበርም" እንዲሉ ራስ ተፈሪ በእኛ እይታ ከንጉሠነገስትነት ያለፈ ሚና ባይኖራቸውም፤ በጃማይካውያን ዘንድም ሆነ በዘመናቸው በነበሩ ጥቁር ህዝቦች ዘንድ የአምላክነት ወይም የነብይነት ስፍራ የተሰጣቸው ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡

በተለይም ለማርክስ ጋርቬይ እና ለመሰሎቹ ወደ አፍሪካ የመመለስ እንቅስቃሴ ጽኑ መሠረት ለመሆን ችለዋል፡፡ አሜሪካ በኢኮኖሚ ቀውስ በምትናወጥበት በ1920ዎቹ የመጀመሪያ አመታት ከነበረው የጭቆና አገዛዝ ጋር ተዳምሮ የጥቁር ህዝቦችን ጭቆና የመረረ አደረገው፡፡ ከ1887 እስከ 1940 ዓ.ም ድረስ ምድር ላይ የነበረው



ጃማይካዊ ማርክስ ጋርቬይ "Back to African Movement" ወደ አፍሪካ የመመለስ ንቅናቄ መስራችና አስተባባሪ በመሆን ታሪካዊውን የአድዋ ድል መነሻ በማድረግ ንቅናቄውን አጠናከረው፡፡

ከ1920ዎቹ ጀምሮ ብዙዎች ወደ አፍሪካ ምድራቸው ሲመለሱ ጥቂቶች ወደ ኢትዮጵያ መጥተዋል፡፡ይህ በእንዲህ እንዳለ ራስ ተፈሪ ንጉሠነገስት ሆነው ማስተዳደር ከጀመሩ በኋላ ፋሽስትም ዳግም ወረራ ባደረገበት ጊዜ ንጉሡ በስደት ለንደን ሆነው አቤቱታቸውን በሚያቀርቡበት ወቅት ጥቂት ጃማይካውያን ጥቁሮች ከንጉሠነገስቱ ጋር በመገናኘት በፌዴሬሽን ከኢትዮጵያ ጋር የመተሳሰር ሀሳባቸውን አቀረቡላቸው፡፡ጃንሆይም ሀሳባቸውን ተቀብለው ፈቃዳቸውንም ገልፀው አሰናበቷቸው፡፡

በዚያን ጊዜ "W.F.R. (World Federation of Rasta)" በሚል ለመጀመሪያ ጊዜ የዓለም የራስ ተፈሪያውያን ፌዴሬሽን ተመሠረተ፡፡ ከዚህ ጊዜ በፊትም እ.ኤ.አ በ1920 ዓ.ም ኃይለስላሴ ከመንገሳቸው በፊት (ራስ ተፈሪ እያሉ) ማርክስ ጋርቬይ አውሮፓውያን ለአውሮፓ እንደሆኑት ሁሉ አፍሪካውያንም ለአፍሪካ ሆነው ባርነትን ትተው ወደ ምድራቸው መመለስ እንዳለባቸው፤ ባለመብት በሆኑበት በአፍሪካ ውስጥም በነፃነት ራሳቸውን በማደራጀትና በማስተባበር ታላቅ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ለውጥ መፍጠር መቻል አለባቸው የሚለውን አቋሙን በአሜሪካ ማስተማር ጀምሮ ነበር፡፡ ማርክስ ጋርቬይ አውሮፓና አሜሪካ የማስተማር ቆይታውን ጨርሶ በ1927 እ.ኤ.አ ወደ ጃማይካ ተመለሰ፡፡

ለህዝቦቹም ትምህርቱን ከነፖለቲካዊ ዓላማው እየተነተነ በደንብ አስረዳቸው፡፡ "የአፍሪካ ቀን እየመጣ ነው፡፡ ቀኑ መቼ እንደሆነ የሚያውቅ የለም፣ ነገር ግን ይመጣል" በማለት ሲያስተምር ቆየ፡፡

በትምህርቱ ውስጥም ለጥቁሮች ችግር መፍትሔ አፍሪካ መሆኗን፤ ጥቁር ህዝቦች የአምላክ አምሳያ መሆናቸውን፤ በቅርቡ የሚነሳ ጥቁር ንጉስ የዚህ ትምህርት ትንቢት ፍፃሜ አመላካች መሆኑን" ደጋግሞ ገለፀ፡፡

የጋርቬይ ትምህርት በጃማይካ ጥቁር ህዝቦች ዘንድ ከሰረፀ ከጥቂት አመታት በኋላ ራስ ተፈሪ ንጉሠነገስት ሆኑ፡፡ ይህ ክስተት ጃማይካውያንን ጋርቬይ በመሠረተው ድርጅት እንዲያምኑና እንዲቀላቀሉ አስገደዳቸው፡፡ በሁኔታዎችና በሚዲያ በሚሰጡ መግለጫዎች የበለጠ አላማው እየታወቀለት ትንቢቱ መስመሩ ተቀባይነት እያገኘለት ይሄድ ጀመር፡፡

ከዚያም ታሪኩ መፅሐፍ ቅዱሳዊ ይዘት እንዳለው ሆነና በአውሮፓና በአሜሪካ የደም ላባቸውን የሚያፈሱና በባርነት ቀንበር ስር የአውሮፓን ሀንፃ የሚገነቡ፣ ግብርናውን የሚያቀላጥፉና ኢንደስትሪውን የሚያንቀሳቅሱ ባሮች በአጠቃላይ በነጭ ስር የሆኑ ጥቁር ህዝቦች ራሳቸውን እንደ እስራኤላውያን ተገዥዎች መቁጠር ሲጀምሩ፤

ገዥዎቻቸው የሆኑ ነጮችን እንደ ግብፅ ፈርኦኖችና ህዝቦች መቁጠር ጀመሩ:: ጋርቬይም ይህንኑ መፅሐፍ ቅዱሳዊ ቃል ምሳሌ እያደረገ ማስተማሩን ቀጠለ::

እናም አፍሪካውያን ጥቁር ህዝቦች በባርነት የሚኖሩበት አገር "ባቢሎን" ሲባል፤ የሚመለሱባት የተስፋይቱ ምድር "ከነዓን" እንደሆነች እሷም ኢትዮጵያ መሆኗን አምነው ተቀበሉ::

ኢትዮጵያ ከባርነት አገር ተነስተው የሚመጡባት የተስፋ ምድር ከነዓን የመሆኗን ሚስጥርም የማርክስ ጋርቬይ /የነብያቸው/ ትምህርት የፈጠረው መሆኑ ነው:: ጋርቬይ ቀደም ሲል በጀመረው የመመለስ እንቅስቃሴ ይህ ነው የሚባል ተጨባጭ ለውጥ ያልመጣ ቢሆንም፤ ራስ ተፈሪ ከነገሱ በኋላ ግን ትንቢቱ ተፈፀመለትና ራስ ተፈሪያኒዝም ራሱን የቻለ ሃይማኖት /እምነት/ እየሆነ ሄደ::

በዚህም በርካቶች ወደተስፋይቱ ምድር የመመለስን ጥያቄ በውስጣቸው ማንሰላሰል ያዙ:: ቀስ በቀስም በመላዋ ጃማይካ ተከታዮቹ በረከቱ:: ቀደም ሲል ይዝናኑበትና ይታወቁበት የነበረው የ"ብሉዝ" የዜማ ስልት በ"ሬጌ" ስልት ተለወጠና እነ ኒስታ ቦብ ማርሌይ ለራስ ተፈሪያኒዝም ተከታዮች ዓላማቸውን የማስረጫ መንገድ አደረጉት:: ቦብ ማርሌ (ኤክሲደስ) "ዘፀዓት" ሲል አዜመ:: ተቀብለው አቀነቀኑ:: በዘፈናቸው ተደጋግሞ የሚደመጠው "ባቢሎን" የሚለው ቃልም ካየነው ታሪክ በመነሳት ሳይጠቀስ የማይታለፍ ሆነ::

የጃንሆይ የንግስና ስማቸው ኃይለስላሴ ስለሆነም በስላሴ ትምህርት መሠረታቸውን በማድረግ እንደ አምላክ እንዲቀበሏቸው ማረጋገጫ ሆነላቸው:: በዚህ ጊዜ ማርክስ ጋርቬይ ነብይ፤ ራስ ተፈሪ አምላክ ሆነው ታመኑ::

ንጉሡ ጃማይካን በጎበኙ ጊዜ "እኔ አምላክ አይደለሁም" ብለው ቢያስተባብሉም መላው የጃማይካ ህዝብ ግን የንጉሡን ንግግር እንደ ትህትና ቆጥረው "አምላካችንን አየናቸው" አሉ እንጂ ማስተባበያውን አልተቀበሉትም::

እ.ኤ.አ በ1966 ዓ.ም አፄ ኃይለስላሴ ጃማይካን በጎበኙበት ጊዜ በመላው ጃማይካዊ ራስ ተፈሪያኒዝም ዘንድ ታላቅ ታዓምራት የታየበት እለት ተባለ:: የጃንሆይን የጃማይካ ጉብኝት በተመለከተ በአዲስ ውበት መፅሔት በ1997 ዓ.ም ቃለ-ምልልስ ያደረገው የራስ ተፈሪያን ተከታይ የሆነው ዳኒ በወቅቱ ቦታው ላይ ነበርና ሁኔታውን እንዲህ ይገልፀዋል::

"ንጉሡ ከአውሮፕላን በወረዱ ጊዜ አለቀሱ::የማልቀሳቸውም ምስጢር ያንን ከቦ የሚጮህ ህዝብ ማየታቸው ነው::የህዝቡ ፍቅር፣ደስታ፣መሪና አምላክ መፈለግ ልባቸውን ነካው::ደግሞም የሚያዩት ህዝብ ከኢትዮጵያውያን ጋር የሚመሳሰል ነው::ንጉሡም"በእርግጥ የማየው



ህዝብ በትክክል ከኢትዮጵያውያን ጋር የሚመሳሰል ነው" ማለታቸውን" ይገልፃል:: "በወቅቱ ጃማይካ ለ7 ወራት ያህል ዝናብ አጥታ ድርቅ ሆና ነበር::ንጉሡ ግን ዝናብ ዘንቦ ካባራ በኋላ ነበር የደረሱት::

ቀኑ በጣም ጨለማና ጨፍጋጋ ሆኖ ውሎ ልክ ንጉሡ ከአውሮፕላን በወረዱ ጊዜ ገፈፈ:: ብርሃንም ሆነ:: እናም እውነት ነው:: ህዝቡም ዝናቡንም ሆነ ብርሃኑን ያመጡልን ንጉሡ ናቸው በማለት የዓይን እማኝነቱን አረጋግጧል" የሚል ቃሉን የሰጠው በየካቲት ወር 1997 ዓ.ም የቦብ ማርሌ 60ኛ ዓመት በአዲስ አበባ ሲከበር በተደረገለት ቃለ ምልልስ ነበር::

ይህን መሰሉ ታሪካዊ ግጥምጥሞሽ ለራስ ተፈሪያኒዝም ግን እውነት ነውና አፄ ኃይለስላሴ ለአንዳንዶቹ አምላክ፤ ለሌሎቹ ነብይ ሆነው ዛሬም ድረስ ይመለካሉ:: ኢትዮጵያም የተስፋይቱ ምድር መሆኗ ቀጥሏል::

ራስ ተፈሪያኒዝም አንድ ራሱን የቻለ እምነት /ሃይማኖት/ ይሁን እንጂ ተከታዮቹ ግን አንድ የሚያምኑት ነገር አለ:: ይኸውም በውስጡ ፖለቲካዊ የነፃነት ትግል የያዘ መሆኑን ነው::
ራሳቸውን ሲጠሩ ራስታ፣እምነታቸውን ደግሞ ራስተፈሪያኒዝም በማለት አፄ ኃይለስላሴን አምላካችን ናቸው ብለው ማመናቸው እንዳለ ሆኖ፤የነፃነት ትግል በውስጡ መያዙን አይክዱም::ጠቅለል ተደርጎ ሲታይ ራስ ተፈሪያኒዝም ተብለው ቢጠቃለሉም በስሩ ግን በርካታ ልዩነቶችን እናያለን::የተለያዩ ቡድኖችም በስሩ ይገኛሉ:: ለምሳሌ፤"ቦቦ ድሬድ /BOBO -DRED TWELVE/ አንድ የአማኞች ቡድን ሲሆን (በሻሸመኔ የሚገኝ ቡድን ነው)መሪያቸው ፕሪንስ ኢማኑኤል ነው::እንደ ቦቦ እምነት ማንኛውም የእምነቱ ተከታይ ወንድ እንደ ነብይ ይቆጠራል::ሲል እንደ ሌሎቹ ራስ ተፈሪያን ሁሉ የጥቁሮች ደህንነት ከባቢሎን ወደ ኢትዮጵያ መመለስ ነው::

ሌላው ቦብ ማርሌይ እና ቤተሰቦቹ የሚገኙበት የእምነት ቡድን ሲሆን፤ በራስ ተፈሪያን ስር ሆኖ የ12ቱ የእስራኤል ነገዶች /TWELVE TRIBES OF ISRAEL/ የሚባል ነው:: በዶክተር ቬርኖን መሪነት ይተዳደር ነበር:: የአፄ ኃይለስላሴን የልጅ ልጅ ወደዙፋን የመመለስ ህልምም ነበራቸው:: ዛሬም የልጅ ልጅ ልጅ የሆነውን እንዲመለስ ይናፍቃሉ:: መሠረታቸው ኦርቶዶክስ ሆኖ፤ ከእምነቱ መመሪያ ውስጥ በየቀኑ አንድ ምዕራፍ ከመፅሐፍ ቅዱስ ማንበብ የሚል ጥብቅ መመሪያ አላቸው::

ሌላው ቡድን "ኒያቢንጊ" ማለትም "ሞት ለነጮች" የሚል ትርጉም ያለውና "ጥቁር ያልሆነ ወይም ነጭ የሆነ ሰው የራስ ተፈሪያን ተከታይ

ይከበርበት በነበረው ዕለት ይቀርቡ የነበሩ የውዳሴ ግጥሞችም ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ትችት እያካተቱ መነበብ ጀመሩ። በዚህም መንግስት ክፉኛ ተቆጥቶ በ1954 ዓ.ም የተማሪዎችን አስተባባሪዎችና አባላት ከትምህርት እንዲታገዱ እስከመወሰን ደረሰ።

በ1956 ዓ.ም የኢትዮጵያ ዩንቨርሲቲ አገልግሎት የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ከትምህርት ጊዜያቸው ውስጥ አንዱን ዓመት በገጠሪቱ ኢትዮጵያ እንዲያሳልፉ ወስኖ ተግባራዊ ሲሆንም፤የተማረው አካል የገጠሩን ማኅበረሰብ ህይወት እንዲገነዘብ አደረገው።ከዚህም ባለፈ ይህ ተግባር በየግዛቱ ያሉ የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎችንና የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን በማቀራረብ ረገድም የራሱ አስተዋፅኦ ነበረው።

ከተጠቀሰው ዘመን በኋላ ባሉት ተከታታይ ዓመታት ለተማሪዎች የመጀመሪያ ፍላጎትና የትግል ዘዴ ሆኖ የታያቸው ሀሳባቸውን የሚገልፁበትና ለሌሎችም የሚያሰራጩበትን ነፃ መድረክ መፍጠር ነው።ስለዚህም የፕሬስ ውጤት ብቸኛ አማራጭ ነበርና የራሳቸውን መጽሔት የሚያዘጋጁበትን ሁኔታ ማመቻቸትና ነፃ ማኅበራትን ማቋቋም ጀመሩ።

ቀደም ሲል የነበረው የተማሪዎች ምክር ቤት ማኅበር አደረጃጀቱ ነፃ ያልነበረና በኮሌጁ ዲን ቁጥጥር ስር የነበረ ነው። በልሳን ደረጃ ዩ.ሲ ኮልስ (የዩንቨርሲቲ ኮሌጅ ጥሪ) እና ኒውስ ኤንድ ቪውስ (ዜናና አስተያየት) የተባሉ መጽሔቶችም ፖለቲካ ውስጥ የማይገቡና የዩኒቨርሲቲውን የበላይ አካላትና የአስተዳደር እንዲሁም የመማር ማስተማሩን ሂደት የሚተቹ ጽሁፎች አልፎ አልፎ የሚቀርቡባቸው የነበሩ ናቸው።

በዚህ መሠረት ከ1954 ዓ.ም ጀምሮ በስውርም፤በገሃድም ነፃ የተማሪዎች ማኅበር እየተቋቋሙ ልዩ ልዩ የተቃውሞ ድምጾች መደመጥ ጀመሩ።የጃንሆይን አገዛዝ በመቃወም ረገድ ከፍተኛ ተፅዕኖ የፈጠረው በ1956 ዓ.ም የተቋቋመው "ክሮኮዳይል" ወይም "አዞ" የተባለው ቡድን ነው። የኢምፔሪያሊዝምን ክፉ ገፅታ በመተንተንና የማርክሲዝምን ጽንሰ ሀሳብ በማዋካሸት ረገድም ሆነ፤ የንጉሡን አገዛዝ የሚቃወሙትን አካላት ተቃውሟቸው የከረረ ሆኖ እንዲቀጥል በማድረግ ረገድ፤እንዲሁም ኢትዮጵያ ከጃንሆይ አገዛዝ በኋላ ለጠበቃት ተከታይ መዘዝና አገሪቱ ዛሬ ላለችበት ቅርፅና ይዘት ሁሉ አዞዎቹ የአንበሳውን ድርሻ ይይዛሉ።

የተማሪዎች ነፃ ማኅበር ምስረታ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶም በአገር ውስጥና በውጭ አገር አገዛዙን ለመቃወም የተመሠረቱ መሰል ቡድኖች አላማቸውን በጋራ ማራመድ ቀጥለዋል። እነርሱም፤

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ማኅበር (አ. አ. ዩ. ተ. ማ.)



- የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር በሰሜን አሜሪካ (ኢ.ተ.ማ.ሰ.አ)
- የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር በአውሮፓ (ኢ.ተ.ማ.አ)
- የኢትዮጵያ ተማሪዎች ዓለም አቀፍ ማኅበር (ኢ.ተ.ዓ.አ.ማ) የሚባሉ ናቸው። እነዚህ ማኅበራት የየራሳቸውን መጽሔቶችና የንድፈ ሃሳብ ልሳኖችን መሠረቱ።

የኢትዮጵያ ተማሪዎች ዓለም አቀፍ ማኅበር የእህጉር ቅርንጫፍ የሆነው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ማኅበር "ታገል" የተሰኘ መጽሔትን፤ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር በሰሜን አሜሪካ "ቻሌንጅ"ን፤ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር በአውሮፓ ደግሞ የ"ታጠቅ" እና የ"ትግላችን" መጽሔቶችን መስርተው እንቅስቃሴያቸውን አጎልብተው ቀጠሉ።

በተለይ "ቻሌንጅ" እና "ታጠቅ" የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ የጋራ የንድፈ ሃሳብ መጽሔቶች ሆኑ። የድርጅትና የርዕዮተ ዓለም የበላይነቱን አረጋግጦ የነበረው ግን "ታገል" ወይም "Struggle" የሚለው መጽሔት ሲሆን፤ የግራ ክንፍ የበላይነቱንም የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ማኅበር ነበር የያዘው።

በውጭ አገር ያሉትና እንደ ዋና አስተባባሪ ማኅበራት የሚቆጠሩት አንድ ዓላማ የነበራቸው ማኅበራትም በስተመጨረሻ በመገንጠል ጉዳይ ተከፍለው በጠላትነት ሲዋረፉ ኖረው፤ ከአብዮቱ በኋላም የእነርሱ የመረረ ጥላቻ ወደ ኢትዮጵያም ተዛምቶ ብዙ እልቂት አስከተለ። ነገር ግን በዚያ ወቅት በተለይ ልሳኖችን በማሰራጨት በኩል የውጮቹ የተጫወቱት ሚና ከፍተኛ ነበር።

በእነዚህና በሌሎች መሰል የፖለቲካ ትግል ዘዴዎች በመጠቀም ዋና ዋና ማኅበራቱና ንዑሳን ቡድኖች፣ በአገር ውስጥና በውጭ አገር ያሉት ሁሉ በጋራ ይፋ ያደረጉት አቋማቸው በኢትዮጵያ ተማሪዎች ዓለም አቀፍ ማኅበር አባላትና መጽሔቶች ሲገለፅ፤"የኢትዮጵያ ህዝብ ላጋጠመው የስርዓት ችግር መፍትሄው የፖለቲካ ጥገና ሳይሆን አብዮታዊ የስርዓት ለውጥ እንደሆነ፤መሬት ላራሹ የሚለውን የፖለቲካና የኢኮኖሚ ጥያቄ እስከመጨረሻው ማስተጋባት፣ ኢምፔሪያሊዝምና ፊውዳሊዝም የኢትዮጵያ ህዝብ ዋና የመደብ ጠላቶች እንደሆኑና ይህን መሰሉን አገዛዝ ለመገርሰስ የፖለቲካ ትግሉን እስከመጨረሻው መቀጠል" የሚል ነው።

እነዚህን አቋሞች ከኢትዮጵያ ውጭ ያሉ ታጋዮች አቅልለው ቢገልጿቸውም ለአገር ውስጥ የተግባር ተፋላሚዎች ግን እጅግ ፈታኝ ነበሩ። ምንም ቢሆን ግን የአገር ውስጥ ተማሪዎች ከመተግበር ወደኋላ አላሉም። የመጀመሪያውን የከረረ ተቃውሞ በ1957 ዓ.ም ተገበሩት። "መሬት ላራሹ" ብለው የአዲስ አበባን ጎዳና አጥለቀለቁት። ከፀጥታ

አስከባሪዎች ጋር መጋፈጡ ቀላል ያልነበረ ቢሆንም፤ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በየዓመቱ ተማሪዎች ሰልፍ እየወጡ ስርዓቱን መቃወማቸውን ቀጠሉ፡፡

ለአመፅ ወደ ጎዳና የሚወጡበት መፈክርም በተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ላይ በሚታዩ በደሎች መነሻነት ነው፡፡ በዚህም ብቻ ሳይሆን በየሰበብ አስባቡ ሰልፍ ለመውጣት ዝግጁ ነበሩና በጎ እና ተራማጅ የሆኑ ተግባራትንም ከመቃወም አልቦዘኑም፡፡

በ1958 ዓ.ም መንግስት ድሆችን በአዲስ አበባ ሾላ አካባቢ ባዘጋጀው መጠለያ አሰፍሮ እርዳታ ሲሰጣቸው የነበሩትን ዜጎች "የሾላ እስረኞች ናቸው" የሚል ስያሜ ሰጥተውና ይህንኑ መነሻ አድርገው ነበር ሰልፍ የወጡት፡፡

በ1959 ዓ.ም የሲቪክ መብቶችን የሚመለከት የሕግ ረቂቅ ለፓርላማ ሲቀርብ ተማሪዎች "የሲቪክ መብቶችን ለመገደብ ነው" ብለው ወደ ጎዳና ወጥተው ተቃወሙ፡፡ በ1960 ዓ.ም የቬትናምን ህዝብ ፀረ-አሜሪካ አቋም መያዝ ደግፈው ሰልፍ ወጡ፡፡ በዚያው ዓመት ማለቂያ ላይ በዩንቨርሲቲው ጊቢ ይካሄድ የነበረውን የባህል ፌስቲቫል (ፋሽን ሾው) "የኢምፔሪያሊዝም ነፀብራቅ ነው" በሚል ተቃውመው ሰልፍ ወጡ፡፡ በ1961 ዓ.ም "የትምህርት ስርዓቱ ይሻሻል" በሚል ያነሱት አመፅ ከዩንቨርሲቲው አልፎ በየግዛቱ ያሉ የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎችን አዳረሰ፡፡

ቀስ በቀስ እንቁላል በእግሩ ይሄዳል እንዲሉ በ1962 ዓ.ም የመጀመሪያ ወራት ተማሪዎቹ "ብሔር ብሔረሰቦች የራሳቸውን እድል በራሳቸው የመወሰን መብታቸው (እስከመገንጠል) መረጋገጥ አለበት!" ብለው በመወሰናቸው የጃንሆይ መንግስት ክፉኛ ተደናግጦ በተማሪዎቹ ላይ ጠንከር ያለ ጥቃት ለመሰንዘር ተገደደ፡፡ በዚያን ጊዜ ወደ ፊት እንደምናገኘው በመንግስት ጋዜጦች አማካኝነት መንግስት የፀረ ተማሪ ፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ካካሄደና ካስጠነቀቀ በኋላ ነበር እርምጃ የወሰደው፡፡

ይህ የራስን እድል በራስ መወሰን የሚለው ጉዳይ በ1962 ዓ.ም በአደባባይ ይውጣ እንጂ ቀደም ካለው ጊዜ ጀምሮ የ"ጀብሃ" ዓላማ የነበረና በ1961 ዓ.ም ፊት ለፊት በማይጋፈጠው "አዞ" በተሰኘው ቡድን አማካኝነት ወደ ዩኒቨርሲቲው እንዲሰርፅ የተደረገ ነው፡፡ አዞዎቹ እንደማንኛውም ተማሪ ሆነው በስውር ስለሚንቀሳቀሱ በሚያሰርጿቸው ድብቅ የጀብሃ ጥያቄዎች ምክንያት ሌሎች አገዛዙን ከመቃወም አንፃር ብቻ ሆ ብለው ሰልፍ የሚወጡና የጀብሃን ዓላማ የማይደግፉት ተማሪዎች ነበሩ፤ የመንግስት የቅጣት እርምጃ ሰለባ የሚሆኑት፡፡

ፐ/ር ላጲሶ ይህን ጉዳይ ሲገልፁት፤ "በዘመኑ በአገር ውስጥና በውጪው ዓለም ስርዓቱን ለመጣል የሚታገሉት አካላት አስከፊው የፊውዶ ቡርዣ ስርዓት ላይ አስቀድሞ የመሣሪያ ትግል በመክፈቱ ጀብሃ ተራማጅ



ቡድን እንደነበር በመገመት ከ1954-1961 ድረስ የአንድነት ድጋፍ ይሰጡት ነበር፡፡ ነገር ግን ታሪክና ጊዜ በኋላ እንዳሳየው የጀብሃ ዓላማ ፀረ-ኢትዮጵያ ከሆኑ አካባቢ አገሮች የመሣሪያና የገንዘብ እርዳታ አግኝቶ የኤርትራን ክፍለ ሀገር ከኢትዮጵያ ቆርጦ የዓረቡ ዓለም አካል ማድረግ ነበር፡፡ ከ1954-1961 ድረስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የ"አዞ" ማኅበር በሚል ህቡዕ ድርጅት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ማኅበር (አአዩተማ) አመራር ውስጥ ጀብሃን በስውር አሰራር የሚደግፉ ግለሰቦች ነበሩ" በማለት ነው፡፡

ይህን የጀብሃን የመገንጠል ዓላማ በሰሜን አሜሪካ ያለው የተማሪዎች ማኅበር ለረጅም ጊዜ መርምሮ በ1961 ዓ.ም በነሐሴ ወር በፊላደልፊያ ከተማ ባካሄደው 17ኛው ጉባኤ ላይ ዓላማውን የሚነቅፍ አቋም ወሰደ፡፡ ምክንያቱም የጀብሃ አቋም "የኤርትራን ህዝብ የማይወክል፣ በኢምፔሪያሊዝምና በፊውዳሊዝም የጋራ ጠላቶቻቸው ላይ የኢትዮጵያ የብሔረሰቦችንና የሠርቶ አደሩን ህዝብ መደባዊ የትግል አንድነት የሚያዳክም አድሃሪ ኃይል ነው" በሚል አወገዘ፡፡ ይህን የሰሙት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ማኅበር ውስጥ ያሉት የጀብሃ ደጋፊዎች ማለትም "አዞዎቹ" በፊላደልፊያ የተወሰደውን አቋም "የብሔር ትምክህተኝነት መገለጫ ነው" ብለው የነቀፋ መልስ ሰጡ፡፡ በዚህም ሳይወሰኑ ለፊላደልፊያው አቋም ምላሽ ይሆን ዘንድ በህዳር 7 ቀን 1962 ዓ.ም በማኅበሩ መጽሔት በታገል ቅጽ 5 ቁጥር 2 ላይ "የብሔረሰቦች ጥያቄ በኢትዮጵያ" በሚል ርዕስ "አብዛኛው የኢትዮጵያ ማኅበረሰቦች በማኅበራዊ የእድገት ደረጃቸው ብሔሮች ስለሆኑ ከጨቋኙ ስርዓትና መንግስት የመገንጠል መብታቸው የተጠበቀ ነው" በማለት ጠንካራ አቋም በመውሰዳቸው የታህሳስ 1962 የመንግስት ቁጣና ርምጃን እንዲከሰት አደረጉ፡፡

ጽሁፉ በሕዳር 7 በታገል መጽሔት ከወጣበት ጊዜ ጀምሮም መንግስት ለሁለት ሳምንታት ያህል የኃይል እርምጃ ከመውሰዱ በፊት የተማሪዎችን አቋም የሚያጣጥል የማስ ሚዲያ ዘመቻ ከፍቶ ተማሪዎችንም እያስጠነቀቀ ቆየ፡፡

ህዳር 19 ቀን 1962 ዓ.ም መንግስት በ"አዲስ ዘመን" ጋዜጣ ላይ ጉዳዩን አስመልክቶ ተከታዩን ጽሁፍ አትሞ አወጣ፡፡ የጽሁፉ ርዕስ "ከመጠኑ አለፈ" የሚል ነው፡፡

"ገና በማደግ ላይ ያሉ አገሮች ከሚመኙት የኢኮኖሚ፣የፖለቲካና የማኅበራዊ ኑሮ የስልጣኔ ደረጃ ለመድረስ ከተፈጥሮ ሐብት፣ከሰው ጉልበትና ከካፒታል ሌላ፤ እውቀት፣ኅብረት እና ፀጥታው የተጠበቀ መንግስት የፀና አቋም እንዲኖር አስፈላጊ ነው፡፡ሠላምና ፀጥታ ሲታጣ፣ ስርዓትና ሕግ ሲጣስ በህይወትና በንብረት ላይ የሚያስከትለውን ጥፋት

ለመገንዘብ የሩቅ ምሳሌ መሻት አያስፈልግም፡፡ ባለፉት ወራቶች ውስጥ በጥቂት ተማሪዎች አነሳሽነት አልፎ አልፎ ፀጥታ የሚያደፈርስ በህዝብ፣ በህይወትና ንብረት ላይ አደጋ የሚያደርስ ሁከት እየተፈጠረ ጥፋተኞቹ ከሕግ ፊት እየቀረቡ ቅጣታቸውን እንዲቀበሉ መደረጉ ይታወሳል፡፡

ጥቂቶቹ ተማሪዎች የኢትዮጵያን አንድነት በሚጠሉ የባዕድ ተንኮለኞች ጋር በመተባበር በአገሪቱ ውስጥ ፀጥታ ለማደፍረስ፣ ለሠላማዊው ህዝብ ሠላም ለመንሳት ያደረጉት ጥፋት በትዕግስትና በይቅርታ ታልፎ ሳለ ሰሞኑን ጥቂቶች የዩንቨርስቲ ተማሪዎች የሚያሳዩት ተግባር ሕገወጥ ከመሆኑም አልፎ መንግስት ከዚህ ቀደም እንዳደረገው ሁሉ በትዕግስት ከማይታለፍበት ደረጃ ደርሷል" ይላል፡፡

ቀጥሎም በማግስቱ ህዳር 20 ቀን 1962 ዓ.ም "ፍሬ ቢስ ሙከራ" በሚል ርዕስ በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ ላይ ተከታዩን ጽሁፍ መንግስት አውጥቷል፡፡ "የኮሚኒዝምን አይዲኦሎጂ እናስፋፋለን የሚሉት ጥቂት የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በየጊዜው በሚያወጡት መጽሔታቸውና በሚበትኗቸው ወረቀቶች የህዝብ ፀጥታና ሠላማዊ ኑሮ ለማደፍረስ መሞከራቸው ተደጋግሞ ተገልጧል፡፡ የባዕድን ፍልስፍና በመከተል የአገሪቱን ነዋሪ ስርዓትና ባህል ለመሻር መሞከር ከንቱነት ነው፡፡

ኢትዮጵያ እንደሌሎች መንግስቶች በሕገ-መንግስት ትመራለች፡፡ሕገ-መንግስቱም ግልፅና ቀና ነው፡፡ከሕገ-መንግስቱ ውጪ የሆነ ሁሉ ሕጋዊ አይደለም፡፡ ያስከስሳል፡፡ያስቀጣል፡፡ሕገ-መንግስቱን የሚሳደብ፣የሚፃረር፣ የሚተናኮልና የሚቃረን የመንግስት ጠላት ነው፡፡ ህዝብ አምኖ የተቀበለውን ስርዓት ለመሻር ባዕድ አሳብ የመሰንዘር፣የቆየውንና የኖረውን ልማድ ሁሉ የሚያንኳስስ፣ሃይማኖትን የሚያቃል፣አባቶችን የሚያዋርድ፣የተደነገጉትን ሕጎች የማይታዘዝ፣በእጉል ትምክህትና ትዕቢት የሚመራ ብቻ ስለሆነ አሳቡና ዝንባሌው አደገኛ ነው፡፡"

በዚህ ዓይነቱ ዘመቻ መንግስት ለህዝቡ አቋሙን በተደጋጋሚ ከገለፀና ተማሪዎችንም ካስጠነቀቀ በኋላ ተማሪዎቹም ከተግባራቸው ለመታቀብ ስላልሞከሩ ታህሳስ 19 ቀን 1962 ዓ.ም ቀደም ሲል እንዳየነው የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ማኅበር ፕሬዝዳንት የነበረውን ጥላሁን ግዛውን ጨምሮ ከ20 በላይ ተማሪዎች በግርገሩ ተገደሉ፡፡ ዩንቨርሲቲውም ላልተወሰነ ጊዜ ተብሎ ተዘጋ፡፡ የታገል መጽሔት ህልውናም አከተመ፡፡ በዚህ ጊዜ ነው ጎሚሱ የጀብሃ ደጋፊዎች የነበሩት የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ወደ ትጥቅ ትግሉ አምርተው ከጀብሃ ጋር የተቀሳቀሉት፡፡

The crocodile society ወይም የ"አዞ" ማህበር በስውር የትግል ስልቱ እየተጠቀመ ረጅም መንገድ የመጓዙን ያህል፤ በማኅበሩ ስም የሚከናወኑትን እመጾች አጋግኗል፡፡ መንግስት የአገር ውስጡን የተማሪ



ማኅበር ከበተነው በኋላም ጎሚሶቹ በርሃ ቢገቡም የቀሩት ደግሞ የመንግስት ተፅዕኖ ያስመረራቸው መስለው ያንኑ የአዞ ዓላማና ተግባር፤ እንዲሁም ምስጢራዊ የትግል ስልትና አሰራራቸውን ይዘው በልዩ ልዩ መንገዶች ወደ አሜሪካና ወደ አውሮፓ ተሰደው በኢተማአ እና በኢተማሰአ ውስጥ ተቀላቀሉ፡፡

በነሐሴ ወር 1962 ዓ.ም ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ማኅበር አባላት ጥቂቶቹ የአዞ ማኅበር አስራር ኢንጂነር በነበረው በብርሃነ መስቀል ረዳ መሪነት አንድ የኢትዮጵያ መንገደኞች አውሮፕላን ጠልፈው ወደ ሱዳን ካርቱም ገቡ፡፡ ከካርቱም ወደ አልጀሪያ በመሄድም በብርሃነ መስቀል መሪነት ራሳቸውን የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር በሰሜን አፍሪካ ብለው ሲሰይሙ ቁጥራቸው 8 ያህል ነበር፡፡

ወደ አውሮፓና ወደ አሜሪካ የፈለሱት የቀድሞው የአአዩተማ አባላትና የአልጀሪያው ቡድንም በኢትዮጵያ አብዮትና የብሔረሰብ ጥያቄዎችን በሚመለከቱ ጉዳዮች ተመሳሳይ አቋም የነበራቸው ሲሆን፤ በአገር ውስጥ ከቀሩት አባላትና አመራር ጋርም የትግል አንድነታቸው እንደፀና ነበር፡፡

የሰሜን አሜሪካው ቡድን በፊላደልፊያ የወሰደውን አቋም የአውሮፓው ቡድን ሳይቀበለው የቀረና ከአገር ውስጡ ቡድን ጎን ተሰልፎ ያወገዘበት ሁኔታ ተፈጥሮ የነበረ ቢሆንም፤ በስተመጨረሻ ግን የአልጀሪያው ቡድንና ሸሽተው የሄዱ አባላትና አመራር መልሰው በአውሮፓው ቡድን የሂስ ዘመቻ ሲከፍቱበት እናያለን፡፡

የተማሪዎች ዓለም አቀፍ ስርጭትን ተከትሎም በአውሮፓና በአሜሪካው ቡድን ገብተው የተቀላቀሉ የጀብሃ ዓላማ አራማጆች ሁኔታውን አወሳሰቡት፡፡ ወደ አሜሪካ የተጓዙት የአገር ውስጥ ማኅበሩ አባላትና አመራር በነሐሴ ወር 1962 ዓ.ም በዋሽንግተን ዲሲ በጆርጅ ዋሽንግተን ዩኒቨርሲቲ በተካሄደው 18ኛው የኢተማሰአ ጉባኤ ላይ ተገኝተው የ17ኛውን የፊላደልፊያ አቋም "አደገኛ የሆነ የብሔር ትምክህተኝነት ነበር" በማለት የውግዘት መግለጫቸውን ደግመው አሰሙ፡፡ ሲቀጥሉም በኢትዮጵያ አብዮቱን ለማስነሳት ጊዜው መድረሱን በመጠቆምና የላቲን አሜሪካ ታጋዮችን ፊደል ካስትሮንና ቼጉቬራን በመጥቀስ እነሱ ያካሄዱትን አይነት የትጥቅ ትግል በኢትዮጵያ ለመጀመር "ፋኖ ተሰማራ እንደነካስትሮ እንደቼጉቬራ" በማለት ከሌሎች መሰል መፈክሮች ጋር በታላቅ ጩኸት መሸለል ጀመሩ፡፡ የኢተማሰአ አባላትንና አመራሮችንም "የወንበር ላይ ምሁር" ብለው ዘለፏቸው፡፡

እነዚሁ ፎካሪዎች ከጉባኤው በኋላ በነበሩ 12 ወራቶች በሰሜን አሜሪካ የሚገኙትን ቅርንጫፍ ማኅበራትና አባላት በመቀስቀስና

በማሳመን "በ19ኛው ጉባኤ ላይ የወንበር ላይ ምሁራንን ገፍትረን የኢተማሰአን የመሪነት ቦታ መያዝ አለብን" አሉ።

ይህ በእንዲህ እንዳለም "The National Question In Ethiopia" "የብሔሮች ጥያቄ በኢትዮጵያ" በሚል ርዕስ "ጥላሁን ታከለ" በሚል የብዕር ስም በብርሃነመስቀል ረዳ እና በኢያሱ አለማየሁ ተዘጋጅቶ የተሳከውን የአልጀሪያ ቡድን አንድ ጽሁፍ በኢተማሰአ የኒዮርክ ቀበሌ ቅርንጫፍ ማኀበር መጽሔት በነበረው "The New York chapter Newsletter" በቅጽ 1 ቁጥር 3 ላይ በድብቅ አሳትመው በመጋቢት ወር 1963 ዓ.ም በመላው ዓለም ለሚገኙ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኀበራትና አባላት እንዲሰራጭ አደረጉ። ጽሁፉ የብሔረሰቦች ጥያቄ ይባል እንጂ ከማንም ያልመነጨና የራሳቸውን ዓላማ በብሔረሰቦች አስመስለው ያችኑ የራስን ዕድል በራስ መወሰን የምትለውን ጥያቄ ነው ያስተጋቧት። የከፋው ነገር ደግሞ ጽሁፉ በኢተማሰአ ስም ታትሞ መውጣቱ ነበር።

በዚህ መልኩ አዞዎቹ የሰሜን አሜሪካውን የአዛዥነት ስልጣን የመጨበጥ መሠረትን ጣሉ። በኢተማሰአ ደንብ መሠረት የማኀበሩ ፕሬዝዳንት ምርጫ በየዓመቱ ይካሄድ ነበርና በ1963 ዓ.ም በ19ኛው የሎስአንጀለስ ጉባኤ ላይ በአንድነትና በትግል አጋርነት የተሰየሙት አባላት በተለሙት መሠረት ነበር አመራሮችን አውርደው በረቀቀ ዘዴያቸው የመሪነቱን ስልጣን የተረከቡት። የ12 ወር ወጥመዳቸው ሰራላቸው።

ራሳቸውንም "አዲሱ ኢተማሰአ" ብለው በመሰየማቸው አዲሱና አሮጌው ኢተማሰአ የሚል ነገር ተከተለ። በዚህ መሠረት ከ1963ቱ ጉባኤ በኋላ ዓለም አቀፉ የምሁራን የአመፅ እንቅስቃሴ የጀብሃና የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ጥያቄ በአንደኝነት፣ የአብዮትና የመደብ ጥያቄ በሁለተኝነት አጀንዳ ተይዘው ሊቀጥሉ ግድ ሆነ።

አዲሱና አሮጌው ኢተማሰአ ሁለት አንጃ ሆነው ቢናቆሩም፤ አዲሱ የበላይ ሆኖ መቀጠል ችሎ ነበርና "የፊላደልፊያውን አቋማችንን ለውጠናል" በማለት አዲስና አሮጌ የሚባል ነገር እንደሌለ አስመስለው፤ አዞዎቹ ከአልጀሪያው ቡድን ጋር ተመሳጥረው ያወጡትን ጽሁፍ "የመጨረሻ አቋማችን" በማለት ያንኑ የፖሊሲ አቋም በልዩ መጽሔታቸው አውጥተው በዓለም ላይ አሰራጩት።

የአውሮፓው ቡድን (ኢተማአ) ቀደም ሲልም የፊላደልፊያውን አቋም ተቃውሞ ነበርና አሁንም በኢተማሰአ ላይ የተደረገውን ኩዴታ በደስታ መቀበሉን ይፋ አደረገ። ሆኖም የአልጀሪያው ቡድንና አዲሱ ኢተማሰአ ኀብረት ፈጥረው የአውሮፓውን የመሪነት ስልጣን ለመያዝ የተለመደውን የአዞ ዘመቻ ጀመሩ። በ1964 ዓ.ም የኢተማአ 12ኛ ጉባዔ በፈረንሣይ አገር ሲካሄድ በአዞዎቹ ተዘጋጅቶ በቀረበ ጽሁፍ



በብርሃነመስቀል ረዳ የሚመራው የአልጀሪያ ቡድን የኢተማአ አመራሮችን ክፉኛ ነቀፋቸው።

አዞዎቹ በዚህም ሳይወሰኑ በዚሁ ጉባኤ ላይ የኢተማአ የራሱ አባላት ተወካዮች "የኢትዮጵያ ተማሪዎች የዓለም አቀፍ ማኀበር (ኢተዓአማ) ደንብና አሰራር የሚሻሻልበትን የውሣኔና የደንብ ረቂቅ በድርጅታዊ አሰራር አዘጋጅተን አቅርበናል" ብለው አቀረቡ። የቀረበውን ረቂቅ በእለቱ አዲሱ ኢተማሰአ እና የአልጀሪያው ቡድን ተወካዮች ተስማሙበት።

በዚህ መሠረት ዓለም አቀፉ የኢተዓአማ ጉባኤ በሚያዚያ ወር 1965 ዓ.ም በጀርመን በርሊን ከተማ መካሄድ ነበረበት። በበርሊኑ ጉባዔ ለኢተዓአማ ምስረታ የአባል ማኀበራት ውክልናና የምርጫ ስነ-ሥርዓት ጥያቄ ተነስቶ ለአንድ ሳምንት ተጨቃጨቁ።

ከዚህ ቀደም የነበሩት የኢትዮጵያ ተማሪዎች ዓለም አቀፍ የአመፅ እንቅስቃሴ ማኀበራት አእዩተማ፣ ኢተማሰአ፣ ኢተማአ ነበሩ። በ1965ቱ ጉባዔ ላይ ግን ከብዙ ውዝግብ በኋላ ሦስት አዳዲስ ማኀበራት እንዲኖሩ ተወሰነና 1ኛ የአልጀሪያው ቡድን፣ 2ኛ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኀበር ሌባኖን (ኢተማሌ) 3ኛ የኢትዮጵያ ሴቶች ዓለም አቀፍ ጥናት ክበብ (ኢሴዓአጥክ) እንዲሆኑ ተወሰነ።

በወቅቱ ኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩት የአእዩተማ ተወካዮች በነበረው የፖለቲካ ችግር ምክንያት በጉባዔው ላይ አልተገኙም። አሮጌው ኢተማሰአ ከአውሮፓውና ከአዲሶቹ ጋር የአላማ መለያየትና ፀብም ስለነበረ በጉባዔው አልተሳተፈም። በመሆኑም ከላይ የተጠቀሱት ሦስቱ ማኀበራት ለዓለም አቀፉ የአመፅ እንቅስቃሴ ቅርንጫፍ ማኀበራት መሆናቸው ፀና።

በበርሊኑ ጉባኤ የአልጀሪያ ቡድን ተወካይ ሆነው የቀረቡት ስምንቱ ሰደተኞች ሲሆኑ፤ በሌባኖን የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኀበር ተወካይ ተብለው የቀረቡት ደግሞ በመካከለኛው ምስራቅ በስደት የነበሩ 30 ተማሪዎች ናቸው።

ኢሴዓአጥክ ተብለው የተወከሉትና የአባልነትና የምርጫ መብት የተሰጣቸው የሴቶች ቡድንም አዲሡ ኢተማሰአ በአሜሪካን አገር ለማደራጀት ያሰበውን የሴቶች ማኀበር ለመመስረት ሲል የጣላቸው መሠረቶች ነበሩ።

በመሆኑም እነዚህ ግለሰቦች እንጂ በብዙሃኑ ተማሪ የተደራጁ ማኀበራት ተወካዮች አልነበሩም። ከኢተማሌ ውጪ ያሉት ሁለቱ ቡድኖች የጀብሃንና የኢትዮጵያ ብሔረሰቦችን ጥያቄ በሚመለከት አንድ አይነት አቋም የያዙ ናቸው። የአዲሱ ኢተማሰአ እና የኢተማአን የአመራር ቦታ የያዙት አዞዎቹ ኢተአዓማን በአዲስ መልክ አዋቅረው

ሁሉንም ስልጣን በአዞ የትግል ስልት ጠቀለሉት፡፡ የአጠቃላዩና የብዙሃኑ የኢትዮጵያ ተማሪ ተወካይ ሆነው በድርጅት ስም ብቻ አሉ፡፡

በመጨረሻ ለተሻሻለው ኢተዓአማ ምስረታ ጉባኤ ላይ ከተገኙ አምስት አባል ማኅበራትና ቡድኖች ማለትም አዲሱ ኢተማሰአ፣ ኢተማአ፣ የአልጀሪያ ቡድን፣ ኢተማሌ፣ እና ኢሴዓአጥክ ውስጥ በጉባኤው የምርጫ ሂደትና ውጤት የኢተማአንና የኢተማሌን ተወካዮች በምርጫ ስነስርዓት በማሸነፍ አዞዎቹ በእቅዳቸው መሠረት ራሳቸውን በኅብረት "የኢትዮጵያ ተማሪዎች ዓለም አቀፍ ፌዴሬሽን" (ኢተዓአፌ) ብለው ሰይመው በአዲስ መልክ መዋቀራቸውን ይፋ አደረጉ፡፡

በፌዴሬሽኑ ምርጫ የተሸነፉት የኢተማአ እና የኢተማሌ ተወካዮችም የጉባኤውን ውጤት ውድቅ አድርገው ወደየማኅበራቸው ተመለሱ፡፡

የኢትዮጵያ ተማሪዎች የአመፅ እንቅስቃሴ ሄዶ ሄዶ በአዞዎቹ ቁጥጥር ስር ሆኖ ኢተዓአፌ ላይ ተወስኖ ቀረ፡፡ በበርሊኑ ጉባኤ ያልተገኘው የአገር ውስጡ እአዩተማ ግን የፌዴሬሽኑ አካል ነበር፡፡ ከዚህ በኋላ አዲሱና አሮጌው ኢተማሰአ ጠላትነታቸው ቀጠለ፡፡ ስለዚህም በአብዮቱ ዋዜማ የኢትዮጵያ ተማሪዎች የፌዴሬሽን፣ የኢተማአ እና የአሮጌው ኢተማሰአ አመራርና አባላት እርስ በርሳቸው ጎራ ለይተው በፖለቲካና በስልጣን ትግል ሲፋለሙ እንደቆዩ ሁሉም ባልጠበቁት ሁኔታና መንገድ ያሳበጡት አብዮት ሲፈነዳ ለሁሉም አስገራሚ ነበር፡፡

የጃንሆይ መንግስት የተማሪዎችን አመፅ ለማስቆም የተለያዩ እርምጃዎችን ለመውሰድ ቢሞክርም ሙሉ ለሙሉ መገደብ አልተቻለም፡፡ ይልቁንም የመንግስትን ተፅዕኖ መቋቋም ያልቻሉት ወደ ሌላ አገር እየተሰደዱ በውጭ አገር ያሉትን ማኅበራት እየተቀላቀሉ የየማኅበራቱን የሰው ኃይል እያጎለበቱ አመፁን አጠናክረው ቀጠሉ እንጂ ከስመው አልቀሩም፡፡ መንግስት በ1962 ዓ.ም በዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ላይ የግድያ ተግባር ከፈፀመ በኋላ የአገር ውስጡን ማኅበር ከነመጽሔቱ ሊያከስም ቢችልም፤ ከመጠነኛ ፋታ ያለፈ ዘላቂ ውጤት ስላልተገኘ በ1964 ዓ.ም ንጉሠነገስቱ፣ አልጋወራሹ፣ ጠቅላይ ሚኒስቴሩ፣ የዘውድ አማካሪዎችና የካቢኔ ሚኒሰትሮች ተሰብስበው በተማሪዎች ጉዳይ ላይ የሚያተኩር አዲስ የስራ መመሪያ ቀርፀው በተግባር እንዲተረጎም አዘዙ፡፡

ለዚህም አንድ ከፍተኛ ኮሚቴ በአገር ግዛት ሚኒስትር ሰብሳቢነት ተቋቋመና የአገር መከላከያ ሚኒስትር፣ የትምህርት ሚኒስትር፣ የጦር ኃይሎች ኤታማዦር ሹም፣ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ፣ የምድር ጦር ዋና አዛዥ፣ የፖሊስ ሠራዊት ዋና አዛዥ፣ የክቡር ዘበኛ ዋና አዛዥ፣ የህዝብ ፀጥታ ጥበቃ ዋና ሹም፣ የልዩ ካቢኔ ሹምና የዩንቨርሲቲው ፕሬዝዳንት



የኮሚቴው ተሳታፊ ሆነው፤ "የተማሪዎችን ፀጥታ ለማስከበር" በሚል ተከታዩን ውሣኔ አሳለፉ፡፡

"የኢትዮጵያ ተማሪዎች በየጊዜው እየተነሱ ትምህርት በማቆም በህዝብ ንብረትና ህይወት ላይ አደጋ በማድረስ ትምህርት ቤቶችን በመስበር፣ የትምህርት እድገት እንዲጨናነል፣ የልጆች እድል እንዲሰናከል፣ ህዝብና የመንግስት ባለሥልጣን የሚዘልፍ ሕገወጥ ፖለቲካ አዘል የሆነ ልዩ ልዩ ጽሁፍ በመበተን ግርግርና ሽብር አድርገው ፀጥታ በመንሳታቸው ጉዳይ ግርማዊ ጃንሆይ፣ ልዑል አልጋወራሽ፣ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር፣ ክቡራን የዘውድ አማካሪዎችና የካቢኔ ሚኒስትሮች ባሉበት ስብሰባ ተደርጎ አጥፊ እንዲቀጣ፣ ትምህርት የሚፈልግ እንዲማር ፀጥታው በአስራ አራቱም ጠቅላይ ግዛቶች በሚገባ እንዲከበር ተብሎ በተወሰነው መሠረት ከዚህ በላይ በተዘረዘሩት ባለስልጣኖች ስለተማሪዎች ፀጥታ ማስከበር ቀደም ብለው ስለተቋቋሙ ጉባዔው ስብሰባ አድርጎ ከዚህ ቀጥሎ በተመለከተው መሠረት እንዲፈፀም ወስኗል፡፡

<u>ውሣኔ</u>

1. "ማናቸውም የዩኒቨርሲቲ፣ የ2ኛ ደረጃና የግዛት ትምህርት ቤት ተማሪዎች እንማራለን ካሉ ፀጥታ ነሾችን ለመከላከል ፖሊስ ትምህርት ቤት ውስጥ ገብቶ እንዲጠብቅ፣
2. ብጥብጥ ያስነሱ የተማሪ መሪዎች እንዲያዙና እንዲቀጡ፣ ቅጣትም ከልማት ጋር የተያያዘ አድካሚ ስራ እንዲሆን፣ እንማርም ብለው ከትምህርት ቤት የወጡት ተማሪዎች ዳግመኛ እንዳይገቡና እንደወጡ እንዲቀሩ፣
3. ተማሪዎች በየጊዜው የሚያደርጉትን ሕገወጥ ስራ ህዝብና ወላጆች እንዲያውቁት በወላጆች ኮሚቴ በኩል በቴሌቪዥን፣ በሬዲዮ፣ በጋዜጣ፣ በገዥዎች ጭምር ያለማቋረጥ እንደሚገባ እንዲገለፅ፣
4. ሕገወጥ የሆኑ የዩንቨርሲቲ፣ የኮሌጅና የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎች ማኅበር ጥፋታቸው በፖሊስና በፀጥታ በኩል ተጣርቶ ለዩኒቨርሲቲ ቦርድና ለትምህርት ሚኒስትር እያቀረቡ ማኅበሩ እንዲፈርስ ማድረግ፣
5. ትዕዛዙን አክብረን እንማራለን ያሉ ተማሪዎች ጥቂትም ቢሆኑ ጥበቃ እየተደረገላቸው እንዲማሩ፣
6. በዚህ ቃለ ጉባዔ በቁጥር 2 የተመለከቱና፣ ከትምህርት ቤት ከወጡ በኋላ ጥፋታቸውን እየቀጠሉ የሚማሩትን እንዳይማሩ የሚያውኩ ለጥፋት ስራ የሚዘጋጁ ተማሪዎች ሲገኙ በ28ኛው ዓመት በቁጥር 13 በአንቀጽ 3 በፊደል "ሀ" መጋቢት 27 ቀን 1961 ዓ.ም በወጣው ነጋሪት ጋዜጣና ይኸው ፀንቶ

የሚቆይበትን ጊዜ በማስረዘም በ31ኛው ዓመት ቁጥር 5 በ“ሀ” ፊደል ታህሳስ 19 ቀን 1964 ዓ.ም በወጣው አዋጅ መሠረት ፖሊስ እየያዘ አስፈርዶ ቅጣታቸውን እንዲቀበሉ ያደርጋል፡፡

7. አጥፊ ተማሪዎችን ፖሊስ እየሰበሰበ፣ ብዛታቸው ከፍ ያለ እንደሆነ በፀጥታ ማስከበሪያ አዋጅ መሠረት ለአገር ግዛት አቅርቦና አስወስኖ ለጦር ሠራዊትና ለክብር ዘበኛ ያከፋፍላል፡፡
8. ተማሪዎች በጥፋታቸው ሲቀጡ ለዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የዩኒቨርሲቲ አስተዳደር ለሌሎችም ተማሪዎች የትምህርት ሚኒስትር ለምግብና ለሌላ ወጪ የሚሰጠውን ገንዘብ ተማሪዎች ለተሰሩበት ክፍል ይከፍላል፡፡ ከዩኒቨርሲቲና ከትምህርት ሚኒስትር የሚገኘው ተመላሽ ባይበቃ በተለየ ቀርቦ እንዲፈቀድ ይደረጋል፡፡
9. እነዚህ ከዚህ በላይ የተመለከቱት ውሣኔዎች በአስራአራቱም ጠቅላይ ግዛቶች፣ አውራጃዎችና ወረዳዎች እንዲሰሩባቸው ስለተወሰነ ክቡራን ጠቅላይ ገዥዎችና የጠቅላይ ግዛት እንደራሴዎች፣ የጠቅላይ ግዛት ፖሊስና ዋና አዛዦች፣ የክብር ዘበኛና የብሔራዊ ጦር አዛዦች፣ የጠቅላይ ግዛቱ የትምህርት ስራ መሪ፣ የአውራጃና የወረዳ ትምህርት ቤቶች ስራ መሪዎች በአገረገዥዎች ኃላፊነት እየተሰበሰቡ በኅብረት ጥናን በትእዛዝ እያወጡ ያፈፃፀሙን ውጤት በየጊዜው እንዲሰጡ ማድረግ ነው፡፡

የስብሳቢውና
የአባሎች ፊርማ
ያገር ግዛት
ሚኒስትር
ማሕተም”

አንድ የህዝብ አመፅ የተነሳበት መንግስት እንዲህ አይነት ውሣኔ ከማሳለፍ የተሻለ ምርጫ ይኖረዋል ብሎ ማሰብ ቢከብድም፤ የወረዳና የአውራጃ ገዥዎች እንዲሁም ውሣኔውን ለማስፈፀም የተፈቀደላቸው ሹሞች ግን ከዚህ ጠንካራ ውሣኔ ያለፈ ተጨማሪ በደል በየግዛቱ መፈፀም ጀመሩ፡፡ የአመፁ ተባባሪ ያልሆኑ የተማሪ ወላጆችን በሌላ ቂም በቀል “ተባባሪ ናቸው፣ አነሳስተዋል...” እያሉ በመወንጀል ማሰር፣ ማንገላታት፣ መዝረፍ፣ መግደል ሆነ ስራቸው፡፡

በውሣኔው ደስተኛ ያልነበሩ ተማሪዎች መኖራቸው ሳያንስ፤ ይህ መሰሉ ተደራቢ ሕገወጥ የሹማምንቱ ዝርፊያ በመጨመሩም የአውራጃና የወረዳ የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች እና መምህራን የየግዛቱን



ሹማምንት ሕገወጥ “የአመፅ ቅጣት”ን ተቃውመው ወደ አደባባይ መውጣት ጀመሩ፡፡

የከተማ ውስጡ ተመሳሳይ እርምጃም አመፁን የበለጠ የሚያጋግል እየሆነ ሄደ፡፡ አጠቃላዩ የአመፅ እንቅስቃሴ ሁኔታ የሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍል ትኩረት በመሳቡም ሁሉም የየራሱን ብሶት ይዞ ወደ አደባባይ እንዲወጣ የሚጋብዝ ነበር፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለም የኢትዮጵያ መንግስት ከዓለም ባንክ በተሰጠው የገንዘብ እርዳታ 30 የውጭ አገር፣ 51 የአገር ውስጥ የትምህርት ባለሙያዎችና 69 የመንግስት ሠራተኞች በጋራ ሆነው ብዙሃኑ መምህራን ባላወቀው መንገድ በሚስጥር አጥንተው ያቀረቡትና በ1967 ዓ.ም ሊተገበር የታሰበው አዲስ የትምህርት ፖሊሲ በመምህራን ማኅበር ዘንድ እንደተሰማ ተጨማሪ ከፍተኛ ቁጣ አስነሳ፡፡
በ150 ባለሙያዎች ለሁለት ዓመታት ተጠንቶ የቀረበው አዲስ የትምህርት ፖሊሲ “ሴክተር ሪቪው” የተሰኘው ሲሆን፤ ዓላማውም ከ1934-1965 ዓ.ም ድረስ የነበረው የኢትዮጵያ የትምህርት ፖሊሲ ተደራሽነቱ አጥጋቢ አልነበረምና፤ ለህዝቡ የሙያ ትምህርት በዝቅተኛ ደረጃ በስፋትና በፍጥነት ማዳረስ ያስፈልጋል” የሚል ነው፡፡

ይህ ዓላማ ሊተገበር መሆኑን ዘግይተው የሰሙት መምህራን “ይህ አይነቱ ትምህርት አውሮፓውያን ለቅኝ ተገዥ አገራት ህዝቦች ያስተምሩት የነበረው ዝቅተኛ የሙያ ትምህርት ስለሆነ አያስፈልግም” በማለት የመንግስትን አቋም የሚያጣጥል የቅስቀሳ ዘመቻ ከፈቱ፡፡ የዚህ ዘመቻ መሪ የኢትዮጵያ መምህራን ማኅበር /ኢመማ/ ሆነና፤ አዲሱን የትምህርት ስርዓት በመቃወምና የደመወዝ ጭማሪ ጥያቄን በጥምረት በማንሳት አገዛዙን ተፋታተኑት፡፡ የ1ኛና የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎችም ከኢመማ ጎን ተሰለፉ፡፡

በ1941 ዓ.ም የተመሠረተው የኢትዮጵያ “መምህራን ኅብረት” የመጀመሪያው የሙያ ማኅበር የነበረና በ1958 ዓ.ም በመንግስት ዘንድ በይፋ ታውቆ የኢትዮጵያ መምህራን ማኅበር /ኢመማ/ የሚል ስያሜ ይዞ የቀጠለ ማኅበር ነው፡፡

ኢመማ በብሔራዊ ደረጃ ከተደራጀ በኋላም እስከ 1964 ዓ.ም ድረስ የአባላቱን ቁጥር እና የገንዘብ አቅሙን እያዳበረ ሄዶ በ14ቱም ጠቅላይ ግዛቶች ቅርንጫፍ ማኅበራት ያሉት ግዙፍ ድርጅት ሆኖ ነበር፡፡ የመምህራን የመረዳጃ ድርጅት እስከመመስረትም ደርሷል፡፡ የአገሪቱን የፖለቲካ ጉዳይም በየዓመቱ በሚያካሂዱት ጉባዔ ላይ እያነሱ ሲወያዩበት ቆይተዋል፡፡

ኢመማ በመስከረም ወር 1966 ዓ.ም በአርባ ምንጭ ከተማ ባካሄደው በ8ኛው ዓመታዊ መደበኛ ጉባዔ ላይ የ“ሴክተር ሪቪው”ን ጉዳይ

በመቃወምና የደመወዝ ጭማሪን በማመላከት ተወያይተው ያሳለፉት ውሣኔ፤

"1. የእያንዳንዱ መምህር ደመወዝ አስር በመቶ እንዲያድግ፣ 2. መምህራን ከስራቸው በጡረታ እስኪገለሉ ድረስ በደሞዛቸው እድገት የጣራ ወሰን እንዳይደረግ፣ 3. በደሞዝ ጭማሪ ጉዳይ ለቀረበው ጥያቄ መንግስት እስከ ህዳር 30 ቀን 1966 ዓ.ም ድረስ ተገቢውን የስምምነት መልስ እንዲሰጥ" የሚል ጠንካራ ጥያቄ ሲያቀርቡና ሲያሳስቡ፣ የትምህርት ስርዓቱን በሚመለከት ደግሞ፤

"1. የስርዓተ ትምህርቱ "ብሔራዊ ፍልስፍናው" በቅድሚያ ሳይገለፅ፣ 2. የስርዓተ ትምህርቱ ትምህርታዊ ጽሁፎችና መሣሪያዎች በደንብ ሳይዘጋጁ፣ 3. የግል ትምህርት ቤቶች በአዲሱ ስርዓተ ትምህርት መሠረት የሚሰሩ መሆናቸው በቅድሚያ ሳይታወቅ፣ 4. በአዲሱ ስርዓተ ትምህርት የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት እንዲከፈልበት መጠየቁ የማይገባ በመሆኑ እንዲሰረዝ፣ 5. በአዲሱ ስርዓተ ትምህርት ለመምህራኑ የስራ ዋጋ የተመደበው 153 ብር ካለው ሁኔታ ጋር የማይመጣጠን በመሆኑ "እስኪለወጥ ድረስ" የስርዓተ ትምህርቱን በሥራ ላይ መዋል በጥብቅ እንቃወማለን" በማለት ኢመማ አስጠነቀቀ፡፡

መንግስት የደሞዝ ጥያቄውን በሚመለከት በህዳር 30 ቀን 1966 ዓ.ም የሰጠውን መልስ የኢመማ አመራርና አባላት "ጥያቄያችን በከፊል እንጂ ሙሉ ለሙሉ ያልመለሰ ሆኖ ስላገኘነው ውድቅ አድርገናል" አሉ፡፡ ሲቀጥሉም፤ "ከታህሳስ እስከ የካቲት ድረስ ባሉት ሁለት ወራት ውስጥ የመምህራኑ የተስተካከለ የደሞዝ ጭማሪ ባይደረግ በፋሽዝም ሰማዕታት የዋዜማ በዓል ላይ የካቲት 11 ቀን 1966 ዓ.ም የአገሪቱ መምህራን በአገር አቀፍ ደረጃ ስራ እንደሚያቆሙ" ወስነው ተለያዩ፡፡ (የበዓሉ ዋዜማ ያሉት በየካቲት 12 ቀን በኢጣሊያ የተጨፈጨፉትን ሰማዕታት የመታሰቢያ እለት ማለታቸው ነው)

ኢመማ ታህሳስ 12 ቀን ያየነውን ውሣኔ ካሳለፈ በኋላ የትምህርት ሚኒስትር ጥያቄያቸውን ሳይመልስ አንድ ወር አለፈ፡፡

በእርግጥም አንዲት በሙስና ስትበዘበዝ የኖረችና እርቃኗን የቀረች አገር ይህን መሰሉን ጥያቄ ለመመለስ የሚያስችል አቅም አልነበራትም፡፡

አንዱ እያምጣው ነውና በዚሁ ወቅት ደግሞ በወሎ የተከሰተውና ሊደበቅ የታሰበው ረሃብ በህዝቡ ዘንድ ታውቆ ሌላውን ኅብረተሰብ አስቆጣ፡፡ በዚሁ በታህሳስ ወርም የነዳጅ ዘይት ዋጋ በዓለም አቀፍ ደረጃ በመጨመሩ የንግድና ኢንደስትሪ ሚኒስትር ታህሳስ 30 ቀን 1966 ዓ.ም የ50 በመቶ ጭማሪ መደረጉን በዜና አውታሮች ሲያስታውቅ ህዝቡ እሪታው እየጎላ ሄደ፡፡ በጥቅሉ የአገሪቱ የኢኮኖሚ ሁኔታ ከነበረው



የፖለቲካ ችግር ጋር ተዳምሮ ከቁጥጥር ውጭ ሆነ፡፡ ይህ የነዳጅ ጉዳይ ዓረቦችና እስራኤል ጦርነት በማድረጋቸውና የስዊዝ ቦይ እንዲዘጋ በመደረጉ በድንገት 45 ሣንቲም የነበረው አንድ ሌትር ነዳጅ 65 ሣንቲም እንደገባ በመገለፁ ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍል ስለሚነካ፣ የሸቀጦች ዋጋ ጋርም ስለሚነካካ የእያንዳንዱን ቤት ለከፋ ችግር ማጋለጡ ግልፅ ነበር፡፡ ወዲያውም "የምንበላው እህልና የምንጠጣው ውሃ ከአፈር ጋር እየተቀላቀለ ተቸግረናል" በማለት ጥር 4 ቀን የአራተኛው ብርጌድ ወታደሮች በነገሌ ቦረና ያሉት በኑሮ ችግር ምክንያት ተማርረው በማመፅ የብርጌድ አዛዡን ጨምሮ ሁሉንም አለቆቻቸውን አሰሩ የሚል ወሬ ተሰማ፡፡ ጉዳዩን ለማጣራት ከአዲስ አበባ የተላኩት የምድር ጦር አዛዥ ጄኔራል ድረሴ ዱባለ ወደ ቦታው ሲሄድ እሳቸውንም አስረው የተበላሸውን እህል ውሃ እንዲበሉ አደረጓቸው፡፡ የሄደው ሁሉ እየታሰረ መቅረቱን ያዩት ጃንሆይ በመጨረሻ የአየር ኃይሉን አዛዥ ብ/ጄ/ል አበራን ላኩ፡፡ጄ/ሉ ጥያቄያቸው ሁሉ እንደሚመለስ የተላከውን መልዕክት ለጦሩ አንብበው ታጋቾቹን አስፈትተው ተመለሱ፡፡ የነገሌው ጦር ይህን ጥያቄ ዱጋግሞ አመልክቶ የነበረ ቢሆንም፤ ጥያቄው ወደ መሀል አገር ሳይደርስ በአዛዦች ታፍኖ ቆይቶ ነበር፡፡ በእነዚህ ችግሮች ላይ ነው እንግዲህ የአዲስ አበባ ተማሪዎችና መምህራን ልዩ ልዩ ወረቀቶች አትመው እያሰራጩ ህዝቡ በአገዛዙ ላይ እንዲነሳ መቀስቀሳቸውን የቀጠሉት፡፡

የቅስቀሳ ጽሁፎች በኢመማ ጽ/ቤት እየታተሙ በየጎዳናው ለህዝቡ መድረሳቸውን ያስተዋሉት የፀጥታ ጠባቂዎች በፖሊስ ሠራዊት አዛዡ አቅራቢነት የኢመማ ፕሬዝዳንት ወደ ጃንሆይ ቀርበው ጉዳያቸውን በቀጥታ እንዲያመለክቱ ተደረገ፡፡

ለፀረ-መንግስት እንቅስቃሴው ዋና ማዕከል የሆነው ኢመማ ነው የሚባለው ሐሰት እንደሆነና፤ የኢመማ ጥያቄ የደመወዝና የአዲሱን ስርዓተ ትምህርት የሚመለከት ብቻ መሆኑን ፕሬዝዳንቱ ለጃንሆይ ገለፁ፡፡

ጃንሆይም ከሹማምንቱ የሰሙትና የኢመማ ፕሬዝዳንት ያስረዳው የተለያየ ሲሆንባቸው "የተባለውን ችግር በሚመለከት አስፈላጊውን ማስረጃ ይዘህ በማግስቱ ጥር 28 ቀን ከጠዋቱ 4 ሰዓት ወደ ታላቁ ቤተ-መንግስት እንድትቀርብ" አሉት ባረጀው አንደበታቸው፡፡

በማግስቱ ከጃንሆይ ጋር ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ የአገር ግዛትና የትምህርት ሚኒስትሮች፣ የዘውድ ምክር ቤት ፕሬዝዳንት፣ የእልፍኝ ዋና አስከልካይ፣ የክብር ዘበኛና የፖሊስ ዋና አዛዥ፣ የህዝብ ፀጥታ ጥበቃ ሹም በተገኙበት የኢመማ ተወካዮች ችግራቸውንና ጥያቄያቸውን አስረዱ፡፡ በእለቱ የትምህርት ሚኒስትር "የኢመማ ጥያቄ መሠረተ ቢስ" መሆኑን ሲገልፅ፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ደግሞ "የየካቲት 11ዱ ስራ የማቆም አድማ

ካልቀረ ተጠያቂዎቹ እናንተ የኢመማ አመራሮች ናችሁ" ብሎ ዛተ። የፖሊስ ሠራዊትና የክብር ዘበኛ አዛዦች ግን "ችግሩ ወደ ኅብረተሰቡም ተዛምቷልና ጥያቄአቸው አፋጣኝ መፍትሄ ማግኘት አለበት" በማለት የጠቅላይ ሚኒስትሩንና የትምህርት ሚኒስትሩን አካሄድ ተቃወሙ። ኢመማዎች በበኩላቸው "የኢመማ አመራር ኮሚቴ ብቻውን አቋሙን ለመለወጥ የሚያስችል ስልጣን የለውም" ብለው ገለፁ። ጃንሆይ "መምህራኑ ስራ እንዳያቆሙ የሚያደርግ ሌላ ውሣኔ እሳልፍልንና በአጭር ጊዜ ውስጥ መፍትሄ እንፈልጋለን" አሉና ስብሰባው ተበተነ።

ከሁለት ቀናት በኋላ የኢመማ የየግዛቱ ቅርንጫፍ ማኅበራት ተወካዮች ወደ አዲስ አበባ መጡ። በትምህርት ሚኒስትር እና በኢመማ መካከል ጥብቅ ክርክር የካቲት 2 ቀን ተካሄደ ለውጥ የለም። በመጨረሻ የኢመማ አመራርና የክፍለ አገር ተወካዮች በጽሁፍና በቃል ያንኑ ጥያቄያቸውን በኢዮቤልዩ ቤተ-መንግስት ለጃንሆይ በይበልጥ አስረዱ።

ጃንሆይም "ይህ በንባብ ያቀረባችሁት ነገር እውነት ከሆነማ ከሚኒስትሮች ጋር በአንድነት ምክሩበትና ውጤቱን እንድናውቀው ይሁን" የሚል ትዕዛዝ ሰጥተው ሽማግሌው ንጉሠነገስት በማግስቱ ለአንድ ሳምንት ጉብኝት ወደ ኤርትራ ሄዱ። በንጉሠነገስቱ ትዕዛዝ መሠረት ከየካቲት 4 ቀን ጀምሮ ለተከታታይ ሦስት ቀናት በያሬድ የሙዚቃ ትምህርት ቤት የኢመማ ተወካዮችና የትምህርት ሚንስትር ከመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር ኮሚሽን ባለሥልጣኖች ጋር ሆነው ያካሄዱት ስብሰባ ሁሉ ውጤት አልባ ሆነ።

የባለሥልጣናቱ ትኩረት በጥያቄዎችና በሚቀርቡ የመፍትሄ ሀሳቦች ላይ ሳይሆን የየካቲት 11ን አድማ በተፅዕኖ ማስቀረቱ ላይ ያተኮረ ነበር። የኢመማ ተወካዮች የባለስልጣናቱን ተፅዕኖ ተቋቁመው ሲሟገቱ ሙግቱን ይከታተሉ የነበሩ የአዲስ አበባ ተማሪዎች በሚበትኑት ጽሁፍ የኢመማ አካሄድ ትክክል መሆኑን እየገለፁ ህዝቡን ይቀሰቅሱ ነበር። ከዚህም ባለፈ የመንግስትን የተደበቁ ገመናዎች ማጋለጥ ተጨማሪ ስራ አድርገው ያዙት።

የካቲት 5 ቀን የደብረዘይት የአየር ኃይል አባሎች በእመፅ አዛዥ መኮንኖችን በቁጥጥር ስር አውለው የራሳቸውን የኑሮ ችግር ሲገልፁ ለመንግስት ሌላ ተፅዕኖ ሲሆን፤ ለኢመማ ግን ጥሩ እድል ሆኖ ተገኘ።

የካቲት 7 ቀን የአዲስ አበባ ተማሪዎች ከኢመማ ጎን በመሰለፍ በጎዳናው ላይ በሚዘዋወሩ የመንግስት መኪኖች ላይ የድንጋይ ናዳ አወረዱ። ኢመማ የበለጠ የልብ ልብ ተሰማው። በዚህ እለት በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ የትምህርት ሚኒስትር ተከታዩን ጽሁፍ አትሞ አወጣ፤

"አዲሱን የትምህርት ስርዓት አጠቃላይ መንፈስ በሚገባ ያልተገነዘቡ አንዳንድ ሰዎች ይኖሩ ይሆናል፤ አያስገርምም። ማንኛውም አዲስ ሀሳብ ለጊዜው ግራ የሚያጋባ መሆኑ የታወቀ ነው። አዲሱ የትምህርት አጠቃላይ ጥናት መንፈስና አላማ ዛሬ ያልገባቸው አንዳንድ ሰዎች ቢኖሩ ነገ ከፀፀት ላይ ይወድቁ ይሆናል። ዋናው ቁም ነገር ግን ካለማወቅ ለኢትዮጵያ የትምህርት እርምጃ እንቅፋት ከመሆን መቆጠብ ነው። በታሪክ ምዕራፍ ላይ ጥቁር ነጥብ ከጣሉ በኋላ መፀፀት ውጤት አያስገኝም። ትምህርትን ለማዳረስ የወጣውን እጅግ የሚያጓጓ እቅድ ስራ ላይ ለማዋል እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ከፍተኛ መስዋዕት እንዲያደርግ የሚጠበቅበት ጊዜ ነው።" (ረቡዕ የካቲት 7 ቀን 1966 ዓ.ም አዲስ ዘመን)

ሐሙስ የካቲት 8 ቀን የትምህርት ሚኒስትር ለኢመማ አመራር ኮሚቴ ' "የመምህራን ደመወዝና የስርዓተ ትምህርት ጥያቄዎችን በሚመለከት የሚወሰደው እርምጃ ከላይ ውሣኔ ሲሰጥበት በኢመማ በኩል ለመምህራን ይገለፃል" የሚል-ደብዳቤ ልኮ ጉዳዩን ዘጋ።

ኢመማ የትምህርት ሚኒስትሩን ውሣኔ በመቃወም ለጠቅላይ ሚኒስትሩ አስረዳ። ጠቅላይ ሚኒስትሩም "ጉዳዩ በትምህርት ሚኒስትር በኩል መልስ ካላገኘ ለግርማዊ ጃንሆይ ቀርቦ ተጠንቶ አንድ ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ውሣኔ ይሰጥበታል። ይህንንም ኢመማ ለሁሉም መምህራን ይግለፅ" ሲል የስርዓተ ትምህርቱን ጉዳይ ደግሞ "የትምህርት አጠቃላይ ጥናቱ እንደ ፕላን የሚቆጠር ስለሆነ በየጊዜው አስፈላጊ ማሻሻያ እየተደረገለት በስራ ላይ ይውላል እንጂ አይቀርም..." የሚል መልስ ሰጥቶ ነበር።

ከዚያም የኢመማ ተወካዮች በጥበቃ ኃይሎች ተከበው 24 ሰዓት የፈጀ ስብሰባ አድርገው ተገደው ያሳለፉት ውሣኔ "የስራ ማቆም አድማው ቀርቷል" የሚል የነበረ ይሁን እንጂ፤ ጎን ለጎን ግን "ውሣኔው እንዳልቀረና ተገደን የተናገርነው ነው" የሚል መልዕክት በማስተላለፍና በኮድ መልዕክቶች በመጠቀም የየካቲት 11ዱን ቀጠሮ እውን አደረጉት። የመንግስት ባለሥልጣኖች ውሣኔውን ያስቀሩት መስሏቸው ተረጋግተው ነበር።

ዕለተ ማክሰኞ የካቲት 11 ቀን የኢመማ መላው አባላት የስራ ማቆም አድማውን ተገበሩት። በዚያው እለት የአዲስ አበባ ታክሲ ሾፌሮች አገልግሎታቸውን አቆሙ። ከዚህች እለት ጀምሮ ምሁሩ፣ ነጋዴው፣ ሹፌሩ፣ ወታደሩ፣ ወዛደሩ ... ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል ማለት ይቻላል ለተከታታይ ቀናት አገዛዙን እየተቃወመ ቀጠለ።

ጃንሆይ "የደሃ ልጆችን ያገላልና ይህ የትምህርት ፖሊሲ (ሴክተር ሪቪው) መታጠፍ አለበት" የሚለውን የኢመማን ጥያቄ አመፁን ለመግታት ሲሉ አጠፉት። ቀጥለው የነዳጅ ዋጋ ጭማሪውን እንዲነሳ አስደረጉት። የደመወዝ ጭማሪውን እንደሚያጠኑት ቃል ገቡ። ግን ለውጥ የለም። የነገሌውን ጦር ጥያቄ አዎንታዊ ምላሽ ሰጡ፤ ለውጥ

የለም፡፡ ይልቁንም የንጉሡ "እሽ እሽ" ባይነት ዓላማው አመፁን ለማርገብ የተወሰደ እርምጃ አድርጎ ከማሰብ ይልቅ፤ እንደ ፍርሃት እየተቆጠረ ቀጠለና፣ ቀደም ሲል ከተማሪዎችና ከጅብሃ በስተቀር አንድም ፖለቲካዊ ጥያቄ ያላነሱትና ጥያቄያቸው ማኅበራዊ ጉዳዮችን ማለትም የኑሮ ችግር እንዲቃለል፣ ደመወዝ እንዲጨመር፣ አስፈላጊ ቁሳቁሶች እንዲሟሉ ይጠይቁ የነበሩት ሁሉ በተለይ ጦር ሠራዊቱ ቀስ በቀስ ጥያቄያቸውን ፖለቲካዊ ወደማድረግ አመሩ፡፡

የካቲት 18 ቀን 1966 ዓ.ም በኤርትራ አስመራ የነበረው የሁለተኛው ክፍለ ጦር አባላት የነገሌ ቦረናው ጦር በቀደደው ፈር በመጓዝ ጠንከር ያለ ጥያቄ ይዘው ተነሱ፡፡ ሁሉም ባለማዕረጎች ማዕረጋቸውን አውልቀው (በጦር ሠራዊት ሕግ መሠረት ጦሩ ሲያምፅ ከተገኘ ከተራ ወታደሩ ይልቅ መሪ መኮንኖች ከባድ ቅጣት ስለሚወሰንባቸው) ሁሉም ተራ መስለው ታጥቀው ወደ ከተማ በመውጣት የአስመራን የአየር ጣቢያ፣ የሬዲዮ ማሰራጫ ጣቢያና ሌሎች ወሣኝ ቦታዎችን በቁጥጥር ስር በማድረግ የከፍተኛ መኮንኖችንና የሲቪል ባለሥልጣናትን እንቅስቃሴ በመግታት ጥያቄአቸውን በሬዲዮ ለንጉሡ አቀረቡ፡፡ ይህም እንደነገሌው የሠራዊቱን ብሶቶችና የኑሮ ችግሮችን የሚመለከት ጥያቄ ነበር፡፡

የጃንሆይ መንግስት አሁንም ለጦሩ ጥያቄ ፈጣን አዎንታዊ ምላሽ በእለቱ ሰጠ፡፡ ምክንያቱም በኤርትራ ያለው ጦር አመፀ ማለት ወይም የማይሆን እርምጃ ተወሰደበት ማለት የአካባቢውን የጅብሃ የትጥቅ ትግል አጎልብቶ ኢትዮጵያን አደጋ ላይ መጣል ማለት ነበርና ጃንሆይ አላንገራገሩም፡፡ ያመፀው ጦር ግን መሽቶ እንደነጋ የካቲት 19 ቀን የሚከተለውን አጀንዳ ለመንግስት በሬዲዮ አስተላለፈ፤ "1. የፖለቲካ ፓርቲ የማቋቋም ነፃነት፣ 2. የጠቅላይ ግዛት ገዥዎች በዴሞክራሲያዊ መንገድ በአካባቢው ነዋሪ ህዝብ እንዲመረጡ፣ 3. የተባባሰውን የዋጋ ግሽበት የሚቆጣጠር ደንብ እንዲወጣ፣ 4. የመሬት ይዞታ ለህዝብ በሚጠቅም መልኩ ተሻሽሎ እንዲወጣ፣ 5. ለመለዮ ለባሹ፣ ለመንግስትና ለፋብሪካ ሠራተኞች ወቅታዊውን የኑሮ ውድነት መቋቋም የሚያስችል የደመወዝ ጭማሪ እንዲደረግ፣ 6. የህዝብ ገንዘብ ያባከኑ ባለሥልጣናት በቁጥጥር ስር ውለው ለፍርድ እንዲቀርቡ፣ 7. እነዚህ ጥያቄዎች ተገቢ መልስ እንዲያገኙ ተከታትሎ የሚያስፈፅም ከመንግስትና ከጦሩ የተውጣጡ አባላት የሚገኙበት የጋራ ኮሚቴ እንዲቋቋም..." የሚሉ የንጉሣዊ አገዛዙን የሚፈታተኑ ጥያቄዎች ቀረቡ፡፡

ይህ በሆነ በሁለተኛው ቀን የወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስትር አክሊሉ ሐብተወልድ በድንገት የስራ መልቀቂያ ደብዳቤ ለጃንሆይ አቀረቡ፡፡ ጃንሆይም የአክሊሉን ጥያቄ ተቀብለው ካቢኔውን አሰናበቱ፡፡



የሁለተኛ ክፍለ ጦር አባላት በመጀመሪያው ቀን 23 ያህል ጥያቄዎችን በሬዲዮ ለንጉሡ ሲገልፁ አንድም ፖለቲካዊ ጥያቄ አላቀረቡም ነበር፡፡ ከደመወዝ ጀምሮ እስከጡረታ ... ወዘተ የሚያትቱ ብቻ ነበር፡፡ ይህንንም "እሽ" ተብለው ሳለ በፍጥነት አገዛዙን የሚፈትን ከባድ ፖለቲካዊ ጥያቄ በማግስቱ ያስከተሉት ግን በጦሩ ብሶት ተከልለው የራሳቸውን ዙፋን የመንጠቅ (የመተካት) እቅድ የነበራቸው የንጉሡ የበታች ሹማምንት የሆኑ መሣፍንት ስለገፋፏቸው ነበር፡፡

በአንድ በኩል የግራ ክንፎች ሹማምንት ስር ነቀል ለውጥ የሚፈልጉ፣ በሌላ በኩል የቀኝ ክንፎች ጃንሆይን ከስልጣን አውርደው ሌላ ንጉሥ ለመተካት የሚያስቡት ናቸው፡፡

የጦሩ አመፅ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ከፈለጉት መሣፍንት ውስጥ ዋናው አስተባባሪ ቀደም ሲል የኤርትራ ጠቅላይ ግዛት እንደራሴ የነበሩት ልዑል ራስ አስራት ካሣ ነበሩ፡፡ (ምስክርነት 2001 ዓ.ም)

የጦሩን ቅፅበታዊ የጥያቄ ለውጥና የጥያቄዎችን ይዘትና ጥልቀት የመረመሩ ምሁራንም የመሳፍንቱ ግፊት እንደነበረበት ያምናሉ፡፡ ይህ የውስጥ ለውስጥ የመሳፍንቱ የፖለቲካ ደባም ጠቅላይ ሚኒስትር አክሊሉ ሐብተወልድ ስልጣን ሲለቁ በምትካቸው ልጅ እንዳልካቸው መኮንን ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው እንዲሾሙና አዲሱ ካቢኔ ተቋቁሞ፣ አዲስ ሹም ሽር ተደርጎ 19 አዳዲስ ሚኒስትሮች በየካቲት ማለቂያ ከጃንሆይ ፊት ቀርበው ቃለ-መሀላ ፈጽመው ስራቸውን እንዲጀምሩ አድርጓል፡፡

ምንም እንኳን ጃንሆይ ከዚህ ሹም ሽር በፊት ጄኔራል አብይ አበበን አዲስ ካቢኔ እንዲመሰርት አዘውት የነበረ ቢሆንም፤ የጄኔራል አቢይ ካቢኔ ገና ሳይመሠረት ተቃውሞ ስለገጠመው እንዲቀር ሆኗል፡፡

በመሆኑም የልጅ እንዳልካቸው መኮንን ጠቅላይ ሚኒስትር ሆኖ መሾም በመሳፍንቱና በመኳንንቱ መካከል የነበረው የስልጣን ትግል መሳፍንቱ አሸንፈው በድል የተወጡበት ሆኖ ታዬ፡፡ የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር አክሊሉ ሐብተወልድ ከመሳፍንት ወገን ያልሆኑና ከታችኛው መደብ የተገኙ ነበሩና፡፡

ሆኖም ልጅ እንዳልካቸው ከልዑል ራስ አስራተ ካሣ ጋር ሽርክ ነው የሚለው ጉዳይ መሣፍንቱን ረፍት ሊሰጣቸው አልቻለም፡፡ በሌላ በኩልም የእነ ልዑል አስራተ ካሣ ተቀናቃኝ ሆነው በጦሩ ብሶት የራሳቸውን የስልጣን ጥም ለማርካት የሚሻኮቱት በአዲሱ ካቢኔ የግቢ ሚኒስትር ሆነው የተሾሙት የጃንሆይ የረጅም ጊዜ ታማኝ አገልጋይ ደጃዝማች ከበደ ተሠማ ነበሩ፡፡

ከመኳንንት ወገን ደጃዝማች ከበደ፣ ከመሳፍንት ወገን ልዑል ራስ አስራተ ካሣ ሆነው የስልጣን ገመድ ሲጓተቱ፣ ፍፁም እምነት የጣሉባቸውንና ለረጅም ዓመታት ያገለገሏቸውን፣ ያልበደሏቸውን

የጃንሆይን ጉዳይ እርግፍ አድርገው ትተዋል፡፡ በዚህ መካከል የህዝቡ አመፅ ጋብ ሊል ቀርቶ ይብሱኑ "ጉልቻ ቢቀያየር ወጥ አያጣፍጥም" እየተባለ ተባብሶ ቀጥሏል፡፡ ድምፁ ተሰምቶ የማያውቀው የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበር ኮንፌዴሬሽን ውጤታማ የተባለውን ለተከታታይ አራት ቀናት የቆየ አጠቃላይ የስራ ማቆም አድማ አደረገ፡፡ ጥያቄያቸውም "የሠራተኛና አሠሪ ሕግ እንዲደነገግና በነፃነት የመደራጀት መብት እንዲከበር፤ እንዲሁም ደሞዝ እንዲጨመር" የሚል ነበር፡፡

አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር "ፋታ ይሰጠኝ ሁሉንም ነገር አስተካክላለሁ" ቢሉም ሰሚ አጡ፤ ተዋከቡ፡፡ አዲሱ ካቢኔ ግን ተገቢ ስራዎችን በፍጥነት እያከናወነ ነበር፡፡ ለምሳሌ ካቢኔው ስራ በጀመረ በቀናት ውስጥ በጃንሆይ ትዕዛዝ ሕገመንግስቱን ለማሻሻል እቅድ ነደፈ፣ በመጋቢት ወር መጀመሪያ የመንግስት ሹማምንትን አለአግባብ መበልፀግ አጣርቶ ለፍርድ የሚያቀርብ የምርመራ ኮሚሽን ተቋቋመ፣ ቀጥሎ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ችግሮችን የሚያብራራና ወደመፍትሄው የሚያደርሰውን መንገድ የሚያሳየውን የእንግሊዝ አገር ፖሊሲን የተከተለውን ኋይት ፔፐር (ነጭ ሠነድ) የተሰኘውን መመሪያ ይፋ አደረገ፡፡ ነገር ግን "ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ" ተብሎ ተጮኸ፡፡ እነዚያን የመሳሰሉ ወሣኝ ወሳኝ ተግባራት የሚያዩ ኢትዮጵያዊ ዓይኖች የሉም፡፡ ረፍዷል፡፡ በዚያም ላይ የካቢኔው ሹማምንት የዚያው አገዛዝ ባለሥልጣን የነበሩ ስለሆኑ ከስራቸው ይልቅ የቀድሞ ታሪካቸው ነውና የሚታየው ስር ነቀል ለውጥ ለሚፈልግ ህዝብ ትኩረት ቢነፈጋቸው አይገርምም፡፡

ተቃውሞው ሂዶ ሂዶ ሚያዚያ 10 ቀን ከመቶ ሺ በላይ የሚገመት ህዝብ የተሳተፈበት ግዙፍ ሠላማዊ ሰልፍ ተካሄደ፡፡ በእለቱ የወጣው ህዝብ ከሁሉም ዓይነት የኅብረተሰብ ክፍል የተውጣጣ ሲሆን፤ የቤተ-ክህነትና የቤተ-መንግስት ቁርኝት እንዲቀር ከመጠየቅ ጀምሮ ባለሥልጣናትን በየቢሮአቸው እየቆለፉ ለቀናት ታሽገው እንዲቆዩ እስከማድረግ የደረሰ ነበር፡፡ ይህን ህዝባዊ ማዕበል መግታት የማይሞከር ሆነ፡፡ ያልተነሳ ጥያቄ አለ ማለት አይቻልም፡፡ በአጭሩ ሁሉንም ጥያቄዎች መመለስ ማለት ንጉሣዊ አገዛዙ ያብቃ የሚል የማያሻማ ትርጉም ያለው መሆኑ ግልፅ ነበር፡፡

አዲሱ ካቢኔ ግራ ሲጋባ በሚያዚያ 22 "ብሔራዊ የፀጥታ ኮሚሽን" አቋቁሞ ሰላምና ኃይልን ያጣመረ የአመፅ መግቻ ዘዴን ተግባራዊ በማድረግ ሠራዊቱን ከካቢኔው ጎን ለማሰለፍ ሞከረ፡፡ ይህም ያስገኘው ውጤት የቀድሞው ካቢኔ ሚኒስትሮችንና ሌሎች ከፍተኛ የመንግስት ባለሥልጣናትን በሌላ አገላለፅ የልጅ እንዳልካቸውን ተቃዋሚዎች በኮሎኔል ዓለምዘውድ ተሠማ አማካኝነት (በኮሚቴው ውስጥ የመሪነት ስልጣን ተሰጥቶት ስለነበር) በቁጥጥር ስር እንዲውሉ ማድረግን



ነበር፡፡ልጅ እንዳልካቸው በስተመጨረሻ ራሳቸውም ሳይቀርላቸው በዙሪያቸው የነበሩ ተቃዋሚዎቻቸውን ሲያስለቅሙም የጃንሆይን ፈቃድ በመጠየቅ የነበረ ሲሆን፤ ንጉሡም "ይሁን ብያለሁ" ባይ ነበሩ፡፡

ከየካቲት ወር ጀምሮ እስከ ግንቦት ድረስ በነበረው ጊዜ የጦር ሠራዊቱ ጥያቄ በተለይም የደሞዝ ጭማሪው ተደርጎለት ጥያቄዎቹም ተመልሰውለት ነበርና ሰቪሉ ኅብረተሰብ "ወታደሩ የራሱን ጥቅም ብቻ አስከብሮ የህዝቡን እሮሮ አያገባኝም ያለ ከሃዲ ነው" እየተባለ መወረፍ ጀመረ፡፡ የዚህ ትችት አሰራጮች ለውጥ ፈላጊ ነን ያሉ ምሁራን ናቸው፡፡ በዚህም መለዮ ለባሹን ላላሰበውና ላልፈለገው ስልጣን መንገድ ጠረጉለት፡፡ ከምሁራኑ ባለፈም ቀደም ሲል ያየናቸው የግራና የቀኝ የቀድሞ የጃንሆይ ታማኝ ሹማምንት "ውሻ በቀደደው ጅብ ይገባል"ን መርህ አድርገው በወታደሩ አመፅ ሳቢያ ጃንሆይ ሲወርዱ ለመተካት አሰፍስፈውና የየራሳቸውን ስልጣን የመያዝ እቅድ ከግብ ለማድረስ ሲሉ አመፁ እንዲቀጣጠል እንጂ እንዲረግብ የወሰዱት ይህ ነው የሚባል ቀና እርምጃ አልነበረም፡፡ እውነታውን እያወቁትም ለጃንሆይ "አይዞዎት፤ ህዝቡም ጦሩም ለእርስዎ ያለው ታማኝነት ጽኑ ነው፤ የጠላው አንዳንድ ባለሥልጣናትን ነው፤ እነዚያ ባለሥልጣናት ከተሻሩ አመፁ ይቆማል" እያሉ ይደልሏቸው ነበር፡፡ በተለይ የግቢ ሚኒስትሩ ደጃዝማች ከበደ ተሰማ ታማኝም ስለነበሩ ለዚህ መሰሉ የማዘናጋት ተግባር በብርቱ ጥረዋል፡፡

ምሁራኑም ሆኑ መሣፍንቱ እንዲሁም መኳንንቱ በመለዮ ለባሹ ትግል ስልጣን ለመያዝ ሲያቅዱ፤ "ራሱ ጦሩ ስልጣኑን ቢይዘውስ?" ብለው ለማሰብ የሞከሩበት ሁኔታ የለም፡፡ ምናልባትም ያው ያደጉበትና ያረጁበት ራስን በዘር ሐረግ ከፍ አድርጎ የማየት አስተሳሰባቸው ወታደሩን እንዲንቁትና "ስልጣን ለእኔ አልተፈቀደም፤ አይገባኝም" ብሎ ያስባል ብለው ካላመኑ በቀር ይህን መጠርጠር ነበረባቸው፡፡ ከዚህ አንፃር የነሱ መነሻ ብዙ ላይገርም ይችላል፡፡ ነገር ግን ለዘመናት የፖለቲካ ትግል ሲያደርጉና "ስር ነቀል ለውጥ" እያሉ ሲያቀነቅኑ የኖሩት፤ የትኛው ርዕዮት ለኢትዮጵያ እንደሚሻላት ቀድመው ሲገልፁ የቆዩት ምሁራንና ምሁር ነን ባዮች፤ ስለ አብዮትም ብዙ ያነበቡት ሁሉ ያንን የመሰለ የህዝብ አመፅ ሲያስተውሉ ቢያንስ ተከታዩን ተግባር አውቀው አንዳችም ቅድመ ዝግጅት አለማድረጋቸው ያስገርማል፡፡

የዚያ ወቅት ምሁራንም ሆኑ ስልጣን ፈላጊዎች ያንን አመፅ ሲያጋግሉ አንድ አይነት ግብ ነበራቸው፡፡ "ጦሩ ንጉሡን በአመፅ ያወርዳል፤ ምክንያቱም ታጥቋልና፡፡ ከዚያ በኋላ ወታደር አገር መምራት ስለማይችል ጦሩ ወደ ክፍሉ ይመለሳል እኛ ስልጣን እንጨብጣለን" የሚል ነው፡፡ ቢያንስ የጎረቤት አገሯን የግብፅን የቅርብ አብዮት ማሰብ

አልፈለጉም፡፡ እንደተባለውም ያንን አብዮተኛ የህዝብ ማዕበል የሚያስተባብር አንድም አካል፣ አንድም የተደራጀ ቡደን ስላልነበረ የግድ ህዝቡን የሚያስተባብር አካል አስፈለገ፡፡ እርግጥ ነው ወቅቱም ሕጉም የፖለቲካ ፓርቲ መመስረትና መንቀሳቀስ የሚቻልበት አልነበረም፡፡ ነገር ግን በአደባባይ ማመፅ የቻለና ለውጥ የፈለገ ምሁር እንዳደረጉት ከአብዮት በኋላ ሳይሆን ከአብዮቱ በፊት ቢያንስ በጦሩ እየታገዘ መፈፀም የነበረበት የቤት ስራ መኖር ነበረበት፡፡ አልሆነም፡፡

ሁኔታው ያለቀለት መሆኑ ገሃድ ወጣ፡፡ አብዮቱ መያዝ ከሚገባው ትንፋሽ በላይ የያዘ የልጆች ፊኛ መስሎ ተወጥሯል፡፡ እንዳያስተነፍሱት በማይፈታ እስትሳሰር ከጫፍ ታስሯል፣ የቀረው መፈንዳት ነው፤ ለዚህ ደግሞ ቅንጣት ምክንያት ብቻ በቂ ነበር፡፡ ያላቸውን ኃይል ተጠቅመው ያሳበጡት በውጭ አገር ያሉት ለሥልጣን ሲባሉ ይህን የሚያስቡበት ጊዜ አጡ፤ በቅርብ ያሉትም ከፈነዳ በኋላ ስለሚነፉት አዲስ የልጆች ፊኛ ሲያውጠነጥኑ ነበር፡፡ በመሆኑም አገሪቱ በአስር አለቆች መመራትና ብዙ እልቂት መድረስ ነበረበት፡፡ በሌሎች ይሁንታ ያበጠውን አብዮት ማፈንዳት ለወታደሩ ቀላል ነበር፡፡ እናም "ለማስተባበር" በሚል መነሻ ከየጦር ክፍሉ ተውጣጥተው እንደቀልድ በላንድሮቨር መኪና ለስብሰባ መጡ፣ በዚያው ተባብረው፣ አስተባብረው፣ በዚያው ስልጣን ይዘው፣ ባላሰቡት መንገድ አገር መርተው፣ በዚያው ቀሩ፡፡ ለማንኛውም ባየነው መልኩ የኢትዮጵያ አብዮት አበጠ፡፡



አንበሳ እንራሹ ጃንሆይ

*የደርግ ውልደትና እድገት*

በየካቲት ወር 1966 ዓ.ም ህዝባዊ አመፅ ሲቀጣጠል የተቋቋሙ የጦር ኃይሉ አባላት የተሰባሰቡባቸው ኮሚቴዎች ነበሩ፡፡

የመጀመሪያው ኮሚቴ የደመወዝ ጭማሪ እንዲደረግለት ለጃንሆይ ጥያቄ ባቀረበበት ወቅት የተቋቋመ ነበር፡፡ ይህ ኮሚቴ ወደ 200 የሚጠጉ



ባለሥልጣናትን በቁጥጥር ስር አድርጎ የነበረ ሲሆን፤ ጃንሆይ የጦሩን ጥያቄ ምላሽ ሲሰጡት የታሰሩትን ከፍተኛ ባለሥልጣናት ፈትቶ ተበተነ፡፡

ሁለተኛው ኮሚቴም በተመሳሳይ ይሰበሰብና ኮሎኔል የዓለምዘውድ ተሠማን ሲቀመንበሩ አድርጎ ይመርጣል፡፡ በመኮንኖች ክበብ የሁተለኛው ኮሚቴ ስብሰባ ሲካሄድ ከዓለምዘውድ ሌላ ኮሎኔል ይገዙ ይመኔ፣ ሻለቃ አጥናፉ አባተና ሻምበል እንዳለ ተሠማ ተመርጠው ነበር፡፡ ልጅ እንዳልካቸው መኮንን ይህንን ኮሚቴ በዘመዳቸው በኮሎኔል የዓለምዘውድ መዳፍ ውስጥ በመሆኑ 20 ከፍተኛ ባለሥልጣናትን አስለቅመው ጎፋ ሰፈር እንዲታሰር ያደረጉት በዚህ በሁለተኛው ኮሚቴ አባላት አማካኝነት ነው፡፡ ልጅ እንዳልካቸው የኮሎኔል የዓለምዘውድን ኮሚቴ በዚህ አይነት ከተጠቀሙበት በኋላ፤ በጎን ያሴሩና በጄኔራል ወልደሰላሴ በረካ አማካኝነት የኮሎኔል የዓለምዘውድን ኮሚቴ እራሳቸው ልጅ እንዳልካቸው ያስበትኑታል፡፡ ሁለቱ ኮሚቴዎች በዚህ ዓይነት ከተበተኑ በኋላ አንድ ወር ያህል ቆይቶ ሰኔ 20 ቀን አንድ ነገር ይከሰታል፡፡

ይህም ከንጎና ኮርያ ዘምተው የተመለሱ የሠራዊቱ አባላት ያቀረቡት አቤቱታ ነው፡፡ እነዚህ 80 የሚሆኑ የኮንጎ ዘማች የበታች ሹሞች ሰኔ 20 ቀን 1966 ዓ.ም በቀጥታ ወደ ቤተመንግስት ይሄዱና ከንጉሠነገስቱ ፊት ቀርበው፤ "ጃንሆይ ከፊትዎ ዛሬ የቀረብነው የደከምንበት፣ ላብና ደማችን የፈሰሰበት፣ ከተባበሩት መንግስታት የተከፈለን ገንዘብ እንዲሰጠን ለግርማዊ ጃንሆይ ለማመልከት ነው" በማለት አቤቱታ አቀረቡ፡፡

- ጃንሆይ በጣም ተበሳጭተው "እናንተ ምቀኞች፤ ተንኮለኞች፣ የሠላም ፀሮች! ማዘጋጃ ቤቱም የተሰራው በእኛ ገንዘብ ነው ትላላችሁ! ለመሆኑ ይህን ህንፃ ለመስራት ኢትዮጵያ ገንዘብ አጥታ የናንተን ገንዘብ ወሰደች? እናንተ እርጉሞች! ገንዘቡን ብታገኙ እንኳን ልትጠጡበትና ልትሰክሩበት እንጂ ቁም ነገር አትሰሩበትም" የሚል መልስ ሲሰጧቸው፤ ከመካከላቸው አንዱ ሃምሳ አለቃ እሸቱ አያሌው "ጃንሆይ! ገንዘቡን የፈለግነው ከሐብታም ኩሽና ለመውጣት እንጂ ልንሰክርበት አይደለም" የሚል ምላሽ በመስጠት ሲሞግት ጃንሆይ "ቀጣፊ ዝም በል!" እንዳሉትና በሙግቱ መሐል ሌተናል ጄኔራል አቢይ አበበ ድንገት ሲደርሱ አቤቱታ አቅራቢዎች ሙግቱን ትተው እንደወጡና ጃንሆይም ሰድበው እንዳባረሯቸው ከአቤቱታ አቅራቢዎች አንዱ የነበረው ለሻምበል ተስፋዬ ርስቴ በእስር ቤት ውስጥ ገልጸላቸው በመፃህፋቸው አካተውት ይገኛል፡፡

እነዚህ ወታደሮች ከወጡ በኋላ ብንበታተን እየለቀሙ ያስሩናል በሚል ስጋት ጥያቄያቸው ምላሽ እስኪያገኝ ድረስ መበተን እንደሌለባቸው ይወስኑና የዚያኑ ዕለት በጋራ ወደ ጠቅላይ ሚኒስትር እንዳልካቸው ቢሮ በመሄድ ጥያቄያቸውን ለጃንሆይ እንዳቀረቡና ጃንሆይም አዋርደው

እንዳባረሯቸው በመግለፅ አቤቱታቸውን ያሰማሉ፡፡ጠቅላይ ሚኒስትሩም የወታደሮቹን ቁጣ አብርደው፤ከንጉሡ ጋር ተመካክረው ለጥያቄያቸው አፋጣኝ ምላሽ እንደሚሰጡ ቃል ገብተው ያሰናብቷቸዋል፡፡
ከዚያ ወጥተውም መበታተኑን አልፈለጉምና ወታደራዊ እንቅስቃሴ ለማድረግ መነጋገር እንዳለባቸው ወስነው በቀጥታ ወደ አራተኛ ክፍለ ጦር ጠቅላይ መምሪያ ሄዱ፡፡ ዘማቾቹ 4ኛ ክፍለ ጦር ግቢ ውስጥ ተሰብስበው ሲነጋገሩ በመምሪያው ውስጥ የነበሩ የክፍለ ጦሩ አባላትም ተጨምረው "ለውጥ ማምጣት አለብን!" እያሉ ማጋጋል ያዙ፡፡

ከዚህ በፊት የነበረው ሁለተኛው የዓለምዘውድ ኮሚቴ ሲበተን ቅር የተሰኙ የነበሩት ሻለቃ አጥናፉ አባተ ይመኙት የነበረውን ለውጥ የማምጣት ሀሳብ በራሳቸው ክፍለ ጦር ጊቢ ውስጥ የሚጀምሩበትን አዲስ እድል አገኙ፡፡ ያ ኮሚቴ ከተበተነ በኋላም እነ ሻለቃ አጥናፉ ውስጥ ውስጡን በድብቅ እየተገናኙ ይዶልቱ ነበር፡፡

ስለዚህ ሻለቃ አጥናፉ አባተ፣ ሻምበል እንዳለ ተሠማ፣ ሃምሳ አለቃ ዓሊ ሙሜ፣ ሻምበል ወንድወሰን ብርሃኑ የተባሉ መኮንኖች ወደ እንግዶች ስብሰባ ተቀላቀሉ፡፡ የኮንጎ ዘማቾች የለውጥ ማምጣት ሀሳብ ካነሱ በኋላ ስብሰባቸው መልክ ይኖረው ዘንድ መሪ መምረጥ እንዳለባቸው ይወስናሉ፡፡ ተከታዩ ጥያቄ የሚመረጠው መሪ መኮንን ይሁን ወይስ የበታች ሹም? የሚል ነበርና ውይይቱ ቀጥሎ የጦሩ ሙሉ ድጋፍ እንደሚያስፈልግ፣ የጦሩን አባላት አስተባብሮ ለመምራት ደግሞ የግድ መኮንን የሆነ መሪ እንደሚሻል፤ ነገር ግን ከፍተኛ መኮንን እንደማያስፈልግና ማዕረጉ ከሻለቃ መብለጥ እንደሌለበት ተስማሙ፡፡

ምክንያቱም ከፍተኛ መኮንኖች መሪ ከሆኑ የራሳቸውን ጥቅም አስከብረው የበታቹን ጥያቄ ቀብረው ያስቀሩት ስለነበር ነው፤ ከሻለቃ መብለጥ የለበትም የተባለው፡፡ በውሣኔው መሠረት ሻለቃ አጥናፉ አባተ የስብሰባው መሪ፣ ሃምሳ አለቃ አበራ አጋ ከፖሊስ ሠራዊት፣ ጄኔር ቴክኒሺያን ዮሐንስ ፍትዊ ከምድር ጦር አቪዬሽን ለኮሚቴው አባልነት ተሰየሙና ተሰብሳቢዎቹ በሻለቃ አጥናፉ መሪነት ወደ ስብሰባ አዳራሽ ተዛወሩ፡፡

ይህ ሦስተኛው ኮሚቴ የመጨረሻው መጀመሪያ ሊባል ይችላል፡፡ በእለቱ ከተሰብሳቢዎች ውስጥ ብዙዎቹ የ4ኛ ክፍለ ጦር አባላት ስለነበሩ እንዲቀነሱ ተደረገ፡፡ በስብሰባው የተለያዩ ሀሳቦችን እያነሱ እየጣሉ ቆይተው በመጨረሻ የደረሱበት ውሣኔ "1. የምድር ጦር ልዩ ልዩ ክፍሎች የአየርና ባህር ኃይል እንዲሁም የፖሊስ ሠራዊት የየራሳቸውን ወኪል መርጠው እንዲልኩ፣ 2. በአዲስ አበባ ያሉት የሬዲዮና የቴሌቪዥን ጣቢያዎችን፣ እንዲሁም ልዩ ልዩ ቁልፍ ቦታዎችን በጦሩ እንዲጠበቁ ማድረግ፣ 3. የስጋት ምንጭ ይሆናሉ ተብለው የሚገመቱ የሲቪልና የጦር



አለቆችን በቁጥጥር ስል ማዋል፣ 4. ለመለዮ ለባሹ ሁሉ ለተጀመረው እንቅስቃሴ ድጋፍ እንዲሰጡ ጥሪ ማቅረብ፣ በተለይ ለኮሚቴው አባልነት አዲስ አበባ፣ አስመራና ሐረር ከሚገኙ ልዩ ልዩ የጦር ክፍሎች ማስመረጥና ማሳተፍ..." የሚሉ ሲሆን፤ ተወካዮች ከተላኩላቸው በኋላም ሁኔታዎችን የሚከታተል፣ የሚያስተባብርና ድጋፍ የሚያሰባስብ፣ ለንጉሡ ታማኝነትን የሚገልፅ ኮሚቴ እንደሚሰይሙ ተወያይተው ተስማሙ፡፡ እነዚህ በ4ኛ ክፍለ ጦር የተሰባሰቡት 31 መለዮ ለባሾች በምርጫ ያልተወከሉ የመጀመሪያ የደርግ አንቀሳቃሾች ናቸው፡፡ እነዚህን እቅዶች መርጠው ያስቀመጡትና በፍጥነትም በተግባር እንዲተረጎም ያደረጉት ሻለቃ አጥናፉ አባተ ሲሆኑ፤ከመኮንንነታቸው ባለፈ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ቢዝነስ አድሚንስትሬሽን ተምረዋል፡፡

የዚያኑ ዕለት ምሽት ሁለት ሠዓት ከ4ኛ ክፍለ ጦር በተውጣጡ ወታደሮች አቡነ ጴጥሮስ ሐውልት አጠገብ ይገኝ የነበረውን የኢትዮጵያ ሬዲዮ ጣቢያ፣ ማዘጋጃ ቤት ህንፃ ውስጥ የሚገኘውን የቴሌቪዥ ማሰራጫ ጣቢያ፣ ጌጃ ሠፈር የሚገኘውን የብስራተወንጌል ሬዲዮ ጣቢያ፣ የቴሌኮሙኒኬሽንን መስሪያ ቤት፣ የመብራትና የውሃ አገልግሎት ማሰራጫዎችንና የአዲስ አበባ ከተማ መግቢያ መውጫ መንገዶችን በወታደር ጥበቃ ስር እንዲሆኑ አደረጉ፡፡ ለዚህም ከሻለቃ አጥናፉ ጋር የፖሊስ ሠራዊት አባሉ ሻለቃ እንየው ፈረደ (ለደርግ ምስረታ አስተዋፅኦ ቢያደርጉም ሻለቃ ፈረደ የደርግ አባል ግን አልሆኑም) ጦሩን በማንቀሳቀስና ለጥበቃ በመመደብ ተባብረዋል፡፡

ለመገናኛ ብዙሃኑም ሻለቃ አጥናፉ ከምሽቱ ሦስት ሰዓት ጀምሮ 4ኛ ክፍለ ጦር ከተመሠረተው ኮሚቴ የሚሰጠውን ትዕዛዝ መፈፀም ተግባራቸው መሆኑን ለተረኛ ሹሞች ገለፁ፡፡ ወቅቱ ወታደራዊ ዲሲፒሊንም ሆነ የአዛዥና ታዛዥ ግንኙነት ቅጥ ያጣበት ነበርና እቅዱን ለማሳካት እንቅፋት አልነበረም፡፡ በመሆኑም ጦሩ በመስክ ሬዲዮ ያለገደብ እየተገናኘ መልዕክት እንደልቡ ይለዋወጥ ነበር፡፡ በኮሚቴው እቅድ መሠረትም በአገሪቱ ካሉት 40 ያህል ልዩ ልዩ የጦር ክፍሎች 3 አባላት መርጠውና ወክለው ወደ አዲስ አበባ 4ኛ ክፍለ ጦር ጠቅላይ መምሪያ ጊቢ እንዲልኩ መልዕክት ደረሳቸው፡፡ ከአራቱም ክፍለ ጦሮችና በክፍለ ጦሩ ስር ካሉ ልዩ ልዩ ክፍሎች ፖሊስ ሠራዊትን ጨምሮ ተመርጠው የተላኩ አባላት ፈጥነው ደረሱ፡፡ ግሚሱ "ሂድ እስቲ የሚባለውን ስማ" ተብሎ የመጣ ነበር እንጂ ለጉዳዩ ብዙዎች ትኩረት የሰጡ አልነበሩም፡፡ ብቻ ግን እንቅስቃሴው ሂደቱን ቀጥሎ ወደ ስኬት እያመራ ነው፡፡ ነገር ግን የደርግ አባላቱ በመጀመሪያ ተጠራርተው በ4ኛ ክፍለ ጦር ሲሰበሰቡ ሹፌሩም ምኑም ተጠራቅሞ ስለነበር 170 ነበሩ፡፡ ቆይቶ ሻለቃ መንግስቱ ሰብሳቢ ሆነው ከተመረጡ በኋላ የየክፍሉ ተወካይ አባላት በአግባቡ ስም

ዝርዝራቸው እንዲመዘገብ ስለተደረገ 50ዎቹ ወደየክፍላቸው እንዲመለሱ ተደርጎ 120 ሆኑ፡፡ ሆኖም ቀስ በቀስ በመኪና አደጋ ከሞተው አንድ አባል በስተቀር 10 ያህሉ ገና ከጅምሩ መዝረፍ፣ መስከር፣ ቁማር መጫወት፣ አስገድዶ መድፈር፣ በሆነ ባልሆነው ታሳሪዎችን በእሳት እየለበለቡ በማሰቃየትና በሌሎች ወንጀሎች የደርግን ስም እያከፉት በመሄዳቸው የተገደሉ ናቸው፡፡ (ምስክርነት 2001 ዓ.ም)

በመሆኑም 109 አባላት ረዥም ጉዞ ተጉዘዋል፡፡

በሻለቃ አጥናፉ የሚመራው አስተባባሪ ኮሚቴ ሰኔ 21 ቀን 1966 በ4ኛ ክፍለ ጦር ጊቢ ውስጥ መቋቋሙን በሬዲዮ ይፋ አደረገ፡፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ስብሰባዎች መካሄድ ቢጀምሩም፤ አባላቱ ተጠቃለው ለመግባት የቀናት እድሜ ወስዶባቸዋል፡፡ እነዚህ በጥሪ የመጡ አባላት አብረዋቸው ከመጡ አባላት ውጪ አይተዋወቁም፣ ለምን እንደመጡ፣ አላማቸው ምን እንደሆነ በውል የተረዱ አልነበሩም፡፡

ሰብሳቢው ሻለቃ አጥናፉ ስብሰባውን ሲከፍቱ በጦሩ ውስጥ ስላለው ያስተዳደር ጉድለት፣ በስልጣን የባለጉ ሹሞች መበርከታቸው፣ ስልጣንን ተገን አድርገው በሙስና የተሰማሩ በዝባዦች አገሪቱን እያራቆቷት እንደሆነ መተንተን ጀመሩ፡፡ ተሰብሳቢውም አገዛዙን እየወነጀለ የመሰለውን ይናገራል፡፡ ምን መደረግ አለበት? የሚለውን ግን የሚያስረዳ ጠፋ፡፡

እርግጥ ነው አስተባባሪ ኮሚቴው ምስረታውን በሬዲዮ ይፋ ሲያደርግ ህዝቡ "ጀግና! በርቱ!" የሚል ምላሽ ሰጥቷል፡፡ ኮሚቴውም ዓላማዬ ብሎ ያቀረበው ማኑፌስቶ የመሰለ መግለጫው "የሠራዊቱን አባላት ደመወዝ ማስጨመር፣ የድርጅትና የትጥቅ መሟላትንና የአስተዳደር በደል እንዲወገድ፣ መለዮ ለባሹ ሲጠይቀው የቆየውን ልዩ ልዩ ጥቅማ ጥቅሞች እንዲሟሉና በአገሪቱ መሠረታዊ ለውጥ እንዲከሰት መጣር የኮሚቴው ዓላማ ነው" ብሏል፡፡

ነገር ግን በምን መልኩ? የሚለው አንኳር ጥያቄ አልተብራራም፡፡ ስለዚህም ከሰኔ 22 ጀምሮ ለ4 ቀናት ያህል ጥቂት የቀድሞው ባለሥልጣናትን እየመረጠ በ4ኛ ክፍለ ጦር ጊቢ ውስጥ ሲያስር ቆዩ፡፡ ኮሚቴው ሀሳቦችን ሲያነሳ ሲጥል ሠንብቶ ሰኔ 26 ቀን ከምስራቅ አንበሳው ክፍለ ጦር ተውጣጥተው ተመርጠው የተላኩ የ3ኛ ክፍለ ጦር አባላት ደረሱ፡፡ ከምስራቁ ክፍል ከመጡት 10 አባላት ውስጥ አንዱ ሻለቃ መንግስቱ ኃይለማርያም ነበሩ፡፡

የደረሱት ስብሰባው ላይ ነው፡፡ ሻለቃ መንግስቱ ስብሰባውን በፀጥታ ሲከታተሉ ቆይተው ግራ ተጋቡ፡፡ ሀሳቦች እየተነሱ እየተጣሉ፣ ማን ይታሰር፣ ማን ምን ይደረግ? ሲባባሉ አምሽተው ተለያዩ፡፡ በተከታዩ ቀን ሁሉም አባላት ተጠቃለው ገብተው የተለመደው ስብሰባ ተጀመረ፡፡



የሚባለውን በፀጥታ ሲያዳምጡ የቆዩት ሻለቃ መንግስቱ እጃቸውን አወጡ፡፡ ሻለቃ አጥናፉ እንዲናገሩ ፈቀዱላቸው፡፡ "... ለመሆኑ መለዮ ለባሹ ተወካዮቹን ወደ 4ኛ ክፍለ ጦር እንዲልክና ለምታደርጉትም እንቅስቃሴ ድጋፍ እንዲሰጥ ስትጠይቁት ምን እቅድ ይዛችሁ ነው? ምን ለመስራት ነው ዓላማችሁ?" የሚል ጥያቄ አነሱ፡፡ ፀጥታ ሰፍኖ ቆዩ፡፡ ከዚያም ሻለቃ አጥናፉ መልስ መስጠት ነበረባቸውና "እኛ ጥሪ ስናስተላልፍ የተጠናና የታቀደ ይህ ነው የምንለው የተለየ እቅድ ይዘን አይደለም፡፡ ሰቃይና መከራ ላንገላታው ርሐብና እርዛት ዕጣፈንታው ለሆነው ለኢትዮጵያ ህዝብ ተስፋ የሚሰጥ ለውጥ ለማምጣት ግን እንፈልጋለን፡፡ የአገርን ዳር ድንበር ለማስከበር የተሰማራው መለዮ ለባሽ ጎስቋላ ህይወትም ያሳስበናል፡፡ ተወክላችሁ የመጣችሁት መለዮ ለባሾች ምን እናድርግ? እንዴት እናድርግ? ዓላማችንስ ምን ይሁን? ምን መርህ እንከተል? ለሚሉት ጥያቄዎች በጋራ ተወያይታችሁ ከውሣኔ እንደሚደረስ ተስፋ አለን፡፡ ለአሁኑ ግን በጎ ምኞት እንጂ ይህ ነው የምንለው ልዩ እቅድ የለንም" ብለው መለሱ፡፡

በዚህ ጊዜ ሻለቃ መንግስቱ፤ "... ከምስራቅ መርጬ ያመጧቸው መለዮ ለባሾችና እኔ መሰብሰቡን የምንቀበለው አንድ እቅድ ኖሮ፣ ለህዝብ መሠረታዊ ለውጥ ለማስገኘት ዝግጅት ያለ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ መለዮ ለባሹ ከግምጃ ቤት መሣሪያ እያወጣ ጥቃቅን ብሶቶችን እያወሳ ዘላቂነት የሌላቸው መልሶችን እየተቸረ ወደ ጦር ሠፈሩ መመለሱን አይደለም አሁን መመልከት ያለብን፡፡ ይህ አይነቱን ተግባር ለመፈፀም ከሆነ ከቡድኔ ጋር ወደ አንበሳው ክፍለ ጦር ሰፈር ሐረርጌ እመለሳለሁ፡፡ በጎ ምኞት ብቻ አይበቃም፤ መርህ ያስፈልጋል፤ ወደተግባር የሚለወጥ እቅድ ያስፈልጋል" በማለት የተናገሩት ንግግር በሁሉም ተሰብሳቢዎች ዘንድ ትኩረትን አስገኘላቸው፡፡

ስብሰባው ቀጠለ፡፡ በወቅቱ የነበሩት አባላት የዚያን ጊዜውን የመንግስቱን እንደበተርቱዕነት በመገረም ያስታውሱታል፡፡ በገነት አየለ "የመንግስቱ ትዝታዎች ቁጥር 1" ላይ ቃላቸውን ከሰጡት አባላት ውስጥ አንዱ "... ሁላችንም በንግግር ችሎታውና በሀሳቦቹ ጥልቀት ተደነቅን፡፡ ይህ ሰው የሚናገረውን የሚያውቅ መሆኑን ተረዳን፡፡..." ሲል፤ ሌላው ጓድ "...መንግስቱ ስማርት ነበር፡፡ ተራ ተሰጥቶት መናገር ሲጀምር ተሰብሳቢዎችን በመጠየቅ ነበር የጀመረው፡፡ ምንድን ነው ዓላማችን? ምን ማድረግ ነው የምንፈልገው? ግባችን ምንድነው? ሲል እርስ በርሳችን መተያየት ጀመርን፡፡ ብዙዎቻችን ይህን መሠረታዊና ዋና ጥያቄ አላጤንነውም፡፡ የመለሰም አልነበረም፡፡ መንጌ ቀጠለና "ይሄን ግልፅ ካላደረግን ብዙም ወደፊት ልንራመድ አንችልም ሲል አንዳንዶች በጦሩ የተመረጡ ተወካዮች መሆናቸውን አመለከቱ፡፡ ቢሆንስ? So what? ነበረ

መልሱ፡፡ ... እያለ ሁላችንም እንድናደንቀው ያደረገ ንግግር ተናገሩ፡፡ ብዙዎቻችን ይህ ሰው ሊመራን ይችላል ብለን ሳንል አልቀረንም..." በማለት ያስታውሳሉ፡፡ ወዲያው ሻለቃ አጥናፉ "ለምን ከአሁኑ ሰዓት ጀምሮ ተወያይተን ውሣኔ ላይ አንደርስም? የኢትዮጵያ ህዝብ ግፍና መከራ ተሸካሚ ሆኗል፤ ለውጥ ይፈልጋል፣ የተሻለ ህይወት ይመኛል፣ ከስቃይና መከራ የሚያወጣው ይሻል፡፡ ስለዚህ እንወያይና ከአንድ ውሣኔ ላይ እንድረስ" ወደማለት አመሩ፡፡

አንደበተርቱው ሻለቃ መንግስቱ ኃይለማርያም ንግግራቸውን ካንበለበሉት በኋላ ሌሎች ተወካዮችም እየተነሱ ሀሳባቸውን መግለፅ ሲጀምሩ መንግስቱ ብድግ ብለው ግድግዳ ላይ ወደተሰቀለው ጥቁር ሰሌዳ አመሩና የአባላቱን ፍሬ ሀሳቦች ማስፈር ጀመሩ፡፡ የተለያዩ ሀሳቦች ካቀረቡ በኋላ፤ ለኢትዮጵያ የሚበጃትን የመንግስት ዓይነት በሚመለከት 1. ሕገ-መንግሰታዊ የዘውድ አገዛዝ፣ 2. ዴሞክራሲያዊ የሲቪል መንግስት፣ 3. ወታደራዊ መንግስት የሚሉ ነጥቦች ተመርጠው ተቀመጡ፡፡ ለብዙ ሺ ዓመታት ዘውዳዊ አስተዳደር ላራመደች አገር የቱ ተመራጭ እንደሚሆን ግልፅ ከመሆኑም በላይ፤ ዘውዱን ማስወገድ ለእነዚህ መለዮ ለባሾች ፈጽሞ በዚያ ወቅት የሚታሰብ አልነበረም፡፡ "ሀሳቡ ራሱ ያስፈራ ነበር" ይላሉ አባላቱ፡፡

ስለዚህ ሻለቃ መንግስቱ "ሕገ-መንግስታዊ የዘውድ አገዛዝ" የሚለውን በጠመኔ አከበቡትና ተቀመጡ፡፡ ሁሉም ተስማማ፡፡ ከ15 ደቂቃ ዕረፍት በኋላ ውይይቱ ሲቀጥል ከአባላቱ ውስጥ "አዲስ ፕሮግራምና መመሪያ የምናወጣ ከሆነ ለምን አዲስ ሊቀመንበር አንመርጥም?" የሚል ሀሳብ ተነሳ፡፡ ሻለቃ አጥናፉ አልተቃወሙም፡፡ በቅንነታቸው ብቻም ሳይሆን ሙሉ አባላቱ ከተሰባሰቡ በኋላ ሌላ የጋራ ምርጫ መደረጉ አግባብ ነበር፡፡

"ሻለቃ መንግስቱ" አለ አንዱ አባል፡፡የሁሉንም ቀልብ የሳቡ መንግስቱ መሆናቸው ይታወቃል፡፡ሻለቃ አጥናፉ ራሳቸው በመንግስቱ ብቃት የተደነቁ ናቸው፡፡ ስለዚህ ያለአንዳች ተቃውሞ በሙሉ ድምፅ ሻለቃ መንግስቱ ሊቀመንበር፣ ሻለቃ አጥናፉ ምክትል ሊቀመንበር ሆነው ተመረጡ፡፡ ቀጥሎ ዋና ፀሐፊ ሊመርጡ ሲሉ መንግስቱ ተቃወሙና፤"ሊቀመንበር እንድሆን እምነት ጥላችሁብኝ ከመረጣችሁኝ ዋና ፀሐፊውን የምመርጠው እኔ መሆን አለብኝ" አሉ፡፡በዚያ አዳራሽ ውስጥ የመንግስቱን ሀሳብ የሚቃወም ቢኖር እንደ ጅል በተቆጠረ ነበር፡፡ ማንም አልተቃወመም፡፡መንግስቱ ጓደኛቸውን /ኮርስ ሚታቸውን/ ገብረየስ ወልደሃናን መረጡ፡፡ሻለቃ ብርሃኑ ባየህንም የእቅድ ኮሚቴው አባል እንዲሆን አደረጉ፡፡



ሻለቃ መንግስቱ በአንደበት ብቻ የአጥናፉን ቦታ ያለችግር ነጥቀው ሊቀመንበር /በዚያ ሰዓት በመሠረቱ ሊቀመንበር ሳይሆን ሰብሳቢ ነው ሊባል የሚችለው/ ከመሆናቸው ባለፈ ሁለት ጓደኞቻቸውን ፀሐፊና የእቅድ አውጪ ኮሚቴ አባል ማድረጋቸው ላፅላዩንም ታህታዩንም መዋቅር በራሳቸው እቅድና መንገድ የማስቀጠል እድላቸውን አመቻችተዋል፡፡ ይህ ኮሚቴ "የጦር ኃይሎች፣ የፖሊስና የህዝባዊ ጦር አስተባባሪ ኮሚቴ" በሚል ራሱን ይፋ አድርጓል፡፡ ከየጦር ክፍሉ ተመርጠው የተላኩ አባላቱን መዝግቦ ጨርሷል፡፡ ስራውንም ንዑስ ኮሚቴዎችን በማቋቋም ሲጀምር 1. የፖለቲካና የውጭ ጉዳይ ኮሚቴ፣ 2. የኢኮኖሚ ኮሚቴ፣ 3. የመከላከያ ኮሚቴ፣ 4. የሰሻል ጉዳይ ኮሚቴ፣ 5. የህዝብና ደህንነት ኮሚቴ፣ 6. የአስተዳደርና ሕግ ኮሚቴ፣ 7. የእስረኞች አስተዳደር ጉዳይ ኮሚቴ፣ 8. የስራ መቆጣጠሪያ ኮሚቴ፣ 9. የጽህፈት አገልግሎት ኮሚቴ የሚባሉትን አቋቋመ፡፡

ሻለቃ መንግስቱ የአስተባባሪው ኮሚቴ መሪ ስለሆኑ የእቅድ አውጪ ኮሚቴውን ሰብስበው ተከታዮቹን እቅድ አቀረቡ፡፡

1. የመለዮ ለባሹን አስተባብሮ ለለውጥ ማዘጋጀት፣ 2. ለውጥ ፈላጊውን ህብረተሰብ በተለይም ምሁራንን ከጎኑ አሰልፎ ረዳቱ ማድረግ፣ 3. ከጠቅላይ ሚኒስትር እንዳልካቸው መኮንን መንግስት ጋር ተባብሮ እንደሚሰራ መግለጫ እንዲያወጣ ማድረግና በአገሪቱ መሠረታዊ ለውጥ ማምጣት፣ 4. ለንጉሡ በተመረጡ አባሎች አማካኝነት ታማኝነትን መግለፅ የሚሉ ናቸው፡፡ በተጨማሪም ከህዝቡ አስተያየቶችን መሰብሰብ የሚችሉበት የሀሳብ መስጫ ሳጥኖችን በየአደባባዩ ማዘጋጀት በሚሉት ነጥቦች ተወያይተው ኮሚቴው ይህንንም በሙሉ ድምፅ ተቀበለው፡፡

ቀጣዩ ጥያቄ "መርሃችንስ ምን ይሁን?" የሚል ነበር፡፡ ፈጣኑ መንግስቱ በቅፅበት "ኢትዮጵያ ትቅደም!" አሉ፡፡ ማንም አልተቃወመም፡፡ በእርግጥ ይህቺ መፈክር የአዶልፍ ሂትለር "ጀርመን ትቅደም" ናት፡፡ በኢትዮጵያ ምድር ግን የመንጌ ሆናለች፡፡ "እንዲያውም" ብለው ቀጠሉ መንግስቱ "ያለምንም ደም ኢትዮጵያ ትቅደም!" የአድናቆት ጭብጨባውን ተከትሎ ፀደቀ፡፡

ይህ አስተባባሪ ኮሚቴ ከእርሱ በፊት ከነበሩት ሁለት ኢምንት አስተባባሪ ኮሚቴዎች የበለጠ ሆኖ በጠንካራ መሠረት ላይ ቆመ፡፡ወዲያውም ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች አስተያየት ሲሰነዘርለት አንድ ግለሰብ የግዕዙን ቃል አጣቅሰው "ደርግ" የሚለውን ስያሜ አቀበሉ፡፡የአማርኛ ትርጉሙ ያው ኮሚቴ ማለት ነው፡፡ እናም "የጦር ኃይሎች፣የፖሊስና የህዝባዊ ጦር አስተባባሪ ኮሚቴ" የሚለው ቀርቶ "ደርግ" የሚለው መጠሪያው ሆኖ ቀረ፡፡የየጦር ክፍሉ ዋና አዛዦችም

ተወካዮቻቸው ተሳታፊ ስለነበሩ ከበስተጀርባ ሆነው ድጋፍ ይሰጧቸው ነበር፡፡

ደርግን በፓርላማ አይነት አወቃቀር ልንመስለው እንችላለን፡፡ ልዩነቱ የጦር ክፍሎች ለደርግ አባልነት ተወካዮቻቸውን መርጠው ከላኩ በኋላ ድጋሚ መሻር አለመቻላቸው ነው፡፡ ይህንን ቀድሞ ለማሰብም መሠረታዊ መነሻ አልነበራቸውም፤ ሊኖራቸውም አይችልም፡፡ "ተወካይ ላኩ" ተባሉ ላኩ፡፡ አበቃ፡፡ አባላቱ በዚያው ጭልጥ ብለው ባልተጠበቀ ሁኔታና ፍጥነት ስር ሰደዱ፡፡ መልሶ የመሻሩ ጉዳይ የሚጠበቅ ባይሆንም፤ በሃይልና በማስገደድ ሊሞከር ይችላል፡፡ ለዚህም ነው ከአብዮቱ በኋላ ብዙም ሳይቆይ መንግስቱ ኃይለማርያምን የያዙት እንባገነናዊ ሂደት ያልጣማቸው የሦስተኛ ክፍለ ጦር አዛዦች "ወደ ክፍልህ ተመለስ" ሲሏቸው "አብዮቱን አደጋ ላይ ጥዬ አልመጣም፣ ይህ የህዝብ አደራ ነው" ብለው ድርቅ ያሉት፡፡ ቢለመኑ ቢለመኑ አሻፈረኝ በማለታቸውም የመጡበት ክፍል አዛዦች የመንግስቱ ኃይለማርያምን ቤተሰቦች አገቱ፡፡ "በጭራሽ" አሉ መንጌ፡፡ ጦሩ ግን እማራጭ ሲያጣ የታገቱትን ቤተሰቦቻቸውን ለቀቀ፡፡ በዚህ መሰሉ አካሄድ ከፓርላማ ሲለይ፤ በተጨማሪም፣ ፓርላማ ሕግን ተከትሎ ሲሰራ ደርግ ግን አንዳንድ ጊዜ ምናልባትም ብዙ ጊዜ ከሕግ ውጪ በስብሰባና በጭብጨባ ብቻ አንኳር አንኳር ጉዳዮችን የሚመለከቱ ውሣኔዎች ያሳልፋል፡፡

ደርግ ቀደም ሲል ያየናቸውን እቅዶች በፍጥነት ተግባራዊ ወደማድረጉ አመራ፡፡ ከተለያዩ ወገኖችም ትኩረት አገኘ፡፡ በዋናነት የስልጣን ጥም ያለባቸውንና ለለውጥ ስንታገል ኖረናል የሚሉት ምሁራን ያቺን ያበቃላትን ወንበር ለመቅለብ ከደርግ ለመጣበቅ ሲጥሩ፤ በሌላ በኩል ልዑል ራስ አስራተ ካሣ እንዲሁም የመንግስቱ ስጋ ዘመድ ደጃዝማች ከበደ ለመንግስቱ ድጋፍና ሽር ጉድ ማድረግ ጀመሩ፡፡ ይህ ሽኩቻ ለደርግ ልዩ ጥቅም ነበረው፡፡ ሌሎች የደርግን ስር እየሠደደ መሄድ ያዩ ምሁራንም ኮሚቴው ስር ነቀል ለውጥ እንደሚያመጣ ቀድመው በመገመት ብቻም ሳይሆን በደርግ እቅድ መሠረት በስደት ውጭ አገር ያሉ ምሁራን ተጠርተው ስለነበር ተንጋግተው መጥተው የየራሳቸውን ጠንካራ ድርጅት ማዋቀር ሲችሉ ከዚህ የበለጠ ትኩረት ሰጥተው በግልና በጋራ የተንቀሳቀሱት ከደርግ ጋር ለመወዳጀት መሪውን እያጣሩ በአክብሮትና በልምምጥ ጎንበስ ቀና ማለትን ነበር፡፡ ደርግ የመንግስትን ስልጣን መቦርቦርን ነበር ቅድሚያ የሰጠው ተግባር፡፡ ይህንንም ሲያደርግ ለንጉሱ ያለውን ታማኝነት በተደጋጋሚ እየገለፀ የነበረ ሲሆን፤ ጃንሆይም እውቅና አልነፈጉትም፡፡

ደርግ ለጃንሆይ ያቀረባቸው የመጀመሪያ ጥያቄዎች "... የተረቀቀውን አዲስ ሕገ-መንግስት ባፋጣኝ በስራ ላይ እንዲውል (አዲሱ



ካቢኔ በህዝብ ጥያቄ ያረቀቀውን)፣ ለፖለቲካ እስረኞችና ስደተኞች አጠቃላይ ምህረት እንዲታወጅ፣ ለዚህም ሲባል ፓርላማው እንደቀድሞው ክረምት ላይ መዘጋቱ ቀርቶ በእነዚህ መሰል ጉዳዮች ላይ እንዲመክር" የሚሉ ነበሩ፡፡ ጃንሆይ ከሌላው አመፀኛ እነዚህ ትንንሾች ሳይሻሉኝ አይቀሩም፣ እንዲያውም ጄኔራል ቢሆን እንጂ ሃምሳ አለቃና አስር አለቃ መቸም ዙፋን አይመኝም ብለው ያሰቡ ይመስላል፡፡ ምክንያቱም ከጥቂት ማንገራገር በቀር እምቢ ያሉት ጉዳይ አልነበረምና፡፡

የደርጉ አባላትም በልዩ አክብሮት፣ እንክብካቤና ፍቅር ነበር ጥያቄያቸውን የሚያቀርቡት፡፡ የጃንሆይ አለማንገራገር ደግሞ ደርጎችን የበለጠ እያደፋፈራቸው ሄደና፣ ሌሎች ተከታታይ ጥያቄዎችን ማቅረብ ቀጠሉ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ዋናው ደርግን የተረጋገጠ ህልውና እንዲኖረው ያደረገው ጥያቄ መመለሱ ሲሆን፤ ወደፊት የለውጥ እንቅፋት ይሆናሉ ተብለው የሚፈሩትን ታላላቅ ባለሥልጣናትና የጦር ጄኔራሎችን በቁጥጥር ስር እንዲውሉ ተጠይቆ ሳይውል ሳያድር እጃቸውን እንዲሰጡ ታዘው መታጎራቸው ነው፡፡ የዚያ ግዙፍ ግንድ ቅርንጫፎች ሁሉ ተመልምለው አለቁ፡፡ የደርጉ አባላት እጅ እየነሱ በጃንሆይ ፊት ቀርበው የሚጠይቋቸውና በይሁንታ የሚመለሱ ጥያቄዎች ሁሉ በመገናኛ ብዙሃን እንዲታዩና እንዲደመጡ የሚል ጥያቄም የተካተተበት ነውና ህዝቡ ክንውኑን እንዲከታተል ሆኗል፡፡

ይህ ሁሉ ሲሆን የደርግ ዓላማ ምን እንደሆነ ህዝቡ አልገባውም፡፡ ኮሚቴው ራሱ ያስቀመጠው ግብ በምን መልኩ እንደሚፈፀም ያወቀው አይመስልም፡፡ ብቻ ግን ምንጠራውን አጧጧፈው፡፡

ደርግ ምንም እንኳን ጦር ያዘምታሉ ያላቸውን ታላላቅ ባለሥልጣናት መልምሎ ቢጨርስም፤ የመለዮ ለባሹን ሙሉ ድጋፍ አላገኝ ይሆን? በሚል ስጋት ተወጥሯል፡፡ ስለዚህም በጦሩ ውስጥ እጅግ ታዋቂና ተወዳጅ ከፍተኛ መኮንን መርጦ የኮሚቴው መሪ ለማድረግ ፈለገ፡፡በርግጥም አስፈላጊ ነበር፡፡ተወዳጁ መኮንን ጄኔራል አማን ሚካኤል አንዶም ነበሩና እርሳቸውን ከፊት ማስቀደሙ ለጊዜውም ቢሆን አስፈላጊ ነበርና ሊያሾሟቸው ወሰኑ፡፡ጄኔራል አማን ከስራ ገበታቸው ከመወሰኛ ምክር ቤት ተጠርተው የኮሚቴው ውሣኔ ሲነገራቸው ያለማወላወል ተቀበሉት፡፡ቀጣዩ ስራ ወደ ጃንሆይ ሄዶ "ይህን ሰው ይሹሙልን" ብሎ መጠየቅ ነበር፡፡ይህን ጥያቄ ከሌሎች ካልተመለሱ ጥያቄዎች ጋር አጣምረው፤ በንጉሠነገስቱ ፊት እንዲያነቡ የተላኩት የደርግ ልዑካን በሻለቃ ተስፋዬ ገብረኪዳን እየተመሩ ሄዱ፡፡ሻለቃ ናደው ዘካርያስ ጽሁፉን እንዲያነቡ ተመድበዋል፡፡በሐምሌ ወር 1966 ዓ.ም ልዑካኑ ጠቅላይ ሚኒስትር እንዳልካቸው መኮንን፣ልዑል ራስ እምሩና ሌሎች ጥቂት የካቢኔ አባላት ከጃንሆይ ጋር አብረው ባሉበት ጥያቄዎች ተነበቡ፡፡

ጃንሆይ እጅግ ተቆጥተው "ለመሆኑ ጄኔራል አማንን ታውቁታላችሁ? ከሠራዊታችን ውስጥ ሌላ ሰው አጣችሁ? ቧሚና ሻረስ እናንተ መሆናችሁ ነው?" አሉ፡፡ (ሌላ ሰው አጣችሁ? ያሉት ለምን እንደሆነ ግልፅ አይደለም፡፡ ምክንያቱም አማንን ጃንሆይ ይወዷቸዋል፣ ያከብሯቸዋል፣ ከስደት ሲመለሱ አማን ሱዳን ውስጥ በስደት ነበሩና አብረው እየተዋጉ የመጡ ናቸው፡፡ ብቻ ጃንሆይ በእርጅና ምክንያት አንዳንዴ የንግግር ውሉ ዝብርቅ ይልባቸው ስለነበር ይሆናል) ቀጠሉ ጃንሆይ፤ "... ደግሞስ ማን የሚባል የፖለቲካ እስረኛ ነው እንዲፈታላችሁ የምትፈልጉት? እስኪ አንድ የፖለቲካ እስረኛ ስም ጥሩ?" ብለው አፋጠጧቸው፡፡

እንባቢው ሻለቃ ናደው መልስ አጡ፡፡ሻለቃ ተስፋዬ ገ/ኪዳንም ፀጥ አሉ፡፡ የካድሬ ነገር ይሄው ነው፤የተሞላውን ከመናገር ያለፈ ጥልቅ ጥያቄ ቢመጣ መልስ የለውም፡፡ድጋሚ ሄዶ ተሞልቶ (ቻርጅ ተደርጎ) ካልመጣ ከየት አምጥቶ ይመልሳል? የካድሬ ትክክለኛ መገለጫ ወይም ትርጉም ይሄ ነው ለማለት ነው፡፡ጥያቄው የቀድሞ ምሁራን የሆኑና ከደርግ ለመጣበቅ አንዳንድ ሀሳቦችን ከርዕዮት አመራረጥ ጀምሮ በማቅረብ የግፊት ምክርም ይለግሱ ከነበሩ ምሁራን የመነጨ ነው፡፡

የሆነ ሆኖ የንጉሡን ጥያቄ መመለስ ስላልቻሉ ለደቂቃ ያህል ፀጥታ ሰፍኖ ከቆየ በኋላ ከአባላቱ አንዱ የነበረው እንዳለ ተሠማ "ግርማዊ ሆይ! እኛ ቧሚም ሻሪም አይደለንም፣ሠራዊቱ ለጃንሆይ የላከውን መልዕክት ይዘን የመጣን ነን፡፡ የእርሰዎ ዙፋን እንዲታፈር፣የኢትዮጵያ ዳር ድንበር እንዲከበር፣የተቀሰቀሰው ሠራዊትም መንፈስ እንዲረጋጋ፣ ጄኔራል አማንን ግርማዊነትዎ እንዲሾምልን ነው የጠየቅነው፤ጥያቄዎቹም የጦሩ እንጂ የእኛ አይደሉም"በማለት አለሳልሰው መመለሳቸውን የዓይን እማኙ ደበላ ዲንሳ ትውስታቸውን በምስክርነት መፃህፍ ላይ ገልጠው እናያለን፡፡

ወዲያው ጃንሆይ ቀዝቀዝ ብለው "ይህ እንኳን ይሻላል፤ ሹሙልን ብሎ መጠየቅ ያባት ነው፤ ለሁሉም መልሱን ማታ በሁለት ሰዓት አዳምጡ" የሚል ምላሽ ሰጡ፡፡ ልዑካኑ ቁርጥ ያለ መልስ ይዘን ካልሄድን ጦሩ ይገድለናል እያሉ በልስላሴ ሞገቱ፡፡ "እኮ ማታ በሁለት ሰዓት ጠብቁ!" አሏቸው ተቆጥተው፡፡ ይህም አጥጋቢ መልስ አልነበረምና ተገትረው ሲቀሩ ልጅ እንዳልካቸው "እሺ ማለታቸው ነው" ብለው ልዑኩን አሰናበቱ፡፡ እዚህ ላይ ጃንሆይ ሙሉ ለሙሉ መረታታቸውን እንረዳለን፡፡ እንምከርበት፣ እናጥናው የሚሉ የተለመዱ ቃላቶቻቸው የሉም፡፡ የኮሚቴውንም ተፅዕኖ በድርቅናው ስንረዳ "እምቢ የሚል ቃል የመናገሪያ ጊዜዎ አልፏል" የሚል መልዕክት ያለው ነው፡፡በዘውዲቱ ጊዜ ተፈሪን ያንግሱልን የሚል ግፊት እንደነበረው ሁሉ አሁንም ታሪክ ራሱን ደግሞ



ማዕረጋቸው በማይፈቅድ ሰዎች ግፊት የተባለውን መፈጸም ግድ ሆነ፡፡ሰው የዘራውን ያጭዳልና፡፡

ጄኔራል አማን የደርጉ ሊቀመንበር ሆነው ተሾሙ፡፡ ደርግ ንጉሡን ማስወገድ የሚለው ሀሳብ አስደንጋጭ መስሎ እንዳልታየው ዛሬ ይህን መሰል ተግባር በኃይል ማስፈፀሙን ሲረዳ ዘውዱ እየቀለለበትና አስፈሪ ሀሳብም እንዳልሆነ በውል ተረዳ፡፡ ጃንሆይም እጅ መስጠታቸውን ለራሳቸው ከማሳመን በቀር ሌላ ምርጫ አልነበራቸውም፡፡

ሻለቃ መንግስቱ አማንን ከፊት አስቀድመው አሯሯጭ አደረጓቸው፡፡ ደርግ አሁን በአማን ሹመት የጦሩን እይደግፈኝ ይሆን? ስጋት ካስወገደ በኋላ የቀረው የሲቪል ኅብረተሰቡን ድጋፍ ሊያስገኝለት የሚችል ተግባርን መፈፀም ነበርና ፋታ ቢስ ሆነው ለወራት በጠቅላይ ሚኒስትርነት ያገለገሉትን፣ ደርግንም ከመነሻው ሲበትኑት ሞክረው ያልተሳካላቸውን ልጅ እንዳልካቸው መኮንንን ሽሮ በሌላ ታዋቂ ግለሰብ መተካት አሰኘው፡፡ ለዚህ ስልጣን ታጭተው የነበሩት ሀዲስ አለማየሁ ነበሩ፡፡ ነገር ግን "እኔ የስነ-ጽሁፍ እንጂ የፖለቲካ ሰው አይደለሁም ይቅርብኝ" አሉ፡፡ እናም በጨዋነታቸው የሚታወቁት የራስ እምሩ ልጅ፤ ልጅ ሚካኤል እምሩ ለሹመቱ ታጩ፡፡

በአምባሳደርነት አገራቸውን ያገለግሉ ነበርና በአባታቸው በኩል ተልኮባቸው መጥተው ሁለተኛው ሲቪል ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው ተሾሙ፡፡ ደርግ ልጅ ሚካኤልን የመረጠበትን ምክንያት ሲገልፅም፤ ታማኝና በኢትዮጵያ ህዝብ ዘንድ ተወዳጅ፣ በሠራዊቱም ዘንድ የሚከበሩ መሆናቸውን ነው፡፡ ይህንንም ህዝቡ በቀላሉ ተቀበለው፡፡ ምክንያቱም በተለይ አባታቸው ራስ እምሩ ከጃንሆይ ዘመን ባለሥልጣናት ውስጥ ብቸኛው በክፉ የማይነሱና ለደሃ አዛኝ፣ ያላቸውን ሐብት ለድሆች አከፋፍለው የሰጡና ምንም አይነት የዘረፋ ተግባር ያልፈፀሙ መሳፍንት መሆናቸው ይታወቃልና ነው፡፡ ከጃንሆይ ጋርም ከልጅነታቸው ጀምሮ አብረው በአንድ ላይ ያደጉ ነበሩ፡፡ ልጃቸውም በአባታቸው የወጡ መሆናቸው ስለሚታወቅ ጥሩ ዘዴ ነበር ደርግ የዘየደው፡፡ ከዚህም በላይ ሚካኤል እምሩ የተማሩ ናቸው፡፡ የአስተዳደር ችሎታና ልምድም ነበራቸው፡፡ ይህም ሲሆን ተሻሪው ሚኒስትር ልጅ እንዳልካቸው "ቦታዎ እስር ቤት ነው" ተባሉና አስለቅመው አሳስረዋቸው ከነበሩት ባለሥልጣናት ጋር ተቀላቀሉ፡፡

ልጅ ሚካኤል እምሩ ደርግ ፊት ቀርበው የተሰጣቸውን ኃላፊነት ለመወጣት ፈቃደኛ መሆናቸውን ገልጠው የጠቅላይ ሚኒስትርነት ስራቸውን ጀመሩ፡፡ አገሪቱ ከባድ ውጥረት ውስጥ ነበረችና የደርግ ዓላማ የተጠበቀውን ለውጥ እንደሚያመጣ ሂደቱ እየገለፀ መሆኑን በመረዳት የህዝብ ድጋፍ ይጎርፍ ጀመር፡፡

አሁን ለደርግ የቀረው እንቅፋት የለም፡፡ በጃንሆይ ዙሪያ የነበሩ ወፋፍራም ባለሥልጣናት ሁሉም ተለቅመው አልቀዋል፡፡ የቀሩት ጃንሆይና ጥቂት አሽከሮቻቸው ብቻ ናቸው፡፡ ጃንሆይ ሐምሌ 16 ቀን 1966 ዓ.ም የመጨረሻውን የልደት በዓላቸውን በቤተ-መንግስት ውስጥ አክብረዋል፡፡ ያውም ብቻቸውን፡፡ 82ኛ ዓመታቸውን መሆኑ ነው፡፡ እንዲት የልደት በዓል ትቀራቸው ይሆናል፡፡ እሷንም በእስር ያሳልፏታል፡፡

ጃንሆይ ፍዝዝ ... ብለዋል፡፡ባለሥልጣኖቻቸው ሁሉ ሲለቀሙ አንዲት የተቃውሞ ድምፅ አላሰሙም፡፡ ደርግ ሂደቱን ቀጥሏል፡፡ቅርንጫፎቹን መልምሎ ከጨረሰ በኋላ ወደ ሀብት ወረሳ አመራ፡፡ጃንሆይ በከፍተኛ የአክሲዮን ድርሻ ይቆጣጠሩት የነበረውን የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ ፋብሪካንና የአንበሳ አውቶቢሶችን ደርግ ወረሰ፡፡እነዚህንና ሌሎች መሰል የንጉሣዊ ቤተሰቡን የግል ሐብት ወደ ራሱ አዞረ፡፡ እነዚህንም ድርጊቶች ለህዝብ በሚዲያ እያሳዬ ጃንሆይን ህዝቡ እንዲጠላ አደረገ፡፡

ወደመጨረሻው ግድም ጥቂት የደርግ አባላት ወደ ቤተ-መንግስት ጎራ ብለው የእልፍኝ አስከለካያቸውን ጄኔራል አሠፋን ለማሰር ሲሞክሩ ከፊዘዙበት ነቃ በማለት ልዑካኑ ሰምተውት በማያውቁት ከባድ የቁጣ ጩኸት፤ "የፈለጋችሁትን ውሰዱ! እሱን ግን አትነኩም!" ብለው እንባረቁባቸው፡፡ "ለምን እሱን ትወስዳላችሁ? ምን አደረገ ነው የምትሉት? ተውት! ያለበለዚያ እኛንም እሰሩን!" አሉ፡፡ ደርግ "በቃ ይቅር" ብሎ ለጊዜው ተወላቸው፡፡ ጄኔራሉ ማታ ወደቤታቸው ሲሄዱ ግን ተይዘው ታሰሩ፡፡ ጃንሆይ በማግስቱ ሁኔታውን ሰሙ፡፡ ከማዘን በቀር ምንም አላሉም፡፡ በመጨረሻ አቶ ሽመልስ አዱኛ የተባሉት ሰው ለደርግ የምሰጠው ሚስጥር አለ አሉና የደርግ አባላቱ እንዲያይላቸው ጠየቁ፡፡አባላቱ ብቻ ተሰብስበው አዩት፡፡ ጆናታን ዲምቢልቢ የተባለው እንግሊዛዊ ጋዜጠኛ የቀረፀውን "የተደበቀ ረሃብ" የሚል ርዕስ የሰጠውን፤ የወሎ ህዝብ በረሃብ ሲረግፍ የሚያሳየውን ፊልም ነው፡፡ ፊልሙ እንግሊዝ አገር ታይቷል፡፡ይህን አሰቃቂ ፊልም ያዬ ኢትዮጵያዊ ብቻ ሳይሆን፣ ማንኛውም ሰብዓዊ ፍጡር እንባውን መቆጣጠር አይችልም፡፡ የደርጉ አባላት እየዘገነናቸው አይተው ጨረሱትና ለኢትዮጵያ ህዝብ የሚያሳዩበትን ጊዜ መጠበቅ ጀመሩ፡፡ፊልሙን በጥንቃቄ ለጥቂት ጊዜያት አስቀምጠውም እንደመጨረሻ ጥይት ሊጠቀሙበት ፈለጉ፡፡ፊልሙ ብቻውን የጃንሆይን አገዛዝ ህዝቡ አንቅሮ እንዲተፋው የማድረግ ኃይል ቢኖረውም፤ ደርግ ግን የበለጠ ለማድረግ ሲል ከፊልሙ ጎን ለጎን ጃንሆይ ውሾቻቸውን በቅንጦት ሲመግቡና ሌሎች መሰል የቤተ-መንግስት ፌሽታዎችን አጣምሮ እያነፃፀር ለማቅረብ ፈለገ፡፡ ኢዲቲንጉም የተዋጣለት ሆነ፡፡የደርግ አባላት በነሐሴ ወር መጨረሻ ስለንጉሡ ቀጣይ



ዕጣ ፋንታ መወያየት ጀመሩ፡፡ምን እናድርጋቸው? በሚል፡፡ጳጉሜ 4 ቀን 1966 ዓ.ም አባላቱ ተሰብስበው በእጅ ብልጫ የወሰኑት ውሣኔ፤"ከዙፋን ማውረድ" የሚል ሆነ፡፡

ጳጉሜ 5 ቀን 1966 ዓ.ም ደግሞ አባላቱ "ስዊዝ ባንክ ብር አለዎትና ለኢትዮጵያ ህዝብ ይስጡ" ብለውሞገቷቸው፡፡ "ገንዘብ የለንም" ብለው መለሷቸው፡፡ መስከረም 1 ቀን 1967 ዓ.ም ምሽት ላይ የኢትዮጵያ ህዝብ የዘመን መለወጫ በዓልን አክብሮ ሁሉም በየቤቱ ሲከተት ደርግ "እኛ ለህዝብ የምንሰጠው ስጦታ የለንም፡፡ ያለን ይህ ነው" በማለት ያ ዘግናኝ ፊልም ለህዝቡ በቴሌቪዥን ተላለፈ፡፡ ሁሉም ኢትዮጵያዊ የቁጣ እንባውን አነባ፡፡ ለንጉሡም ፍፁም ጥላቻ እንዲኖረው ሆነ፡፡ ደርግ ባየነው መልኩ ተመስርቶ ንጉሣዊ አገዛዙን ቦርቡሮ ቦርቡሮ እቅዶቹን ሁሉ በአግባቡ አከናውኖ እዚህ ደረጃ ደረሰ፡፡ በተወለደ በአጭር ጊዜ ውስጥ አደገ፡፡ ብዙዎቹ አዝጋሚ ሂደት ቢሉትም ከኢትዮጵያ ህዝብ ባህል እምነትና ንቃተ ህሊና አንፃር፣ እንዲሁም ከህዝቦች ታሪክና ልማድ ተነስቶ ሲመዘን (ምንም እንኳ ሁሉም ለውጥ ፈላጊ ሆኖ ቢታይም) ዘውዳዊውን ኢትዮጵያዊ ስርዓት በአንድ ጊዜ ደንፍቶ በደራሽ አብዮት ማስወገዱ ከፍተኛ የርስ በርስ ፍጅት ማስከተሉ የማይቀር ይሆን ነበር፡፡ በቀለም ትምህርት ብዙ ያልገፉት የደርግ አባላት የተጓዙበት መንገድ ግን በአዝጋሚነቱ ውስጥ ፈጣንነቱ የሚገለፅ ነው፡፡ በወቅቱም ተአማኒነትን ከሁሉም ዘንድ አስገኝቶላቸዋል፡፡ ለዚህ ሁሉ ሂደት ሻለቃ መንግስቱ ትልቁን ስራ ሰርተዋል፡፡ በእስር ላይ ያሉ አባላትም ይህንኑ ነው የሚሉት፣

ለደርግ ብዙ ምሁራን በግንባር እየቀረቡ ምክር ይለግሱና ንጉሡን እንዲያወርዱ ግፊት ያደርጉ ነበር፡፡ ከዚህም ባለፈ አንድ የደርግ አባል ምስክርነታቸውን ሲሰጡ "... በተለይ ሻለቃ መንግስቱ ኃይለማርያም ማታ ማታ ከለውጥ ፈላጊ ምሁራን ብቻ ሳይሆን፤ ከደጃዝማች ከበደ ተሠማ ጋር እየተገናኙ በተከታይ ቀን አዳዲስ ሀሳብ ይዞ ይመጣ ነበር፡፡ ሁላችንም በአንድ አስተባብሮ ከውሣኔ ያደረሰን ሻለቃ መንግስቱ ነበር" ብለዋል፡፡

ተጀምሮ እስኪጨረስ የሒደቱ አራማጅ "አባላቱ" ይባሉ እንጂ በአንድ መንግስቱ ሀሳብ፣ እቅድና ውሣኔ እንዲሁም የተግባር እርምጃ ብቻ ደርግ የደርግነቱን ህልውና ማግኘቱን የካደም የሚከድም አባል የለም፡፡

ከተለያዩ የጦር ክፍሎችና ከፖሊስ ሠራዊት ጭምር ተውጣጥተው፤ ተደራጅተው ደርግን የመሠረቱ አባላት ስም ዝርዝር የሚከተለውን ይመስላል፡፡ የአባላቱን የቀለም ትምህርት በሚመለከት፣ ከፍተኛው የሻለቃ አጥናፉ አባተ 12+4፣ዝቅተኛው ምንም ያልተማረ ሲሆን፤ ብዙዎች 7 እና 8፣ እንዲሁም 11 እና 12ኛ ክፍል መሆናቸው ብቻ ሳይሆን፤ 3ኛና 4ኛ ክፍሎችም ቀላል ቁጥር አልነበራቸውም፡፡ 12+3፣ 12+2 ድረስ የገፉም

ነበሩ፡፡ ይህም ሲባል ከደርግ ምስረታ በኋላ "በጣት የሚቆጠሩት" በአገር ውስጥና በውጭ ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ መደረጉ መዘንጋት የለበትም፡፡

ደርግ ሲመሠረት የነበራቸውን ማዕረግና ስም ስናይ ከተለያዩ የጦር ክፍሎች መውጣጣታቸው እንዳለ ሆኖ፤ በየክፍላቸው የነበራቸው የስራ ድርሻም የተለያዩ እንደነበርና በየጊዜውም የማዕረግ እድገት እያገኙ እንደሄዱ ተረድተን እንቀጥል፡፡



1. ሻለቃ አጥናፉ አባተ
2. ሻለቃ አባተ መርሻ
3. ሻለቃ አበበ በላይነህ
4. ሻለቃ አስራት ደስታ
5. ሻለቃ ፋንታዬ ይህደጎ
6. ሻለቃ ጎሩይ ኃይለሰላሴ
7. ሻለቃ ተስፋዬ ገብረኪዳን
8. ሻለቃ መንግስቱ ኃይለማርያም
9. ሻለቃ ዘለቀ በየነ
10. ሻለቃ እሡፋ መኮንን
11. ሻለቃ ሲሳይ ሐብቴ
12. ሻለቃ ብርሃኑ ባይህ
13. ሻለቃ ፍስሐ ደስታ
14. ሻለቃ ጌታቸው ሽበሺ
15. ሻለቃግርማ ኃይለገብርኤል
16. ሻለቃ ሐዲስ ተድላ
17. ሻለቃ ደምሴ ደሬሳ
18. ሻለቃ ከተማ አይተንፍሱ
19. ሻለቃ ኪሮስ አለማየሁ
20. ሻለቃ እንዳለ ተሰማ
21. ሻለቃ መኩሪያ ኃይሉ
22. ሻለቃ ናደው ዘካርያስ
23. ሻለቃ ነጋሽ ተስፋፅዮን
24. ሻለቃ ሽመልስ ሙሉጌታ
25. ሻለቃ ተካ ቱሉ
26. ሻለቃ ደበላ ዲንሳ
27. ሻለቃ መለሠ ኃይሌ
28. ሻለቃ ገብረየስ ወልደሃና
29. ሻምበል የማነ ተስፋንጉስ
30. ሻምበል ካሳሁን ታፈሰ
31. ሻምበል ካሣዬ አራጋው
32. ሻምበልሚካኤል ገብረንጉስ
33. ሻምበልሞገስ ወልደሚካኤስ
34. ሻምበል የኋላሸት ግርማ
35. ሻምበል ተፈራ ደነቀ
36. ሻምበል ውብሸት ደሴ
37. ሻምበል ንጉሴ ፋንታ
38. ሻምበል መለሰ ማሩ
39. መቶ አለቃ ዓለማየሁ ኃይሌ

40. መቶ አለቃ ተሰማ በላይ
41. መቶ አለቃ ዓሊ ሙሣ
42. መቶ አለቃ በላይ ቢተው
43. መቶ አለቃ በዕውቀቱ ካሣ
44. መቶ አለቃ ፍቅረስላሴ ወግደረስ
45. መቶ አለቃ መላኩ ተፈራ
46. መቶ አለቃ ገበየሁ ተመስገን
47. መቶ አለቃ ስለሺ በየነ
48. መቶ አለቃ ግርማ ፍስሃ
49. መቶ አለቃ ኃይሌ መለሰ
50. መቶ አለቃ አሸብር አማረ
51. መቶ አለቃ ተሰፋዬ ተክሌ
52. መቶ አለቃ ስለሺ መንገሻ
53. መቶ አለቃ ግርማ አየለ
54. መቶ አለቃ ንጉሴ ነጋሣ
55. ሻ/ ባሻ ማንመክቶት ወንድማገኝ
56. ሻ/ል ባሻ ግዛው ወልደሚካኤል
57. ባሻ ታደሰ አደራ
58. ባሻ ከበደ ዓሊ
59. ማስተር ሠርጀንት ደሣለኝ በላይ /አየር ኃይል/
60. ሃምሳ አለቃ ጌታሁን አቦዬ
61. ጁኒየር ኤክማን ዮሐንስ ፍትዊ /አየር ኃይል/
62. ማስተር ሠርጀንት ማሞ እጅጉ /አየር ኃይል/
63. ሃምሳ አለቃ ተፈራ ወልደመስቀል
64. ሃምሳ አለቃ ከበደ ክብረት
65. ሃምሳ አለቃ ንጉሴ ፋንታ
66. ሃምሳ አለቃ ደመቀ ባንጃው
67. ሃምሳ አለቃ ነሹ አለማየሁ
68. ሃምሳ አለቃ ታምራት ፈዬ
69. ሃምሳ አለቃ ኃይሌ ገበየሁ
70. ሃምሳ አለቃ አድማሱ አየለ
71. ሃምሳ አለቃ ጴጥሮስ ገብሬ
72. ሃምሳ አለቃ ተፈራ ጅፋር
73. ሃምሳ አለቃ ግዛው ወልደሚካኤል
74. ሃምሳ አለቃ ጥሩነህ ኃይለስላሴ
75. ሃምሳ አለቃ ገብረሀይወት ገብረፃድቅ
76. ሃምሳ አለቃ ከበደ አበጋዝ
77. ሃምሳ አለቃ እበራ አጋ
78. ሃምሳ አለቃ አክሊሉ በላይነህ



79. ሃምሳ አለቃ በቀለ ደጉ
80. ሃምሳ አለቃ ተገኝወርቅ ተሰፋ
81. ሃምሳ አለቃ ለገሠ አስፋው
82. ሃምሳ አለቃ ይልማ ከበደ
83. ፔቲ ኦፊሰር ትምራት ፈረደ /ባህር ኃይል/
84. ፔቲ ኦፊሰር ሚካኤል አስገዶም /ባህር ኃይል/
85. ሲኒየር ቴክኒሽያን ደምሰው ካሳዬ /አየር ኃይል/
86. ሲዲኒግ ቴክኒሽያን ገሠሠ ወልደኪዳን /አየር ኃይል/
87. አስር አለቃ አለማየሁ አየለ
88. አስር አለቃ ፍስሃ አንደቶ
89. አስር አለቃ በጋሻው ጉርሜሳ
90. አስር አለቃ ኃይሉ በላይ
91. አስር አለቃ ግርማ ቡርቃ
92. አስር አለቃ መንግስቱ ገመቹ
93. አስር አለቃ ንጉሴ ወልዴ
94. አስር አለቃ ሙሉጌታ አብርሃም
95. አስር አለቃ ግርማ አድማሱ
96. አስር አለቃ ገብረሀይወት ገብረእግዚአብሔር
97. አስር አለቃ ፍቅሬ ዘርጋባቸው
98. አስር አለቃ ጌታቸው አረጋ
99. አስር አለቃ ዳምጠው ገረመው
100. አስር አለቃ ጌታቸው ተቀባ
101. ም/ል አስር አለቃ አራጋው ይመር
102. ተራ ወታደር ደምሴ አብተው
103. ተራ ወታደር ደጀኔ ወንድምአገኘሁ
104. ተራ ወታደር ደምስ አላምረው
105. ተራ ወታደር ገዛኸኝ ወርቁ
106. ተራ ወታደር በጋሻው አታላይ
107. ተራ ወታደር ዓለማየሁ ከልካይ
108. ተራ ወታደር ፀጋዬ ጥሩነህ
109. ተራ ወታደር ገብረጊዎርጊስ ብርሃኔ

ደርግ በእነዚህ አባላት ሰብሰብ ተመስርቶ፤ ነገር ግን ከጅምሩ አባል ያልሆኑትን ሁለት ጄኔራሎች የደርግ ሊቀመንበር አድርጎ አሳይቷል፡፡ በዚህ መሠረት ጄኔራል አማን 2 ወር፣ ጄኔራል ተፈሪ በንቲ 2 ዓመት በሊቀመንበርነት የቆዩ ሲሆን፤ ከዚያ በኋላ ያለውን ጊዜ መሪነቱን ይዘው የቀጠሉት ሻለቃ መንግስቱ ናቸው፡፡ ሁለቱ ጄኔራሎች ስለተጨመሩም ነው ብዙ ጊዜ የደርግ አባላት ቁጥራቸው 111 ተደርጎ ሲዘረዘር የምናየው፡፡

የደርጉ ሊቀመንበር መንግስቱ ግንቦት 19 ቀን 1933 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ የተወለዱ ናቸው፡፡ ውልደትና እድገታቸውን በሚመለከት ጥርት ያለ ትንታኔ አናገኝም፡፡ ብዙዎች የደጃዝማች ከበደ ልጅ ናቸው ሲሉ፤ ሌሎች ደጃዝማቹ አጎታቸው፣ አንዳንዶች የእናታቸው አባት አያታቸው፣ የቀሩት አጎታቸው አድርገው ጽፈውታል፡፡

ይህን ለማለት የሚያስችሉ በርካታ መነሻዎችም አሉ፡፡ ጥቂቶቹን ለመጠቃቀስ 1ኛ. ከዚያ ሁሉ የቀድሞው ሹማምንት ሳይታሰሩ የቀሩ መሆናቸው፣ ደጃዝማቹ የሞቱ እለት የቤተመንግስቱ ያማረ ምንጣፍ ሄዶ እንደተነጠፈላቸውና፤ መንግስቱ ለመጀመሪያ ጊዜ የቀድሞው ባለሥልጣናት ሞተው ያለቀሱትና ለቅሶ የደረሱት እሳቸው ዘንድ መሆኑ፣ የጃንሆይ ታማኝ ሆነው ሳለ፤ ነገር ግን የንጉሱን ሚስጥር ዘክዝከው ለመንግስቱ መግለፃቸው ... ወዘተ ይጠቀሳሉ፡፡

ሃምሳ አለቃ ኃይለማርያም ወልዴ ሳይቀሩ አሳዳጊው ነኝ እንጅ አባቱ አይደለሁም የሚል ቃል እንደተናገሩ ተጽፏል፡፡ የመንግስቱ እናት ቤተመንግስት ውስጥ ዝቅ ያለ ሥራ እየሰሩ ይተዳደሩ ነበር መባሉም ለውዝግቡ በር ከፍቷል፡፡ ምንም ቢሆን ግን "ውልደትን" በተመለከተ ባለቤቱ የተናገረውን መቀበል የውዴታ ግዴታ ነውና እንዲህ ነው፤ እንዲያ ነው ብሎ መደምደሙ የአንድ ፀሐፊ ተግባር ስላልሆነ ትቼዋለሁ፡፡ ምክንያቱም ከላይ የተጠቃቀሱትን አይነት አንታኔዎች መንግስቱ "የሃሰት ወሬ ነው" ብለው ዛሬ ድረስ አስተባብለዋልና ነው፡፡ መንግስቱ እንዲታወቁ የፈለጉት በኢትዮጵያዊነታቸው ብቻ እስከሆነ ድረስም ዘር መዘርዘሩ አስፈላጊ አይደለም፡፡

እናም በአዲስ አበባ ጊዎርጊስ ብተክርስቲያን አካባቢ ተወልደው እናታቸውን በ9 ዓመታቸው በሞት ያጡት መንግስቱ በጃንሆይ ጊዜ በውትድርና ተሰማርተው ከነበሩት ከአባታቸው ከሃምሳ አለቃ ኃይለማርያም ወልዴ ጋር ሲያድጉ፤ አባታቸው በየተመደቡበት አገር ከፋ፣ ጅማ፣ ድሬዳዋ፣ ሐረር፣ ... አብረው እየዞሩ የልጅነት ጊዜያቸውን ያሳለፉት የቀለም ትምህርታቸውን በመከታተል ነበር፡፡



ከዚያም የኢትዮጵያ ሠራዊት በእንግሊዞች አማካኝነት ሲደራጅ በቀረበው ሀሳብ መሠረት የጃንሆይ መንግስት ወጣት ልጆችን ከልጅነታቸው መልምሎ በወታደራዊና በቀለም ትምህርት አጎልብቶ በተለያዩ ዘርፎች እንዲያገለግሉ ማድረግ ሲጀምር ከእነዚህ ውስጥ አንዱ መንግስቱ መሆን ቻሉ፡፡

"የልጅ ወታደርነት" በሚል ስያሜው የሚታወቀው የዚያ ዘመን ምልመላ ከሞላ ጎደል መመዘኛው የነበረው ወላጆቻቸው በአርበኝነቱ ዘመን ያለቁባቸው፣ የባለሥልጣናቱ ይሁኝታና፣ በቀጣሪ መኮንኖች ዘንድ በቅርብ የሚታወቁ፣ እንዲሁም የወታደር ልጆችን ማዕከል ያደረገ ነበር፡፡ መንግስቱ የልጅ ወታደር ሆነው እንዲቀጠሩ ያስቻላቸው ተብሎ ሁለት ነገር ሲጠቀስ፤ አንዱ የወታደር ልጅ መሆናቸው፣ ሌላው በደጃአዝማች ከበደ ተሰማ እገዛና ይሁንታ እንደሆነ ይነገራል፡፡ ብቻ ግን መንግስቱ በ1946 ዓ.ም ወደ ውትድርና ገብተው እስከ 1950 ዓ.ም ድረስ የዕጩ መኮንኖችን ኮርስ በሆለታ ገነት የጦር ትምህርት ቤት ተከታትለው ከ19ኛው ዙር ተመራቂዎች ውስጥ አንዱ ሆነው፣ የምክትል መቶ አለቃነት ማዕረጋቸውን ይዘው ስራቸውን ጀምረዋል፡፡ በተለያዩ ጊዜያቶችም ሁለት ጊዜ ያህል ለትምህርት ወደ አሜሪካ ተጉዘው ስለመሣሪያ ይዞታና አስተዳደር ተምረው ተመልሰዋል፡፡ በሌሎች የጦር ክፍሎች ተመድበው ቢሰሩም፤ በዋናነት ግን በመሣሪያ ግምጃ ቤት ውስጥ ነው ረጅም ዓመታት ያገለገሉት፡፡ በመጨረሻም ወደ ሦስተኛ ክፍለ ጦር ተዛውረው የመሣሪያ ግምጃ ቤቱ ኃላፊ ሆነው ሐረር ውስጥ በማገልገል ላይ ሳሉ በክፍለ ጦሩ አዛዥ ብርጋዴር ጄኔራል ጥላሁን ቢሻኔ ተመርጠው ከሌሎች አባሎቻቸው ጋር ከሐረር ተነስተው አዲስ አበባ 4ኛ ክፍለ ጦር ጊቢ ውስጥ ገቡ፡፡ እዚያም መሪ ሆኑ፤ ከዚያ ወጥተውም ቤተመንግስት ገቡ፤ እዚያም መሪ ሆኑ፡፡

*አብዮቱ ሲፈነዳ*

አቶ ብርሃኑ ድንቄ በቄሳርና አብዮት መፃሀፋቸው መደምደሚያ ላይ አብዮትን በተመለከተ ያሰፈሩትን ሐተታ ሳስቀድም፤ "... ሪቮሉውሽን /አብዮት/ በማስነሳት በአንድ አገር ውስጥ የሚገኘውን ኢፍትህ፣ የመብት መነፈግ፣ ጭካኔ፣ ግፍ፣ የአስተዳደር ንቅዘት ለማረም በፍፁም የማይቻል ነው፡፡ የሰዎች ማኅበራዊ ድርጅት ከተቋቋመ ጀምሮ እስከዘመናችን ድረስ ብዙ ሪቮሊውሽኖች እንደተደረጉ በታሪክ አንብበናል፤ ጥቂቶቹንም በዘመናችን አይተናል፡፡ ግን ለሰው ልጅ ምን አተረፉለት?" ብለው በመጠየቅ መልሱን ከጆርጅ በርናንድ ሾው እንድንረዳ ይጋብዙናል፡፡ "Revolutions have never lighted the burden of tyranny: They have only shifted it to another shoulder." "አብዮቶች የጭካኔን ሸክም

አቃለው እያውቁም፤ ነገር ግን ወደ ሌላው ትክክ ያዛውሩታል" እንደማለት፡፡

አምባሳደሩ ሲቀጥሉ፤ "ይህ እውነተኛ ቃል ነው፡፡ ግን የሰው ልጆች አትኩረው ሊመረምሩትና ሊጠቀሙበት አልቻሉም፡፡ ሰዎች እንደሰዎች ሊያስቡና እንደሰዎች ሊኖሩ የሚችሉበት አንድ ዘዴ መገኘት አለበት፡፡ በበኩሌ በመንፈሣዊ ሪቮሉሽን አምናለሁ፡፡ በርግጥ መንፈሣዊ ሪቮሉሽን የቤተ-ክርስቲያን ቋንቋ አይደለም፡፡ እኔ ከቋንቋው ጉዳይ የለኝም፡፡ ቋንቋ ገለባ ነው፡፡ እኛ መፈለግ ያለብን በገለባው ውስጥ የሚገኘውን ፍሬ ነው፡፡ እውነተኛ መንፈሣዊ ሪቮሉሽናሪ የናዝሬቱ እየሱስ መሆኑን አውቃለሁ፡፡ እርሱ በባዶ ቋንቋ መጠቀምን አይፈቅድም፡፡ እርሱ ስለእውነትና ስለፍትህ ተናገረ፡፡ በባዶ ቋንቋ የሚያምኑ ፈሪሳውያን ትምህርቱን ተቃወሙ፡፡ ግን ዓለም የርሱን ትምህርት መከተል እስካልቻለ ድረስ ፍትህ ማግኘት አይቻልም" በማለት ጽሁፋቸውን ይደመድማሉ፡፡ *(ቄሣርና አብዮት ገፅ 69)*

የደርግ አብዮትስ? ብለን እንጠይቅ፡፡ እንዲያውም ጠያቂው ራሳቸው ጃንሆይ ይሁኑና መላሹ ኮሎኔል ዳንኤል ይሁን፡፡ በመንግስቱ ትዝታዎች ቁጠር 1 መጽሐፍ ውስጥ ከአልባሾቻቸው አንዱ ጃንሆይ በእስር ላይ በነበሩ ጊዜ ኮሎኔሉን ጠርተው እንዲህ ማለታቸውን ያስታውሳል፤ "... አንድ ቀን ጃንሆይ "ኮሎኔል ዳንኤልን ለመሆኑ እናንተ ዓላማችሁ ምንድነው?" ብለው ቢጠይቋቸው፤ ኮሎኔል ዳንኤል "ዓላማችን ዝቅ ያለውን ከፍ፤ ከፍ ያለውን ዝቅ ማድረግ ነው" አሏቸው፡፡ንጉሡም "አይሆንላችሁማ!" ብለው መለሱላቸው፡፡"

አብዮት ማለት ይህ መሆኑን ስንረዳ በጆርጅ በርናንድ ሾው አባባል ለመስማማት እንገደዳለን፡፡ ሌላው እንግሊዛዊ ጆርጅ ኦርዌል ደግሞ "አብዮት በመጀመሪያ ሁሉንም እኩል ያደርጋል፤ ነገር ግን ብዙም ሳይቆይ አንዳንዶች ይበልጥ እኩል መሆናቸውን ያውጃሉ" ብሏል፡፡ ኮሎኔል ዳንኤል "ዝቅ ያለውን ከፍ፤ ከፍ ያለውን ዝቅ" ሲሉ ከድጡ ወደ ማጡ ማለታቸው ነው ባይባልም፤ የእኩልነትን ፍልስፍና ገለፃቸው አያካትትም፡፡ ከፍ ያሉት ዝቅ ሲሉ ዝቅ ያሉት ከፍ ይሉና፤ ከፍ ብለው ይቀራሉ የማለት ያህል ነው፡፡ ስለዚህ በጆርጅ ኦርዌል አባባልም ልንስማማ እንገደዳለን፡፡ አብዮት የአንድ አገር ህዝብ የመንግስትን አገዛዝ ተቃውሞ፤ በትብብር አመፅ ያንን መንግስት በኃይል አስወግዶ በሌላ የመተካት ፍላጎትና ውጤት ነው፡፡ ከተሳካ በኋላ የሚተካው መንግስትም ያኛውን አገዛዝ ለመቃወም ያደረሱትን ብልሹ አሰራሮች አስወግዶ የተሻለ አስተዳደር ዘርግቶ ለውጥ ማምጣት ነው፡፡ ስለዚህ አብዮት ለውጥ ነውና አገርን ይለውጣል፡፡



የደርግ አብዮት ወደፊት እንደምናገኘው ያስገኛቸው ፍሬ ነገሮች አሉ፡፡ ነገር ግን የኢትዮጵያ አብዮት ከሌላው አገር አብዮት የሚለይበት የስልጣን አብዮት ሆኖ መቅረቱ ነው፡፡ መስከረም 2 ቀን 1967 ዓ.ም የደርግ ልዑካን ወደ ቤተ-መንግስት ሄደው ለጃንሆይ የአገዛዝ ዘመናቸው ማብቃቱን አረዷቸው፡፡

ደርጎች ገና ከጅምሩ በማንኛውም የኅብረተሰብ ክፍል እንዳይነቀፉ ልዩ ጥንቃቄ ያደርጉ ነበር፡፡ እያንዳንዷን እንቅስቃሴያቸውን አክብሮት በተሞላበት ሁኔታ ነው ያከናወኑት፡፡ በጄኔራል አማን አስማሪነት ሌሊቱን ሙሉ ጥበቃውን ሲያጠናክሩ አድረዋል፡፡ በቤተ-መንግስቱ ዙሪያ ታንክ ሳይቀር አጥምደው አስከብበዋል፡፡ በማለዳ ጃንሆይን ለማውረድ ሲሄዱም ሌላ ታሪክ ተፈጥሮ እንዳይወራባቸው ከጃንሆይ ጋር ራስ እምሩ በእማኝነት አብረው እንዲገኙ አድርገዋል፡፡ 13 ሆነው የሄዱት የደርግ ልዑካን፤ ቤተ-መንግስት የገቡት ማለዳ ላይ ነው፡፡ ጃንሆይ እንደተፈለጉ ተነግሯቸው ከፎቅ እየወረዱ ነውና ልዑካኑ ደንግጠው ጥቂት ጠበቁ፡፡ በዝግታ የመጡት ንጉሠነገስት በዙፋኑ አዳራሽ ባለው ወንበር ቀስ ብለው ተቀመጡ፡፡

ሻምበል ደበላ ዲንሳ የኮሚቴውን የውሣኔ ቃል ለጃንሆይ አነበቡ፤ "... ለአገርና ለህዝብ ደህንነት ሲባል በዛሬው ዕለት ግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃይለስላሴ ከስልጣን ወርደዋል፤ ለደህንነትዎ ሲባልም አስተባባሪው ኮሚቴ ወዳዘጋጀልዎት ቦታ እንዲሄዱ ተወስኗል..." የሚል ጭብጥ ያለው ሃተታ ተነበበላቸው፡፡ አንባቢው ከማንበባቸው በፊት የሰጡትን ወታደራዊ ሠላምታ እንብበው ከጨረሱ በኋላም ደገሙት፡፡ ጃንሆይ በዝምታ ተውጠው ደቂቃዎች አለፉ፡፡ ደርግ ንጉሱን ከስልጣን ለማውረድ በወሰነ ጊዜ አዋጅ አውጥቶ አዋጁንም በወታደራዊ ማርሽ ታጅቦ በመገናኛ ብዙሃን ለህዝብ እንዲቀርብ አድርጓል፡፡

"በኢትዮጵያ የኖረው ዘውድ በህዝቡ ዘንድ በቅን ልቦና የአንድነት ምልክት ሆኖ ታምኖበት ቢቆይም ለ50 ዓመታት አገሪቱን የመሩት ንጉስ ከህዝብ የተሰጣቸውን ስልጣን ለራሳቸውና በአካባቢያቸው ለሚገኙ ሰዎች በማዋል አገሪቱን አሁን ካለችበት ከፍተኛ ችግር ላይ በመጣላቸው፣

አሁን በእድሜ መግፋት ሳቢያ ይህን ከፍተኛ አገር የመምራት ኃላፊነት ሊሸከሙ የማይችሉ መሆኑን በመረዳት፤

ያለው የህዝብ ምክር ቤት አመራረጥ ዲሞክራሲን ያልተከተለ፣እስካሁን ያገለገለውም ለህዝብ ሳይሆን ለዘውዳዊው ስርዓት በመሆኑ፤የአገሪቱ መሠረታዊ ችግር የሆነው የመሬት ይዞታን የሚያሻሽል ሕግ ከማውጣት የተቆጠበ፤አባላቱም ከህዝብ የተሰጣቸውን ከፍተኛ ስልጣን ለግል መጠቀሚያ አድርገው በህዝብ ላይ ተጨማሪ ችግር እያደረሱ

በመሆኑና አሁን የምክር ቤቱ መኖር ለ"ኢትዮጵያ ትቅደም" መርህ እንቅፋት ስለሚሆን፣

የ1948ቱ ሕገ-መንግስት የተዘጋጀው ለንጉሱ የፈላጭ ቆራጭነት ስልጣን የሰጠ ለውጭው ዓለም ደግሞ ዲሞክራሲያዊ አስተዳደር ያለ ያስመስላል እንጂ እውነተኛ ዲሞክራሲ የሌለበት፣ ለህዝብ ጥቅም ታስቦ ያልተዘጋጀ፣ለሰው ልጅ ተፈጥሮ የሰጠውን መብትም ከንጉሠነገስቱ የተሰጠ የሚል፤ ኢትዮጵያን ለማስቀደም ለተጀመረው ህዝባዊ እንቅስቃሴና የኢኮኖሚ፣የፖለቲካና የሶሻል እድገት መሻሻል ተፃራሪ በመሆኑ፣የነበረው የመሣፍንት አገዛዝ ስርዓት ባስከተላቸው ጉድለቶች አገሪቱን በኢኮኖሚ፣በማኅበራዊና ፖለቲካ አዘቅት ውስጥ ስለጣላትና ባለንበት የመሸጋገሪያ ወቅት ልዩ ልዩ የፀጥታ ችግሮች በመፍጠራቸው ችግሮችን አስወግዶ አገሪቱን ወደፊት ለማራመድ የሚያስችል ለህዝብ ጥቅም የተሰለፈ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ለመፍጠር በመታሰቡ" በሚል የአዋጁ መግቢያ ተነበበ፡፡

አንድ አዲስ ስልጣን ያኘ ኢትዮጵያዊ መንግስት የተለመደውን ህዝብን የመሸንገል ተግባሩን ለማከናወን ከዚህ የተሻሉ ቃላትን መቀሸርና ማንበብ የሚጠበቅበት አይመስልም፡፡ "ስልጣን የህዝብ ነው" ይሉናል፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ስልጣን የህዝብ ሆኖ ያዩ ትውልድ ካለ ይመናቸው እንጂ በኢትዮጵያ ከዘውዳዊ አገዛዙ ማክተም በኋላ ሆኖ አያውቅም፡፡ ስንመለስ አዋጁ፤

1ኛ. ንጉሡን ከስልጣን ማውረድና በአልጋወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋወሰን መተካት፣

2ኛ. ንጉሡን የሚተኳቸው ንጉስ ከርዕሰብሔርነት ውጪ ምንም የፖለቲካና የአስተዳደር ስልጣን እንደማይኖራቸው፣(ሁለቱ አዋጆች ተግባራዊ አልሆኑም)

3ኛ. የሕግ መምሪያና መወሰኛ ምክር ቤት መዘጋቱን፣

4ኛ. የጦር ኃይሎች፣ የፖሊስ ሠራዊትና የብሔራዊ ጦር አስተባባሪ ኮሚቴ የመንግስትን አመራር መያዙን፣

5ኛ. የኢትዮጵያ ትቅደም መርህን የሚቃወም፣ የስራ ማቆም አድማና ሠላማዊ ሰልፍ ያለፈቃድ ማድረግና የህዝብን ፀጥታና ሠላም የሚነሳ ተግባር መፈፀም መከልከሉን፣

6ኛ. የኢትዮጵያ ትቅደምን መርህ ተቃውመው ወንጀል የሚፈጽሙትንና በቀድሞው መንግስት የዳኝነትና የአስተዳደር በደል የፈፀሙትን ያለአግባብ የመበልፀግ ወንጀል የፈፀሙትን ሰዎች ጉዳይ የሚመለከት ይግባኝ የሌለበት ፍርድ ቤት መቋቋሙን ደንግጓል፡፡

ወደጀመርነው ወዳጃንሆይ ዝምታ እንመለስ፡፡





ጃንሆይ የደርጉን ንባብ ሲያደምጡ

ደበላ ዲንሳ ለጃንሆይ ያነበቡትን በአንዲት ዓረፍተነገር የተዋቀረች መርዶ ያደመጡት ንጉስ ከደቂቃዎች ድንዛዜያቸው እንደመንቃት ብለው አንባቢውን ትኩር ብለው ማየት ጀመሩ፡፡ አልሄድም ቢሉስ? የሚል ውጥረት ይዟቸዋል ልዑካኑ፡፡ መልስ ሲጠፋ አንባቢው ወደራስ እምሩ ቀረብ አሉና "ልዑልነትዎ አንድ ያድርጉ እንጂ፡፡ ሰዓት እያለቀብን ነው፤ ግርማዊነታቸውን ፍጠኑ ማለት አልችልም" አሉ በአክብሮት፡፡

ራስ እምሩም ቁጭት ላይ ነበሩ፡፡ ምክንያቱም በተደጋጋሚ ለአብሮ አደጋቸው ጃንሆይ በቀና መንፈስ ለውጥ እንዲያደርጉ፣ ሕገ-መንግስቱ እንዲሻሻል፡ ስርዓቱ እንዲለወጥ ወንድማዊ ምክራቸውን ሲለግሱ የኖሩ ናቸው፡፡ ጃንሆይ ግን እንዲህ ያለውን ጉትጎታ አይወዱትም ነበርና በአምባሳደርነት እየሾሙ ያርቋቸው ነበር፡፡ ቁጭታቸው ከዚህ የመነጨ ነው፡፡ አሁን ግን ራስ እምሩ ወደ ጃንሆይ ጠጋ ብለው "እንዳሉት ማድረግ ነው እንግዲህ፤ ሁሉም ነገር አልቆለታል፤ ሌላ አማራጭ የለንም" አሏቸው፡፡ ጃንሆይ ወደ አብሮአደጋቸው ቀና አሉና በማይሰማ ሹክሹክታ ጥቂት ቃላት ተለዋወጡ፡፡

በመጨረሻም ንጉሡ መናገር ጀመሩ፤ "ያነበባችሁትን ሠምተናል፤ የኢትዮጵያ ንጉሠነገስት ስንሆን ስም ብቻ አይደለም፤ ቢሆንም በየጊዜው የሚለዋወጠው ነገር ደግሞ ለአገር የሚጠቅም ነገር እስካለበት .... ያነበባችሁትን ሰምተናል፡፡ የኢትዮጵያን ታሪክ ጠብቃችሁ ማልማት ከቻላችሁ የእኛ ታሪክ እዚህ ላይ ያበቃል፤ ካልቻላችሁ የናንተ ታሪክ እዚያ ላይ ይቆምና የእኛ ይቀጥላል፡፡ አገራችንንና ህዝባችንን በምንችለው አገልግለናል፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ እድል የእኛን መወገድ የሚጠይቅ ከሆነ

ከዚህም በላይ በክቡር ዘበኛ አዛዥ በጀኔራል አበበ ተቀነባብሮ የነበረውን ደርግን የመበታትን ዘመቻ እንደነው ጃንሆይ "አንተ ሰው አርፈህ ተቀመጥ" ብለው ኳስትተዋቸዋል፡፡

ጃንሆይ የህዝብ አመፅ ከተነሳ በኋላ የሚወሰድ የኃይል እርምጃ መጨረሻው ታሪክን ማበላሸት መሆኑንም ያውቃሉ፡፡ ባለፈው ምዕራፍ አልጋወራሽ እያሉ በጃንሜዳ ለተሰበሰበው ህዝብ ጽፈው የላኩት መልዕክት ላይ ደጋግመው ሹሞቻቸውን ሲያስጠነቅቁ አንብበናል፡፡ "ለወደፊቱ ይህን የመሰለ የህዝብ መሰብሰብና በመንግስት ስራ መግባት የሚያስፈልግ አይደለም..." እያሉ የሩሲያን አብዮት ምሳሌ እየሰጡ ያስጠነቀቁትም ህዝብ ካመፀ መንግስት ዋጋ እንደሌለው ተረድተው ለማስረዳት የተጠቀሙት ምሳሌ ነበር፡፡ ከእነዚህ ነገሮችና ከወቅቱ ነባራዊ ሁኔታ አንፃር በመነሳት መንግስታቸው ማብቃቱን ስለተረዱት ቀሪውን ለእድል ብቻም ሳይሆን ለፈጣሪ ትተውታል ሊባል ይችላል፡፡ ምንም ቢሆን ግን ጃንሆይ በተፈጥሮ ባህሪያቸው ጠላታቸውን ካላንበረከኩ እንቅልፍ የማይተኙ ነበሩና አንድ ነገር ያደርጋሉ ተብሎ ይጠበቅ ነበር፡፡ ግን ምንም አላደረጉም፡፡ ለምን? አርጅተዋል ነው መልሱ፡፡

ጃንሆይ የቅርብ ሰዎችም እንደሚመሰክሩት በቀን 20 ሰዓት ያህል እየሰሩ የኖሩ ናቸው፡፡ እረፍትም ሆነ ከስልጣን ገለል ማለት አልፈለጉም፡፡

የጃንሆይ እርጅና ለውድቀታቸው እንደ አንድ ግብአት የሚቆጠር ነው፡፡ እሳቸው አርጅተው በወሣኝ ወሣኝ ጉዳዮች ላይ አፋጣኝ እርምጃ መውሰድ ሲያቅታቸው በዙሪያቸው ያሉ ሹማምንት ሊያግዟቸው ይገባ የነበረ ቢሆንም፤ በጣት ከሚቆጠሩት በቀር ሌሎች ንቅዝ ስለነበሩ እንኳን የዙፋኑ ጠበቃ ሊሆኑ ለራሳቸው ህልውና እንኳ ጥብቅና የሚቆሙበት ደረጃ ላይ አይገኙም፡፡ ይህም ስለሆነ ሹማምንቱ "ከሸተቱ አይቀር ጥንብት ክርፍት" በሚል መርህ ንቅዘታቸውን አፋጥነው ቀጥለው የግል ሐብት ሲያጋብሱ በእሳት ላይ ቤንዚን እንደሚባለው አደረጉት፡፡ ጃንሆይ ብቻቸውን ነበሩ፡፡ በዚህም ላይ በእርጅና ምክንያት ፈዘዋል፡፡ ያለማንገራገር ታስረዋል፡፡

የጃንሆይን እርጅና በሚመለከት ከዶ/ር ኃይለገብርኤል ደግለኝ አንድ ገጠመኝ እንስማ፡፡ በመውደቂያቸው የመጨረሻ ወራት ላይ አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር ሚካኤል እምሩ አዲሱን ተሿሚ መርጠው በጃንሆይ ለማሾም ወደቤተመንግስት ያመራሉ፡፡ ለትምህርት ሚኒስትርነት የተመረጡትን ዶ/ር ኃይለገብርኤልን ይዘው ጃንሆይ ፊት በመቅረብ "ጃንሆይ አዲሱ የትምህርት ሚኒስትር እነሆ" ሲሉ ጃንሆይ እንደመባነንም እንደመደንገጥም ብለው አንድ ጥያቄ ሠነዘሩ፡፡ "ትምህርት ምንድነው?" ተሿሚው ያልጠበቁት ጥያቄ ቢሆንም አንዳንድ ገለፃዎችን ስለ ትምህርት



ማድረግ ሲጀምሩ፤ ጃንሆይ "አይደለም!" ብለው አቋረጧቸው፤ ቀጠሉና "ትምህርት ማለት ምን ማለት ነው?" ካሉ በኋላ ራሳቸው ንጉሡ መልስ መስጠት ጀመሩ፡፡ ከንግግራቸው ውስጥ ግን አንዱም ቃል ከትምህርት ጋር የማይገናኝና ቅብጥርጥር ያለ የቅዠት ገለፃ ነበር፡፡ "ይህ አንድ ነገር አስረዳኝ" ይላሉ ምሁሩ ተሿሚ ዶ/ር ኃይለገብርኤል "ለካንስ ንጉሡ በእርጅና ምክንያት በትክክል ማሰብ አቅቷቸው ነበር" በማለት የተሰማቸውን ሐዘን እያስታወሱ ተርከዋል፡፡ (አዲስ ነገር 2001 ዓ.ም) ትምህርት ጥንቃቄ ያስፈልገዋል ብለው ለረጅም ዓመት የትምህርት ሚኒስትርን ስልጣን ራሳቸው ነበር የያዙት፡፡ በመጨረሻ ግን የቃሉ ትርጉም ሳይቀር ጠፋባቸው፡፡ እነዚህን የመሳሰሉ የመርሳትና የመሳት ባህሪ በተደጋጋሚ ማሳየት የጀመሩት ገና ከስልጣን ሳይወርዱ ጀምሮ ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ ያለ ንጉስ ዘዴው ቢጠፋበት አይገርምም፡፡

ጃንሆይ ከቤተ-መንግስት ተወስደው 4ኛ ክፍለ ጦር ጊቢ በቁም እስር ላይ ቆይተው፤ እንደገና ደግሞ ወደቤተ-መንግስቱ ጊቢ ተመልሰው በአንድ መካከለኛ ቤት ገብተው እንዲኖሩ(እንዲታሰሩ) ከተደረገ በኋላ ፍፃሜያቸውም እዚያው ሆኗል፡፡

በቁም እስር ላይ በነበሩበት ጊዜም ምግብ ከቤተ-መንግስት እየሄደላቸው፤ አሽከሮቻቸው በስርዓቱ እያገለገሏቸው፤ ዘመዶቻቸው እየጠየቋቸው በክብር እንዲያዙ መደረጉን የደርግ አባላቱ መንግስቱን ጨምሮ ይገልፃሉ፡፡ እንዲያውም ልዕልት ተናኘወርቅ ከእኛ ጋር ትቀመጥ ስላሉ ደርግ ፈቅዶ አብረዋቸው እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡

ደርግ ከ4ኛ ክፍለ ጦር ለቆ ወደ ታላቁ ቤተ-መንግስት በማምራት ቢሮውን የጃንሆይ ጽ/ቤት የነበረውን አድርጓል፡፡ በጊቢው ውስጥ አፄ ምኒልክ አሠርተው ይኖሩበት በነበረው አሮጌ የእንጨት ፎቅ ስር አንድ መለስተኛ ቪላ ነበርና ያ የጃንሆይ መኖሪያ እንዲሆን ተደረገ፡፡ በጊቢው ውስጥ አበቦችና አትክልቶች የሚገኙ ሲሆን፤ ለጃንሆይ የሚከፋ አልነበረም፡፡ አጥሩንም ሰፋ አድርገው ሠርተው እንዳይወጡ በጥብቅ ማስጠበቅ ጀምረዋል፡፡ ከደርግ አባላት ውስጥም ከ3 የማይበልጡ ሰዎች ብቻ እየሄዱ ያነጋግሯቸው ነበር፡፡ ዋናው ሻለቃ መንግስቱ ናቸው፡፡

ጃንሆይ አንዳንድ ጊዜ እንደመቃዠት ያድርጋቸው እንጂ፤ ብዙ ጊዜ በትክክል ሲናገሩ ተደምጠዋል፡፡ መንግስቱ ኃይለማርያም ትዝታቸውን ሲገልፁ፤ "ከስልጣን ከመውረዳቸው በፊትና በኋላ በጠቅላላው ያነጋገርኳቸው ሦስቴ ወይም አራቴ ቢሆን ነው፡፡ ብቻዬን ሳይሆን ከኮሎኔል አጥናፉ ጋር (ያኔ ሻለቃ) እንዲሁም ከሌሎች ጥቂት የደርግ አባሎች ጋር፡፡ በመጀመሪያ የሄድነው አራተኛ ክፍለ ጦር እንደደረሱ ከሌሎች ጓዶቻችን ጋር ሆነን ነው፡፡ እኔ ቀርቤ በአክብሮት አነጋገርኳቸው፡፡ "ግርማዊ ሆይ፤ እዚህ እንድትሆኑ ያደረግነው አሁን

ባለው የአገራችን ተጨባጭ ሁኔታና ችግር ምክንያት ለዕርስዎ ደህንነት ጥበቃ ሲባል ነው፡፡ እና መቼም እንደ ኢዮቤልዩ ቤተመንግስት ባይሆንም የሚያስፈልግዎ ነገር እንደማይጎድልብዎ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ በጎደለ ነገር ይጠይቁ" ብያቸው አስገብተናቸው ነው የመጣነው፡፡"

መንግስቱ ጃንሆይ የሚያስቡት ኢትዮጵያን ከፍተኛ ቦታ ላይ አድርሻታለሁ ብለው ነው በሚል መነሻ "እሳቸው የነበሩበትን ስርዓት ለማስታወስ ጉልታዊው ስርዓት ብዬ ስናገር፣ ጉልታዊ ስርዓት አትበል! ጉልታዊውን ስርዓት ከደመሰስነው ጊዜ የለውም" ማለታቸውን ያስታውሳሉ፡፡ ጃንሆይ ከህዝብ ርቀው በመኖራቸው ምክንያት ሰው ስለሳቸው ያለውን አስተያየትና ግምት አያውቁም ማለት ይቻላል የሚሉት መንግስቱ "አንዳንድ ነገር ሲነገራቸው እንዴት ሆኖ? ከየት ነው እንዲህ ያለውን ፈጥራችሁ የምታወሩት? ነበር የሚሉት" በማለት "ስለህዝቡ የኑሮ ደረጃ ስለችግሩ እንኳን ሲነገራቸው "ኢትዮጵያን የት ታውቋትና? ነበር የሚሉን" ሲሉ ያክሉበታል፡፡

" ስለ ለውጥ ስናነሳባቸው "እናንተ ይሄን ውጭ ሄዳችሁ የቀላወጣችሁትን ነገር አምጥታችሁ ነው እዚህ የምትናገሩት፡፡ ይሄንን ህዝብ አለማወቅና አለመረዳት ነው" አሉን፡፡"

ገነት እየለ ትጠይቃለች "ማን መሆንዎን አውቀዋል?"

መንግስቱ "በእሳቸው ግምት አብዮቱን የቀሰቀሱትና አገሪቱን በመምራት ላይ ያሉት ጄኔራል አማን ናቸው፡፡ "ጄኒናር አማን የታለ? መጥቶ ያነጋግረኝ" ነው የሚሉት እንጂ ሻለቃ መንግስቱ ብለው አያውቁም፡፡ እኛም ጄኔራል አማንን ሲሉ፣ ጄኔራል አማንን እናቀርብላቸው ነበር፡፡ ልዕልት እከሌን ሲሉም ይምጡላቸው ነበር የምንለው እንጂ ከልክለን አናውቅም" (ትዝታዎች ቁጥር 1 ገፅ 130)

ጃንሆይ እስር ላይ ሆነው ከአንበሶቻቸው ናፍቆት በስተቀር በሠላም ኑሮአቸውን እየገፉ የነበረ ቢሆንም፤ ድብርቱን አልቻሉትም፡፡ ለዚህ መፍትሄ ይሆን ዘንድም ከጠባቂዎቻቸው ጋር አንዳንድ ቀልዳቀልዶችን በጥያቄና መልስ ዓይነት መወያየት የጀመሩ ይመስላል፡፡ አንድ ቀን ከጠባቂዎቻቸው ውስጥ አንዱ የሆነውን ወታደር "እስቲ ጠመንጃህን ልየው" ይሉታል፡፡ ወታደሩም በአክብሮት ይሰጣቸዋል፡፡ ጃንሆይ በሣቅ ተፍለቀለቁና "አይ ሞኞ፤ ጠባቂያችን ሆነህ እንዴት መሣሪያህን ትሰጠናለህ?" ብለው በፈገግታ ይመልሱለታል፡፡ እነዚህን የመሰሉ ንግግሮች የሚያደርጉት በጊቢያቸው ውስጥ ይንሸራሸሩ በነበረበት ጊዜ መሆኑን መንግስቱ ያስታውሣሉ፡፡

ጃንሆይ እንዲህ ያለ ጭውውት ሲያደርጉ ይቆዩና ወዲያው ደግሞ የመሳት ሁኔታ ያንፀባርቃሉ፡፡እነመንግስቱ ሊያነጋገሯቸው ሲሄዱ፤ "እናንተዬ፤ደጎል ደህና ነው?" ብለው ይጠይቋቸዋል፡፡ቻርለስ ደጎል እ.ኤ.አ



በ1970 ዓ.ም ሲሞት ጃንሆይ ለፈረንሣይ ህዝብ የሐዘን መግለጫ ልከዋል፡፡ይወዱት ስለነበርም በጣም አዝነዋል፡፡ያ ከሆነ ከ4 ዓመት በኋላ ደህና ነው?ብለው መጠየቃቸውና ሌሎች ተመሣሣይ ተደጋጋሚ የመሣት ባህሪያቸው እየባሰ ሲቀጥልም ነው ጤናቸው አሳሳቢ ደረጃ ላይ መድረሱን በቀላሉ ደርጎች መረዳት የቻሉት፡፡

ደርግ አንድ ራሱን የቻለ "የእስር ቤት ጥበቃ ኮሚቴ" አቋቁሟል፤ የሁሉም የጥበቃዎች የበላይ ኃላፊ ኮሎኔል ዳንኤል አስፋው ነበር፡፡ ሐኪማቸው ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ ነበሩ፡፡ ፕሮፌሰሩ ጃንሆይን እየሄዱ ያዩዋቸው ነበር፡፡ የጥበቃ ኮሚቴውም የጤንነታቸውን ሁኔታ ለደርግ በየጊዜው ሪፖርት ያደርጋል፡፡

ከጊዜ በኋላ ህመማቸው እየከፋ ሄደ፡፡ ፊኛቸውን እንደታመሙ ተገለፀ፡፡ ፕሮፌሰር አስራት የጃንሆይ በሽታ አሳሳቢ ስለሆነ፤ "ውጭ አገር ሄደው መታከም አለባቸው" አሉ፡፡ ይህን ሀሳብ ደርግ ተወያየበት፡፡ የማይሞከር ነበር፡፡ ኩዴታ የተከናወነበትን ንጉሠነገስት፣ በቁጥጥር ስር የዋለ መሪ ውጭ ልኮ ማሳከም ምን ያህል ፈተና መሆኑ ለማንም ግልፅ ነው፡፡ ይህንን ለሐኪማቸው አስረዱና፤ "ነገር ግን እዚሁ እንዲታከሙ የሚያስፈልገውን ወጪ፣ የሚያስፈልገውን ትብብር እናድርግ" አሉ መንግስቱ፡፡

ፕሮፌሰር አስራት "የማይቻል ከሆነ ምን ይደረጋል? እዚሁ ህክምናውን እንሞክራለን፡፡ ለህክምና የሚያስፈልጉ መሣሪያዎችንና አጠቃላይ ሁኔታውን አጥንቼ ልምጣ" በማለት ሄዱ፡፡ ተመልሰውም "የህክምና እቃው ተሟልቶ የሚገኘው ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ነውና እዚያ እንዲታከሙ ይፈቀድልን" አሉ፡፡ አሁንም ሻለቃ መንግስቱ እዚያ ይሂዱ ቢባል የሚፈጠር ግርግር ይኖራል በማል ስጋት "እቃው እዚህ ቢመጣስ?" አሉ፡፡ "መብራት የጠፋ እንደሆንስ?" "ጄኔሬተር መትከል አይቻልም?" "አይሆንም፤ አደገኛ ሊሆን ይችላል፡፡ ሆስፒታል ካልመጡ አስቸጋሪ ነው"

አሁንም ጉዳዩ ለደርግ ቀርቦ "ሆስፒታል የግድ መግባት ካለባቸው ክቡር ዘበኛ ሆስፒታል ይግቡ" ተብሎ ተወሠነ፡፡እዚያ ገብተው ቀዶ ጥገና ተደርጎላቸው በጥቂቱ አገግመው ደህና ሆነው ተመለሱ፡፡ደርግ የንጉሡ ጤና ዘላቂ እንዳልሆነ ያውቃል፡፡ያቺ ውጭ አገር ሄደው የመታከማቸው ጉዳይ ከተነሳች በኋላ ደርግ (መንግስቱ) ጃንሆይን በሚመለከት ከነበራቸው የተለየ አቋም ለመውሰድ ተገደዱ፡፡በአንድ በኩል "ውጭ አገር ሄደው ታክመው መዳን እየቻሉ አስረው ይዘው ለሞት አበቋቸው" እንዲባሉ አልፈለጉም፡፡ በሌላ በኩል እዚያ ካልሄዱ ሙሉ በሙሉ ጤናቸው እንደማይመለስ አውቀዋል፡፡ስለዚህ በአገር ውስጡ ህክምና ለጊዜውም ቢሆን ስለተሻላቸው ደርግ "የንጉሡ ጤንነት በተደረገላቸው ህክምና

ምክንያት ተመልሷል፣ ደህንነታቸውም የተጠበቀ ሆኗል" ብሎ ከገለፀ በኋላ ጥረቱንና ለንጉሡ ጨንነትም እንደሚጨነቅ ካሳዬ፣ካስገነዘበ በኋላ፤ደግሞ ሳያገረሽና ሊጎ አጣብቂኝ ሳይፈጠር በዚህች ክፍተት ውስጥ አፋጣኝ እርምጃ መውሰድ ነበረበት፡፡ እስከዚህች አጣብቂኝ ወቅት ድረስ ግን ደርግ ጃንሆይን በአክብሮት ይዟቸው መቆየቱ ግልፅ ነው፡፡

የጃንሆይን አሟሟት በሚመለከት ብዙ ጊዜ "ይባላል፣ ይባላል" የሚሉ ገለፃዎች አሉ፤ በዚህ መጽሐፍ ከ"ይባላል" ለመውጣትና ወደ አንድ ድምዳሜ አንባቢውን ለማድረስ ይሞክራል፡፡

መንግስቱ ኃይለማርያም የጃንሆይን አሟሟት በሚመለከት ለገነት አየለ የሰጡት ቃል ፍጥጥ ያለ ሐሰት ነው፡፡ "... በጥሩ ሁኔታ ታክመው ከዳኑ በኋላ ጥቂት ሳምንታት ቆይተው ሞቱ! ብሎ ዳንኤል ሲነግረኝ ምክንያቱ ሊገባኝ አልቻለም፡፡ እንዴት ሊሆን ቻለ? እንዴት ተሽሏቸው ደህና የነበሩ ሰውዬ በድንገት ሞቱ ትላላችሁ? በማለት ዳንኤልን አፋጥጬ ያዝኩት፡፡..." እያሉ ወሽክተዋል፡፡

ለጣሊያናዊው ጋዜጠኛ ለሪካርዶ ኦሪዚዮ የሰጡት ቃል ግን የዚህ ተቃራኒ ነው፡፡ ሪካርዶ ኦሪዚዮ እ.ኤ.አ በ2003 ዓ.ም ከ8 ወራት መጉላላት በኋላ መንግስቱን ቃለ-ምልልስ ለማድረግ ያቀረበው ጥያቄ ምላሽ አግኝቶ ዙምባቡዌ ሄዶ ቤታቸው ውስጥ ጠይቋቸዋል፡፡የእርሳቸውንና የሌሎችን አምባገነን የቀድሞ መሪዎች ቃለ-ምልልስ አድርጎ የሁሉንም ታሪክ /ጉዛዜ/ አሰባስቦ መጽሐፍ ጽፏል፡፡ ወደ እንግሊዝኛው ተተርጉሞ በዓለም ላይ ተቸብችቧል፡፡ "TALK OF THE DEVIL" የሚል ርዕስ ያለው ሲሆን፣ "የሠይጣን ኑዛዜ" በሚል ርዕስም በአጥናፍ ሠገድ ኪዳኔ በአማርኛ ተተርጉሞ በእኛ አቆጣጠር በ1996 ዓ.ም ለሕትመት በቅቷል፡፡

ምናልባት መንግስቱ ለገነት አየለ መልስ ሲሰጡ በአማርኛ መዋሸት ቀሏቸው፣ ለሪካርዶ መልስ ሲሰጡ በእንግሊዝኛ መዋሸት ከብዷቸው ይሆናል፡፡ወይም ለአውሮፓውያኑ መዋሸቱ ትርፍ አልባ፣ ለኢትዮጵያውያኑ ትርፍ ያለው ሆኖባቸውም ሊሆን ይችላል፡፡ እሱን እናቆየውና ግን ከገነት አየለ መጽሐፍ ውስጥ ከአልባሾቻቸው አንዱ የተናገረውን እናስቀድም፡፡

"ትዝ እንደሚለኝ ነሐሴ 20 ቀን 1967 ሌላ ጊዜ ተራዬ ሲሆን እንደማደርገው ከንጉሡ መኖሪያ ለማደር ስሄድ ኮሎኔል ዳንኤል አስፋው ለዛን ዕለት ማደሬ እንደማያስፈልግ ነገሩኝ፡፡ ይህንኑ ለጃንሆይ ለመንገር ጠይቄ ተፈቀደልኝና የታዘዝኩትን ልነግራቸው ገባሁ፡፡

ጊዜው ከምሽቱ ሦስት ሰዓት ይሆናል፡፡ ወደጌቶቹ ቀርቤ የተባለውን ስነግራቸው ከአልጋቸው ላይ ተነሱና "ቤቱ ጠቧቸው ነው? እንግዲህ ... ውጣላቸው፡፡ ሰፋ አድርገን እንሰራላቸዋለን" ብለው በርከክ አሉና እንባቸውን ከዓይናቸው ላይ እየጠረጉ፤ "አይ አንቺ ኢትዮጵያ! እውነት በድለንሻል?! እውነት አልደከምንልሽም? ብለው እንባቸውን ፈነጠቁ፡፡ እኔም ሳልወድ በግድ ሌላ አማራጭ ስላልነበረኝ ጌታዬን ጥዬ ወደ ቤቴ ሄድኩኝ፡፡ የማያቸው ለመጨረሻ ጊዜ መሆኑን ግን አልጠረጠርኩም ነበር፡፡ ንጉሡ ሞተው የተገኙ ዕለት የመኝታ ክፍላቸው የመድሐኒት ጠረን ይሸት ነበር፡፡ በንጉሡም አንገት አካባቢ ለቁስል ማሰሪያ የሚያገለግል ፋሻ ተቀምጦ አይቻለሁ" (ቁ1 ገፅ 28)

ቀደም ሲል ያሻው ሰው እየሄደ እንዲጠይቃቸው የተፈቀደላቸው ንጉስ ዛሬ አንድ አገልጋይ ተነፈጋቸው ማለት ነው፡፡ እናም አዘኑ፡፡

ሌላው ከ12 ዓመታት በላይ በዘመነ ኢህአዴግ ታስረው፤ እዚያው ወህኒ እያሉ የደርግን ባለሥልጣናት ሁሉ ያነጋገሩትና ከተፈቱ በኋላ "ምስክርነት" በሚል ርዕስ ሻምበል ተስፋዬ ርስቴ ለሕትመት ያበቁት መጽሐፍ ውስጥ የተካተተው እውነታ ሲሆን፤ የመንግስቱ ኃይለማርያም ጠባቂ የነበረው ልዩ ጦር አዛዥ የነበሩት መቶ አለቃ ወንድሙ አበበ የሰጡት ምስክርነት ነው፡፡ "ንጉሡ የተገደሉት በነሐሴ 20 ቀን 1967 ሲሆን ግብዓተ መሬት የተፈፀመው በተከታዩ ቀን ነሀሴ 21 ነበር፡፡ ግድያው የተፈፀመው ከደብረብርሃን በመጣው ልዩ ጦር አማካኝነት በሻለቃ ዳንኤል አስፋው ነው፡፡ ንጉሡ የተገደሉት ሰመመን ሰጪ መድሐኒት በአፍንጫቸው እንዲያሸቱ ከተደረገ በኋላ በተንተራሱት ትራስ በማፈን ነበር፡፡ እንዲያፍን የተላከው ወታደር ህሊናው እንቢ ብሎት እየተርበተበተ በመቸገሩ ራሱ ዳንኤል አስፋው አፈናውን ፈጽሞታል" በማለት ገልፀዋል፡፡(ገፅ70)

ቀጥለን "የሠይጣን ኑዛዜ" በተሰኘው መጽሐፍ የተካተተውን ገለፃ እናስከትል፡፡ ሪካርዶ ኦሪዚዮ ይህን ጥያቄ ሲያነሳ መንግስቱ ለማስተባበል በሞከሩበት ገለፃ ውስጥ እውነታውን ሲፈነጥቁና ያየናቸውን ሁለት ገለፃዎች ሲያጠናክሩ እናያለን፡፡

"... "አስፈላጊ አልነበረም" አሉ በዛለ ስሜት፡፡ በመቀጠልም "ኃይለስላሴ ሽማግሌ፣ በሽተኛና ከሁሉም በላይ ደግሞ በሁሉም ዘንድ የተጠሉ ነበሩ፡፡ ባለፉት ዘመናት ተራማጅና የዘመናዊ አስተሳሰብ ባለቤት የነበሩ ቢሆንም፤ ህዝቡ እንድናወርዳቸው አጥብቆ በመጠየቁ እኔና ባልደረቦቼ አወረድናቸው፡፡ ልናድናቸው አልቻልንም፡፡"

ታዲያ እንዴት ሞቱ? ለሚለው ጥያቄ መንግስቱ መልስ ለመስጠት ከነበራቸው አብዮታዊ ራዕይ አኳያ ሲታይ፤ እንዲህ ላለው ዝርዝር ጉዳይ ቦታ ሊሰጡት እንደማይችሉ በሚጠቁም ሁኔታ ትከሻቸውን ከፍ ዝቅ ካደረጉ በኋላ ጥያቄውን በማናናቅ "እኔ እስከማውቀው ድረስ አሟሟታቸው ተፈጥሮአዊ ነው፡፡ በእርግጥ ከባልደረቦቼ መካከል በንጉሡ የተገደሉባቸውን የአባቶቻቸውንና የወንድሞቻቸውን ደም ለመበቀል በባዶ እጃቸው ሳይቀር አንቀው ለመግደል የሚፈልጉ አልነበሩም ብዬ ለመካድ

ግን አይቃጣኝም፡፡ ህክምና ያደርግላቸው የነበረው ዶክተር የጤንነታቸው ሁኔታ እስጊ ደረጃ ላይ መድረሱንም አልነገረኝም፡፡ ስለዚህ ምን እንደተከሰተ በግሌ ለማረጋገጥ አልቻልኩም" አሉ (ገፅ 224)

ይህ ገለፃ የማያሻማ ትርጉም እንዳለው ግልፅ ነው፡፡ መንግስቱ ለጋዜጠኛ ገነት አየለ የሰጡትን "በጭራሽ! በጭራሽ! እኔ አላውቅም!" የሚል ይዘት ያለውን ቃል ስናይ ደግሞ የበለጠ ግልፅ ይሆንልናል፡፡

ምናልባት ጋዜጠኛ ሪካርዶ ኦሪዚዮ ካየነው ምላሽ በኋላ አንድ ተከታይ ጥያቄ መጠየቅ የነበረበት ይመስላል፡፡ "ከባልደረቦቼ መካከል በንጉሡ አባቶቻቸውና ወንድሞቻቸው የተገደሉባቸውን ደም ለመበቀል ሲሉ..." የሚለውን ገለፃ አንስቶ "ለምሳሌ ማን?" ብሎ አልጠየቀም እንጂ ቢጠይቅ መንግስቱ ምን ይመልሱ ነበር? ከደርግ አባላት ውስጥ በጃንሆይ ዘመዱ የተገደለበት አባል ማነው? ቢባሉ መልስ አይኖራቸውም፡፡ በጃንሆይ ጊዜ በተማሪዎች ላይ በፀጥታ ጠባቂዎች አማካኝነት ከተወሰደው እርምጃ በተጨማሪ፣ ሁለት ሰዎች ብቻ በፍርድ ችሎት ተገድለዋል፡፡ በላይ ዘለቀና ጄኔራል መንግስቱ ነዋይ በቃ፡፡ ከዚህም ባለፈ በይባላል ሲወራ እንኳ ገዳዮች ተብለው የሚጠቀሱት ዳንኤልና መንግስቱ እንጂ ሌላ አባል ወደ ጃንሆይ ድርሽ አይል እንደነበር ራሳቸው መንግስቱ ደጋግመው ገልፀዋል፡፡

እናም ጃንሆይ ነሐሴ 20 ቀን 1967 ዓ.ም የጥበቃ ኮሚቴው አሽከሮቻቸውንም ወደቤታቸው ሸኝቶ ብቻቸውን ካስቀረ በኋላ ምሽት ላይ በትራስ አፍኖ የጥበቃው አዛዥ ከጨረሳቸው በኋላ የመሞታቸውን ሪፖርት ለደርጉ አቀረበ፡፡

ጃንሆይ 11 ወራት ተኩል በቁም እስር ካሳለፉ በኋላ በ83 ዓመታቸው ህይወታቸው አለፈ፡፡ ደርግም እፎይ አለ፡፡ ት...ዝ ሲላቸው መሞታቸው ብቻ እፎይ አያስብልም፡፡ ገና የቀብራቸው ጉዳይ ደርጎችን ሌላ ውጥረት ውስጥ ይከታልና፡፡

የጃንሆይ ማረፍ እንደተገለፀ፣ የወቅቱ ፓትሪያሪክና ሌሎች ሁለት ጳጳሳት ወደ መንግስቱ ቢሮ መጥተው "ንጉሡ ካረፉ ስላሴ ቤተ-ክርስቲያን እንዲያርፉና አስፈላጊውን ፀሎተ ፍትሐት እንድናደርግላቸው ይፈቀድልን" አሉ፡፡ መንግስቱ ከባድ ጥያቄ እንደሆነ ያውቁታል፡፡ "አባላቱን አነጋግሬ የሚሉትን እነግራችኋለሁ" ብለው መለሱ፡፡

"በደርጉ ስብሰባ ላይ ይሄ ነገር ቢነሳ አቧራው እንደሚጨስ አውቃለሁ" በማለት የዚያን ጊዜውን ሁኔታ የሚተርኩት መንግስቱ! ጉዳዩ ስብሰባ ላይ ሲቀርብ ከአባላቱ የተሰነዘሩትን ልዩ ልዩ ሀሳቦችንም ጨምረው ገልፀዋል፡፡ አንዱ "ንጉሡን እንደልዩ ፍጡር ከማየት እምነት አልወጣችሁም እንዴ? ሲል ሌላው እሳቸውን ማየት ያለብን እንደተራ ሰው ነው! በየቀኑ ስንቱ ወታደር ይሞት የለ እንዴ? ይላል፡፡ በ83 ዓመት መሞት እድለኝነት ነው ያለም አለ፡፡ ... አንዱ ተነስቶ እንዲህ አለ አሉ፣



"ለመሆኑ ለምንድነው ስላሴ የሚቀበሩት? እሳቸው'ኮ አርበኛ አይደሉም፣ ስላሴ የሚቀበሩት አርበኞች ብቻ ናቸው" (ምናልባት ጃንሆይ በማይጨው ጦርነት የጠላትን አየር ለመጣል አርሊኮን ተኳሽ ሆነው መዋጋታቸውን አያውቅ ይሆናል፡፡ )ብቻ ብዙ ሀሳቦች ተነስተው ተጥለው ንጉሡን በኤፊሴላዊ መንገድ መቅበር ለፖለቲካቸው ስጋት መሆኑን ደምድመዋል፡፡

መንግስቱ በትዝታቸው እንዲህ ይላሉ "አይ እንግዲህ ... አልኩና ፓትሪያሪኩን፣ ይቅርታ ያድርጉልኝ፣ ነገሩ እናንተ እንደምታስቡት አልሆነም፡፡ መልኩን ለውጦ እንዲያውም ሌላ ነገር ነው ያስከተለው፡፡ ንጉሡ አርበኛ አይደሉም፣ እዚያ አያርፉም፡፡ ፍትሐት ስላሉት ደግሞ ጳጳሱስ ቢሆኑ ስንቱ ወታደር በየቀኑ ሲረግፍ ምነው ለእነሱ ፍትሐት ለማድረግ አልጠየቁም? የሚል ነገር ሁሉ ተነስቷል፡፡ ከእርስዎ የምደብቀው ነገር የለም፡፡ ያለው ስሜት ፍፁም እንደምታስቡት አይደለም፡፡ አንድ የፖለቲካ ችግር የሚያስከትል ስለሆነ ይቅርታ አድርጉልኝ፣ ምንም ማድረግ አልችልም አልኳቸውና ተሰናብተው ሄዱ፡፡"

የት ይረፉ ሆነ ጥያቄው ብለው መንግስቱ ገለፃቸውን ይቀጥላሉ፣ "ባዕታ ተባለ፡፡ ባዕታ ገብተው ሲያበቁ ምንም አይነት ክብር፣ ጡሩንባና ጋጋታ ሳይኖር ይረፉ ተባለ፡፡ ይሄንኑ ትዕዛዝ ለእስር ቤቱ ኮሚቴ አስተላለፍኩ፡፡ በዚሁ አከተመ" ብለው ሲያቆሙ ጋዜጠኛ ገነት አየለ "ታዲያ ትዕዛዙ መፈፀሙን አረጋግጠዋል?" ስትል ትጠይቃለች፡፡ መንግስቱ "አይ ትዕዛዜ ፍንክች የማይል ነገር ነው፡፡ ይፈፀማል፡፡ አይፈፀምም ብዬ ጥርጣሬ የለኝም፡፡ ሰውየው አርፈዋል፡፡ መሠረታዊው የቄሶች ጥያቄ መልስ አግኝቷል፡፡ እኔ በጣም የሚያጣድፍና ጊዜ የማይሰጥ ስራ አለብኝ፡፡ ችግር አለ፡፡ ወደዚያ ዞሬያለሁ" ብለው ነው ያስተባበሉት፡፡ ገነት እስከመጨረሻው ብትሞግታቸውም በዚሁ አቋም ድርቅ እንዳሉ ነው የቀጠሉት፡፡

በእርግጥ ግን መንግስቱ ምንም አጣዳፊ ስራ ቢኖርባቸው የዚህን ጉዳይ አፈፃፀም በዓይናቸው ብሌን አይተው ሳያረጋግጡና አፈፃፀሙንም መጨረሻው ድረስ ሳያስጉዙ "ትዕዛዜ መፈፀሙ ስለማይቀር..." ብለው የሚተውት ጉዳይ ነው? "አዝዣለሁ፣ ባዘዝኩት መሠረትም ተፈፅሟል" ብለው አፈፃፀሙን ሳያዩ ፊታቸውን ወደሌላ ስራ ያዞራሉ ብሎ ማሰብ ትልቅ የዋህነት መሆኑን መግለፅ ሳያስፈልግ ማንም በቀላሉ የሚረዳው ይሆናል፡፡ ከዚህ አንፃር ነው ተከታዩ የቀብር ስርዓት እውነትነቱ ታምኖበት የተደመደመውና የመንግስቱ ገለፃ ቀርሽ መሆን የታወቀው፡፡

ቀደም ሲል ያሟሟታቸውን ሁኔታ የገለፁት የቤተ-መንግስቱ የልዩ ጦር አዛዥ መቶ አለቃ ወንድሙ አበበ ለ"ምስክርነት" መጽሐፍ ፀሐፊ ከተገደሉ በኋላ ስለተከተለው ነገር ሲያብራሩ፣ "በዚያን ወቅት ቤተ-

መንግስቱ ጊቢ ውስጥ የተቀራረቡ፣ ግን የተለያዩ ጥልቅ ጉድጓዶች ጠሩ መቆፈሩን እስታውሳለሁ። ምሽግ ለማድረግ እንዳይባል አጭር ነው፣ የውሃ ማጠራቀሚያ እንዳይባል ደግሞ ሞላላ ነው። ጥልቅ የሆኑ አራት ወይም አምስት ጉድጓዶች ተቆፍረው ውለው ሳያድሩ ደግሞ በሲሚንቶ ተለስነው ተዘጉ። በማለት የጉድጓዶቹን አቆፋፈርና መዘጋት ይገልፃሉ። ከላይ የተገለፀውን ሀሳብ ሻምበል መንግስቱ ገመቹ እውነት መሆኑን አረጋግጠዋል" (ሻምበል መንግስቱ ገመቹ ከፍተኛ የደርግ ባለሥልጣንና የመንግስቱ ቁጥር አንድ ታማኝ መሆናቸው ይታወቃል)

ፀሐፊው ሲቀጥሉም፣ በተለይ የታላቁ ቤተ-መንግስት የጥገና ክፍል ኃላፊ ነበርኩ፣ ጉድጓዶችንም ያስቆፈርኩ እኔ ነኝ የሚሉት መሐንዲስ ጥላሁን ኪዳኔ፣ "ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለስላሴ እንደሞቱ አውቃለሁ። የሞቱት ነሐሴ 20 ቀን 1967 ዓ.ም ነበር። በነሐሴ 21 ቀን ከጠዋቱ 2:30 ሰዓት በመርዕድ ንጉሴ ተጠርቸ የከፊን ጨርቅና የሬሣ ሳጥን እንዳቀርብ ተጠይቄ... ሰጥቻለሁ። በ7 ሠዓት ላይ ሦስት ጉድጓዶች 3 በ 3 ሜትር አስቆፈርኩ። አራተኛ ጉድጓድም ተቆፍሯል። ቦታው በኋላ የፕሬዝዳንቱ ቢሮ ተሰራበት። አራት ጉድጓድ መቆፈሩ እኛ እንዳናውቅ መሰለኝ። ጉድጓዶቹን በዳንኤል አስፋው ትዕዛዝ በኮንክሪት ዘጋኋቸው፣ በአጭር ጊዜም በጉድጓዶቹ ላይ ቤት ተሰራ።

ኢህአዴግ ሲገባ ኮሎኔል ስለሺ መኩሪያ ቦታውን ካሳዩ በኋላ ስምንት ሜትር ተቆፍሮ 3 በ 3 ሜትር ቱቦ ተገኘ፣ በኮሎኔሉ መሪነት እንደገና ወደ ውስጥ 3 ሜትር ሲቆፈር የንጉሡ አፅም ተገኘና በሙሉ ወጣ። በማለት ሰኔ 4 ቀን 1988 ዓ.ም ለዋለው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አንደኛ ወንጀል ችሎት ቀርበው የምስክርነት ቃላቸውን ሰጥተዋል። (የምስክሩን ቃል ያገኘሁት ሻለቃ መላኩ ተፈራ ከማስታወሻ ደብተራቸው ዓለም በቃኝ ውስጥ ጽፈው ሰጥተውኝ ነው)" ይላሉ ፀሐፊው። (ምስክርነት ገፅ 71)

ከመንግስቱ ቢሮ አጥንት ተቆፍሮ ሲወጣ በቴሌቪዥን የታየ ቢሆንም፣ ባዕታ ነው የተቀበሩት የሚሉት መንግስቱ፣ ይሄ ተራ የኢህአዴግ ፕሮፓጋንዳ ነው ባይ ናቸው። የጃንሆይ ፍፃሜ ያየነውን አይነት ሆኖ አለፈ። አፅማቸውም ከጊዜ በኋላ ከዚያ ወጥቶ ስላሴ ቤተ-ክርስቲያን እንዲያርፍ ተደረገ።

በትራስ ታፍነው ሲገደሉ የሰአታት እድሜ ቀርቷቸው በነበረ ጊዜ ጃንሆይ "እውነት ግን በድለንሻል? እውነት አልደከምንልሽም?" በማለት ተንበርክከው የጠየቁት ሰዎችን አልነበረም፣ ኢትዮጵያን እንጂ። ኢትዮጵያ ምን መለሰች ብሎ መጠየቅ ሳይገባ ስራቸው ራሱ መልስ እየሰጠ ይገኛል።

በጃንሆይ ፓርላማ እየተሰበሰብን፣ በጃንሆይ ቴአትር ቤት እየተዝናናን፣ በጃንሆይን ስታዲየም እየተጫወትን፣ በጃንሆይ ዘመን የፍትሐብሔር ሕግ እየተዳኘን፣ በጃንሆይ... ብዙ ነገር እየተጠቀምን መሆናችን ማሰቡ ብቻ መልስ ይሆነናል ለማለት ነው።



# ምዕራፍ 85

*የሊቀመናብርቱ ዘመን*

መስከረም 2 ቀን 1967 ዓ.ም አብዮቱ ከፈነዳ በኋላ ኢትዮጵያ በሊቀመናብርቱ ተመርታለች። በመጀመሪያ ጀኔራል አማን ሚካኤል አንዶም ለሁለት ወራት ሊቀመንበር ሆነው ቆይተው በመንግስቱ ትዕዛዝ ከተገደሉ በኋላ ቀጥሎ ብርጋዴል ጄኔራል ተፈሪ በንቲ ለሁለት ዓመታት ያህል የሊቀመንበርነቱ ቦታ ተሰጥቷቸው መርተዋል። እሳቸውንም ደርግ ገደለና ተተኪው ሻለቃ መንግስቱ ሆኑ። እነዚህ ሁለት ጀኔራሎች በጠሩ ዘንድ ተቀባይነት ለማስገኘት ሲባል በሽፋንነት ከፊት እንዲቀድሙ የተደረጉ ይሁኑ እንጂ፣ ከበስተጀርባ መንግስቱ ነበሩ የደርጉ መሪ። ጀኔራሎቹ የደርግ አባላት አልነበሩም። የቀሩት የደርግ መስራች ሻለቃ አጥናፉም ተፈሪ ባንቲ በተገደሉ ማግስት ተወግደው መንጌ ብቸኛው ሊቀመንበር ሆነው ዘልቀዋል።

ደርግ ንጉሣዊ አገዛዙን አስወግዶ፣ "የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር" ብሎ ራሱን ሰየመ። የመጀመሪያ ስራውም አዲሱን ሕገ-መንግስት ማገድ፣ ፓርላማውን መበተንና ማናቸውንም አይነት ሠላማዊ ሰልፍንና የስራ ማቆም አድማን መከልከል ነበር። "ኢትዮጵያ ትቅደም" የሚለውን መርህ መቃወም የዘመኑ ቁጥር አንድ ወንጀል ሆነ።

የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ መቋቋም ወዲያው ነበር ተቃውሞ የገጠመው። በዋናነት የተማሪዎች ቡድን፣ ቀጥሎ "ፎረም" በመባል የሚታወቀው ግራ ዘመም የሆነው የዩኒቨርሲቲ መምህራን ቡድን፣ እንዲሁም የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበራት ኮንፌዴሬሽን ሲሆኑ፣ እነዚህም "ዴሞክራሲያ" እና "የሠፊው ህዝብ ድምፅ" በተባሉ መጽሔቶች ዙሪያ ተሰባስበው የግራ ክንፍ ድርጅቶች ሆነው ተቃወሙ። ከወታደሩ በኩል ደግሞ የክቡር ዘበኛና የወታደር የበረራ ክፍል (አርሚ አቪየሽን) እንዲሁም የመሐንዲስ ክፍል ተቃዋሚ ሆነው ቀረቡ። የተቃውሞ መነሻቸውም "የጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት ነው መቋቋም ያለበት" የሚል ነው። ይህንንም ቀደም ካለው የደርግ ምስረታ ጊዜ ጀምሮ በተለይ የመምህራን ቡድን ለደርግ ያቀርቡት የነበረ ሀሳብ ነው። ያን ጊዜ "ህዝባዊ መንግስት ይቋቋም" ሲሉ ቢቆዩም፣ አሁን ከባድ እንደሚሆን ስለተረዱ፣ "ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት" በሚል አሻሻሉት።

ሆኖም የዚህ መፈክር ደጋፊዎች አቋማቸው አንድ ይሁን እንጂ በአመሠራረቱ ላይ የሚያቀርቡት አጀንዳ የተለያየ ነበር። ከፊሉ "ከሰራተኞች፣ ከተማሪዎች፣ ከመምህራንና ገበሬዎች የሚውጣጣ መንግስት ይሁን" ሲሉ፣ የቀሩት "የየካቲቱ ህዝባዊ ንቅናቄ ባፈራቸው ኮሚቴዎችና ድርጅቶች ላይ ይመስረት" ይላሉ። ይህ የ"ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት"

መፈክር አተገባበር ጉዳይም በዴሞክራሲያ እና የሰፊው ህዝብ ድምፅ በተሰኙ የፕሬስ ውጤቶች ዙሪያ የተደራጁትን "የኢትዮጵያ ህዝብ አብዮታዊ ፓርቲ" (ኢሕአፓ)ን እና "የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ" (መኢሶን)ን ወደፊት የምናያቸውን የእርስ በርስ የስልጣን ፍልሚያ ሲፈጥር ችሏል፡፡

በአብዮቱ ወቅት በአገር ቤት የ"ሰፊው ህዝብ ድምፅ" ላይ በቀረበ ትንቢታዊ ትንታኔ "ወታደራዊ መንግስት ምን ቅን ልቦና ቢኖረው አገሪቱን በአንድ አንባገነን መሪ መዳፍ ስር ይጥላታል" የሚል አቋም የያዘ ጽሁፍ ቢሰነዝርም፤ ይህ የመኢሶን አቋም ከአገር ውጪ ካለው የመኢሶን አመራር ጋር የሚጣጣም አልሆነም፡፡ ምክንያቱም ሰፊውን ህዝብ ለማደራጀት ጊዜ ስለሚያስፈልግ ስልጣኑ በወታደሩ እጅ እንዲቆይለት የውጭ አገሩ ቡድን ይፈልግ ስለነበር ነው፡፡ ከዚህም በላይ ኢህአፓ በብዙሃን ድርጅቶች በመምህራን፣ በተማሪዎችና በሠራተኛው ዘንድ ቀድሞ መሰረፅ ችሏልና የሚቋቋመውን ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት እረከባለሁ ብሎ ያስብ ስለነበርና መኢሶን ገና ይቀረው ስለነበር፤ ወታደሩን ጊዜ መግዣ ሊያደርግ ሽቶታል፡፡

የመኢሶን የውጭ ቡድን አገር ቤት ከገባ በኋላም ከኢህአፓ ጋር ቢፎካከር ውጤት አልባ እንደሚሆን ስለተረዳው ያን የጋራ መፈክር ጥሎ፣ የአገርቤቱን አጋሩንም አስጥሎ ከደርግ ጋር ተንጠላጥሎ /ተለጥፎ/ ስልጣን መያዙን መርጧል፡፡

የኢህአፓና የመኢሶን የጦፈ ክርክር ማርክሳዊ ጭብጥነቱ አንድ ስለሆነ ፉክክሩ "ለርዕዮቱ እኔ ታማኝ ነኝ" ሲል አንዱ፤ ሌላው "እኔ የበለጠ ታማኝ ነኝ" የሚል እንጂ የርዕዮት ልዩነት የላቸውም፡፡ ከዚህ አንፃር ፉክክሩ የስልጣንና የስልጣን ብቻ ተብሎ ይደመደማል፡፡ ደርግ ግን እንኳን ስልጣን አስረክቦ ወደ ካምፕ ለመመለስ ለማጋራት እንኳ የፈለገ አይመስልም፡፡

እርግጥ ነው ደርግ ሰደት ላይ ያሉትን ቀደምት የአመፅ እንቅስቃሽ የነበሩ ምሁራንንና ማኅበራቱን ከአውሮፓም፣ ከአሜሪካም ... ለሁሉም ጥሪ አቅርቧል፡፡ ነገር ግን ምሁራኑን አስቀድሞ ሲጋብዝ ስልጣን ለመልቀቅ ሳይሆን ያሰብ የነበረው፤በምን መልኩ ተጠቅሜባቸው ነው ስልጣኔን የማጠናክርባቸው? በሚል ዓላማ መሆኑ ዘግይቶ ገሀድ የወጣ ሀቅ ሆኗል፡፡

ደርግ ጃንሆይን ከስልጣን ከማውረዱ በፊት በምን መልኩ እናውርዳቸው? የሚለውን አጀንዳ ተወያይቶ ውሣኔ ካሳለፈ በኋላ፤ ቀጣይ ውይይቱ ጃንሆይ ከወረዱ በኋላስ ምን ዓይነት መንግስት ይተካ? የሚለው ነበርና በዚህ አጀንዳ የከረረ ክርክር ተደርጓል፡፡ ይህን ጥያቄ የሚመለከቱ



ሀሳቦችንም ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በቡድንም በግለሰብ ደረጃም እየቀረቡለት ሲሰበስብ ቆይቷል፡፡

በደርግ ስብሰባ ከተነሱ ነጥቦች ውስጥ አንዱ "አፍሪካ ውስጥ የተቋቋሙትን ወታደራዊ መንግስቶች ምሳሌ በማድረግ ህዝቡን አስተባብረን አገራችንን መምራት ያቅተናል እንዴ? ስለዚህ ንጉሡ በንጉስ እንዲተካ ይሁንና ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግስት ተቋቁሞ፤ እኛ በሠራዊቱ የተወከልነው አባላትም ሳንለያይ ለተወሰነ ጊዜ መሪነቱን ይዘን እንቆይ፡፡ በህዝብ የተወከለ መንግስት ሲደራጅ አስረክበን ወደየጦር ክፍላችን እንመለስ" የሚለው ከደርግ አባላት የተሰነዘረው ሲሆን፤ በሌላ በኩል ደግሞ ልጅ ሚካኤል እምሩ የመሩት የባለሙያ ቡድን አጥንቶ ያቀረበው እንደሆነ የሚነገርለት የሰለጠነ ሀሳብ ነበር፡፡ ይህን ሀሳብ ከቀናት በፊት የአስተባባሪው ኮሚቴ ሊቀመንበር እንዲሆኑ የተሾሙት ጄኔራል አማን አቀረቡት፡፡ "ከአስተባባሪው ኮሚቴ ውስጥ በድምፅ ብልጫ የሚመረጡ 10 እውቀትና ችሎታ ያላቸው መኮንኖችና 10 ከሲቪል፣ ከታዋቂ ሰዎች ተመርጠው የሁለቱ ጥምር ቡድን መንግስት ኢትዮጵያን ያስተዳድሩ" አሉ ጄኔራል አማን፡፡

ይህ ማለት የደርግ አባላት ተበተኑ ማለት መሆኑ ነው፡፡ይህን ሀሳብ ሻለቃ መንግስቱ ኃይለማርያም በጽኑ ተቃወሙት፡፡"የደርግ አባላትን በትና ወደ ጦር ክፍላቸው መላክ ሠራዊቱን ለሌላ አመፅ ማነሳሳት ይሆናል! መቋቋም ያለበት ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግስት ነው፡፡በሽግግር ወቅት ወታደሩ ስልጣን ለብቻው መያዝ አለበት፡፡ሲቪሎችን ማካፈል ተገቢ አይደለም" ሲሉ፤ጠቅላላው የደርግ አባላት የመንግስቱን ሀሳብ ደግፈው አጨበጨቡ፡፡

ጄኔራል አማን "ሲቪልና ወታደር" ሲሉ ከወታደሩ ቀዳሚ ተመራጭ እንደሚሆኑ ያውቁታል፡፡ ሻለቃ መንግስቱ ከ10 ተመራጮች አንዱ ሊሆኑ እንደሚችሉ ባያጠራጥርም፤ ወደፊት ስልጣንን ለብቻቸው የመያዝ ህልማቸው ግን ይጨናገፋል፡፡ ምናልባትም እውቀት፣ ችሎታና ትምህርት ካላቸው ተመራጮች ጋር ተካተው ሲመዘኑ አንዲት ዝቅ ያለች ቦታ ብቻ ሊያገኙ እንደሚችሉ እሱዋውም ቀጣይነት ላይኖራት እንደሚችል መገመት አይከብዳቸውም፡፡

ሌላው የበታች ሹማምንት የደርግ አባልማ የመንግስቱን አቋም ካልደገፈ ምንም አይነት ቦታ አይኖረውም፡፡ ይህ ስለሆነ የአማን የ"ይበተኑ" አቋም በቀላሉ ተሸነፈ፤ የመንግስቱ የ"አይበተኑም" አቋም በቀላሉ አሸነፈ፡፡

ሻለቃ መንግስቱ ያለእነዚያ ዝቅተኛ ሹማምንት ኃይል፤ ዝቅተኛ ሹማምንቱ ያለሻለቃ መንግስቱ አቋም ህልውና አይኖራቸውም፡፡ ስለዚህ ላለላይና ታህታይ መዋቅሩ እስከመጨረሻው ተሳስረው ከመቀጠል ውጪ

ሌላ ምርጫ አልነበራቸውም፡፡ ከዚህ በኋላ ጄኔራል አማን ለደርግ፣ ደርግ ለአማን ጥሩ ምልከታ እንዳይኖራቸው ሆነ፡፡ ነገር ግን ለጊዜውም ቢሆን ልዩነታቸውን ውበት አድርገው መቀጠል ነበረባቸውና ቀጥለዋል፡፡

በዚህ መሠረት "የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ" መመስረቱን በአዋጅ ቁጥር 1 1967 ዓ.ም ደንግገው ስራቸውን ቀጥለዋል፡፡

በሻለቃ መንግስቱ አስተባባሪነትም በቀጥታ በደርግ የሚታዘዝ ልዩ ጦር አዘጋጅተዋል፡፡ ከነበሩት አባላት በተጨማሪም ሌሎች ከየጦር ክፍሉ የተውጣጡ በመቶዎች የሚቆጠሩ ንዑስ የደርግ አባላት ተደራጅተው አጋር ሆነዋል፡፡ በውስጥና በውጭ ያሉ ምሁራን በቃላት ጦርነት ሲጠዛጠዙ፤ "የበላይነት ላለው ለእኛ ቡድን ስልጣን ይገባል" እያሉ ሲሸልሉ ደርግ ራሱን አደላድሎ፤ የምሁራኑን ሀሳብ ለራሱ በሚመቸው መንገድ እየተረጎመና ስልጣን የሚሰጥ መስሎ እያማለለ ጥቂት ምሁራንን አስጠግቶ እየተጠቀመባቸው ቀጠለ፡፡ ፍርፋሪ ስልጣን ለመቃረም የነበረው የምሁራን ሽኩቻ ከፍተኛ ነበር፡፡ ለደርግም በእጅጉ ጠቅሞታል፡፡ ደርግ ከህቡዕ ቡድኖች የሚሰነዘረውን የስልጣን ጥያቄ ሲቻል በዘዴ፣ ካልሆነም በኃይል ለማስወገድ ተዘጋጅቷል፡፡

ውክልናው በህዝቡ ዘንድ እውቅና እንዲኖረውም መንግስታዊና ሃይማኖታዊ ተቋሞችን፣ ህዝባዊና የሙያ ድርጅቶችን የሚወክሉ አባላት የሚገኙበት ብሔራዊ የመማክርት ሸንጎ ለይምሰል ሰየመ፡፡ የይምሰል መሆኑን ተረድተው ለተቃውሞ የሚነሱትን መደምሰስ መፍትሄ አደረገው፡፡ ሲጀምርም የተቃዋሚ ድርጅቶች መሪዎችን አሰረ፡፡ ወዝአደሩ የመሪዎቹን መታሰር ተቃውሞ ሲነሳ በኃይል በተናቸው፡፡ የደርግን ተደላድሎ ስልጣን መያዝ የተቃወሙት ሲቪሎች ብቻ አልነበሩም፡፡ ወደ ሠራዊቱም ተዛምቷል፡፡ ክቡር ዘበኛና የአርሚ አቪየሽን ደርግን ተቃውመዋል፡፡ እነዚህ ክፍሎችም መሪዎቻቸውን በደርግ ተፅዕኖ አሳልፈው ሊሰጡ ተገደዋል፡፡ የመሐንዲስ ክፍሉ ግን በተቃውሞው ስለገፉና እጅ አልሰጥም በማለቱ መስከረም 27 ቀን በሻለቃ መንግስቱ ብቻ ታማኝ እንዲሆን ተደርጎ የተዋቀረውና በእሳቸው ትዕዛዝ ብቻ የሚመራው ወታደር ካምፑን ሰብሮ ገብቶ በከፈተው ጥቃት 5 የመሐንዲስ ጦር አባላት ተገድለው፣ በርካቶች ቆስለው፣ የቀሩት እንዲታሰሩ ተደረገ፡፡ ደርግ ራሱን የአብዮቱ ጠበቂና ብቸኛ አለኝታ አድርጎ ወስዶታልና በዚህ ጉዳይ የወጣበትን ክፍሉን እንኳ እንደማይምር አረጋገጠ፡፡ አብዮቱ በደም ተጀመረ፡፡

በደርግ ውስጥ ሻለቃ መንግስቱ ኃይለማርያም በአንዳበተ ርቱዕነታቸው ተወዳጅ ሆነው ቀጥለዋል፡፡ በተለይ የበታች ሹማምንቱ ከደርግ አባልነት ቀስ በቀስ ወደ መንግስቱ አሽከርነት ተለውጠዋል ቢባል አልተጋነነም፡፡



መንግስቱ ሊለጠፉ ከፈለጉት ምሁራንና ከሰላያቸው ከደጃዝማቹ የሚጎርፉትን ሀሳቦች ለደርግ እያቀረቡ በእጅ ብልጫ ያስወስናል፡፡ መወደድና መከበር ያልቻሉት በጄኔራል አማን ብቻ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ውሎ አድሮም በአማንና በመንግስቱ መካከል በሀሳብ አለመጣጣም መሽካከር ተከሰተ፡፡

የኤርትራ ግዛት ተወላጁ ጄኔራል አማን ሚካኤል አንዶም በራሳቸው የሚተማመኑ፣ የጦር ጀግና፣ ኩሩና አስተዋይ መሆናቸው ይነገርላቸዋል፡፡ በኢጣሊያ ወረራ ጊዜ በስደት ሱዳን የነበሩና፣ ንጉሡ ከስደት ሲመለሱና በሱዳን በኩል አድርገው ከእንግሊዝ ጦር ጋር እየተዋጉ ሲመጡ አማን ተሳታፊ ነበሩ፡፡ ከነፃነት በኋላ ከኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ጋር ተቀላቅለው አገራቸውን ሲያገለግሉ የቆዩና እስከ ከፍተኛው ሌቴናል ጄኔራልነት የደረሱ ናቸው፡፡ "አሸዋ ልብሱ፣ ኮዳ ትራሱ" እየተባሉ በጦሩ ዘንድ ከፍተኛ አድናቆትና ተወዳጅነት ያተረፉ ከመሆናቸውም በላይ፤ ከፍተኛ ወታደራዊ ትምህርቶችን በምዕራቡ ዓለም የተከታተሉ ናቸው፡፡ በአሜሪካና በሌሎች አገሮች በወታደራዊ አታሼነት ተመድበው ሰርተዋል፡፡ ኮሪያ ለዘመተው ለአንደኛው ቃኘው ሻለቃ አዛዥ ሆነው ዘምተዋል፡፡ በአገር ውስጥም በተለያዩ የምድር ጦር ክፍሎች እየተመደቡ በአዛዥነት አገልግለዋል፡፡ አሁን በደርጉ ዘመን ደግሞ የመከላከያ ሚኒስቴርና ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም ሆነው የደርግን የሊቀመንበርነት ስልጣንም ይዘዋል፡፡

በጥቅምት ወር 1967 ዓ.ም ወደ ኤርትራ ለጉብኝት እንዲሄዱ ተደረገ፡፡ የኤርትራ ሁኔታ የወቅቱ አሳሳቢ ጉዳይ ነበር፡፡ የሻዕቢያና የጀብሃ እንቅስቃሴ የኢትዮጵያ ስጋት የሆነው ከጃንሆይ ዘመን ጀምሮ ነበርና ከአብዮቱ በኋላ የሠላም ጥረት ማድረጉ /መሞከሩ/ ተገቢ ነበር፡፡ የጄኔራል አማን የጉብኝት ዓላማም በዋናነት በግዛቱ ያሉትን የኢትዮጵያ ሠራዊቶች ከተራ ወታደር እስከ አዛዥ በቡድንና በግል ማነጋገርና መገምገም፣ የየግዛቱን ሲቪል ህብረተሰብ ማነጋገር፣ ከአገር ሽማግሌዎች ጋር የኤርትራን ችግር እንዴት መፍታት እንደሚገባ ለመወያየት የታቀደ ሲሆን፤ የአማን የትውልድ አገር መሆኑ ደግሞ ለእቅዱ ስኬታማነት ሚና ይኖረዋል ተብሎ ነው፡፡ እንደተባለውም የኤርትራ ህዝብ በሳባ ስታዲየም ተሰብስቦ የጋለ አቀባበል አድርጎላቸዋል፡፡
በእቅዳቸው መሠረትም የአገር ሽማግሌዎችን እየሰበሰቡ የእርስ በርስ ጦርነቱ ቆሞ ሰላም መውረድ እንዳለበት፣ወላጆችም ልጆቻቸውን ወደ ሠላም የሚመራ ምክር እንዲለግሱ፣ የስልጣን ሱሰኞች የጫሩት እሣት ባፋጣኝ መጥፋት እንዳለበት ገልፀዋል፡፡ ሠራዊታቸውንም አበረታተው ስለሠላም ሰብከዋል፡፡የመጨረሻ ጉብኝታቸውን በደመቀው ስታዲየም ሲያደርጉም የተሰብሳቢውን ህዝብ ልብ የነካ ንግግር እንዲህ በማለት

ቦታ ያስቀመጠት'ኮ እነዚህ ቂጣቸውን ያልጠረጉ ያኗቸው ናቸው..." የሚል መልስ ሰጡ፡፡

አማን ዱቄት ሰፋሪ ያሉት መንግስቱ የመሣሪያ ግምጃ ቤት ኃላፊ ሆነው ይሰሩ ስለነበር ነው፡፡ አማን ጦሩን ለማንቀሳቀስና በደርግ ላይ እንዲነሳ ለማድረግ የጣሩት ጥረት ሁሉ አልተሳካም፡፡ ረፍዶባቸዋል፡፡

እንግዲህ በመጀመሪያ የአማን ፊጥኖ ተወዳጅነት ማግኘት በደርጉ አልተወደደም፡፡ ሻለቃ መንግስቱን የከነከናቸው ይመስላል፡፡ ከዚያ "ደርግ ይበተን" ቀጥሎ "ሰጥቶ መቀበል" እንደገና "ጦር አይላክ" ከዚያም "ታንከኛ ይሂድ" ሲሉና፤ በመጨረሻም ተሳድበው ሲወጡ፤ በዚህም ላይ ኤርትራዊነታቸው ሲደረብና፤ በሳባ ስታዲየም "የኤርትራና የኢትዮጵያ አንድነት ዘላለማዊ ነው" በማለት ያደረጉት ንግግር አንዷን አገር ነጣጥለው ሁለት አድርገው ለየቅል ገለጿቸው የሚል ትርጉም ውስጥ ደርግ ሲገባ፣ በመጨረሻው መጨረሻም ስብሰባውን ረግጠው ወጥተው ጦሩን ለመቀስቀስ ሲሰናዱ የጄኔራሉ ግብ ምን እንደነበር ለመገመት ቢቸግርም፤ ለደርግ በተለይም ለሻለቃ መንግስቱ ምን ማለት እንደሆነ ግን ግልፅ ነው፡፡ ያም ሆነ ይህ ደርግ አማን ላይ እርምጃ ለመውሰድ ከዚህ የበለጠ ምክንያት መጠበቅ ነበረበት ብሎ ማሰብ የደርግን ባህሪ በቅጡ ካለመረዳት የሚመነጭ ነው የሚሆነው፡፡ መንግስቱ የአማንን ጉዳይ እልባት ለመስጠት የሚያስችል መነሻም፤ ድጋፍም፣ ፈፃሚ አካልም አላቸው፡፡ ነገር ግን ከዚያ በፊት ነገሩ መልሶ ቅርፅ መያዝ ነበረበት፡፡

የአማን ስብሰባ ረግጦ መውጣት ለደርግ አስደንጋጭ ዱብ ዕዳ ነበር፡፡ ስለዚህ ቤታቸው ገብተው ቁጭ ያሉትን ሊቀመንበር እንደምንም ተለማምጦ በስራ ገበታቸው እንዲገኙ ማድረግ የግድ ነው፡፡ "ጀግና፣ ኮዳ ትራሱ" እያሉ ራሳቸው ደርጎች እያሞካሹ በቴሌቪዥን በሬዲዮ እያዘመሩለት የነበረውንና መርጠው መሪ ያደረጉትን ሰው ዛሬ እንዲህ መሆኑ ቢታወቅ በጦሩ ውስጥ ምን ሊፈጠር እንደሚችል አስበው ተጨንቀዋል፡፡

ፍርሃት የናጣቸው ሻለቃ መንግስቱ ችግሮችን በውይይት እንፍታ የሚል የልምምጥ ቃልን አስይዘው ጄኔራል ግዛውንና ሻለቃ ብርሃኑ ባየህን በአማላጅነት ላኩ፡፡ አማን በጅ አላሉም፡፡ ቀጥሎ በመረጃ ኃላፊው የሚመሩ ልዑካን በሽምግልና ተላኩ፡፡ አማን ቤታቸው ውስጥ ሆነው "ወግድ!" ብለው መለሱዋቸው፡፡ በመጨረሻ መንግስቱ ራሳቸው መሄድ ነበረባቸውና ሄዱ፡፡ በምን አይነት መደራደሪያ እንደተመለሱ ከማየታችን በፊት መንግስቱ ስለ አማን በትዝታቸው ያሰፈሩትን ገለፃ እናስቀድም፡፡

"... ሰውየው ሁለት ሦስት ጊዜ እንደ ልጅ እያኮረፉ ትተውን ሄደው ነው ቤታቸው የሚቀመጡት፡፡ ሽማግሌ እየያዝኩ እየሄድኩ ነበር የምለምናቸው፡፡ ምን ነካዎት ጄኔራል? እባክዎ ይተው፤ ይች ልክ እንደ



እንቁላል የሆነች አገር ናት'ኮ እጃችን ውስጥ ያለችው፡፡ እኛ ላይ ታሪክ ጥሏታል፤ ብንለቃት'ኮ እንቦጨ የምትል ናት፡፡ እርስዎ እኛን ሰብሳቢ፣ እኛን መካሪ ነዎት እንጂ እኛ እየመጣን ጠዋት ማታ እንዴት ነው? ስላቸው "እኔን የማንም ሃምሳ አለቃና አስር አለቃ አያዘኝም!" አሉ፡፡

"እኔን በበኩሌ ብዙ ጊዜ በሚያንን ስልጣን ሲደልሉኝ ሞክረዋል፡፡"ብትፈልግ አንተ ጠቅላይ ሚኒስቴር፣ብትፈልግ መከላከያ ሚኒስቴር፣የፈለገህን ውሰድ፡፡ይሄን ሃምሳ አለቃውን ምናምኑን ግማሹን ሹመት ስጡት፡፡ወረዳ ገዥ ምናምን እያላችሁ ማሰናበት ነው፡፡ ከዚያ በኋላ ስራ ይሰራል እንጂ፤ እንዴት ነው በአስር አለቆች አገር የምትመራው? ብለውኛል፡፡

"እንዴት ነው ነገሩ? እርስዎ ምን ቸገረዎት? እርስዎን ያመጣዎ'ኮ ይሄ ኃይል ነው፡፡ ይሄ ኃይል ደግሞ የሚያገለግልበትና የሚፈለግበት ወቅትና ጊዜ አለ፡፡ ከዚያ በኋላ የራሱን ሂደት በራሱ ጨርሶ ይሄዳል፡፡ አሁን እስቲ በመጀመሪያ በዙሪያችን ያሰፈሰፈውን ጠላት እንመከት፡፡

.... ደርጉን በሚመለከት ላለው ነገር እኔ አለሁ፤ እርስዎ ስራዎን ይስሩ ብዬ ስንት ጊዜ ለምኛቸው አቅተውኛል..." ባይ ናቸው መንግስቱ፡፡ ሲቀጥሉም "ለምን እንደዚህ እንዳስቸገሩን ሳይገባን ቀርቶ በኋላ ነው የተገለጠልን፡፡ ኤርትራን የመገንጠል ዓላማ ነው፤ ደርግን የማፍረስ ጉዳይ ነው፡፡ ኃላፊነት የጎደላቸው ሆነው ነው ያገኘኋቸው" ሲሉ ይደመድማሉ መንግስቱ፡፡

የመጨረሻውን የመንግስቱን ልመና ተቀብለው፤ ነገር ግን አሁንም ቅሬታቸው እንዳለ በመግለፅ አንድ መደራደሪያ ያቀርባሉ፡፡ ይህም ሻለቃ መንግስቱ ጥር 7 ቀን 1967 ዓ.ም ጎፋ ሰፈር የሚገኘውን የታንከኛ ክፍል ጎብኝተው ስለ ኢትዮጵያ ትቅደም መርህ ለጦሩ መግለጫ ሰጥተው ነበርና "ይህ ተግባር እኔ ሳላውቅና ሳልፈቅድ የተከናወነ ነው፡፡ (መንግስቱ የጦር ክፍሉን በራሳቸው ስልጣን ነበር ያነጋገሩት) ስለዚህ እኔ ካልተፈለግሁና የእኔ አመራር ቦታ ከሌለው ለምልክትነት የምቀመጥ ሰው አይደለሁም፡፡ በመሆኑም የጎፋ ሠፈር ጉብኝቱም ሆነ መግለጫው በመገናኛ ብዙሃን እንዳይገለፅ ከተደረገ ብቻ ወደ ስራ ልመለስ" አሉ አማን፡፡ መንግስቱ ተስማሙና ጄኔራሉ ወደስራቸው ተመለሱ፡፡

መንግስቱ ቃላቸውን በማጠፋቸውና በእሁዱ የጦር ኃይሎች ፕሮግራም ጉብኝቱ በሚዲያ ሲተላለፍ አማን በማድመጣቸው ይበሳጫሉ፡፡ ለስራ ጉዳይ ወደ አንድ ክፍል ለመሄድ ጉዞ ላይ የነበሩት አማን ዘገባው መተላለፉን ሲሰሙ እቅዳቸውን ሰርዘው ተመለሱና ወደ ቤታቸው ሄዱ፡፡ አልተመለሱም፡፡ በዚህ ጊዜ ነው ከላይ ያየነውን እንቅስቃሴ የጀመሩትና ከአዛዦች ጋር ትብብርን የሚጠይቁ የስልክ ልውውጦች፣ ስድቦችና

ዛቻዎች የተኸኮንደነዱበት ንግግራቸው ተጠልፎ ለሻለቃ መንግስቱ የተሰጣቸው፡፡

ሻለቃው ጊዜ አላጠፉም፤ ከአዲስ አበባና ከሌላውም ክልል ንዑስ የደርግ አባላትን ባስቸኳይ ጠሩ፡፡ ንዑስ አባላቱም ዋና አባላቱም ፈጥነው በደርግ ጽ/ቤት ተሰበሰቡ፡፡ በመንግስቱ አገላለፅ አጠቃላይ የተሰብሳቢው ቁጥር ስድስት መቶ ይደርሳል፡፡ ጎን ለጎን ደግሞ ከአንደኛው ክፍለ ጦር 6ኛ ብርጌድ የተውጣጡ ወታደሮች ተመርጠው ጄኔራል አማንን እንዲይዙ ትዕዛዝ ተሰጣቸው፡፡ ወታደሮቹ ግን "እንዴት በአማን ላይ አፈሙዝ እንቀስራለን?" በማለት ትዕዛዙን አንቀበልም አሉ፡፡ ደርግ ክው አለ፡፡ አሁንም ለሌላ ክፍሎች ትዕዛዝ ተሰጠ "አማንን የሚያክል ጀግና ምን ሲደረግ? አንችልም!" አሉ፡፡ የአማን ማፈንገጥ፣ የወታደሩን ትዕዛዝ አንቀበልም ማለት የደርግን ሀልውና እንደሚያፈራርሰው የሰጉት አባላት ተስፋ ቆረጡ፡፡ ጦሩ አፈሙዙን ወደ ደርግ ሊያዞር እንደሚችል ታመነ፡፡ ስለዚህ የመጣው ይምጣ ብሎ ባለው የቅርብ ጦር አማንን መደምሰስና የሚመጣውን ለመቀበል ከመዘጋጀት ውጪ ደርግ ሌላ ምርጫ አልነበረውም፡፡ ለደርግ ጥበቃ ተብለው የመጡ ኮማንዶዎችን ከተወሰኑ የደርግ አባላት ጋር በታንክ ታግዞ ሻለቃ ዳንኤል አስፋው ጦርኃይሎች አካባቢ ወደሚገኘው የጄኔራል አማን መኖሪያ ቤት ዘመተ፡፡ ጄኔራሉ እጅ እንዲሰጡ ቢጠየቁም ጀግና እጁን ስለማይሰጥ የጦፈ ውጊያ ገጠሙ፡፡ አንድ ግለሰብ በታንክ የታገዘውን ጦር ገጥመው ጥቂቶችንም ገድለው በመጨረሻ ተገደሉ፡፡

በዚሁ ጊዜ ደርግና ንዑስ የደርግ አባላቱ ስብሰባ ተቀምጠው ስለአማን አስቸጋሪነትና ስለፈፀማቸው ተግባራቶች እየተነተኑ ምን እናድርጋቸው? ተብሎ እየተጠየቀ ነው፡፡ በዚህ መሀል ሻለቃ ዳንኤል የአማንን መገደል ለመንግስቱ በጆሯቸው ሹክ ብሏቸው ይወጣል፡፡ ይህን የሰሙት መንግስቱ የስብሰባውን አጀንዳ በድንጋጤ አሰፉትና ስለታሰሩት የንጉሡ ሹማምንት ጉዳይ አነሱ፡፡

እርግጥ መንግስቱ "የዚያን እለት አጀንዳ የጄኔራል አማን ጉዳይ ነበር፡፡ብቸኛው አጀንዳ እሳቸው ነበሩ፡፡ሌላ ስለቀድሞ የኃይለስላሴ መንግስት ባለስልጣኖች የሚል ነገር ጨርሶ አልነበረም፡፡አሁንም ደግሜ ላረጋግጥ የምፈልገው እኔ፣ሌሎች የንዑስ ደርግ አባላት፣ የጦሩ ተወካይ የተባለ ሁሉ አንድ ሳይቀር እንዲገኝ የፈለግሁት ውሣኔው ምንም ይሁን ምን የአማን ጉዳይ ሠራዊቱ ውስጥ የሚያስከትለውን ስሜት ስለማውቅ ሁሉም እጁን እንዲያስገባ ነው፡፡እኔ ይህቺን አስቤ ነው የጠራኋቸው እንጂ ለኃይለስላሴ ሚኒስትሮችና ጄኔራሎች ምን ስብሰባ መጥራት ያስፈልጋል? መርማሪ ኮሚሽን ተቋቁሟል፣በቃ ይሄው ነው..." ብለዋል፡፡እናም ስለአንድ ጄኔራል ስብሰባ መጠራታቸው ያላስደሰታቸው አባላት "የሱን ጉዳይ ተውት



ምን አንድ ጄኔራል ይልቅስ የነዚያን ደም መጣጭ ጉዳይ ዳር ሳናደርስ አንወጣም!"በሚል ተሰብሳቢዎቹ አዳራሹን ቀውጢ እንዳደረጉት ነው የሚገልፁት፡፡

ምንም ይሁን፣ ምንም ይባል ግን የአማን ሞት በሚዲያ በሚገለፅበት ጊዜ ምን ሊፈጠር እንደሚችል በማሰብ ፍርሃት የወረራቸው የደርግ አባላት በተለይ መንግስቱ ጦሩ ቢያምፅና በደርግ ላይ ቢነሳ ደርግም መፍረሱ ነውና፣ ያ ከሆነ አይቀር ደግሞ ያለፈው ስርዓት እንደይመለስ ቢያንስ እነዚያን (በተለምዶ ስልሳዎቹ የሚባሉትን) የቀድሞ ታላላቅ ባለስልጣናት አጥፍቶ መጥፋት የሚሻል መሆኑን እንደመረጡ ግልፅ ነው፡፡ ሻለቃ መንግስቱ ከደቂቃዎች በፊት ብቻቸውን የሰሙትን የአማንን መገደል የተሰብሳቢው ስሜት እየጋለ መሄድን ሲረዱ ስብሰባው ላይ ይፋ አደረጉት፡፡

ከዚህ በኋላ ማለትም ከህዳር 1967 ዓ.ም ጀምሮ የደርግ መንግስት የ"በለው!" አራማጅ ሆነ፡፡ የደርግ መንግስት በ"በለው!" ጀምሮ በ"በለው!" ሊፈፀም ግድ ሆነ፡፡ 60ዎቹ የቀድሞው ባለስልጣናት መንግስቱ እንዳሉት የእለቱ አጀንዳ አልነበሩም፤ ሊሆኑም አይችሉም፡፡ ምክንያቱም የእነሱን ጉዳይ አጣርቶ ለፍርድ የሚያቀርብ መርማሪ ኮሚሽን ተቋቁሟል፡፡ እጅግ በተደራጀ መልኩ እነ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያምን የመሳሰሉ ምሁራን ሳይቀሩ የኮሚሽኑ አባላት ሆነው፣ በስርዓት ዳኞች ተሾመው ጉዳያቸው በሕግ እየታየ ነው፡፡ ኮሚሽኑ አጣርቶ የሚደርስበትን ውጤትም ለህዝብ ይፋ እንደሚደረግ ቃል ተገብቷል፡፡

- ነገር ግን የጄኔራል አማን መገደልና በጦሩ ውስጥ የነበራቸው ተሰሚነት፤ እንዲሁም እሳቸውን ለመያዝ የታዘዙት ሁሉ አሻፈረኝ ማለት፣ ይህንንም ተከትሎ የተፈጠረው ፍርሃት ወለድ ምስቅልቅል ነገሮችን ለዋወጠ፡፡ ስለዚህ ደርግ "እቃ እቃ ፍርስርስ፣ አንድ እንጀራ ቁርስርስ" አይነት የልጆች ጨዋታ አድርጎት አረፈ የኮሚሽኑን ጉዳይ፡፡

ከዚያ በኋላማ ምኑ ቅጡ! "በለው፣ በለው፣ በለው!" ተባለ፡፡ ይህን ጉዳይ ራሳቸው መንግስቱ እለቱን እያስታወሱ አዳራሹ ውስጥ የተከሰተውን የዚያችን እለት ሁኔታ ሳይዋሹ ይተርኳታል፡፡

"... ምን የእኛ ነገር ... በለው! ነው" በማለት ስም እየጠቀሱ ትዝታቸውን አካፍለዋል፡፡ ቀንጨብ ቀንጨብ እያደረግን እንየው "... ትዝ ይለኛል መቶ አለቃ እገሌ ይባላል፡፡ ከሦስተኛ ክፍለ ጦር ህክምና ክፍል ነበር የመጣው፡፡ መቼም ተናጋሪ ነው እሣት ነው የሚተፋው፡፡ ብድግ ብሎ ሲናገር ቤቱን በጭብጨባ አናጋው፡፡ ዛሬ ታሪካዊ ቀን ናት፡፡ የኢትዮጵያ ትንሣኤ ቀን ናት፡፡ ይህቺን ታሪካዊ ቀን እንጠቀምባት፡፡ ይሄን ዶሮ እየተቀለበ የተቀመጠ የወሎ ህዝብ ነብሰ ገዳይ (ረሃቡን) አንድ ውሣኔ ሳንሰጠው መሄድ የለብንም፡፡ አይሸታችሁም እንዴ ዶሮው?

የሻለቃ መንግስቱ ኃይለማርያም መልስ ነው፡፡ (ትዝታዎች ቁ.1 ገፅ 163) ይሄ ነው አስቂኙ ፍርድ፡፡

ለጥቂት ወራት ያህል ታስረው የቆዩት የቀድሞው ባለስልጣናት ህዳር 14 ቀን 1967 ዓ.ም ሞት ከተበየነባቸው በኋላ ምሽት ላይ ከታሰሩበት ከታላቁ ቤተ-መንግስት ጊቢ ውስጥ በጃንሆይ ጊዜ ለጠጅ ማቀዝቀዣ ያገለግሉ ከነበሩት የምድር ቤት ክፍሎች እየተጠሩ እንዲወጡ ከተደረገ በኋላ ሁለት ሁለት ሆነው እየተጣመሩ በካቴና ታስሩና በትልቅ ካሚዮን ተጫኑ፡፡ ደርግ መቼም ፈጣን ነው ሁሉንም ነገር አዘጋጅቷል፡፡ የጫናቸው ካሚዮን ወደ ዋናው ወህኒ ቤት ነበር የሚነጉደው፡፡ ታሳሪዎቹ በውስጣቸው ተስፋ አለ፡፡ ቤተሰብ አይጠይቃቸው ስለነበር ከዚህ በኋላ ጥየቃ ያለበት ቦታ ሊታሰሩ እንደሚችሉ ጠብቀዋል፡፡ ወህኒ ቤቱ ጊቢ ውስጥ ደርሰው ከመኪና ሲወርዱ በውስጣቸው የነበረው ተስፋ ሳያንሰራራ አይቀርም፡፡ ሆኖም ከወረዱ በኋላ እስረኞች ወደሚታሰሩበት ቦታ የሚወስደውን መንገድ ትተው ታጠፉና ድቅድቅ ጭለማ ውስጥ ተደርድረው እንዲቆሙ ተደረገ፡፡ ለመደንገጥ የሚያበቃ ጊዜ አላገኙም፤ በተጠንቀቅ ቆመው ይጠብቋቸው የነበሩ ወታደሮች በእሩምታ ተኩስ ይረሽኗቸዋል፡፡ ወዲያውም እዚያው በቡልዶዘር በተቆፈረ ወጥ ጉድጓድ ውስጥ በጅምላ ተቀብረው አፈሩ ተመልሶ እንደቀድሞው ሜዳ ሆነ፡፡

ህዳር 15 ቀን 1967 ዓ.ም ደርግ በብዙሃን መገናኛ ይህን ጉዳይ ይፋ አደረገ፡፡ "በእስር ላይ የነበሩት የቀድሞው ባለስልጣናት በትናንትናው እለት አማንን ጨምሮ አብዮታዊ እርምጃ ተወስዶባቸዋል!" በማለት ሲገለፅ ድፍን የኢትዮጵያ ህዝብ በአግራሞትና በድንጋጤ ነበር ያደመጠው፡፡

ጂሚ ካርተርማ ይሄን ወሬ እንደሰሙ በድንጋጤ ባሉበት ደርቀው ቀሩ ማለት ይቻላል፡፡ በዚያው ወቅት "የዓለም ሰብዓዊ መብት ጥበቃ መሪ እሆናለሁ" በሚል ማኑፌስቶ የአሜሪካንን ምርጫ አሸንፈው ፕሬዝዳንት የሆኑት ካርተር "ያለምንም ደም" የተሰኘውን የኢትዮጵያ አብዮት በበጎ ዓይን አይተውት ነበር፡፡ ሆኖም ወዲያው በደም መጀመሩን ሲያዩ ክፉኛ ተቃወሙት፡፡ ሳይውሉ ሳያድሩም በኢትዮጵያ ላይ ጠንካራ አቋም በመውሰድ ፊታቸውን አዞሩ፡፡

የኢትዮጵያና የአሜሪካ ጉዳይም በዚሁ ያከትማል፡፡ እንጂማ ደርግ በመጀመሪያ ያንኳኳው የአሜሪካንን ደጃፍ ነበር፡፡ መንግስቱ ሐራሬ ሆነው ለሪካርዶ ኦሪዚዮ እንዲህ ብለውታል፤ "... የቆምኩት ከጎናችሁ ነው፤ ሁለቱ ሀገሮቻችን የረጅም ጊዜ ወዳጆች ናቸው፡፡ ሌላው ቀርቶ ኢትዮጵያ ከእናንተ ጎን ተሰልፋ ወታደር በመላክ በኮሪያ ጦርነት ተካፍላለች፡፡ አሁን ሀገራችንን እንደገና ለመገንባትና ለማሳደግ የእናንተን እርዳታ እንፈልጋለን፤ በማለት የአሜሪካኖችን በር አንኳኳሁ" አሉና ለጊዜው



ንግግራቸውን አቋርጠው በትዝታ ጭል...ጥ አሉ፡፡ ወዲያው ቀጠሉና "ካርተር በሰጡኝ መልስ የቬትናም ጉዳይ ከአቅም በላይ እንደሆነባቸውና በስትራቴጂ ደረጃም አፍሪካ ላይ ምንም ትኩረት እንደሌላቸው ገለፁልኝ፡፡

"... ቀጥዬ ያንኳኳሁት የቻይናን በር ነበር፡፡ ሆኖም ከቁም ነገር የቆጠረኝ ሰው አላገኘሁም፡፡ መጨረሻ ላይ ፊቴን ወደ ሞስኮ፤ ወደ ሊዮኔድ ብሬዥኔቭ አዞርኩ፡፡ እውነቱን ነው የምልህ ለመጀመሪያ ጊዜ በክሬሚሊን ቤተ-መንግስት እንዴት አድርገው አንገቴን አቅፈው እንደተቀበሉኝ አሁንም ድረስ ትዝ ይለኛል" አሉ፡፡

ሪካርዶ ኦሪዚዮ ትረካውን ይቀጥላል፤ ... "መንግስቱ የዚያን ጊዜውን ሁኔታ በዓይነህሊናቸው እያስታወሱ፤ ዝም እንዳሉ ቀሩ፡፡ አፍሪካዊው ፕሬዝዳንት በዚያን ቀን የብረት መጋረጃ ሀገራት መሪዎች አድርገውት ያዩትንና ከግልገል በግ ፀጉር የተሰራውን የሱፍ ባርኔጣ አድርገው ነበር፡፡ በወቅቱ የነበረው የሞስኮ አየር ከመቀዝቀዙም በላይ ኢትዮጵያ ለመጡት ወጣት መኮንን የፖለቲካው አየር ብዙም የሚሞቅ አልነበረም፡፡

መንግስቱ ይቀጥላሉ "እናም ስለሁኔታው ለብሬዥኔቭ ገልጬ ሳስረዳቸው "መንግስቱ ሀገሬ ከአቶሚክ ቦንብ በስተቀር ያስፈልገኛል የሚሉትን ነገር ሁሉ ልትሰጥዎት ፈቃደኛ ነች" የሚል መልስ ሰጡኝ፡፡ እንግዲህ ግንኙነቱ የተጀመረው በዚህ መልክ ነበር" አሉ መንግስቱ፡፡ ሲቀጥሉም "የሶቭየት እርዳታ በቃላት ብቻ የተወሰነ ሳይሆን በማቴሪያልም ጭምር ነበር፡፡ ከዚያች ቀን በኋላ ብሬዥኔቭ ልክ እንደ አባቴ ሆኑ፡፡ ለ12 ጊዜ የተገናኘን ሲሆን፤ ሁሉም ግንኙነታችን የተደረገው እዚያው ሞስኮ ውስጥ ነበር፡፡ በተገኘን ቁጥር ችግሬን ከመናገሬ በፊት ምንጊዜም "ጓድ ብሬዥኔቭ ልጅዎ ነኝ፡፡ ውለታዎም ይህ ነው አይባልም" ነበር የምላቸው፡፡ እውነትም ታዲያ ብሬዥኔቭን የማያቸው ልክ እንደወለዱኝ አባቴ ነበር" /Talk of the Devil/ ኢትዮጳያና ሶቭየት በዚህ መልኩ ተጣብቀው ቀሩ፡፡

ደርግ የቀድሞ የጃንሆይ ባለስልጣናትን መገደል ይፋ ካደረገ በኋላ ያሰጋው የህዝብ ተቃውሞ የፈራውን ያህል ሆኖ ሳይደመጥ ቀረ፡፡ የደርግ ቀጣይ ስራ በተገደሉት በጄኔራል አማን ምትክ አንድ አሯሯጭ ከፊት ማስቀደም ነበርና ብርጋዴል ጄኔራል ተፈሪ በንቲን መርጦ የደርግ ሊቀመንበር ብሎ ሾመ፡፡ መንግስቱም በምክትልነታቸው ቀጠሉ፡፡

### *የአብዮቱ ፍሬዎች*

የደርግ ታሪክ ገለባ ብቻ ተደርጎ በተደጋጋሚ ይወሳል፡፡ ነገር ግን ገለባው ይብዛ እንጂ በውስጡ ፍሬዎች ነበሩት፡፡

ደርግ ያንን የ"በለው" ፍርድና የአማንን ግድያ ለማስዘብ ሁለት አፋጣኝ ስራዎች ይጠብቁት ነበር፡፡ የመጀመሪያውን በአገር ውስጥና

ከአገር ውጪ በወታደራዊ ተግባራቶች ተሰማርተው አገራቸውን ያገለገሉትንና በሠራዊቱም ዘንድ ተወዳጅነት ያላቸው፣ ነገር ግን እንደ ጀኔራል አማን የስልጣን ጥም የማይንፀባረቅባቸውን የሁለተኛው ክፍለ ጦር አባል ብርጋዴር ጀኔራል ተፈሪ በንቲን በአማን ቦታ መተካት ነበረበትና እሱኑ ተግባራዊ አደረገ:: የኦሮሞ ተወላጅ ስለነበሩም ሰፊውን የኦሮሞ ማኅበረሰብ ድጋፍ ያስገኛሉ ተብሎ ታስቧል:: በዚህ ሹመት የደርግን አካሄድ በጥርጣሬ ዓይን ለማየት የተዘጋጀውን የሚሊቴሪ ክፍል ለማረጋጋት ተቻለ::

በሌላ በኩል ሲቪሉን ህብረተሰብ ዳር እስከ ዳር፣ ከምሁር እስከ ገበሬ የሚያስፈነድቅ ተግባር ጊዜ ሳይሰጥ ማከናወን ነበረበትና እሱኑ ተግባራዊ አደረገ።።

በእነ ዶ/ር ሠናይ ልኬ እና ኃይሌ ፊዳ ምክር በመደገፍ ሶሻሊስታዊውን ስርዓት ዘረጋ:: የሠራተኛ አዋጅ አሻሽሎ ካወጣ በኋላ፣ የእድገት በኅብረት የእውቀትና የስራ ዘመቻንም በማወጅ የኢኮኖሚ ፖሊሲውን ቀየሰ::

ታህሳስ 11 ቀን 1967 ዓ.ም "የኢትዮጵያ የእድገት ጎዳና የሚመራው በሳይንሳዊ ሶሻሊዝም ነው" ሲል ይፋ አደረገ። በዚህ አዋጁ ምሁራኑንና የግራ ክንፍ ኅቡዕ ቡድኖችን ሁሉ በደስታ አዘለለ።አዋጁ ይፋ በሆነ ማግስት የተማረው ወጣት ትውልድ ወደ ገጠሩ እንዲዘምት የቀረበለትን ጥሪ በደስታ ተቀበለ::

ታህሳስ 12 ቀን የእድገት በኅብረት የስራ ዘመቻ የክተት አዋጅ በዓል በድፍን ኢትዮጵያ ተከበረ:: ለዘመቻው 60 ሺ. ተማሪዎችን የወከሉ የአዲስ አበባ ዘማቾች እለቱን ለማክበር በጃንሜዳ ተሰለፉ:: በዓሉን በጋራ ለማክበር በጃን ሜዳ ሰልፍ ላይ ሦስቱ ሊቀመናብርት ማለትም ጀኔራል ተፈሪ በንቲ፣ ሻለቃ መንግስቱና ሻለቃ አጥናፉ አባተ ተገኝተዋል። ያ ሁሉ ህዝብ በአንድ ድምፅ "መንጌ! መንጌ! መንጌ!" ሲል ጮኸ። ለመጀመሪያ ጊዜ ሊቀመናብርቱ በአደባባይ ታዩ:: መንግስቱም ላንቃው እስኪሰነጠቅ ስማቸውን እየጠራ ለደቂቃዎች ያህል የቆየውን ህዝብ ሲያዩ ልዩ ስሜት ተሰማቸው።

ደርግ የጋራ ውሣኔ አሳልፎ ያንን ግድያ ከፈፀመ በኋላ ስልጣን አስረክቦ ወደ ካምፕ መመለስ ማለት እራሱን ለፍርድ ማቅረብ መሆኑን ያውቃል። እንኳን ይህ ምክንያት ኖሮ ባይኖር እንኳ ስልጣን አስረክቦ የመመለስ እቅድ አልነበረውም። ስለዚህ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግስትነቱን ትቶ ቋሚነቱን አጠናክሮ ከመቀጠል ሌላ ምርጫ ስላልነበረው፤ በተቻለ መጠን የምሁራኑን ሀሳብ የራሱ አድርጎ ወደተግባር መተርጎምና አገሪቱን መምራት ነበረበት። ጊዜያዊ መንግስትነቱን ግን ለሽፋንም ቢሆን አልቀየረም። እናም ደርግ ርዕዮቱን ሶሻሊዝም አድርጎ



ሳይውል ሳያድር የገጠሩን ህይወት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለመቀየር የነደፈውን እቅድ ተግባራዊ አድርጓል::

ይህ "ብሔራዊ የእድገት በኅብረት ዘመቻ" ዓላማው የሁለተኛ ደረጃና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎችንና መምህራንን ወደ ገጠር በማዝመት የኢትዮጵያ ትቅደምን መርህ መሠረት ያደረጉ የልማት እንቅስቃሴዎችን እንዲመሩ ማድረግ ነው።

እቅዱ በትክክለኛ ሚዛን ሲቀመጥ ኢትዮጵያን ከኋላቀርነት ለማውጣት የሚረዳና፣ በተለይም በተማረው ክፍል የምክር፣ የትምህርትና የጉልበት ድጋፍ የገበሬው ህይወት የተሻለ እንዲሆን የሚያደርግ ነበር። ይህን በመረዳትም ነው ብዙሃኑ ምሁራን በደስታ የተቀበሉትና የዘመቱት። ሆኖም የደርግ የስልጣን ተፋላሚ የሆነው ኢህአፓ ብቻ የእቅዱ ተቃዋሚ ሆነ:: ምክንያቱንም ሲያስቀምጥ፤ "የተማረውን ክፍል በልማት ስም ወደ ገጠሩ በማግለል ደርግ ብቻውን በስልጣን ላይ ለመደላደል ሲል የነደፈው" በማለት ነው:: ኢህአፓ ሰሚ አላገኘም፣ ዘማቾቹ የድጋፍ ሰልፋቸውን ካሳዩ በኋላ ወደ ገጠር ዘመቱ:: የገጠሩን ህይወት የመለወጡን ተግባርም ተያያዙት።



ዘማች ተማሪዎች ተግባራቸውን ሲወጡ

ደርግ የግራ ኃይሎችን ተቃውሞ ወዲያው ለማለዘብ የኢትዮጵያ ትቅደምን መርህ በመከለስ "ዓላማችን ኅብረተሰባዊነት፣ ርዕዮታችን ሶሻሊዝም ነው" ቢልም፤ ብቸኛ ዓላማቸው ስልጣን ብቻ የነበረው ተቃዋሚዎች (ኢህአፓዎች) ሊሰሙት አልቻሉም።

ደርግ እያራመደ ያለው የኢህአፓንና የመኢሶንን ማኑፌስቶ ነው። መኢሶን ከደርግ (ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን) ተለጥፎ የነበረ ሲሆን፤ ኢህአፓ በውጭ ሆኖ ነበር የሚሞግተው። ደርግም ከመኢሶን መስራች ምሁራን በሚቀበለው እቅድ ስራውን ቀጥሏል። የንግድ፣ የኢንደስትሪና የገንዘብ ተቋማትንም ደርግ ወርሷል። ይህ በእንዲህ እንዳለ የካቲት 25 ቀን 1967 ዓ.ም የጃንሆይ ተቃዋሚ የነበሩ ምሁራን ለዘመናት ሲያቀነቅኑት የኖሩትና በጉጉት ይጠብቁት የነበረውን የመሬት ስሪት

እንዲያድርባቸውና፤ በገፍ የያዙት ሐብትና ንብረት ለአገራቸው ተቆርሶ ቢሰጥና ማኅበራዊ ለውጥ ቢመጣ ተጠቃሚዎች ራሳቸው መሆናቸውን ማሳመን ይጠበቅበታል፡፡ ከራስ ጥቅም ይልቅ የሀገርን ጥቅም የማስቀደም ባህል ያላቸው ህዝቦች ያሏት አገር ብቻ ሳያኮርፉ "ይሁን" በማለታቸው በርዕዮቱ ተጠቃሚ ሆነው ያለፉ አገራት ታይተዋል፡፡

በኢትዮጵያ ግን አኩራፊዎችን ማሳመን አልተቻለም፡፡ አይቻልምም፡፡ ምክንያቱም ኩርፊያው የርዕዮትና ርዕዮቱን ተከትሎ በሚመጣው ጉዳይ ስላልሆነና በስልጣን ብቻ ስለሆነ ነው፡፡ የብዙሃኑ ምናልባትም ከጃንሆይ ዘመን ባለስልጣናትና ሹማምንት በስተቀር የሁሉም ህዝቦች፣ የተደራጁ የግራ ክንፍ ተቃዋሚ ቡድኖች፣ በአገር ውስጥም በውጭም ያሉ የቀድሞው አገዛዝ ተቃዋሚዎች ዓላማና ርዕዮት ደርግ እየተገበረው ያለው ነው፡፡ ከተገንጣይና አስገንጣይ ቡድኖች ውጪ ሁሉም የዚህ መፈክር አራማጅ ነበር፡፡

ስለዚህ "በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ" እንደሚባለው ሆነ፡፡ ርዕዮቱ በራሱ በአፈፃፀም ችግር የሚፈጥረው ቀውስ አልበቃ ብሎ፣ ጭራሽ የተደራጀ ተቃዋሚ ቡድን በኢትዮጵያ ኖሮ የደርግን የሚደገፍ (ሁሉም ሲመኘው የነበረውን) አዋጅና ተግባር ማጨናጎል ደርግን ለመቃወም ከሚተኩሷቸው መሣሪያዎች ያልተናነሰ የማጥቂያ መሣሪያ አደረጉት ኢህአፓዎች፡፡

የደርግ መንግስት የእድገት በኅብረትን እቅድ ተግባራዊ ሲያደርግና ዘማቾቹም በሙሉ ልብ ችግር ያደቀቀውን አርሶ አደር ያሳተፈ ስልት እየተከተሉ ስራቸውን ሲሰሩ፤ ከዘማች ተማሪዎች ውስጥ የተቃዋሚ ኃይሉ ደጋፊዎችም ተካተው ዘምተዋል፡፡ ይህም አልበቃ ብሎ ተማሪዎች ገበሬውን በመለወጡ ተግባር ላይ ሲያተኩሩ፤ የደርግ ባለስልጣናት ደግሞ ቢሮክራሲው ላይ አተኮሩ፡፡

ቀስ በቀስም የዘመቻ ጣቢያዎች ደርግና ደጋፊዎቹ በአንድ ወገን፣ የደርግ ተቃዋሚ የኢህአፓ አባላትና ደጋፊዎቹ በሌላ ወገን ሆነው የሚፋለሙበት ምቹ መድረክ ሆነ፡፡ ዘመቻው እየተራዘመ በሄደ ቁጥርም ፍልሚያው አብሮ እየተጋጋለ ስለሄደ ተቃዋሚዎች የዘመቻ ምድብ ጣቢያቸውን እየለቀቁ የስልጣን ፍልሚያ ለማድረግ ምቹ ወደሆነችው ወደ አዲስ አበባ መምጣት ጀመሩ፡፡ ሙግቱንም ቀጠሉ፡፡ ደርግ የሚከተለውን ርዕዮት መሰረት በማድረግ የወሰዳቸው እርምጃዎች የርዕዮቱ አንድ አካል /እሠራር/ ነውና ከገጠር መሬት ስሪቱ በኋላ አርሶ አደሩ ምርቱን መንግስት በተመነው ዋጋ ለመንግስት ብቻ እንዲያቀርብ ተብሎ ለተቋቋመው የእርሻ ሰብል ገበያ ድርጅት ማቅረብ ነበረበት፡፡



የከተማ መሬትንና ትርፍ ቤቶችን በሚመለከት ተግባራዊ የሆነው አዋጅም ብዙዎቹን ተጠቃሚ ማድረጉ ባይዘነጋም፤ ስልጣን የተሰጣቸው ቀበሌዎች ከአስተዳደር ስራቸው ይልቅ ቁጥጥሩ ላይ በረቱ፡፡

በአንድና በሌላ አገላለፅ የደርግ መንግስት፤ የአገር ሐብት ሆነው ሳለ በግለሰብ እጅ ገብተው ቀርተው የነበሩትን ሐብቶች ወደ መንግስት እጅ በማዛወሩና ፍትሐዊ ክፍፍል በማድረጉ ተጠቃሚ የሆነው ብዙሃኑ ህዝብ በደርግ ቁጥጥር ስር መሆን ነበረበት፡፡ ያጠፋውን ቀጪ፣ ታምኖ ያገለገለውን ሸላሚ ደርግ ሆነ፡፡ በመንግስት እጅ የገቡት የኢኮኖሚ አውታሮች የደርግን ስልጣን ለማደላደል ረዱት፡፡

ከገጠሩ ዘመቻ ለቀው የመጡትም ሆኑ በከተማ የነበሩት ተቃዋሚዎች ከርዕዮቱ ጋር ሳይሆን ርዕዮቱን ተከትለው በሚመጡ ችግሮች መነሻነት የጠላትነት ክርክራቸውን ያጧጧፉትም በእነዚህ ክፍተቶች እየሆነ ሄደ፡፡

የመሬት ስሪቱን "ምርታማነት ወይስ ፍትሐዊነት?" ሲሉ ተቹት፡፡ ገበሬው በመሬቱ ላይ ያለው ስልጣን በማምረት ብቻ መወሰኑም "የባለቤትነት ስሜት ካላደረበትና በባለቤትነት የተሰጠውን መሬት ያሻውን ካላደረገው ትርጉም የለውም" የሚል ነቀፋ ጀመሩ፡፡ ከዚህም ባለፈ ከመሬት አዋጁ ጋር በተያያዘ አዲስ የሰፈራ ፕሮግራም መደረጉ የግድ ነበርና፤ ይሄንንም "በሰፋሪው ፈቃደኝነት ላይ ያልተመሠረተ ነው" አሉት፡፡ የሚገርመው ይሄን ሁሉ የተቃውሞ ትችት የሚያዥጎደጉዱት ተቃዋሚዎች ማርክሳዊ መፈክርን ያነገቡ መሆናቸው ነው፡፡ ምንም ቢባል ግን እነዚህ የደርግ ወይም የአብዮቱ ፍሬዎች ብዙሃኑን የኢትዮጵያ ህዝብ ተጠቃሚ ማድረጋቸው አይዘነጋም፡፡

ከእነዚህ አዋጆች ተግባራዊነት ጋር በተያያዘ የተከሰተው አንኳር ችግር ግን የአገሪቱ ኢኮኖሚ በደርግ መንግስት ቁጥጥር ስር ሆኖ ሲቀጥል የግሉ ዘርፍ እየተሽመደመደ መሄዱ ነው፡፡ (ይህን ያስተዋሉት የቢዝነስ አድሚንስትሬሽን ትምህርት የተከታተሉት ከመንግስቱ ቀጥሎ ስልጣን የነበራቸው ሻለቃ አጥናፉ "ቅይጥ ኢኮኖሚ" /mixed economy/ ይሻለናል ብለው ነበር፡፡ በዚህች ንግግራቸውም ነበር በደርግ የተገደሉት፡፡)

እንግዲህ ከተማን ማዕከል ያደረገው የደርግ እርምጃ በትርፍ ቦታና ቤት ዙሪያ እንደመሆኑ መጠን አዲስ የቤት ቁጥር የተሰጣቸው ተጠቃሚዎችም እንቅስቃሴያቸው ሁሉ በመንግስት ቁጥጥር ሆኖ፤ ያስተዳደር ስልጣን በተሰጣቸው የቀበሌ ሹማምንት መዳፍ ስር ገብተዋል፡፡ ሲሆን በስለላ አሊያ በጥቆማ ቀበሌውን መርዳት ነበረባቸው፡፡ ቀበሌውም ተቃዋሚዎችን ያድናቸው ነበር፡፡

በእነዚህ መሰል መነሻዎችም ነው በቀጣዮቹ ተከታታይ አመታት የኢህአፓ ታጣቂዎች የቀበሌ መሪዎችን፣ የቀበሌ መሪዎች የኢህአፓ

ታጣቂዎችን እያደኑ መግደል ባህላቸው ያደረጉትና ነጭና ቀይ ሽብር ድረስ ያዘለቁት፡፡

ደርግ የጎን ውጋት የሆነበትን ኢህአፓን እርሙን ያወጣ ዘንድ ጥቂት ምሁራንን ከጎኑ አድርጎ በሚያዚያ 12 ቀን 1968 ዓ.ም የብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮትን መመሪያ አድርጎ አወጀ፡፡ ይህች ከቻይና አብዮት የተኮረጀች ቀመርም ዓላማና ግቧ በወዝአደሩ፣ በአርሶ አደሩና በንዑስ ከበርቴው አብዮታዊ ጥምረት የሰፊው ህዝብ ጠላቶች ተብለው የተፈረጁትን ፊውዳሊዝምን፣ ኢምፔሪያሊዝምንና ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝምን ድራሻቸውን ማጥፋትና፤ ህዝባዊ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን መመስረት ነው፡፡ ይህም ኢሠፓአኮ፣ ኢሰፓ፣... ወዘተ... እየተባለ ቀጥሎ ወደፊት እንደምናየው በ1980 ዓ.ም እውን መሆን የቻለ ሲሆን፤ተጀምሮ እስኪጨረስም ብቸኛው መሪ መንግስቱ ኃይለማርያም ሆነው እንዲቀሩ ሆኗል፡፡

ሶሻሊስታዊ ስርዓትን መመሪያው አድርጎ በመንግስቱ ኃይለማርያም መሪነት ለ17 ዓመታት የዘለቀው የደርግ አገዛዝ፤ በአብዮቱ ማግስት ቀደም ሲል ያየናቸውን ለውጦች አምጥቷል፤ ብዙሃኑ የኢትዮጵያ ህዝብም ከአብዮቱ የድል ፍሬዎች ተቋዳሽ በመሆኑ ተጠቃሚ ሆኗል፡፡ ደርግ ስልጣን ላይ በቆየባቸው ከ1967-1983 ድረስም እንደ መንግስት ለአገር መስራት ያለበትን ስራ ሠርቷል፡፡ የመሠረተ ልማት አውታሮችን ዘርግቷል፣ የኢንደስትሪ ተቋማትን ገንብቷል፣ ማሃይምነትን ለማስወገድ ልዩ ጥረት አድርጓል፡፡ ጥቂቶቹን ከወዲሁ በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር ጠቃቅሶ ለማለፍ ያህል፤ የብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ቁ.4/ሀ/ "ለሰፊው ህዝብ እድገትና ለተሟላ ኑሮ የሚያገለግል፣ ለህዝብ ልጆች በሙሉ የሚደርስ፣ ለፀረ ፊውዳል፣ ለፀረ ኢምፔሪያሊስት ትግል የሚያግዝ ነፃ ትምህርት ደረጃ በደረጃ እንዲስፋፋና ማሃይምነት ከአገሪቱ እንዲጠፋ የሚደረግ መሆኑን" ስለሚገልፅ ይህን አዋጅ መሠረት አድርጎ በገጠርም በከተማም ተግባራዊ በማድረግ ከፍተኛ ለውጥ አሳይቷል፡፡ "የማይጽፉ እጆች፣ የማያነቡ ዓይኖች አይኖሩም" በሚል መፈክር በአንድ ዙር የ3 ወር ዘመቻ ብቻ 1,543,678 ሰዎችን ከመሃይምነት አላቋል፡፡ በከፍተኛ የትምህርት ተቋማትና በኮሌጆች በመማር ላይ የነበሩትን ተማሪዎች በ10 ዓመት ውስጥ በ33 በመቶ ከፍ እንዲል አድርጓል፡፡

በሶሻሊስት አገሮች ትምህርት በነፃ ስለሚሰጥም በግል ተይዘው የነበሩትን ሁሉ ወደመንግስት በማዞር የትምህርት ስርጭቱ በነፃ እንዲዳረስ ሆኖ በህዝቡ እንዲተዳደር ሆኗል፡፡ የጤና ጣቢያዎችንና የጤና ኮሌጆችን በማስፋፋትም ከ15 በመቶ አይበልጥ የነበረውን የጤና ሽፋን ወደ 38 በመቶ ከፍ አድርጓል፡፡



የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦትን ከ10 በታች የነበረውን ሽፋን ወደ 19 በመቶ አሳድጎታል፡፡ የአንደኛ ደረጃ አውራ ጎዳና መንገድንም ከነበረው ጨምሮ 18ሺ ኪሎ ሜትር አድርሷል፡፡ የአገልግሎት ሽፋኑ በገጠር ባዶ፣ በከተማ 30 በመቶ የነበረውን፣ ደርግ በገጠር 15፣ በከተማ 59 እንዲሆን አድርጓል፡፡

የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫውንም ከነበረበት 50 ሜጋ ዋት 370 ሜጋ ዋት አድርሶታል፡፡ የሙገር ስሚንቶ ፋብሪካን አቋቁሟል፡፡ የአርባ ምንጩ የውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲቲዩት የደርግ መንግስት ውጤት ነው፡፡ የናዝሬት የእርሻ ትራክተር መገጣጠሚያ፣ በአፋር ውስጥ እንፋሎትን ወደ ኃይል የመቀየር (ጅኦ ተርማል) ሞካሪው ደርግ ነው፡፡ በናዝሬቱ የእርሻ ትራክተር መገጣጠሚያ ድርጅት ውስጥም "እሸት" የሚል ስያሜ ያለው የግብርና አውሮፕላን በአገር ውስጥ ተገጣጥሞ ስራ ላይ ውሏል፡፡ የደርግ መንግስት በተለይ የውጭ አገር ምርትን በአገር ውስጥ ለመተካት ሲል ከትንሹ ጨርቃ ጨርቅ እስከ ከፍተኛው የኢንደስትሪ ዘርፍ ድረስ ጠንክሮ ሰርቷል፡፡ የጦር መሣሪያዎችን መገጣጠምና ጥይቶችን እስከማምረትም ደርሷል፡፡ እስከ ሚሳኤል ደረጃ መሄድም እቅዱ ነበር፡፡

በመቶዎች የሚቆጠሩ ዜጎችንም በውጭ አገር የቴክኒክ ሙያዎችን ተምረው እንዲመለሱ አድርጓል፡፡ ቀጥሎም 80 ሺ የሚደርሱ የፋብሪካ ሠራተኞች በስራ አመራር፣ በሂሳብ አያያዝ፣ በምርትና በጥገና የሙያ መስኮች በአገር ውስጥ ተምረው ወደ ስራ እንዲሰማሩ አድርጓል፡፡

እነዚህንና ከዚህም ያለፉ በርካታ አገራዊ ስራዎችን ሲሰራ ግን ከምስራቅ የሱማሊያው መንግስት ዚያድ ባሬ ለያዥ ለገራዥ አስቸግሮ ኦጋዴንን ለመንጠቅ ጦር ሰብቆበታል፡፡ ከሰሜን ሻዕቢያ (ሻዕቢያ እስኪደመሰሰው ድረስ አብሮት ጀብሃ) ሸምቀው የደርግን መንግስት ፋታ ነስተዋል፡፡ እንደገና በትግራይ ተሃህት(ተጋድሎ ሃርነት ህዝቢ ትግራይ) በኋላ ህወሃት የተሰኘው እየተፈታተኑት ነበር፡፡ በከተማ ውስጥ ኢህአፓ አለ፡፡

በዚህ ሁሉ አጣብቂኝ መሀል ያለው የደርግ መንግስት ግን "እየተዋጋን እናመርታለን፤ እያመረትን እንዋጋለን" የሚለውን መፈክር የሙጥኝ ብሎ ቀጥሏል፡፡

ኢትዮጵያን ለመውረር ያሰፈሰፈውን ኃይል ለመቋቋም ይቻል ዘንድም መንግስቱ በሶቭየት እርዳታ ተደግፈው በአፍሪካ ደረጃ ቁጥር አንድ የተባለ ሠራዊት አደራጅተው አስታጠቁ፡፡ በ12 ቢሊዮን ዶላር (በዚያን ጊዜው ምንዛሬ 24 ቢሊዮን ብር ነው) ጦሩን ሲገነቡ ግን ኢትዮጵያን ለቆት የማያውቀው ረሀብ በዘመናቸው ተከሰተ፡፡ ምንም ለጦርነቱ ቅድሚያ ቢሰጡም፤ እንደ ሁለቱ መንግስታት አይተው ያላዩ አልመሰሉም፡፡ ይልቁንም በተቻለ መጠን፣ ረሃብተኞችን (በድርቅ

የተጠቁትን ዜጎች) ከወሎና ካካባቢው በአውሮፕላን እያጋዙ ወደ መሀል አገር በማስመጣትና አንቶርጫን (ከቡተቤ ፡ጎዶይ) በመሳሰሉ ጊዜያዊ የመጠለያ ካምፖች እያስጠጉ እህል ውሃ በማቅረብ፣ ከዚያም ወደ ለም የኢትዮጵያ ግዛቶች ወስደው በማስፈርና ኑሮአቸውን እንዲመሠርቱ በማድረግ የቻሉትን ፈጽመውላቸዋል፡፡ ወላጆቻቸውን በድርቁ ያጡ ህፃናትንም ሰብስበው የማሳደጊያ ተቋማትን /ህፃናት አምባ/ እየመሠረቱ አሳድገዋል፣ አስተምረዋል፡፡

ደርግ የድርቅ አደጋውን ዘላቂ መፍትሄ ለመስጠትም ሞክሯል፡፡ የጣና በለስ ግድብ ፕሮጀክትን ቀርፀው ከጣሊያንም የገንዘብ ችሮታ ተደርጎላቸው ወደ ተግባር ተገብቶ ነበር፡፡ ይህ ፕሮጀክት የኢትዮጵያን ግብርና ለማስፋፋት የረዳና በመቶሺዎች የሚቆጠሩ አርሶ አደሮች ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለው ለም ወደሆነው የአገሪቱ ደቡባዊ ክፍል እንዲሰፍሩ ያደረገ ነው፡፡ ከዚህም አልፎ በጣሊያን እርዳታ በተገነቡ አዳዲስ ግድቦች አማካኝነት 20ሺ ሔክታር መሬት ለማልማት ጭምር ተችሏል፡፡

የደርግ መንግስት ይህን ፕሮጀክት ወደ ተግባር ሲለውጥም ከፍተኛ ገንዘብና ጉልበት አፍስሶበት ነው፡፡ ሆኖም የኤርትራና የትግራይ አማፅያን ወደ አዲስ አበባ ሲገሰግሱ አውድመዋቸዋል፡፡ ሙሉ በሙሉም ከጥቅም ውጪ ሆነዋል፡፡

መንግስቱ ኃይለማርያም ለጣሊያናዊው ጋዜጠኛ ጥያቄ ሐራሬ ሆነው መልስ ሲሰጡ፤ "ለረሃብተኞቹ ትኩረት አልተሰጠም የሚባለው ፈጽሞ ውሸት ነው! ከጣና በለስ ግድብና የገጠሩን ነዋሪ ወደምቹ ቦታ ከማስፈሩ በስተጀርባ የነበረው ስራ ረሃብ ዳግመኛ የማይከሰት ለመሆኑ ማረጋገጫችን ነበር፡፡ እንደገና ልድገመውና በጦርነት ላይ ነበር የምንገኘው፡፡ ጦርነቱን ለመዋጋትና ለማሸነፍ ደግሞ ለጦርነቱ ቅድሚያ መስጠት ነበረብን፡፡"

ይቀጥላሉ መንግስቱ፤ "... እንዲታ! በአፍሪካ ውስጥ እጅግ ጠንካራና ኃይለኛ የተባለ ሠራዊት ገነባሁ፡፡ በአደረጃጀቱ በመላው ዓለም ከሚገኙ የፖለቲካ ፓርቲዎች ተርታ ይመደብ የነበረ የፖለቲካ ፓርቲ አደራጀሁ፡፡ አንዲት እናት ህፃን ልጇን ከአደጋ እንደምትጠብቀው ሁሉ እኔም የሀገሬን አንድነት፣ ዳር ድንበርና ሉዓላዊነት ስከላከል ቆይቻለሁ፡፡ ግን ምን ያደርጋል? ድካሜ ሁሉ ከንቱ ሆነ፡፡" ብለዋል፡፡

እናም አብዮቱ ለዘመናት ሲቀነቀን የነበረውን የመሬት ላራሹን የብሶት ጥያቄ በመመለስና የብዙሃኑን ምኞት ዳር በማድረስ ፍሬ ያለው ስራ የሰራ ሲሆን፤ይህም ደርግንና አባላቱን ዛሬ ድረስ የሚያኮራ ተግባር ሆኖ ተመዝግቧል፡፡





ከቀደምቱ "ኢህአፓ" እና በኋላ ላይ በደርግ ከተመሰረተው "ኢሠፓ" ውጪ ሌሎች የተቃዋሚና የደጋፊ ቡድኖች "ፓርቲ" የሚለውን መጠሪያ አልተጠቀሙበትም፡፡ "ሊግ" "ድርጅት" "ንቅናቄ" "ኅብረት"... ወዘተ የሚሉትን ነው የመረጡት፡፡ የእነዚህን ቡድኖች ስራና ሴራ በአጭሩ ለማየት ከቀደምቱ ኢህአፓ እንጀምር፡፡ የኢህአፓ ቁንጮ መሪ ቀደም ሲል ያየነው የ"አዞ" ፍልፍል ነው፡፡

አውሮፕላን ጠልፈው ሱዳን፣ ከዚያም አልጀሪያ መግባታቸውን በጃንሆይ ታሪክ ውስጥ አንብበናል፡፡ ዓለም አቀፍ ግንኙነታቸውንም አጠንክረው መቀጠላቸውን አይተናል፡፡ ያኔ ስምንት ሆነው በብርሃነመስቀል ረዳ መሪነት አልጀሪያ የገቡት ቡድኖች በአልጀሪያ መንግስት እርዳታ ከፍልስጤም ነፃ አውጪ ድርጅት /PLO/ ጋር ግንኙነት አድርገው ወታደራዊ ስልጠና ተሰጣቸው፡፡

የሻዕቢያን ተልዕኮ ኢትዮጵያ ውስጥ ለማስፈፀም በሻዕቢያ ሽፋን ደቡብ የመን በመድረስ ቁጥራቸውን በእጥፍ አሳድገው ቀይ ባህርን አቋርጠው ሳህል በረሃ ገቡ፡፡ ሻምበል ተስፋዬ ርስቴ "ምስክርነት" በሚል ርዕስ በ2001 ዓ.ም በፃፉት መፃህፍ ስማቸውን እንዲህ ይዘረዝሩታል፤ "ብርሃነመስቀል ረዳ፣ ቢንያም አዳነ፣ አብዲሳ አያና፣ ኃይለኢየሱስ ወልደሰንበት፣ አዱኛ መንግስቱ፣ አብዱራሀማን አህመድ፣ ውብሸት ረታ፣ አበበ /ያባቱ ስም ያልታወቀ/ ተፈሪ ብርሃኔ፣ መሐመድ ማህፉዝ፣ መሐሪ ገብረእግዚአብሔር፣ ስመረአብ ዮሐንስ፣ ስዩም ከበደ፣ ዘርዓብሩክ አበበ፣ እስክንድር ደምሴና ሌሎች ሆነው ከብርሃነ መስቀል ረዳ በስተቀር ሁሉም በኢህአፓ ስም ሳይሆን በተገንጣዮች ስም ሳህል በረሃ ገቡ፡፡

"ቆይቶም ከተለያዩ አገራት በሶማሊያና በሱዳን ከመጡ ሃያ አምስት የሚሆኑ አባላት አንድ ሐኪም ተጨምሮላቸው ሙሉ ወታደራዊ ትጥቅ ከሻዕቢያ ተሰጥቷቸውና ገንዘብም ታድለው የካቲት 25 ቀን 1967 ዓ.ም የመሬት አዋጅ በታወጀበት እለት ለትግል ትግራይ አሲምባ ገቡ፡፡ ብዙ ሳይቆይ 6 ያህሉ አባላት ድርጅታቸውን ክደተው ትግራይ ለነበረው የደርግ መንግስት ባለስልጣን እጅ ሰጡ፡፡ እነተስፋዬ መኮንን እጅ ሲሰጡ እነ ዶ/ር ተስፋዬ ደበሳይ፣ ብርሃነመስቀል ረዳ እና እስክንድር ደምሴ በስውር አዲስ አበባ ገብተው ከጀብሃና ከሻዕቢያ፤ ከእነዚህ በስተጀርባ ደግሞ ከአልጀሪያ የተሰጣቸውን የቤት ስራ ለማከናወን ዝግጅት ጀመሩ፡፡..." /ገፅ 143/

ጀብሃንና ሻዕቢያን በዓረባዊ ስሜት የዓረብ አገር መንግስታት ይረዷቸው ነበር፡፡ ይህን ስልጠና ወስደው ኤርትራን ለመገንጠል ቀድመው በሸመቁት ቡድኖች ነው ኢህአፓ የሚመራው፡፡እነክፍሉ ታደሰ አዲስ አበባ ውስጥ ሸምቀው ከኤርትራ በመጣው የሻዕቢያ ነብስገዳይ

ቡድን መሪ በሆነው በኀይቶም ለባሲ እሰልጣኝነትና የተቀናጀ አመራር ደርግንና የደርግን ተባባሪ እያደኑ በመግደል አዲስ አበባን በደም ጎርፍ አጥለቀለቋት፡፡ከአዲስ አበባም አልፈው በየክልሉ ተመሳሳይ ተግባራቸውን ቀጥለዋል፡፡ወጣቱን በሐሰት ፕሮፓጋንዳ ቀስቅሰው ከጎናቸው በማሰለፍም ስውር ሴራቸውን ያላወቁትን ዜጎች ፈጁ፤ አስፈጁ፡፡

በቅድሚያ የገደሉት ዶ/ር ፍቅሬ መርዕድን ነበር፡፡ ሻምበል ተስፋዬ ርስቴ በመፃህፋቸው፤ "የዶ/ር ፍቅሬ ገዳይ ዛሬ ስሙን ለውጦ በብዓዴን ውስጥ አለ" ይሉናል፡፡

ከአገር ውጪ የነበረው የተማሪ ንቅናቄ አካል አብዮቱ ሲፈነዳ በሁለት አክራሪ ጎራዎች ተሰልፎ ነበር፡፡ እነዚህም የኢህአፓ እና የመኢሶን ድርጅቶች ተከታይ ነበሩ፡፡ ሁለቱ ቡድኖችም በተማሪ ድርጅቶች ሽፋን ደጋፊዎቻቸውን ማብዛትና ማጠናከሩን ተያይዘውት ነበር፡፡ በአብዮቱ ዋዜማ የተማሪዎች ማኅበራት ዱላ ቀረሽ ክርክር ላይ ነበሩ፡፡ የኢህአፓ ወገኖች በአዲስ መልክ የተዋቀረውን የኢትዮጵያ ተማሪዎች ዓለም አቀፍ ፌዴሬሽንን (ኢተዓአፌ)ን ሲደግፉ፤ (በአዞዎቹ ቁጥጥር ስር የነበረውን) የመኢሶን ተከታዮች ደግሞ አዞዎቹ ያፈረሱትን የኢትዮጵያ ተማሪዎች ዓለም አቀፍ ማኅበር (ኢተዓአማ) እንዲቀጥል ይሟገቱ ነበር፡፡

የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር በሰሜን አሜሪካ (ኢተማሰአ) በጃንሆይ ዘመን ታሪክ ውስጥ እንዳየነው የአዞዎቹ የበላይነት ስለነበረበት የፌዴሬሽኑና የኢህአፓ ደጋፊ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር በአውሮፓ /ኢተማአ/ ደግሞ ከሁለት ተከፋፍሏል፡፡ እነዚህን የውጭ አገር እንቅስቃሴዎች ደርግ ብዙም ትኩረት አልሰጣቸውም ነበር፡፡ ከአብዮቱ በኋላ ግን ክርዕዮት ክርክር አልፈው ወደ መተላለቅ አምርተዋል፡፡

የውጪ ቡድን ከአገር ውስጥ ቡድኖቹ በርቀትም ቢሆን እየተገናኘ ማርክሳዊ ሌኒናዊ መፈክሮችን ሲያስተጋባ አመታት ተቆጥረዋል፡፡

በአገር ውስጥ ያሉት አብዮቱ እንደፈነዳ በልሳኖቻቸው በዴሞክራሲያ እና በሰፊው ህዝብ ድምፅ አማካኝነት በሚያሰርጓቸው መልዕክቶች የህዝብ ድጋፍ ሲሰበስቡ ቆይተዋል፡፡ ምሁራኑ ከውጭ አገር ወደ አገር ቤት ከእነ ክፍፍል ቁርሿቸው መጥተው እንደተቀላቀሉም ልሳኖቹ የኢህአፓና የመኢሶን መሆናቸው ገሃድ ወጣ፡፡

ኢህአፓ እነ ብርሃነመስቀል ረዳ እና እነክፍሉ ታደሰን ያካተተ ቀንደኛ ተቃዋሚ ሆኖ ቀረበ፡፡ መኢሶን እነ ዶ/ር ወርቁ ፈረደ፤ እነዶ/ር ንግስት አዳነ፣ ዶ/ር መስፍን ካሱ፣ ዶ/ር ነገደ ጎበዜና ዶ/ር ኃይሌ ፊዳ የተካተቱበት ነበር፡፡ በደርግ ምስረታ ማግስት ሌሎችም የግራ ክንፍ ኃይሎች ብቅ ብቅ ይሉ ጀመር፡፡



የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር በሰሜን አሜሪካ የአሮጌው (ኢተማሰአ) መሪ በነበረው በዶ/ር ሠናይ ልኬ የሚመራ "ወዝ ሊግ" የተሰኘ ድርጅት ተከተለ፡፡ይህ ቡድን ከውጭ አገር ጀመሮ ቂም የነበረበት ስለሆነ ከደርግ ጋራ ወዳጅ ለመሆን ጊዜ አልፈጀበትም፡፡መኢሶንም በተመሳሳይ ለደርግ እውቅና ሰጥቶ በመለጠፍ ግንባር ቀደም ነበር፡፡
ቀጥሎ "የኢትዮጵያ ጭቁን ህዝቦች አብዮታዊ ትግል "(ኢጭህአት) የተባለ ቡድን በተለይ የደቡብ ኢትዮጵያን ህዝቦች እወክላለሁ በማለት ብቅ አለ፡፡ከዚያም ከኢህአፓ አፈንግጠው እጅ የሰጡት አባላት አገር ውስጥ ካሉ ጥቂት ህቡዕ ድርጅቶች ጋር በመቀናጀት"ማርክሲስት ሌኒኒስት ሪቮሉሽናሪ ድርጅት"(ማሌሪድ)የተባለ ቡድን መሠረቱ፡፡

ደርግ ግር እያለው ሄደ፡፡ ወዲያውም ፍልሚያውን መቀላቀል እንዳለበት ለደርግ እውቅናና ቅድመ እውቅና ከሰጡት ከወዝሊግ እና መኢሶን አመራር አባላት ባገኘው ምክር፣ እንዲሁም በቀሰሙት ትምህርት በመንዝ፤ በተለይ በወዝ ሊግ አዋላጅነት "አብዮታዊ ሠደድ" የተሰኘ ድርጅት ተወለደ፡፡ ይህም በ1968 ዓ.ም የተደረገ ሲሆን፤ የሰደዱ አባላት የመንግስቱ ወዳጅ የሆኑ መለዮ ለባሾች ናቸው፡፡ በሃምሳ አለቃ /በኋላ ሻምበል/ በለገሠ አስፋው የሚመራ ሆነ፡፡

ከዚህ በኋላ በእለታዊው አዲስ ዘመን ጋዜጣ "አብዮታዊ መድረክ" በሚለው ዓምድ ስር የሁሉም ፓርቲና ድርጅት የብዕር ፍልሚያ ጦፈ፡፡ በዋናነትም መኢሶንና ኢህአፓ የጽሁፍ ችሎታ ባላቸው ምሁራን አባላት አማካኝነት በማርክሳዊ ቃላቶች አሸብርቀው የሚቀርቡ ሀሳቦችን መሰንዘር ቀጠሉ፡፡

የእነ ለገሠ አስፋው (የእነ መንጌ) የሠደድ አባላት አነጣጥሮ መተኮስ እንጂ አንጥሮ መፃፍ ላይ እምብዛም ነበሩና ወሣኝ ወሣኝ ሀሳቦችን ከሁለቱ ተፋላሚ ወገኖች እየቀዱ፡ እየተማሩ፣ ዳር ላይ ሆነው ምንንም የማያውቁትን ርዕዮት በውል ተረዱት፡፡ ይህን እስከ 1969 ድረስ የዘለቀ የጋዜጣ ትምህርት ይዘውም የርዕዮቱ ተንታኝ፤ ብሎም ተግባሪ ሆኑ፡፡ በእርግጥም የሀሳብ ፍጭቱ ለደርግ ጠቃሚ ነበር፡፡ የብዕር ተፋላሚዎቹም በልዩነት ላይ ሳይሆን አንዱ አንዱን ለማንቋሸሸና እርቃኑን ለማስቀረት የነበረ ሲሆን፤ ውሎ አድሮ ብዕሩ ቀርቶ በጥይት መፋለም ይጀምራሉ፡፡

ደርግ በመሃል የብሔራዊ ዴሞክራሲ አብዮትን በ1968 ሚያዚያ 12 ካወጀ በኋላም ለአዋጁ አስፈፃሚ አካል የሚሆን "ጊዜያዊ የህዝብ ድርጅት ጉዳይ ጽ/ቤት" ማቋቋም ነበረበት፡፡ዓላማውም በደርግ አገላለፅ "ሰፊውን ህዝብ ማንቃትና ማደራጀት ነው" ጽ/ቤቱን ለመምራትም 15 አባላት ያሉት ኮሚሽን ሲደራጅ ከሊቀመንበርነት ጀምሮ ያለውን ስልጣን መኢሶን ስለያዘው ድርጅቱን ለማጎልበት ተጠቀመበት፡፡ከኢህአፓ

የማይወዳደር አቅም የነበረው መኢሶን በወራት ውስጥ ጥሩ ለውጥ አሳዬ፡፡ከተሞችን ለመቆጣጠር የሚያስችለውን የከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴርን ደርግ ሆን ብሎ በመኢሶን ስር እንዲሆን በማድረጉም በ1968 መገባደጃ ላይ በተካሄደው ተራ የቀበሌ ምርጫ ደጋፊዎቹን ለማስመረጥ በመቻሉ መኢሶን ደስ ተሰኘ፡፡ነገር ግን ደርግ ይህን ያደረገው ኢህአፓን "እንቁልልጭ" ለማለትና፤"ስልጣን ለህዝብ በተወካዮች አማካኝነት የሚተላለፈው እኔን የአብዮቱን ባለቤት ቀርቦ በመወዳጀት እንጂ በግትርነት አይደለም" በሚል ሾርኒ ለመንካት ነበር፡፡በዚህም ኢህአፓ በግኗል፡፡ስለዚህም ወዲያው ሠራተኛውንና ሌሎች ጥቃቅን ተቃዋሚ ቡድኖችን በመቀስቀስና ደጋፊዎቹን በማነሳሳት የኢህአፓን መፈክር አንግበው ሰልፍ እንዲወጡ አደረገ፡፡ ኢህአፓ "የወዛደሩ ብቸኛ ፓርቲ እኔ ነኝ" ሲል በመከረሙና በአማላይ ቃላቶችም ብዙሃኑን መማረክ በመቻሉ የብሔረተኝነት አላማውን የተረዳውም ያልተረዳውም ተሰለፈለት፡፡ ደርግና የደርግ አሯሯጮች ኢህአፓ መቼም እረፍት እንደማይሰጣቸው ቢረዱትም የወሰዱት የኃይል እርምጃ ግን አልነበረም፡፡

ኢህአፓ በደርግና በአጋሮቹ ላይ የሽምቅ ውጊያን ጨምሮ፤ እያደነ እንደሚገድልም ዛተ፡፡ መስከረም 13 ቀን 1969 ዓ.ም ኢህአፓ መንግስቱ ኃይለማርያምን ለመግደል ያደረጉት ሙከራ ለጥቂት ሳይሳካ ቀረ፡፡በዚህ ተኩስ ክፉኛ የቆሰሉት መንግስቱ ድንጋጤያቸውን በውስጣቸው ይዘው ሙከራውን ለፖለቲካዊ ፕሮፓጋንዳ ተጠቀሙበት፡፡ "አስቡት እኔን የመሰለ አብዮተኛ" እንደማለት፡፡ ጎን ለጎንም የኢህአፓን ፖለቲካዊ ኪሣራ አስገነዘቡበት፡፡

ከጥቂት ቀናት በኋላ ቀደም ሲል ያየነውን የመኢሶን አመራር አባልና የህዝብ ድርጅት ጉዳይ ጽ/ቤት ባለደረባ የነበሩትን ዶ/ር ፍቅሬ መርዕድን ሠንጋተራ አካባቢ መኪና ውስጥ ቁጭ ብለው ባለቤታቸውን ሲጠብቁ አልሞ መግደልን ሰልጥነውበት፣ ተክነውበት የመጡት የኢህአፓ አባላት ተኩሰው ገደሏቸው፡፡

"ነጭ ሽብር" አሉት፡፡ የነጭ ሽብር ተግባራቸውንም በተጠቀሱት ኢትዮጵያዊ ዶ/ር ጀመሩት፡፡ የመጀመሪያውን ጥይት ያጮኸች ኢህአፓ መሆኗ ግልጽ ነው፡፡ ደርግ ከኢህአፓ የሽብር ተግባር በኋላ "የአንድ አብዮታዊ ህይወት በሺ ፀረ-ህዝቦች ህይወት ይመነዘራል" አለ፡፡ ከዚህ መግለጫ በኋላ የኢህአፓ አባሎችንና ደጋፊዎችን ደርግ በውል ስለማያውቃቸውና አገር ውስጥ ድንበር ሲጠብቅ ስለነበር፤ የፖለቲካ ዲያስፖራዎች እዚያው ይተዋወቃሉና የመኢሶን አባላት ስም ዝርዝራቸውን ለደርግ አቀረቡ፡፡ ደርግም እየለቀመ ማሰር ቀንደኞችንም መረሸን ጀመረ፡፡ ሲቪል ታጣቂዎችንም እያደነ ትጥቅ አስፈታ፡፡ ቀጥሎ በሰርጎ ገብነት የሚጠረጠሩ የራሱ የደርግ አባላትና ደጋፊዎች ለኢህአፓ



እየሰሩ ነው የሚል ነገር መጣ፡፡ የነገሩ እውነትነት ባያጠያይቅም ደርግ "ሠርጎ ገብ" የተባሉትን አባላት በሚመለከት የወሰደው እርምጃ "ከኑግ ጋር የተገኘህ ሰሊጥ አብረህ ተወቀጥ" የሚባለውን ብሂል የተከተለ ነበር፡፡ ጠቋሚዎቹም የየራሳቸውን የስልጣን ቦታ ለመያዝ ሲሉም ሆነ ያልተዋጠላቸውን ሹም የማስወገጃ መድረክ አድርገውታል፡፡

መንግስቱ የደርግን ሀልውና አስጠብቀው ለመቀጠል ቀድመው የተዘጋጁ ነበሩና፤ በቤተመንግስቱ ቅልብ ጦር አኑረዋል፡፡ በኮሎኔል ዳንኤል አስፋው ይመራል፡፡ "መቺ ኃይል" የሚሉትን ቡድንም መስርተዋል፤ በሻለቃ ጌታቸው ሺበሺ ይመራል፡፡ የደርግ አባላቱ ተራ ወታደር 10 አለቃ እየተባሉ "አድሃሪ" ተብለው ስለተተቹም ለእያንዳንዱ አባል በውስጥ አሰራር ማዕረግ እንደ ፈንዲሻ እየተዘገነ እንዲሰጥ አድርገዋል፡፡ በዚህም የእሳቸው ሌተናል ኮሎኔል መሆን አግባብነት ቢኖረውም፤ እያንዳንዱ አባል ከምክትል መቶ አለቃ በላይ እንዲሆን የተደረገው በፍጥነት ነበር፡፡ ከዚህም አልፎ አብዮታዊ ሠደድ አለ፡፡ በጥቅሉ ዙሪያውን አጠባብቀው ሲያበቁ፤ ይህ የኢህአፓ ተግባር አገር የማፍረስ ተልዕኮ መሆኑን በመገንዘብ፤ "ውስጡ መጥራት አለበት" የሚል አቋም ወሰዱ፡፡ ይሄ ሁሉ የስልጣን ህልመኛ ፓርቲ የአብዮቱ ፀር እንደሚሆን ጠረጠሩ፡፡ ዝግጅቱን ያዩት ጄኔራል ተፈሪ በንቲ "እሣት በእሣት አይጠፋምና ብሔራዊ እርቅ ለማድረግ ጥሪ እናቅርብ" ብለው አረፉ፡፡

- ወፉ ዛፉ በኢህአፓነት በሚጠረጠርበት በዚያ ጊዜ ይሄን የመሰለ ቃል ከደርጉ ዋና ሊቀመንበር መሠንዘሩ ለኮሎኔል መንግስቱ (ሲፈጥራቸውም ጠርጣሪ ናቸውና) ምን ማለት እንደሆነ ግልፅ ነው፡፡ እርግጥ ነው ከጥር 26 ቀን 1969 ዓ.ም በፊትም ለወራት ያህል መጠነኛ አለመግባባት ነበር በተፈሪና በመንግስቱ መካከል፡፡ ሆኖም የዝግጅት ጊዜ አስፈልጓል፡፡ በደርግ ውስጥም ጥርጣሬው ጎልቶ በጎሪጥ መተያየት ተፈጥሯል፡፡ ስለዚህም የደርግ የፖለቲካና የውጭ ጉዳይ ኮሚቴ ሊቀመንበር የነበሩትን የአየር ኃይል አባሉን ሻለቃ ሲሳይ ሀብቴን በአብዮቱ ላይ አሲሯል በሚል ክስ በጦር ፍርድ ቤት ቀርበው ተረሸነዋል፡፡ ቀጥሎም በኤርትራ ያለው 2ኛ ክፍለ ጦር አዛዥ የነበሩት ብርጋዴል ጄኔራል ጌታቸው ናደው ላይ ተመሳሳይ እርምጃ ተወሰዷል፡፡ ጄኔራል ጌታቸው ናደው ልክ እንደ ጄኔራል አማን እጅ አልሰጥም ብለው ቤታቸው ውስጥ ተታኩሰው ነበር የተገደሉት፡፡ ከዚያም መቶ አለቃ በወቅቱ ካሣና መቶ አለቃ ስለሺ በየነ የተባሉ ሁለት የደርግ አባላት ሊወሰድባቸው የታሰበውን እርምጃ ቀድመው በማወቃቸው በሽሽት ላይ እንዳሉ በደርግ የተላከው ጦር አሳዶ ይዞ ገድሏቸዋል፡፡ በተመሣሣይ

ጥርጣሬም የእድገት በኅብረት ዘመቻ አስተባባሪ የነበሩት ሻለቃ ኪሮስ አለማየሁ ተይዘው ታስረው ሳለ ራሳቸውን በእስር ላይ እንዳሉ ገድለዋል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለም በተጠቀሰው አመት የመጀመሪያው ወራት የደርግ አወቃቀር ላይ መሠረታዊ ለውጥ ተደርጎ ነበርና፣ በዚህም ሁሉም የደርግ አባላት የሚሳተፉበት ሸንጎ ዋናው የስልጣን አካል ሆኖ፣ በተዋረድ ደግሞ የማዕከላዊ ኮሚቴና ቋሚ ኮሚቴ ተቋቋሙ፡፡ በዚህም ዋና ሊቀመንበሩ ዋናውን ሸንጎ በበላይነት መምራት ሲችሉ፣ ምክትሉ መንግስቱ ግን ከደርግ ጋር ያልተያያዘውን የሚንስትሮች ምክር ቤትን በሊቀመንበርነት ከመምራት ያለፈ ስልጣን እንዳይኖራቸው ሆነ፡፡

በተጨማሪም የደርጉ ዋና ፀሐፊ የጽ/ቤቱን ስራ ከመምራት ባለፈ ከአዲሱ አወቃቀር በፊት በሌተናል ኮሎኔል መንግስቱ ስር የነበረውን የህዝብ ድርጅት ጉዳይ ጽ/ቤትንም እንዲቆጣጠሩት ተደረገ፡፡

ይህ አወቃቀር ከግራ ቀኝ ሲታይ መንግስቱና ደጋፊዎቻቸውን አስሮ የማስቀመጥ ዘዴ ሆኖ ስለተገኘ ፍጥጫ ቢፈጠር አይገርምም፡፡ በዋናነት አዲሱን አወቃቀር አቅደው በተግባር እንዲሰራበት ያደረጉት በኢህፓንነት የሚጠረጠሩ የተባሉት የደርጉ የኢኮኖሚ ኮሚቴ ሊቀመንበር የነበሩት ሻምበል  ሞገስ ወ/ሚካኤልና በአዲሱ አወቃቀር የደርጉ ዋና ፀሐፊ የሆነው ሻምበል አለማየሁ ኃይሌ መሆናቸው ነው፡፡ እንደገናም አወቃቀሩ የአብዮቱ ጠባቂ አለኝታ ተደርገው በብዙሃኑ የሚታዩትን፣ የሚፈሩትን መንግስቱን አግልሏል፡፡ ከሁሉም የከፋው ደግሞ በዚህ አሠራር ሠርጎ ገቦች ካሉ እንደልባቸው የመሆን እድል የሚሰጥ መሆኑ ነው፡፡ ተጠርጣሪዎች ይህን አድርገው አስጊውን መንግስቱን ቀፍድደው ስራቸውን ቀጠሉ፡፡ የረሱት ነገር ቢኖር ለመንግስቱ ፍፁም ታማኝ የሆነውና ከሆለታ ትምህርት ቤት ጀምሮ ጓደኝነት የነበራቸው፣ ከደርግ ምስረታ ጀምሮ የመንግስቱ ቀኝ እጅ የሆነው፣ ጃንሆይንም አማንንም ሲጥ ያደረገው ኮሎኔለ ዳንኤል አስፋው የደርግን ህልውና ለማስጠበቅ የተደራጀው የቅልብ ጦሩ የበላይ አዛዥ መሆኑን ነው፡፡ እናም ጠላታቸውን በፍጥነት በማንበርከክ ወደር የማይገኝላቸው መንግስቱ የረቀቀ የማጥቃት ዘዴያቸውን ከደጋፊዎቻቸው ጋር አቅደው ጨረሱ፡፡

ጥር 26 ቀን 1969 ዓ.ም ሁሉም የደርግ አባላትና ሊቀመንበሩ ጄኔራል ተፈሪ በንቲ በስብሰባ ላይ እንዳሉ አንድ መልዕክተኛ ይመጣና መንግስቱ አስቸኳይ የስልክ ጥሪ እንዳላቸው ይገልፃል፣ መንግስቱ አስፈቅደው ይወጣሉ፡፡

ወዲያው ባልተጠበቀ ፍጥነትና ሁኔታ የታጠቁ ወታደሮች በኮሎኔል ዳንኤል አስፋው መሪነት ወደአዳራሹ ገብተው "እጅ ወደ ላይ!" አሉ፡፡ ሁሉም በድንጋጤ እጆቻቸውን በጭንቅላታቸው ላይ አጣምረው አፈጠጡ፡፡ በአንድ አዳራሽ ከታጎሩት አባላት ውስጥ ሰባት ሰዎች



ተመርጠው ስማቸው እየተጠራ ወጡና በአንድ ክፍል ተቆለፉ፡፡ ሌሎቹ አባላት "አይዟችሁ እናንተን አይደለም" ተብለው ተተውና ሰባቱ ወዲያው ተረሸኑ፡፡ ጄኔራል ተፈሪ በንቲ የደርጉ ሊቀመንበር፣ ሻምበል አለማየሁ ኃይሌ በአዲሱ አወቃቀር የደርጉ ዋና ፀሐፊ፣ ሻምበል ሞገስ ወልደሚካኤል የኢኮኖሚ ኮሚቴ ሊቀመንበር፣ ሌተናል ኮሎኔል አስራት ደስታ የደርግ የማስታወቂያ ኮሚቴ ሊቀመንበር፣ ሻለቃ ህሩይ ኃይለስላሴ፣ ሻምበል ተፈራ ደነቀ፣ አስር አለቃ ኃይሉ በላይ የተረሸኑት የጊዜያዊው የደርግ መንግስት ከፍተኛ ባለስለጣናት የነበሩና በኢህአፓ ደጋፊነትና አባልነት ስለተጠረጠሩ ነው፡፡

በቅፅበት መፈንቅለ መንግስቱ በስኬት ቢደመደምም፣ ወዲያው በተፈጠረው የተኩስ ልውውጥ ሽብሩ ቀጠለ፡፡ መንግስቱ ከመፈንቅለ መንግስቱ በኋላ ወደ አዳራሹ ሄደው "አማንን መርጠን ምሩን ብንላቸው አብዮታችን ለመቀልበስ ተነሱ፣ ዛሬ ደግሞ ጄኔራል ተፈሪ በንቲ ለዘብተኛ በመሆናቸው አብዮቱን ለማዳን ርምጃ ተወስዷል፡፡ እኔ ለአብዮቱ ያለኝ አቋም ቁርጠኛ ነው፡፡ አሁን በእርጋታ ስራችሁን መቀጠል ትችላለህ..." እያሉ ሲያረጋጉ የመጨረሻዋን ቃል ሳይጨርሱ የቤተመንግስቱ ጊቢ በተኩስ ሲናጥ መንግስቱ ሮጠው ወጥተው ታንክ ውስጥ ተደበቁ፡፡ ሌላው ባለበት ሆኖ በሽብር ተናጠ፡፡ ጉዳዩን ወዲያው የተረዳው ሻለቃ ዮሐንስ ምትኩ ጊቢ ውስጥ ነበርና የኢህአፓ አባልም ስለነበር ሳይቀድሙኝ ልቅደም ብሎ ተኩስ በመክፈት ዶ/ር ሰናይ ልኬንና ኮሎኔል ዳንኤል አስፋውን ቅል ቅልአቸውን ብሎ አስተኛቸው፡፡ ቀጥሎም መንግስቱን ለመግደል ነበርና ያሰበው ይገኙበታል ወዳለው ቢሮ ገብቶ አጣቸው፡፡ ግድግዳ ላይ የተሰቀለውን የመንግስቱን ፎቶ ግራፍ በጥይት ቦረዳድሶ ከመውጣቱ በፊት አንድ ታንክ ቢሮውን ደርምሶ ገብቶ ሻለቃ ዮሐንስንም ጨፍልቆ ሲያበቃ ሁሉም ነገር ፀጥ አለ፡፡

የመንግስቱ ድል በወዳጆቻቸው በዶ/ር ሠናይ ልኬና በኮሎኔል ዳንኤል አስፋው መገደል ደበዘዘ፡፡ ፍንቀላው ግን ተሳካ፡፡ ከዚህ በኋላ የመንግስቱ አምባገነንንነት የበለጠ እልህ የተሞላበት ሆነ፡፡ የዚህ መፈንቅለ መንግስት አደራጆች መንግስቱ ብቻ ሳይሆኑ የመኢሶን እና የወዝ ሊግ አመራር አባላት የሆኑ ምሁራን ሰፊውን ድርሻ ይይዛሉ፡፡በዚህ ጊዜ  ነው መንግስቱ "ለምሳ ያሰቡንን ለቁርስ አደረግናቸው" በማለት መግለጫ የሰጡት፡፡

አሁን ደርግ የኢህአፓ ተሟጋች ሆነው "እርቅ" የሚሉትን ሁሉ ደምስሶ ነፃ እርምጃ ለመውሰድ መንገዱን ጠርጓል፡፡ ኮሎኔል መንግስቱ የጄኔራሎችን መጋረጃ ገላልጠው ከፊት ሆኑ፡፡ ከተቀዳሚ ሊቀመንበርነት የደርጉ ዋና ሊቀመንበር ሆኑ፣ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥነቱንም ደርበው ያዙ፡፡ ቀጥሎ አስጊ ያልሆኑት፣ ነገር ግን በየስብሰባው ያውካሉ

የተሰኙት ምክትል የደርጉ ሊቀመንበር ኮሎኔል አጥናፉ አባተ ቀሩ፡፡ አዋኪነታቸው እንዴት ነው? ቢባል በአስተዳደር ጉዳይ እንጂ ለአብዮቱ ፍፁም ታማኝ መሆናቸው ይታወቃል፡፡

አንድ ቀን በስብሰባ ላይ እጃቸውን አውጥተው ሲናገሩ ሲሉ፤ ያ የተለመደ ጭቅጭቃቸው ነው ተብሎ እድል ተነፈጉ፡፡ እሳቸው ግን ተሰብሳቢው አዳራሹን ለቆ እየወጣ ሳለ ጮክ ብለው "ተው ግዴለም ስሙኝ! ይቺ አገር የሚበጃት ቅይጥ ኢኮኖሚ ነው..." ማለታቸውን እስር ላይ የሚገኙ አባላት ደጋግመው ገልፀዋል፡፡ ሰሚ ግን አላገኙም፡፡ ጭራሽ ይሄ አብዮቱን የማወክና የማርክሲዝምን ርዕዮት የሚቃወም ተደርጎ ተፈረጀና ጣት ተቀሰረባቸው፡፡ በዚህም ላይ በተቃዋሚዎች ላይ የሚወሰደው እርምጃ መልክ እንዲኖረው ደጋግመው ያሳሰቡ ነበር፡፡ እኚህ ሰው የእነ ተፈሪ በንቲን መረሸንም የሰሙት ለስራ ከሄዱበት ክፍለሃገር ሆነው ነበርና እንደሰሙ በጣም ደንግጠው በቁጣ "ትናንት አማንን ገደልን ዛሬ ደግሞ..." በሚል ቁጭት ላይ ነበሩ፡፡ ወዲያውም በአስቸኳይ ተጠርተው ከነቁጣቸው ቤተመንግስት እንደደረሱ መንግስቱ አረጋግተውና የተረሸኑት በሴራቸው ምክንያት እንደሆነ ገልፀው፤ አለዝበው ሸኟቸው፡፡ የአጥናፉን መናደድ መንግስቱ አልወደዱትም፤ ከ10 ወራት በኋላ በህዳር ወር 1970 ዓ.ም ሆነ ተብሎ በተጠራ የደርጉ ስብሰባ ላይ የአጥናፉ ጉዳይ ተተነተነ፡፡ "እርምጃ ሲወሰድ ይቃወማል፣ የሶሻሊዝምን መሠረታዊ መርሆዎች የሚፃረሩ አስተያየቶች እየሰነዘረ ያውካል..." ተባለና የመንግስቱ አጫፋሪዎች የይረሸን ውሣኔውን ለገሱ፡፡ ተፈርዶባቸው ተረሸኑ፡፡ ፍፁም ስህተት የተሰራው እዚህ ላይ ነው ይላሉ ተፀፃች አባላቱ፡፡ ያለሀጥያቱ ለአገር ጥቅም ሲል በተናገረው የተገደለ ነው ይሉታል፡፡ ብቻ የደርጉ መሰራች ተቀጩ፡፡

አበቃ፡፡ መንግስቱ በእሺ ባይ የበታቾቻቸው ብቻ ታጀቡ፡፡ አዲሱን የደርግ አወቃቀርም በራሳቸው ታማኞች ሞሉት፡፡ ግለሰቦች በዚህ መልኩ ከተመነጠሩ በኋላ ቀጣይ ስራ የሆነው ፓርቲዎችን ወይም የፖለቲካ ድርጅቶችን ማጥራት ሆነ፡፡

የግራ ክንፍ ሆነው ነገር ግን ለደርግ በጎ ምልከታ ያላቸው ድርጅቶች ተባብረው በአንድ በኩል ኢህአፓን ለመደቆስ፣ በሌላ በኩል ከደርግ የሚመነጨውን ስልጣን ለመቀራመት ያመቹ ዘንድ፤ እንዲሁም ከኢህፓ በልጠ ለመፈርጠም ሲሉ "የኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅቶች ኅብረት (ኢማሌድኅ)ን መሠረቱ፡፡ በየካቲት ወር 1969 ይህን ኅብረት መሰርተውም ሰፊውን ህዝብና ተራማጅ ኃይሎችን በማደራጀት ግንባር ቀደም ፓርቲ መመስረት የሚቻለው በዚህ ዘዴ መሆኑን እየገለፁ ተኩራሩ፡፡



ኢማሌድኅ ግን እንደታሰበው ጠንካራ ፓርቲ አምጦ ሲወልድ ቀርቶ ጭራሽ የመበታተኛ መድረክ ሆኖ አረፈው፡፡ በአንድ ጥላ ስር የተሰባሰቡት ድርጅቶች የበላይነትን ለማወጅ እርስ በርስ መፎካከር ጀመሩ፡፡ በተለይ መኢሶን እኔ ነኝ የበላይ የሚል አቋም ይዞ መኩራራት ስራው ሆነ፡፡ በዚህ ሳቢያ ሌላ ግብግብ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ተጀመረ፡፡ እንኳኑ የመከራከሪያ ጉዳይም "ዴሞክራሲያዊ መብቶች በምን ዓይነት ሁኔታ ይፈቀዱ? ያለገደብ ወይንስ በገደብ? አብዮቱ ሲረጋጋ ወይስ አሁኑኑ?" የሚሉ ነበሩ፡፡

በሰፊው የስልጣን መሠረቱን እንደጣለ የተሰማውና በኅብረቱ ውስጥ ከተሰባሰቡት ድርጅቶች አንዱ የሆነው መኢሶን "አሁኑኑ ያለ ገደብ ይፈቀድ" ሲል፤ ሌሎቹ ደግሞ "ሰፊው ህዝብ ሳይደራጅ ገና በእንጭጩ እንዲህ ያለ ተግባር መፈፀም አብዮቱን ለፀረ አብዮተኞች አሳልፎ መስጠት ነው" እያሉ ሞገቱ፡፡

ደርግና ሠደድ የመኢሶን "አሁኑኑ" ባይነትና ሌሎች የእንቡር እንቡር እንቅስቃሴ አላማረውምና "መኢሶን ወዳጅ ብለን ብናስጠጋው እብጠት ተሰማው" በሚል ተወንጅሎ በደርግ ዘንድ የነበረው ተቀባይነት ቀረና ንቀትና ተፅዕኖ ደረሰበት፡፡ ይህን የተረዱትና ጥርስ እንደተነከሰባቸው የገባቸው የመኢሶን አባላት ያለእንዳች ዝግጅት በደርግ ላይ የትጥቅ ትግል አውጀናል ብለው አኩርፈው አዲስ አበባን ለቀው በተለያየ መንገድና በተለያየ አቅጣጫ ነጎዱ፡፡ ግማሹ በጅማ የቀረው በሌላ ተበታትነው ሲጓዙ በደርግ የማሳደድ ዘመቻ ከፊሎቹ ተይዘው ታሰሩ፤ የቀሩት ተገደሉ፡፡ በለስ የቀናቸው አገር ጥለው ሸሹ፡፡ የመኢሶን ታሪክ በዚሁ ያበቃል፡፡

ጥቂት ዘግየት ብሎም ኢጭአት የመኢሶን ዕጣ ገጠመውና በደርግ ተደመሰሰ፡፡ እነዚህን ድርጅቶች በመምታት የደርግ ተባባሪ የነበረው ወዝሊግም በ1971 ዓ.ም ሰደድን ለመቆጣጠር ሠርጎ ገብቷል በሚል ውንጀላ በደርግ ተመታ፡፡ ወይም ተበተነ፡፡ የቀረው ምንም አቅም ያልነበረው ማሌሪድ ነበርና ደርግ እሱን ለማጥፋት አንድ ቀንም አልፈጀበት ተመታ፤ ተበተነ፡፡

ከዚህ በኋላ ማለትም ከ1971 ዓ.ም ጀምሮ ብቸኛው አውራ ፓርቲ አብዮታዊ ሠደድ ሆነ፡፡ ደርግና ሠደድ ያንድ ሣንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው፡፡ በሠደድ ስም ሲቪሉ ይደራጃል፤ ሲቪሉንም ደርግ ያዘዋል ማለት ነው፡፡ የደርግ ዘመን ፓርቲዎች በአጭሩ ባየነው መልኩ ተወልደው ባየነው መልኩ ከሰመዋል፡፡ የቀሩት ስልጣን የያዘው ደርግ እና፤ ተቃዋሚው ኢህአፓ ነው፡፡ እነዚህም የከተማ ጦርነቱን ስራቸው አደረጉት፡፡

## የኢሀአፓ ነጭ ሽበር

ከአልጀሪያው ቡድን እነ ብርሃነመስቀል ረዳ፣ እያሡ አለማየሁ፣ አብዲሣ አያና፣ ዶ/ር ተስፋዬ ደበሳይ፣ ዶ/ር መኮንን ጆቴ እንዲሁም ከሶቭየት፣ ከአሜሪካና ከምዕራብ አውሮፓ እነ ክፍሉ ታደሰ፣ መሐመድ ማህፉዝን የመሳሰሉ ፖለቲከኞች አንድ ድርጅት ማቋቋማቸውን አውሮፓ ሆነው ይፋ ካደረጉ በኋላ፤ ከአገር ውስጥ ሽማቂ ቡድኖችና ከሲቪል ደጋፊዎቻቸው ጋር በተለያዩ ጊዜ፣ ዓይነትና ሁኔታ ግንኙነት እያደረጉ ከአብዮቱ በኋላ ጠንካራ የግራ ክንፍ ሆነው የስልጣን ትግል አድርገዋል፡፡ በአገር ፍቅር ስሜት ልቡ የነደደውን የኢትዮጵያ ወጣት ለስውር አላማቸው ማስፈፀሚያ ይሆን ዘንድ በፕሮፓጋንዳ ከጎናቸው አሠልፈው የቀይ ሽብር ሰለባ አድርገውታል፡፡ በመጨረሻም ለገዳይ አሳልፈው ሰጥተውት ፈርጥጠዋል፡፡

ነጭ ሽብር የኢህአፓ የግድያ መፈክር ነበር፤ ቀይ ሽብር የደርግ የመልስ ምት መፈክር ነው፡፡ ኢህአፓ ነጭ ሽብርን ባይጀምር ቀይ ሽብር የሚባል ነገር ኢትዮጵያ ውስጥ ባልኖረ ነበር፡፡ የኢህአፓ ዓላማ ምን ነበር? ስንል ምላሹ ሁለት ነው፤ አንደኛ ስልጣን፣ ሁለተኛ ከበስተጀርባ ያሉትን አጋሮች የመገንጠል ጥያቄ በኢትዮጵያ ብሔሮች ሽፋን ማስፈፀም፡፡

ኢህአፓና ደርግ ወይም ሌሎች የዚያ ዘመን የፖለቲካ ድርጅቶች ርዕዮት አንድ ነው፡፡ ሁሉም ፊውዳሊዝምንና ኢምፔሪያሊዝምን በጽኑ የሚያወግዙና ሲያወግዙ የኖሩ ማርክሲስቶች ናቸው፡፡ ደርግ ስልጣኑን ለሌላ አካል ያስረክብም አያስረክብም አስተዳደራዊ መዋቅሩን የዘረጋው በሳይንሳዊ ሶሻሊዝም ሲሆን፤ይህም የኢህአፓ የራሱ መሻት የነበረ ነው፡፡

ታዲያ እነዚህ አገር በቀል ቡድኖች ምን አጋጫቸው? ብለን ስንጠይቅ ነው ከላይ የተጠቀሱት ምላሾች ብቸኛ መልስ ሆነው የምናገኛቸው፡፡ ለዚህም ነው በርካታ ምሁራን "ገንጣይና አስገንጣይ" በሚል ታሪኩ ካለፈ በኋላ በየፕሬስ ውጤቱ ሲሞላለጩ የከረሙት፡፡

ደርግ በወቅቱ ስልጣኑን ለኢህአፓ ሰጠ ማለት ኢትዮጵያን ለገንጣይና አስገንጣዮች አሳልፎ ሰጠ የማለት ያህል ነው፡፡ ደርግ የእነዚህን ኃይሎች ተቃውሞ ለማለዘብ ሲል ሲሹት የኖሩትን ርዕዮትና ሀሳባቸውን ሁሉ በተግባር ቢለውጥም ማለዘብ አልቻለም፡፡ ኢህአፓ በደርግ አሰሳ ከከተማ ከተደመሰሰ በኋላም በርሃ ካሉ ቡድኖች ጋር ተቀላቅሎ ሲታገልና በስተመጨረሻም ደርግ ሲወድቅ ያችኑ ዓላማ ተግባራዊ ማድረግን ነበር የመጀመሪያ ስራው ያደረገው፡፡ እንጅማ በዚያ ወቅት ኢህአፓ ዓላማው ስለኢትዮጵያና ስለህዝቦቿ ከልቡ ተቆርቁሮ ቢሆን ኖሮ በተከታይነት በምናየው በሶማሊያ ወረራ ከሶማሊያ ጎን ተሰልፎ ደርግን ባልወጋ ነበር፡፡



በጠንካራ ዲሲፕሊን የተደራጀውና አንድ አባል ለሦስት ተከታታይ ጊዜያት በስብሰባ ላይ ካልተገኘ እንደሚገደል ለአባላቱ ይፋ ያደረገው ኢህአፓ መንግስቱ ኃይለማርያም ላይ የመግደል ሙከራ ካደረገና በዶ/ር ፍቅሬ መርዕድ ላይ ከዚህ በፊት ያየነውን ግድያ ከፈፀመ ጀምሮ፤ በጊዜያዊ መንግስቱ ባለሥልጣናትና ደጋፊዎች ላይ "ነጭ ሽብርን" አውጆ ተከታታይ ግድያዎችን ፈጽሟል፡፡ ኢህአፓ በወቅቱ የግድያ ኢላማዎቹ ማን ማን እንደሆኑ ጠንቅቆ ያውቃል፤ ደርግ ግን በስተመጨረሻ በመኢሶን አመራር አባላት አማካኝነት የስም ዝርዝር እስኪቀርብለት ድረስ ምንም መረጃ አልነበረውም፡፡ "ቀይ ሽብር" የሚባለውን መፈክርም ደርግ አያውቀውም ነበር፡፡ ከነጭ ሽብር በኋላ ሊያውቀውና ሊፎክርበት ተገደደ፡፡ ስለቀይ ሽብር ብዙ ተብሏል፡፡ የቀይ ሽብር ሰለባዎች ታስበዋል፤ ተዘክረዋል፣ ሐውልትም ታንጾላቸዋል፡፡ ይህ ተገቢ ተግባር መሆኑ ለማንም ግልፅ ከመሆኑም በላይ፤ ለምን ተዘከሩ? የሚል ተቃውሞ አያስነሳም፡፡

ነገር ግን የነጭ ሽብር ሰለባዎችን እንኳን መዘከር ቀርቶ ስማቸውን ያነሳ አካል አለመኖሩ በርካቶችን አሳዝኗል፡፡

ጦርነት ነው፡፡ የወንድማማቾች የፖለቲካ ፀብ የፈጠረው ጦርነት፡፡ የነጭና የቀይ ሽብር ሰለባዎች ኢትዮጵያዊ ናቸው፡፡ በኢህአፓም በደርግም በኩል ተሰልፈው በሁለቱም አይነት ሽብሮች በሽዎች የሚቆጠሩ ዜጎች ተገድለዋል፡፡ በኢህአፓ ጎን የተሰለፉት የቀይ ሽብር ሰለባ ሲሆኑ፤ በደርግ በኩል የተሰለፉት የነጭ ሽብር ሰለባ ሆኑና፤ ደርግ ሲወድቅ ቀይ ሽብርን የፈፀሙት ለፍርድ ቀረቡ፡፡ ነጭ ሽብርና ሰለባዎቹ ግን ከታሪክ ተፍቀው ወጡ፡፡ፍትህ የአሸናፊዎች ደንገጡር ሆነች፡፡

በነጭ ሽብር ከተገደሉት ዜጎች ይልቅ በቀይ ሽብር የተገደሉት በቁጥር ቢበልጡም፤ በነጭ ሽብር ብቻ ግን 1 ሺ 119 ሰዎች እንደተገደሉ የተረጋገጠ ነው፡፡ እንዲያውም ከዚህ በላይ ናቸው የሚሉ በርካታ ምስክሮች አሉ፡፡ በቀይ ሽብር ያለቁትን ልዩ ዐቃቤ ሕግ 6 ሺ ነው ብሏል፡፡ የደርግ አባላት ግን 2ሺ ነው ብለው ይከራከራሉ፡፡ ምንም ቢሆን ቁጥሩ ተቀራራቢ መሆኑ እንዳለ ሆኖ፤ የነጭ ሽብር ሰለባዎችን የሚፋረድላቸው አላገኙም፡፡

እነዚህን ኢትዮጵያውያን ታሪክ ረስቷቸዋል፤ ወይም እንዲረሳቸው ልዩ ጥረት ይደረጋል፡፡ የእነሱ ደም ከንቱ ሆኖ የቀረበት ምክንያት ምንድነው ሊባል ነው? ቢባል መልስ የለም፡፡ መጠየቅም ያስኮንናል፡፡ ኢህአፓ የመጀመሪያውን ጥይት ተኩሷል፡፡ ይህ ስልጣን ላይ ባለ መንግስት እይታ ሽብር ፈጠራ ነው፡፡ ሠላማዊ ትግል ግድያ አያካትትምና፡፡ ለአገርና ለህዝብ ተቆርቋሪ የሆነ ድርጅት ደግሞ በከተማ

ውስጥ ሆኖ ሠላማዊ ትግል እያደረኩ ነው ብሎ ጎን ለጎን በግድያ ተግባር መሠማራት ምን ማለት መሆኑ ለማንም አይሰወርም፡፡

በእስር ላይ የሚገኙ የደርግ ባለሥልጣናት በአንድ ነገር በጋራ ይፀፀታሉ፤በ60ዎቹ የጃንሆይ ባለስልጣናት ግድያ፡፡ በቀይ ሽብርስ? ሲባሉ በፍፁም አይፀፀቱም፡፡ "ራሳቸው የጫሩት እሣት ነው" ሲሉ ይመልሳሉ፡፡አሳማኝ መከራከሪያቸው "ነጭ ሽብርስ?" የሚለው ነው፡፡

ሻ/ል ተስፋዬ ርስቴ በ"ምስክርነት" መፃህፋቸው የኢህአፓን የግድያ ተግባር በሚያትቱበት ገጽ ላይ "... የድርጅቱ የፖለቲካ ቢሮ ተለዋጭ አባል የነበረው ጌታቸው ማሩ የእልቂት ድርጊታቸው ትክክል አለመሆኑን በመግለፁ መስፍን ሐረር መንገድ በላይ ዘለቀ በሽመቁበት ቦታ ገድለው ራሱን፣ እጁን፣ እግሩንና ሌላውን አካሉን ለየብቻ ቆራርጠው በጆንያ ከትተው ክፍሉ ታደሰና ተስፋዬ ደበሳይ አውጥተው ሊጥሉት ሲሉ (ለተገንጣይ ስትራቴጂስቶች ሲሉ) ሻለቃ ጌታቸው ሽበሽ የመራው ጦር ደርሶባቸው የተቆራረጠውን አስከሬን ጥለው አምልጠዋል፡፡ ..." በማለት የኢህአፓን ኢሰብአዊ ተግባር ይገልፃሉ፡፡

ሲቀጥሉም "... ለነገሩማ ተስፋዬ ደበሳይ በንግስት እሌኒ ጠቋሚነት ፖስታ ቤት አካባቢ ሊያዝ ሲል አምልጦ ከአምባሳደር የመጨረሻ ፎቅ ተወርውሮ ራሱን የገደለው ለኢህአፓ በነበረው ቁርጠኛ እምነት ሳይሆን በታዋቂው የኢትዮጵያ የመረጃ ድርጅት ምርመራ የሻዕቢያን የአዲስ አበባ ግድያና የመረጃ መዋቅር አወጣው ይሆናል ብሎ ሰግቶ እንደነበር እነክፍሉ ታደሰ ገና ሊጠረጥሩ አልቻሉም..." ይሉናል፡፡ (ምስክርነት 2001 ዓ.ም ገፅ 145)

የታችኛው የኢህአፓ አባላት ትግላቸው ኢትዮጵያዊነትን የተላበሰ እንደሆነ አስበውና ተነግሯቸው ይፋለሙ እንጂ፤ ቁንጮ ቁንጮው አመራር የሻዕቢያ እቅድ አስፈፃሚዎች የነበሩ ናቸው፡፡ ፀሐፊው የአሠፋ ጫቦን ገለፃም አካተዋል፤ "ዶ/ር ፍቅሬ መርሻድ ባለቤቱን ሊያመጣ ሄዶ ከሚጠብቅበት ሞርጌጅ ባንክ ህንፃ አጠገብ በኢህአፓ ተገደለ፡፡ በአገራችን በኋላ ቀይ ሽብር፣ ነጭ ሽብር የተባለውን መንገድ የከፈተው የፍቅሬ መገደል ነበር፡፡ ብቻ የመጀመሪያውን ቃታ የሳበ ኢህአፓ ነበር" ሲሉ ያረጋግጣሉ፡፡

የእነክፍሉ ታደሰ አጋር የነበሩትን በመጥቀስም ".... አገሬ ዛሬ ለደረሰባት ንቅዘ የበላው ቤትነት አንድ ደርግ በሚባል ጭራቅ ላይ ብቻ ብንለክክ የህሊና ንፅህና የምናገኝ አይመስለኝም" በሚል የዚያ ዘመን የ"ነጭ ሽበር" አራማጆች ጥፋታቸውን እያመኑ እንደሆነ ተገልጿል፡፡ በሌላ ወገን የመኢሶን አመራር አባላት ደርግ ላይ ብቻ ጥፋቱ ተደፍድፎ እንዲቀር የካዱ ይኑሩ እንጂ፤ ደርግ ቀይ ሽብርን ተግባራዊ ሊያደርግ የእነሱ እገዛ እንደነበረበት ያመኑ አልጠፉም፡፡ ከላይ የጠቀስናቸው ፀሐፊ



"... የኢህአፓ አባላትን ስም ዝርዝር መኢሶን ለደርግ ባይሰጥና በጋዜጣ ባይወጣ ደርግ የኢህአፓን ነብሰገዳዮች ከህዝብ ባህር ውስጥ ፈልፍሎ ለማውጣት ጊዜ ይፈጅበት ነበር" ይላሉ፡፡ (ገፅ 146)

በጥቅሉ ኢህአፓ ከላይ እስከታች መዋቅር ዘርግቶ በሚስጥራዊ ኮዶች ከአባላቱ ጋር እየተገናኘ የከተማ ውስጥ ትግሉን አጧጡፎ፣ ግድያውንም በነጭ ሽብር መፈክር አጠንክሮ ከመቀጠል ባለፈ፤ አዲስ አበባ ውስጥ የሚገኙን ባንክ እስከመዝረፍ ድረስ የዘለቀ ተግባር ፈፅሟል፡፡ በአንድ ዙር ዝርፊያ ብቻ ከሾላ ገርጂ ባንክ ግማሽ ሚሊዮን ብር ዘርፏል፡፡ ለምሳሌ በሰኔ ወር 1969 ዓ.ም የአዲስ ከተማ ቁጭራ ባንክን የዘረፈው የሻዕቢያ አባል የሆነው ኃይቶም ለባሲ የመራው የኢህአፓ ቡድን ነበር፡፡ በተጨማሪም በትግራይ በኩል ባስገቡት ፈንጂ የአዲስ አበባ መዘጋጃ ቤትና በዋቢሸበሌ ሆቴል አፈንድተው በርካታ ንፁሀን ሲቢሎችን ገድለዋል፡፡ (ትዝታዎች ቁ.1 ገጽ 30)

በዚህና በዚህ መሰል ተግባር ኢህአፓ ደርግን መቀመጫ አሳጣው፡፡እንደመንግስትም ሆነ እንደ ጊዜያዊ መንግስት ደርግ መከላከልና እርምጃ መውሰድ ነበረበት፡፡ነጭ ሽብሩ ተጧጡፎ በመቀጠሉም "አስታጥቁን አታሰጨርሱን!" የሚለው ህዝብ በረከተ፡፡

ደርግና መኢሶን ተባብረው ባሳለፉት ውሣኔ ከላይኛው መቺ ጦር ጀምሮ እስከታችኛው የቀበሌ ተመራጮች ድረስ አስታጠቁ፡፡ "ነፃ እርምጃ በኢህአፓ ላይ እንዲወሰድ አወጁ፡፡ "ቀይ ሽብር ይፋፋም!" አሉ፤ ተፋፋመ፡፤ እዚህ ላይ መጠቀስ ያለበት ጉዳይ አለ፤ ይኸውም ከኢህአፓ ጥቃት ራሱን እንዲከላከልና እንዲያጠቃበት የታጠቀውን መሣሪያ በተለይ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የነበሩት የቀበሌ ሹሞች በኢህአፓነት ሽፋን በግል ቂም በቀል እና በድንበር ገፋህኝ ... ወዘተ ሕገ-ወጥ ግድያዎች አከናውነዋል፡፡

ደርግና መኢሶን ከላይ እስከታች ካስታጠቁ በኋላም፤ "አብዮቱ ከተከላካይነት ወደ አጥቂነት ተሸጋግሯል" አሉ፡፡ ይህ አዋጅ በ1969 መገባደጃ ይፋ ከሆነ በኋላም ደርግ የነጭ ሽብር አራማጅ የሆኑትን ፀረ ሠላም ኃይሎች እያደነ በመያዝ፣ ከድተው በሚመጡ የኢህአፓ አባላት ጠቋሚነት እየታገዘ መዋቅራቸውን ማፈራረስ ጀመረ፡፡ የተያዙትንና ምስጢር አላወጣ ያሉትንም በከባድ ግርፊያ እያሰቃዩ ማውጣጣት፣ መግደል ስራው አደረገ፡፡ በ1971 ዓ.ም የኢህአፓን መዋቅር ለማፈራረስ እና የመሳሪያ ግምጃ ቤታቸውን ሳይቀር መማረክ ቢቻልም፤ ከወራት በኋላ እንደገና በልዩና በረቀቀ ዘዴ አባላቱ ሊደራጁ ሞክረዋል፡፡ በራሱ በደርግ ውስጥ ሠርጎ ለመግባት ጥረዋል፣ በየጦር ክፍሉም ሠርገው ለመግባትና የበላይ አዛዦችን እስከመመልመል ደርሰዋል፡፡

ባየነው መሠረት ኢህአፓ በራሱ ቀስቃሽነት የጀመረው ነጭ ሽብር ተጋግሎ በመቀጠሉ ደርግ እና መኢሶን የመልስ ምት ለመስጠት ቀይ ሽብር ብለው በማወጃቸው በርካታ አገር ወዳድና ወጣት የኢትዮጵያ ልጆች አልቀዋል፡፡ የመኢሶን ሚና እስከሸፈተበትና ህቡዕ ገባሁ ብሎ እስካወጀበት እስከ ሰኔ 10 ቀን 1969 ድረስ የቆየ ሲሆን፤ ቀሪውን እርምጃ ደርግ ራሱ ቀጥሎበታል፡፡ ስለሆነም በሁለቱም አይነት ሽብር ሠለባ ስለሆኑት ዜጎች ሲነሳ ተጠያቂው ደርግ፣ ኢህአፓና መኢሶን መሆናቸው መታወቅ አለበት፡፡ ከዚሁ ጋርም ስለቀይ ሽብር ሰለባዎች ሲነሳ ስለነጭ ሽብር ሰለባዎችም መዘከር አለበት የሚለው የብዙሃኑ ፍትሐዊ ምልከታ በክፉ ሊታይ እንደማይገባ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ "ክብር ለነጭ ሽብር ሰማዕታት" "ክብር ለቀይ ሽብር ሰማዕታት" ብለናል፡፡

ጓድ ቁጥር· አስራ አንድ ለገነት አየለ ቀይሽብርን በሚመለከት ከገለፁት ውስጥ ተከታዩ ሐተታ ይገኛል፤ "በኢህአፓ በትር በነጭ ሽብር የተጨፈጨፉት በይፋ የሚታወቀው 1,319 ይሁን እንጂ ቁጥራቸው ከዚህ በላይ ነው፡፡ አሁን እኛን በቀይ ሽብር የሚወነጅሉን ለምን የነጭ ሽብርን ሰለባዎች አይፋረዱላቸውም? እነሱ ኢትዮጵያውያን አይደሉም? ወይስ የእነሱ ደም ደመ ከልብ ነው? የቀይ ሽበር ተፋራጅ ኮሚቴ እንደተቋቋመ ሁሉ፤ የነጭ ሽብርም ቢቋቋም ኖሮ ፍትሐዊ ይሆን ነበር፡፡ ቀይ ሽብርን ከመጠሪያው ከቃሉ ጀምሮ ያመጡት እነሱው ራሳቸው ናቸው፡፡ ወታደር ይሄንን ከየት ያውቃል? በሶማሊያ ወረራ ወቅት ኢህአፓ የፈፀመው ክህደት መረሳት የለበትም፡፡ በኤርትራም ችግር ኢህአፓ በግልፅ የወገነው ከጠላቶቻችን ጋር ነበር፡፡ ሻዕቢያን እንደሚደግፍ በይፋ ተናግሯል፡፡ በኢትዮጵያ ሕግ ደግሞ በአገር ላይ የሚፈፀም ክህደት እስከሞት ድረስ ያስቀጣል፡፡..." (ገፅ 31) በመጨረሻ ዋናው አቀናባሪ ተስፋዬ ደበሳይ ያለበት ቦታ በጥቆማ ተደርሶበት ደርግ ሲከበብ ራሱን ከፎቅ ወርውሮ ከሞተ በኋላ ግድያው ጋብ እንዳ፡፡ የቀድሞው ሊቀመንበር መንግስቱ ይናገራሉ፡፡ በ1970ዎቹ የመጀመሪያ አመታት ጀምሮም ኢህአፓ እየተሰነጣጠቀ፣ እየተበታተነ ሄደ፡፡ ብርሃነመስቀል ረዳም ከባለቤቱ ጋር ከከተማ ወጥቶ ሲሸሽ ወሎ አካባቢ በገበሬዎች እጅ እንደተገደለ ይነገራል፡፡ ባለቤቱ ወ/ሮ ታደለች ኃይለሚካኤል ነብሰጡር ስለነበሩ የተባሉት ገበሬዎች ሳይገድሏቸው እንደተረፉ እና ለረጅም ዓመታት በእስር ላይ ቆይተው ኢህአዴግ አዲስ አበባ ሲገባ ከእስር ተፈትተው፤ በመጀመሪያ የሴቶች ጉዳይ ኃላፊ፣ በአሁኑ ጊዜ ደግሞ በኮትዲቯር የኢትዮጵያ አምባሳደር እንደሆኑ በ"መንግስቱ ትዝታዎች" ቁጥር 1 መጽሐፍ በገፅ 190 ተጠቅሶ ይገኛል፡፡

የቀይ ሽብርን ሕገወጥነት በሚመለከት መንግስቱ ሲጠየቁ፤ "እሺ እኛስ እንዲህ ተባልን፡፡ ሌላውስ ምን ሲያደርግ ነበር? ለምን የሌላው ወገን



ስህተት አይታይም? ኢህአፓ በየትኛው ሕግ ተመርታ ኖሯል ሰውን በጠራራ ፀሐይ እየደፋች ስትሄድ የነበረው? በየትኛው ፍርድ ቤት ብይን አግኝታ ነው ሰው ላይ እርምጃ ስትወስድ የነበረው?" በማለት ነው፡፡

ይህ ሁሉ ሲሆን ተደጋግሞ እንደተገለፀው ክስር ያሉ የኢህአፓ ምልምል አባላት አብዛኛዎቹ ለኢትዮጵያ አብዮት እየታገሉ እንደሆነ ነበር የሚያውቁት፡፡ ለዚህም ነው ተበትነው ወደ በረሃ ሲገቡ ብዙዎች ያልጠበቁት ጉዳይ የገጠማቸውና የተገረሙት፡፡ ይህን ጉዳይ ከመንግስቱ ኃይለማርያም ገለፃ ተረድተን እናብቃ፡፡

"... እዚህ ላይ ሁልጊዜ የማይነሳ ወይም ሆን ተብሎ የሚዘለል ጥያቄ አለ፡፡ ኢህአፓ ሠርጎ ገቦችና ከሞላ ጎደል የከተማ ትጥቅ ትግል የሚያካሂዱ፤ ለዚያውም በሚሰጣቸው ሊስትና ጥቆማ ዒላማ የሚመቱ የተወሰኑ ወጣቶችን በከተማ ውስጥ ስታሰማራ ከተከታዮቿ የሚበልጠው ኢትዮጵያን ለማጥለቅለቅና መንግስትን ለመገልበጥ የተሰበሰበው ኃይሏ የሄደው ትግራይ አሲምባ ነው፡፡

"የት ሄደ ያሁሉ የኢትዮጵያ ወጣት? የት ደረሰ? ማን ፈጀው? ይሄንን የጠየቀ ሰው አለ? የኢህአፓ ዋናው ሠራዊት የነበረው ትግራይ ነበር፡፡ አሲምባ የከተተው ያ ሁሉ የት ደረሰ?

"ልጆቹ የኢህአፓን ዓላማ ለማራመድ ትግራይ ሲሄዱ ያልገባቸው ነገር አለ፡፡ እነሱ አብዮት የሚያካሂዱ፣ ለኢትዮጵያ ህዝብ የሚታገሉ ነው የመሰላቸው፡፡ ብሔራዊ ስሜት የነበራቸው ናቸው፡፡ እዚያ ሲደርሱ ግን ያጋጠማቸው ጀብሃና ሻዕቢያ ነበር፡፡ ኢትዮጵያ ብሎ ነገር በአጀንዳቸው የሌለ ፍፁም ፀረ ኢትዮጵያ አቋም ያላቸው ገንጣዮች፡፡ እንዴ? ምንድነው ይሄ ነገር? የሚል ጥያቄ ሲያነሱ "እሃ!" ይህቺ ባቄላ ካደረች አትቆረጠምም" ተብሎ በወያኔ ሠራዊት ተጨፍጭፈዋል፡፡ አተኙበት ቦታ፣ ለ...ሽ ብለው እንደተኙ ሌሊት በደንብ በተዘጋጀ ሠራዊት ጭፍጭፍ አድርገው ፈጅተዋቸዋል፡፡ በዚህ አይነት በግፍ ያለቁት ቁጥር ስንት ነው? ይህን ያነሳ አለ? መለስ ዜናዊ "ኢህአፓ" እያለ ተቆርቋሪ ሆኖ ሲናገር ግርም ነው የሚለኝ፡፡ ወደደም ጠላም ሀቢና ካለው ዛሬ ለሀሊና ፍርድ ነገ ደግሞ ለህዝብ ፍርድ መቅረቡ የማይቀር ነው፡፡ የትግራይ ህዝብ ይሄንን ያውቃል፡፡ ኢህአፓዎች ሁሉም አላለቁም፡፡ ቢጠየቁ ይናገራሉ፡፡"

ገነት፤ "እና እርሰዎ የሚሉት ወያኔ ነው የፈጃቸው ነው?"

መንግስቱ፤ "ታዲያስ! ወያኔና ሻዕቢያ በአንድነት ነው የፈጁቸው፡፡ "እኛ አስልጥነንና አስታጥቀን ለዚህ ስናበቃቸው የኢትዮጵያን አንድነት ይጠይቃሉ እንዴ?" ብለው ነው ሙልጭ አድርገው ያጠፏቸው፡፡ እኛ እንደሆነ መጀመሪያ ነገር አሲምባ ሠራዊት የሚባል አልነበረንም፡፡ እዚያ ሄደንስ እናውቃለን እንዴ? የእኛ ሠራዊት የዚያን ጊዜ ያለው ምፅዋና ባሬንቱ ነበር፡፡" (ትዝታዎች ቁጥር 1 ገጽ 207)

እናም የሸማቂ ቡድኑን የደገፉት እዚያው ቀርተው ሲታገሉ፡ ያልደገፉት ወደ ደርግ ተመልሰው ይቅርታ በመጠየቅና ወደ መንግስት ስራዎች ገብተው እስከ ደርጎ ፍፃሜ ድረስ ሲቆዩ፤ ጥቂቶቹ ተሰደዋል፡፡ ሌሎቹም ተገድለዋል፡፡ •

የምስራቁ ጦርነት

ኢጣሊያና እንግሊዝ ተካፍለው ይዘዋት የነበረችው ሶማሊያ፤በ1952 ዓ.ም ነፃ ከወጣች በኋላ የራሷን ነፃ መንግስት መሰርታ ከ1953 ጀምሮ በጠቅላይ ሚኒስትር ሸርማኬን ዓሊ ስትመራ ከቆየች በኋላ ኢትዮጰያን የመውረር እቅድ እንደነበራት በተደጋጋሚ ባሳየችው ሙከራ አረጋግጣለች፡፡ነገር ግን በመፈንቅለ መንግስት ስልጣን የያዙትን የዚያድ ባሬን ያህል የተጠናከረ ዘመቻ አልተደረገም፡፡የዚያድ ባሬ መንግስት ከ1969-1973 ዓ.ም በተጠናከረ ዘመቻ ኢትዮጵያን ተፈታትኗል፡፡በ1956 በጃንሆይ ዘመን የወረራ ሙከራ ያደረገችው ሶማሊያ ሙከራዋን የኢትዮጵያ ጦር ሠራዊት በእንጭጩ ማስቀረት ችሏል፡፡

በ1970 ዓ.ም ተመሳሳይ ሙከራ ያደረገው የዚያድ ባሬ መንግስት በድጋሚ ተሸንፎ ተባረረ፡፡ ከዚህ በኋላ የአንድ ዓመት ከፍተኛ ዝግጅት በማድረግ 'የኢትዮጵያ ጦር ፊቱን ወደ ኤርትራ ማዞሩንና ከምስራቁ ግንባር ጦር ተቀንሶ ወደ ሰሜን መዝመቱን በመረዳት የዳግም ወረራ እቅዷን ለማሳካት እንቅስቃሴ ማድረግ ጀመረች፡፡ በኢትዮጵያ የበረራ ክልል ውስጥም የሶማሊያ አየር ኃይል ከ100 ጊዜ በላይ ጥሶ መግባቱ በጋሃድ ታየ፡፡

የዚያድ ባሬ እቅድና ፍላጎት ታላቋን ሶማሊያ ለመመስረትና በዚህ ምስረታም ኦጋዴን መካተት አለበት የሚል ነው፡፡

"ኦጋዴን በግዛትም፣ በባህልም፣ በቋንቋም፣ በሃይማኖትም ሆነ በዘር ረገድ የሶማሊያ አንድ አካል ነውና ህዝቡም ግዛቱም ወደ ታላቋ ሶማሊያ መጠቅለል አለበት" የሚል አቋም የያዙት ዚያድ ባሬ በተለያዩ አገራት መሪዎች ቢመከሩ፣ ቢዘከሩ እንቢ አሉ፡፡ የተባበሩት መንግስታት የአፍሪካ አገሮችን የግዛት ወሰን ሲከልል ኦጋዴንን የኢትዮጵያ ማድረጉም ሆነ ከዚያ በፊት ከነበሩት ዘመናት ጀምሮ የኢትዮጵያ ግዛት መሆኑን ዚያድ ባሬ ቢያውቁም የወረራ እቅዳቸውን ተግባራዊ ከማድረግ አልተቆጠቡም፡፡

ሶማሊያና ኢትዮጵያ ሶሻሊስት አገሮች የነበሩ በመሆናቸውም የሊቢያው ጋዳፊ፣ የኩባው ፊደል ካስትሮና ሌሎች ሊቀመንበር መንግስቱንና ዚያድ ባሬን ለማግባባት በእጅጉ ጣሩ፡፡ ኢትዮጵያ ያለባትን አጣብቂኝ አገናዝባ ወደ ዲፕሎማሲው ብታጋድልም አልሆነም፡፡ በዚህ መሀል ሶቭየት ማን እንደሚሻላትና ማንን ብትረዳ እንደምትጠቀም ስታወጣ ስታወርድ ቆየች፡፡ በመጨረሻ ዚያድ ባሬ የሶሻሊዝም አራማጅነታቸውን ጥርጣሬ ውስጥ የሚከት እንቅስቃሴዎችን በማሳየታቸው



ሶቭየት ስትረዳቸው ከቆየችው ከሶማሊያና ከኢትዮጰያ ማንን መምረጥ እንዳለባት ተረዳች፡፡ "በቃል ብቻ ሶሻሊስታዊ አገር ናት ከሚሉት ዚያድ ባሬ ይልቅ በተግባር ያረጋገጡት የሊቀመንበር መንግስቱ አገር ትሻለናለች" በሚል ውሣኔ ሶቭየት ለኢትዮጰያ ያልተቆጠበ የማቴሪያል ድጋፍ አደረገች፡፡ (በወቅቱ ኢህአፓ የሶማሊያንና የሻዕቢያን ወረራ ትክክል ነው ብሎ እውቅና የሰጠ ሲሆን፤ ይህንንም ዴሞክራሲያ በተሰኘ ልሳኑ ይፋ አድርጓል፡፡)

የሶማሊያ መንግስት ሠርጎ ገቦችን በኦጋዴን ድንበር እያስገባ የኢትዮጵያን አንዳንድ የመሠረተ ልማት አውታሮች በፈንጂ ማውደምና ሌሎች ተመሣሣይ ተግባራትን ሲያከናውን ቆዬ፡፡ ቀጥሎ መደበኛ ሠራዊታቸውን በኢትዮጵያና በጅቡቲ ድንበር በኩል እስከ ሽንሌ፣ በኦጋዴን በኩል እስከ ቀላፎ፣ በባሌና በሲዳሞ ክፍለሀገሮች በኩል ሞያሌና ነገሌ ቦረና ድረስ በማስገባት ይፋዊ ወረራ አደረጉ፡፡ የኢትዮጵያ መንግስት የኤርትራው ጦርነት ፋታ ባይሰጠውም በተቻለ መጠን የሱማሊያን ጦር በፍጥነት ለመደምሰስ ይቻል ዘንድ "ዘመቻ ላሸ" የተባለ የውጊያ እቅድ ነደፈ፡፡ ሊቀመንበር መንግስቱ ዘመቻው ተግባራዊ እንዲሆን በህዳር 1972 ዓ.ም ለመከላከያ ሚኒስትር ትዕዛዝ ሰጡ፡፡

ዘመቻው ተገቢ ዝግጅት ከተደረገበት በኋላ በአራት ምዕራፍ ተከፈለና፤ 1. ነሐሴ 22 ቀን 1972 ዓ.ም ተጀምሮ ከሽንሌ ተነስቶ ጅቡቲንና ሶማሊያን ከኢትዮጵያ ጋር የሚያዋስነውን ድንበር አፅድቶ ህዳር 15 ቀን 1973 እንዲጠናቀቅ፣ 2. ወደ ደጋማው የሐረርጌ ክፍል ሠርገው የገቡ የሶማሊያ ታጣቂዎችን ማፅዳት ስለሆነ ከመጀመሪያው ምዕራፍ እኩል በሆነ የጊዜ ገደብ እንዲጠናቀቅ፣ 3. በሁለቱ ምዕራፎች ድል የሚደረጉት ወራሪዎች በዋርዴር፣ በቀብሪደሐርና በጎዴ አውራጃዎች የሚጠራቀሙትን ኃይሎች መምታትና ማባረር ሲሆን፤ ይህም ጠንካራ ዘመቻ ስለሚሆን ነሐሴ 22 ቀን 1972 ዓ.ም ተጀምሮ በታህሳስ ወር 1973 ዓ.ም እንዲጠናቀቅ፣ የሚል ሆኖና በታቀደው መሠረት በጀግናው የኢትዮጰያ ጦር ሠራዊት ድል ከሆነ በኋላ 4ኛው ምዕራፉ ቀጠለ፡፡ ይህም በየቦታው ከተደመሰሱት ሠርጎ ገብ ኃይሎች ተርፈው የሸሹትንና ቁጥራቸውም ከ30 ሺ በላይ የሚሆኑትን የሶማሊያ እግረኛና ሜካናይዝድ ኃይሎች ተጠራቅመው የመሸጉበትን 420 ኪሎ ሜትር ስፋት ያለውን ግዛት ነፃ ማውጣት የሚል ነበር፡፡ ይህም በታህሳስ 15 ቀን 1973 ዓ.ም ተጀምሮ 10 ቀናት የፈጀ የምድርና የአየር ውጊያ ተደርጎ በኢትዮጵያ የበላይነት ታህሳስ 15 ቀን 1973 ዓ.ም በድል ተደመደመ፡፡ (ነበር ቁጥር 2)

በዚህ ጦርነት ከሶማሊያ ብቻ ሳይሆን ከኢትዮጵያም ከፍተኛ የህይወት መስዋዕትነት ተከፍሏል፡፡የኢህአፓ አባላትም ከሶማሊያ ጎን

ተሰልፈው መዋጋታቸውና መንገድ መሪ ሆነው ሶማሊያን ማገዛቸው በደምብ የሚታወቅ ነው፡፡በተጨማሪም ዚያድ ባሬና የኤርትራ አማፂያን መሪ "እኔ ከዚህ አንተ ከዚያ" በሚል ትስስርም፣ትብብርም አድርገው ነበር፡፡ "ሆኖም ዘመቻ ላሽ" ስኬታማ ሆኖ ወራሪው ጦር እንደ ላሽ ጥርግ ተደርጎ ተወገደ፡፡የዚያድ ባሬ መንግስት ያ ሁሉ ዝግጅት ከንቱ ሲሆንበት ክፉኛ ተበሳጭቶ በመጋቢት ወር 1973 ዓ.ም "ኢትዮጵያ በሶማሊያ ላይ ወረራ አውጃ ጦሯ ወደ ሞቃዲሾ እየገሰገሰ ነውና ከሠራዊትህ ጎን ተሰልፈህ ለአገርህና ለሃይማኖትህ ተዋጋ..." በማለት ለህዝቡ ጥሪ አቀረበ፡፡ ወዲያውም በግንቦት ወር 1973 ዓ.ም የመልሶ ድርጅታቸውን አጠናቀው ለ3ኛ ጊዜ ኢትዮጵያን ወረሩ፡፡የኢትዮጵያ ሠራዊት በ6 ቀናት ውስጥ የሶማሊያን ጦር ብትንትኑን አወጣው፡፡

ከዚህ በኋላም የሠላም ድርድሮች በየመንና በሌሎች አገራት ቢደረጉም ለውጥ የለም፡፡ ዚያድ ባሬ "ኦጋዴን ካልተሰጠችኝ ሠላም ብሎ ነገር የለም!" የሚል ቁርጥ ያለ አቋም ያዙ፡፡ ሊቀመንበር መንግስቱ የሶማሊያ የወረራ እቅድ ለዝንት ዓለም የማይለወጥ መሆኑን በመረዳት "እሾህን በእሾህ" የሚለውን መርህ ለመከተል ወሰኑ፡፡ የደርግ መንግስት በኦጋዴን አካባቢ የነዳጅ ዘይት ቁፋሮ እቅድም ነበረውና ይህም እውን ይሆን ዘንድ የምስራቁ ጦርነት ዛላቂ እልባት ማግኘት ስላለበት፤ ለዚህ ደግሞ የዚያድ ባሬ መንግስት መወገድ ብቸኛው መፍትሄ መሆኑን ተረድቶ እሾህን በእሾህ ቢልም፤ ለተግባራዊነቱ ግን የኢኮኖሚ አቅም አልነበረውም፡፡ ስለዚህ የሁነኛ ወዳጅ እገዛ ያስፈልግ ነበርና ጋዳፊን መምረጥ መፍትሄው ሆነ፡፡

ንጉስ እድሪስን በኃይል አውርደው ስልጣን የያዙት ጋዳፊ አንድ የተባበረ የዓረብ መንግስት የመመስረት እቅድ የያዙት ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ነው፡፡እንቅስቃሴያቸውንም ጀምረው ለዓረብ አገራት የነፃነት ታጋዮች እገዛ ማድረግ የጀመሩት በማለዳ ነበር፡፡የሱዳኑ ጄኔራል ጃፋር ኑሜሪ እና የሶማሊያው ዚያድ ባሬ ብቻ የጋዳፊን የእስልምና ተከታይ የሆኑ የአፍሪካ አገራትን የማስተባበርና የበላይ የመሆን እቅድ አልተቀበሉትም ነበርና ፀበኞች ነበሩ፡፡

ሊቢያና ኢትዮጵያ ደግሞ በ1970 ደቡብ የመን ውስጥ የጋራ የሠላም ስምምነት ተፈራርመዋል፡፡ ስለዚህ የመንግስቱን የ"እሾህን በእሾህ" እቅድ ተግባራዊ ለማድረግ ከጋዳፊ ጋር ከነበረው የበለጠ ግንኙነቶችና ምክክሮች ቀጠሉ፡፡ ጋዳፊ የኢትዮጵያን ጥያቄ ወዲያው ተቀበሉት፡፡ ጋዳፊ ለሱዳን አማፅያን በጆን ጋራንግ ይመራ ለነበረው ቡድን እገዛ ያደርጉ ነበር፡፡ በሶማሊያም ተመሳሳይ ተቃዋሚ ቢኖር ሊረዱ ዝግጁ ናቸው፡፡



ጄኔራል ፋራህ አይዲድ የሶማሊያ ምድር ጦር አዛዥ ነበሩ፡፡ ከፕሬዝዳንት ዚያድ ባሬ ጋር ስላልተስማሙ ታስረው ቆዩና በ1969 ዓ.ም የሶማሊያ ጦር ኢትዮጵያን ሲወር ያስፈልጉ ስለነበር ተፈቱና አዛዥነታቸውን እንደገና ተረከቡ፡፡ አሁንም በድጋሚ ተጣሉ፡፡ የጥላቸው መንስኤም ኢትዮጵያን መውረር የለብንም የሚል ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ ዚያድ ባሬ ከጦር አዛዥነታቸው አንስተው በህንድ የሶማሊያ አምባሳደር አደረጓቸው፡፡

የሁለቱን መቃቃር የሚያውቁት ሊቀመንበር መንግስቱ ኃይለማርያም የሊቢያን ድጋፍ እንደሚያገኙ ካወቁ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ ሲነግሯቸው ጄኔራል ፋራህ ወዲያው ወደ አዲስ አበባ መጡ፡፡ "ዚያድ ባሬን ከስልጣን አውርድና አንተ ስልጣን ያዝ፤ ኢትዮጵያና ሶማሊያም ወዳጅ አገር ይሁኑ" አሉ መንግስቱ፡፡ ጄኔራል ፋራህ አይዲድ "እሺ" አሉና ቡደናቸውን አደራጅተው በዚያድ ባሬ መንግስት ላይ የትጥቅ ትግል ጀመሩ፡፡

ኮሎኔል አብዱላሂ የሱፍ በሶማሊያው መሪ በዓሊ ሸርማኬን ላይ መፈንቅለ መንግስት ሞክረው ታስረው የነበረ ሲሆን፤ ዚያድ ባሬ በስልጣን ሲተኩ ከእስር የተለቀቁ ናቸው፡፡ ከዚያድ ባሬ ጋርም ወዲያው ተጋጩና ታሰሩ፡፡ ከዓመታት በኋላ ከእስር እንደተፈቱ በቀጥታ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ጥገኝነት ጠይቀው መኖር ጀምረዋል፡፡

መንግስቱ ኃይለማርያም ድጋፍ እንደሚያደርጉላቸው ቃል ስለገቡላቸው የጄኔራል ዚያድ ባሬን መንግስት ለመጣል የትጥቅ ትግል በ1972 ዓ.ም ጀመሩ፡፡ ከዚያም ባለፈ በሶማሊያ "የሶማሊያ ብሔራዊ ንቅናቄ" (ኤስ.ኤን.ኤም) የተሰኘ ተቃዋሚ ቡድን ነበረና በጄኔራል ፋራህ አይዲድ የሚመራው "የሶማሊያ ብሔራዊ ቅንጅት" (ኤስ.ኤን.ኤ) በኮሎኔል አብዱላሂ የሱፍ የሚመራው "የሶማሊያ መድህን ቅንጅት" (ኤስ. ኤን. ኤም) ሲጨመሩ ሦስት የተለያዩ ተቃዋሚ ቡድኖች ሆነው በዚያድ ባሬ ላይ እንዲነሱ ሆነ፡፡

ለእነዚህ ኃይሎች ኢትዮጵያ ታስፈልጋቸው ነበርና፣ ኢትዮጵያ የመደራጃ መሬት፣ ማረፊያ ቦታ፣ የስልጠናና የህክምና አገልግሎትን ጨምሮ የሰው ኃይል ድጋፍ ሳይቀር ስታደርግላቸው፣ ሊቢያ የስንቅ፣ የትጥቅና ሌሎች ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቁ ወታደራዊ ቁሳቁሶችን ታሟላ ጀመር፡፡ ኢትዮጵያና ሊቢያ ለአማፅያኑ ነፃ ፓስፖርት፣ ነፃ እንቅስቃሴ፣ ለፕሮፓጋንዳ የሚውሉ ነፃ የሚዲያ አውታሮችን መፍቀድ እንዳለባቸው ተስማምተዋል፡፡

ከሊቢያ የሚመጣውን መሣሪያ ኢትዮጵያ እየተረከበች ታከፋፍላለች፤ በዚህ መልኩ የሱዳንና የሶማሊያ አማፅያን እየተጠናከሩ ሄዱ፡፡

በጄኔራል ፋራህ እና በኮሎኔል አብዱላሂ የሱፍ የሚመሩ ቡድኖች ጠንካራ ተፋላሚ መሆን ቢችሉም፤የኮሎኔል አብዱላሂ ሁኔታ ግን ለሊቀመንበር መንግስቱ ኃይለማርያም የሚዋጥ አልሆነም፡፡ መንግስቱን ወደ ጎን አድርገው በግላቸው በምስጢር ከጋዳፊ ጋር ብቻ በተደጋጋሚ መገናኘት አዘወተሩ፡፡ ከኢትዮጵያ መንግስት ተደጋጋሚ ማስጠንቀቂያ ቢሰጣቸውም ለመስማት አልቻሉም፡፡ "ኢትዮጵያ የወደፊት ጠላቷን በጉያዋ ሸጉጣ አታሳድግም" አሉና መንግስቱ ኃይለማርያም ወደ እስር ቤት ወረወሯቸው፡፡ ይመሩት በነበረው ቡድን ላይም ዓሊ መሐዲ መሐመድ የተባሉ ሶማሊያዊ እንዲመሩት ተተኩ፡፡ የአብዱላሂ የሱፍን መታሰር ጋዳፊ ተቃወሙና ከመንግስቱ ጋር ተቃቃሩ፡፡ ከዚህ በኋላ ሦስቱ አንጃዎች የጋዳፊንና የመንግስቱን ድጋፍ ተንተርሰው ከግባቸው መድረስ ስለነበረባቸው የሁለቱን አገራት መሪዎች በተናጠል እያባበሉ ቀጠሉ፡፡

ሦስቱ ቡድኖች በሐርጌሳና በሞቃዲሾ በኩል እያጠቁ አብዛኛውን የሶማሊያ መሬት በቁጥጥራቸው ስር አደረጉ፡፡

በሐርጌሳና በሞቃዲሾ መሀል የሚገኘው ሁሉም የመገናኛ መስመር ተቋረጠ፡፡ ስለዚህ የሀርጌሳና የሞቃዲሾ ግንኙነት በአየርና በባህር ብቻ መሆን ነበረበት፡፡ የሶማሊያ ከሁለት የመሰንጠቅ ታሪክም ከዚሁ ጀመረ፡፡

የጋዳፊ ማኩረፍ ለመንግስቱ ኃይለማርያም ከባድ ፈተና ቢሆንም፤ ያለረዳት የተጀመረውን የእሾህን በእሾህ እቅድ ብቻቸውን ዳር ለማድረስ አልተሳናቸውም፡፡

የጄኔራል ፋራህ አይዲድና የዓሊ መሐዲ መሐመድ ቡድኖች በመጨረሻ በጥር ወር 1983 ዓ.ም ሞቃዲሾንም በቁጥጥር ስር አውለው ፕሬዝዳንት ዚያድ ባሬን ከስልጣን አስወገዱ፡፡ የፕሬዝዳንት መንግስቱ ኃይለማርያም የእሾህን በእሾህ እቅድም በመጨረሻዋ የስልጣን ጊዜያቸው እውን ሆኖ አዩት፡፡ በዚህ ተግባራቸውም ሶማሊያ ኢትዮጵያን የማታሰጋ አገር እንድትሆን አደረጉ፡፡

እነዚያ ሦስት ቡድኖች በጋራ የዚያድ ባሬን መንግስት ያስወግዱ እንጂ ስለቀጣዩ ሂደት ምንም የተወያዩት ነገር አልነበረምና እርስ በርስ ሲናቆሩ ኖሩ፡፡ ሶማሊያም ከሁለት ተከፈለች፣ መንግስት አልባ ሆናም ሁለት አስርት አሳለፈች፡፡ የሶማሊያ ቀውስ ዛሬም ድረስ የቀጠለ ሆኖ ይታያል፡፡ ዚያድ ባሬ ያለሙት ታላቅነት ጭራሽ አገሪቱን አሳንሳት ማለት ነው፡፡በዚህ መሠረት የደርግ መንግስት በዘመኑ የተረከባትን አገር ዳር ድንበሯን አስከብሮ የመቆየት ኃላፊነቱን በውጊያም በዘዴም ተወጥቷል፡፡



የሰሜኑ ጦርነት

በምስራቁ ግንባር ድልን የተጎናፀፈው የደርግ ጦር፤ "የምስራቁ ድል በሰሜን ኢትዮጵያም ይደገማል!" ብሎ ፊቱን ወደ ሰሜኑ ግንባር አዞረ፡፡

ባለፈው ምዕራፍ እንዳየነው በኤርትራ የትጥቅ ትግል ቀድሞ የጀመረው ጀብሃ፣ እንዲሁም አፈንግጦ የወጣው ሻዕቢያ የአካባቢው ፀረ ሠላም ኃይሎች ሆነው ቆይተዋል፡፡

ከ1967 ጀምሮ ደርግ በሁለቱም ላይ የከፈተባቸው ዘመቻ እንኳ ኅብረት እንዲፈጥሩ አላደረጋቸውም፡፡ የደርግ ጥቃት ሲመጣባቸው የተናጠል መከላከል ሲያደርጉ፤ ጥቃቱ ጋብ ሲል እርስ በርስ እየተዋጉ ዓመታት ካሳለፉ በኋላ በ1973 ጅብሃ በሻዕቢያ ሙሉ ለሙሉ ተደምስሶ ሻዕቢያ ብቻውን ተጠናክሮ የወጣ ኃይል ሆኗል፡፡

የመጀመሪያው የደርግ ማጥቃት የተሰነዘረው በ1968 "ዘመቻ ራዛ" በሚል የሰሜን ኢትዮጵያ አርሶ አደሮችን አሰባጥሮ ለማዝመት የተደረገው ሙከራ ሲሆን፤ እቅዱ ሙሉ ለሙሉ ባይሰምርም 10 ሺህ የሚሆኑ የሰሜን ወሎ አርሶ አደሮችን አሰባስቦ ለማዝመት ተችሎ ነበር፡፡ ነገር ግን የህወሓትና የኢህአፓ የታጠቁ ሠራዊቶች "የኢትዮጵያ ህዝባዊ አብዮታዊ ሠራዊት" (ኢሕአሠ) በሰነዘረባቸው ወታደራዊና ፕሮፓጋንዳዊ ጥቃት ተዋክበው እንኳን ኤርትራ ሊደርሱ የትግራይንም ግዛት ማለፍ ሳይችሉ ድስ ሆነው ተበታትነዋል፡፡ ገበሬዎችን ማዝመት ግድ የሆነው ዋናው ጦር ለምስራቁ ግንባር ያስፈልግ ስለነበር ነው፡፡ ሁለተኛው ጠንካራ ዘመቻ ደግሞ በ1970 ዓ.ም ክረምት ላይ ስምንት ግብረኃይሎች ተዋቅረው እንዲዘምቱ የተደረገበት እርምጃ ሲሆን፤ በዚህ ዘመቻ የደርግ ሠራዊት ጀብሃና ሻዕቢያ ቀደም ብለው የተቆጣጠሩዋቸውን የኤርትራ ዋና ዋና ግዛቶች ለቀው እንዲሸሹ ያደረጋቸው ሆኖ ነበር፡፡

በዚህ ጥቃት ሻዕቢያ አስተማማኝ ዳጀኑ ወደሆነው የተራጥሮ ምሽጉ ወደ ናቅፋ እንዲያፈገፍግ ተገዷል፡፡ ያም ቢሆን የሻዕቢያ አስጊነት ቀጣይ ሆኖ በመገኘቱ ሦስተኛና የመጨረሻ የሆነ መጠነ ሰፊ ዘመቻ በሻዕቢያ ላይ መደረግ ነበረበትና "የቀይ ኮከብ ዘመቻ" ታወጀ፡፡ የዚህ ዘመቻ ዓላማ በየእለቱ እየተጠናከረና በመሐልም ጀብሃን አስወግዶ ትጥቅና የሰው ኃይሉን በምርኮም፣ በእርዳታም አጎልብቶ፤ ሲችል ፊት ለፊት የሚዋጋውን፤ ሳይችል በየከተሞች ላይ ልዩ ልዩ የመሠረተ ልማት አውታሮችን በፈንጅ እየደረመሰ፣ የመንግስት ተቋማትን እያጋዩ፣ የህዝብ መገልገያዎችን እያወደመ፣ ባለስልጣናትን በሠርጎ ገብ ኃይሎች እያፈነ ወደ በረሃ የሚወስደውን ሻዕቢያን ለመጨረሻ ጊዜ መደምሰስ ነው፡፡

የጦር መሣሪያ በገፍ ተገዝቷል፡፡ ለአዲስ ምልምል ሠራዊት ... ወዘተ ... እያለ ቀጥሎ ለአጠቃላይ የቀይ ኮከብ ዘመቻ ብቻ ከ5 ቢሊዮን በላይ የሚገመት ብር ወጪ ተደርጓል፡፡ ይህም ከፊሉ ለልማት ከፊሉ ለጦርነት መሆኑ ነው፡፡ በዚህ መልኩ የኢትዮጵያውያን ዓይንና ጆሮ ብቻ ሳይሆን ሁሉ ነገራቸው ኤርትራ ላይ ሆነ፡፡

በታቀደው መሠረትም በጦርነት የወደሙ ፋብሪካዎች፣ የመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ ት/ቤቶች፣ የጤና ተቋሞች፣ መንገዶች፣ ባንክ፣ ውሃና መብራት ... የፈረሱት ተጠግነው ያልነበሩት ተሰርተው •እንቅስቃሴ ጀመሩ፡፡ ሠርቶ አደሩ፣ ላብ አደሩ ወደየስራ መስኩ እንዲመለስ ተደረገ፡፡ ተማሪው ትምህርቱን ቀጠለ፡፡ በሽተኛው ህክምና ማግኘት ጀመረ፡፡

አያሌ ገንዘብ የወጣበት ፌስቲባልና ባዛር በምፅዋ ሠሜናዊ ድንበር "ጉርጉሱም" በተባለ ሥፍራ ተዘጋጅቶ በጓድ ሊቀመንበሩ ተመርቆ ተከፈተ ... በጦርነት የደቀቀችው ከተማ ነብስ ዘራች...፡፡

ጥር 17 ቀን 1974 ዓ.ም ሊቀመንበር መንግስቱ "…. የኤርትራ ህዝብ ሆይ! ልብ ብለህ ስማኝ ... አባቶች፣ እናቶች፣ እህቶች፣ ወንድሞች ... ስል የለበጣ አይደለም፡፡ የፖለቲካ ወይም የዲፕሎማሲ ቋንቋ አይደለም ከሐቅ ነው! ከአንጀት ነው!... የጋራ ችግራችንን፣ የጋራ ስቃያችንን ልናስወግድ፤ ወይም መፍትሄ ልንፈልግ ተሰብስበን እንደሆነ በግልፅና በሐቅ እንነጋገር ..."

"…. ቀደምት አባቶቻችን ስልጣኔን ለዓለም አሻግረው የሰጡበት ድንበር፣ በጠላት ላለማስነጠቅ የከፈሉት መስዋዕትነት፣ ጠብቀው አቆይተው ያስረከቡንን አደራ፣ በጀግንነት የተዋደቁላትንም ምድር ..." እያሉ ተርከው የአሉላ አባ ነጋን ጀብዱ እያስታወሱ ወደ አብዮቱ ዘመን መጥተው የቀይ ኮከብ ዘመቻን ዓላማና ግብ፤ እንዲሁም ቀጣይ ሂደቱን የሚመለከት ሰፊ ገለፃ አድርገው የዘመቻውን ጉባዔ ከፈቱ፡፡ ሊቀመንበሩን ተከትለውም የኢትዮጵያን ህዝብ የሚወክሉ የተባሉ ታላላቅ ሰዎች፣ የሃይማኖት መሪዎች፣ ባለስልጣናት ... ተመሣሣይ ልብ የሚነካ ንግግር አደረጉ፡፡ የኤርትራ ህዝብም የመኖር ተስፋ ጭላንጭል በማየቱ ተደሰተ፡፡

ጉባዔው በዚህ ሁኔታ ተከፍቶ ሲሰነብትም አጠቃላይ አፈፃፀሙ በሁሉም ገጽታው ታሪካዊ እንዲሆንና የታሪክ አሻራም ትቶ እንዲያልፍ፤ ታሪኩ ለትውልድ ተከትቦ ይቆይና ይተላለፍም ዘንድ ልዩ ዝግጅቱ ተጠናቆ ጋዜጠኞች፣ የኪነጥበብ ሰዎች፣ ደራሲያን፣ የታሪክ ምሁሮች፣ ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናትና የአገር ሽማግሌዎች ታድመው ጉባኤውን አድምቀዋል፡፡ እንጋፋው ደራሲና ጋዜጠኛ፣ በዓሉ ግርማ አንዱ ነበር፡፡ ያያቸውን ሚስጥሮች ሁሉ በኦሮማይና በቀይ ኮከብ ዘመቻ መጽሐፉ ተርኮታል፡፡ በዓሉ ግርማ በወቅቱ አጠቃላይ ሁኔታውን አይቶ ዘገባውን እንዲያቀርብ በመንግስት ታዞ ነበር የሄደው፡፡ ይህ ታላቅ ብዕረኛ



ያያትን ሁሉ ሲፅፍ በሳንሱር እንደሚወድቅ ቢረዳም እውነታውን ከመፃፍ ወደ ኋላ አላለም፡፡ በመጨረሻ ለፕሮፓጋንዳ ይረዳል ተብሎ የታሰበውን ዘገባ ሲያቀርብ ጽሁፉን ሳንሱር የሚያደርጉ የበላይ አለቆቹ ተቀብለው "እገሌ ይየው" እገሌ ይየው እየተባባሉ ሲዘባቱና ከተለመደው መንግስታዊ አዘጋገብ የተለዩ አይሆንም ብለው በመዘናጋታቸው ጭምር ትኩረት ስላልሰጡት በደንብ ሳይፈተሽ ሄዶ ሄዶ ለህትመት በቃ፡፡ ወይም ባልታሰበ መንገድ ታትሞ ተሰራጨ፡፡ ይህ የፀሐፊው ጥፋት አይደለም፡፡ የፃፈውን ለበላዮቹ ገምጋሚዎች ሰጥቷል፡፡ ገምግሞ መጣልም ሆነ ለህትመት እንዲበቃ መፍቀድ ያለባቸው እነሱ ነበሩ፡፡ ሳይሆን ቀርቶ አምልጦ ታተመ፡፡ "ኦሮማይ" ማለት አበቃለት ማለት ነው፡፡ ደራሲው ባለስልጣናቱን እየጠቀሰ ያየውን ሁሉ አጋለጠ፡፡ ገመናቸውን ያዩ ደነገጡ፡፡ በተለይ ደህንነቱን አፍረጥርጦታል፡፡ እናም ገደሉት....፡፡

ሁሉም ለዘላቂ ውጤት ጓጉቷል፡፡ በተቃራኒውም ዘመቻውን ለማክሸፍ የሚያስችል መረጃ ለጠላት አሳልፎ ለመስጠት ቀብድ የተቀበሉ ጉቦኛ የኢትዮጵያ ልጆች (የጦር አዛዦች) አብረው ነበሩ፡፡ የሻዕቢያ ደጋፊ የሆኑ የውጪ ኃይሎች "ኢትዮጵያ በሻዕቢያ ላይ የመርዝ ጋዝ ልትጠቀም ስለሆነ የመርዝ ጋዝ መከላከያ ጭንብል ለሻዕቢያ እንስጣለን" እያሉ የሐሰት ወሬ ይነዙ ጀመር፡፡

በጉባኤው ላይ "የአስመራ ማኑፌስቶ" ተብሎ የተሰየመው የአቋም መግለጫ የሁሉም ክፍላተ አገር ተወካዮችና በአካባቢው የሚኖሩ የኩናማ፣ የቤኒአመር፣ የአፋርና የሌሎች ብሔረሰብ ተወካዮች በተገኙበት ይፋ ሲደረግም ሁሉንም ያስደሰተ በመሆኑ ተቀባይነቱ አላጠያየቀም፡፡ በጥቅሉ በዘመቻው ጉባዔ ላይ የተነገሩት ንግግሮችና በተግባር የተጀመሩት ስራዎች መላውን የኤርትራ ህዝብ ያጓጓ ሲሆን፤ በተቃራኒው ሻዕቢያ በድንጋጤ የራደበት ክንውን ነበር፡፡

ከጉባኤው በኋላ በሊቀመንበር መንግስቱ ሰብሳቢነት የተነደፈው የወታደራዊ ዘመቻ እቅድ ላይ የክለሳ ውይይት ተካሄደ፡፡ የውይይቱ ዓላማ የአዛዦቹ ቅድመ ዝግጅት ምን እንደሚመስል የሚገልፅ ሪፖርት ማሰማት ነበር፡፡ በጠላት ላይ ጥቃት እንዲሰነዝሩ፣ ደጀን ሆነው እንዲጠብቁና ቁልፍ ቦታዎችን ይዘው እንዲቆዩ ግዳጅ የተሰጣቸው ዕዞችና ክፍለጦሮች ዝግጅታቸውን አጠናቀው በተጠንቀቅ ላይ መሆናቸውን ገለፁ፡፡ ቀድሞ በግብረ ኃይል ተዋቅሮ የነበረው ወደ ዕዝ ተለውጦ ነበርና፤ ውቃው ዕዝ፣ ናደው ዕዝ፣ መብረቅ ዕዝ፣ መከት ዕዝ፣ የሚል ስያሜ ተሰጥቷቸዋል፡፡ እያንዳንዱ ዕዝ በውስጡ በርካታና የተለያዩ ክፍለጦሮችን ያካተተ ሆኖ የተዋቀረ ነው፡፡

በዚህ መሰረት 1. በብርጋዴል ጄኔራል አበራ አበበ የሚታዘዘው ውቃው ዕዝ በአልጌና ግንባር ከቀይ ባህር በኩል በናቅፋ ጀርባ

እንዲያጠቃ፣ 2. ብብርጋዴል ጀኔራል ውበቱ ፀጋዬ የሚታዘዘው ናደው ዕዝ ከከረን ናቅፋ በር በከርከበት ግንባር ከናቅፋ ደቡባዊ ምስራቅ በኩል እንዲያጠቃ፣ 3. በብርጋዴል ጀኔራል ቁምላቸው ደጀኔ የሚታዘዘው መብረቅ ዕዝ ከቃሮራ ናቅፋ በር ግንባር ማለትም ከናቅፋ ሰሜናዊ ምዕራብ በኩል እንዲያጠቃና የሻዕቢያን መውጫ እንዲዘጋ፣ 4. በብርጋዴል ጀኔራል ከበደ ጋሼ የሚታዘዘው መከት ዕዝ የአስመራን ዙሪያ እንዲይጥር፣ 5. የሰሜን ዕዝ ልዩ ልዩ ክፍል የአስመራ ከተማን የውስጥ ጥበቃ እንዲያከናውን የሚል የዘመቻ ትዕዛዝ ተቀብለው ተዘጋጅተዋል፡፡ ከአንድ እስከ ሦስት ያሉት የዘመቻ እቅዶች ግባቸው የናቅፋ ከተማ ናት፡፡

አዛዦቹ ሪፖርታቸውን ሲያሰሙ "ጓድ ሊቀመንበር ዘመቻው ሙሉ በሙሉ ይሳካል፤ ሁሉንም ነገር ለእኛ ይተውት፤ እያሰቡ" የሚሉት ቢበረክቱም፣ ጀኔራል አበራ አበበ ግን በተለይ በመብረቅ ዕዝ ስር ያለውን 21ኛ ተራራ ክፍለ ጦር በሚመለከት፤ "ከተቋቋመ አንድ ዓመት ያልሞላው፣ ምንም የውጊያ ልምድ የሌለው፣ ከአጋዴን ኤርትራ ከገባ ወር ያልሆነው፣ ከኤርትራ መሬትና ከሻዕቢያ የውጊያ ስልት ጋር ትውውቅ ያላደረገ አዲስ ጦር ነው፡፡ ተራራ ክፍለ ጦር ስለተባለ ብቻ ተዓምር ሊሰራ አይችልም፡፡ ተጨማሪ የልምምድ ጊዜ ተሰጥቶት መለማመድ አለበት፡፡ አልጌና ግንባር ያለው ጦርም ቢሆን ለኃይል ማሟያ የተሰጡን አዳዲስ ጦር ስላሉን ተጨማሪ የልምምድ ጊዜ ተሰጥቶን ከታንከኛና ከመድፈኛ ጋር የንብረት ውጊያ መለማመድ አለብን፡፡ የጦሩ መንፈስ ዝግጁነት በቂ ስላልሆነ ውጊያ ለመጀመር ባንቸኩል ጥሩ ነው" የሚል ሀሳብ አቀረቡ፡፡ መንግስቱ የጀኔራል አበራን ሀሳብ "አልቀበልም" ብለው ዘመቻው በቀጥታ እንዲጀመር አዘዙ፡፡ የካቲት 8 ቀን 1974 ዓ.ም ሲነጋጋ ሲል በሁሉም ግንባር ወደ ናቅፋ የመጠጋት እንቅስቃሴ ተጀመረ፡፡ የናቅፋ ተራሮች በቢ.ኤም.ሮኬት፣ በመድፍ፣ በሞርታር፣ ከሰማይ በሄሊኮፕተርና በጀት በሚወነጨፉ ከባባድ ተኩሶች ተንቀጠቀጠች፡፡ አካባቢው እሳት ለበሰ፡፡

ሻዕቢያ ያለ የሌለ ኃይሉን ተጠቅሞ ተከላከለ፤ ግን አልቻለምና ናቅፋን ለቆ ሊወጣ ዝግጅት ጀመረ፡፡ ሆኖም ሁሉም መንገድ ታጠረበት፡፡ እዚያው በተከበበበት ሆኖ ማለቅ የመጨረሻው ምርጫ ሆኖበት በእለታማው ተራራ ተለጥፎ መጨፍጨፍ ዕጣው ሆነ፡፡

በሰሜን ምዕራብ በኩል የተንቀሳቀሰው መብረቅ ዕዝ ለወሣኝ ድል ተስፋ የተጣለበት ሲሆን፤ እንዲያጠቃ የተሰጠው ቀጠና ለእግረኛና ለሜካናይዝድ ጦር ውጊያ አመቺ በመሆኑ ግራ ቀኝ ያሉ ተራሮችን አስለቅቆ ከተቆጣጠረና በጠላት ላይ ተፅዕኖ ካደረሰ በኋላ ቀጣዩን ግዳጅ እንዲወጣ ለተመደበው የእግረኛና የሜካናይዝድ ጦር መክፈት ነበረበት፡፡



ይህ ከሆነ ብቻ ነበር ሙሉ ድል ሊገኝ የሚችለው፡፡ ለዚህም ተብሎ እጅ አስፈላጊው የሰው ኃይልና ትጥቅ በበቂ ሁኔታ ነበረው፡፡ ሆኖም ዛሬም ድረስ ባልታወቀ ምክንያት ዕዙ በተሰጠው ትክክለኛ ሰዓት መንቀሳቀስ ባለመቻሉ ጠላት ክፉቅ ያሉትን የሰው ኃይሎች አሰባስቦ እንዲጠናከር ጊዜ ሰጠው፡፡ በዚህች በተፈጠረች የጊዜ ክፍተት ሻዕቢያን ለማገዝ ክፉቅ ቦታ ተነስቶ ተጉዞ የመጣው አንድ ሙሉ የወያኔ ብርጌድ ደረሰለት፡፡የዚህ የወያኔ በርጌድ መሪ አርከበ ዕቁባይ እንደነበሩ በርካቶች ፅፈዋል፡፡በዚህም ሻዕቢያ ነብስ ዘራ፡፡

በመብረቅ ዕዝ ስር ያለውና ግንባር ቀደም የማጥቃት እርምጃ እንዲወስድ ግዳጅ የተሰጠው 21ኛው ተራራ ክፍለ ጦር እንኳን ተራሮችን አስለቅቆ ሊይዝ ቀርቶ፤ ሰብሮ ሊወጣ ባልቻለው የጠላት ቀለበት ውስጥ ገብቶ ተጨፈጨፈ፡፡ ሻዕቢያና ወያኔ በምርኮ ተንበሸበሹ፡፡ ጥቂቶች ብቻ አፈግፍገው ማምለጥ ቻሉ፡፡ ይህ የጦር ክፍል ለምን በተሰጠው ሰዓት እንዳልተንቀሳቀሰ የተለያዩ አስተያየቶች ዛሬም ድረስ ቢነሱም የብዙሃኑ የቀድሞ አዛዦች መንግስቱን ጨምሮ "ሆን ተብሎ የተደረገ ነው" የሚል ነው፡፡ ተራ ወታደሮችም ከዚያ ግንባር ተርፈው የመጡና ዛሬ ድረስ በህይወት ያሉት "መንቀሳቀስ በነበረብን ሰዓት ለመነሳት ዝግጅት እንደጀመርን ሆን ተብሎ አንዳንድ ዝግጅቶች፣ ልምምዶች እንድናደርግ ተደረገ" የሚሉ ናቸው፡፡ ከዚህ ባለፈ ደግሞ 4 ነገሮች ይጠቀሳሉ፡፡ 1. መንግስቱ ለድል ቸኩለው የተሰጠውን አስተያየት ባለመቀበላቸው፣ 2. በመንግስቱ ላይ ቂም የነበረባቸው አዝማቾች በመኖራቸው፣ 3. መብረቅ ዕዝ ሰዓት አለማክበሩ፣ 4. የወያኔ ጦር ለሻዕቢያ ገስግሶ መድረሱ የሚሉ ናቸው፡፡ ብቻ እንደማይሆን ሆነ፡፡

ከዚህ በኋላ ነገሩ ሁሉ ተበላሽቷልና ከአልጌና በኩል የተነሳው ውቃው ዕዝ በከፍተኛ መስዋዕትነት ከናቅፋ እስከ ሱዳን ጠረፍ የሚደርሰውን ካታር የተባለ ሰንሰለታማ ተራራ ጥግ ደርሶ ለመቆም ተገደደ፡፡ ከከርከበት በኩል እንዲያጠቃ የታዘዘው ናደው ዕዝ በውጤታማ ውጊያ ተጉዞ የናቅፋ ከተማን ለመያዝ 8 ኪሎ ሜትር እንደቀረው መግፋት ተስኖት ቆመ፡፡ያ ሁሉ የእግር ሐብት፣ ያ ሁሉ ጥሪት፣ ያ ሁሉ ወጣት ዜጋ ወደ ትቢያነት ተለወጠ፡፡የቀይ ኮከብ ዘመቻ ትርፉ ኪሳራ ሆነ፡፡ "እሮማይ" እንደማለት፡፡ ደራሲው ከውጊያው በፊት በብዕሩ ያሰፈረው ጽሁፍ በጦር ሜዳ ላይ ሲተገበር ታዬ፡፡

በወቅቱ ድልን የጠበቀ ዜጋ ሁሉ አንገቱን ደፋ፤ "እንዴት ሊሆን ቻለ?" ብሎ ያልጠየቀ ዜጋ የለም፡፡ ለውድቀት ምክንያት የሆነው ክስተት እንዲጣራና በዘመቻ ጽ/ቤቱ መምሪያ ተጠንቶ የውሣኔ ሀሳብ እንዲቀርብ ጓድ ሊቀመንበር አዘዙ፡፡ አጣሪ ቡድኑ ለውድቀት ምክንያት ያላቸውን ዘገባዎች አቀረበ፡፡ ዘገባውን ተመርኩዞ የተቋቋመው የጦር ፍርድ ቤት

ባሳለፈው ውሣኔ መሰረትም የመብረቅ ዕዝ አዛዥ ብርጋዴል ጄኔራል ቁምላቸው ደጀኔ ላይ የእስር ቅጣት፣ የ21ኛው ተራራ ክፍለ ጦር አዛዥ ኮሎኔል ውብሸት ማሞ የሞት ቅጣት፣ የክፍለ ጦሩ 47ኛው ብርጌድ አዛዥ ሌተናል ኮሎኔል ስለሺ አስፋው ማዕረጋቸው ተገፎ እንዲታሰሩ ሲል ብይን ሰጠ፡፡ ኮሎኔል ውብሸትን በሠራዊቱ ፊት ወስደው ረሸኗቸው፡፡ በጄኔራል ቁምላቸው ላይ መንግስቱ ያሳዩት ርህራሄ ብዙዎችን አስገረመ፡፡

በዚህ ሽንፈት ሊቀመንበሩ ምን ያህል እንደተበሳጩ ማሰብ አይከብድም፡፡ ባየነው መልኩ ቀይ ኮከብ በጥቁር ደመና ተዳፍኖ እንዳለ ዕዞች ይዞታቸውን አጠናክረው ባሉበት ሆነው እንዲደራጁ ተደረገና በተከታታይ ቀይ ኮከብ ሁለት፣ ሦስት… አራት… እየተባለ በተለያዩ የዘመቻ ስያሜዎች የሻዕቢያን ጉዳይ ዳር ለማድረስ በእጅጉ ተሞከረ፡፡ በከባድ ትንቅንቅ አንዴ ሲያስለቅቁ፣ መልሰው ሲለቁ፣ ሲያጠቁ፣ ሲከላከሉ… ቆዩ፤ አልተቻለም፡፡ ለምን? የናቅፋ ተራሮች ለሻዕቢያ ምትክ የሌለው የተፈጥሮ ደጀን ስለሆኗቸው፡፡ እናም ከተጠቀሰው ቢሊዮን ገንዘብ ውስጥ ግማሹ አመድ ቢሆንም ከፊሉ ግን ለኤርትራ ህዝብ ልማት በመዋሉ እንደኪሳራ አይቆጠርም፡፡

የሰሜኑ ጦርነት ሲባል ከሻዕቢያ ጋር ብቻ እንዳልነበር ይታወቃል፡፡ ከሻዕቢያ በኋላ የተነሳው ህወሓት ሌላው የደርግ መንግስት ተቃዋሚ ሆኖ ነፍጥ ያነሳው ገና በማለዳ ነበር፡፡

በምዕራብ ትግራይ ሽሬ አውራጃ፣ ደደቢት በምትባል በረሃማ ቀበሌ የካቲት 11 ቀን 1967 ዓ.ም ጥቂት የዩንቨርስቲ ተማሪዎችና የአካባቢው መሪዎች "ሕወሓት" "ህዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ"ን መሠረቱ፡፡ ራሳቸውንም ዳግማዊ ወያኔ ሲሉ ሰየሙ፡፡ ህወሓት የሚለውን መጠሪያ ይፋ ከማድረጋቸው በፊትም በተለያዩ ምህፃረ ቃላቶች ይጠሩና ይታወቁ ነበር፡፡

በጃንሆይ ዘመን በተለያዩ የኢትዮጵያ ግዛቶች ላይ የገበሬዎች አመፅ ተቀጣጥሎ እንደነበር አይተናል፡፡ በወቅቱም የገበሬዎችን አመፅ በቀላሉ ማርገብ ተችሏል፡፡ ከእነዚህ ውስጥም የትግሬ ጠቅላይ ግዛት አንዱ ነበር፡፡

በአፄ ዮሐንስ 4ኛ የስልጣን ዘመን የኢትዮጵያ ማዕከል ሆና የቆየችው ትግራይና አካባቢዋ በ1882 ዓ.ም ንጉሠነገስቱ በጦርነት ላይ ከተሰውበት ጊዜ ጀምሮ፤ የትግራይ መሣፍንትና መኳንንት የሆኑት ሁሉ የቀደሞውን አይነት ክብርና ተሰሚነት ማግኘት አልቻሉም፡፡ ዳር አገር በመሆናቸውም የፖለቲካ ተሳትፏቸውና ተጠቃሚነታቸው የቀዘቀዘ ሆኖ ነበር፡፡ ያም ቢሆን ለኩርፊያና ለሸፍትነት የሚጋብዝ ባለመሆኑ ለረጅም ጊዜ በግዛቱ ላይ ሠላም ሰፍኖ ቆይቷል፡፡



ከኢጣሊያ ዳግም ወረራ በፊት ግን በመንግስትና በራያና አዘቦ ህዝብ መካከል የተፈጠረው አለመግባባት፣ እሱንም ተከትሎ የደረሰው ደም መቃባት ለአካባቢው ሠላም መደፍረስ የመጀመሪያው ሆኗል፡፡ ከንግስት ዘውዲቱ የግዛት ዘመን ጀምሮ ማዕከላዊ መንግስቱን ሲፈታተንና በየጊዜውም ከሚላክበት ጦር ጋር በሽፍትነት ይፋለም የነበረው የራያና አዘቦ ህዝብ ይህን ተግባሩን በቀጠለበት ሁኔታ የኢጣሊያ ወረራ ተከሰተ፡፡ በዚህም ማዕከላዊ መንግስቱን ለመበቀል ምቹ ሁኔታ ተፈጠረላቸው፡፡ከማይጨው ጦርነት ሸሽቶ ይመጣ በነበረው የኢትዮጵያ ጦር ላይ ያደረሱት ግፍም የሚረሳ አይደለም፡፡

ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ሙሉ ለሙሉ ለቃ ከወጣች በኋላም የጃንሆይ መንግስት እስኪደላደል ድረስ በነበረው የጊዜ ክፍተትና ጣሊያኖች ትተውት የሄዱትን መሣሪያ በገፍ ማግኘት ቀላል ስለነበር በነፃነት ማግስት የመጀመሪያውን የተደራጀ አመፅ ማካሄድ ቻሉ፡፡ ይህም በነፃነት ማግስት በትግሬ ጠቅላይ ግዛት የተቀሰቀሰው የመጀመሪያው የ"ወያኔ" አመፅ ነው፡፡

የራያና አዘቦ ህዝብ አመፁን የለኮሰውም እንደመጀመሪያ ተግባሩ በአፋሮች ላይ ከፍተኛ ዝርፊያ በመፈፀም ሲሆን፤ በዚህም የማዕከላዊ መንግስቱን የበቀል እርምጃ በራሱ ላይ አስከተለ፡፡ የመንግስት ማጥቃትና የአማፅያኑ የመከላከል ተግባር እየተጋጋለ ሄዶ በመጨረሻ አማፅያኑ ከመከላከል ወደማጥቃት አመሩ፡፡ ይህ ሁኔታ ከተራ የሽፍትነት አመፅ ወደ ፖለቲካዊ አመፅ ተሸጋገረ፡፡

አማፅያኑ የመጀመሪያ ድላቸውን ያገኙት ግንቦት 14 ቀን 1935 ዓ.ም በተንቤን አውራጃ "አዲ አቡን" በተባለ ስፍራ ነው፡፡ ከዚያም በተከታታይ መቀሌ አጠገብ የሚገኙትን ቅዊሓንና እንዳ እየሱስን በቁጥጥር ስር አዋሉ፡፡ በመጨረሻም የጠቅላይ ግዛቱን ዋና ከተማ መቀሌን ሙሉ ለሙሉ ያዟት፡፡

ለዚህ ድል የረዳቸው ዋና ምክንያት የህዝቡን ቅሬታ ዘውጋዊ ወይም ጎሳዊ ርዕዮት በመስጠት ማስተባበር የቻለው የብላታ ኀይለማርያም ረዳ አመራር ነው፡፡

የአመፁ ስፋት፣ ጥልቀትና እድገት መንግስትን ክፉኛ ስላስደነገጠው በአርበኝነቱ ዘመን በፈፀሙት ጀብድ ስመጥርነትን ያተረፉትን ራስ አበበ አረጋይን የጦር አዝማች አድርጎ ላከ፡፡ ከሁኔታው አስጊነት አንፃርም በወቅቱ በኢትዮጵያ ከነበሩ የእንግሊዝ ጦር ባለስልጣኖችን እርዳታ መጠየቅ አስፈልጎ ነበር፡፡ በእንግሊዝ ይሁንታም የጦር አውሮፕላኖች ማግኘት ተችሎ ቀዳማዊ ወያኔን በምድርና በአየር ውጊያ ማሸነፍ ተቻለ፡፡ መስከረም 25 ቀን 1936 ዓ.ም ሙሉ ለሙሉ ድል የሆነው የአማፅያኑ ጦር ተበታተነ፡፡

ቀዳማዊ ወያኔ ትግሉን የጀመረው ምስራቃዊ ትግራይን መነሻ በማድረግ ነበር፡፡ ዳግማዊ ወያኔ ደግሞ ከመረብ ወንዝ በስተደቡብ በሚገኘው በምዕራብ ትግራይ መነሻውን አድርጎ ከ31 ዓመታት በኋላ የአርነት ንቅናቄውን እንደዋዛ ጀምሮ እየተጠናከረ ቀጥሏል፡፡

የመጀመሪያው ወያኔ ርዕዮቱን ዘውጋዊ አድርጎ የተነሳ ሲሆን፣ ሁለተኛው ወያኔ ደግሞ ከኢትዮጵያ የተማሪዎች ንቅናቄ በወረሰውና "የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት እስከመገንጠል" በሚለው መርህ የሚመራ ነበር፡፡ቀዳማዊ ወያኔናዳግማዊ ወያኔ የሚመሳሰሉበት ሁኔታኖሮ ሳይሆን፣ህወሓት ለራሱ ፕሮፖጋንዳ ታሪካዊ መሰረት ለመስጠት የፈጠረው ነው፡፡

አካባቢው ዳር አገር በመሆኑ የተቃውሞ እንቅስቃሴ ለማድረግ ምቹ ቢሆንም፣ በአካባቢው ኅብረተሰብ ዘንድ ተቀባይነት ማግኘት የግድ ነበርና፣ ለዚህ የሚረዳ በቂ ምክንያት በጠቅላይ ግዛቱ ውስጥ መኖሩ ለዳግማዊ ወያኔ የበለጠ ምቹ ሁኔታ ፈጠረለት፡፡ ይህም ከ1950ዎቹ አጋማሽ አመታት ጀምሮ በግዛቱ ውስጥ የተከሰተው ተደጋጋሚ ድርቅና የኢኮኖሚ ችግር ነው፡፡ ከዚህም በላይ የቀድሞ ባለባት ሹማምንት የፖለቲካ ማዕከላዊነት በማጣታቸው ምክንያት ሲሰማቸው የቆየው ቁጭት ስለነበር፣ በጣት የሚቆጠሩ ግለሰቦች የመሰረቱትን የነፃነት ንቅናቄ በግዛቱ የሚኖረው ሁሉም ወገን የየራሱን መነሻ ምክንያት መሰረት በማድረግ ለመደገፍና ለማበረታታት ዝግጁ ነበር፡፡ ለዚህም ነው በተመሠረተ በአጭር ጊዜ ውስጥ በቂ የሚባል የሰው ኃይል፣ የስንቅና የትጥቅ አቅርቦቱ ሳይቸግረው ባለበት ፈጥኖ ተደራጅቶ የደርግ መንግስትን መፈታተን የቻለው፡፡

ህወሓት ይዞት የተነሳውን "የራስን ዕድል በራስ የመወሰን እስከመገንጠል" የሚለውን የሌኒን መርህ ግን ለትግራይ ህዝብ ከማስረዳት ይልቅ ከእሱ ቀድሞ የመገንጠል ዓላማ ይዞ ለተነሳው ለሻዕቢያ መግለፅ ይቀለው ነበር፡፡ ያደረገውም ያንን ነው፡፡ሆኖም ሻዕቢያ የትግራይን የመገንጠል ትግል የኔን ትግል ያዳክምብኛል በሚል የወያኔን የመገንጠል ዓላማ ማኑፌስቶ እንዲያሰወግድ አስገድዶታል፡፡

ለወያኔ የአካባቢውን ህዝብ ድጋፍ ለማግኘት የኢኮኖሚ ችግር ሰለባ መሆኑን መግለፅ ብቻውን በቂ ስለነበር የርዕዮት ትንተና ውስጥ መግባት አስፈላጊ አልነበረም፡፡ ለሻዕቢያ ግን ጠቃሚና አስፈላጊ መሆኑ አያጠያይቅም፡፡ስለዚህ የ"ገንጣይ" እና "አስገንጣይ" ጥምረት መስርቶ መደጋገፉ ለሁለቱ ቡድኖች ወሣኝ በመሆኑ፣ ከልዩነታቸው ይልቅ አንድነታቸው ጠንክሮ በመቀጠሉ በመጨረሻ የየግል ግቦቻቸውን ዳር ማድረስ ችለዋል፡፡



ደርግ ጊዜያዊ መንግስት በሆነ ማግስት የወሰዳቸው እርምጃዎች፣በተለይም የ60ዎቹ ግድያና ሌሎች በፍርደ ገምድልነት የተደረጉ ነገሮች መደራረባቸውም ለሽመቁ ተቃዋሚዎች ድጋፍና ትኩረት አስገኝቶላቸዋል፡፡የአገር ውስጥ ብቻም ሳይሆን የውጭ አገራት ድጋፍን በተከታታይ አመታት ሊያገኙ የቻሉት የደርግ አምባገነንነት በየጊዜው እየጎላ በመሄዱ ነው፡፡

ደርግ ለአብዮቱ ሲል የሚወስዳቸው ጥንቃቄ አልባ እርምጃዎች በአብዮቱ ደጋፊዎች ዘንድ ተወዳጅ ያደርገኛል ብሎ ሲያስብ ራሱን ለጠላት ፕሮፓጋንዳ መጠቀሚያ አድርጎ ማቅረቡን ለደቂቃ አስቦት አያውቅም፡፡

ህወሓት "ወያኔ" የሚለውን ወኔ ቀስቃሽ ስያሜ ይዞ የትጥቅ ትግል ሲጀምር ልክ እንደሻዕቢያ የመጀመሪያ ስራው ያደረገው በግዛቱ ውስጥ የበላይነቱን ማረጋገጥ ነበር፡፡ ስለዚህም በቅድሚያ ከሦስት ተቀናቃኝ ድረጅቶች ጋር መፋለም ነበረበት፡፡ በመጀመሪያ ከእሱ ቀድሞ የተደራጀውን "የትግራይ እርነት ግንባር"ን ማስወገድ ቻለ፡፡ ይህን ግንባር ለማስወገድ ብዙ ድካም አልነበረውም፡፡ ሁለተኛውን "የኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ኅብረት" በእንግሊዝኛ ምህፃረ ቃሉ "ኢዲዩ"ን ግን ብርቱ የሆነ ውጊያና ከፍተኛ የህይወት መስዋዕትነት በመክፈል ነው መደምሰስ የቻለው፡፡

ኢዲዩን ከምዕራብ ትግራይ ጠራርጎ ካስወጣ በኋላ ቀጣዩን ፍልሚያ ያደረገው በሰሜን ምስራቅ ትግራይ አሲምባ በምትባለው ተራራማ ቦታ ከመሸገው ከኢህአፓ ሠራዊት ጋር ነበር፡፡ ኢህአፓ በከተማው ትግል ስኬታማ መሆን ሳይችል ሲቀር ወደ ገጠር አምርቶ አሲምባ ላይ ቢመሽግም ለአካባቢው እንግዳ ነው፡፡ ኢህአፓ አሲምባን የመረጠው በሁለት ምክንያቶች ሲሆን፣ አንዱ ከመንግስት ጥቃት ለመሸሽ፣ ሌላው በትግራይ ያለው ሸማቂ ቡድን የኅብረብሔራዊነት ዓላማ ካለው አብሮ ለመቀናጀትና ለመታገል ነው፡፡

ህወኀትም ኢህአፓም ግራ ዘመም ከሆነው ከኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ አብራክ የወጡ ድርጅቶች ይሁኑ እንጂ፣ ዓላማና ግባቸው እጅግ የተራራቀ ነው፡፡ ከዚህም በላይ ገሃድ በሆነው ትግላቸው ውስጥ ስውር የሆነ የየግል ዓላማ ነበራቸው፡፡

የትግሉን ይዘት በሚመለከት ኢህአፓ "በኅብረብሔራዊ ድርጅት የሚመራ የመደብ ትግል"ን በቀዳሚነትና በአፅንኦት ሲያስቀምጥ፣ ሕውሓት ግን "ትግሉ ሊሰምር የሚችለው የተለያዩ ጭቁን ብሔር ብሔረሰቦች በራሳቸው ድርጅት አማካኝነት ትግላቸውን ጀምረው ከዚያ በኋላ የኅብረት ግንባር ሲፈጥሩ ነው" የሚል አቋም ያዘ፡፡ ከዚህ ልዩነት በተጨማሪም ሕወሓት ሙሉ እምነቱን በገጠር የትጥቅ ትግል ላይ

ሲያሳርፍ፤ ኢህአፓ ደግሞ ተቀባይነት አግኝቶ የነበረው በከተማ ነው ብሎ ስላሰበ በከተማ የትጥቅ ትግል ላይ እምነቱን አሳድሯል፡፡በተጨማሪም ኢህአፓ እንደ ነጭ ማርክሲስትነቱ አርሶአደሩ አብዮታዊ ሀይል አይደለም ሳብ አደሩ እንጅ ብሎ በማመኑ ነበር፡፡ ከሁሉም በላይ ግን (የሻዕቢያን ከጀርባ ሆኖ በሰርጎ ገቦቹ አማካኝነት ኢህአፓን መጠቀሚያ ማድረጉን ሳንዘነጋ) ዋናው ልዩነታቸው በህወሓት ውስጥ የነበረው የመገንጠሉ መሻትና "በኢህአፓ ውስጥ የነበረው መገንጠልን ያለመሻት የፀባቸው መንስዔ ነው፡፡

በዚህ ልዩነት ሕወሓት የኢህአፓን አባላት ቢቻል በእሱ አቋም እንዲስማሙ አድርጎ ማሳመንና መቀላቀል፣ ካልተቻለ ያመኑለትን መርጦ ወስዶ የቀሩትን መደምሰስ፣ ካልሆነም ከአካባቢው ማባረር ነበረበት፡፡ ያደረገውም ይሄንኑ ነው፡፡

በዚህ መሠረት ገሚሱ የኢህአፓ አባላት ተደመሰሰ፡፡ጥቂቶቹ ተባባሪ ሆነው ተቀላቀሉ፡፡ የቀሩት ጓዛቸውን ጠቅልለው ወደ ጎንደርና ወደ ወሎ አፈገፈጉ፡፡ አንዳንዶቹም የከተማ ሸብራቸውን ቀጠሉ፣ሌሎችም ለደርግ እጃቸውን ሰጥተው ከደርግ ጋር መስራት ጀመሩ፡፡ደርግም ምልስ የኢህአፓ አባላትን እጁን ዘርግቶ ተቀበላቸው፣የድርጅታቸውን ሚስጥር አወጡ፣በደርግ ተይዘው የሚታሰሩ አባላትን መርማሪ ሆነው እስኪሰሩ ድረስ ለደርግ ታማኝ ሆነው ዘለቁ፡፡ይህ በእንዲህ እንዳለም የየራሳቸውን ብሔር እንዲያደራጁ ወደየክልላቸው ቀድመው የተላኩ ምልምሎች የተገኙት በዚህ አጋጣሚ መሆኑ መዘንጋት የለበትም፡፡

በዚህ ዓይነት በትግራይ ግዛት ውስጥ ብቸኛው የትጥቅ ትግል አራማጅ ህወሀት ሆነ፡፡ እነዚህ ጅምር የነፃነት ንቅናቄዎችና የውስጥ ፍጭቶች ለሻዕቢያ ሠርግና ምላሹ ነበሩ፡፡ ኅብረብሔራዊነት፣ ብሔረተኝነት ወዘተ ... ለሻዕቢያ ምኑም አይደሉም፡፡ ብቻ ኢትዮጵያ ውስጥ ሽብሩም፣ ተቃውሞውም፣ ፍጅቱም ይፋፋምለት እንጂ ሌላው ሁሉ ነገር አያገባውምም፣ አይገባውምም፡፡ የእሱ ስራ በኢትዮጵያውያን የግራ ኃይሎች ውስጥ የራሱን ዓላማ ማስፈፀም የሚችልበት፣ የመገንጠል ግቡን የሚያፋጥኑለትን ልዑካን ማሰማራት ብቻ ነው፡፡ ለዚህም ምቹ ሆኖ ያገኘው ከሕወሓት ይልቅ ኢህአፓን ነበር፡፡

መጀመሪያ ላይ ደርግ ሕወሓትን ከመጤፍ አልቆጠረውም ነበር፡፡ ለድርጅቱ መፈጠር ምክንያት የሆኑ ሁኔታዎችን ትኩረት በመንፈግ አንድ የሻዕቢያ ተቀፅላ ቡድን አድርጎ ነበር የወሰደው፡፡ ስለዚህም ደርግ ሙሉ ኃይሉን ያዘመተበት ሻዕቢያ ከተመታ ሕወሓትም አብሮ ይከስማል ብሎ ጥርጣሬ አልባ ግምት ውስጥ ገባ፡፡

ነገር ግን ሕውሓትና ሻዕቢያ አንድ አልነበሩም፡፡ አንድነታቸው ሰፊ፣ ልዩነታቸው ጠባብ የሆኑ የተነጣጠሉ ቡድኖች ናቸው፡፡ ይልቁንም



ሻዕቢያ መጀመሪያ ላይ ከሕወሓት ይልቅ ቀድሞ ወደጎለበተው ወደ ኢህአፓ ነበር ያተኮረውና በኅብረት ለማመፅ ሁኔታዎችን ያመቻቸው፡፡ ሆኖም ኢህአፓ ከትግራይ ተጠራርጎ ሲወጣ ፊቱን ወደ ሕወሓት አዞረ፡፡

ሕውሓት በመላ ትግራይ የበላይነቱን ካሰፈነ በኋላ የተመሠረተው ግንኙነትም የፍቅር ሳይሆን የጥቅም ብቻ ነበር፡፡ የኢጣሊያ ቅኝ አገዛዝ አንድ ህዝቦችን ለመከፋፈል ሲል ተክሎት በሄደው መርዛማ ችግኝ ምክንያት በሁለቱ የመረብ ወንዝ ተዋሳኝ ወንድማማች ህዝቦች መካከል ከመቃቃርም አልፎ በጣም በጥቂቱ መናናቅም ይታይ ነበር፡፡ ሆኖም ከጃንሆይ ዘመን ጀምሮ የተፈጠረው ውህደት ተለያይተውና ተቃቅረው የነበሩ ህዝቦችን አንድ አድርጎ ወደ ቀድሞው ፍቅራቸው መልሷቸው ነበር፡፡ በዚህ መሠረት በሁለቱ ህዝቦች መካከል አንዳች ልዩነት አለመኖሩን ስንረዳ፤ የሁለቱ ህዝቦች ተቆርቋሪ ሆነው የትጥቅ ትግል በጀመሩ የስልጣን ተፋላሚዎች ዘንድ ግን የተካረሩም ባይሆኑ ልዩነቶች አልጠፉም፡፡

ሕወሓት "ብሔር ብሔረሰቦች" ሲል ሻዕቢያ ግን በኤርትራ ትግል ውስጥ ብሔር ብሔረሰብ የሚባል አጀንዳ ፈፅሞ የለም ባይ ነበር፡፡ ሕወሓት ሶቭየት ኅብረት ለደርግ በምታደርገው እገዛ ምክንያት ጠንካራ ፀረ ሶቭየት አቋም ሲወስድ፤ ሻዕቢያ ግን ፀረ ሶቭየት አቋም አልያዘም፡፡

የሕወሓት የጦር ስልት በደፈጣ ውጊያ ላይ ሲያተኩር፤ ሻዕቢያ ግን መደበኛ ውጊያን መርጧል፡፡ በዚህም ሕወሓት ሻዕቢያን ተቻኩሎ ወደ መደበኛ ጦርነት በመግባቱ ክፉኛ ይተቸው ነበር፡፡ "ሳንደራጅ አታስጨርሰን፤ ተረጋጋ" መሆኑ ነው፡፡

እነዚህን በመሳሰሉ የሀሳብና የዘዴ ልዩነቶች ሲተቻቹ ከቆዩ በኋላ፣ የደርግ የማጥቃት እርምጃ እየጠነከረ ሲሄድና በተለይም ከቀይ ኮከብ ዘመቻው ከ1974 ጀምሮ በነበሩት ተከታታይ አመታት፤ የነበራቸውን ጥቃቅን ልዩነቶች ሁሉ እርግፍ አድርገው ትተው በጋራ ርብርብ፣ በጋራ ጠላታቸው በደርግ መንግስት ላይ ተነሱ፡፡ ውድቀቱን ለማፋጠንም በቁርጠኝነት ተፋለሙ፡፡

እነሱን ለማጥፋት ደርግ የወሰዳቸው ተደጋጋሚ እርምጃዎች ከሸፉበት፡፡ ቢቸግረው ለኤርትራና ለትግራይ የራስ ገዝ አስተዳደር ስልጣን ሊሰጥ ሞከረ፡፡ ይህን ግን የኃይል ሚዛኑ ወደነሱ ማዘንበሉን የተረዱት ሁለቱ ቡድኖች ሊቀበሉት አልፈቀዱም፡፡

ሻዕቢያና ሕወሓት ሲመች በጥምረት ሳይመች በተናጠል ደርግን በፅኑ ሲፋለሙ እነሱ ተሳዳጅ ደርግ አሳዳጅ ሆኖ የዘለቀው ለጥቂት ዓመታት ነው፤ እያደር ግን ደርግ ተሳዳጅ እነሱ አሳዳጅ ሆነው ተገኙ፡፡

ግራ የተጋባው ደርግ አብዮታዊ ሠራዊቱን እንደገና በአዲስ መልክ አደራጅቶ በአራት ዕዞችና በውስጡም የተለያዩ ኮሮችን አቅፎ የሚይዝ

ከማድረጉም በላይ "የሦስት ማዕዘን ዕዝ" በሚል 1ኛ አዛዥ፣ 2ኛ የፖለቲካ ኃላፊ፣ 3ኛ የወታደራዊ ደፀንነት ኃላፊ የሚባሉ ባለሥልጣኖችን በጦሩ ላይ ሹሞ ዝብርቅርቁን አወጣው፡፡

የዕዙ ማዕከል ዋና አዛዥ ቢሆንም የፖለቲካና የወታደራዊ ደህንነት ኃላፊዎች በዋና አዛዡ ስራ ላይ በቀጥታ ጣልቃ መግባት ይችላሉ፡፡ በተለይ የፖለቲካ ኃላፊው በአዛዡ ላይ ጣልቃ መግባት ብቻ ሳይሆን ትዕዛዙንም መሻር ይችላል፡፡ ይህ ያልተለመደ አደረጃጀት ሙያና ችሎታው ያለውን አዛዥ ሙያው የሌላቸው ኃለፊዎች ሊገድቡት እንዲችሉ ከማድረጉም በላይ፤ የእኔ እበልጥ እኔ እበልጥ ፉክክሩን ዋና ስራቸው አድርገው እንዲቀጥሉ በር ከፈተ፡፡ ሽንፈት ሲደርስም የሱ ችግር ነው፣ የእኔ አይደለም ተብሎ መጠቋቆም ሆነ፡፡ ሠራዊቱ ዋና አዛዡን ለይቶ ማወቅ ተሳነው፡፡

ይህ አይነቱ ከሶቭየት የተኮረጀ የቀዩ ጦር ስልት ዓላማው አፈንጋጭነት እንዳይፈጠርና በአንድ አዛዥ ክህደት ችግር እንዳይደርስ አጥብቆ ለመያዝ ነበር፡፡ ሆኖም በእኛ አገር ላይ ተግባራዊ ለማድረግ ብዙ ቅድመ ዝግጅቶች ይቀሩ ነበር፡፡ የታሰበው ሳይሆን ቀርቶ አደረጃጀቱ የጣት መቀሳሰሪያና የአጥፊና ጠፊ መድረክ ሆኖ ቁጭ አለ፡፡

ሻዕቢያን ከኤርትራ፣ ሕወሓትን ከትግራይ ለመደምሰስና ሙሉውን የኢትዮጵያ ድንበር ለማስከበር ይቻል ዘንድ ሠራዊቱ በሰው ኃይል ጠንክሮና በዕዝ ደረጃ ራሱን ችሎ እንዲደራጅ፣ ግዳጁን የመወጣት ብቃትም እንዲኖረው ታስቦ የተደራጀው አብዮታዊ ሠራዊት፤ 1. አንደኛው አብዮታዊ ሠራዊት በሜጀር ጄኔራል ደምሴ ቡልቶ አዛዥነት፣ የዕዝ ቀጠናው ምስራቅ ኢትዮጵያ ሆኖ የሰው ኃይሉ 30,498፣ 2. ሁለተኛው አብዮታዊ ሠራዊት በሜጀር ጄኔራል ረጋሳ ጅማ አዛዥነት የዕዝ ቀጠናው ኤርትራ ራስ ገዝ ሆኖ የሰው ኃይሉ 124,024፣ 3. ሦስተኛው አብዮታዊ ሠራዊት በሜጀር ጄኔራል ሙላቱ ነጋሽ አዛዥነት የዕዝ ቀጠናው ትግራይ፣ ጎንደርና ወሎ ሆኖ የሰው ኃይሉ 107,407፣ 4. አራተኛው አብዮታዊ ሠራዊት በሜጀር ጄኔራል ጌታቸው ሸበሺ አዛዥነት የዕዝ ቀጠናው ምዕራብና መሀል ኢትዮጵያ ሆኖ የሰው ኃይሉ 20,700 ተደርጎ፣ በስራቸው ልዩ ልዩ ኮሮችና ክፍለ ጦሮች አቅፈው ተደራጁ፡፡

ሦስተኛው አብዮታዊ ሠራዊት በጄኔራል ሙላቱ ነጋሽ ዋና አዛዥነት ከተቋቋመ በኋላ በትግራይ ላይ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ታወጀ፡፡ ሻምበል ለገሰ አስፋው የትግራይ ራስ ገዝ የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ አስተዳደር የበላይ አስተዳዳሪ ሆኖ ተሾመ፡፡ በአዋጁ አግባብነት በቀጥታ የሠራዊቱ የበላይ አዛዥ ሆነ ማለት ነው፡፡

ለገሠ አስፋው ተሹሞ ሄዶ መቀሌ እንደደረሰ በፍጥነት ሦስተኛውን አብዮታዊ ሠራዊት "በቁልፍ ወታደራዊ ቦታዎች ላይ ጠላት



ሠፍሯል፤ ሠራዊታችን፣ በሚገባ ተደራጅቷል፤ ስለዚህ ከየአቅጣጫው ተወርውሮ ይምታው!" ሲል አዘዘ፡፡

ሕወሓትም በበኩሉ፤ "ጦሩ ሲወረወር ተሰወር" የሚል ትዕዛዝ ሰጥቶ ስልታዊ ማፈገፈግ አደረገ፡፡ በዚህ አይነት የሚለቀቁ ቦታዎችን በተናጠል ክፍል እያስጠበቁ ሲገሰግሱ የሠራዊቱ ኃይል እያነሰ ቢበታተንም ድል ያልሆነ ድል መሰል ተግባር ሆኖ ሰፊ የፕሮፓጋንዳ ሽፋን ተሰጠው፡፡ ምርኮ ተብለው ጥቂት መሣሪያዎች በመገናኛ ብዙሃን ታዩ፡፡ ቀጣይነት ግን አልነበረውም፡፡ ይልቁንም በጄኔራሉና በሻምበሉ መካከል የነበረው የታዥነትና የአዛዥነት አለመጣጣም እየተካረረ ሄዶ በየጦር ግንባሩ የሚታየውን ችግር አስተውሎ የጋራ የመፍትሄ እርምጃ መውሰድ ተሳናቸው፡፡

ብዙም ሳይቆይ የቁርጡ ቀን ደረሰና በ1980 ዓ.ም ከህዳር 27 እስከ 30 ባሉት ሦስት ተከታታይ ቀናት ሻዕቢያ በሳህል አውራጃ ውስጥ በሚገኙ የናደው ዕዝ ክፍለ ጦሮች ላይ ጠንካራ በትሩን አሳረፈ፡፡ በ15ኛው ክፍለ ጦርና በ22ኛው ተራራ ክፍለ ጦር ላይ ያረፈው ምት ከቀይ ኮከብ ዘመቻ በኋላ የመጀመሪያው ከባድ ውጊያ ሆኖ "አፋቤት የተባለውን ቁልፍ ወታደሪዊ ቦታ ሻዕቢያ በቁጥጥሩ ስር አደረገው፡፡

በዚህ ወቅት የናደው ዕዝ አዛዥ ብርጋደር ጄኔራል ታሪኩ ዐይኔ ለአለቆቻቸው ሳያሳውቁ ሠራዊታቸውን ትተው አስመራ ከተማ ነበሩ፡፡

እኚህ ጄኔራል ወደ ሳህል ተመድበው ከመሄዳቸው በፊት መቀሌ አካባቢ ለሰፈረው ጦር አዛዥ ሆነው በ1970ዎቹ ይሰሩ ነበር፡፡ በዚያ ወቅት ወያኔ "ዘመቻ አግአዚ" (አግአዚ ኦፕሬሽን) ብሎ በሰየመው እስረኞችን የማስለቀቅ ድንገተኛ ወረራው ሲከሰት በወህኒ ቤቱ ዙሪያ የሚገኘው የጥበቃ ኃይል ከአቅም በላይ የሆነ ወረራ እንደመጣባቸው ገልፀው፤ እርዳታቸውን ሲጠይቁ ጄኔራሉ "የወህኒ ቤት ጠባቂ አይደለሁም" የሚል መልስ ሰጥተው በመቅረታቸው የወያኔ ኃይል ያለ ችግር ወህኒውን ጥሶ ገብቶ የራሱን ሰዎች ስም እየጠራ በ15 ደቂቃ ውስጥ ይዞ ሄዷል፡፡ (ነበር ቁጥር 2)

በተጨማሪም የሲቀመንበሩንም ሆነ የሌሎች አዛዦቻቸውን ትዕዛዝ "አላመንኩበትም" እያሉ ከመፈፀም ይቆጠቡ እንደነበርና በሁሉም ዘንድ ጥርስ ውስጥ የገቡ ጄኔራል መሆናቸው ይነገርላቸዋል፡፡ አሁን ደግሞ የአፋ ቤት ውድቀት የመጣው በጄኔራል ታሪኩ ዐይኔ ጥፋት ነው ተባለና ያለፍርድ ተረሸኑ፡፡ እንዲሁም ብ/ር/ጄ/ል ከበደ ጋሼ ድል ከሆኑ ሁለት ክፍለ ጦሮች ውስጥ አንዱን ይመሩ ስለነበር በጥፋተኝነት ሙሉ ማዕረጋቸው እንዲገፈፍ ተደረገ፡፡ እንዲህ ያለው ተግባር በጦሩ ፊት በተግባር መፈፀሙ ደግሞ የጦሩን ስሜት የሚጎዳና ሞራሉንም የሚነካ መሆኑ አያጠያይቅም፡፡

በአፋቤት ጦርነት 20 ሺህ የደርግ ሠራዊት በአንድ ጊዜ ያለቀ ሲሆን፤ ስፍር ቁጥር የሌለው የጦር መሣሪያ በሻዕቢያ እጅ ገባ፡፡ ይህ ቦታ ለሻዕቢያ መጀመሪያ ወደ ምፅዋ፣ እንዲሁም ወደ አስመራ መረማመጃ ሆነው፡፡ በጦርነቱ የወደፊት አቅጣጫ ላይም ለሻዕቢያ ድል መፋጠን ትልቁን ሚና ተጫውቷል፡፡ በርካታ መኮንኖች በመማረካቸውም ሚስጥሩን ሁሉ፣ የሠራዊቱን አሠፋፈር ሳይቀር በቀላሉ ለመረዳት ለሻዕቢያ ጠቅሞታል፡፡

ሻዕቢያ እስከ መጋቢት ወር ድረስ አፋቤትን የማፅዳትና ሙሉ ለሙሉ የግሉ ለማድረግ በወሰደው ተከታታይ የማጥቃት እርምጃ ከነሙሉ የጦር ግምጃ ቤቷ ተረከባት፡፡ ዘጠኝ የሶቭየት የጦር አማካሪዎችን ጨምሮ ማረከ፣ የናደው ዕዝ በተጠቀሰው ወር ተናደ፡፡ የኢትዮጵያ መንግስት ኤርትራን ሊነጠቅ ምንም እንዳልቀረው እየተረዳ ነበር፡፡

በትግራይ ላይ የተሰማራው የሶስተኛው አብዮታዊ ሠራዊት 604ኛ ኮር የሕወሓትን ሰልታዊ ማፈግፈግ መነሻ አድርጎ ሲገሰግስና ቅጥ ባጣ ሁኔታ እየሳሳ ሲሄድ፤ በተናጠል ምት እየተደመሰሰ ራሱን መከላከል በማይችልበት ደረጃ ላይ ደረሰ፡፡

በየካቲት ወር 1981 ዓ.ም በሻዕቢያ ሜካናይዝድ ጦር ታግዞ በምዕራብ ትግራይ የምትገኘውን ሽሬ እንዳስላሴን በከፍተኛ መስዋዕትነት መቆጣጠር ቻለ፡፡ 40 ሺ ወታደር የያዘው 604ኛ ኮር ሙሉ ለሙሉ ተደመሰሰ፡፡ ሕወሓት የምስረታውን የልደት ቀንን ጠብቆ የካቲት 11 ያደረሰው የ18 ሰዓታት ጥቃት ሽሬን መቆጣጠር ሲያስችለው፤ ብርጋዴል ጄኔራል ክንፈና ብርጋጄል ጄኔራል ገሞራውን ጨምሮ በርካታ መኮንኖችን መማረክም ችሏል፡፡ በኢትዮጵያ ጦርነት ውስጥ ጄኔራል ሲማረክ ይህ የመጀመሪያው ነበር፡፡

የአፋ ቤት ድል ለሻዕቢያ ወሣኝ የድል ምዕራፍ እንደሆነው ሁሉ ለሕወሓትም የሽሬ ድል ተመሳሳይ ገፅታ ነበረው፡፡

ቀጥሎ ተመሳሳይ ሽንፈትና ኪሳራ እዳይደርስ በሚል ከየካቲት 18 ጀምሮ የደርግ ሰራዊት ያለውጊያ ከመቀሌ መውጣት ጀመረና ግማሹ ወደ አስመራ፣ ግማሹ ወደ ሰሜን ወሎ ጓዙን ጠቅልሎ እንዲሄድ ተደረገ፡፡ በሚስጥር የተከናወነው ሽሽት በ15 ቀናት ተጠናቆ የካቲት 22 ቀን 1981 ሙሉ ለሙሉ መቀሌ ተለቀቀች፡፡

የደርግ መንግስት ያለአንዳች ውጊያ ለሕወሓት የትግራይን ግዛት አስረከበ፡፡ የሚገርመው ቦታውን ለማስከበር ሰፍሮ የነበረው ጦር "ዘመቻ ቅጣው" በሚል ስያሜ የዘመተ መሆኑ ነው፡፡ ሳይቀጣም፣ ሳይቀጣም ሹልክ አለ፡፡

ከዚህ በኋላ ሕወሓት ትግራይን ደጀን አድርጎ ዘመቻውን ወደ መሐል አገር አስፋፋ፡፡ የትግራይ ወጣትም ወደ እነሱ ከቀድሞው የበለጠ



እየተቀላቀላቸው የሰው ኃይላቸውን አሳደጉ፡፡ ትግራይን ነፃ አወጣለሁ ብሎ የተነሳው ድርጅት አገር አቀፍ የሆነ ሌላ አጀንዳ ማውጣት ግድ ሆነበት፡፡

ከ"ኢሠፓአኮ" ወደ "ኢሠፓ"

የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር መንግስት ደርግ ከምስራቁና ከሰሜኑ ጦርነት ጎን ለጎን ስልጣኑ ሕጋዊ ከለላ ያለውና፤ በህዝብ ተሹሞ የተሰየመ መንግስት ሊያስመስለው የሚችል ተግባር ለመፈፀም ደፋ ቀና ይል ነበር፡፡

ይህም በየካቲት ወር 1972 ዓ.ም ተጀምሮ በ6 ወራት ውስጥ እንዲዋቀር የተደረገውን "የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ አደራጅ ኮሚሽን" (ኢሠፓአኮ)ን መመስረት ሲሆን፤ አደራጅ ኮሚሽኑ ከተዋቀረ በኋላ ደግሞ እምጦ የሚወልደው "የኢትዮጵያ ሠርቶ አደር ፓርቲ" (ኢሠፓ) የመጨረሻው አውራ ፓርቲ ይሆንና፤ የደርጉን ሊቀመንበር ሌተናል ኮሎኔል መንግስቱ ኃይለማርያምን ብቸኛ መሪ አድርጎ እስከፍፃሜው እንዲዘልቁ ማድረግ ዓላማና ግቡ ነው፡፡

ዓላማው ከግቡ ይደርስ ዘንድም ገና ከጅምሩ በጽኑ መሠረት ላይ መገንባት ነበረበትና የኮሚሽኑ ምስረታ አዋጅ ይፋ ከመደረጉ በፊት በክፍላተ አገራት፣ በአውራጃና በወረዳዎች ላይ ታማኝ ታማኝ የመንግስቱ ተጠሪዎች ከታህሳስ ወር ጀምሮ ቅድመ ስራቸውን እንዲያከናውኑ ተመደቡ፡፡

በየቦታው ቢሮዎችን ማዘጋጀት፣ ተገቢ ሰዎችን መመልመል፣ መሰናክል ሊሆኑ ይችላሉ የተባሉትን ማጥራት፣ የመንግስቱን መልካም ስብዕና ማንፀባረቅ... የሚሉት ከቅድመ ስራዎች ውስጥ ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

ከዚህ በኋላ በ"ኢማሌድኅ" ጥላ ስር ተሰባስበው ከነበሩ ድርጅቶች ውስጥ በአባልነት ይሳተፉ ከነበሩ ግለሰቦች ጀምሮ፤ የፖለቲካ ተሳትፎ እስከሌላቸው ግለሰቦች ድረስ፣ ምሁራን፣ የኪነጥበብ ሰዎች፣ ታዋቂ ግለሰቦች፣ የፈጠራ ባለቤቶች፣ አምባሳደሮች፣ ሚኒስትሮች፣ ከጦር ኃይሉም፣ ከፖሊስ ሠራዊትም ፣ጡረተኛ እርበኞችም ... ሳይቀሩ ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል በ ኢሠፓአኮ መስራች ጉባዔ ላይ እንዲሳተፉ ተደረገ፡፡

እነዚህ ከድፍን ኢትዮጵያ ተመርጠው በጉባዔው ለመገኘት የተጋበዙ ዜጎች ቁጥራቸው 2ሺ ሲሆን፤ በታላቁ ቤተመንግስት ጊቢ ውስጥ ባለው የምኒልክ አዳራሽ ጳጉሜ 1 ቀን 1972 ዓ.ም ከጠዋት ጀምረው በመስራች ጉባኤው ላይ በጋራ ተገኝተው ያዳራሹን ግድግዳና ኮርኒስ በጋለ ጭብጨባ ሲያናጉት ዋሉ፡፡

ጉባዔው በማግስቱም ቀጠለና 93 ቋሚ፣ 30 ተለዋጭ አባላት ያሉት ማዕከላዊ ኮሚቴውን ሰየመ፡፡ ከቋሚ የማዕከላዊ አባላት ውስጥ 60ዎቹ መለዮ ለባሾች (ፖሊስን ጨምሮ) እንዲሆኑ ሲደረግ፣ 33ቱ

በአፋቤት ጦርነት 20 ሺህ የደርግ ሠራዊት በአንድ ጊዜ ያለቀ ሲሆን፤ ሰፍር ቁጥር የሌለው የጦር መሣሪያ በሻዕቢያ እጅ ገባ፡፡ ይህ ቦታ ለሻዕቢያ መጀመሪያ ወደ ምፅዋ፣ እንዲሁም ወደ አስመራ መረማመጃ ሆነው፡፡ በጦርነቱ የወደፊት አቅጣጫ ላይም ለሻዕቢያ ድል መፋጠን ትልቁን ሚና ተጫውቷል፡፡ በርካታ መኮንኖች በመማረካቸውም ሚስጥሩን ሁሉ፤ የሠራዊቱን አሠፋፈር ሳይቀር በቀላሉ ለመረዳት ለሻዕቢያ ጠቅሞታል፡፡

ሻዕቢያ እስከ መጋቢት ወር ድረስ አፋቤትን የማፅዳትና ሙሉ ለሙሉ የግሉ ለማድረግ በወሰደው ተከታታይ የማጥቃት እርምጃ ከነሙሉ የጦር ግምጃ ቤቷ ተረከባት፡፡ ዘጠኝ የሶቭየት የጦር አማካሪዎችን ጨምሮ ማረከ፣ የናደው ዕዝ በተጠቀሰው ወር ተናደ፡፡ የኢትዮጵያ መንግስት ኤርትራን ሲነጠቅ ምንም እንዳልቀረው እየተረዳ ነበር፡፡

በትግራይ ላይ የተሰማራው የሶስተኛው አብዮታዊ ሠራዊት 604ኛ ኮር የሕወሓትን ስልታዊ ማፈግፈግ መነሻ አድርጎ ሲገሰግስና ቅጥ ባጣ ሁኔታ እየሳሳ ሲሄድ፤ በተናጠል ምት እየተደመሰሰ ራሱን መከላከል በማይችልበት ደረጃ ላይ ደረሰ፡፡

በየካቲት ወር 1981 ዓ.ም በሻዕቢያ ሜካናይዝድ ጦር ታግዞ በምዕራብ ትግራይ የምትገኘውን ሽሬ እንዳስላሴን በከፍተኛ መስዋዕትነት መቆጣጠር ቻለ፡፡ 40 ሺ ወታደር የያዘው 604ኛ ኮር ሙሉ ለሙሉ ተደመሰሰ፡፡ ሕወሓት የምስረታውን የልደት ቀንን ጠብቆ የካቲት 11 ያደረሰው የ18 ሰዓታት ጥቃት ሽሬን መቆጣጠር ሲያስችለው፤ ብርጋዴል ጄኔራል ከንፈና ብርጋጄል ጄኔራል ገሞራውን ጨምሮ በርካታ መኮንኖችን መማረክም ችሏል፡፡ በኢትዮጵያ ጦርነት ውስጥ ጄኔራል ሲማረክ ይህ የመጀመሪያው ነበር፡፡

የአፋ ቤት ድል ለሻዕቢያ ወሣኝ የድል ምዕራፍ እንደሆነው ሁሉ ለሕወሓትም የሽሬ ድል ተመሳሳይ ገፅታ ነበረው፡፡

ቀጥሎ ተመሳሳይ ሽንፈትና ኪሳራ እዳይደርስ በሚል ከየካቲት 18 ጀምሮ የደርግ ሰራዊት ያለውጊያ ከመቀሌ መውጣት ጀመረና ግማሹ ወደ አስመራ፣ ግማሹ ወደ ሰሜን ወሎ ኅዙን ጠቅልሎ እንዲሄድ ተደረገ፡፡ በሚስጥር የተከናወነው ሽሽት በ15 ቀናት ተጠናቆ የካቲት 22 ቀን 1981 ሙሉ ለሙሉ መቀሌ ተለቀቀች፡፡

የደርግ መንግስት ያለአንዳች ውጊያ ለሕወሓት የትግራይን ግዛት አስረከበ፡፡ የሚገርመው ቦታውን ለማስከበር ሰፍሮ የነበረው ጦር "ዘመቻ ቅጣው" በሚል ስያሜ የዘመተ መሆኑ ነው፡፡ ሳይቀጣም፣ ሳይቀጣም ሹልክ አለ፡፡

ከዚህ በኋላ ሕወሓት ትግራይን ደጀን አድርጎ ዘመቻውን ወደ መሐል አገር አስፋፋ፡፡ የትግራይ ወጣትም ወደ እነሱ ከቀድሞው የበለጠ



እየተቀላቀላቸው የሰው ኃይላቸውን አሳደጉ፡፡ ትግራይን ነፃ አወጣለሁ ብሎ የተነሳው ድርጅት አገር አቀፍ የሆነ ሌላ አጀንዳ ማውጣት ግድ ሆነበት፡፡

ከ"ኢሠፓአኮ" ወደ "ኢሠፓ"

የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር መንግስት ደርግ ከምስራቁና ከሰሜኑ ጦርነት ጎን ለጎን ስልጣኑ ሕጋዊ ከለላ ያለውና፤ በህዝብ ተሹሞ የተሰየመ መንግሰት ሊያስመስለው የሚችል ተግባር ለመፈፀም ደፋ ቀና ይል ነበር፡፡

ይህም በየካቲት ወር 1972 ዓ.ም ተጀምሮ በ6 ወራት ውስጥ እንዲዋቀር የተደረገውን "የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ አደራጅ ኮሚሽን" (ኢሠፓአኮ)ን መመስረት ሲሆን፤ አደራጅ ኮሚሽኑ ከተዋቀረ በኋላ ደግሞ እምጦ የሚወልደው "የኢትዮጵያ ሠርቶ አደር ፓርቲ" (ኢሠፓ) የመጨረሻው እውራ ፓርቲ ይሆንና፤ የደርጉን ሊቀመንበር ሌተናል ኮሎኔል መንግስቱ ኃይለማርያምን ብቸኛ መሪ አድርጎ እስከፍፃሜው እንዲዘልቁ ማድረግ ዓላማና ግቡ ነው፡፡

ዓላማው ከግቡ ይደርስ ዘንድም ገና ከጅምሩ በጽኑ መሠረት ላይ መገንባት ነበረበትና የኮሚሽኑ ምስረታ አዋጅ ይፋ ከመደረጉ በፊት በክፍላተ አገራት፣ በአውራጃና በወረዳዎች ላይ ታማኝ ታማኝ የመንግስቱ ተጠሪዎች ከታህሳስ ወር ጀምሮ ቅድመ ስራቸውን እንዲያከናውኑ ተመደቡ፡፡

በየቦታው ቢሮዎችን ማዘጋጀት፣ ተገቢ ሰዎችን መመልመል፣ መሰናክል ሊሆኑ ይችላሉ የተባሉትን ማጥራት፣ የመንግስቱን መልካም ስብዕና ማንፀባረቅ... የሚሉት ከቅድመ ስራዎች ውስጥ ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

ከዚህ በኋላ በ"ኢማሌድኅ" ጥላ ስር ተሰባስበው ከነበሩ ድርጅቶች ውስጥ በአባልነት ይሳተፉ ከነበሩ ግለሰቦች ጀምሮ፤ የፖለቲካ ተሳትፎ እስከሌላቸው ግለሰቦች ድረስ፣ ምሁራን፣ የኪነጥበብ ሰዎች፣ ታዋቂ ግለሰቦች፣ የፈጠራ ባለቤቶች፣ አምባሳደሮች፣ ሚኒስትሮች፣ ከጦር ኃይሉም፣ ከፖሊስ ሠራዊትም ፣ጡረተኛ አርበኞችም ... ሳይቀሩ ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል በ ኢሠፓአኮ መስራች ጉባዔ ላይ እንዲሳተፉ ተደረገ፡፡

እነዚህ ከድፍን ኢትዮጵያ ተመርጠው በጉባዔው ለመገኘት የተጋበዙ ዜጎች ቁጥራቸው 2ሺ ሲሆን፤ በታላቁ ቤተመንግስት ጊቢ ውስጥ ባለው የምኒልክ አዳራሽ ጳጉሜ 1 ቀን 1972 ዓ.ም ከጠዋት ጀምረው በመስራች ጉባኤው ላይ በጋራ ተገኝተው ያዳራሹን ግድግዳና ኮርኒስ በጋለ ጭብጨባ ሲያናጉት ዋሉ፡፡

ጉባዔው በማግስቱም ቀጠለና 93 ቋሚ፣ 30 ተለዋጭ አባላት ያሉት ማዕከላዊ ኮሚቴውን ሰየመ፡፡ ከቋሚ የማዕከላዊ አባላት ውስጥ 60ዎቹ መለዮ ለባሾች (ፖሊስን ጨምሮ) እንዲሆኑ ሲደረግ፣ 33ቱ

ሲቪሎች ነበሩ፡፡በዚህም የአማን አንዶምን የመጀመሪያ ዕቅድ ደርግ በመጨረሻ በከፊል መተግበሩን እንረዳለን፡፡

ከተለዋጭ አባላቱ ውስጥ ደግሞ 21ዱ መለዮ ለባሽ፣ 9ኙ ሲቪሎች ናቸው፡፡ በተለዋጮቹ ውስጥ 2ቱ፣ በቋሚዎቹ ውስጥ 26ቱ የደርግ አባላት እንዲሆኑ ተደረገ፡፡ ሁሉንም አባላት በዕጩነት ያቀረቡት ሊቀመንበር መንግስቱ የነበሩ ሲሆን፤ ያለአንዳች ተቃውሞ ይሁንታ ማግኘቱን ቆመው በጋራ ጭብጨባ ያረጋገጡት ደግሞ ሁሉም ተሳታፊዎች ነበሩ፡፡

ኢሠፓአኮ ከተመሠረተ በኋላ ባደረገው የመጀመሪያ ስብሰባም የአደራጅ ኮሚሽኑ ሊቀመንበር አድርጎ መንግስቱን መምረጡን ለጠቅላላ ጉባዔው ሲያበስር ያ ከፍተኛ ድምፅ ያለው የጋለ ጭብጨባ ያለማቋረጥ ተስተጋባ፡፡

ኮሎኔል መንግስቱ በደርግ ሊቀመንበርነታቸው ላይ የኢሠፓን ሊቀመንበርነት ደርበው ያዙ፡፡ ከዚህ በኋላ ሊቀመንበሩና የመስራች ጉባዔ አባላቱ በሲቪልና በወታደራዊ ሰልፍ የደመቀውን የአብዮቱን 5ኛ ዓመት በዓል በአብዮት አደባባይ አክብረው ወደየመጡበት ተመለሱ፡፡ ወደየመጡበት . የተመለሱት የመስራች ጉባዔ አባላት በየክልላቸው ኢሠፓአኮን አቀነቀኑ፡፡ ሊቀመንበር መንግስቱም በተሰጣቸው ስልጣን መሠረት የማዕከላዊ ኮሚቴውን ስራ አስፈፃሚዎች (የፖሊት ቢሮ አባላትን) መርጠው በየዘርፉ መደቡ፡፡

1. ሻምበል ለገሠ አስፋው - የድርጅት ጉዳይ መምሪያ ኃላፊ
2. ሻምበል ፍቅረስላሴ ወግደረስ - የርዕዮተዓለም ጉዳይ መምሪያ ኃላፊ
3. ኮሎኔል ተካ ቱሉ - የዲሲፒሊንና ቁጥጥር ጉዳይ መምሪያ ኃላፊ
4. አቶ ታዬ ጉርሙ - የኅብረት ስራ ማኅበራት ማደራጃ መምሪያ ኃላፊ
5. ኮሎኔል ብርሃኑ ባይህ - የውጭ ጉዳይ መምሪያ ኃላፊ
6. ኮሎኔል ውብሸት ደሴ - የአስተዳደርና ፋይናንስ ጉዳይ መምሪያ ኃላፊ
7. ኮሎኔል ገብረየስ ወልደሃና - የአብዮታዊ ጦር ዋና ፖለቲካ አስተዳደር ኃላፊ
8. ሻለቃ ተካልኝ ባልቻ - የማዕከላዊ ኮሚቴ ጽ/ቤት ኃላፊ ሆነው ተመድበው ስራቸውን ቀጠሉ፡፡

ኢሠፓአኮ በዚህ መልኩ ተዋቅሮ ሲያበቃ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጉዳዮች ሁሉ በስሩ ሆኑ፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ ወሬ ስለ ኢሠፓአኮ እንዲሆን ሰፊ የፕሮፓጋንዳ ስራ ተሰራ፡፡ ሲቪልና ወታደሩ እየተናናቀ፣ እንዲሁም ሌሎች የውስጥ ችግሮችን ይዞ ለመቀጠል



ከመገደዱም ባለፈ፤ አደራጅ ኮሚሽኑ የፀነሰው ፓርቲ ነውና አብሮ ለመወለድ ሲባል የሚደረገው ሹኩቻ የበረታ ነበር፡፡ በዚህም ላይ የሰሜንና የምስራቁ ጦርነት አለ፣ የኢህአፓ ሠርጎ ገቦችን መከላከልም ሌላ ፈተና ነበር፡፡ የክፍለሃገራት ኮሚቴዎችን ፀብ ማርገብና መሸምገልም ተጨማሪ ስራ ሆኗል፡፡ ምንም ቢሆን ግን ኮሚሽኑን ተንከባክቦ ዳር ማድረስ አላዳገተም፡፡

ኢሠፓአኮ ከፍተኛ በጀት ተመድቦለትና የህዝብ ድጋፍም አግኝቶ ጠቅላላ ጉባዔ፣ ማዕከላዊ ኮሚቴ፣ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ፣ የክፍላተሃገር ኮሚቴ እና በየቀበሌው ማኅበራትና መስሪያ ቤቶች የተዋቀሩ መሠረታዊ ድርጅቶች እንዲኖሩት ተደርጎና ራሱን የቻለ የአሠራር መዋቅር ተዘርግቶለት፣ ከቀበሌ እስከ አጠቃላይ ምክር ቤት ባለው የአመራር ቦታ ላይ ይመጥናል የተባለ እድሜው ከ18 ዓመት በላይ የሆነ ዜጋ ከየአቅጣጫው ተሰብስቦ በዕጩነት ተመዘገበ፡፡ ከሞላ ጎደል የዕጩዎች መመዘኛ አጭር የህይወት ታሪክና ለአብዮቱ ያደረጉት አስተዋፅኦ የሚል ነበር፡፡

ዕጩዎችን ለማበጠር የተሰየሙት ኮሚቴዎችም "የአብዮታዊ ሠደድ" አባላት የበረከቱበት ነው፡፡ በደርግ የበላይነት እየተዳፈኑ የነበሩ የዘመኑ ፓርቲዎችም በዚያ ወቅት ገና ተደመስሰው አልከሰሙም ነበርና በተቻላቸው መጠን ዕጩዎቻቸውን አቅርበዋል፡፡ የዕጩዎች ዝርዝር ከተጠናቀቀ በኋላም ምርጫው በቀበሌ፣ ቀጥሎ በከፍተኛ፣ በመጨረሻም በአጠቃላይ ምክር ቤት ተካሂዶ በሁሉም ከተሞች በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ተጠናቀቀ፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞም የሠራተኛና የገበሬ ማኅበራት ተደራጁ፡፡

በዚህ መሠረት ኢትዮጵያንና ህዝቦቿን በአንድ በኢሠፓአኮ አመራር መዳፍ ስር ማድረግ ተቻለ፡፡ "የኢሠፓአኮ ተልዕኮ በሰፊው ህዝብ የጋራ ርብርቦሽ ይሳካል" የሚል መፈክር ያላሰማ ዜጋ ፀረ አብዮተኛ ተብሎ ይፈረጃል፡፡ የኮሚሽኑ ልሳን "ሠርቶ አደር" ጋዜጣ ሙሉ ገፁ ስለኢሠፓአኮ የሚያትት ሆነ፡፡

እንዲህ ሆኖ የፓርቲው መወለጃ ጊዜ እስኪቃረብ የተጀመሩ የመሠረተ ልማት ግንባታዎች እንዲፋጠኑ፣ አስፈላጊ ዝግጅቶች እንዲደረጉ፣ የሌኒንና የትግሎችን ሐውልቶች ግንባታቸው አልቆ በጌጣጌጥ እንዲንቆጠቆጡ ተደረገ፡፡

ኢሠፓአኮ በተመሠረተ በ4ኛ ዓመቱ በ1977 "የኢትዮጵያ ሠርቶ አደር" ፓርቲን (ኢሠፓ)ን ሲወልድ በጥቂቱ በዓሉን የወሎው ድርቅ አደበዘዘው እንጂ፤ አጠቃላይ የከተማዋ በመብራትና በባንዲራ ማሸብረቅና ሌላው ሁሉ ዝግጅት የቀድሞውን የእነጃንሆይን የንግስ በዓል

ሠዎች ብቻ ገድሎ በሽታውን መግታት ተቻለ፡፡ እንዲህ እያለ የአገሪቱ ኢኮኖሚ በፍጥነት እያሽቆለቆለ ሲሄድ መንግስት ለህዝቡ የተለያዩ ምክሮችንና የተመጠነ ኑሮ ማልመድ እንደሚገባ ማስተማር ጀመረ፡፡ "ቁጠባን ልመዱ" ሲል አስጠነቀቀ፡፡

ጓድ ሊቀመንበር ራሳቸውን አርአያ አድርገው ማሳየት ነበረባቸውና ... ያው የወታደር ልብሳቸውን ካወለቁ ቆይተው ነበርና በምትኩ ሱፍና ክረባት አድርገው ይታዩ ስለነበር አሁን ደግሞ የአገር ውስጥ ምርት የሆነውን ሠማያዊ ካኪ ኮምፕሌቱን ገጥመው መጡ፡፡

"አለው አለውና

በካኪው ላይ ጠና ..." የሚል ስንኝ ተቋጠረ፡፡ ከካኪ ወደ ሱፍ፣ ከሱፍ ወደ ካኪ ማለት ነው፡፡ ወዲያው የፓርቲው አባላትና ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ ይህንኑ ጥቁር ሠማያዊ ካኪ እንዲለብስ የሚያስገድድ ደንብ ወጣ፡፡ ተግባራዊም ሆነ፡፡ ያጉረመረሙት ብዙ ቢሆኑም ግን፤ "አሁን ካኪ ተለብሶ ምን ለውጥ ሊመጣ ነው?" ቢሉም ተግባራዊ ከመሆን አልዳኑም፡፡የህ ልብስ ሶስት አይነት ደረጃዎችና ቀለማት ነበሩት፡፡ ቀጥሎ ለመንግስት ስራም ሆነ ለግል ማንኛውም አውቶሞቢልና ሌሎች የቅንጦት እቃዎች ከውጭ እንዳይገቡ ታገደ፡፡

የመንግስት ተሽከርካሪዎች በባለሥልጣናቱ በግል መያዛቸው ቀርቶ በጣም አስፈላጊ ሲሆን በሹፌር እንዲጓጓዙ፣ የግል አውቶሞቢል እሁድ ቀን እንዳይሽከረከር፣ ነዳጅ በኩፖን እጅግ አስፈላጊ ለሆነ ጉዳይ ሲፈለግ ብቻ እንዲሸጥ፣ ውድ ዋጋ ያላቸው ጨርቃጨርቆች ተገዝተው ከውጪ እንዳይመጡ፣ነዳጅ፣የሞተር ዘይትና ቅባት ለምርት፣ ለወታደራዊ አገልግሎት፤ እንዲሁም ለህዝብ መጓጓዣ ተግባር ብቻ በእቅድና በቁጠባ እንዲውል፣ የተጋነነ የመኖሪያ ቤት አሠራር ስርዓት እንዲይዝ፣እያንዳንዱ ዜጋ በድርቅ ለተጎዱ ወገኖቹ መልሶ ማቋቋሚያ የሚሆን ቋሚ የገንዘብ መዋጮ እንዲያደርግ፣በመጠለያ ጣቢያ የሚገኙትን ተጎጂዎች ለመርዳት ጥያቄ የሚቀርብለት ዜጋ በማንኛውም የስራ ዓይነት በፈረቃ መሳተፍ ግዴታው እንደሆን የሚደነግግ ደንብ ወጥቶ በስራ ላይ እንዲውል ተደረገ፡፡

እነዚህን የመሰሉ ሕጎች አውጥቶ በመንግስት ብቻ ጉዳዩ ሳይያዝና በብሔራዊ ደረጃ ችግሩን ለህዝብ ገልጾ፣ አቅምን አገናዝቦ የተመጠነ ኑሮ መኖር ግዴታ መሆኑን አውጆ፤ በተለይም በገቢና ወጪ ንግድ ላይ የተከሰተውን ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ችግር ለመቅረፍ የሞከረ መንግስት "ረሃብ ደብቋል" እየተባለ መታማቱ ተገቢ አይመስልም፡፡ ከዚህ ይልቅ "ትኩረት የሰጠው ዘግይቶ ነው" በሚለው ማማቱ የተሻለ ይሆናል፡፡

ፓርቲው በአዋጅ የያዘውን አገር የመምራት ስልጣን መሠረት አድርጎ የመንግስትነት ኃላፊነቱን በውጊያም፣ በኢኮኖሚ ግንባታም በሌሎችም ዘርፎች ሁሉ ከመዋከቡ ጎን ለጎን የተቻለውን ጥሯል፡፡



የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ያሽቆለቆለው በድርቅ ምክንያት ብቻ አልነበረም፡፡ በዋናነት በጦርነት ነው፡፡ የራስ ወዳድ ግለሰቦች ንቅዘትም አብሮ ይጠቀሳል፡፡ በጦርነት የፈሰሰው ገንዘብ ግን እጅግ ከፍተኛ የሆነውን ድርሻ ይይዛል፡፡ ይህም የአገር ዳር ድንበር ጉዳይ እስከሆነ ድረስ ደርግ ከጃንሆይ የተረከባትን ድፍን ኢትዮጵያን ጠብቆ የመቆየት ኃላፊነት አለበትና እንደመንግስት በዘርፉ ፈሰስ ማድረግ ነበረበት፡፡ "አገሪቱን በጦርነት ዘፍቆ ህዝቡን ለረሃብ አጋለጠ" ይባላል፡፡ ማነው ጦርነት የፈለገው? ደርግ? ይሄ አባባል መመርመር ያለበት ነው፡፡ ምክንያቱም ጤናማ አስተሳሰብ አይመስልም፡፡ በጥቂቱ ከላይ የተጠቃቀሱትን አይነት የኢኮኖሚ ተሐድሶ በማድረግ በወቅቱ የነበረውን ችግር በመጠኑ ማሻሻል ተችሏል፡፡

ሁኔታው በዚህ በቀጠለበት ወቅት በፓርቲው የማዕከላዊ ኮሚቴ ጽ/ቤት ውስጥ በተለይ የወታደርና የሲቪሉ ፍጥጫና መናናቅ እየተካረረ ሄደ፡፡ በነብሰ አድን ስራው ላይ ይታይ የነበረው የጋራ ርብርብ ፓርቲው የወታደርና የሲቪል እየተባለ በሽኩቻ ውስጥ መሆኑ ቀርቶ ውህደት እየተፈጠረ ነው ወደሚል እሳቤ አምርቶ የነበረ ቢሆንም፤ ብዙም ሳይቆይ የስልጣን ትግል ተጀመረ፡፡

አንዱ ቡድን ኃያሉ የወታደር ቡድን ሆነና፤ ሌላው ቡድን ስልጣን ከወታደሩ ለመንጠቅ ይገዳደራል የተባለው አራት ሲቪል ግለሰቦችን ያቀፈ ቡድን ሆኖ ቁርቁሱ ቀጠለ፡፡ "ጋንግስ ኦፍ ፎር" (አራቱ ነውጠኞች) ተብለው የተፈረጁት በቁጥር እንጂ በስም ተለይተው አይታወቁም፡፡ ብቻ ግን ጓድ ሊቀመንበር መፍጠን ነበረባቸው፡፡ ፓርቲው (ኢሠፓ) ከተመሠረተ ከሦስት ዓመት በኋላ የሊቀመንበሩ የመጨረሻ ዓላማ ግቡን ሲመታ እናያለን፡፡

ሕገ መንግስትና ምርጫ

ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ በአብዮቱ ወቅት በገባው ቃል መሠረት ስልጣኑን ለህዝብ ለማስረከብ በዝግጅት ላይ መሆኑን በአብዮቱ 11ኛ ዓመት የልደት በዓል ላይ መስከረም 2 ቀን 1978 ዓ.ም በአብዮት አደባባይ ለተሰበሰበው ህዝብ ጠቁሞ ነበር፡፡

ይህን ለማድረግ የመጀመሪያው ስራ ሕገመንግስት ማርቀቅ ነበርና የአርቃቂ ኮሚሽኑ አባል ሊሆኑ የሚችሉ ዕጩዎችን መመልመል ተጀመረ፡፡ ለዚህና ለቀጣዩ ሂደት ሲባልም "የብሔረሰቦች ጥናት ኢንስቲቲዩት" የተባለ የአገሪቱ ምርጥ ምርጥ ምሁራን የተሰባሰቡበት ተቋም እንዲመሰረት ተደርጎ ነበርና፤ ተቋሙ ያካሄደውን ጥናትና የጥናቱንም ውጤት በመመርኮዝ ሂደቱ እንዲቀጥልና ውጤታማ ግብ ላይ እንዲደረስ ትልቅ ሚና ተጫውቷል፡፡

በኢትዮጵያ አንድነት የሚያምኑና አብዮቱን የሚደግፉ ዜጎች ተሳታፊ እንዲሆኑ የተደረገበት ‘ምልመላም ከህዝባዊ ማኅበራት፣ ከሙያ ማኅበራት፣ በአካባቢያቸው ከታወቁ ሰዎች፣ ከፓርቲ አባላት፣ ከሃይማኖት መሪዎች፣ ከጦር ሠራዊት፣ ከፖሊስ፣ ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት መምህራንና ተማሪዎች፣ እንዲሁም ከሕግ ባለሙያዎች የተውጣጡ 344 አባላት ያሉት የሕገመንግስት አርቃቂ ኮሚሽን ማቋቋም ተቻለ፡፡ ስራውንም በዚያው ዓመት የካቲት 7 ቀን ጀመረ፡፡ ህዝቡ እንዲወያይበት ስለታቀደም አራት ወራት የፈጀ የአወያዮች ስልጠናና የመወያያ መድረኮችን የማመቻቸት ስራ ተሠራ፡፡

ረቂቁ በአማርኛ ከተዘጋጀ በኋላ ሁሉም ብሔረሰብ በቋንቋው እንዲወያይበት በሚል በኦሮምኛ፣ በትግርኛ፣ በሲዳምኛ፣ በወላይትኛ፣ በሶማልኛ፣ በአፋር፣ ሐድያ፣ ከንባታ፣ ጌዲኦ፣ ኩናማ፣ ከፋ፣ ሽካ፣ ሳሆ እና በስልጥኛ ተተርጉሞ ለወይይት ተሰራጨ፡፡

ምሽግ ውስጥ ካሉት ወታደሮች ጀምሮ ውጪ አገር ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን ሳይቀር ለሁሉም ዜጎች እንዲደርስና አስተያየት እንዲሰጥበት ከተደረገ በኋላ ከአወያዮች ዘገባ ጋር ወደ አርቃቂ ኮሚሽኑ ተመለሰ፡፡

ኮሚሽኑ "አስተያየቶችንና የማሻሻያ ሀሳቦችን ተቀብዬ አስተካክዬ ጨርሻለሁ" በሚል ጳጉሜ 1 ቀን 1978 ዓ.ም ለጓድ ሊቀመንበሩ አስረከበ፡፡

በ17 ምዕራፎች የተከፈለውና 119 አንቀጾች ያሉት ሕገ-መንግስት ጥር 24 ቀን 1979 ዓ.ም የህዝብ ውሣኔ ያገኘ ሲሆን፤ እንደ ኮሚሽኑ ዘገባ ከተመዘገበው ህዝብ 81 በመቶው "ተቀብለናል" የሚል ነበርና ሕገመንግስቱ በሪፈረንደም ፀደቀ፡፡

ሕገመንግስቱ በሚደነግገው መሠረትም የመንግስት ከፍተኛ አካል ነው ለተባለው ለብሔራዊ ሸንጎ አባልነት ምርጫ መካሄድ ነበረበት፡፡ ለዚህም "የምርጫ ኮሚሽን" ሚያዚያ 14 ቀን 1979 ዓ.ም ተቋቋመ፡፡ የዚህ ብሔራዊ ሸንጎ (የእንደራሴዎች ሸንጎ) አባል ሆኖ ለመመረጥ የፓርቲው ዝቅተኛ አባላት መብት አላቸው፡፡ በዚህም በፓርቲው የተደገፉ ዕጩዎች አሸናፊ እንዲሆኑና የብሔራዊ ሸንጎው አባል እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡የአውራጃ ፓርቲ ኮሚቴዎች ለህዝብ እንደራሴነት ይመጥናሉ ያሏቸውን ግለሰቦች ስም ዝርዝር በመመዘኛው መሠረት አጣርተው ለክፍለሀገር ኮሚቴዎች ሲያሳልፉ፤እዚያም አስፈላጊው ማጣራት ተደርጎና "እገሌን በእገሌ ለውጥ" በሚል ወደ አውራጃ ስም ዝርዝሩ ተመልሶ፤ የተለወጡትም "ለምን ተለወጥን?" የሚል ክርክራቸው ውድቅ ተደርጎ፣ የተጣራው ዝርዝር ለማዕከላዊ ኮሚቴ ድርጅት ጉዳይ መምሪያ ተላከ፡፡ ማዕከላዊ ኮሚቴውም የደረሰውን ስም ዝርዝር አይቶ፣የሚሰርዘውን ሠርዞና



በሌሎች ዕጩዎች ተክቶ ለመጨረሻ ስራ ወደ አውራጃ ኮሚቴዎች መለሰው፡፡ በዚህ ጊዜ ነው የበታች የሆኑ የአውራጃ የፓርቲ አባላቱና፤ የፓርቲው የበላይ አካላት ጥምረታዊ የፓርቲ ስራ እየሰሩ እንዳልሆነና፤ፓርቲው የይምሰል መሆኑ ለብዙዎች ግልፅ የሆነው፡፡የበታች የሆኑ የፓርቲው አባላት በዕጩነት የመዘገቧቸውን ተራ የፓርቲ አባላት የላይኛው ክፍል እየሰረዘ የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላትን ተካበት፡፡

ከዚህም በላይ በህዝብ ዘንድ ተደማጭነትን ያስተርፋሉ ተብሎ የታመነባቸው ግለሰቦች ባይፈልጉትም በዕጩነት እንዲቀርቡ ግፊት ተደርጎባቸዋል፡፡ ለአብነትም ብፁዕ አቡነ ተክለሃይማኖት ይጠቀሳሉ፡፡ "አልፈልግም" ብለው ቢከራከሩም በብዙ ማግባባት እሺ አሰኝተው ቅፅ እንዲሞሉ ሲደረግ "ብሔር" የሚል ነገር ሲያዩ "እኔ ብሔር ብሎ ነገር አላውቅም እምቢ ያልኩትም ለዚህ ነው፤ እኔ የምወክለው ምዕመኑን ብቻ ነው" ብለው ጥለው ሊወጡ ሲሉ፤ "ግድ የለም እሱን ይተውትና ሌላውን ይሙሉ" ተብለው የሚያምኑበትን ብቻ ሞልተው እንደሄዱ በ"ነበር" ቁጥር 2 ላይ ተጠቅሷል፡፡

በዚህ ዓይነት የዕጩ እንደራሴዎች ቅድመ ዝግጅት ከተጠናቀቀ በኋላ 150 ሺ አባላት ያሏቸው ከ ክፍለሀገር እስከ ቀበሌ የምርጫ ጣቢያ ድረስ ምርጫውን የሚያስተባብሩ "የምርጫ አስፈፃሚ ኮሚቴዎች" በድፍን ኢትዮጵያ ተቋቋሙ፡፡

የምርጫ ኮሚሽኑ ዝግጅቱን አጠናቆ የዕጩ እንደራሴዎችን ዝርዝር ተቀብሎ ካፀደቀና የምርጫ አፈፃፀምና የዕጩዎች ማስታወቂያ መመሪያዎችን ካዘጋጀ በኋላ ለእያንዳንዱ ዕጩ የምርጫ ምልክት ብሎ ራሱ የሰየመላቸውን "ዝሆን፣ አንበሳና ጎሽ" ሰጣቸው፡፡ በተለመደው አሠራር መሠረት አንድ ዕጩ መወዳደር ያለበት በሚኖርበት ወረዳ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ነገር ግን በአዲስ አበባ የፓርቲ አባላትና የመንግስት ባለሥልጣናት በጣም ብዙዎቹ በሌ አካባቢ ይኖሩ ስለነበር ችግር ተፈጠረ፡፡

መቼም ቀድሞ ያለቀለት ምርጫ ቢሆንም (እንደማንኛውም የአፍሪካ አገራት ምርጫ) ለደንቡ ያህል ነውና የቦሌዎቹን ባለሥልጣናት ወደ ሌሎች ወረዳዎች መበተን የግድ ሆነ፡፡ በማይኖሩበት ቀበሌ ሄደው ተመረጡ ማለት ነው፡፡

የዝሆን ምልክት የያዘ ዕጩ ማሸነፍ እንዳለበት ቀድሞ ተወስኗል፡፡ ግን አንበሳና ጎሹ እንዲያው በስህተት ሊያሸንፉ ቢችሉስ? በሚል መነሻና በአንዳንድ የምርጫ ጣቢያዎች ሊመረጡ ይችላሉ ተብለው የተፈሩ ዕጩዎች ስለነበሩ፤ ከዕጩ እንደራሴነት ራሳቸውን እንዲያገሉ ተደረገ፡፡

በከፍተኛ (ወረዳ) 14 ቀበሌ 18 በነበረው የምርጫ ጣቢያ ላይ ዕጩ ሆነው ከቀረቡ 3 ሰዎች ውስጥ አንዱ ጓድ ሊቀመንበር መንግስቱ

ኃይለማርያም ናቸው፡፡ የፕሬዝዳንትትነት ወንበሩ የትም እንደማይሄድ ቢያውቁትም ግን፤ ከዚያ በፊት ከዚህ ቀልሌ በእንደራሴነት ምርጫ ማለፍ አለባቸው፡፡

እንደማንኛውም ዕጩ እንደራሴም በቀበሌው ህዝብ ፊት ቀርበው ራሳቸውን አስተዋውቀዋል፡፡ እናም አንዳች አስጊ ነገር እንዳይከሰት የጎሽና የአንበሳ ምልክት ባለቤቶች በደረሰባቸው ተፅዕኖ ምክንያት "ከእሳቸው ጋር በዕጩነት በመቅረቤ ብቻ ታሪካዊ ኩራት ይሰማኛል፣ ልወዳደራቸውና ልመጥናቸው ስለማልችል ብቻ ግን ራሴን በፈቃዴ ከምርጫው አግልያለሁ" እያሉ ወጡ፡፡ የቀበሌው ብቸኛ ዕጩ እንደራሴ ሆነው ጓድ መንግስቱ ብቻቸውን ተወዳድረው ብቻቸውን ተመርጠው አለፉ፡፡

የምርጫውን አጠቃላይ ድባብ በሚመለከት የ"ነበር" ፀሐፊ ዘነበ ፈለቀ በቁጥር 2 መጽሐፋቸው በገፅ 109 ያሰፈሩትን ብናይ ሁኔታውን በአጭሩ ለመገንዘብ ይረዳናል፡፡

"... እንዲህ ሆኖ በሌሎች ምርጫ ጣቢያዎችም ተመሣሣይ እርምጃ ተወስዷል፡፡ ሆኖም አንዳንድ ጣቢያዎች ላይ ጠንካራ እንቢታ ገጥሟል፡፡ ለምሳሌ እኔ ምርጫ ባስፈፀምኩበት ቀጠና ከፍተኛ 17 ቀበሌ 17 ላይ የዝሆን ምልክት የያዙት ኮማንደር የኋላእሸት ግርማ ነበሩ፡፡ የአንበሳውን ምልክት የያዘው የትምህርት ሚኒስትር ኢሠፓ መሠረታዊ ድርጅት ፀሐፊ መብራቱ ገብረንጉስ ነበር፡፡ ከእርሳቸው ይልቅ እርሱ በቀበሌው ህዝብ የታወቀ በመሆኑ፤ "ዝሆኑን ይጥለዋል" በሚል ስጋት ከዕጩነት ራሱን እንዲያገል የምርጫ ጣቢያው አስተባባሪ ኮሚቴ ጠየቀው፡፡ መብራቱ ሆዬ "ኧረ ምን ሲደረግ? ምርጫ ብላችኋል፤ ብላችኋል! የህዝብ ድምፅ ይለየን እንጂ ራሴን አላገልም" ብሎ በፅናት ቆመ፡፡

ቢለመን፣ ቢለመን አሻፈረኝ በማለቱ ወደኔ ላኩት፡፡ "ጓድ መብራቱ ... ምን መሰለህ .... ብዬ ላግባባው ከመጀመሬ "ጓድ ዘነበ ብዙ አትድከም፡፡ እስከላይ ድረስ ሂጄ (እስከ ማዕከላዊ ኮሚቴው) ያለሁበት ፓርቲ የእኩል ፓርቲ መሆኑን ቁርጡን ማወቅ እሻለሁ" ብሎ እንቅጩን ነገረኝ፡፡ .... እላይ ደርሶ ምን እንደተባለ ባላውቅም፤ ከፍቶት ተመለሰ፡፡ ከዚያም ከምርጫው ራሱን አገለለ፡፡..." ይሉናል የዓይን እማኙ፡፡

ምናለ ግን አፍሪካ ውስጥ ቀድሞ ለታወቀ አሸናፊ ምርጫ እየተባለ ያ ሁሉ ጋጋታ፣ ለጋጋታው ሲባል ያ ሁሉ ሚሊዮን ብር ባይባክን? ያስብላል፡፡ ወይስ የአፍሪካ መሪዎች ህዝቡ ሴራችንን አያውቅም የእውነት ይመስለዋል ብለው ያስባሉ? ዘወትር ሲገርመኝ የሚኖር የግል ጥያቄዬ ነው፡፡ መልስ አልባ ጥያቄ!



እዚህ ላይ እግረመንገዴን አንድ ፈገግ ያሰኘኝን ገጠመኝ ላስፍር፡፡ በ2002 ዓ.ም ምርጫ በኢትዮጵያ ከተካሄደ በኋላ የኢትዮጵያ ፓርቲዎች (ብዛታቸው 93 ነበር) ሁሉም በየጽ/ቤታቸው የምርጫውን አጠቃላይ ሂደት የሚመለከቱ መግለጫዎች ይሰጡ ነበር፡፡ በጥምረት በተመሠረተውና መድረክ በተሰኘው ፓርቲ ውስጥ አመራር አባል የሆኑት ዶ/ር መረራ ጉዲናን ፓርቲው መግለጫ ከመስጠቱ በፊት ለሥራ ተገኝቼ ነበርና "ምርጫው እንዴት ነበር ዶ/ር?" አልኳቸው፡፡ "የምን መርጫ?" አሉኝ፡፡ "እንዴ የአሁኑ ምርጫ ነዋ፤ እናንተ ኢህአዴግን በብርቱ የተፈታተናችሁበት የትናንቱ ምርጫ" ስላቸው፤ "ታዲያ ቅርጫ በላ! ምን ምርጫ ትላለህ? ቅርጫ አይደለም እንዴ? ቅርጫ እንኳን ስርዓት አለው" ነበር መልሳቸው፡፡ ይህችን አገላለፅ ስብሰባው ከተጀመረ በኋላም ደጋግመው እያሏት የተገኘውን ጋዜጠኛ ሁሉ በሣቅ ሲያፈርሱት ቆዩ፡፡ ምርጫና ቅርጫ የዚያ ወቅት ሰሞነኛ ጥምር ቃላት ሆነው ሰነበቱ፡፡

ስንመለስ ሰኔ 7 ቀን 1979 ዓ.ም ከንጋቱ 12 ሰዓት የጀመረው ምርጫ ምሽት 12 ሰዓት አበቃ፡፡ የውጭና የአገር ውስጥ ጋዜጠኞች እየተዟዟሩ ሁኔታውን ዘገቡ፡፡ ቀድመው ያሸነፉት የዝሆን ዕጩዎች በካርድ ቆጠራ በድጋሚ አሸነፉ፡፡

ከዚያም ጳጉሜ 4 ቀን 1979 ዓ.ም የብሔራዊ ሸንጎ መስራች ጉባዔ በከፍተኛ ድምቀት ተከፈተ፡፡ 2ሺ የሚሆኑ ጉባኤውን የሚያደምቁ ከአገር ውስጥ የፓርቲ አባላት፣ የመንግስት ባለሥልጣናት፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ ታዋቂ ግለሰቦች፣ ምሁራን፣ መለዮ ለባሽ ጉባዔው ሲከፈት የተገኙ ሲሆን፤ ከውጭ አገር በተደረገላቸው ጥሪ መሠረት የግብፁን ሆስኒ ሙባረክ ጨምሮ፤ የታንዛኒያ፣ የናይጄሪያ፣ የዛምቢያ፣ የቶጎ፣ የሊቢያ፣ የሳዑዲዓረቢያ፣ የኩዌትና የሌሎች አገሮች መንግስታት ተወካዮች የሆኑ የልዑካን ቡድኖች በክብር እንግድነት ተገኙ፡፡

የመታሰቢያ ስጦታቸውን ሲያበረክቱም በወቅቱ ሻዕቢያን እየረዳች ኢትዮጵያን ታሳርድ የነበረችው አገር የሳዑዲዓረቢያ ተወካይ ለመንግስቱ ያበረከቱት ስጦታ ጎራዴ ነበር፡፡ "እኛ የምንሰጥዎ ከንጉሣችን የተላከ የሳዑዲ ጎራዴ ነው!" ብለው በጩኸት ከተናገሩ በኋላ ጎራዴውን ከአፎቱ መዥረጥ አድርገው ለጓድ ሊቀመንበር ሰጧቸው አሉ፡፡ እረደው ይሁን፣ እያረድናችሁ ነው ይሁን ትርጉሙን በውል ባይረዱትም መንግስቱ ስጦታውን ተቀበሉ፡፡ ከተሰብሳቢው ጉርምርምታ ተደመጠ፡፡

በእለቱ ጓድ ሊቀመንበር መንግስቱ ከክርስቶስ ልደት በፊት ጀምረው እስከዚያች ታሪካዊ ያሏት ቀን ድረስ የነበረውን የኢትዮጵያ ታሪካዊ ገፅታ 4 ሰዓት በፈጀ ሐተታቸው አቀረቡ፡፡

ሲቀጥሉም፤ "... ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ህዝባዊ አደራ በተቀበለበት በዚያ ቀውጢ ወቅት በገባው ቃል መሠረት ስልጣን

ለታሪክ ሰሪውና ከታሪክ ጋር ለሚዘልቀው ለሠርቶ አደሩ ህዝብ እነሆ ሊያስረክብ ነው፡፡ ደርግ ባለፉት የትግልና የድል አመታት ለተከናወኑት አብዮታዊ ተግባራት ከሁሉም በላይ የድርጊቶቹም ሆነ የውጤቶቹ ባለቤት ለሆነው ለሠርቶ አደሩ ህዝብ ያለውን ጥልቅና ታላቅ አክብሮት እየገለፀ፡ ለወደፊቱም ህዝቡ ለኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ አመራር፣ በኢትዮጵያ ህዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ግንባታ የእድገት ትልሙን ሙሉ በሙሉ ዳር እንደሚያደርስ ከልብ ይመኛል፡፡..." አሉ፡፡

በዚህም የስልጣን ምርኩዝ ሆኖ ያገለገላቸውን "ደርግ" የተባለ ቡድን መክሰሙን አረዱ፡፡ የደርግ አባላት መክሰም የጀመሩት ከኢሠፓ ምስረታ ጀምሮ የነበረ ቢሆንም፤ ይፋ የወጣው እና በሕገመንግስቱ መሠረትም መኖር እንደሌለበት ግልፅ የሆነው በዚሁ ጊዜ ነው፤ ይህ ማለት ግን አባላቱ ቁልፍ ቁልፍ ቦታዎችን ከሚገባቸው ስልጣን ጋር ይዘው ስለዘለቁ መክሰም ሊባል አይችልም፡፡ ከቡድናዊ ባለሥልጣንነት ወደተናጠላዊ ሹማምንትነት ተለወጡ የሚለው የተሻለ ይገልፃቸዋል፡፡

ከሊቀመንበሩ ንግግር በኋላ የነበረውን ጊዜም ልዩ ልዩ ሕገመንግስቱን ተንተርሰው የወጡ አዋጆችን በማፅደቅ ነበር ያለፈው፡፡ በዚህም በ813 እንደራሴዎች አማካኝነት ስልጣኑን ተግባራዊ እንደሚያደርግና፤ ዋናው የመንግስት ምክር ቤት እንደሆነ፤ የመንግስት ምክርቤቱም የጉባኤና የስራ አስፈፃሚ አካል የተሰኙ የስራ ዘርፎች እንዳሉት ተገለፀ፡፡ በሕገ መንግስቱ መሠረትም፤

- የኢትዮጵያ ህዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (ኢሕዴሪ) ብሔረሰቦች በእኩልነት የሚኖሩበት ብሔራዊ መንግስት ነው፡፡
- ሠርቶ አደሩ ህዝብ የስልጣን ባለቤትነቱን ተግባራዊ የሚያደርገው በምርጫ በሚያቋቁመው ብሔራዊ ሸንጎና የአካባቢ ሸንጎዎች አማካይነት ይሆናል፡፡
- ብሔረሰቦች በሸንጎው መወከላቸው ይረጋገጣል፡፡
- ኢሕዴሪ በዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት፣ በሶሻሊስት ሕጋዊነትና፤ ወዝአደራዊ ዓለም አቀፋዊነት መርህ የሚመራ መንግስት ነው፡፡
- የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ ኢሠፓ የመንግስትና የመላው ህዝብ መሪ ኃይል ነው፡፡
- የውጭ ፖሊሲው በወዝአደራዊ ዓለምአቀፋዊነት፣ በሠላም አብሮ መኖርና በገለልተኝነት መርሆዎች ላይ የተመሠረተ ነው፡፡
- ኢህዴሪ በራስ ገዝና በአስተዳደር አካባቢዎች የሚዋቀር አሃዳዊ መንግስት ነው፡፡
- ከፍተኛ የመንግስት ስልጣን አካል ብሔራዊ ሸንጎው ነው፡፡



ብሔራዊ ሸንጎው ዋና ባለሥልጣን መሆኑን ካወጀ በኋላ የራሱን ስብሰባ አድርጎ በመሪነት ላይ መሪነት፣ በመሪነት ላይ መሪነት እየተቀዳጁ እዚህ የደረሱትን ሊቀመንበር መንግስቱ ኃይለማርያምን "የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት ፕሬዝዳንት" አድርጎ መርጦ እንደሾማቸው ይፋ አደረገ፡፡

ፕሬዝዳንት መንግስቱ ኃይለማርያም በዕለቱ ሳቃቸውን መቆጣጠር እያቃታቸው፤ "... ኢትዮጵያ በታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ ህዝብ በመረጠው ፕሬዝዳንት ተመራች!" በማለት የእንጨት መደሻዋን አንስተው ጠረጴዛዋን ኳ አደረጓት፡፡

ሸንጎው የኢህዴሪን ልዩ ልዩ የስልጣን አካላት ያዋቀረ ሲሆን፤ እነዚህም፤ የመንግስት ምክር ቤት፣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት፣ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ፣ እና የቁጥጥር አካላት ናቸው፡፡

በዚህም መሠረት መንግስቱ ኃይለማርያም የምክር ቤቱ ፕሬዝዳንት፣ ሻምበል ፍቅረስላሴ ወግደረስ ጠቅላይ ሚኒስትር፣ አቶ አስፋ ሊበን የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ፕሬዝዳንት ሆነው ሲሾሙ፤ ሌሎች የደርግ አባል የነበሩና ያልነበሩ መለዮ ለባሾችና ሲቪሎች በሚኒስትርነት፣ በምክር ቤቱ አባልነት፣ በምክትል ፕሬዝዳንትነትና በምክትል ጠቅላይ ሚንስትርነት፣ እንዲሁም በልዩ ልዩ የኃላፊነት ቦታዎች ላይ እንዲሾሙ ሆነው በጦርነት አጣብቂኝ ውስጥ ገብታ ውጥረት የነገሰባትን ኢትዮጵያን ማስተዳደር ቀጠሉ፡፡

የሌተናል ኮሎኔል መንግስቱ ኃይለማርያም የመጨረሻው የስልጣን ጣራ ላይ የመውጣት ህልም እውን ሆኖ በ1980 ዓ.ም ግቡን መምታት ቻለ፡፡ ስለዚህም 13ኛው የድል በዓል ላይ ስልጣን ህዝቡ ተረክቧልና፣ ወይም ስልጣን የህዝብ ሆኗልና ... የዚያ ዓመት መስከረም ሁለት ከሌላው ጊዜ በተለየ መልኩ ደምቆ ተከበረ፡፡

*መፈንቅለ መንግስቱ እና ያስከተለው መዘዝ*

ግቦት 8 ቀን 1981 ዓ.ም ፕሬዝዳንት መንግስቱ ኃይለማርያም ወደሚወዷት ምስራቅ ጀርመን ለስራ ጉብኝት ብለው ሄዱ፡፡ የኢሠፓ የፖሊት ቢሮ አባላት፣ የመንግስት ምክር ቤት አባላት፣ ሚኒስትሮችና ጀኔራሎች ኤርፖርት ድረስ ሄደው በተለመደው መሽቆጥቆጥ በክብር ሸኝተዋቸው ተመለሱ፡፡

መንግስቱ ግትር ሆነዋል፣ ጦሩ እየተሸነፈ ነው፣ የጄኔራሎች የጦር እቅድ በመንግስቱ ዘንድ ብዙም ተቀባይነት አያገኝም፣ የተለየ ሀሳብ የሚያቀርብ የጦር አዛዥ በጥርጣሬ ዓይን ይታያል፣ ሊቀመንበሩ የመረጡትና ወደተግባር እንዲተረጎም የሚሹት የዘመቻ ስልት በሶቭየት ህብረት የጦር አማካሪዎች የሚቀርበውን የወረቀት ላይ የዘመቻ ንድፍን

ነው፡፡ ከፍተኛ የጦር ጄኔራሎች በበታቾቻቸው በደርግ አባላት ይታዘዛሉ፡፡ አንድ መቶ አለቃ ወይም ሻምበል አንድን ጄኔራል ያዛል፣ መንግስቱ በታማኝነት እንጂ በሙያ ብቃት ማመንና መሾም አልፈጠረባቸውም፡ የተናቁም ይመስላቸዋል፤ ከዚሁ ጋርም የደርግ አባል የሆኑ የበታች ሹማምንት ቁምነገሩ የበላይና የበታችነት ጉዳይ ሳይሆን የመንግስቱ ታማኝና ቀኝ እጅ ሆኖ መገኘቱን በመረዳታቸው በማዕረግ የሚበልጧቸውን ታላላቅ የጦር ጀግኖች ይንቋቸዋል፡፡

በእነዚህና እነዚህን በመሣሠሉ መነሻ ምክንያቶች በርከት ያሉ ጄኔራሎች የመንግስቱን አገዛዝ ጠልተውታል፡፡ ፊት ለፊት መጋፈጥ የማይሞከር በመሆኑም ያለው ምርጫ መፈንቅለ መንግስት ማድረግ ነበርና በዚህ ጉዳይ በተለያዩ ቦታዎች ተሰብስበው መመካከር ከጀመሩ ቆይተዋል፡፡

የጉዳዩ ጀማሪና ጠንሳሽ ሜጀር ጄኔራል ፋንታ በላይ ነበሩ፡፡ እቅዱ ከሁለትና ሦስት ዓመት በፊት ተነድፎ ሲብላላ የቆየ ነው፡፡ በተለይ መንግስቱ በኤርትራ ያለው ጦር በተሸነፈ ቁጥር ችግሩ የጄኔራሎች ነው ብለው በማመናቸው ብዙዎችን ከነበሩበት ቦታ እያነሱና ዝቅ፣ ከፍ እያደረጉ መሾም መሻር የጀመሩት ከ1978 ጀምሮ ሲሆን፣ ለአብነት ሜጀር ጄኔራል ፋንታ በላይን ከአየር ኃይል ዋና አዛዥነታቸው አንስተው የኢንደስትሪ ሚኒስቴር ሚንስትር እንዲሆኑ አድርገዋል፡፡ ይህ መሰሉ ሹም ሽር ለአመታት ተከታትሎ የተከናወነ እንደመሆኑ መጠንና በጄኔራሎቹም ዘንድ ስላልተወደደ ጥርስ ነክሳው ከተጠቀሰው ጊዜ የጀመረና ሲብላላ የኖረ፣ ነገር ግን በ1981 ግንቦት ወር ሊተገበር የተሞከረ ነው፡፡

የዚችን እለት የመጨረሻ የአድማ ስብሰባ ለማድረግ የተመረጠው ቦታ በመከላከያ ሚኒስትር መስሪያ ቤት ጊቢ ውስጥ የሚገኝና ከሚኒስትሩ ከሜጀር ጄኔራል ኃይለጊዮርጊስ ቢሮ አጠገብ ያለው አነስተኛ የመሰብሰቢያ ክፍል ነው፡፡

በእለቱ ባልተለመደ ሁኔታ ይህ ጊቢ የጄኔራሎች መጠራቀሚያ ሆታ ታዩ፡፡ አድመኞቹም በቀጠሯቸው መሠረት አንድ በአንድ ወደዚያች ክፍል ገቡ፡፡ በስብሰባው ላይም የተገኙት፤

1. ሜ/ጄ/ል መርዕድ ንጉሴ - የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማገር ሹም
2. ሜ/ጄ/ል ኃይሉ ገብረሚካኤል - የምድር ጦር ዋና አዛዥ
3. ሜ/ጄ/ል አምሃ ደስታ - የአየር ኃይል ዋና አዛዥ
4. ሪረ አድሚራል ተስፋዬ ብርሃኑ- የባህር ኃይል ዋና አዛዥ
5. ሜ/ጄ/ል አለማየሁ ደስታ - የምድር ጦር ምክትል አዛዥ
6. ሜ/ጄ/ል ወርቁ ዘውዱ - የፖሊስ ሠራዊት ጠቅላይ አዛዥ



7. ሜ/ጄ/ል አብዱላሂ ዑመር - የመከላከያ ሚ/ር አስተዳደር መምሪያ ኃላፊ
8. ሜ/ጄ/ል ፋንታ በላይ - የኢንደስትሪ ሚኒስትር
9. ሜ/ጄ/ል አበራ አበበ - የጦር ኃይሎች ምክትል ኤታማገር ሹም
10. ሜ/ጄ/ል ተስፋዬ ትርፌ - የአብዮታዊ ዘመቻ መምሪያ ኃላፊ
11. ብ/ጄ/ል ሰለሞን ጋሻው - የአየር ኃይል ኤታማገር ሹም
12. ብ/ጄ/ል ደሣለኝ አበበ - የጦር ኃይሎች አካዳሚ አዛዥ
13. ብ/ጄ/ል እርቅይሁን ባይሳ - የ67ኛው ኮር ዋና አዛዥ
14. ብ/ጄ/ል ተስፋዬ ደስታ - የአየር ኃይል ዘመቻ መኮንን
15. ብ/ጄ/ል ነጋሽ ወልደየስ - የ608ኛው ኮር ዋና አዛዥ
16. ብ/ጄ/ል እንግዳ ወልደአምላክ - የ606ኛው ኮር ዋና አዛዥ
17. ብ/ጄ/ል ገናናው መንግስቱ - የ6ኛው አየር ምድር አዛዥ
18. ኮሞዶር ኃይሌ ወልደማርያም - የጦር ኃይሎች ዘመቻ መምሪያ ባልደረባ ናቸው፡፡(ነበር ቁ.2)

በስብሰባው የተገኙት እነዚህ ብቻ ይሁኑ እንጂ ከየጦር ክፍሉ የተመለመሉ አዛዦችም የሚሰጣቸውን ትዕዛዝ ለመፈፀም ተዘጋጅተዋል፡፡ እነዚህ ከፍተኛ ባለሥልጣናት ተሰብስበው የመጀመሪያ ውሣኔ ያደረጉት ሊቀመንበሩን ቀይ ባህር ሲደርሱ ፕሌኑን በሚሳኤል መምታትና ማሰናበት የሚል የነበረ ቢሆንም፤ ከመንግስቱ ውጪ የተሳፈሩ በርካታ ንፁሃን ሰቪሎች ስላሉ እነሱንም አብሮ መግደል ተገቢ አይደለም የሚል ሀሳብ ስለተነሳ ውሣኔው ተሻረና፤ ከዚህ ይልቅ በወጡበት ማስቀረት እንደሚሻል ስምምነት ላይ ተደረሰ፡፡

ዋና ሰብሳቢው ሜጀር ጄኔራል ፋንታ በላይ ነበሩ፤ ነገር ግን ወደ ስብሰባው የመጡት ዘግይተው ነበርና የሰብሳቢነቱን ቦታ ሜጀር ጄኔራል መርዕድ ንጉሴ ይዘውታል፡፡ ጄኔራል ፋንታ በላይ ወደ ስብሰባው ገብተው ሲያዩ ቦታው ተይዟል፡፡ ጄኔራል መርዕድ ዋና ሰብሳቢው ሲመጡ ቦታውን መልቀቅ ሲገባቸው ፀጥ አሉ፡፡ ቢታይ፣ ቢታይ መርዕድ ለፋንታ ሊለቁ ቀርቶ የመልቀቅ አዝማሚያም ሳያሳዩ ስብሰባውን መምራት ቀጠሉ፡፡

መፈንቅለ መንግስት ለማድረግ የተሰባሰቡት ጄኔራሎች እዚያው በዚያው ሌላ መፈንቅለ መንግስት አደረጉ፡፡ ስልጣን ሠይጣን ነዋ! አስቂኝነቱም እዚህ ላይ ነው፡፡ እናም በዚያች ጠባብ ቢሮ ኩዴታ የተከናወነባቸው ጄኔራል ፋንታ በላይ በሁኔታው ተበሳጭተው ስብሰባውን ጥለው ወጡና በር ላይ እጃቸውን ኪሳቸው ከተው መንጎራደድ ጀመሩ፡፡ ሜጀር ጄኔራል መርዕድ ንጉሴ ቦታውን የያዙት "ይምሩት" የሚል ፈቃድ

አጥፍተው፤ ሁኔታውንም ለተሰብሳቢዎች ሳይገልፁ፤ ሄቻለሁም ሳይሉ ጊቢውን ለቀው እግሬ አውጪኝ አሉ፡፡

ተሰብሳቢዎቹ ያወቁት ጉዳይ የለም፤ ስብሰባውን ቀጥለዋል፡፡ከአስመራ ይመጣል ብለው የሚጠብቁት የአየር ወለድ ጦር በምን ሁኔታ ላይ እንዳለና መድረስ አለመድረሱን አያውቁም፡፡

ጄኔራል አበራ አበበ ጥለው እንደሸሹ አያውቁም፣ ከአስመራ ይዘዋቸው የመጡትን አየርወለዶች ጄኔራል ቁምላቸው ምን እንደሚያሏቸው አያውቁም፤ ምክንያቱም የጄኔራል አበራን ትዕዛዝ በመጠባበቅ ላይ ናቸውና፡፡ ጄኔራል ቁምላቸው ቀጣይ ትዕዛዙ ለምን እንደዘገየ አያውቁም፣ አየር ወለዶችም ስላልተገለፀላቸው ለምን እንደመጡ አያውቁም፡፡ በቃ አያውቁም ባያውቁም ሆን ነገሩ ሁሉ፡፡

የፖሊስ ጠቅላይ አዛዥ ሜጀር ጄኔራል ወርቁ ዘውዴ ነገሩ አላምር ብሏቸው ይሁን፣ ጥበቃውን ለማጠናከር ይሁን በማይታወቅ ሁኔታ ስብሰባውን ጥለው ወጡ፡፡ ከዚህ በኋላ ማንም አልወጣም፡፡ ወዲያው እሩብ ጉዳይ ለሰባት ሲሆን በሻምበል መንግስቱ ገመቹ የተመራው የቤተመንግስቱ ቅልብ ጦር የመሰሪያ ቤቱን ጊቢ ዙሪያውን አጠረው፡፡ የልዩ ጥበቃ ብርጌዱ ጦር ከበባውን እንዳደረገም ማንም እንዳይወጣ፣ ማንም እንዳይገባ የሚል ትዕዛዝ ከሻምበል መንግስቱ ገመቹ ተሰጠና ይሄው ትዕዛዝ ተግባራዊ ሆነ፡፡

ሻምበል መንግስቱ ገመቹ ይህን በድል እንዳጠናቀቀውና የቀረው በምድር ጦር ውስጥ አርሚ አቭየሺን የመሸገው ኃይል እንደሆነ ለሌተናል ጄኔራል ተስፋዬ ገብረኪዳን ገለፀ፡፡ ቀጥል ተባለ፡፡ ቀጠለ፡፡

በዚህ መሐል ሁለተኛው ዙር የአየር ወለድ ጦር ከአስመራ ተነስቶ ቦሌ ደረሰ፡፡ ይህንንም እዚያ የነበረው ጠባቂ በታዘዘው መሠረት ለደህንነቱ ለኮሎኔል ተስፋዬ ገለፀ፡፡ አለቃቸውን ጠይቆ እንደተረዳውም ከጄኔራል ቁምላቸው ደጀኔ ብቻ ትዕዛዝ ተቀበሉ ተብለው የተላኩ መሆናቸውን ጨምሮ ነበር በመስከ ሬዲዮ መረጃ ያስተላለፈው፡፡

ይህን ገለፃ በያዘው ሬዲዮ ከደህንነቱ እኩል ያዳምጥ የነበረው ሻምበል መንግስቱ ገመቹ በደህንነት ሚኒስትሩ እና በመረጃ አቀባዩ የሬዲዮ ንግግር ጣልቃ ይገባና "አንድም ነገር አትንገራቸው፤ እንሄዳለን ወደሚሉበት ይሂዱ" ብሎ ትዕዛዝ አስተላለፈና አብሮት የነበረውን ሻለቃ ሽለማ ኤልማናን "አብዮት አደበባይ ላይ ጠብቀህ አስቁማቸውና ጄኔራል ቁምላቸው ታላቁ ቤተመንግስት እንደሚገኙ ነግረህ ወደዚያው ይዘሃቸው ሂድ" ብሎ አዘዘው፡፡ ሻምበል መንግስቱ ገመቹ እነዚህን ትዕዛዞች ከሰጠ በኋላ የምድር ጦር ጠቅላይ መምሪያንና አርሚ አቭየሽንን ይዘው ትዕዛዝ ይጠባበቁ የነበሩትን "ወንድሞች ጥቂት ችግር ነበር፤ አሁን ችግሩ ተወግዷል፤ ስለደከማችሁ መሣሪያችሁን አስቀምጡና ረፍት አድርጉ"



አላቸው፡፡ መሣሪያቸውን ከግምጃ ቤት እንዲያስቀምጡ ካደረገ በኋላ "የመጣችሁት ለተሳሳተ ተግባር መጠቀሚያ እንድትሆኑ ነበር፡፡ ነገሩ እስከሚጣራ በጥበቃ ስር ሆናችሁ እዚህ ትቆያላችሁ" በማለት በቁም እስር አቆያቸው፡፡ ይሄን ተግባር ፈፅሞ ሲመለስ ሻለቃ ሽለማ በታዘዙት መሠረት በሁለተኛው ዙር የመጣውን አየርወለድ ወደ ቤተመንግስት መርተው አስገብተዋቸው ነበር፡፡

በሁለት ዙር የመጡት ከታገቱ በኋላ ሦስተኛው አንቶኖቭ አዲስ አበባ ደርሶ ለማረፍ እያንዣበበ እንዳለ "ለተሳሳተ ተግባር የተላኩ ወታደሮችን መጫንህ ስለተረጋገጠ፤ ወደመጣህበት ተመለስ፡፡ እንቢ ካልክ ባለህበት እንደምትጋይ እወቅ" የሚል ማስጠንቀቂያ ለአብራሪው ሲነገረው ወደመጣበት ተመለሰ፡፡

በዚያች ዕለት አገሪቱን እየመሯት የዋሉት ሻምበል መንግስቱ ገመቹና ኮሎኔል ተስፋዬ ወልደስላሴ ነበሩ ለማለት ይቻላል፡፡ የአድመኞቹን የግንኙነት መስመር በማቋረጥ ደህንነቱ ኮሎኔል ተስፋዬ፣ የአድመኞቹን አጋዥ ወታደሮችና የአዛዦችን የትብብር መረብ በመበጣጠስ ሻምበል መንግስቱ መተኪያ የሌለው ሚና ተጫውተዋል፡፡

ከስብሰባው ውጪ ሆነው ጦር እንዲያስተባብሩ የተመደቡት ጄኔራል ቁምላቸው ደጀኔ ጥቂት ወታደሮችን ይዘው በግራ መጋባት ሲጠባበቁ ከቀኑ 10 ሰዓት በአንድ መቶ አለቃ የሚመሩ በሻምበል መንግስቱ የተላኩ የልዩ ጥበቃ ብርጌድ ወታደሮች እርሳቸው ወዳሉበት ሄዱ፡፡ እነዚህ ወታደሮች አካባቢውን እንዲቃኙ ቀድመው ተላኩ እንጂ ሌላ ትዕዛዝ ያልተሰጣቸው ነበሩና ሄደው ከጄኔራል ቁምላቸው ሠራዊት ጋር ተላተሙ፡፡ ጄኔራሉ ይህን ምንነቱን ያላወቁትን ወታደር አብረዋቸው በነበሩት ወታደሮች አስከብበው ትጥቁንም አስፈትተው ባዶ ቤት ውስጥ አዘጉባቸው፡፡ እነርሱን ተከትለው የሄዱ ሌሎች ወታደሮችም በታንክ ታግዘው ወደ ቦታው ሲያመሩ ጄኔራሉ በተመሳሳይ አስከብበው ታንካቸውንም ማርከው በግራ መጋባት መጠባበቃቸውን ቀጠሉ፡፡

ሜጀር ጄኔራል ቁምላቸው ያለውጊያ እነዚህን ወታደሮችና ታንካቸውንም ጭምር በቀላሉ መማረክ ቢችሉም ከበላዮቻቸው ጋር የነበረው ግንኙነት በመቋረጡና ቀጣይ ስራቸውንም ባለማወቃቸው ምንም ሊያደርጉ አልቻሉም፡፡

ምሽት 12 ሰዓት ላይ ሻምበል መንግስቱ ገመቹ እንደተከበበ ወደዋለው ወደ መከላከያ ጊቢ አምርቶ በድምፅ ማጉያ ጊቢው እንደተከበበና በውስጡ የሚገኝ ዘበኛ፣ ሲቪል ሠራተኛ፣ ባለሥልጣን፣ ጄኔራል ሁሉም እጁን ጭንቅላቱ ላይ አጣምሮ በሁለተኛው በር እንዲወጣ አሳሰበ፡፡ ሁሉም በአምባሳደር ቴአትር ቤት በኩል ባለው በር እጅ ወደ ላይ አድርገው ሲወጡ፤ ብርጋዴል ጄኔራል አምሃ ደስታ እዚያው

ራሳቸውን ገደሉ፡፡ ቀጥሎ ሜጀር ጄኔራል መርዕድ ንጉሴ ራሳቸውን በሽጉጥ ገደሉ፡፡ ሜጀር ጄኔራል ፋንታ በላይ እና ኮሞዶር ኃይሌ ወልደሚካኤል ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን እዚያው ውስጥ ተደብቀው ቀሩ፡፡ ሌላው በሠላም ወጥቶ እጅ ሰጠ፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ በሜጀር ጄኔራል ደምሴ ቡልቶ የተመራው የአስመራው አድማ እንደተጧጧፈ ቀጥሎ የነበረ ሲሆን፣ በአስመራው ሬዲዮ ጣቢያ የመንግስቱ ኃይለማርያም አንባገነናዊ አገዛዝ እንዳበቃና ለውጥ እንደተደረገ፣ ኢትዮጵያ ሠላም የሰፈነባት አገር ሆና እንደምትገነባ ወዘተ እየተገለፀ ነበር፡፡ ሻዕቢያና ወያኔም "ጉዳያችሁ ዳር እስኪደርስ ተኩስ አቁመናል" ብለዋል፡፡ በተመሳሳይም በጎንደር አዘዞ የነበሩት የ603ኛው ኮር አዛዥ ሜጀር ጄኔራል ዘውዴ ገብረየስ በአስመራ ሬዲዮ የሚሰራጨውን መልዕክት በወረቀት እያባዙ ለህዝብ ይበትኑ ነበር፡፡ በሰሜን ጎንደር የኢሠፓ ዋና ፀሐፊ የነበረው ሻምበል ገዛኸኝ ወርቄ ለስራ ጉዳይ አዲስ አበባ ወጥቶ ነበርና ወደ ጄኔራል ዘውዴ ደውሎ ሁሉም ነገር በቁጥጥር ስር መዋሉን በመግለፅ ጦሩን እንዲያረጋጉ ሲያዛቸው "ዞር በል ያንተ አዛዥነት አክትሟል" ብለው ስልኩን ዘጉበት፡፡ ሻምበል ገዛኸኝ ወርቄ ወደ ዕዙ የፖለቲካ ኮሚሳር ደውሎ "እዚህ ያለው አድመኛ ጄኔራል ሁሉ በቁጥጥር ስር ውሎ ታጉሯል፡፡ አጠገብህ ያለውን ጄኔራል ከነተከታዩ አፍስህ አስረህ ጠብቀኝ" አለው፡፡ ከሚሳሩ የታዘዘውን ፈፀመ፡፡

አመሻሹ ላይ ግራ የተጋቡት ጄኔራል ቁምላቸው ደጀኔ ከነበሩበት አርሚ አቪየሽን ጊቢ ወጥተው ሁኔታውን አጣርተው ለመምጣት አንድ ታንክ አስከትለው የመከላከያን ጊቢ ከርቀት ለማየት ወደሚያስችለው ወደ ጎማ ቁጠባ ዳገታማ ጎዳና ሄደው ሲያዩ የተለየ ድባብ አስተዋሉ፡፡ ጄኔራሉ ከአርሚ አቭየሽን እንደወጡ ወዲያው ነበር ጊቢው የተከበበው፡፡ ስለዚህ አየር ወለዶች እዚያው እንዳሉ በቁጥጥር ስር ዋሉ፡፡

ጄኔራል ቁምላቸው ባቅራቢያቸው ወዳለው 5ኛ ፖሊስ ጣቢያ ሄደው የፖሊስ መምሪያ ጠቅላይ አዛዥ የሆኑትን ሜጀር ጄኔራል ወርቁ ዘውዴን በስልክ እንዲያገኟቸው ቢያዙም ቀድመው ከስብሰባው የወጡት ጄኔራል ሊገኙ አልቻሉም፡፡ የፖሊስ አዛዡ ማምለጫ መንገዱ ሁሉ ተዘግቶባቸው ቤታቸው ውስጥ መሽገው የሚመጣውን ለመቀበል ተዘጋጅተው ነበር፡፡

ከዚህ በኋላ ጄኔራል ቁምላቸው ሁሉም ነገር ማክተሙን ተረድተው ጥለዋቸው የመጡትን ጥቂት አየርወለዶችንም "የራሳቸው ጉዳይ" ብለው ራሳቸውን የሚያድኑበትን መንገድ መፈለግ ጀመሩ፡፡

የአዲስ አበባው የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ በሻምበል መንግስቱ ገመቹ ብርቱ ትግል በተደረገ ከበባ እኩለ ሌሊት ላይ በድል



ተደምድሟል፡፡ በሁሉም የጦር ክፍሎች የነበሩት ተባባሪዎች ሁሉ እጃቸውን ተይዘዋል፡፡

አጠገባቸው ይገኝ የነበረውን ብሔራዊ ሚዲያ መቆጣጠር ሳይችሉ፣ ወታደሮቻቸውን በየቦታው ሳይመድቡ፣ ለህዝብ መረጃውን ሳያሰራጩ፣ እርስ በርስ ሳይስማሙ፣ ለማክሸፍ ማን ምን ሙከራ ሊያደርግ እንደሚችል ሳያውቁ፣ ሳይገምቱና ሳይዘጋጁ፣ በአንድ ጊቢ ውስጥ በምትገኝ ቢሮ ተሰብስበው መፈንቅለ መንግስት አድርገው፣ ስኬታማነቱን ለጥቂት የቢሮው ሠራተኞች እና ለራሳቸው አውጀው፣ ጊቢ ውስጥ ያሉትን አስጨብጭበው፣ እዚያው ጊቢ ውስጥ ደም ተፋሰው፣ እዚያው ጊቢ ውስጥ ተይዘው ቀሩ፡፡ የአዲስ አበባው አስቂኝ መፈንቅለ መንግስት ሳይጀመር ተጨረሰ፤ ሳይሞከር ከሸፈ፡፡

ከሌሊቱ በ9 ሰዓት ጓድ ሊቀመንበር መንግስቱ ኃይለማርያም የምስራቅ ጀርመን ጉብኝታቸውን አቋርጠው አዲስ አበባ ደርሰው የተቀባይ ጋጋታ በሌለበት በቀጥታ ወደቤታቸው ገብተው፤ እንቅልፍ ይወስዳቸዋል ብለን ባናስብም ተኙ፡፡

ነግቶ ግንቦት 9 ቀን 1981 ዓ.ም ሆነ፡፡ ማለዳ ላይ አስመራ የሚገኘው የ202ኛ የአየር ወለድ ክፍለጦር አባላት "የፕሬዝዳንት መንግስቱን አመራር የሚቃወም ማንኛውም ድርጊት አብዮቱን የመቀልበስና ኤርትራን የማስገንጠል ሴራ ነው!" በሚል አምፀው ሬዲዮ ጣቢያውንም ተቆጣጥረው መፈንቅለ መንግስቱ የከሸፈ መሆኑን አወጁ፡፡ በዚህም አላበቁም ሌሎች የሁለተኛው አብዮታዊ ሠራዊት ኮሮችና ክፍለጦሮች ከአየርወለድ ቡድኑ ጎን ተሰልፈው አገርን ጉድ ያሰኘ ተግባር ፈፀሙ፡፡

የአስመራውን አድማ በዋናነት የመሩትን ሜጀር ጄኔራል ደምሴ ቡልቶን ጨምሮ ተባባሪ ያሏቸውን ጄኔራሎች ሁሉ ረሸኑ፡፡ ሬሳቸውንም በአደባባይ እየጎተቱ ተጫወቱበት፡፡ ቀጥለን ዝርዝራቸውን የምናየው ተረሻኞች ውስጥ ግን የአድማው ተባባሪ ያልሆኑና የበታቾች አጋጣሚውን ተጠቅመው ቂማቸውን የተወጡባቸው ይገኙባቸዋል፡፡ ጦሩ "የእኛን ስንቅ ለጠላት ሸጧል፤ ጦሩን ሲመራ ሆን ብሎ ወደ ጠላት ወረዳ ከቶ አስከብቦ አስፈጅቶናል፣ እኛ የምንለብሰው እጥተን በእኛ ገንዘብ በውስኪ ይራጫል ... ወዘተ" በሚል ቂም በቀል ያሉበትንም የሌሉበትንም በጭካኔ ጨፈጨፈ፡፡ አስመራ በዚህ ሁኔታ ስትውል፤የአዲስ አበባዎችም ከጥቂቶች በስተቀር ተለቅመው ከታሰሩ በኋላ ግንቦት 10 ቀን ጓድ ሊቀመንበር በብሔራዊ ሚዲያ ጥቂት ጄኔራሎች ለስልጣን ሲሉ የሞከሩት ሴራ በእንጭጩ መቀጨቱን ከሰፊ ሐተታ ጋር ገለፁ፡፡

የአድማው እንቅስቃሴና የህዝቡ ጉርምርምታ በአንድ ጊዜ ፀጥ ረጭ አለ፡፡ በአስመራ ራሳቸው ይመሩት በነበረው ሠራዊት የተረሸኑት የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. ሜ/ጀ/ል ደምሴ ቡልቶ - የሁለተኛው አብዮታዊ ሠራዊት ዋና አዛዥ
2. ብ/ጀ/ል ወርቁ ቸርነት - የዕዙ የፖለቲካ ጉዳይ ኃላፊና ምክትል አዛዥ
3. ብ/ጀ/ል ታደሠ ተሰማ - የዕዙ ዘመቻ መኮንን
4. ብ/ጀ/ል ንጉሤ ዘርጋው - የሁለተኛው አየር ምድብ አዛዥ
5. ብ/ጀ/ል ከበደ ወልደፃድቅ - የሁለተኛው አብዮታዊ ሠራዊት መምሪያ
6. ብ/ጀ/ል ሠለሞን ደሣለኝ - የ202ኛው አየር ወለድ ክፍለ ጦር አዛዥ
7. ብ/ጀ/ል ከተማ አይተንፍሱ - የ11ኛው ክፍለ ጦር አዛዥ
8. ብ/ጀ/ል ታዬ ባለኬር - የኤርትራ ሪስ ገዝ ፖሊስ አዛዥ
9. ብ/ጀ/ል ተገኔ በቀለ - ሁለተኛው አብዮታዊ ሠራዊት መምሪያ
10. ብ/ጀ/ል ከበደ መሐሪ- የዕዙ ድርጅት መኮንን
11. ብ/ጀ/ል ፈለቀ እንግዳ - ሁለተኛው አብዮታዊ ሠራዊት መምሪያ
12. ዶክተር ኮሎኔል ጌታቸው አወቀ - የዕዙ ሆስፒታል ዳይሬክተር
13. ሌ/ኮ/ል መስፍን አሠፋ - የ2ኛ ሜካናይዝድ ክፍለ ጦር አዛዥ
14. ሌ/ኮ/ል ዘርዓይ ዕቁባይ - ሁለተኛው አብዮታዊ ሠራዊት መምሪያ
15. ሌ/ኮ/ል ዮሐንስ ገብረማርያም - ሁለተኛው አብዮታዊ ሠራዊትመምሪያ
16. ሻለቃ ካሣ ፈረደ - የዕዙ መሐንዲስ ክፍል ባልደረባ
17. ሻለቃ ሚካኤል ሚሪቦ - ሁለተኛው አብዮታዊ ሠራዊት መምሪያ
18. ሻምበል ጌታሁን ግርማ - ሁለተኛው አብዮታዊ ሠራዊት መምሪያ

በዚህ እልቂት ሻዕቢያና ወያኔ በከፍተኛ የደስታ ስሜት ተጥለቀለቁ፡፡ በሣቅ እያሽካኩም አላገጡ፡፡ የአስመራው ሁኔታ ባየነው መልኩ ፈጣን ግድያ ተከናውኖ ተደመደመ፡፡ የአዲስ አበባዎቹን ጀኔራሎች ስም ዝርዝር ከአድማው አጀማመር ጋር ቀድመን ስላዩነው ደግሞ መዘርዘሩ አያስፈልግምና ቀጣይ ዕጣፋንታቸውንና ፍፃሜያቸውን በአጭሩ ወደማየት እናልፋለን፤ ከዚያ በፊት ግን ከመፈንቅለ መንግስቱ ሙከራ ጋር የተያያዙ ሁለት ያህል ነጥቦችን እናንሳ፡፡

የመጀመሪያው የመፈንቀለ መንግስቱ ዓላማ ምን ነበር? የሚለው ነው፡፡ በርካታ የንደን እማኝ የነበሩ የቀድሞው ጀኔራሎች አሁን ላይ ሆነው ዓላማውን ለመተንተን ይዳዳሉ፡፡ ካለፈ በኋላ የሚገለፀውና በወቅቱም የተነገረው፤ "ጦርነቱ በአስቸኳይ እንዲቆምና ከተቃዋሚ ኃይሎች ጋር ንግግር እንዲደረግ፣ ከሁሉም ተቃዋሚዎች የተውጣጣ የሽግግር መንግስት እንዲቋቋም፣ አዲሱ ሕገመንግሰት ዴሞክራሲያዊ ባልሆነ መንገድ የፀደቀ ስለሆነ እንዲታገድ፣ የሀገር መከላከያ ከግለሰብ አገልጋይነት ነፃ ሆኖ በአዲስ መልክ እንዲደራጅ፣ ህዝቡን በመለዮ ለባሹ



ጠመንጃ አፈሙዝ መግዛት እንዲቆም፤ ለህዝቡ የጋዜጣ፣ የንግግርና የሠላማዊ ሰልፍ ነፃነት እንዲሰጠው ..." የሚል ዓላማ እንደነበር ይገለፃል፡፡ አንዳንድ የቀድሞው ጀኔራሎችማ አሁን ላይ ሆነው "ህዝባዊ መሠረት የነበረውና የተደራጀ፣ ቢሳካ ኖሮ ለኢትዮጵያ የተሻለ ..." በሚል ያብራሩታል፡፡

በመሠረቱ ህዝባዊ መሠረት ሊኖረው ቀርቶ ሠራዊታዊ መሠረት አልነበረውም፡፡ አቀናባሪ የነበሩ አባላት እንኳ በጽኑ የጋራ መሠረት ላይ የቆሙ አልነበሩም፡፡ ከዚህም በላይ ይህን መሰሉን ተንታኔ በግምታዊ ገለፃ መደምደም ቀላል የመሆኑን ያህል፤ ቢሳካ ኖሮ ዓላማው ከላይ የተገለፀውን አቅድ በተግባር መተርጎም አልነበረም ብሎ መገመትም እኩል ቀላል ይሆናል፡፡ ይልቁንም ገና ከጅምሩ የተከናወነውን የኩዴታ ተግባር ስናይ የመጀመሪያውን ገለፃ ከመቀበል ይልቅ ሁለተኛውን ግምታዊ ድምዳሜ መምረጥ የበለጠ ቀላል ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ሁሉም አካል ስልጣን ሲይዝ የሚለው ያንኑ ነው፡፡ አገሪቱ በዚያ አይነት የስልጣን ትግል ውስጥ በነበረችበት ወቅት፣ ለጠላት መረጃ አሳልፎ መሸጥ ፋሽን በሆነበት በዚያ ወቅት፣ በዚያ ላይ ኢትዮጵያዊ ባለሥልጣን ስልጣን ይዞ ለሌላ አካል አሳልፎ ለመስጠት ሲል ህይወቱን አደጋ ላይ የሚጥል፣ .... እንኳን በጦርነት ሠዓት በሠላማዊ ምርጫ አሸንፎ ስልጣን የያዘ፣ ተሸንፎ ስልጣን የለቀቀ አካል ባልታየባት አህጉር (ከሁለት የአፍሪካ አገሮች በስተቀር) ይልቁንም በኢትዮጵያ መሆኑን ስናስብ ዓላማው ምን እንደነበረ ግልፅ ይሆንልናል፡፡ ምንም እንኳ በሞካሪዎቹ አሳዛኝ ፍፃሜ ልባችን ቢነካም፤ በግለሰብ ደረጃ እንኳ ቤተሰቦቻችን፣ ዘመዶቻችን ቢሆኑ፣ በተጨማሪም በኢትዮጵያዊነታቸው ብቻ በእክብሮት ብናያቸው፤ የመፈንቅለ መንግስቱ ዓላማ ምን ነበር? ለሚለው ጥያቄ አንድ ዓይነት የሆነ የብዙሃኑ የጋራ ምላሽ ከመስጠት አያግደንም፡፡ ከእውነት አብልጦ ራሱን የማይወድ አንባቢ የሚሰጠው ምላሽ "የግንቦት 8 ቀን 1981 ዓ.ም የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ አላማው ስልጣን ነው" የሚል፡፡ ... ስልጣን ... ስልጣን!

ሌላው ሁለተኛው ነጥብ ሙከራው ለምን ከሸፈ? ደጋፊና ተቃዋሚዎችስ እነማን ነበሩ? የሚለው አንድም ሁለትም የሆኑ ጥያቄዎች ሲሆኑ፤ ምላሻቸውን በጥምረት አጠቃለን ለማየት እንሞክር፡፡ የመፈንቅለ መንግስት ሞካሪዎች እቅዳቸውን ቀድመው ለጀኔራል ተስፋዬ ገብረኪዳንና ለኮሎኔል ተስፋዬ ወልደስላሴ ገልፀውላቸዋል፡፡ ያገኙት መልስ፤ "ጥሩ ነው ቀጥሉ፤ ግን በገሃድ አብረን ልንሳተፍ አንችልም" የሚል መልስ በተናጠል ሰጥተዋል፡፡ ይህም ታስረው በነበሩ አንድ ጀኔራል የምርመራ ቃል ተረጋግጦ የነበረ ቢሆንም፤የምርመራውን ውጤት ተቀብለው ደህንነቱ ቀብረው አስቀርተውታል፡፡

የሞካሪዎቹ የቅንጅትና የዝግጅት ጉድለት ዋና የመክሸፊያ ምክንያቱ እንደነበር አይዘነጋም፡፡ ነገር ግን ሙከራው የከሸፈው ለውጥ እየፈለጉ ግን ፍርሃት ያርበተበታቸው ባለሥልጣናት ቁርጠኛ አቋም ባለማሳየታቸው ነው፡፡ ለምሳሌ ቁልፉን ሚና የሚጫወቱት የደህንነት ሚኒስትሩ ኮሎኔል ተስፋዬ ወልደስላሴ ከሁለት አንድ ያጣ ላለመሆን ሲሉ በአንድ በኩል እንዲሳካ የሻምበል መንግስቱ ገመቹን አካሄድ ዘገምተኛ ለማድረግ መሞከራቸውን እስር ላይ ሆነው አምነዋል፡፡ በሌላ በኩል ቢከሽፍ የሚደርስባቸውን አደጋ እያሰቡ በተለይ ወደመጨረሻው ገደማ ክሽፈቱ እየተረጋገጠ ሲሄድ ሙሉ በሙሉ ጄኔራሎችን ክደው የመንግስቱ ታማኝ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ እርምጃ ወስደዋል፡፡ ኮሎኔሉ ብቻ ሳይሆን ሚኒስትሮችና ሌሎች የፖሊት ቢሮና የመንግስት ምክር ቤት አባላት፣ ሌተናል ጄኔራል ተስፋዬ ገብረኪዳንን ጨምሮ "ምን እናድርግ?" በሚል ተጠራርተው በተሰበሰቡ ጊዜ ጉዳዩን ለማጓተት የሚረዱ የተለያዩ ሀሳቦችን አንስተዋል፡፡ ጄኔራል ተስፋዬ ገብረኪዳን እንኳ ሳይቀሩ የአድማው ተባባሪ ነበሩ፡፡ ግን ሁሉም ተፈራሩ፡፡ ሁሉም ከሁለት አንድ ያጣ ላለመሆን አመነቱ እንጂ ለውጡን ከጓድ ሊቀመንበር መንግስቱ ኃይለማርያም በስተቀር ሁሉም ይፈልገው እንደነበር በደንብ ተረጋግጧል፡፡ ግን ማን የውስጡን ያውጣ፣ ማን ደፍሮ የውስጥ አቋሙን ይናገር፡፡ በዚያን ጊዜ አንድ ቆራጥ ሰው ድጋፍ ቢያሳይ ተሰብሳቢው በሙሉ የድጋፍ ጩኸቱን ያቀልጠው እንደነበር ግልፅ ነው፡፡ የሁሉም ማመንታትና ዝም ብሎ የሆነ ያልሆነ ነገር መቀባጠር ግራ ያጋባው ሻምበል መንግስቱ በምን እናድርግ ስብሰባው ላይ ብድግ ብሎ "ማስቆም ካለብን ፈጥነን እናስቁማቸው፤ ቤቱ አቅዳቸውን የሚደግፍ ከሆነ ደግሞ ሊወሰድ የታሰበውን እርምጃ ልቀጥልበት፡፡ በሉ እንጂ?" ሲል ጠየቀ፡፡ አሁንም ፈሩ፡፡ ሻምበል መንግስቱ ከዚህ በኋላ ነው የማክሸፍ ስራውን የጀመረው፡፡

ለአገርና ለህዝብ ሲባል ለውጥ መደረግ አለበት ብሎ የሚያምን እውነተኛና ቆራጥ ልብ ያለው ዓላማና ምኞቱ አገርና ህዝብ እንዲለወጡ፣ እንዲሻሻሉ ነውና ለአንድ ህይወቱም ሆነ ለአንድ ስልጣኑ ሲል በፍርሃት አይንቀጠቀጥም፡፡ ግን ቢከሽፍስ? በሚል መነሻ እራሴንም ስልጣኔንም ለምን እጣለሁ? የሚለው አካሄድ ከቁርጠኛ ለውጥ ፈላጊ ባይጠበቅም፤ ከአፍቃሬ ስልጣን ግን ይጠበቃል፡፡ የሆነውም ያ ነው፡፡ ዛሬ ላይ ሆነው ሁሉም ታሳሪ ባልሥልጣናት በተለይ ደህንነቱ አንባ ቀረሽ ፀፀታቸውን ደጋግመው ይገልፃሉ፡፡ "አንድም የማይደግፍ አባል አልነበረም!" ይሉናል፡፡ በዚህ መሰሉ የልቦናና የአንደበት ግጭት ሙከራው ከሸፈ፡፡

አሁንም ይህ በእንዲህ እንዳለ ብለን ስንቀጥል እንደተባለው መፈንቅለ መንግስቱን በአንደበትም፣ በልቦናም የማይደግፉት ጓድ



ሊቀመንበሩ ብቻ መሆናቸው ግልፅ የመሆኑን ያህል፤አሜሪካና ሶቭየትም በስለላ ድርጅቶቻቸው በሲ.አይ.ኤ. እና በኬ.ጂ.ቢ. አማካኝነት ሙከራው እንዲሳካ ድጋፍ አድርገዋል፡፡ ለዚህም ይረዳቸው ዘንድ ለሁለቱም የስለላ ድርጅቶች በሚስጥር ተቀጥረው ይሰሩ እንደነበር የሚነገርላቸው የደህንነቱ ኃላፊ ኮሎኔል ተስፋዬን ተጠቀመውባቸዋል፡፡ በተለይ የአስመራውን አድማ ሁለቱ አገሮች ፈጥነው እውቅና የሰጡት ሲሆን፤ የአዲስ አበባዎችንም "በርቱ" እያሏቸው ነበር፡፡

ኢትዮጵያና ሶቭየት መልካሙ ግንኙነታቸው በተለይ በ1970ዎቹ የመጨረሻ አመታት ከመሻከር አልፎ ተበጥሷል ማለት ይቻላል፡፡

ከፓርቲ ምስረታውና ከሕገመንግስቱ መጽደቅ በፊት በነበረው ጊዜ ሶቭየት የደርግን ሊቀመንበር ሌተናል ኮሎኔል መንግስቱ ኃይለማርያምን "የዳህላክ ደሴት ግዛትን ለወዳጅዎ ለሶቭየት ያበርክቱ፣ አካባቢው ላይ የጦር ቅኝት ማድረጊያ ጣቢያ አስፈልጎናል" የሚል ጥያቄ አቅርበው ነበር፡፡ በአገር ጉዳይ ድርድር የማያውቁት መንግስቱ "እንዴ! ይሄ እንዴት ይሆናል? እኛ'ኮ በሕግ ስልጣን የተሰጠንና በህዝብ ተመርጠን መንግስት የሆንን አይደለንም፡፡ እንዲህ አይነት ጥያቄ በጭራሽ አንቀበልም፤ ስልጣንም የለንም" የሚል ምላሽ ከሰጡበት ጊዜ ጀምሮ ሶቭየት ኢትዮጵያን አንቅራ ተፍታለች፡፡

ይልቁንም ለእማፅያኑ እርዳታ ወደማድረጉ አምርታለች፡፡ ለዚህም ነው የደርግ የስልጣን ዘመን መገባደጃ ላይ ጄኔራል ተስፋዬ ገብረኪዳን ወደ ኤርትራ ግዛት ዳህላክ አካባቢ ወደሚገኝ ቦታ ለስራ ሊሄዱ ሲሉ፤ "ጌታዬ ወደ ዳህላክ ለመሄድ የሶቭየት ባለሥልጣናትን ፈቃድ ማግኘት የግድ ነው" ሲባሉ በድንጋጤ አብድ የሆኑት፡፡ የአካባቢው ክፊል ግዛት በሻዕቢያ ቁጥጥር ስር ሆኖ ስለነበርም በሻዕቢያ መልካም ፈቃድ የሶቭየት ጥያቄ ያለኢትዮጵያ መንግስት ይሁንታ ተመልሷል፡፡

በዚህና በሌሎች የርዕዮት ፍርክስክሶች የጓድ መንግስቱ አገዛዝ እንዲወገድ ሶቭየት መፈለጓ ስለማይገርም ለውጡ እንዲሳካ መፈለጓም የሚደንቅ አይሆንም፡፡

የአሜሪካ አቋም ከድሮውም ግልፅ የሆነና ተጀምሮ እስኪጨረስ የታወቀ ነው፡፡ ሙሉ በሙሉ የአማፅያኑ ደጋፊ፣ የመንግስቱ ተቃዋሚ የነበረች ናት፡፡ ስለዚህ ሁለቱ አገራት ሙከራው እንዲሳካ ብቻ ሳይሆን ከተሳካ በኋላም ከፈንቃዮቹ ጎን እንደሚሆኑ አረጋግጠዋል፡፡

በሠራተኞቻቸው በደህንነቱ አማካኝነትም ትብብርዎን ይቀጥሉላቸው ብለዋል፡፡ ደህንነቱም የሂደቱን ዘጠና በመቶ እቅፍ ድግፍ አድርገው በማያስነቃ መልኩ አስጉዘውታል፡፡ ከመጀመሪያው ጀምሮም ጥንቁቅ የደህንነት ጠባቂ መሆናቸውን በሚያረጋግጥ አኳኋን ያዩትን ለተስፋዬ ገብረኪዳንና ለመንግስቱ ቀኝ እጅ ለሻምበል መንግስቱ ገመቹ የገለፁት

በሙሉ ልብ እንዲከሽፍ በመፈለጋቸው ሳይሆን፤ ሂደቱ ከተጀመረ እንዲቀጥል ሁሉም መፈለጉ ስለማይቀር ችግር እንደሌለው በማመናቸው እንጂ (በእርግጥም እንደዚያ ነበር ማንም ያሰበው) ለመንግስቱ አገዛዝ ተቆርቋሪ ሆነው አልነበረም፡፡

ስለዚህ መጀመሪያ በሚስጥር አይዟችሁ ያሏቸውን በስተመጨረሻ ውድቀታቸው አይቀሬ መሆኑን ሲረዱ በሚስጥር ካዷቸው፡፡ ተጠርጣሪዎችን አሳዳጅ ሆኑ፡፡ በጉዳዩ ላይ እንደነበሩበት የሚያረጋግጡ ተጨባጭ መረጃዎችን ማጥፋት ስራቸው ሆነ፡፡ ያጋልጡኛል ያሏቸውን እና የፈሯቸውን በተለያየ ዘዴ ቦታ ቦታቸውን አስያዙና በመንግስቱ ፊት "የታባታቸው!" ብለው ሸለሉ ማለት ነው፡፡ ወደ ሞካሪዎች ፍፃሜ ስንመለስ፤ ጊቢ ውስጥ ተደብቀው የቀሩት ሁለት ብቻ ነበሩ፡፡ ኮሞዶር ኃይሌ ወልደማርያም በመከላከያ ሚኒስትር ጊቢ ውስጥ ከሚገኝ መታጠቢያ ቤት ተገኝተው ታሰሩ፡፡ ሜጀር ጄኔራል ፋንታ በላይ (የእቅዱ ጠንሳሽና ሰብሳቢ የነበሩትና መፈንቅለ መንግስት የተደረገባቸው) በጊቢው ውስጥ በሚገኝ የዕቃ ማሸጊያ ኮንቴነር ውስጥ ተደብቀው 3 ቀናት ያለ እህል ያለ ውሃ ከቆዩ በኋላ የሚያመልጡበትን ቀዳዳ በመፈለግ ላይ እንዳሉ ተያዙ፡፡

"ፎፕሲና ሚሪንዳ በከተማው ጠፍቶ፤

ፋንታ ተገኘ አሉ በኮንቴነር ሞልቶ፡፡" ተብሎ ተገጠመላቸው፡፡

በዚያ ወቅት የተቋጠሩ ስንኞችን በሚመለከት የ"ነበር" ፀሐፊ ዘነበ ፈለቀ በቁጥር 2 መጽሐፋቸው ያካተቱትን አንድ ገለፃ ላክል፡፡

ሊቀመንበሩ አዲስ አበባ ገብተው ሁሉም ነገር በቁጥጥር ስር ከዋለ በኋላ የአዲስ አበባን ህዝብ ለማመስገን በአብዮት አደባባይ ግንቦት 12 ቀን ተገኝተዋል፡፡ በእለቱ በርካታ ህዝብ ተገኝቶ የተለያዩ አብዮታዊ መፈክሮች ተደምጠዋል፤ቀርቶና ሽለላም ነበር፡፡ የዝግጅቱ ዓላማም "እንኳን እግዜር አዖጣዎ" ለማለት ነው፡፡

"እንጋፋው የሽለላና የቀረርቶ አቀንቃኝ ዓለማየሁ ፋንታ ጭንቅላቱን በነጭ ሻሽ በቀጭኑ ሸብ አድርጎ፤ ለምዱን ለብሶ ማሲንቆውን በቄንጥ እየገዘገዘ

"አባሮ ገዳይ ከዳመናው ስር!

ትመለሳለህ ብዬም አልነበር!" በማለት ሲያቅራራ ላዳመጠው ለዓመታት ሲያቅራራበት የነበረ ስንኙ ሳይሆን "ለምን መጣህ?" በሚል ቁጭት ለዚያች ዕለት አስቦ የቀመረው ይመስል ነበር" ይሉናል፡፡

ጄኔራል ፋንታ በላይ ተይዘው ማዕከላዊ ምርመራ ታስረው ሳለ፤ "ለማምለጥ በመሞከራቸው በጠባቂዎች ተገደሉ" ተብሎ በብዙሃን መገናኛ ተሰራጨ፡፡ ሆኖም ታሪኩ ካለፈ በኋላ እንደተባለው የደህንነቱ ኃላፊ ሚስጥር ያወጡና ተባባሪነቴን ያሳውቁብኛል ብለው የራሳቸውን ሰው



ልከው እስር ቤት ውስጥ እንዳስገደሏቸው ነው፡፡ ለዚህም የተለያዩ የአሟሟታቸውን አይነት መሠረት ያደረጉ አሳማኝ ምክንያቶች ተዘርዝረዋል፡፡ ከዚህም በላይ ሊቀመንበር መንግስቱ "ዋና ጠንሳሽ የሆኑትን ጄኔራል ፋንታን ማነጋገር ስለምፈልግ እንድታመጡልኝ" የሚል ቀጠሮ አስይዘው ስለነበር ሁለቱ ከመገናኘታቸው በፊት ነበር የተገደሉት፡፡

ከዚያም ሚኒስትሩን ገድለው ያመለጡት ጄኔራል አበራ አበበ አምልጠው እንደሄዱ ዘመዳቸው ቤት ተሸሽገው ለጥቂት ቀናት ከቆዩ በኋላ ለደህንነቱ ለኮሎኔል ተስፋዬ የሚያመልጡበትን ሁኔታ እንዲያመቻቹላቸው ቢጠይቋቸውም ዳግመኛ እንዳይደውሉ አስጠንቅቀው ቻው አሏቸው፡፡

ጄኔራል አበራ የደህንነቱ እምቢታ ቢያበሳጫቸውም ምንም ሊሉት አይችሉምና ይልቁንም የት ሆኜ እንደደወልኩ አጣርቶ እንዳያስይዘኝ በሚል ስጋት የመሸሸጊያ ቦታቸውን ለውጠው ወደ ሌላ ዘመድ ቤት ሄዱ፡፡ የሴትዮዋ ባለቤት ኮሎኔል ነበርና የባለቤቱን ዘመድ መሸሸግ ለደህንነቱ ተናገረ፡፡ ወደ ራሱ ቤት እየመራ ወስዶ አስያዛቸው፡፡ ለባለውለታነቱ 5ሺ ብር ተሰጠው፡፡ ከባለቤቱና ከዘመዶቿ ጋር ተኮራረፈ፡፡ በወቅቱ ጄኔራል አበራ አበበን ለመያዝ የሄደው ቡድን ከነህይወታቸው መማረክ እየቻለ ነገር ግን የእጅ መስጠት እድልም ሳይሰጣቸው ታዘው በሄዱ ፖሊሶች ተኩስ ተገደሉ፡፡

በዚያ ወቅት ከሚሊቴሪው አልፎ የአመፁ ተባባሪ ነበር እየተባባሉ መጠቋቆም ወደሲቪሉም ተዛምቶ ነበርና ሁሉም ስጋት ላይ ነው፡፡ የጄኔራል አበራ ወዲያው መገደልም ለደህንነቱ ሌላ እፎይታ ነበር፡፡

ሌላው ሜጀር ጄኔራል ቁምላቸው ደጀኔ ሲሆኑ በራሳቸው አገላለፅ በእለቱ ከአዲስ አበባ ወጥተው በጎጃም አድርገው ሱዳን፣ ከዚያ አሜሪካ ገባሁ ሲሉ፤ ውስጥ አዋቂ ነን የሚሉ ወገኖች ደግሞ እድማው ሲከሽፍ አሜሪካ ኤምባሲ ውስጥ ገብተው እንደተሸሸጉና ምቹ አጋጣሚ ተጠብቆ በኤምባሲው ትብብር ከአገር ወጥተው አሜሪካ መግባታቸውን ነው፡፡ ዞሮ ዞሮ አምልጠው አሜሪካን አገር ገብተዋል፡፡

የቀሩትን ጄኔራሎች በሚመለከት ፕሬዝዳንት መንግስቱ ለህዝቡ "የጥቂት ጄኔራሎች ጉዳይ በአጭር ጊዜ ውስጥ በፍርድ ታይቶ ይወሰናል" ብለው በገቡት ቃል መሠረት ከጠቅላይ ጦር ፍርድ ቤት ጀምሮ ልዩ ልዩ ደረጃ ያላቸው የጦር ፍርድ ቤቶች ተቋቁመው ስራ ለመጀመር 6 ወራት ያህል ጊዜ ወስዶ ክሱ ህዳር 27 ቀን 1982 ዓ.ም ተመስቶ ጉዳያቸው መታየት ጀመረ፡፡

20 ጄኔራሎችንና 86 ከፍተኛና መካከለኛ ማዕረግ ያላቸውን መኮንኖች ፍርድ ለመስጠት በታላቁ ቤተመንግስት ውስጥ ራሱን የቻለ ፍርድ ቤት ተቋቋመ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ የ14ቱ ጄኔራሎች ክሳቸው የታየው በጠቅላይ ጦር ፍርድ ቤት አንደኛ ችሎት ሲሆን፤ ለዳኝነት የተሰየሙት

ሌተናል ጄኔራል ተስፋዬ ገብረኪዳን የመሀል፣ ሜጀር ጄኔራል አስራት ብሩ የግራ፣ ብርጋዲል ጄኔራል ዓለማየሁ ስዩም የቀኝ ዳኞች በመሆን ነው፡፡ ዐቃቤ ሕጉ ኮሎኔል ታጠቅ ነበሩ፡፡

የክሱ ዋና ነጥብ የሁሉም "መንግስትን በኃይል ለማስወገድ የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ ማድረግ" የሚል ነው፡፡ የተለያዩ አገራት መንግስታት ለሊቀመንበር መንግስቱ የከፋ እርምጃ እንዳይወስድባቸው በምክርም፣ በልመናም ሲማፀኑ ቆይተዋል፡፡ በነፃ እንዲለቋቸው የጠየቁ መንግስታትም ነበሩ፡፡ መንግስቱ አልሰሟቸውም፡፡ እናም ሂደቱ ሲጀመር አግባብ ባለው መንገድ እንዲከራከሩ፣ ጠበቃ ማቆም ከቻሉ እንዲያቆሙ፣ ካልቻሉ መንግስት እንዲያቆምላቸው ተፈቅዶላቸው ተከራክረዋል፣ ተከላክለዋል፡፡ ጠበቃ፣ ቤተሰብ፣ የውጭ ጋዜጠኛ ሳይቀር በችሎቱ ተገኝተው ነበር፡፡ ያደረሱት የከፋ አደጋ አለመኖሩን እያነሱ ተከራክረዋል፣ ጠበቆችም የቅጣት ማቅለያ ጠይቀዋል ... ወዘተ፡፡

የቀኝ ዳኛው የሕግ ምሩቅ ቢሆኑም፤ ሁለቱ ዳኞች ግን እንደማንኛውም ሚሊቴሪ ከውስን የሕግ እውቀት ውጪ ባለሙያ አልነበሩም፡፡ ያም ቢሆን ክፋት አልነበረውም፡፡

ህዳር ላይ የተጀመረው ችሎት በቀጠሮ ሄዶ ሄዶ ለውሣኔ ግንቦት 13 ቀን 1982 ዓ.ም ተቀጠረ፡፡ እስከዚህ ድረስ በአግባቡ ከሄደ በኋላ ግን የውሣኔ ቀጠሮው በ13 የነበረው ለጠበቆቹ ባልተለመደ አሰራር ሰልክ ተደውሎ ወደ ግንቦት 11 መለወጡ ተነገራቸው፡፡ በተባለው ቀን ተከሳሶችም ጠበቆችም ተገኙ፡፡ ሌላ ታዳሚ አልተገኘም፡፡ ጋዜጠኛና ቤተሰብ ተባረረ፡፡ ክርክሩ ሙሉ ቀን ወስዶ ከምሽቱ 12 ሰዓት ድረስ ቆየ፡፡ ረፍት ተወጣ፡፡ ጠበቆቹ ግን ለእረፍት እንዳይወጡ ተከልክለው እዚያው ቀሩ፡፡

ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ላይ ዳኞች ተሰየሙ፡፡ ያ ሁሉ ክርክርና አግባብነት የነበረው አሠራር ሁሉ በአንዴ ገደል ገብቶ ፍርድ ቤትነቱም ቀረና እስረኞች በካቴና የኋልዮሽ ታስረው ሽሎቱ ላይ እንዲቆሙ ተደረገ፡፡ (ችሎት ሲቀረብ ተከሳሽ እጆቹን አይታሰርም) ይሄም ባልከፋ ግን መዝገብ ማገላበጡ፣ ሙግት መስማቱ ቀርቶ ተፅፎ የተላከች አንዲት ብጣሽ ወረቀት ይዘው እንባ እየተናነቃቸው ሜጀር ጄኔራል አስራት ብሩ ሊያነቡ ተዘጋጁ፡፡ ያቺ ግማሽ ገጽ ወረቀት በሊቀመንበሩ ተፅፎ የተላከች ትዕዛዝ መሆኗ ነው፡፡ እስኪመሽ የተጠበቀውም ለዚሁ ነበር፡፡

ጄኔራል አስራት የሐዘን እንባቸውን እያፈሰሱ በሲቃ ድምፅ አነበቧት፡፡

እንግዲህ ቀደም ሲል በአድማው ስብሰባ ላይ የነበሩ ተብለው ከተዘረዘሩት 18 ጄኔራሎች ውስጥ ጄኔራል አበራ አበበ እና ጄኔራል ፋንታ በላይ ስለተገደሉ፤ ጄኔራል መርዕድ ንጉሴና ጄኔራል አምሃ ደስታ



ራሳቸውን ስለገደሉ፣ ሌሎቹ 14ቱ ግን በቁጥጥር ስር ሆነው ስለቆዩ ተከታዩ ፍርድ ተበየነባቸው፡፡

ሜጀር ጄኔራል አብድላሂ ዑመር በ10 ዓመት እስራት፣ ሪር አድሚራል ተስፋዬ ብርሃኔ በ15 ዓመት እስራት እንዲቀጡ ሲወሰን፤ ሌሎቹ 12ቱ ጄኔራሎች የሞት ፍርድ እንደተበየነባቸው የሚገልፀውን ወረቀት አንብበው እንባቸውን እየጠረጉ ፈጥነው ከችሎት ወጡ እንባቢው፡፡ ማለትም ዳኛው፡፡ ከተከሳሾች እንደበት የተለያዩ አሳዛኝ ቃሎች በጩኸት ተደመጡ፡፡ "ቤተሰቦቻችን ሳንሰናበት! ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ እድሜ የለውም... ቤተሰቦቻችን አደራ ..." የሚሉ ድምጾች፡፡

ተከሳሾች በወታደሮች እየተገፈተሩ ከአዳራሹ ወጡ፡፡ የዚያኑ ዕለት ምሽት ተረሸኑ፡፡

ሌላውን ሁሉ ትተን ጄኔራሎችን ብቻ ብንደምር አስመራ ላይ ከተገደሉት ጋራ 24 ጄኔራሎች ተገድለዋል፡፡ ከፍርድ በፊት የተገደሉትንና ራሳቸውን ከገደሉት 4 ጄኔራሎች ጋር 28 ሲሆኑ፣ በመከላከያ ሚኒስትር ጊቢ ውስጥ በአንድ ጥይት ከሞቱት ሚኒስትር ጋር 29፣ አንድ አምልጠው የተሰደዱ፣ አንድ 15 ዓመት የተፈረደባቸውን ስንጨምር አገሪቱ ከ6 ወር በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ 30 የጦር ጄኔራሎቿን በቅፅበት ማጣቷን እንረዳለን፡፡ ምን ቀረ ይባላል? ኢትዮጵያ በታሪኳ ዘመናዊ ጦር ሠራዊት ያደራጀችው ከጥቂት አስርት በፊት ነበር፡፡ ዘመናዊ ጦር ሠራዊት ከተገነባ በኋላም እነዚህ ጄኔራሎች እዚህ ማዕረግ ለመድረስ አመታት ወስዶባቸዋል፡፡ ከዚህ አንፃር አገሪቱ በ30 ዓመት ውስጥ ያፈራቻቸውን 30 ጄኔራሎች በቅፅበት ስታጣ ምን ሊፈጠር እንደሚችል ለማወቅ የጦር ሰው መሆን ሳያስፈልግ ማንኛውም ሲቪል ዜጋ በቀላሉ ይረዳዋል፡፡ ከዚህም በላይ በጦርነት ውስጥ የነበረች አገር ላይ አንድ የጦር ጄኔራል ምን ያህል አስፈላጊ ዜጋዋ እንደሆነ ግልፅ ነው፡፡ ጓድ መንግስቱ ይሄን ለማሰብ አልፈለጉም፡፡ የሶማሊያው ዚያድ ባሬ እንኳን ኢትዮጵያን ሲወሩ ሲሉ ራሳቸው ያሰሩትን ጄኔራል ራሳቸው ፈትተው የአዛዥነቱን ቦታ ሰጥተውታል፡፡ ዚያድ ባሬ ፕሬዝዳንት ከመሆናቸው በፊት ጄኔራል ስለነበሩ ጥቅሙን ያውቁ ስለነበር ነው ቢባል እንኳ መንግስቱ ይሄን ማወቅ አይችሉም ብሎ ማሰብ ያከብዳል፡፡ ግን አፍሪካዊ መሪ ናቸውና የአፍሪካውያን መሪዎች የጋራ መፈክር የሆነውን "በስልጣን የመጣ ዓይኑ ይውጣ"ን መፎክር ነበረባቸውና ፎከሩት፡፡

ይህ ድርጊት የደርግ የመጨረሻው መጀመሪያ ነው፡፡ የእነዚህ ጄኔራሎች መገደል በቁም ለነበሩት ጄኔራሎች እንዴት ያለ ስሜት እንደሚፈጥርባቸው፣ ምን አይነት የሞራል ዝቅጠት እንደሚያስከትልባቸው አልታሰበም፡፡ ከዚህ በኋላስ ጦርነትን ለማሸነፍ እንዴት ይታሰባል? ለሁሉም ጦር ሠራዊት ተስፋ አስቆራጭ ሆነ፡፡ በተለይ የቀሩት ጄኔራሎች

ስርዓት ያለው ግልፅነትን መፍጠር፣ ለእያንዳንዱ ግለሰብ ከፍተኛ ትኩረት መስጠት፣ ሰብዓዊ ክብሩን መጠበቅ፣ በራሱ መቆምና በራሱ መተዳደር እንደሚችል መንገር፣ በሶሻሊስታዊ ስርዓት ያልተቆጠበ የንግድ ስራን ማበረታታትና ታላቋን ሶቭየት በየዘርፉ በፍጥነት ማዘመን..." የሚል ሆኖ፤ በግርድፉ ሲታይ በጎ አስተሳሰብ መስሎ ውስጡን ለቄስ የሚሉት አይነት መፈክር ቢሆንም፤ ጎርቫቾቭን "ያዲሲቷ ሩሲያ መሪ" ብሎ ህዝቡ አወደሰው፡፡ ምዕራባውያን ጎርቫቶቭ ምን እያለ እንደሆነ በጥልቀት ገብቷቸዋልና የብሪታኒያና የአሜሪካ መሪዎች ባልተለመደ ሁኔታ ጎርባቶቭን ደጋግሞ መገናኘት፣ መወያየት ትልቁ ስራቸው ሆነ፡፡

የግላስኖስትና የፔሬስትሮይካ ጥምር ፖሊሲ በሂደት የሶቭየትን ብቻ ሳይሆን የዓለምን የኃይል ሚዛን ሙሉ ለሙሉ ለወጠው፡፡ ታላቋ ሶቭየት ኃያልነቷ አክትሞ ለምዕራቡ ርዕዮት መንበርከክ ነበረባት፡፡

ሌላው አገር እንኳ በሶሻሊስት ስርዓት የሚገኙ አገራዊ ጥቅሞችን አጣጥሞ ሰላቆዬ ብዙም አይከነክንም፡፡ ለኢትዮጵያ ግን ደፍራ የማትጎነጨው ፅዋ ነበር፡፡ ፔሬስትሮይካ ስራ ላይ ከዋለ በኋላ፤ ሶቭየት በምስራቅ አውሮፓ አገሮች ላይ አሳርፋው የነበረውን ክንድ አነሳች፡፡ የኢኮኖሚ ትብብሯን አቆመች፣ የሚጠቅሟትንም የማይጠቅሟትንም ራስ ራስህን ቻል በሚል ግልፅነት በተሞላበት አገላለፅ እየገፈተረች ወደራሷ ተመለሰች፡፡ ምስራቅ አውሮፓ በለውጥ ማዕበል ተናጠ፡፡ የበርሊን ግንብ ፈርሶ ምስራቅና ምዕራብ ጀርመን ተቀላቀሉ፡፡

በሶቭየት ሶሻሊስታዊ ርዕዮት ተጠምቀው ለዘመናት የርዕዮቱ ታማኝ ሆነው ሲተዳደሩ የነበሩ የፖላንድ፣ የሮማኒያ፣ የቼኮዝላቫኪያ፣ የአልባኒያ ... ህዝቦች ኮሚኒስት መሪዎቻቸውን በአመፅ ከስልጣን አባረሩ፣ አሰሩ፣ ገደሉ፡፡

እነ ብሬዥኔቭ "የኢምፔሪያሊዝም ነፀብራቅ" እያሉ ሲያወግዙት የኖሩት ነገር ሁሉ በጎርቫቶቭ ተቃራኒ መፈክር ይበረታታ ጀመር፡፡

ፔሬስትሮይካ ኢኮኖሚያዊ ለውጥ የሚያመጣ፣ ግላስኖስት ፖለቲካዊ ነፃነት የሚያላብስ ትርጉም እንዳለው ግልፅ እየሆነ ሄደ፡፡ በግላስኖስት መፈክር በ14 ትናንሽ አገሮች ታጅባ በታላቅነት ስም ሶቭየት ኅብረት እየተባለች በገናናነት የቆየችው ሩሲያ የፌደሬሽን ውላቸውን ቀድዳ ጥላ በሠላም ሸኘቻቸው፡፡ አገራቱ የየራሳቸውን ባንዲራ መልሰው አነሱ፡፡ እነዚህ አገሮች ኮሚኒስት መሪዎቻቸውን በአመፅም በምንም አስወግደው ሌላ ባለሥልጣን ሲተካ የምዕራብ ዓለሙን ርዕዮት ለመከተል አማተሩ፡፡ ምዕራባውያንም እቅፍ ድግፍ አድርገው ተቀበሏቸው፤ በካፒታሊዝምም አጠመቋቸው፡፡



በፔሬስትሮይካ መፈክር መሠረትም የቅይጥ ኢኮኖሚን በመከተል ሩሲያ ብቻዋን የምትገፋ መስላ ቆየች፡፡ የቀዘቃዛው ጦርነት ማክተም የዚህ መፍክር ውጤት ሆኖ እንደትልቅ ጀብደኛ ጎርባቶቭ ተወደሰበት፡፡

በአሜሪካና በእንግሊዝ ጉትጎታ የመፈክሩን ውስብስብነት በፍጥነት እንዲገላልጥ የተመከረው ጎርባቶቭ፤ "እሺ" አለ፡፡ ከአነሳሱ በበጎ ታይቶ የነበረው መፈክር የሶሻሊስት አራማጅ አገሮችን ሁሉ አጠቃሎ በአሜሪካና በእንግሊዝ ጎተራ ከተታቸው፡፡ ከዚሁ ጋር ታላቋ ሶቭየት ፈራረሰች፡፡ ለዚህ ተግባሩ ነው ጎርቫቶቭ የኖቤል ሽልማት የተሸለመውና ከሽልማቱ ጋር በተሰጠው ገንዘብ ሚሊየነር ሆኖ ህይወቱን በተደላደለ መንገድ መምራት የቀጠለው፡፡ የጎርባቶቭን ክህደት የተረዳው የሶቭየት ሠራዊት በመሪው ላይ አደመ፡፡መፈንቅለ መንግስትም ሞከረ፤ ሆኖም ወዲያው አድማው ተበትኖ ሙከራውም ከሸፈ፡፡ ጉርባቾቭ ይህን ካደረገ በኋላም ስልጣኑን ለቦሪስ አስረክቦ ከጨዋታ ሜዳው ወጣ፡፡

በሶቭየት አንጋችነት ህልውናቸውን መስርተው የነበሩ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ አገሮች ሶቭየት ስትፈራርስ በድንገት ክልትው፣ ክልትው አሉ፡፡

መንግስቱ ኃይለማርያም በዙምባቡዌ ሐራሬ ሆነው ለጣሊያናዊው ጋዜጠኛ ለሪካርዶኦሪዚዮ ይህን ጉዳይ በተመለከተ የገለፁለትን ከራሳቸው አንደበት እናድምጥ፡፡

"... ጎርባቶቭን የማውቀው ገና ወጣት የማዕከላዊ አባል ሳለ ነው፡፡ ፖሊት ቢሮ ሳይገባ በፊት" ... መንግስቱ በእርጋታና በጥርጣሬ የተሞላው እንግሊዝኛቸው፤ የሶቭየት ጉዳይ ሲነሳ ለወጥ ይልና ፊጣን ይሆናል ይለናል ሪካርዶ ኦሪዚዮ፡፡

"... ጎርባቶቭ ሲመለከቱት ጥሩ ሐቀኛና ለሶሻሊዝም ታማኝ ሰው ይመስል ነበር፡፡ ለእኔ የነበረው ስሜትም ወዳጃዊና የጋለ ነበር፡፡ ይሁንና በ1985 ስልጣን ላይ ፊጥ ብሎ ከወጣ በኋላ ግን ፔሬስትሮይካና ግላስኖስት ማለት አመጣ፡፡ በዚህ ጊዜ ታዲያ ስለሁኔታው በጥልቀት ለመረዳት በማሰብ አዲስ አበባ ሆኜ ቀጠሮ ለመያዝ ስልክ ደወልኩለት፡፡ ምን እየተሰራ እንደሆነና የሁለቱን መፈክሮች ትርጉምም ለመረዳት ወደ ሞስኮ አቀናሁ፡፡ ሁለቱ ቃላቶች መፈክሮች ይሁኑ እንጂ ምንነታቸውን አልተረዳሁም ነበር፡፡ ለምን? ቢባል ደግሞ መልሱ እንኳን እኔ ቀርቶ የሶቭየት ህዝብም ስላልተረዳቸው ነው፡፡ እናም ጓድ ጎርባቶቭ፤ እርስ በርሳችን ግልፅ እንሁን፡፡ የራሳችንን አቅጣጫ በጊዜ ለማስተካከል እንዲያመቸን የአቅጣጫ ለውጥ ካለ ይነገረኝ፡፡ የናንተ ጥንካሬ ጥንካሬያችን፣ ድክመታችሁ ድክመታችን ነው አልኩት፡፡"

ጎርባቶቭ ይህን የግል ሚስጥሩን ለሶሻሊዝምና ለሶቭየት ታማኝ ለሆኑት ለመንግስቱ መንገር አልፈለገም፡፡ ስለዚህ ሣቅ አለና "ጓድ

መንግስቱ አያስቡ፣ ከማርክሲዝም ሌኒኒዝም ርዕዮት አንዲት ሚሊሜትር እንኳ አላፈገፍግም፡፡ በሶሻሊስታዊ የስራ ውጤታችን እኮራለሁ፡፡ ወደፊትም የምኮራ ነኝ" አላቸው፡፡

"ከዓመታት በኋላ" አሉ መንግስቱ፤ ረጋ ባለና በተቆጠበ አንደበታቸው "ከዓመታት በኋላ አማጺያኑ ወደ አዲስ አበባ በመግስገስ ላይ እንዳሉ እርዳታ በመሻት ስልክ ደወልኩለት፡፡ ለጥያቄዬ የሰጠኝ መልስ፤ እንረዳሃለን አንተ ብቻ በፅናት ቁም፡፡ ሊነቅፉህ ይችላሉ፤ ሆኖም በታሪክ ውስጥ እንደ ትልቅ መሪ የሚያስቆጥርህ ትልቅ ስራ ለኢትዮጵያ ሠርተሃል፡፡ ጥንታዊውን ዘውዳዊ አገዛዝ በመገርሰስህና በመካከለኛው ዘመን የእድገት ደረጃ ላይ የነበረችውን ሃገርህን ዘመናዊ እንድትሆን በማድረግህ በታሪክ ውስጥ ተገቢ ስፍራህን ይዘሃል፤ የሚል ነበር፡፡ ግብዝ! አሁን ለዚህ የኖቤል የሠላም ሽልማት ይሰጡት? ለጠላቶች መሣሪያ እያቀበለ እኔን በቃላት ይሸነግለኛል፡፡ እየዋሸኝ እንደሆነ ስለገባኝ ከዚያ ቀን በኋላ ዳግመኛ አልደወልኩለትም፡፡ ማን ወዳጃችን፡ ማን ጠላታችን እንደሆነ እንኳ ለመለየት ባለመቻላችን መጥፎ ጊዜ እየተቃረበ ለመሆኑ ጠቋሚ ነበር"

መንግስቱ ሞስኮ ችላ ካለቻቸው በኋላ ፊታቸውን እንደገና ወደ ዩ.ኤስ. አሜሪካ አዞሩ፡፡ "... ፕሬዝዳንት ማን ነበር ስሙ? .... ማን ነበር .... ካርተር? አይደለም ቆየኝ ... ማን ነበር ከእሱ በኋላ የነበረው ...? እዎ አስታወስኩት ሮናልድ ሬጋን ነው፡፡ ሬጋን እኔን ለመርዳት እምቢ አለ፡፡ ሬጋንና ጐርቫቶቭ ማለት ለእኔ ሁለት ገፅታ ያለው አንድ ሠይጣን ማለት ናቸው! ጐርቫቶቭና ሬጋን ፀረ እድገት የሆነ ሴራ አንድ ላይ አሲረዋል፡፡ ጐርቫቶቭ የካደው እኔን መንግስቱን ብቻ ሳይሆን መላው ዓለምንም ነው፡፡ ያፈራረሰውም ሀገሩን፡ መላውን ዓለም አቀፍ ሶሻሊስት ንቅናቄ ማለትም ኮሚኒስቱንና ብሔራዊውንም ጭምር ነው፡፡

ስልጣን ላይ የወጣው በሶቭየት ኅብረት ኮሚኒስት ፓርቲ አካባቢ የሰፈነውን ሙስና በጽኑ ለመዋጋት እንደሚፈልግ በማሳመን ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ፓርቲውን ከአደጋ ለማዳን የሚያስችል ምንም አይነት የስርዓት ማሻሻያ ወይም ለውጥ ለማድረግ አልፈለገም፡፡ ስለዚህ አመጣጡ ፓርቲውን ለማፈራረስ እንጂ ለማዳን አልነበረም፡፡ ..." /TALK OF THE DEVIL 2003/

መንግስቱ እንዳሉት ምንም የቅድመ ዝግጅት ሁኔታ እንዳይደረግ ጐርቫቶቭ በማለሳለስ እያዘናጋ 4 ዓመታት ያህል ከቆየ በኋላ፤ ነገሩ ሁሉ በምስራቅ አውሮፓ ትርምስምስ እየወጣ መሆኑን ያዩት መንግስቱ ጉዳዩ ግልፅ እየሆነላቸው ሄደ፡፡

ታዲያ በቅፅበት ምን ማድረግ ይቻላል? ሲያብጠለጥሉት የኖሩትን ካፒታሊስት አገር ተደግፈው አያንሰራሩ ነገር፡፡ የርዕዮት ለውጥ



ለማድረግም እጋዥ አገር በተለይ በራሷ ላልቆመች አገር የግድ ያስፈልጋታል፡፡ በነበረው አይቀጠል ነገር ባለቤቱ ተንሻፈፈ ብሎ የጣለውን ጫማ እኛ አጥልቀን እየተባለ ተቃዋሚው በዛ፡፡ እንዲያ ሲያዜሙለት፡ ሲፎክሩ ሲሸልሉበት፣ ተፈጥሮን በቁጥጥር ስር እናደርጋለን እያሉ ሲዝቱበት የነበረው ርዕዮት፣ ሶሻሊስታዊ ኢትዮጵያን እንገነባለን ተብሎ በሕገመንግስቱ ሳይቀር እንቀፅ የተበጀለት ... ሕገመንግስቱ በፀደቀ ገና ሁለት ዓመት ሳይደፍን ሶሻሊዝም ሲሞት መንግስቱ እንዴት ግራ ይገባቸው? መጥኔ! እንግዲህ ምን ይሁን? ያን መራራ ፅዋ ከመጎንጨት በቀር ምርጫ የለም፡፡

ከጥቅምት 29 እስከ ህዳር 2 ቀን 1981 ዓ.ም ተደርጎ በነበረው የኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ 9ኛ መደበኛ ስብሰባ ድርጅቱ የመጨረሻ ግቡ የሶሻሊስት ስርዓቱን መገንባት እንደሆነ ቢያረጋግጥም፤ የግል ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት መጠነኛ እርምጃዎች ለመውሰድ ተገዶ ነበር፡፡ በዚህም ከመንግስት ጋር በጋራ የሚሰሩ ኢንቨስተሮችን፣ የአነስተኛ ኢንደስትሪዎችንና የሆቴል አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶችን የካፒታል ጣራ ከፍ ለማድረግ ተሞክሯል፡፡ ነገር ግን በዓለም አቀፍ ደረጃ እየተካሄደ ከነበረው ለውጥ ጋር ሲመዛዘን ፈፅሞ በቂ አልነበረም፡፡ ስለዚህ የነገሩን ቁርጥ መሆን የተረዱት ጓድ ፕሬዝዳንት የካቲት 28 ቀን 1982 ዓ.ም በተካሄደው የኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ 11ኛ መደበኛ ስብሰባ ላይ የሶሻሊስት ግንባታ መርሀን በመሠረዝ የቅይጥ ኢኮኖሚ መርሐግብርን አፀደቁ፡፡ በፖለቲካው በኩልም ኢሠፓን የተለያዩ የፖለቲካ አመለካከቶችን ሊያቅፍ በሚችልና "የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ አንድነት ፓርቲ (ኢዴእፓ) በተሠኘ አዲስ የፖለቲካ ፓርቲ እንደሚተካ አረጋገጠ፡፡ ምንም ቢባል ግን ረፍዶ ነበር፡፡

እነ አጥናፉ አባተ የሞቱበት፣ የሞቱለት ወይም የተገደሉበት የ"ቅይጥ ኢኮኖሚ" ጭቅጭቅ ቀን ከጨለመ በኋላ ፀደቀ፡፡

በጣም የሚገርመው ነገር ደግሞ ፕሬዝዳንት መንግስቱ እነዚህን ውሣኔዎች ሲያፀድቁ የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላቱ በስብሰባው እለት እየተነሱ ሶሻሊዝምን እየወረፉ በሚያስቅ አነጋገር አዳራሹን በሣቅ ሲንጡት መዋላቸው ነው፡፡ ይህንንም ያይን እማኞች ደጋግመው ተርከውታል፡፡

ሻለቃ ካሣዬ አራጋው ከስብሰባው መሃል ብድግ ብለው፤ "ይሄንን የሰው አገር ደበሎ አውልቀን እንድንጥል በማድረግዎ፤ በታሪክ ትልቅ ስፍራ የሚያሰጥዎ ነው ...!" እያሉ ሲናገሩ፤ ፕሬዝዳንት መንግስቱ ቀበል አድርገው፤ "ደበሎ አልከው ካሣዬ? ሰው አበላሸው እንጂ ቢያንስ ለደሃው ገበሬ የኑሮ ለውጥ ያመጣ ስርዓት ነበር፡፡ የአንድ እናት ልጆች እርስ በርስ የተላየፍንበት የብዙ ሺህ ሰዎች ደም የዋጀው ክቡር ዓላማ ነበር" አሉ በቁጭትም፤ በትዝብትም፡፡ ቀጥሎ ኮሎኔል እንዳለ ተሠማ ተነሱና፤

"በእውነቱ ጓድ ሊቀመንበር እርስዎ ትናንት በተናገሩት የአዲስ አበባ ህዝብ ከደስታው ብዛት በውስኪ ሲራጭ ነው ያነጋው…" ሲሉ ተሰብሳቢው ሁሉ በሣቅ እውካካ፡፡

ፕሬዝዳንቱ በምፀት ሣቅ ጥርሳቸውን ብልጭ አድርገው አንገታቸውን ደፉ፡፡

ዳቦ ጠፍቶ ህዝቡ በየዳቦ ቤቱ ወረፋ ይዞ በሚፋለምበት ወቅት ስለውስኪ መራጨት ማውራት አስቂኝም፣ አሳዛኝም ነዋ፡፡ ያም ሆኖ ከ5 መቶ ሺ. ብር በላይ ካፒታል ያለው ግለሰብ ነጋዴ እንዳይኖር ተደርጎ የነበረው ደንብ ከፍ ማለት እንደሚችል በመታወጁ ደስ የተሰኙ ባለሃብቶች መኖራቸው አይዘነጋም፡፡

የሆነው ሆኖ ተግባራዊ ለውጡን በውል ያላወቁትን፤ ነገር ግን በቃሉ ፍቅር ወድቀው የተዋደቁለትን ርዕዮት ሳይወዱ በግድ መነጠላቸው ሳያንስ፤ ትናንት የወርቅ ካባ ያሉትን በቅፅበት ደበሎ እያሉ ሲፎልሉበት ማየት እስተዛዛቢ ነበር፡፡

ከዚህ በኋላ ልዩ ልዩ የሙያ ማኅበራት እየፈራረሱ፣ የተደራጁ አምራቾች ጥሪታቸውን ተከፋፍለው እየተበታተኑ፣ ከመንግስት ቁጥጥር ውጪ ሆነው በየመሰላቸው የግል መንገድ መንጎድ ጀመሩ፡፡ ሁሉም ነገር አቅል አጣ፡፡ ፓርቲ ነሽ፣ ወታደር ነሽ ምንድነሽ .... እየተሰነጣጠቀ፣ እየተፍረከረከ ሄደ፡፡ ትዕዛዝ ከላይኛው አካል ወደታች ደርሶ መፈፀሙ አጠራጣሪ ሆነ፡፡ አማፅያኑ በየቀኑ አዳዲስ ግዛት መያዝ ቀላል ተግባር ሆነላቸው፡፡ ጦሩ ሽሽትን ስራዬ ብሎ ያዘው፡፡ ለደርግ መንግስት የሚወግን ታማኝ ወዳጅ አገር ጠፋ፡፡ የመንግስቱ ታማኞች እንደድሮው ማኅብደድ፣ ለመወደድ መጣጣራቸውን አቆሙ፡፡ በአጭሩ ፕሬዝዳንት መንግስቱ ብቻቸውን ሲፍገመገሙ ነው ቀሪዋን አንድ ዓመት ያሳለፉት ማለት ይቻላል፡፡

እንዲያውም ብርቱ ሆነው እንጂ እንደነገሩ አስደንጋጭነት ቢሆንማ፤ "ግላስኖስት፣ ፔሬስትሮይካ፣ ግላስኖስት ፔሬስትሮይካ…" እያሉ አብደው በአደባባይ ቢዞሩ ማን ይፈርድባቸው ነበር? የሰው ብርቱነት ይሄን አይነት ክስተት በመቋቋሙ ይረጋገጣል፡፡

የደርግ መንግስት ፍፃሜ እና የኢህአዴግ ድል

ዛሬም ድረስ ሁሉንም ወገን የሚያስገርም ጥያቄ ነው፡፡ ሌላው ቀርቶ የቀድሞ የኢህአዴግ ታጋዮች የጦር ግንባር ትዝታቸውን ሲተርኩ፤ ".... አሁን ላይ ሆኜ ሳስበው ... ያንን የሚያክል ግዙፍ ሠራዊት፣ ታንኩ፣ ጀቱ፣ ...." ዋ...ይ ዘይግርም! በማለት ከመደነቃቸው ብዛት የጀመሩትን ዓረፍተ ነገር መቋጨት ይሳናቸዋል፡፡

ደርግ በአፍሪካ ውስጥ ግዙፍ የተባለ ሠራዊትን ነበር ያደራጀው፡፡ በ12 ቢሊዮን ዶላር ወጪ እንዲገነባ የተደረገው የደርግ ሠራዊት በመቶ



ሺዎች የሚገመት የሰው ኃይልም ነበረው፡፡ ሽንፈቱ የዳዊትንና የጎሊያድን ፍልሚያ የሚያስታውስ ነው፡፡ ምንም እንኳ ተቃዋሚዎቹ የአሜሪካን መጠነ ሰፊ ድጋፍ ቢያገኙ፤ ታጋዮቹ ራሳቸው የዓላማ ፅናታቸውና ጀግንነታቸው አስደናቂ ቢሆን፣ የአመራሮች ብቃት ባያጠያይቅ፣ በውጊያ ስልት ከደርግ ቢበልጡ፣ እንዴት ለድል በቁ? ብሎ ከመጠየቅ የቦዘነ የለም፡፡

ለድል የበቁበትን ምክንያት የሚገልፁ ዘርፈ ብዙ ትንታኔዎች ቢሰጡም፤ "ምንም ይሁን፤ ቢያንስ እንኳን ደርግ በነበረው የሰው ኃይል ብዛት ብቻ እንዴት አላሸነፈም?" የሚል መከራከሪያ መነሳቱ አይቀርም፡፡ ጥያቄውን ተገቢ ጥያቄ እንዲሆን ያደረገ የሰፋ ያለመመጣጠን ልዩነትም ነበራቸው፡፡

ቢሆንም፤ መፈንቅለ መንግስቱ ያስከተለውን መዘዝ ሳንዘነጋ፤ የደርግ መንግስት የሰው ኃይሉን በአግባቡ ተጠቅሞ እንዳያሸንፍ እንኳ ሌላ መሰናክል ተፈጥሮበት ነበር፡፡ ይህም የወኔ፣ የስንቅና የትጥቅ፣ እንዲሁም የጀግንነት ችግር ያልነበረበትን ግዙፍ ሠራዊት ወኔውን ሰልቦ፣ ጀግንነቱን ነጥቆ፣ ሥነልቦናው እንዲላሸቅና ተፍረክርኮ እንዲቀር የሚያደርግ ተግባር መፈፀሙ ሲሆን፤ ከራሳቸው ከቀድሞ ባለሥልጣናት እንደበት እንደሚከተለው እንሰማዋለን፡፡ ነገር ግን የታጋዮቹን ጀግንነት ለማደብዘዝ እንዳልሆነ በቀላሉ መታወቅ አለበት፡፡ የነሱ ጀግንነት የሚያጠያይቅ አይደለምና፡፡ከዚያ ባለፈ ለማሳየት የሻትኩት የጃንሆይን ዙፋን ያወዛወዘው ሙስና መሆኑን እንዳየነው ሁሉ፤ ለደርግ መንግስት ውድቀት መፋጠንም ሙስና የማይናቅ አስተዋፅኦ ማበርከቱን ነው፡፡

በ1996 ዓ.ም ከእስር የተለቀቁት ሻምበል ተስፋዬ ርስቴ ዛሬም ድረስ በእስር ላይ ሆነው ዓለም በቃኝ የሚገኙ የቀድሞ የደርግ ባለሥልጣኖችን ሁሉ እነጋግረው በ2001 ዓ.ም ለሕትመት ካበቁት "ምስክርነት" ከተሰኘው መጽሐፍ ውስጥ የተገኙ ምላሾችን ነው የምናየው፡፡

ፀሐፊው "የምድር ጦር ወታደራዊ ደህንነት ኃላፊ የነበሩትን ኮሎኔል ታምራት ይልማን ስለመከላከያ እዛዦች ችግር፣ ስለጦር አለቆች ደካማነትና በንቅዘት የተዘፈቁ መሆናቸውን በሚመለከት ላቀረብኩላቸው ጥያቄ መልስ ሰጥተውኛል" ይላሉ፡፡

ኮሎኔል ታምራት ይቀጥላሉ፤ "... ደርግ የጦሩን ድርጅት ለማሟላት በገፍ ያቀርባል፡፡ ነገር ግን የነበሩት የጦር አዛዦች ደግሞ በከፋ ዘረፋ ላይ ተሰማሩ፡፡ አዛዦቹ የጦሩን ቀለብ ያለ ይሉኝታ ለነጋዴ ሸጡት፡፡ ስኳር፣ የጦር ቀለብ፣ ልብስ፣ ጫማና ካልሲ ሳይቀር በጠራራ ፀሐይ መርካቶ፣ ወሎ፣ ደሴና አስመራ ለነጋዴ ተቸበቸበ፡፡ ንቅዘት ነውር መሆኑ የቀረ መሰለ፡፡ የጦሩ መኪናዎች ከነተሳቢዎቻቸው የጦር ድርጅቶችን ጭነው መርካቶ ለገበያ መቅረባቸው ይፋ ሆነ፡፡…"

ይህን ጉዳይ እነ ጄኔራል ተስፋዬ ገብረኪዳን በጦሩ ስም የፍጆታ እቃዎች እያወጡ ለነጋዴ ይሸጡ እንደነበር የምድር ጦር ወታደራዊ ደህንነት ኃላፊ ኮሎኔል ታምራት ይልማ፣ የበፊት የአገር ውስጥ ንግድ ሚኒስትር የነበሩት ኮሎኔል መርሻ ወዳጆም አጉልተው እንደሚናገሩት ፀሐፊው

ይገልፃሉ፡፡ ምላሻቸው ይቀጥላል፤ "... የጦር ድርጅት፣ ቀለብ፣ የሠራዊቱ ደሞዝ፣ መድሐኒት ማናቸውም ለሠራዊቱ የሚጠቅም ነገር ሁሉ እየተዘረፈና እየተሸጠ ወደግል ኪስ ገባ፡፡ የጦር አለቆች ከሾፌሮች ጋር በመመሳጠር ነዳጅ፣ ስኳር፣ ጥይት፣ መድሐኒትና ሌሎች ለውጊያ ጠቃሚ የሆኑ ነገሮችን ጭምር ለሚወጋቸው ጠላት ያለይሉኝታ ሸጡት፡፡ (የደብረብርሃንና የደብረታቦር ግንባር በዚህ የበለጠ ታዋቂ ነበሩ)

"ማሰልጠኛ ማዕከሎች የንቅዘትና የዘረፋ ማዕከሎች ሆኑ፡፡በሰልጣኞች ስም ከማከፋፈያ ድርጅቶች የማይጠየቅና የማይገዛ የፍጆታ ሸቀጥ አልነበረም፡፡ በጦሩ ስም የከፈን ጨርቅና የሬሣ ሳጥን ጣውላ ሳይቀር ተገዝቶ ተሸጧል፡፡ የጦሩ አለቆች የጦሩን ደሞዝ፣ ለቤተሰቡ የሚያደርገውን ተቆራጭ ነግደውበታል፡፡በወለድ ለነጋዴ እያበደሩ ከብረውበታል፡፡ ባንክ ውስጥ በስማቸው እያስቀመጡ ወለድ አግኝተውበታል፡፡በዚህ አድራጎታቸውም በሚመሩት ጦር ላይ የአስተዳደር በደል አድርሰውበታል፡፡ወደ መውደቂያችን መቃረቢያም የጦር አለቆች የቀን ጅብ ሆኑ!" በማለት ይናገራሉ፡፡ለዘረፋና ለጥቅም ሲባል የዘመቻ እቅዶች ይነደፉና እንዲከሽፉ ይደረግ እንደነበርም ጨምረው ይገልፃሉ፡፡

"በሞቱ፣ በጠፉ፣ ወይም በተማረኩ የጦሩ አባላት ስም የሐሰት ሠነድ እየተፈረመ ስርቆት ተፈፅሟል" (ገፅ 409)

ፀሐፊው የምድር ጦር የአስተዳደርና ፋይናንስ መምሪያ መኮንን ለነበሩት ለዘገየ ልዑል ሠገድ ሙስናን በሚመለከት ጥያቄዎችን አዘጋጅተው ይሰጧቸዋል፡፡ ምላሽ ሰጭው መልሱን ለመስጠት ቃል ገቡና በሦስተኛው ቀን እንዲህ አሏቸው፤ "ወንድሜ ሆይ! ቃሌን በማጠፌ አዝናለሁ፡፡ የማስታውሳቸውን የዘረፋና የንቅዘት ጉዳዮች በቅደም ተከተል መዝግቤ ልሰጥህ ካልኩ በኋላ መልሼ ሳነባቸው ህሊናዬን አስጨነቁት፡፡ ዘራፊ ሰዎችን በተራ ደርድሬ ያሰለፍኳቸው መሰለ ታየኝ፡፡ በዚህ የተነሳ የፃፍኩትን ቀድጄ ጣልኩት" በማለት መለሱ፡፡ ይሄን ያህል ዘግናኝና ሰመግለፅ የሚቸግር ከአእምሮ በላይ የሆነ ዝርፊያ ተጧጡፎ ነበር፡፡

የበርካታ ሌቦችን ስም ዝርዝር ቀደው የጣሉት ሰው በቃላቸው በጥቂቱ መልስ ለመስጠት ሞክረዋል፡፡ እንዲህ ይነበባል፤ "እኛ የሠራዊቱ መሪዎች እጅግ አሳፋሪ ታሪክ አለን፡፡ እገሌ ከእገሌ ሳይባል የጦር ማሠልጠኛ ማዕከላት አዛዥ የነበሩ፣ የፋይናንስና የድርጅት፣ የስንቅና ትጥቅ መምሪያ መኮንኖች፣ ደመወዝ ከፋዮችና የትራንስፖርት ክፍል ኃላፊዎች፣ ሐረርጌ ውስጥ ከ"ኩልሚስ" (ከሶማሊያ ታጋዮች) ጋር ተመድበው በማንኛውም ደረጃ የሰሩ የሠራዊቱ አባላት እጅግ ከፍተኛ ዘረፋ አካሂደዋል፡፡

"ማንኛቸውም የስራ ኃፊነታቸውን ትተው በቀጥታ በዘረፋ ተሰማርተው ነበር፡፡ የጦር አለቆችን በስም ጠርቼ ስነግርህ በጣም ቅር ይለኛል፡፡ የፈፀሙትን ዘረፋ መጠን መገመት ለህሊና ይከብዳል! ሠነድ ተደልዟል፣ የሞቱ ወታደሮች ደመወዝ ተበልቷል፣ ሌላው ቀርቶ የጦር አዛዦች የመንግስት ባንክ ዘርፈዋል፡፡ የባህርዳር ንግድ ባንክና የደብረብርሃን ንግድ



ባንክ ቅርንጫፎችን መጥቀስ ይቻላል፡፡ (ዘራፊው ጄኔራል በቦንብ ጋየ ብለው ዋሽተው ነበር) "... የፈንጅ ማምከኛ የሚሆኑ አህዮች መግዣ ተብሎ ከመንግስት ግንዘብ እየወጣ ተዘርፏል፡፡ ሳስበውና ሁኔታው ከፊቴ ሲመጣ ያስጨንቀኛል፡፡ በአገርና በህዝብ ላይ ከፍተኛ ደባና በደል ተፈፅሟል" ብለዋል፡፡ በነገራችን ላይ የሁሉም ባለሥልጣናት ግልፅ የሆኑ ተመሣሣይ የእምነት ቃሎች ናቸው፡፡ በተጨማሪም ቀድሞ በየግንባሩ ሲታገሉ የቆዩና የሲቪል ህይወት የጀመሩ ተራ ወታደሮችና ባለሌላ ማዕረጎችም እየዘገንናቸው የሚተርኩት እውነታ ነው፡፡ ሌላው ፀሐፊው እስር ቤት ውስጥ ያነጋገሯቸው የምድር ጦር ስንቅና ትጥቅ መምሪያ መኮንን የነበሩትን ብርጋዴል ጄኔራል ሰብሰቤ ንጋቱን ነው፡፡

ጄኔራሉ፤ "... አለቆች ብዙዎቹ መጠን የሌለው ስግብግብነት አጠቃቸው፡፡ ለጦሩ ስንቅ ይቀርቡ የነበሩና ገበያ ያላቸው ስንዴ፣ ስኳር፣ ሻይ ቅጠል፣ ጤፍ፣ የመሣሠሉትን መሸጥ የተለመደ ሆነ፡፡ ስኳር "ገፍትር" የሚል ስም ወጥቶለት ለሠራዊቱ ከማደል ይልቅ ለነጋዴ መገፍተር፣ መቸብቸብ የተለመደ ሆኖ ነበር፡፡ ለጦሩ ቀለብ ተብሎ ወደ ጢጣ ወሎ የተላከ የሠራዊት ስንቅ ደሴ ከነጋዴ መጋዘን ውስጥ ሲራገፍ ተይዟል፡፡ ለጦሩ ቀለብ በዋናነት የሚቀርበው ጤፍ ነበር፡፡ ጤፍ ማቅረብ ችግር ስለነበር 40 በመቶ ጤፍ፣ 35 በመቶ ስንዴ፣ 25 በመቶ ማሽላ ወይም ዘንጋዳ ተቀናጅቶ እንዲፈጭና እንጀራ እንዲሆን ይደረግ ነበር፡፡ የአገዳ የእህል ውጤት የሆነ ዱቄት መነፋት ስላለበትና፤ ሲነፋ በኩንታል ከሰባት እስከ አስር ኪሎ ሊጎድል ስለሚችል ተስተካክሎ እንዲላክ ተወስኖ ነበር፡፡ ነገር ግን የጦሩ ቀለብ አቅራቢ መኮንኖች ዱቄቱን አያስነፉትም፤ የማያስነፉትም ለስርቆት እንዲመች ነበር፡፡ ሳይነፋ እንጀራ ሁን ሲሉት እህል እህል አይልም፡፡ ጦሩም ሳይበላ ተዋጋ ይባላል! ችግሩ እየታወቀ እርማት አይደረግም፡፡ ስርቆቱ ከታች እስከ ላይ በሰንሰለት ስለነበር አጥፊዎች አይጋለጡም፡፡ ቅጣት አይደርስባቸውም፡፡

"በወሎ ጢጣ የነበሩ የጦሩ አለቆች ለጠላት የከባድ መሣሪያ ጥይት ጭምር ሸጡ፡፡ ቀለብ የሚሰፈርለት በበጀት የሚታወቅ የኢትዮጵያ ሠራዊት 300,000 /ሦስት መቶ ሺ/ ደርሶ ነበር፡፡ ለቀለቡም መንግስት በዓመት ብር 344,000,000 /ሦስት መቶ አርባ አራት ሚሊዮን ብር/ ይሰፍር ነበር፡፡ የአዛዦቹ ዘረፋ ይሉኝታ አጥቶ ነበር፡፡" በማለት ሁኔታውን ዘርዝረውታል፡፡ ሌሎች ጄኔራሎችም ይሄንኑ አረጋግጠዋል፡፡

"... በተለይም የደርግ አባሉ ሌተናል ጄኔራል ተስፋዬ ገብረኪዳን መጀመሪያ የመከላከያ ሚኒስትር፣ በኋላ የኤርትራ ራስ ገዝ ዋና አስተዳዳሪና የጦሩ የበላይ አዛዥ ሆነው ዓይን ያወጣ ዘረፋ ይፈፅሙ ስለነበር ብዙ ከፍተኛ የጦር መኮንኖች ተከተሏቸው፡፡

"ከጄኔራሉ ጋር እጅና ጓንት ሆነው ዘረፋውን አጧጧፉት፤ በጦሩ ስንቅ ማመላለሻ ከባድ መኪኖች፣ በአውሮፕላንና በመርከብ ያለይሉኝታ ለነጋዴ ሸቀጥ አዲስ አበባና አስመራ እያመላለሱ ሸጡ" የደርግ አባሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ፍቅረስላሴ ወግደረስ ተስፋዬ ገብረኪዳንን ሲገልጿቸው፤ "ደፋር፣

ዘራፊ፣ ከሰው ተግባቢ፣ ለምንም ነገር ደንታ ቢስ፣ ደስታና ፈንጠዝያ ወዳጅ..." በማለት ነው፡፡ /ገጽ 412/

ከዚህም ባለፈ "የሦስት ማዕዘን ፅዝ" አደረጃጀት ለጦሩ ሽንፈት ተጨማሪ ሚና እንደነበረው በብዙዎች ተገልጿል፡፡ የፖለቲካውም ሆነ የወታደራዊው ደህንነት ባለስልጣናት እርስ በርስ ይወነጃጀላሉ፡፡

ብርጋዴር ጄኔራል ግርማ አየለ፤ "የጦር አዛዦች የሙያ ብቃት የጎደላቸው፣ ሌሎች አመራሮች አብዮቱን እምርረው የሚጠሉ፣ መጀመሪያ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደርን፣ በኋላ የኢትዮጵያ ህዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊኩን ለመጣል የታገሉ የአገር ፍቅር የነጠፈባቸው ዘራፊዎች! ናቸው" ብለዋቸዋል፡፡ ሦስት የተለያዩ አዛዦች ሲመደቡም መረጃው እያፈተለከ በጠላት እጅ በቀላሉ ይገባ ነበር፡፡

እንዲህ ነው፡፡ እንዲህ ሆኖ ደመወዜ ለቤተሰቤ ይሰጥልኛል ብሎ ህይወቱን በየግንባሩ ሊሰዋ የተዘጋጀ ሠራዊት ከተማ ያሉ ወላጆቹ ሲራቡ፣ ለአገሩ የሚከፍለው ዋጋ ከንቱነቱ እየገባው ሲሄድ ሠራዊቱ ባይፍረከረክ እንጂ ቢፍረከረክ ምኑ ይገርማል? መልሱ ይሄ ነው፡፡

የእርስ በርስ ጦርነት እንደመሆኑ መጠንም ተዘርፎ የሚቸበቸበው ስንቅና ትጥቅ፣ እንዲሁም አልባሳት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለተጋዳላዮች ይደርስ ነበር፡፡ በተለይ ስኳሩ የኢህአዴግ የጀርባ አጥንት ነበር፡፡

ይህ ሁሉ ሲሆን በሙስና በጠላቶቻቸውም በወዳጆቻቸውም ፈፅሞ የማይታሙት ፕሬዝዳንት መንግስቱ፤ ሁኔታውን መቆጣጠር ተስኗቸው ከወዲያ ወዲህ እየተንከላወሱ ማስልጠኛዎች እንዲገነቡ፣ በፍጥነት ምልመላ እንዲደረግ፣ ለጦሩ ስንቅና ትጥቅ እንዳይጓልበት ይጣጣሩ ነበር፡፡ ህዝቡ ከጎናቸው እንዲሆን በተለያየ መንገድ የማሳመንና የመቀስቀስ ተግባራቸውን ቀጥለውበት ነበር፡፡

ለምሳሌ ነገሩ ሊያበቃ ሦስት ወር በቀረው ጊዜ "የሻዕቢያ የወያኔና የኦነግ የተባበረ ውጊያ መንግስትን ከመጣልና ፕሬዝዳንቱን ከማባረር አልፎ ህዝብን የመከፋፈልና ሌላ ግዛት የመፍጠር ዓለማ ያለው መሆኑን ተረድተናል...." የሚሉ በተለያዩ አህጉራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በግልና በፖለቲካ ድርጅቶቻቸው አማካኝነት ህዝቡ የአማፅያኑን ውጊያ እንዲያወግዝ ጥሪ አቅርበው ነበር፤ ይህን መሠረት በማድረግም የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ውጊያውንና አሜሪካ ለአማፅያኑ የምታደርገውን ድጋፍ በጽኑ ተቃውመው ሠላማዊ ሰልፍ ወጡ፡፡ ይህን ያዩት መንግስቱ የተማሪው ወኔ ሳይበርድ በቀጥታ ወደ ስድስት ኪሎ ዩኒቨርስቲ ጎራ በማለት፤ "በቃላት ማውገዝ ብቻ ሳይሆን ከአብዮታዊ ሠራዊቱ ጎን ተሰልፋችሁ ገንጣይና አስገንጣዮችን መዋጋት አለባችሁ፡፡ እነሱ እዚህ ሰሜን ሸዋ ጅሁር ደርሰው ትምህርት ነው? ሠላማዊ ሠልፍ ነው? ወይስ እንደወያኔ ወጣቶች መዋጋት ነው ያለባችሁ? ተነሱ እንጂ ጎበዝ!" በማለት ቀስቅሰው አብዛኛው ተማሪ ፈቃደኝነቱን ገልጾ ወደማሠልጠኛ ካምፕ ገብቶ ነበር፡፡ ግን ረፍዷል፡፡ በዘረፋ የተሰማሩ አመራሮች ከውጊያው ይልቅ ለሌብነቱ ልዩ ትኩረት



ስለሰጡ፤ በየግንባሩ ሽንፈት፣ በሽንፈቱም ላይ ሌላ ሽንፈት እየተደራረበ ሄደ፡፡ በአጭር አገላለፅ ከ1980 እስከ 1983 ዓ.ም ድረስ በነበሩት ጊዜያቶች የተካሄዱት ጦርነቶች ለአማፅያኑ አሸቻጋሪ የነበሩ መሆናቸው ባይካድም፣ በጣም አስቸጋሪ ግን አልነበሩም፡፡ እንዲያውም በእስር ላይ የሚገኙ የቀድሞው የጦር አዛዦች እንደሚሉት ከሆነ፤ የመጨረሻዎቹ ሦስት ዓመታት አማፅያኑ ከትግራይ አዲስ አበባ ለመድረስ የወሰደባቸው ጊዜ ነው ባይ ናቸው፡፡ ምንም ተባለ ምን ሻዕቢያና ወያኔን የሚያቆማቸው ኃይል አልተገኘም፡፡

ፕሬዝዳንት መንግስቱ ኃይለማርያም መንግስታቸው ከወደቀና እሳቸውም በሽሽት ዙምባቡዌ ከሄዱ በኋላ፤ "እኔ የታገልኩት ከሻዕቢያ ጋር ነው፤ ወያኔ ጎርፍ ያመጣው ድንጋይ ነው" ብለው ተሳልቀዋል፡፡

እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ወያኔ ጎርፍ ያመጣው ድንጋይ አልነበረም፡፡ እርሳቸውም ይሄንን አሳምረው ያውቁታል፡፡ ስለዚህ ለማለት የፈለጉት "ወያኔን ብቻውን ማሸነፍ እችል ነበር፤ ግን ሻዕቢያ ሲያብርለት ሳላሸንፈው ቀረሁ" እንደማለት ነው፡፡

ይህችን የ"ጎርፍ" ምሳሌ ስለሰጡን እያመሰገነን ጎርፉ እንዴት እየተንፎለፎለ የደርግን መንግስት እንደጠራረገው በአጭሩ ለማየት እንሞክር፡፡

በእርግጥም ድርጊቱ በጎርፍ የሚመስል ነው፡፡ ጎርፉ የመነጨው ከኤርትራ በርሃ ነው፡፡ ገድቦ ለማስቀረት የተሞከረውም እዚያው ነበር፡፡ ሳይሆን ቀረና የናቅፋን ሰንሰለታማ ተራራ አጥለቅልቆ፣ አፋቤትን አዳርሶ ለመረብ ወንዝ ገበረ፡፡

ከዚያ የተነሳው የሕወሓት ጎርፍም ኃይሉን ጨምሮ ያገኘውን ሁሉ እየጠራረገ ሽሬ ደረሠ፡፡ የደርግ ሰራዊት ጎርፉ ሽሬ መድረሱን ሲሰማ ከመጥለቅለቅ አደጋ ራሱን ለማዳን የትግራይን ግዛት በ15 ቀን ጊዜ ውስጥ ለቆ ወጣ፡፡ ማስቀረት እንደማይችል ስለተረዳም ምንም አይነት የመገደብ ሙከራ አላደረገም፡፡ ትግራይን ነፃ ለማውጣት የተነሳው ድርጅት "ህዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ" ሕወሓት ግቡ የነበረችውን የትግራይ ግዛት ሙሉ በሙሉ ቢያጥለቀልቃትም፤ ጎርፍ ነውና፤ ጎርፍ ደግሞ አንዴ ከላይ ከተነሳ ቁልቁል ከመውረድ በቀር ሌላ ምርጫ የለውምና፤ ወረደ ... ጋራ ሸንተረሩን፣ ሜዳ ገደሉን እያዳረሰ አማራ ክልል ሲገባ፤ እዚያም ያገኘውን "ኢህዴን"ን (በኋላ ብዓዴን) ከእንግላንግሉ ጠራርጎት ቀጠለ፡፡ ከላይ ከሰሜን የተነሳው ጎርፍ እንዲህ በፍጥነት ነጉዶ ነጉዶ በምስራቅ ኢትዮጵያ በሐረርጌና ባሌ፣ በምዕራብ ኢትዮጵያ በወለጋ አካባቢ ረጋ ብሎ ይወዛወዝ ከነበረው ሐይቅ ከኦነግ ጋር ተገናኝቶ ከሩቅ የመጣ ጎርፍና ረግቶ የቆየ ሐይቅ የሚያደርጉትን አይነት የሠላምታ ልውውጥ አደረጉ፡፡ ጎርፉ ከላይ፣ ሐይቁ ከስር ሆነው ወዲያ .... ወዲህ ... ሲናጡ የተፈጠረው ማዕበል ፕሬዝዳንት መንግስቱን አሽቀንጥሮ ጣላቸው፡፡ በዚህ መሰሉ ጎርፍ ተገፍትረው ዙምባቡዌ የገቡት መንግስቱም፤

ባሉበት ሆነው ስለጎርፍ ተረቱ፤ ተረቱንም ተጠቀምንበት፡፡ ማን በጎርፍ እንደመጣ፣ ማን በጎርፍ እንደወጣ ተረዳንበት፡፡

ከሕወሓት በኋላ በመጨረሻዎቹ ዓመታት ደርግ ላይ ያመፁ ብሔረተኛ ድርጅቶች "ኢህዴን" (ኢትዮጵያ ህዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ) እና "ኦነግ" (ኦሮሞ ነፃነት ግንባር) ነበሩ፡፡ ስለእነዚህ ድርጅቶች መጠነኛ ቅኝት አድርገን ወደ ተነሳንበት ርዕሰ ጉዳይ እንመለሳለን፡፡

የኦሮሞ ህዝብ የብሔራዊ ማንነት ጥያቄ በተደራጀ መልኩ ለመጀመሪያ ጊዜ የተቀሰቀሰው "የቱለማና ሜጫ ራስ ገዝ ማኅበር" በጃንሆይ ዘመን በጥር ወር 1955 ዓ.ም ሲመሠረት ነው፡፡ ሆኖም የማኅበሩ ዓላማ የነፃነት ትግል ሳይሆን፣ በኦሮሞ ግዛቶች የትምህርት፣ የጤና፣ የመገናኛና ሌሎች የመሠረተ ልማት አውታሮች እንዲገነቡ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት ነበር፡፡ በወቅቱ በኦሮሞ ስም ማኅበሩ ይቋቋም እንጂ የአባላቱ ምልመላ የደቡብ ተወላጆችንም ያካተተ ነበር፡፡

የማኅበሩ ፕሬዝዳንት የነበሩት የፖሊስ ሠራዊት አዛዥ ሆነው የተሾሙት ብርጋዴር ጄኔራል ታደሰ ብሩ ስለነበሩ የጃንሆይ መንግስት ስጋት ቢያድርበትም እንቅስቃሴያቸው ሠላማዊ ነው ብሎ በማሰብ ተወት አድርጓቸዋል፡፡ በዚህ መሐል በ1959 ዓ.ም በጥቅምት የጃንሆይ የንግስ በዓል ላይ የግድያ ሙከራ ለማድረግ ሲያሴሩ ተገኙ ተብለው ተወነጀሉ፡፡ አስተባብለው ታለፉ፡፡ ብዙም ሳይቆይ በሲኒማ አምፒር ቦምብ ሲፈነዳ የማኅበሩ አባላት ተጠያቂ ሆኑ፡፡ አቀናባሪዎቹ ጄኔራል ታደሠ ብሩና ሌላው አባል ሙቶ አለቃ ማሞ መዘምር ናቸው በሚል ውንጀላ ማኅበሩ እንዲፈርስ ተደረገ፡፡ ድርጊቱ ከተፈፀመ በኋላ የተሰወሩትን ጄኔራል መንግስት አድኖ ይዞ ለፍርድ አቀረበና የሞት ፍርድ አሰወሰነባቸው፡፡ ውሣኔው ግን በይግባኝ ወደ እድሜ ልክ ተቀየረ፡፡

ከአብዮቱ በኋላ ጄኔራሉ እንደ ሌሎች የፖለቲከኛ እስረኞች በምህረት ቢለቀቁም፤ ከህቡዕ የኦሮሞ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት ስለፈጠሩና፣ ደርግ አካሄዳቸው ስላለማረው "የመሬት አዋጁን በመቃወም" በሚል ክስ በ1967 አስረሸናቸው፡፡በዚያወቅት ይሙት በቃውን የፈረሙት ሊቀመንበሩ ተፈሪ በንቲ ነበሩ፡፡

ቀጥሎ በቀድሞው የሜጫና ቱለማ ማኅበር አባል በነበረ ግለሰብ መስራችነት "የኢትዮጵያ ብሔራዊ ነፃነት ግንባር" በሚል ስያሜ በ1963 ዓ.ም አካባቢ ተቋቁሞ የነበረው ሲሆን፤ እንዳች ተግባር ሳያከናውንና በአግባቡም መደራጀት ሳይችል በራሱ ጊዜ ተበተነ፡፡

በአብዮቱ ወቅት የፖለቲካ መፈክሩ "ኅብረብሔራዊነት" ላይ ያተኮረ ስለነበር የኦሮሞ ብሔራዊ እንቅስቃሴዎች አልታዩም፡፡ ጥቂት የኦሮሞ ምሁራን በኅብረብሔራዊ ድርጅቶች ውስጥ በተለይም በመኢሶንና በኢጭአት ውስጥ ስለነበሩ ራሳቸውን እንደ ወኪል፣ ህዝቡም እንደተወካይ ካላያቸው በቀር ሌላ እንቅስቃሴ አልነበረም፡፡



ከዚህ አንፃር ለመጀመሪያና ለመጨረሻ ጊዜ በኦሮሞ ህዝብ ስም የሚንቀሳቀስ ድርጅት የተገኘው በ1968 ዓ.ም ኦነግ (ኦሮሞ ነፃነት ግንባር) ሲቋቋም ነው፡፡

ኦነግ ከተመሠረተ ጀምሮ ከሻዕቢያ የማቴሪያልና የቴክኒክ ድጋፍ እየተቸረው በሐረርጌ፣ በባሌ፣ በወለጋና በአካባቢው መሽጎ የሽምቅ ውጊያውን ቢቀጥልም፤ በውስጡ በነበረው የእርስ በርስ ሽኩቻና፤ በህዝቡ ውስጥም ራሱን ለማስረፅ የሚያስችል ዘዴ በአግባቡ ባለመቀየሱ የዓመታት ትግሉ የሕወሓትን ያህል ደርግን መፈታተን አላስቻለውም፡፡ ነገር ግን ከተመሠረቱበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ደርግ የፍፃሜ ዘመን ድረስ በደርግ ላይ ካመፁ ብሔረተኛ ድርጅቶች ውስጥ አንዱ ሆኖ ቆይቷል፡፡ ደርግን ለመጣልም በደቡብ ምዕራብ ያለውን ይዞታውን በማስፋትና ከወያኔ ጦር ጋር ተቀናጅቶ በማጥቃት የድርሻውን ተወጥቷል፡፡ ይህ ድርጅት ከአብዮቱ በኋላ በደርግ ላይ፣ ከደርግ ውድቀት በኋላ በኢህአዴግ ላይ ህቡዕ እንደገባ ዛሬም ድረስ አለ፡፡

ሌላው በ1973 ዓ.ም የተቋቋመው "የኢትዮጵያ ህዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ" (ኢህዴን) ሲሆን፣ ከተበታተነው የኢህአፓ ሠራዊት ተርፈው በሰሜን ወሎ በትጥቅ ትግል ይንቀሳቀሱ የነበሩ ታጋዮች ስብስብ ነው፡፡ ሕወሓት አማራ ክልል ሲደርስ ቅንጅት ፈጥረው አብረው ታግለዋል፡፡ የደርግን ፍፃሜ ለማፋጠን ከፍተኛ መስዋዕትነትም ከፍለዋል፡፡ የአነሳስ መሠረቱ ግን ከስሙም እንደምንረዳው ኅብረብሔራዊ እንጂ፤ ብሔረተኛ አልነበረም፡፡

እንግዲህ ሕወሓት ከትግራይ ግዛት ድል በኋላ ያለው አዝማሚያ ሁሉ ቀላል እንደሆነ ሲረዳና አገራዊ አጀንዳ ማውጣት ግድ ሲሆንበት፤ የዚህ አጀንዳ አስፈፃሚ ይሆናሉ ብሎ ያሰባቸውን ድርጅቶች፤ አነሳሳቸው ብሔረተኝነት ከነበረ እሰየው፤ ኅብረብሔራዊም የሆኑ ካሉ በብሔረተኝነት ማጥመቅ በሚል መነሻ "የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር" (ኢሕአዴግ)ን ወደማዋቀር አመራ፡፡

በዚህ መሠረት ኢህአዴግ የተዋቀረው በተለያዩ ድርጅቶች ጥምረት ሲሆን፤አባል ድርጅቶቹም ሕወሓት፣ ኢህዴን (ከድል በኋላ ብዓዴን ተብሎ የአማራን ህዝብ እንደሚወክል ይፋ ያደረገው)፣የኦሮሞን ህዝብ ይወክላል ተብሎ የተቋቋመው (የኦሮሞ ህዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት) ኦህዴድ፣እንዲሁም የተማሩ የደርግ ሠራዊት መኮንኖች የተሰባሰቡበት የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ መኮንኖች አብዮታዊ ንቅናቄ(ኢዴመአን)ነበሩ፡፡

በእነዚህ በኢህአዴግ ስር ከተካተቱ ድርጅቶች ውስጥ ሕወሓትና ኦህዴድ በብሔረሰብ ላይ የተዋቀሩ ሲሆኑ፤(የመጀመሪያው በትግራይ፣ ሁለተኛው በኦሮሞ)ኢህዴንና ኢዴመአን ኅብረብሔራዊ ናቸው፡፡

ከማይታወቀው ኦህዴድ ይልቅ የሚታወቀው ኦነግ በህዝቡ ዘንድ ተቀባይነት እንዳለው ቢታወቅም፤ ከኦነግ ጋር ከድል በኋላ ግንባር ለመፍጠር ሳይቻል ስለቀረ ሕወሓት ኦህዴድን ለማቋቋም ተገደደ፡፡ ስለዚህ ከኦነግ የጦር ምርኮኞችና በኦነግ ካልታቀፉ ምሁራን የተውጣጡ አባላትን መልምሎ

አቋቋሙ፡፡ ኢህዴንም ከድል በኋላ ብዓዴን ነኝ ይበል እንጂ በአማራ ክልል ውስጥ ሲታገል በነበረበት ጊዜ የሚታወቅበት ስም ኢህዴን የሚለው ነበር፡፡

በመኮንኖቹ ስም የተቋቋመው ኢዴመአን የጦር ምርኮኞችን በፖለቲካ መድረክ ዙሪያ ከማሰባሰብ ያለፈ የፖለቲካ ሚና ሳይኖረው የከሰመ ነው፡፡

እነዚህን የድርጅት አነሳሶችና አወቃቀሮችን ከወዲሁ ቀድሞ መግለፅ ያስፈለገው፤ ኢህአዴግ ኢህአዴግነቱን ያወጀውና በዚህ ስምም እየተጠራ ትግሉን የቀጠለው የትግራይን ግዛት በቁጥጥሩ ስር ካደረገ በኋላ፤ እዚያው ትግራይ ላይ ቅድመ የቤት ስራውን አጠናቆ ለአዲሱ ኢህአዴጋዊ አጀንዳ ኢህአዴጋዊ ትግሉን ቀጥሎ እየተጠራበት መምጣቱን ለማስገንዘብና፤ አዲስ አባባንም የተቆጣጠረው በዚሁ ስሙ መሆኑን ከወዲሁ ለመጠቆም ነው፡፡

በአሁኑ ጊዜም ብዓዴን፣ ኦህዴድ፣ ሕወሓት፣ ከድል በኋላ የተቋቋመው የደቡብ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ደህዴን) እና ሌሎች አጋር ድርጅቶች ተጣምረው የሚገኙበት "ኢህአዴግ" መንግስት ሆኖ አገር እየመራ እንዳለ ይታወቃል፡፡ ይህ በግልፅ የመታወቁን ያህልም በ1993ዓ.ም በውስጡካጋጠመው ክፍፍል ውጭ እንደ ድርጅትም የበላይነቱ እንደተጠበቀ ነው፡፡በግለሰብ መሪዎች ደረጃም እንደዚያው፡፡

እናም ኢህአዴግ ትግሉን ቀጠለ፡፡ የደርግ መንግስት የብሔረተኞችን ጦርነት መቋቋም እየተሳነው ሄደ፡፡

የደርግ መንግስት ውድቀት እጅግ በተፋጠነ መንገድ የቀጠለው ከ1980 ጀምሮ ነው፡፡ እስከ 1983 ድረስ ያለ የሌለ ኃይሉን ተጠቅሞ ለመፋለም ከመሞከሩም ባሻገር፤በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ አዳዲስ ምልምሎችን በውድም በግድም በፍጥነት ወደተገነቡ የማሰልጠኛ ጣቢያዎች እያጋዘ በለብለብ ስልጠና ወደ ጦር ግንባር ቢያሰማራም፤ የጠበቀውን ውጤት ሊያገኝ አልቻለም፡፡

በተለይ በየካቲት ወር 1982 ዓ.ም ሻዕቢያ ከፍተኛ እልቂት በታየበት ጦርነት የደርግን የባህር ኃይል ደምሰሶ ምፅዋን ሲቆጣጠር መንግስት የባህር ወደቡን ከማጣቱም ሌላ፣ ትግራይ ሙሉ በሙሉ በሕወሓት እጅ ስለነበረች ኤርትራ ውሰጥ ለሚገኘው ጦር ስንቅ የማቅረቢያ መንገድ አጣ፡፡

በዚህ መሀል ኢሕአዴግ ወደ አዲስ አበባ የሚያረማምዱትን ተከታታይ ዘመቻዎች ከፈተ፡፡ በ1982 ዓ.ም የመጀመሪያ ወራት የጎንደር ክፍለሀገርን ለመቆጣጠር የከፈተው ዘመቻ ለጊዜው ቢከሽፍበትም "ጉና" በተባለው ተራራ ላይ በተደረገ ጦርነት በብዙ የህይወት መስዋዕትነት ደብረታቦርን ተቆጣጠረ፡፡ ቀጥሎም ደቡብ ወሎ ውስጥ "መራኛ" በተባለው ስፍራ ባገኘው ወሣኝ ድል ወደ ሰሜን ሸዋ ለመረማመድ ቻለ፡፡



እነዚህን ድሎች ከተቀዳጀ በኋላ ኢሕአዴግ አዲስ አበባን ለመቆጣጠር ወኔ በሚቀሰቅሱ ታሪካዊ ስሞች የሰየማቸውን የጦር ዘመቻዎች አወጀ፡፡

በ"ዘመቻ ቴዎድሮስ" ኀጀምን ተቆጣጠረ፡፡ በቀድሞው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ውስጥ መሪ እንቅሳቃሽ በነበረውና የወሎ ተወላጅ በሆነው በዋለልኝ መኮንን ስም "ዘመቻ ዋለልኝ" ብሎ በሰየመው ዘመቻ የደርግን ሠራዊት ከወሎ ክፍለሀገር ጠራርጎ አስወጣ፡፡ ቀጥሎ "ዘመቻ ቢሉሱማፍ ወልቂጡማ" (በኦሮምኛ ነፃነትና እኩልነት ማለት ነው) በሚል ስያሜ ባዘመተው ጦር ከጎጃም ወደ ወለጋ መሸጋገር ቻለ፡፡

እነዚህን የመሳሰሉ ወሣኝ ድሎች በፍጥነትና በተከታታይ እየተቀዳጀ መጥቶ የኢህአዴግ ሠራዊት አዲስ አበባን ከሰሜን፣ ከምስራቅና ከምዕራብ አቅጣጫ ከበባት፡፡ የደርግ ሠራዊት በብዙ ግንባሮች ጠንክሮ ለመከላከል ሞከረ፡፡ በተለይ አምቦ ከተማ ላይ የነበረው ሠራዊትና ህዝቡ የኢህአዴግን ጦር አላሳልፍ ብሎ ከፉኛ ተፋታትኖት ነበር፡፡ የደርግ መንግስት ከጽኑ የመከላከል ተግባሩ ጎን ለጎን ከ1970ዎቹ ጀምሮ ዞር ብሎ አይቶት የማያውቀውን፣ በተቀናቃኞቹ ዘንድም ተቀባይነት ያልነበረውን የሠላም አማራጭ ማማተር የጀመረው ሁኔታው እዚህ ደረጃ በደረሰበት ጊዜ ነበር፡፡

እነዚህ ግንባር የፈጠሩ ብሔተኞች አፍሪካ ውስጥ ታይቶ በማይታወቅ የረጅም ዓመታት የሽምቅ ውጊያ ግዙፉን የደርግ ሠራዊት ደረማምሰው፤ እዚህ ደረጃ ደርሰው፤ ሙሉ ለሙሉም ወታደራዊ ድልን ከተጎናፀፉ በኋላ የሠላም ድርድርን ይፈልጋሉ፣ ይቀበላሉ ብሎ ማሰብ የዋህነት መሆኑ ቢታወቅም፤ በተለይ አፍቃሬ ኢሕአዴግ የነበረችው አሜሪካ የመጀመሪያዋ አደራዳሪ መስላ ለመታየት ሞከረች፡፡ በዚህ መሠረት የመጀመሪያው የሠላም ድርድር በቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዝዳንት በጂሚ ካርተር አማካኝነት በ1982 ዓ.ም መጀመሪያ በአትላንታ፣ ቀጥሎ በናይሮቢ የሠላም ድርድሮች ተካሄዱ፡፡ ይህም በሻዕቢያና በደርግ መንግስት መካከል የተካሄደ ነው፡፡ በምን እንደሚደራደሩ ግን ሻዕቢያም፣ ደርግም፣ አደራዳሪው ቡድንም ቢጠየቁ መልስ የላቸውም፤ ሊኖራቸውም አይችልም፡፡ ስለዚህ ለደንቡ ያህል ጥቂት ተጨቃጭቀው ሳይግባቡ ተለያዩ፡፡

ቀጥሎ በመጋቢት 1982 በደርግና በሕወሓት መካከል ሮም ላይ በቀድሞው የኢጣሊያ አምባሳደር ሸምጋይነት የተደረገው የሠላም ድርድር ሲሆን፤ ሕወሓት "ሌሎች የኢህአዴግ አባል ድርጅቶችም መሳተፍ አለባቸው" የሚል መከራከሪያ በማንሳቱ፤ ቀድሞ የከሸፈው ድርድር ውጤት አልባ ሆኖ ተበተነ፡፡

ሦስተኛውና የመጨረሻው አስገራሚ የሠላም ድርድር ለንደን ላይ በደርግና በኢሕአዴግ መካከል የተካሄደው ነው። በ1983 ዓ.ም በግንቦት ወር የመጀመሪያ ቀናቶች "የለንደን ጉባዔ" ተብሎ በሚታወቀውና በአሜሪካ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትርና የአፍሪካ ጉዳዮች ኃላፊ በነበሩት በሄርማን ኮኸን ሰብሳቢነት የተደረገው ሙከራ ላይ የኢትዮጵያ መንግስትን ልዑክ መርተው የሄዱት ባለቀ ሰዓት ሹመት የተሰጣቸው ጠቅላይ ሚኒስትር ተስፋዬ ዲንቃ ነበሩ። የመደራደሪያ አቅም ቀርቶ የማምለጫ መንገድ ባልነበራቸው ሁኔታ ለሰላም ድርድር መሰብሰባቸው ሳያንስ፤ ጉባኤው እየተካሄደ ባለበት ሰዓት ፕሬዝዳንት መንግስቱ አገር ጥለው መሄዳቸው ተሰማ።

ጂሚ ካርተርና ሄርማን ኮኸን ወደ አዲስ አበባ በተደጋጋሚ መጥተው ከመንግስቱ ጋር ውይይቶችን አድርገው ጨርሰዋል።

ስለዚህ ቀጣዩን ሂደት በደንብ ያውቁት ነበር። በተለይ ሚስተር ኮኸን ለንደን ላይ አደራዳሪ ሆነው ተቀምጠው በነበረበት ጊዜ ፕሬዝዳንት መንግስቱ ኃይለማርያም ግንቦት 13 ከአገር መውጣታቸውን ግንቦት 14 ጉባዔው ላይ ሲሰሙ የመገረም ፊት ያሳዩት ሲቀልዱ እንጂ ከልባቸው አልነበረም።

መጨረሻው ደረሰና ግንቦት 16 ቀን 1983 ዓ.ም ሻዕቢያ የዓመታት ዒላማው የነበረችውን አስመራን ሙሉ ለሙሉ በእጁ አደረጋት። ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ.ም ማለዳ ላይ የኢህአዴግ ሠራዊት አዲስ አበባን ተቆጣጠረ። በእለቱ የመንግስቱና የቤተመንግስቱ ታማኝ ጠባቂዎች ከድል አድራጊው ወገን ጋር ካደረጉት መጠነኛ የተኩስ ልውውጥ በስተቀር የተፈጠረ ሁከት አልነበረም።

ኤርትራ ውስጥ ይገኝ የነበረው ሁለተኛው አብዮታዊ ሠራዊት ከፊሉ ወደ ሱዳን፣ ከፊሉ ወደ ትግራይ ተበተነ። በአስመራና በአካባቢዋ የሚገኘው ጦርም ትጥቁን እየፈታ ለሻዕቢያ እጁን ሰጠ። በተመሳሳይ ሁኔታ አዲስ አበባ ውስጥ የነበሩ የመንግስት ከፍተኛ የጦር ባለሥልጣናት ምንም አይነት አውሮፕላን ከአዲስ አበባ እንዳይነሳና ሁሉም ባለበት እንዲረጋ ኢህአዴግ የሰጠው ማስጠንቀቂያ እንዳለ ሆኖ፤ በልዩ ልዩ ዘዴ ከአዲስ አበባ ወጥተው ለማምለጥ የሞከሩትን ባለሥልጣናት ግን የራሳቸው ባልደረባ የነበሩት የደህንነት ሚኒስትሩ አከሸፉባቸው። ከግንቦት 20 በፊት ከነበሩት ጥቂት ቀናቶች ጀምሮ የአዲስ አበባን መውጫና መግቢያ በአራቱም አቅጣጫ ጠባቂ መድበው የደርግ ባለሥልጣኖችን የማምለጥ ሙከራ በመግታታቸውም፤ ኤምባሲ ውስጥ ገብተው ከተጠጉትና በረቀቀ ዘዴ ማምለጥ ከቻሉት በጣት የሚቆጠሩ ባለሥልጣናት ውጪ ሁሉም እየተለቀሙ ተይዘው ወደ ወህኒ ወረዱ። ከረጅም ዓመታት የፍርድ ሂደት



በኋላም የሞት፣ የእድሜ ልክና ከ5 እስከ 20 ዓመት የሚደርስ የእስር ቅጣት ተወሰነባቸው።

ኢህአዴግ ሙሉ በሙሉ አገሪቱን ያዛት።የሻዕቢያና የኢህአዴግ የተባበረ የረጅም ዓመት ውጊያቸው በድል በተጠናቀቀ ማግስትም በ1984ዓ.ም ኤርትራ በሪፈረንደም ተገንጥላና ነጻ አገር ሆና የራሷን መንግስት መሰረተች። ኢትዮጵያም ሁለት አገር ሆነች።ከ7ዓመት በኋላም በኢሳያስ የሚመራው የሻዕቢያ መንግስት በ1990ዓ.ም የድንበር ትንኮሳ አድርጎ አንድ የነበሩ ሁለት አገሮች ወደ ጦርነት አምርተው በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ የኢትዮጵያና የኤርትራ ወጣቶች በጦርነቱ ሊያልቁ ግድ ሆነ።እነዚህ ሁለት መንግስታት ዛሬም ድረስ በክፉ ዓይን የሚተያዩ ሆነዋል።

ከደርግ ውድቀት በኋላ የኢትዮጵያ የቀድሞው ሕገመንግስት ተሽሮ ኢህአዴግ የራሱን ሕገመንግስት በ1987ዓ.ምአፅድቆ በብሔር ተኮር ፌዴራሊዝም አገሪቱን እየመራ ይገኛል።

ድል አድራጊው የኢህአዴግ መንግስት ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ.ም ስልጣን ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ ይህ መጽሐፍ ለሕትመት እስከበቃበት 2004 ዓ.ም ድረስ ኢትዮጵያን እያስተዳደረ ነው። ይህ ማለት ደግሞ ከ4 ዓመታት በኋላ የ25ኛ ዓመት የብር ኢዮቤልዩ በዓሉን ያከበራል ማለት ነው።

ወደጓድ ፕሬዝዳንት መንግስቱ ሽሽት እናመራለን።

የመጨረሻዎቹ ቀናት

ፕሬዝዳንት መንግስቱ ብዙ ጣሩ፣ ብዙ ዋተቱ፣ የቻሉትን ሁሉ ሞከሩ። ግን አቃታቸው። ሁሉም ፊቱን አዞረባቸው። የጦር አዛዦች አንጓጠጧቸው፣ ከዷቸው። ሚያዚያ ወር ላይ ክፉኛ ተስፋ ቆርጠው ነበር የታዩት። እናም ለመጨረሻ ጊዜ ከህዝባቸው ጋር ማውራት ፈለጉ። ሚያዚያ 11 ቀን 1983 ዓ.ም ሁሉም መስሪያ ቤቶች ተዘግተው ህዝቡ በየቤቱ ተቀምጦ የፕሬዝዳንቱን ንግግር በብዙሃን መገናኛዎች እንዲያደምጥ ተደረገና ጓድ መንግስቱ ግማሽ ቀን የፈጀ ንግግራቸውን አሰሙ። ልብ በሚነካ አገላለፅ የኢትዮጵያ ህዝብ አንድነቱን፣ ሉዓላዊነቱንና ነፃነቱን ለማጠንከር ያደረገውን መስዋዕትነት እያመሰገኑ፣ የጦሩን አሰላለፍና የጠላትን ግስጋሴ እየጠቆሙ፣ የአብዮቱን ፍሬዎች እየዘረዘሩ፣ ብርቱ የመከላከያ ኃይል ለመገንባት የተደረገውን ጥረት እያብራሩ ቀጠሉና፤ የኢትዮጵያ ህዝብ የሚቃጣበትን ማንኛውንም አይነት አፍራሽ ተግባር በውል እንዲመረምርና ማድረግ ያለበትን ነገር መወሰን እንደሚገባው አስገነዘቡ። ገለፃቸውን ሲደመድሙም "... በዚህ ገለፃዬ ውስጥ እንዲህ ይሁን፣ እንዲህ ይደረግ፣ የሚል ጥቆማና መሪ ሀሳብ ለማቅረብ አልፈለግሁም። ነገር ግን የመላውን የኢትዮጵያ ህዝብ ግልፅ

አቋምና ፈጣን ውሣኔ እጠይቃለሁ፡፡" ካሉ በኋላ የብሔራዊ ሸንጎውን አስቸኳይና ልዩ ስብሰባ የጠሩ መሆናቸውን ለህዝቡ አሳውቀው ወደ ትካዜያቸው ተመለሱ፡፡ ከንግግራቸው ውስጥ "ለኢትዮጵያ አንድነት የሚበጅ እስከሆነ ድረስ ስልጣን ይዞ የመቆየት ፍላጎትና ጉጉት የለኝም" የሚል ዓረፍተነገር ስለተካተተበት አዳማጩ ህዝብ "በቃ ስልጣን ሊለቁ ነው" የሚል ግመት ወስዶ ነበር፡፡ ግን አላሉም፡፡

መንግስቱ ሳያውቁት የጃንሆይን የመጨረሻ ትንቢት ፈፀሙት ማለት ነው፡፡ ጃንሆይ "ለአገር የሚጠቅም ነገር እስካለበትና፤ ህዝቡም የእኛን መወገድ ከፈለገ ..." ብለው ነበር፡፡ ሲቀጥሉም፤ "እናንተ ካልቻላችሁ ደግሞ የእናንተ ታሪክ እዚያ ላይ ይቆምና የእኛ ይቀጥላል...." ማለታቸውን አይተናል፡፡ አዎ፤ ሶሻሊዝም ቆሞ የጃንሆዩ ዘመን የአሜሪካ ካፒታሊዝም ቀጠለ...፡፡ ሚያዚያ 14 ቀን "ልዩ" የተባለው 3ኛው የብሔራዊ ሸንጎ ጉባዔ ተካሄደ፡፡ በጉባዔው አዳራሽ ግን የሸንጎው አባላት ብቻ አልነበሩም የታደሙት፡፡ ከተራ ሰው ጀምሮ እስከ ባሥልጣናት ድረስ ከ3ሺ በላይ ዜጎች ታድመው አዳራሹ ሞልቶ ቆመው የታደሙ ሁሉ ነበሩ፡፡ ስርዓት፣ ደንብ፣ ትዕዛዝ፣ መሪ፣ ተመሪ ብሎ ነገር በዚያ ሰዓት ፋሽኑ ያለፈ ከመሆኑም በላይ፤ የመንግስቱ ተፈሪነት ራሱ ቀርቶ እኩል የሚመሳለሱት በርክተዋል፡፡

ይሄንን ጉዳይ መንግስቱ በትዝታቸው ገልፀውታል፤ "አንድ ሰው ቀና ብሎ አይቶኝ አያውቅም ነበር፡፡ 17 ዓመት ሙሉ! በዚያ በመጨረሻው ሸንጎ ብቻ ተደፈርኩ፤ እነ ዶ/ር ኃይሉ አርአያ ሲፎልሉብኝ" ብለዋል፡፡

የሸንጎው ዓላማ በኢኮኖሚያዊና በወታደራዊ ጉዳዮች ላይ ተወያየቶ አስቸኳይ ህዝባዊ ውሣኔ ማሳለፍ የነበረ ቢሆንም፤ የፕሬዝዳንቱ 3 ሰዓት የፈጀ ንግግር ግን "እረ ጎበዝ ምን ይሻላል?" የሚል ሆኖ የሚጠቃለል ነው፡፡ "... ጠላት ሊቦጫጭቀን አሰፍስፎ ከበራችን ላይ ቆሟል፡፡ አሁን ችግሩ የአገር አንድነት ብቻ ሳይሆን የእያንዳንዳችንን ህልውና ፈተና ላይ የጣለ ሆኗል፡፡ በጉዳዩ ላይ ሰፊ ውይይት አድርገን የመፍትሄ ሀሳብ በጋራ ማመንጨት አለብን" በሚል የውይይት መድረኩን ከከፈቱ በኋላ ለ3 ተከታታይ ቀናት ውይይቱ ቀጠለ ፡፡

"ሠላማዊ መፍትሄ እየተፈለገ፤ ጎን ለጎን ደግሞ ለአንድነታችን ጠንክረን እንዋጋ" የሚለውና "የእርስ በርሱ ጦርነት የሚቆምበት ሠላማዊ መፍትሂ ይፈለግ" የሚለው ሀሳብ ተደጋግሞ ከታዳሚው ተሰነዘረ፡፡ እንዴት? ቢባል ግን መልስ የለም፡፡ ብቻ ግን ተሰብሳቢው እየተነሳ ያሻውን ማለት ጀመረ፡፡ እያንዳንዱ ሀሳብ ፕሬዝዳንቱን የሚያስከፋ ነበርና አፀኑ፡፡



አንድ ጄኔራል ተነሱና "ለምን የተኩስ አቁም ስምምነት አናደርግም? አሉ፡፡ ከአንድ የጦር ጄኔራል ይሄ ቃል መውጣቱ ያሳዘናቸው መንግስቱ "ይሄ ባንተ በመነገሩ አዝኛለሁ" አሉ፡፡

የባህር ኃይል አዛዥ ደግሞ "ህዝብ ካልፈለገን ለምን ስልጣን አንለቅም? ህዝብ እስከፈለገን ድረስ ብቻ ነው በሥልጣን መቆየት ያለብን" ሲሉ፤ ከባህር ኃይል አዛዥነታቸው በላይ የኢሠፓና የብሔራዊ ሸንጎው አባልም ስለነበሩ መንግስቱ በመከፋት "እኛም እንዲህ እንላለን እንዴ?" በሚል ቅሬታቸውን በፊታቸው ጭምር አሳዩ፡፡

ኮሎኔል ፍስሃ ደስታ ቀጠሉ፡፡ በግዕዝ የተናገሩት ንግግር ወይም የሰጡት ሀሳብ "የፈላ ውሃና ቀዝቃዛ ውሃ ቀርቦልሃል፤ ወደመረጥከው እጅህን ንከረው" የሚል ነው፡፡ ፕሬዝዳንቱ ቅስማቸው ቢሰበርም ጉባዔው ግን ቀጠለ፡፡ ከመንግስቱ እጠገብ የተቀመጡት ዶ/ር አበበ ዓለሙ ቀጠሉ፤ "የኢትዮጵያ ህዝብ ልጁን አጥባ፣ አጣቢውንም፣ ልጁንም ወደ ደጅ እንደምትደፋ ሰነፍ ሴት የሚሆን አይመስለኝም፡፡ ህዝቡ እኛን ከጠላ ሀገሩን ከእኛ ጋር ሊደፋት አይገባውም" በሚል "ስልጣን እንልቀቅ" አሉ፡፡ ተጨበጨበ፡፡

ተከታዩን ታሪካዊ ንግግር ያደረጉት አቶ አብርሃም ያዬህ የነበሩ ሲሆን፤ በቁጥር 2ቱ ነበር መጽሐፍ ገጽ 356 የተካተተው ገለፃቸው እንዲህ ይነበባል፤ "... እኔና ገብረመድህን በሬዲዮና በቴሌቪዥን ያን ሁሉ የለፈለፍነው መንግስቱ ኃይለማርያምን፣ ለገሠ አስፋውንና ተስፋዬ ወልደስላሴን ከውድቀታቸው ለማዳን አልነበረም፡፡ እነሱ ቢወድቁ ባይወድቁ የእኛ አጀንዳ አልነበረም፡፡ እንደፈቀዳቸው ይሁኑ፡፡ የእኛ ዋና አጀንዳ የኢትዮጵያ ህዝብ ሐቁን አውቆ የወያኔን ማንነትና ምንነት ተገንዝቦ ሴራውን ለማክሸፍ እንዲታገል ማንቃት ነበር፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ ይህን አልተገነዘበልንም፡፡ በወያኔ ጭብጥ ውስጥ ሲገባ ግን አብርሃምና ገብረመድህን የተናገሩት ለካ ይኸ ኖሯል? ብሎ በቁጭት ያስታውሰናል፡፡ ያኔ እሣት ሆኖ ያንገበግበዋል፡፡

አሁንም ስለአገራችን ስለኢትዮጵያ ብዬ እናገራለሁ፤ የእሷ ነገር ያሳስበኛል፤ ያሳዝነኛልም፡፡ ይህ የመጨረሻ ቃሌ ነው፡፡ ከዚህ በኋላ የምናገርበት መድረክ እንደሌለ አውቃለሁ፡፡ ሁሉም ነገር አብቅቷል፡፡ ወያኔ መምጣቱን ልንገራችሁ፡፡ ኤርትራን ያስገነጥላል፣ መሬት ቆርሶ ለሱዳን ይሸጣል፡፡ ይህን ልታውቁት ይገባል፡፡ ዛሬ የተናገርኩት የመጨረሻ ኑዛዜዬን ነው፡፡ ከአሁን በኋላ አንገናኝም፡፡ እኔ መሄጃ አለኝ፤ እሄዳለሁ፡፡፡ እያንዳንዳችሁ ግን ስለአገራችሁም፤ ስለራሳችሁም አስቡ..." በማለት ሲናገሩ አዳራሹ በፀጥታና በተመስጦ ነበር ያደመጣቸው፡፡

ቀጥሎ የላስታ አውራጃ እንደራሴ የሆኑት ቄስ? መነኩሴ? ተነሱና "... መቼም ይሄ የመጨረሻችን ነው፤ ከዚህ በኋላ አንገናኝም፡፡ ስለዚህ

የተሰማኝን ልተንፍስ..." አሉና ቀጠሉ "... እነዚህ ሰዎች (ኢህአዴጎች) እየታገልን ነው የሚሉት ሰፊውን ህዝብ ከጭቆና ለማውጣት በሚል ነው፡፡ ሌሎችም እንዲያ ይላሉ፡፡ እናንተም ወደ ስልጣን ስትመጡ እንዲህ ብላችሁ ነበር፡፡ ወንበሬቱን ካገኛችሁ በኋላ ግን ህዝቡ ተረሣ፡፡ እነዚህም ከጫካ መጥተው እርስዎ የተቀመጡባት ወንበር ላይ ሲቀመጡ ይህን ሰፊ የሚሉትን መከረኛ ሕዝብ ይረሱታል፡፡ እርስዎ ግን እዚችው ወንበር ላይ እንደተጣበቁ እንደ ቴዎድሮስ ሽጉጥዎን ጠጥተው እንደሚያልፉ አተማመንብዎታለሁ!" አሉ፡፡ የእኚህ ሰው ትንቢት ሙሉ ለሙሉ ባይሆንም በከፊል ግን ተፈጽሟል፡፡ መንግስቱ ሽጉጥ አልጠጡምና፡፡

በዚህ ንግግር መንግስቱ ሣቁ፡፡ በዚህ መልኩ ቀጥሎ ብዙ ብዙ ሀሳቦች፣ ሾርኒዎች፣ ዘለፋዎች፣ ተስፋ አስቆራጭ ትንበያዎች ሲንሸራሸሩ ከቆዩ በኋላ የፕሬዝዳንቱ የማጠቃለያ ሀሳብ፤ "... ደም እንደ ጎርፍ ይፈሳል፣ ህንፃዎች ይደረመሳሉ፣ ከዚህ በኋላ የሚሆነው ይሆናል..." የሚል ይዘት ያለው ሆኖ ቢጠናቀቅም ጉባዔው ከላይ እስከ ታች በሚወርድ ትዕዛዝ ተፈፃሚ የሚሆን ውሣኔ አሳልፎ ነበር፡፡ ውሣኔዎቹም ውይይት፣ ድርድር፣ የሠላም ኮሚሽን፣ ህዝባዊ የሆነ የክተት አዋጅ ... ወዘተ እንዲደረግ የሚያሳስቡ ቢሆኑም በአገር ውስጥም በውጭም ድጋፍ ቢቸረውም ረፍዷልና ሊተገበር አልቻለም፡፡ መንግስቱ የመጨረሻ ጊዜያቸው እንደደረሰ ስለተረዱም የመልሶ ማጥቃት ዝርዝር እቅዶችን ማውጣትና ጦሩን እየተዟዟሩ "በርቱ!" ማለታቸውን እርግፍ አድርገው ትተው በትካዜ ተዋጡ፡፡ ሚያዚያ 18 ቀን ባለቀለት ወንበር ላይ ሹመት ሰጡ፡፡ በዚህም ሌተናል ጄኔራል ተስፋዬ ገብረኪዳን የኢህድሪ ምክትል ፕሬዝዳንት፣ አቶ ተስፋዬ ዲንቃ ጠቅላይ ሚኒስትር፤ እንዲሁም ለሌሎች ተመሣሣይ ሹመት ከሰጡ በኋላ ሻምበል ለገሠ አስፋውንና ኮሎኔል ፍስሐ ደስታን በጡረታ አሰናበቱ፡፡

ሚያዚያ 19 "የአሜሪካ መንግስትና ህዝብ በኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት ፀንቶ መኖር ያላቸውን ጽኑ አቋም በድጋሚ በማረጋገጥ የአሜሪካ መንግስት የኢትዮጵያ ህዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ብሔራዊ ሸንጎ 3ኛ አስቸኳይ ጉባዔ ያሳለፈውን ውሣኔ የሚደግፍ መሆኑንና ለተግባራዊነቱም አስፈላጊውን ድጋፍ እንደሚሰጥ ያረጋግጣል..." የሚል መልዕክት ለፕሬዝዳንት መንግስቱ ደረሳቸው፡፡

ጉባዔው ያሳለፋቸው ዝርዝር ውሣኔዎች "አንድነት የፀናባት ኢትዮጵያን" ከማስቀጠል ጋር እንጂ ከመገንጠል ጋር ፈጽሞ የሚስማማ አልነበረምና አዲስ አበባን ከበው የያዟት ተቃዋሚዎች የሚስማሙበት አልሆነም፡፡

ሆኖም የአሜሪካን የይምሰል መግለጫ ተከትለው ሩሲያ፣ ቻይና፣ ካናዳ፣ ግብፅና ሌሎች አገራት የሸንጎውን ውሣኔ መደገፋቸውን ገለፁ፡፡



ኢትዮጵያውያኑም በሠላማዊ ሰልፍ ድጋፋቸውን አረጋግጠው፤ አማፅያኑን የሚደግፉትን አገራትም አወገዙ፡፡

በዝምታ ቀናቶችን አሳልፎ የቆየው ኢህአዴግ በውጭ ቢሮ ጽ/ቤቱ በኩል ተከታዩን መግለጫ ይፋ ሲያደርግ የሸንጎው ውሣኔም ሆነ ማናቸውም ዓይነት የሠላም ድርድሮች ሁሉ ከንቱነታቸው ግልፅ እየሆነ ሄደ፡፡

"ከኢህአዴግ የውጭ ቢሮ ጽ/ቤት የተሰጠ መግለጫ፡፡

"የኢህአዴግ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ከግንቦት 2 እስከ 4 ቀን 1983 ዓ.ም በነፃ መሬታችን ላይ አስቸኳይ ስብሰባ አካሂዶ ወቅታዊ ጉዳዮችን በሚመለከትና አስፈላጊ ውሣኔዎችን በማሳለፍ ተጠናቋል፡፡

አስቸኳይ ስብሰባው በአሁኑ ወቅት ደርግ፣ ኢሠፓና መሰሎቹ በአንድነት በመሰባሰብ የኢህአዴግ የሽግግር ፕሮግራም ተግባራዊ እንዳይሆን የተጠነሰሰ ሴራ በሚመለከት ሆኖ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ደርግ ያወጀው የሽግግር መንግስት ኢህአዴግንና ሌሎች ታጋይ ኃይሎችን በፀረ አንድነት ስያሜ በማግለል ደርግና የትምክህተኞች ኃይል ስብስብ ኢ.ዲ.ኅ.ቅ እና ሌሎችም ስልጣን ለመያዝ በአሜሪካ ኤምፔሪያሊዝም አይዞህ ባይነት በተለያዩ የውጭ አገር ከተሞች ሽር ጉድ እያሉ ይገኛሉ፡፡

የኢህአዴግ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባ የደርግ ሸንጎ ያሳለፈውን የሠላም ውሣኔ አልተቀበለውም፡፡ ኢህአዴግ በስመ አንድነት ወይም በወረራ የተመሠረተ የባርነትና የግዛት አንድነት የህዝብ አንድነት ይሁን ብሎ ለመከራና ለጭቆና አሳልፎ አይሰጥም፡፡ ማንኛውም ብሔርና ብሔረሰብ የራሱን ዕድል በራሱ በመወሰን ነፃ መንግስት መስርቶ ባስፈለገው መንገድ እንዲጓዝ ይበልጥ ኢህአዴግ ሲታገልለት የቆዩ ዴሞክራሲያዊ መንገድ ከመቼውም ጊዜ በላይ ፍቱን መፍትሄ መሆኑን አስምሮበታል፡፡ በኤርትራና በኢትዮጵያ ለ30 ዓመታት ሲካሄድ የቆየውን ጦርነት በተመለከተ ማንም ወሣኝ ሳይሆን የኤርትራ ቅኝ ግዛት ጥያቄ በሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ እልባት አግኝቶ ኤርትራውያን ከኢትዮጵያ ቅኝ አገዛዝ ቀንበር ተላቅቀው ነፃ አገራቸውን እንዲመሠርቱ ሁሉ ኢትዮጵያዊ አምኖበት መቀበል አለበት፡፡ ኢህአዴግ ያቀረበው አስተማማኝና አጥጋቢ መፍትሄ፣ ግልፅና ጠቃሚ ነው፡፡ ኢትዮጵያ አትቆራረስም ብሎ መጮህ ትርፉ ጦርነትና እልቂት ስለሆነ አንድነት ለብዝበዛና ለባርነት አሳልፎ የሚሰጥ መሣሪያ ከመሆኑ ባሻገር የህዝቡን ጥቅም ሊያስጠብቅ አይችልም፡፡ በዚህ ላይ ኢህአዴግ የሽግግር ፕሮግራም ብዙ የፖለቲካ ኃይሎች በነፃና ዴሞክራሲ የሚሳተፉበት፣ ህዝቡ በየድርጅቱ መሪነት እድሉን በራሱ ወደሚወስንበት መድረክ የሚያሸጋግር ፕሮግራም መሆኑን በድጋሚ አረጋግጧል፡፡

አስቸኳይ ስብሰባው በቅርቡ በአሜሪካ መንግስት አቀራራቢነት በደርግ፣ በኢህአዴግ፣ በኦሮሞ ነፃ አውጭ ግንባርና በህዝባዊ ግንባር ጎርነት ኤርትራ መካከል ለንደን ውስጥ ሊካሄድ የታቀደውን የሠላም ኮንፍረንስ የኢህአዴግ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በጥልቀት መርምሮ መሳተፍ ተገቢ ሆኖ ቢያገኘውም፤ በዚሁ የለንደኑ ኮንፈራንስ አቀራራቢ የሆኑት መንግስታትና ደርግም ሆነ ቀኞችና ወላዋይ ድርጅቶች ለኢህአዴግ ሠላማዊ ሽግግር ፕሮግራም ያላቸውን ጠማማ እመለካከት አስወግደው የሽግግር ፕሮግራሙን ሲቀበሉ ብቻ ነው፡፡ ይህ የኢህአዴግ የሽግግር ፕሮግራም ታማኙን በልዩ ልዩ መንገድ ያረጋገጠ ከመሆኑም በላይ ለህዝቡ የሚበጁ መፍትሄዎች ከዚህ የበለጠ ሌላ ተግባራዊ ሊሆን እንደማይችል የኢህአዴግ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በሚገባ አምኖበታል፡፡

ኢሠፓና መስሎቹ ያቀረቡት የሽግግር ፕሮግራም የህዝብን የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት በፍፁም የሚፃረር፣ በይዘቱም ለህዝቡ የማይበጅ ፀረ ህዝብ ነው፡፡ በዚህ መሠረት የለንደኑን ኮንፍረንስ የኢህአዴግ ዓላማ በተግባራዊነቱ ታምኖበት ተቀባይነቱ ካልተረጋገጠ የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አጥብቆ ለማሳሰብ የሚወደው ነገር ቢኖር፤ የምንወስደው ሰፊ ወታደራዊ ማጥቃት በአገሪቱ የሚፈጥረው የእርስ በርስ እልቂት ታይቶ ከማያውቅ ደረጃ ይደርሳል፡፡ የኢህአዴግ ዓላማ ተግባራዊነቱን የሚያገኘው በጦርነቱ ስለሆነ ጦርነቱ በከፋ መልኩ ይቀጥላል፡፡ የአገሪቱ ህዝብ የስቃይና የመከራ ህይወት ይራዘማል፡፡ በፀረ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች የኢህአዴግ ሠንደቅ ይውለበለባል፡፡

ይህ የጦርነት ክስተት እንዳይፈጠር የኢህአዴግ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ጦርነቱን ለማቆም ዋነኛው አማራጭ መንገድ የኢህአዴግ ሠላማዊ ሽግግር ፕሮግራም በውጭና በሃገር ውስጥ ያሉ ኢትዮጵያውያን እንዲቀበሉት ሲያስገነዝብ፤የኢትዮጵያ ህዝብ ከዚህ የጦርነት እሳት ለመዳን የደርግ፣ የኢሠፓና የግብረአበሮቹ ፀረ ዴሞክራሲያዊ ኀዳናዎች ሳይከተል አጥብቆ እየተቃወመና እየታገለ ከኢህአዴግ ጎን ተሰልፎ የሽግግር ፕሮግራሙን ተግባራዊ እንዲያደርግ ጥሪውን ያሰማል"

*የኢህአዴር የውጭ ቢሮ*
*13/03/እ.ኤ.አ 1991፤*

*ማሕተም፡፡*

ይህ መግለጫ ይፋ ከተደረገ በኋላ ደርግ አንድነትን፣ ኢህአዴግ ፀረ አንድነትን ሲያቀነቅኑና ለአመታትም ሲፋለሙበት የኖሩበት ነጥብ እንደመሆኑ መጠን፣ ከዚሁ ጋር ተያይዞም በመካከላቸው አንዳችም ለሠላም ስምምነትና ድርድር የሚያበቃ ክፍተትም ፍላጎትም እድልም፣ ተስፋም ባለመኖሩ የቀረው አንድ ነገር ብቻ ሆኗል፡፡ ያም የእርስ በርስ



ፍጅቱን በአዲስ አበባና በዙሪያዋ ባሉ ከተሞች ማጧጧፍና፤ ህዝቡን ማስጨረስ፣ በጦርነቱም የከተማዎቹን የመሠረተ ልማት አውታሮች ማውደም፤ ህንፃዎቹን ማስደርመስ ....ነበር፡፡ ይህ እንዳይሆን አስበው አገሪቱን በሠላም ለቀው በሚስጥር ሹልክ ያሉትን ጓድ ፕሬዝዳንት መንግስቱ ኃይለማርያምን ማመስገን ተገቢ ይመስላል፡፡

በወቅቱ ባልተያዙ ከተሞች አነስተኛም ቢሆን ሠራዊት ነበራቸው፡፡ 10ሺ የሚደርሱ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ማሠልጠኛ ውስጥ ከመኖራቸውም በላይ፤ ከልዩ ብርጌድ ሠራዊቱና ሸሽተው አዲስ አበባ ከገቡት ጋር ተዳምሮ ወደ 40 ሺ የሚጠጋ ሠራዊት ከእነትጥቁ ነበራቸው፡፡ ያም ሆኖ መንግስቱም እንደሚሉት በርሃ ውስጥ እንደ አዲስ የሽምቅ ውጊያ ለመጀመር ካልሆነ በቀር ፊት ለፊት ለመጋፈጥ የሚያስችል አይደለም፤ ሁኔታውም ምቹ አይሆንም፡፡

በዚህ መሠረት ግራ ቀኙን አይተው ተስፋ ያጡት ፕሬዝዳንት የአሜሪካን ግፊት መቀበል ነበረባቸው፡፡ እናም ግንቦት 13 በጠዋት ብላቴ ማሰልጠኛንና በውስጡ ያሉትን ምልምሎች ለመጎብኘት በሚል ጉዞ ጀመሩ፡፡

የመንግስቱን ከአገር አወጣጥ በተመለከተ እውነታውን በስተመጨረሻ የምናየው ይሁንና የቅርብ አጃቢዎቻቸውና ሾፌሮቻቸው እንዲሁም ራሳቸው መንግስቱ ለጋዜጠኛ ገነት አየለ ያሉትን እናስቀድም፡፡

ጀኔራል ቁጥር 20 እንዲህ ይላሉ "... ለጉብኝቱ በተወሰነው ቀን አብረዋቸው ከሚሄዱት አንዱ በመሆን ከጠዋቱ አንድ ሰዓት አውሮፕላን ማረፊያ ተገኘሁ፡፡ ሌላ አንድ ጀኔራልም በቀጠሮው ሰዓት ተገኝቶ ይጠባበቃል፡፡ ብናይ ብናይ እስከ 5 ሰዓት ድረስ ምንም የለም፡፡ ብላቴ ካለው አዛዥ ጋር በስልክ ስነጋገር አንድ አውሮፕላን በብላቴ በኩል ማለፉን ቢነግረኝም፤ አካባቢው ብዙ አውሮፕላኖች የሚመላለሱበት ስለነበር አልጠረጠርኩምና ዘግይተው ነው ብዬ መጠበቄን ቀጠልኩ፡፡ ወዲያው ግን ቺፍ ኦፍ ስታፉ ደወሉና ባስቸኳይ ቤተመንግስት እንድትመጣ ስላሉኝ ሄድኩ፡፡ ስደርስ ጀኔራል ተሰፋዬ በሬዲዮ የተነገረውን ሲነግረኝ ማመን አቃተኝ ..." በማለት ".... እንደሚመስለኝ የመንግስቱን መሄድ አስቀድመው ያወቁ ሰዎች ነበሩ፡፡ ተገደው ወይም ተፅዕኖ ተደርጎባቸው ሄዱ የሚለውን ለማመን ያስቸግራል" ሲሉ፤ ግምታዊ ድምዳሜያቸውን ካዩዋቸው ነገሮች ተነስተው ያስቀምጣሉ፡፡ ጓድ ቁጥር 22 ደግሞ "ስለአወጣጣቸው ኮሎኔል መንግስቱ ያወሩት ውሸት ነው፡፡ እሳቸው ያወሩትን፣ የሳቸውን ትረካ አላምንም" ሲሉ፤ አጃቢ ቁጥር 5 ተብለው በትዝታዎች ቁጥር 1 መጽሐፍ ቃላቸውን ያሰፈሩት የመንግስቱ

የቅርብ አጃቢና ኬንያ ድረስ የሸኟቸው የሰጡት ምላሽ ደግሞ በአጭሩ እንዲህ ይነበባል፡፡

"... ከመንግስቱ ጋር በጣም ስለምንቀራረብና እንደወንድማቸው ያዩኝ ስለነበር፣ ስለሚያምኑኝና ቤተኛም ስለበርኩ፤ በዚያን እለት ማለዳ ላይ ወደመኖሪያ ቤታቸው ሄጄ ወ/ሮ ውባንቺን ሠላም ብዬ ጓዶች ለእለቱ ፕሮግራም ዝግጁ መሆናቸውን ሪፖርት አደረኩ" በማለት ከሌላው ጊዜ የተለዩ የጉዞ እንቅስቃሴ እንዳልነበር ይጠቁማሉ፡፡ ሲቀጥሉም "ሁላችንም ብላቴ ሞቃታማ ስለሆነ ቀላል ወታደራዊ ዩኒፎርም ነው የለበስነው፡፡ መንግስቱም ቢሆኑ ዘወትር ከሚይዙት ሳምሶናይትና በትረ መኮንናቸው በስተቀር ሌላ ነገር አልያዙም፡፡ ሻንጣ ወይም ቦርሳ አልተጫነም፡፡ ከፓይለቱና ከረዳት ፓይለቱ ጭምር ጠቅላላ አውሮፕላኑ ውስጥ የነበርነው ዘጠኝ ሰዎች ነበርን፡፡ ሁኔታዎች የተለወጡት ብላቴ ልንደርስ ስንል ነው፡፡ ፕሬዝዳንቱ ፓይለቱን ቀጭን ትዕዛዝ ሰጡት፡፡ "ከፍተኛ ስብሰባ ስላለብኝ ወደ ናይሮቢ ሂድ" አሉት፡፡ "ወደዚያ እንሄዳለን ስላልተባልኩ ካርታ አልያዝኩም" አለ ፓይለቱ፡፡ አጃቢዎቹም እኔም ደነገጥን፡፡ እሳቸው ግን ፍንክች ሳይሉ "የምቀርበት ጉዳይ አይደለምና እንደምንም ብለህ ሂድ፤ ካስፈለገ ከኮንትሮል ታወር ጋር ተገናኝተህ እንዲመሩህ አድርግ፣ ብቻ ናይሮቢ መድረስ አለብኝ" አሉት፡፡ በዚህ አይነት ሁኔታ ናይሮቢ ደረስን፡፡ ከዚያ በኋላ የሆነው ፍፁም የተደናበረና ውዥንብር የበዛበት ነው፡፡ በበኩሌ ማታውን ወደዙምባብዌ ከተጓዘው ግሩፕ ጋር እንድሄድ መንግስቱ ጠይቀውኝ ነበር፡፡ እንደማልሄድና ወደአገሬ መመለስ እንደምፈልግ ስገልፅላቸው አልተቃወሙኝም ወይም ሊያሳምኑኝና ሊያስቀሩኝ አልሞከሩም፡፡ ስመለስ የሚጠብቀኝ መጥፎ ነገር ሊኖር እንደሚችል በመግለፅ ግን ስጋታቸውን አልሸሸጉኝም፡፡

"ሀሳቤን እንደማልለወጥ ሲረዱ ለጄኔራል ተስፋዬ ገብረኪዳን የሚሰጥ ደብዳቤ ጽፈው ሰጡኝ፡፡ ይሄንንም በማግስቱ እንደተመለስኩ ለጄኔራሉ ሰጥቻለሁ፡፡ እንግዲህ በሬዲዮ እወጃው እንደሰማነው የወቅቱ ርዕሰ ብሄር ጄኔራል ተስፋዬ ስለነበሩ ይጠቅማል ያሉትንና ከመሄዳቸው በፊት ሊነግሯቸው ያልቻሉትን ጉዳዮች ነው ደብዳቤው ላይ ያሰፈሩት፡፡

ከደብዳቤው ሌላ እኔ በቃል እንድነግርላቸው የላኩኝ መልዕክትም ነበረ፡፡ እሱም፤ 1. በጓድ መንግስቱ ገመቹ ትዕዛዝ ብቻ ሊወጣ የሚችል ከሰባት ሚሊዮን ተኩል በላይ የሆነ ብር፣ 2. ፍቅረስላሴ ወግደረስና ኃይሉ ይመኑ የሚያውቁት ከድሬዳዋ የጫት ገቢ የሚገኝና ለሱዳንና ለሶማሌ ነፃ አውጪዎች በየጊዜው ወጪ እየተደረገ የሚሰጥ ተቀማጭ ገንዘብ፣ 3. በገልፍ ጦርነት ለኩዌት ድጋፍ ስለሰጠን የኩዌት መንግስት በእርዳታ የሰጠን 20 ሚሊዮን ብር (ኃይሉ ይመኑና የገንዘብ ሚኒስትሩ የሚያውቁት) ይሄ ሁሉ ገንዘብ እንዳለ እውቀህ፣ ከጓድ ነሲቡ ታዬ ጋር



ተነጋግረህ፣ ጦርነቱ ከቆመ ለከባድ ኢንደስትሪዎች ማቋቋሚያ ይሆናል የሚል ነበር፡፡ ደብዳቤውንም መልዕክቱንም አድርሻለሁ፡፡

በበኩሌ ምናልባት መንግስቱ ከመሄዳቸው በፊት ለጄኔራል ተስፋዬ ነግረዋቸዋል የሚል ግምት አለኝ፡፡ በሬዲዮ የመንግስቱ መጥፋት የተነገረበትን ሰዓት ሳገናዝበው ተስማምተው ያደረጉት ይመስለኛል፡፡ እኛ ከዚህ ተነስተን እዚያ የደረስንበትን ሰዓትና መሄዳቸው በስድስት ሰዓቱ ዜና ላይ ከመታወጁ በፊት (በኋላ እንደሰማሁት) ጄኔራል ተስፋዬን ከስብሰባ ላይ አስጠርተው በስልክ ያነጋገሯቸውን ጊዜ ሳስበው ሁለቱ ተስማምተው ይሆናል የሚል ጥርጣሬ አሳድሮብኛል፡፡

ባለቤታቸው እኛ ወደ ብላቴ ከሄድን በኋላ በሌላ አውሮፕላን ተሳፍረው ዙምባቡዌ መሄዳቸውን በኋላ ሰማሁ፡፡ ያኔ ቤተመንግስት ስደርስና ሠላምታ ስንለዋወጥ ግን መንገድ ሊሄድ እንደተሰናዱ አልነገሩኝም" የሚል ቃላቸውን ሰጥተዋል፡፡ (ትዝታዎች ቁጥር 1 ገጽ 53) ፕሬዝዳንት መንግስቱ ግን "አካሄዴ ከሀገር ወጥቼ ለመቅረት ሳይሆን፤ ቀደም ብሎ ከቻይና ተገዝቶ በምፅዋና አሰብ ወደቦች መያዝ ምክንያት ሊገባ ያልቻለውን መሣሪያ በኬንያ በኩል ለማስገባት ከፕሬዝዳንት አራፕ ሞይ ጋር ለመነጋገር ነው" የሚል ሲሆን፤ ለአንባብያን ሁኔታው ግልፅ ይሆን ዘንድ ከጋዜጠኛ ገነት አየለ ጋር ያደረጉትን ቃለ ምልልስ ቀንጨብ አድርጌ አካትታለሁ፡፡ ከተጠየቁ በኋላ ዙሪያ ጥምጥም የሆነ መልስ በመስጠት ላይ ሳሉ፤

ገነት፤ "ከአገር እንዴት እንደወጡ እንዲነግሩኝ ነበር የጠየቅሁዎት፤ ወደዚያ ብንመለስ"

መንግስቱ፤ ".... ከቻይና መንግስትና ከሌሎችም ወደ 70 ሚሊዮን ዶላር የሚያወጣ መሣሪያ ገዝተን ስለነበር ያንን ልናስገባ ስንል አሰብን እስያዙት፡፡ የአሠብ መያዝ ጦርነቱን ውስብስብ አደረገው፡፡ ቻይናዎቹን በአውሮፕላን እቅርቡልን ብንል፤ በአውሮፕላን ማቅረብ አንችልም የምንችለው በመርከብ ነው አሉን፡፡ ይሄ በጣም አስቸጋሪ አጣብቂኝ ውስጥ ከተተን፡፡ በምፅዋ አናስገባ፤ በአሰብ አናስገባ፡፡ ....

..... የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ብላቴ ስልጠና ላይ ስለነበሩ ብላቴን ለመጎብኘት ተነሳሁ፡፡ በዚያው አንድ ነገር አሰብኩ፡፡ በሚስጥር ኬንያ ለመሄድ፣ ይህም አስፈላጊ ያልሆነ ግምት ተሰጥቶት ወሬ እንዳይዛባና "እንደዚህ ሄዶ ነበር" እንዳይባል ጥንቃቄ በማድረግ በጣም ከተወሰኑ ሰዎች በስተቀር ማንም ሰው እንዳይሰማ ወሰንኩ፡፡ .... አራፕ ሞይን በሚስጥር ለማነጋገር ፕሮግራም አወጣሁ፡፡ መጀመሪያ ደቡብ በመሄድ ማንም ሳይሰማ ናይሮቢ ደርሼ ለመምጣትና በፕሮግራሙ መሠረት ብላቴ እንደታቀደው ለመሄድ ወሰንኩ፡፡ ....

እኔ ጠዋት በሁለት ሰዓት ወደ ብላቴ በረርኩ፡፡ ከቦሌ የተነሳሁት ከጠዋቱ ልክ ሁለት ሰዓት ላይ ነው፡፡ ቡፋሎ አነስተኛ አውሮችላን ነው፡፡ ወደ ሦስት ሰዓት ላይ እነ ጄኔራል ተስፋዬ ገብረኪዳን፣ በርከት ያሉ ከፍተኛ ባለሥልጣኖችና የጦር አለቆች ይሰባሰባሉ፡፡ አንድ ነገር ማዘጋጀት ነበረባቸው፡፡"

ገነት፡- "እርስዎን ለመሸኘት ነው የተሰባሰቡት?"

መንግስቱ፡- "... ምን እኔን ይሸኛሉ? እኔማ ሄጃለሁ፤ መንገድ ላይ ነኝ፡፡ ሦስት ሰዓት ላይ ነው የተሰባሰቡት፡፡ ገና እግሬ ሲወጣ ማለት ነው፡፡ እኔ ሁለት ሰዓት ላይ ወጣሁ፤ እነሱ ሦስት ሰዓት ላይ ተሰባሰቡ፡፡ ይሄን የምነግርሽ ከወጣሁ በኋላ የተረዳሁትን ነው፡፡ እኔ አምስት ሰዓት ናይሮቢ ደርሼ መውረድና መታየት አልፈለግሁም፡፡ አምባሳደሩ እንዲመጣ ስጠይቅ "የለም ኡጋንዳ ሄዷል፡፡ የፖለቲካ አታሼው ብቻ ነው ያለው" አሉኝ፡፡ እሱን አስጠርቼ ፕሬዝዳንት አራፕሞይን "እባክዎ በጣም ጥብቅ ለሆነ ጉዳይ ለአጭር ጊዜ ላነጋግርዎ እፈልጋለሁና ቢቻል እዚህ ኤርፖርት ያለዚያም ቤተመንግስትዎ ያነጋግሩኝ" ብለህ ንገር ብዬ ላኩት፡፡"

ገነት፡- "ይቀርታ ላቋርጥዎትና ከዚህ በፊት እንዲህ ያለ ሚስጥራዊ የሆነ ጉብኝት በሚያደርጉበት ጊዜ በአካባቢዎ ያሉትን ሰዎች እንዲሁም የፕሮቶኮል ኃላዎች ያሳውቃሉ ወይስ እንዴት ነበር ከዚህ በፊት በሚስጥር ጉብኝት የሚያደርጉት?"

መንግስቱ፡- "አዎን፤ እሱማ አውሮፕላን የሚያዘጋጁልኝ፣ አስፈላጊውን ነገር ሁሉ የሚያደርጉልኝ እነሱ አይደሉም እንዴ?"

ገነት፡- "እና ያውቁ ነበር ማለት ነው?"

መንግስቱ፡- "እንዴ! ከቦሌ አይደለም እንዴ ተሳፍሬ የሄድኩት?"

ገነት፡- "ግን እነሱ ኬንያ መሄድዎን አያውቁማ"

መንግስቱ፡- "እሱንማ እንዴት ብዬ እናገራለሁ? እኔ ብላቴ ነው የምሄደው ነው ያልኩት፡፡ ደግሞ ነው፡፡ ኬንያ ሄጄ ፕሬዝዳንት አራፕሞይን ለማነጋገር ነው፡፡ ማንም እንዲሰማ ማንም እንዲያውቅ አልፈለኩም፡፡ ቢችሉ...."

ገነት፡- "እና ለማንም አላማከሩማ?"

መንግስቱ፡- "ቢችሉ ..." እያሉ ሌላ ነገር ማውራታቸውን ይቀጥሉና ከኬንያው ፕሬዝዳንት ጋር ስለነበራቸው ቆይታ ይተርካሉ፡፡

ቆይታው መሣሪያ በሞምባሳ በኩል የሚያስገቡበትን ሁኔታ እንዲያመቻቹላቸው መጠያየት እንደነበር ነው መንግስቱ የሚገልፁት፡፡ አራፕሞይ ደግሞ እሽታቸውን እንደገለፁና፤ ምሣ በልተው እንዲመለሱ እየጠየቋቸው ሳለ፤ በመሀል አንድ መልዕክተኛ መጣና ለኬንያው ፕሬዝዳንት አንድ ነገር ሹክ አላቸው ይላሉ መንግስቱ፡፡ ሲቀጥሉም "ምን



እንደሆነ አልገባኝም፡፡ ለካስ በአዲስ አበባ ሬዲዮ ስልጣን በፈቃዴ ለቅቄ የመሄዴ ነገር ተነግሮ እሱን ሪፖርት እያደረጉላቸው ነው፡፡ ሁኔታውን ከሳቸው አፍ ሰማሁ፡፡ በፈቃዴ ስልጣኔን ለቅቄ መሄዴን አራፕሞይ ነገሩኝ፡፡ ገረመኝ፡፡ ወዲያውኑ አዲስ አበባ ደወልኩና አንድ ሰው አገኘሁ..." እያሉ ይቀጥላሉ፡፡ ይህ ያገኙት ሰው ሁሉም ስብሰባ ላይ እንደሆኑ ይገልፁላቸዋል፡፡

"በእውነቱ እነተስፋዬ ተሰባሰቡ አልተሰባሰቡ ምንም የሚከፍቱት ድስት እንደሌለ አውቃለሁ፡፡ እኔ ምንም ልሁን፤ ግድ የለኝም፡፡ አሁን ጥያቄው ወያኔ እየገፋ ነው፡፡ የታጠቀ ህዝብና ሠራዊት ይዞ መመከት የሚቻለው እንዴት ነው? ስለዚህ እንደገና አራፕሞይን ሄድኩና "ሌላ ነገር ልጠይቅዎ ነው" አልኳቸው፡፡ "ምን" ሲሉኝ "አንድ አውሮፕላን እዘዙልኝና ቻይና ልሂድ" ስላቸው ነገሩ ከበድ አላቸው መሰለኝ፤ ትንሽ ጊዜ ስጠኝ፣ ልምከርበት ብለው ብዙ አስጠበቁኝ፡፡ ቆይተው መጡ፡፡ በዚያን ጊዜ ውስጥ ለካ ከአሜሪካኖቹ ጋር ግንኙነት አድርገው ኖሯል..." እያሉ በመተረክ አራፕሞይ "አዝናለሁ ወዳጄ አልችልም፤ ስልጣን ለቀህ ከአገር መውጣትህን አሜሪካኖች ሰምተዋል፤ ስለዚህ የጠየከውን ብናደርግ ብሔራዊ ጥቅማችን አደጋ ላይ ይወድቃል..." የሚል መልስ እንደሰጧቸውና፤ ቻይና ሄደው ስለመሳሪያው ጉዳይ በግንባር የመነጋገር እቅዳቸው እንደማይሆን ሲረዱ፤ "እሺ በቃ ወደ ዙምባቡዌ ሄጄ ከሙጋቤ ጋር ተነጋግሬ ሌላ መንገድ እንድፈልግ ወደዚያ የምሄድበትን ትራንስፖርት ስጡኝ አልኳቸው" ይሉናል፡፡

"በመጨረሻ ምሽት ላይ አውሮፕላን ቀርቦልኝ ልሳፈር ስል ሻለቃ ደመቀ ባንጃው ቀረበና "እኛ እንመለስ" አለኝ፡፡ "ለመመለስ ነፃ ናችሁ፤ ግዴታ የለም" ብየው ተሰነባብተን ተለያየን" ብለዋል መንግስቱ፡፡

አንድ ፕሬዝዳንት አገሩን ከመጨረሻው ጥቃት ስለሚከላከልበት ስለ 70 ሚሊዮን ዶላር መሣሪያ ጉዳይ እንዴት ብቻውን ሚስጥር አድርጎ ይይዛል? ኢህአዴግ አዲስ አበባን ሊይዝ ስድስት ቀናት በቀረው ሁኔታ የተባለው ምሣሪያ ስድስት ወር እንኳን ቢቀረው እንዴት በዚያ ሰዓት ይታሰባል? ሁሉም ሽሽት ላይ በነበረበት በዚያ ቅፅበት መሣሪያ ለማምጣት የተዘጋጀ ፕሬዝዳንት ለባለስልጣናቱ መንገርና እየተከላከሉ እንዲቆዩ፣ መሣሪያው ስለሚገባበት ሁኔታ ቅድመ ዝግጅት እንዲያደርጉ ሳይገልፅ በሚስጥር ማድረግ ይገባዋል? ይሄ እንዴት ይታመናል?

በመንግስቱ አገላለፅ'ኮ ሐራሬም የሄዱት ሙጋቤ ከቻይናዎቹ ጋር ጥሩ ቀረቤታ ስላላቸው መሣሪያውን የማስገባቱን ሂደት እንዲያፋጥኑላቸው ለመወያየት መሆኑ ነው፡፡

ከቦሌ አለመነሳታቸውም በደንብ ይታወቃል፡፡ በጥቅሉ በማስተባበያ ገለፃቸው ውስጥ እንዴት የምትታመን ዓረፍተ ነገር

ትተህ "አንተ" እያልክ የጠራሃቸው ለምንድነው?" ተብሎ ሲጠየቅ፤ "ብችል አንቺ ብለው ደስ ይለኝ ነበር" አለ፡፡

እውነትም እንደማንኛውም አፍሪካዊ መሪ የመንግስቱ ረጅምና በውጣ ውረድ የተሞላ የስልጣን ዘመናቸው በውዳሴ ከንቱ የተሞላ እንደነበር ቀልዱ ያስረዳናል፡፡ በእርግጥ ከመንግስቱ አገር ወዳድነት አንፃር፣ በህዝቡም፣ በሠራዊቱም ዘንድ በቆራጥነታቸው ስለሚታወቁ "አገር ጥዬ ሸሽሁ" ቢሉ ሐፍረት ነውና ማስተባበላቸው አይገርምም፡፡ ግን "ማን ያምነኛል?" ብለው ራሳቸውን አለመጠየቃቸው ግልፅ ድክመት ነው፡፡

የመንግስቱ ሽሽት ይፋ ከሆነ በኋላ ርዝራዥ ሠራዊት ወደ ከተማ እየሸሸ መጣ፡፡ ትጥቁን ፈቶ እየተማረከ፣ ሌላውም እየሸጠ ተበታተነ፡፡ መንግስቱ "አገር ጥሎ ኮበለለ ተብሎ ለህዝቡ መገለፁን ስሰማ ታመምኩ..." እስከማለት ደርሰዋል፡፡

ሊያሳምማቸው የቻለው እንዲያ ተብሎ እንዲገለፅ ያልፈለጉት፤ ነገር ግን እንዲህ ተብሎ የተገለፀባቸው ዜና ብቻ ነው፡፡ "... እርሳቸውም አምነውበት፣ አገር ለቀው ሄደዋል፣ ፈርጥጠዋል፣ ሸሽተዋል..." ይህም ሲባል እርሳቸው ምን ተብሎ ለህዘብ እንዲገለፅላቸው ነበር የፈለጉት? የሚል ጥያቄ ማስነሳቱ አይቀርም፡፡

መንግስቱ እንዲባል የፈለጉትና ቀድመውም ከታማኛቸው ከጀኔራል ተስፋዬ ጋር ያቀዱት፤ ሁኔታው ከፍቶ የቀናት እድሜ ብቻ እንደቀራቸው በመረዳት፤ ኢህአዴግ አዲስ አበባ በሚገባበት ጊዜ "ፕሬዝዳንቱ ከቀናት በፊት ከቻይና የተገዛውን መሣሪያ ለማምጣት ከአገር ወጥተው ነበር፡፡ በመሐል ኢህአዴግ ሲገባ ባላሰቡትና ባልጠበቁት መንገድ በወጡበት ለመቅረት ተገደዱ" የሚለው የታሪካቸው ማብቂያ ሆኖ እንዲቀር ነበር፡፡ ሳይሆን ቀርቶ ኢህአዴግ ቤተመንግስቱን ከመቆጣጠሩ በፊት እግራቸው እንደወጣ ለህዝብ ይፋ ሆነ፡፡ በዚህም ፕሬዝዳንቱ ተበሳጩ፡፡ ብስጭታቸውንም ለመግለፅ ስልክ ደውለው ጀኔራሉን አስጠሩ፤ ጀኔራሉ ግን ሊያናግሯቸው ፈቃደኛ አልነበሩም፡፡ ስለዚህ ከነንዱታቸው ቤተሰቦቻቸው ወደሄዱበት ወደ ዙምባቡዌ አመሩ፡፡ መረጃው በእቅዱ መሠረት ይፋ ሲሆን እውነት መስሎ እንዲታይም አወጣጣቸው ድንገት እንደነበር ሊጠቁሙ የሚችሉ ዘዴዎችን መጠቀም ነበረባቸው፡፡ ያንንም አድርገዋል፡፡ ከኬንያ ወደ ዙምባቡዌ የተጓዙትም አሜሪካ በላከችላቸው አውሮፕላን ነው፡፡

## የሶሻሊስት መሪዎች ውድቀትና የመንግስቱ የስደት ህይወት

ውድቀቱ የደርግ መንግስትና የፕሬዝዳንት መንግስቱ ብቻ አልነበረም፡፡ የመላው ዓለም ሶሻሊስት አራማጅ አገራት የሆኑ መንግስታት ሁሉ በጋራና ሆን ተብሎ በተሰራ ስራና ሴራ የወደቁበት ዘመን ነው፡፡



ማን መቼና እንዴት በማን በምን አይነት ዘዴ መውደቅ እንዳለበት ታቅዶ ያለቀና በተያዘለት እቅድ መሠረትም ተግባራዊ የሆነ፤ በኃይል የሚወርዱ መንግስታት የትኛው እስር ቤት መግባት እንዳለበት፣ ማን በግዞት መኖር እንደሚገባው፣ ማን አገሩ ላይ ታስሮ እንደሚቀር በዝርዝር ሰፍሮ ያበቃለት ጉዳይ ነው፡፡ በእምባገነንነት የሚፈረጁ መንግስታት ስም ዝርዝር ተመዝግቦ፣ መውደቅ እንዳለባቸው ታምኖበት ተወስኗል፡፡

በዚያ ወቅት አሜሪካ ከፍተኛ የቤት ስራዋ ይሄ የነበረ ከመሆኑም በላይ፤ ወደ ተግባር ለመለወጥ ቀላል ስራዋ ነበር፡፡ ስራው የከበደው የማንም እጅ እንደሌለበት ለማሳመን የሚደረጉ የረቀቁ አሰራሮችን መቀመር የግድ በመሆኑ ምክንያት ብቻ ነው፡፡ ለዚህ ሽፋንነት ይረዱ ዘንድም አሜሪካ ሠላማዊ አደራዳሪ መስላ መታየት ግዴታዋ ነበር፡፡ የአፍሪካ፣ የእስያና የአውሮፓ ኮሚኒስት አገዛዞች በጋራ ሲወድቁም በተጠቀሱት አገራት ህዝቦች ዘንድ የአሜሪካ ስም እንዳይነሳ ልዩ ጥንቃቄ አድርጋለች፡፡ እንግሊዝም ጭምር፡፡

የደርግ መንግስት ምንም አይነት ተቃዋሚ ባይኖረውና ሻዕቢያ ወያኔ ገለመሌ ባይኖሩ ኖሮም የግድ መውደቅ ግን ነበረበት፡፡ "በአዲሱ የአሜሪካ ርዕዮት እመራለሁ ተውኝ" ቢል እንኳ የቀድሞ መሪ ስለሆነ ብቻ ተቀባይነት አያገኝም ነበር፡፡

ጓድ መንግስቱ "ያካሄድነው'ኮ አብዮት ነው!" እያሉ ይፎክሩ እንደነበረው ሁሉ፤ እኛም አሜሪካን "ያካሄደችው'ኮ የዓለም አብዮት ነው!" ማለት እንችላለን፡፡

ይሄን ለማለት ያስፈለገኝ "የመንግስቱን ከአገር የመውጣት ዘዴ ያቀናበረችው አሜሪካ ናት" የሚለውን እውነት ለማጠናከር አይደለም፡፡ እሱ ከነጭም በላይ ንፁህ ያለ ሐቅ ነውና ምንም ማጠናከሪያ አይፈልግም፡፡

ከዚህ ይልቅ ጦርነት የሌለባቸው ኮሚኒስት አገራትስ መች ቀረላቸው? ለማለትና ለተከታዩ የመንግስቱ ኃይለማርያም ምላሾች መንደርደሪያ ይሆነኝ ብዬ ነው፡፡

መች ቀረላቸው? ለሚለው የፖላንዱ ፕሬዝዳንት ያሩዜልስኪ፣ (ፍፁም አምባገነን ኮሚኒስት መሪ) የአልባኒያ መሪዎች ባልና ሚስቱ ነዝህሚጅ ሆጃ እና ኤንቨር ሆጃ (አልባኒያን የመጀመሪያዋ ሃይማኖት የሌለባት አገር አድርገው መስጊድና ቤተክርስቲያን አፍርሰው በምትኩ 700 ሺ የማይንቀሳቀስ የታንክ ሐውልት በከተማዋ የገነቡና ሶሺሊዝምን ከጥቃት ለመከላከል በሚል በሰሩት ፒራሚድ የአገሪቱን ሐብት ያደቀቁት፣ ህዝቡም በሐውልት ታንኮች እየገባ ተጠልሎ እንዲከላከል ያደረጉ (የሚገርመው የእማሆይ ቴሬዛ አገር አልባኒያ መሆን ነው)፣ የሃይቲው መሪ

ዥን ክሉድ ዱቫልዮ (ቮዶ የሚባል ሚስጥራዊ ሃይማኖት መስርቶ በቤተመንግስት ራሱ አምላክ ሆኖ የሚመለክበትን ስርዓት የመሠረተ፣ አባትየውና ልጁ ዥንክሉድ ዱቫልዮ ፓፓ ዶክ እና ቤቢ ዶክ ሃይቲን ሙልጭ አድርገው የዘረፉ ተከታታይ ፕሬዝዳንቶች ሲሆኑ፤ "አባታችን ሆይ በሰማያት የምትኖር" እያለ የሚቀጥለውን ክርስቲያናዊ ፀሎት "አባታችን ቤቢ ዶክ ሆይ፤ በቤተመንግስት የምትኖር፣ ስምህ ይቀደስ … መንግስትህ በሐይቲ እንደሆነች…" እየተባለ የሚቀጥል ፀሎት አርቅቀው ከትምህርት ቤት ጀምሮ ለሐይቲ ዜጎች ያስተማሩና የአገሪቱን የካቶሊክ ሃይማኖት ተከታይ ህዝብ እምነቱን አስቀይረው በአብዮታውያኑ እንዲያምኑ ያደረጉ…)፣ የሴንትራል አፍሪካው የእድሜ ልክ ፕሬዝዳንት፣ ቀጥሎ ንጉስ የሆኑት ቦካሣ (የሰው ስጋ በመብላት የተከሰሱና ከእያንዳንዱ የዓለም አገራት ሴቶች አንድ አንድ ሚስት ያገቡ፣ በመቶዎች ከሚቆጠሩ ሚስቶቻቸው በመቶዎች የሚቆጠሩ ልጆች የወለዱ፣ ለእያንዳንዷ ሚስት በሴንትራል አፍሪካ ዋና ከተማ በባንጉይ ምርጥ ምርጥ ቪላ ቤት የሰጡ፣ አገሪቱን የግላቸው ሱቅ ያደረጉ፣ በቦካሳ መንገድ፣ በቦካሳ ስጋ ቤት፣ በቦካሳ ዩኒቨርሲቲ፣ በቦካሳ ቡቲክ፣ በቦካሳ ጎዳና፣ በቦካሳ … ተጉዣ መጣሁ በሚያስብል መልኩ የአገሪቱን ሀሉንም ነገር በስማቸው ከመሰየም አልፈው ሁሉም ተቋማት በራሳቸው ስም የተመዘገቡ የነበሩ፣ የትምህርት፣ የገንዘብ፣ የፍርድ፣ የማስታወቂያ፣ የንግድ፣ የሁሉም የአገሪቱ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ሁሉ ሚኒስትር የነበሩ…)፣ በአምባገነንነታቸው የሚታወቁት ሰው በላ የኡጋንዳው ኢዲአሚን ዳዳና ሌሎች ሁሉ በአንድ አይነት ዘመን የወደቁ ናቸው፡፡ የወደቁት ግን በሽማቂ ቡድን አልነበረም፡፡ በተከታታይ በተደረጉ በራሳቸው ህዝቦች የከተማ ሠላማዊ ሰልፍ አማካኝነት ነው፡፡ በመፈንቅለ መንግስት ነው፡፡ ተተኪዎቹንም በካፒታሊዝም አጥምቀው አዘጋጅተዋል፡፡

የኢትዮጵያው መንግስቱም ከተጠቀሱትና ካልተጠቀሱት አገራት መሪዎች ውድቀት እኩል በአንድ ጀንበር የሆነ ሁነት ሲሆን፤ የግላስኖስትና የፔሬስትሮይካ ግብም ይሄው ነበር፡፡ ለእነዚህ መንግሥታት ውድቀትና ስርዐዮቱ ማክተም፣ ብሎም ዓለምን በአንድ አሜሪካና በጥቂት አጋር አገራት እግር ስር ለማንበርከክ፣ ዓለም በአንድ ጎታ ትከተት ዘንድ አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበት እቅድም ተይዞለት ቅድመ ስራው ተጠናቆለት ወደ ተግባር የተለወጠ ዓለም አቀፍ ስራ ነው፡፡ ይህ ዓላማ ግቡን ይመታ ዘንድም በየአገራቱ እንኳንስ የታጠቀ ተቃዋሚ በአገሪቱ ውስጥ ያለበትን መንግስት መርዳት፤ በሠላም እየተገዙ የነበሩ ህዝቦችን በአንድ ቀን ለማሳመፅና መሪውን ለማስወገድ አልከበደም፡፡ ስለዚህም አሜሪካ ጥገኝነት ሰጭ አገራትን ሲቻል በራሷ ምርጫ፣ ካልሆነም ወዳቂውን መንግስት እንዲመርጥ በመፍቀድ በቅድሚያ ማመቻቸትና ሠላም አስከባሪ መስሎ



መታየት የስራው አፈፃፀም እንጂ ሌላ አይደለም፡፡ የአገር ምርጫው ለራሳቸው ከተተወላቸው መሪዎች ውስጥ አንዱ መንግስቱ ኃይለማርያም ናቸው፡፡ ኢዲአሚን ዳዳ ሳውዲ ዓረቢያ፣ ቦካሳን ወደ እስር ቤት፣ ዱቫልዮንና መሰሎቹን ወደ ቀድሞ ገዥዎቻቸው ወደ ፈረንሣይ፣ አውሮፓውያኑን ባገራቸው እስር ቤት ወዘተ… እንደሚሆን እንደሚሆን አደረጓቸው፡፡ የእነቦካሳ ንብረት በፈረንሣይ ተወረሰ፡፡ የዱቫልዮና የሌሎቹ የስዊዝ ባንክ ገንዘብ ተወረሰ፡፡ ያልተወረሰው ገንዘብ የመንግስቱ ኃይለማርያም ሲሆን፤ ያልተወረሰውም በየትኛውም አገር ባንክ ምንም ገንዘብ ስላልነበራቸው ብቻ ነው፡፡ እና … እነዚህን ሁሉ አምባገነን መሪዎች በያሉበት አገር እየዞረ፣ በየታሰሩበት እስር ቤት እየሄደ፣ ጥገኝነት ጠይቀው እየኖሩ ያሉትን በየተጠጉበት አገር እየተዟዟረ ስላለፈው ታሪካቸው እየጠየቀ፣ የሰጡትን ምላሾች አሰባስቦ እ.ኤ.አ በ2003 ዓ.ም ጣሊያናዊው ጋዜጠኛ ሪካርዶ ኦሪዚዮ Talk of The Devil በሚል ርዕስ ለሕትመት አበቃው፡፡ ቀደም ሲል እንዳየነው በአማርኛም ጭምር "የሠይጣን ኑዛዜ" ተብሎ የተተረጎመው ይህ መጽሐፍ፤ በሚያሳፍርና ፍትሐዊነት በጎደለው መልኩ የፕሬዝዳንት መንግስቱ ኃይለማርያምን ታሪክ ከሰው ስጋ በሊታዎች ከእነቦካሳ፣ ከእነ ኢዲአሚን ዳዳ፣ ከእነዱቫልዮ … ከሁሉም ወዳቂ የቀድሞ ሶሻሊስታዊ መሪዎች ጋር አካትቶ ነበር ለሕትመት ያበቃው፡፡ መንግስቱ ምንም አምባገነን ቢባሉም ከእነዚህ ዘራፊዎችና ሰብዓዊነት ካልፈጠረባቸው መሪዎች ተርታ ተመድበው መፃፋቸው ተገቢ አለመሆኑ ለማንም ግልፅ ከመሆኑም በላይ የጣሊያን ምሁራንና ጋዜጠኞች ባገኙት ቀዳዳ ሁሉ እእንደማይተኙልንም ይጠቁማል፡፡

ለማንኛውም መንግስቱ ለሌሎች ከሰጡት ምላሽ ይልቅ ለዚህ ጋዜጠኛ የሰጡት ምላሽ በአጭሩም ቢሆን የተሻለ ይመስላል፡፡ ሊዋሹት መሞከርንም የፈለጉት አይመስልም፡፡ ለዚሁ ጋዜጠኛ በጠየቃቸው መሠረት በመጠኑ ገልፀውለታል፡፡እናም የስደት ህይወታቸው በራሱ ታሪክ ነውና ከዚሁ መጽሐፍ በመነሳት አለፍ አለፍ እያልን ጥቂት ገለፃዎቻቸውን አድምጠንላቸው እናብቃ ልላችሁ ነው፤ እንዲህ የተንደረደርኩት፡፡

መንግስቱ ምንም እንኳ የተስፋ መቁረጥ ስሜት ቢታይባቸውም፤ ከሐራሬ ወጣ ብሎ በሚገኘው እና ለመኖሪያነት በተከለለው አካባቢ በሚገኘው መካከለኛ ቪላ ውስጥ በጥሩ ሁኔታ እየኖሩ ነው፡፡

እድሜያቸው ሰባ ሞልቷል፡፡ ፀጉራቸውንም ሽበት ወሮታል፡፡…‹‹እንዴት ነህ ነው ያልከኝ…››ጥያቄውን ደገሙት፡፡ትንሽ አሰ..ብ ካደረጉ በኋላ መልስ ሰጡ፡፡‹‹እኔነቴን ከጠየከኝማ ተርፌያለሁ፤እንዲያውም ደህና ነኝ እንበለው…››

መንግስቱ ደስ ባላቸውና ፈካ ባሉ ቀን የሚያስቡት በጭራሽ እንዳልታሰሩና ነፃ እንደሆኑ አድርገው ነው፡፡ "ፈጽሞ ተረስቼ አላውቅም፡፡ አሁንም ቢሆን በታዳጊ ሀገሮች በተለይም አፍሪካ ውስጥ ሁነኛ ወዳጆች አሉኝ፡፡ መቼም ስማቸውን ይዘረዝርልኛል ብለህ አትጠብቅም?" ይሉታል ለጋዜጠኛው፡፡

በደበራቸውና በከፋቸው ቀን ደግሞ አብዛኛዎቹ ሰዎች መጥፎ እንደሆኑ አድርገው ይገምቱና ተስፋ በመቁረጥ ስሜት ውስጥ ጭ...ልጥ ብለው ይገባሉ፡፡ "የትም ቦታ ብሄድ እታወቃለሁ፡፡ እንግዲህ የት መሄድ እችላለሁ? ምንም ቢሆን ምን ያው መንግስቱ ነኝ" ይላሉ፡፡ መንግስቱ ሐራሬ ከገቡ ከ10 ዓመት በኋላ ወደ ሆቴሎች እየሄዱ ዘና ማለት ጀምረው ነበር፡፡ ሆኖም የሚከታተላቸው ሐበሻ መኖሩን ካረጋገጡ በኋላ ልማዳቸውን ቀየሩ፡፡ የሙጋቤ መንግስትም ራሳቸውን እንዲደብቁ አስጠነቀቃቸው፡፡

በስደት ህይወት 10 ዓመታትን እንዳሳለፉም የልብ ህመማቸው ስላሰቃያቸው በዚምባብዌ የዲፕሎማቲክ ፓስፖርት ወደ ጆዋንስበርግ በመጓዝ ጋርደን ሲቲ ከሚባል የህክምና ተቋም ቀጠሮ ይይዛሉ፡፡ ህክምና ከማግኘታቸው በፊት ግን ወሬው ጋዜጠኞች ጆሮ ደርሶ ዓለም አቀፍ ርዕስ ሆነ፡፡ የኢትዮጵያ መንግስትም አጋጣሚውን ተጠቅሞ በዘር ማጥፋት ወንጀል እንደሚፈለጉ ገልጾ ባስቸኳይ ተላልፈው እንዲሰጡት እስከመጠየቅ ደረሰ፡፡ ይህም የሞት ፍርድ ማስከተሉን የተረዱት መንግስቱ ህክምናውን ርግፍ አድርገው ትተው ወደ ዚምባብዌያቸው ተመለሱ፡፡

"ውሸታ ቢስ ዲቃሎች!" አሉ መንግስቱ በጥላቻ ድምፅ፡፡ ፊታቸውን ቅጭም አድርገው ቀጠሉ፤ "ደቡብ አፍሪካ በአፓርታይድ መዳፍ ስር በነበረችበት ዘመን ኤ.ኤን.ሲን በፋይናንስ ጭምር ስረዳ ቆይቻለሁ፡፡ ይሁን እንጂ እኔ ዛሬ እርዳታቸውን በምሻበት ወቅት ሊረዱኝ ፈቃደኛ አልሆኑም፡፡ ሐራሬን ከመልቀቄ በፊት አካሄዴ በጤና ጉዳይ እስከሆነ ድረስ ምንም ችግር እንደማይገጥመኝ አረጋግጠውልኝ የነበረ ቢሆንም፤ ለኢትዮጵያ መንግስት አሳልፈው ሊሰጡኝ ተዘጋጅተው ነበር፡፡ .... እነዚህ ዛሬ የፕሪቶሪያን መንግስት የተቆጣጠሩትን ወገኖች የቀድሞ የትጥቅ ትግል ጓዶች፣ ወዳጆቼና የስራ ባልደረቦቼ አድርጌ እገምታቸው ነበር"አሉ፡፡

መንግስቱ ጓድ ሙጋቤን ማሞካሸት ዋና ስራቸው ነው፡፡ ሙጋቤም በበኩላቸው "በአህጉሩ ውስጥ ለነፃነት የተደረጉ ጦርነቶችን ሁሉ የረዱ ሰው ናቸው" በማለት ያንቆለጳጵሷቸዋል፡፡ ከብዙ እቅጣጫ መንግስቱን ከአገራቸው እንዲያባርሩና አሳልፈው እንዲሰጡ የሚሰነዘረውን ግፊት ሙጋቤ ጆሮ አይሰጡትም፡፡



በተለይ አሜሪካ ሙጋቤን "እምባገነን ደብቀሃል" በሚል ለመተቸት አፏን ስታሞጠሙጥ ሙጋቤ በሳቅ እየተፍለቀለቁ "በመጀመሪያ ደረጃ መንግስቱን ወደ ሐራሬ ያመጣችኋቸው እናንተ መሆናችሁን አስታውሱ እንጂ" በማለት ይሳለቃሉ፡፡

የመንግስቱን ጉዳይ በተመለከተ አሜሪካ አስፈላጊ ወጪያቸውን ለመሸፈን ቃል የገባችው ገና በማለዳ ነበር፡፡ ሙጋቤ ግን ተቃወሟቸው፡፡ "ገንዘባቸውን እንደማልፈልግ ነግሬያቸዋለሁ፤ አንድ ድሃ አፍሪካዊ ብሆንም ወጪውን ራሴ እሸፍናለሁ" ነበር ያሉት፡፡

እውነትም ከፍተኛውን የመንግስቱን የስልክ ወጪ ከመሸፈን አልፈው ሌሎች አስፈላጊ ነገሮችን ሙጋቤ በሚገባ ሸፍነውላቸዋል፡፡ መንግስቱም ለቀድሞ ወዳጃቸውና ለአሁኑ ባለውለታቸው ለሙጋቤ ሲ.አይ.ኦ በመባል የሚታወቀውንና በህዝብ ዘንድ ብዙም የማይወደደውን የሙጋቤ የደህንነት መስሪያ ቤት እንደ አማካሪ ሆነው በማገልገል ውለታቸውን እየከፈሉ ነው፡፡

"እኔ የጦር ሰው ነኝ፤ አገሬን ከጎሰኝነትና ከፊውዳሊዝም ለመታደግ ስል ያደረኩትን አድርጌያለሁ፡፡ ዓላማዬ ያልተሳካው ክህደት ስለተፈፀመብኝ ብቻ ነው፡፡ ዘር ማጥፋት የሚባለው ነገር አብዮቱንና ሁሉም ሰው ተጠቃሚ የሆነበትን ስርዓት ለመከላከል ከተደረገ ትክክለኛ ጦርነት ውጪ ምንም ሊባል አይችልም" የሚሉት መንግስቱ ከባለቤታቸው ከወ/ሮ ውባንቺ ቢሻውና ከሦስቱ ዶ/ር ልጆቻቸው ከአንድነት፣ ከትዕግስትና ከትምህርት ጋር ከፊል ነፃነት ባለው አኗኗር ህይወታቸውን ይመራሉ፡፡ ሙጋቤ "ምነው መንግስቱ ሆስፒታል የመክፈት እቅድ አለህ እንዴ?" ብለው የቀለዱትም ልጆቻቸው ሁሉ የህክምና ዶ/ር በመሆናቸው ነው፡፡

መንግስቱ ከሪካርዶ ኦሪዚዮ ጋር በሚነጋገሩበት ጠባብ ያለች ቢሯቸው ውስጥ ግድግዳው ላይ የተሰቀለውን ሙሉ የኢትዮጵያ ካርታ አፈጠጡበት፡፡ እሱ ላይ እንዳተኮሩ በትካዜ አፍጥጠው ቆዩና ቀጠሉ "... በጋው ላይ አማፅያኑ ያለምንም ፋታ ወደ አዲስ አበባ በመገስገስ ላይ ነበሩ፡፡ በመጨረሻው ሰዓት ሁሉም ፊቱን አዙሮብኝ ነበር፡፡ እናም አየር ኃይሉ ለነበሩት ተዋጊ ሚግ አውሮፕላኖች መለዋወጫ ስላልነበረው በረድፍ የሚጓዘውን የጠላት ጦር ለማጥቃት አልተቻለም፡፡

በዚያ ወቅት አሜሪካኖች የጉዳዩ ቀጥተኛ ተሳታፊ እየሆኑ የመጡበት ጊዜ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ጣልቃ የገቡት ወታደራዊ እርዳታ ለመስጠት ሳይሆን የማመልጥበትን ዘዴ ሊያመቻቹልኝ ኖሯል፡፡ ይህ የሚደረገውም ለሀገሪቱ የተሻለ በጎ ነገር እንደሆነ ተደርጎ በመታሰቡ ነበር፡፡ ስምምነቱም፤ እኔን፣ ቤተሰቤንና ጥቂት የቅርብ ደጋፊዎቼን ጭምር ደህንነቱ ባስተማማኝ ሁኔታ ወደሚጠበቅበትና ሠላማዊ ወደሆነ ቦታ የሚወስደንን አውሮፕላን ሊልኩልን ነበር፡፡..." በማለት ገለፀውለታል፡፡

"በዴሞክራሲ ያምናሉ?"

"ዴሞክራሲ የሚሰራው አውሮፓ ውስጥ ነው፡፡ የአፍሪካውያን ባህል የተለዩ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ዛሬ ያለችበትን ሁኔታ ተመልከት፡፡ የመድበለ ፓርቲ ስርዓት እያሰፈንን ነው እያሉ ያወራሉ፡፡ በተጨባጭ በማድረግ ላይ ያሉት ግን ጎሰኝነትን ማስፋፋት ነው፡፡ አገሬ እራሷ ቁጥራቸው አነስተኛ በሆነ አንድ ጎሣ አባላት ቁጥጥር ስር ከመውደቋም በላይ በጎሣ የተከፋፈለች ለመሆን በቅታለች፡፡ ይህ እንግዲህ ልክ እንደ መላዋ አፍሪካ ኋላ ቀር መሆንና ወደአለፈ ታሪክ መመለስ ነው፡፡

"እያንዳንዱ ሰው የፓርቲ አባል የሚሆነው አስተሳሰቡን በሚያራምድለት ፓርቲ ውስጥ ሳይሆን፤ በተወለደበት ጎሣ ነው፡፡ሱዳን፣ ሩዋንዳ፣ ብሩንዲ፣ ኮንጎ፣ ወይም ኬንያ ብትሄድ ሁኔታው ተመሳሳይ ነው፡፡ ዓለም አፍሪካ ውስጥ ከዚህ ቀደም አይቶ የማያውቀውን ጦርነት ወደፊት ያያል፡፡ ጦርነት ሲባልም አስጊ የሆኑ የጎሣ ጦርነቶችን ማለት ነው"

መንግስቱ ድምፃቸውን ጎላ አድርገው ቀጠሉ፤ "ኢትዮጵያ ውስጥ አንድ አባባል አለን፡፡ ዓለም አዲስ ጫማ ካልተጫማችሁ እያለ ይወተውተናል፡፡ ከእኛ የሚጠበቀው ደግሞ እግራችንን ለዚህ ለአዲሱ ጫማ እንዲስማማ ማድረግ ነው፡፡ ይሁንና አንዳንድ ጊዜ አዲስ ጫማ የሰዎችን እግር ክፉኛ ስለሚልጣቸው አውልቀው ይጥሉታል፡፡ ለመሆኑ ይህን እርስ በርስ የሚቃረን የሚመስል አባባል ተረድተኸዋል? እናንተ ምዕራባውያን የምትሰሩልንን ጫማ ለእግራችን እንዲስማማ አድርጋችሁ በማዘጋጀት ፋንታ የምትጠይቁን በተቃራኒው ነው፡፡ ብቻ ምንም ተባለ፣ ምንም ተሰራ፣ እኔ የሰጠሁት ነጠላ ጫማ እስካሁን ድረስ አልተጣለም" በማለት መልሰዋል፡፡

የቀድሞው ፕሬዝዳንት መንግስቱ ኃይለማርያም ከመኖሪያ ቤታቸው ውጪ በ150ሺ ዶላር በኤመራልድ ኮረብታ የተከበበውን ውብና ድንቅ አካባቢ ላይ የተገነባውን ቤት ከመግዛታቸውም በላይ፤ ዙምባቡዌ እንደገቡም የእርሻ መሬት ገዝተው ከባለሃብቶች ተርታ የሚመደቡ ሆነዋል፡፡ ዘውዳዊ ስርዓቱን ከስሩ መንግለው የጣሉት መንግስቱ የዛሬን አያድርገውና በሺዎች የሚቆጠሩ የኢትዮጵያ ወጣቶችን አንድ ዓይነት ዩኒፎርም አልብሰው በሰልፍ አንጉደዋል፡፡ "ከመንግስቱ ኃይለማርያም ቆራጥ አመራር ጋር ወደፊት!" እያሉ ብዙዎች እጃቸው እስኪዝነጠል አጨብጭበውላቸዋል፡፡ ዛሬ ግን ተነስ! ታጠቅ! ዝመት! እናት አገር ወይም ሞት! ሳታጣ ያጣች አገራችን! የታፈረችና የተከበረች ኢትዮጵያ!... ማለታቸውን አቁመዋል፡፡ የጋለ መፈክራቸው ቀርቷል፡፡ የሚፎክሩበት መድረክም የላቸውም፡፡ ስለዚህ ቀዝቀዝ ብለው ቀሪ ህይወታቸውን ያለፈ ታሪካቸውን በመፃፍና ውስኪ በመጎንጨት ያሳልፉታል፡፡



***        ***        ***

"የኢትዮጵያ የ5ሺ ዓመት ታሪክ ከኖኅ እስከ ኢህአዴግ" በሚል ርዕስ ከኖኅ ጀምሮ እስከዳግማዊ ምኒልክ ድረስ የነበረው ታሪክ በክፍል አንዱ መጽሐፍ በ456 ገጾች ተጠናቅሮ በ2003 ዓ.ም ለሕትመት በቅቶ፣ በተደጋጋሚም ታትሞ ለአንባቢ መድረሱ ይታወቃል፡፡ ከልጅ እያሡ ጀምሮ እስከ ኢህአዴግ ዘመን ድረስ የነበረውን ታሪክ "ካልተዘመረለት እያሡ እስከተዘመረለት ኢህአዴግ" በሚል ርዕስ በቅርቡ ጠብቁት" ብዬ በገባሁት ቃል መሠረት የ"መጽሐፍ አንድ"ን ተከታይ ክፍል "መጽሐፍ ሁለት"ን ባያችሁት መልኩ አቅርቤ ሙሉውን የኢትዮጵያ ታሪክ ፈጽሜያለሁ፡፡

ታዲያ "ካልተዘመረለት እያሡ እስከተዘመረለት ኢህአዴግ" ከተባለ፤እያሱ ለምን እንዳልተዘመረለት የመገለፁን ያህል፤ ኢህአዴግ ለምን እንደተዘመረለትስ እንዴት አልተገለፀም? የሚል አንባቢ ሊኖር እንደሚችል ይሰማኛል፡፡

ሁለት ምላሾችን እሰጣለሁ፡፡ ምላሽ አንድ፤ ስልጣን ላይ ያለ መንግስት ለዜና እንጂ ለታሪክ አይሆንም፤ ዜናውም ልዩ ጥንቃቄ ያሻዋል፡፡

ምላሽ ሁለት፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ስልጣን ላይ ያለ መንግስት ምንጊዜም ስለሚዘመርለት ነው እየተዘመረለት ያለው፡፡

……………………………ተፈጸሟል…………………………

Harold Marcus. *The Politics of Ethiopia, Great Brithain and the United States 1941 - 1974: The Politics of Empire.* Berkelay 1983.
Ikeda,Sumihisa(gen). "Nathional defense including defense council,defense policy council and council of commanders"(report to His Majesty).July26, 1957. Mahtheme selassie Wolde Mesqel. "The land system of Ethiopia"(Ethiopian observer vol.1.no9 1957).
Mesfin Woldemariam. *Rural vulnerability of famine in Ethiopia, 1958- 1977.* New Delhi 1984.
Mesay Kbede. *Survival and Modernization.*
Pankhurst,Richard. "The foundations of education, printing, newspapers, book production,libraries and literacy in ethiopia".(Ethiopian Observer v.6 n.3 1962).
Rubenson,Sven. *The survival of Ethiopian independence.*1976.
Riccardo Orizeo. *Talk of the devil.* 2003 (ትርጉም አጥናፍሰገድ ኪዳኔ 1996 ዓ.ም).
*Spark.* A special publication of the Ethiopia Students Union in North America;on the 19th congress of ESUNA. v.1 no 1. December 1971.
Spencer,John. *Ethiopia at bay: a personal account of the Haile Selassie years.* 1984.
Tilahun Takele(pseudonym). The national question (regionalism) in Ethiopia. (Newyork chapter news latter, no3. March 1972.
Yano, Muraji(col). "Draft of central intellignce agency establishment act".
(a study report to the Ethiopian government,october26 1957).
*Challenge.* "Education; challenge to the nation". The world wide federation of Ethiopia students. v.13 no.1. August 1972.

"ፌረሴ ቀይ ባህር ውሐ ሣይጠጣ ዘውድ አልጭንም!!"(ልጅ ኢያሱ)

*********

"እኔን የኢትዮጵያ ህዝብ መርጦ ያነገሠኝ የዋልኩለት ውለታ ኖሮ ሣይሆን የአባቴን ውለታ አስቦ ስለሆነ እኔም በበኩሌ የአባቴ ስም የሚጠራበትን ማሠብ ስላለብኝ በአባቴ ስም የታተመው ገንዘብ ተሠርዞ በእኔ ስም የታተመ ገንዘብ እንዲተካ አልፈቅድምና በዚያ ይቀጥል።"(ንግስት ዘውዲቱ)

*********

"......አገራችንና ህዝባችንን በምንችለው አገልግለናል። የኢትዮጵያ ህዝብ ዕድል የእኛን መወገድ የሚጠይቅ ከሆነ ግን ስራችንን አቁመን ማንኛውንም ነገር ለመቀበል ዝግጁ ነን።"(አፄ ኃይለስላሴ)

*********

"......አንዲት እናት ህፃን ልጇን ከአደጋ እንደምትጠብቀው ሁሉ እኔም የሐገሬን አንድነት፣ዳርድንበርና ሉዓላዊነት ስከላከል ቆይቻለሁ። ግን ምን ያደርጋል? ድካሜ ሁሉ ከንቱ ሆነ።"

(ጓ/ት መንግስቱ ኃይለማርያም)

*********

"ኢትዮጵያ አትቆራረስም ብሎ መጮህ ትርፉ ጦርነትና እልቂት ስለሆነ፤ አንድነት ለብዝበዛና ለባርነት አሣልፎ የሚሰጥ መሣሪያ ከመሆን ባሻገር የህዝቡን ጥቅም ሊያስጠብቅ አይችልም።"(ኢህአዴግ)

*********

ከመጽሐፉ የተወሰደ



ጋዜጠኛ ፍስሐ ያዜ

ሕትመት አልፋ አታሚዎች

ዋጋ ብር 65.00